# ከብርሃን ነፀብራቅ ብርሃንን ለሚናፍቅ

አዘጋጅ፡-

ሰልማን ካሳ (ገ/እግዚአብሔር)

**የአዘጋጁ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው**

የካቲት 2010

# ማውጫ

መግቢያ ........ 13
ምዕራፍ አንድ ........ 16
ኢየሱስ ማን ነው? ........ 16
ምዕራፍ ሁለት ........ 27
ኢየሱስ የሰው ሥጋ ለብሶ አምላክ ሆኖ አልመጣም፤ እንዲሁም አምላክ ሰው አይደለም፤ ሰውንም አይመስልም። ........ 27
ምዕራፍ ሦስት ........ 29
ስለ ኢየሱስ  የአምላክ መልእክተኛነት አራቱ ወንጌሎች ምን ይላሉ?........ 29
በዮሐንስ ወንጌል ........ 31
በሉቃስ ወንጌል ........ 36
ምዕራፍ አራት ........ 41
የኢየሱስ እምነት ምን ነብር? ምንስ አስተማረ ክርስትናን ወይንስ እስልምናን? 41
በማርቆስ ወንጌል ........ 43
በሉቃስ ወንጌል ........ 45
በዮሐንስ ወንጌል ........ 45
በሐዋርያት ሥራ ........ 46
ምዕራፍ አምስት ........ 51
ኢየሱስን በትክክል የሚወደው ማን ይወደዋል? እኛ ሙስሊሞች ወይስ ክርስቲያኖች? ........ 51
ኢየሱስ የሙስሊሞች የእምነት ወንድም ነው።!!! ........ 53
ኢየሱስን ጌታ የሚሉ ሁሉ መንግስተ ሰማያት (ገነት) አይገቡም። ........ 54
ኢየሱስን ጌታ ማለት ሳይሆን ትእዛዛትን መጠበቅ (መፈፀም) መንግስተ ሰማያት (ገነት) ያስገባል። ........ 55
ምዕራፍ ስድስት ........ 59
ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው አዳምና ሔዋን እንዲሁም የሰው ልጆች በሙሉ በሰሩት ወንጀል (ኃጢአት) እርሱ ተሰቅሎ  በመሞት ቤዛ (መስዋዕት) ለመሆን ነው? ወይንስ ለሌላ? ........ 59
ምዕራፍ ሰባት ........ 74
መዳን እንዴት ይቻላል? የሚያድነውስ ኢየሱስ ነው? ወይንስ እግዚአብሔር? ... 74

ምዕራፍ ስምንት ... 76
የአምላክ ባሕሪያቶች ... 76
ምዕራፍ አሥር ... 98
ኢየሱስን ወደ አምላክነት ደረጃ ያደርሰዋል ብለው የሚያነሷቸው መሰረተ ቢስ ሐሳቦች ... 98
ምዕራፍ አሥራ አንድ ... 128
ኢየሱስ (ዒሳ) በኢስላም ዕይታ ... 128
ምዕራፍ አሥራ ሦስት ... 141
ጳውሎስ ማን ነው? ... 141
ምዕራፍ አሥራ አራት ... 154
በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች የማይተገብሯቸው ሙስሊሞች እየተገሯቸው ያሉ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች ... 154
ምዕራፍ አሥራ አምስት ... 164
በመጽሐፍ ቅዱስ ተቀብረው ካልበሰበሱት እውነታዎች መካከል ... 164
ምዕራፍ አሥራ ስድስት ... 176
ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት መጠቀሳቸው . 176
ምዕራፍ አሥራ ሰባት ... 201
ነብያቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ደረጃ ... 201
ምዕራፍ አሥራ ስምንት ... 211
የሴት ልጅ ክብርና ደረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ ... 211
ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ ... 229
መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የፈጣሪ ቃል ነውን? ... 229
ምዕራፍ ሀያ ... 266
የክርስቲያን ጥያቄዎችና የሙስሊም መልሶቻቸው ... 266
The Christian qutions and muslim answers ... 266
ምዕራፍ ሀያ አንድ ... 294
ክርስቲያኖች የምነቅፍባችሁ ነገር አለ። ... 294
ዋቢ መጽሐፍት ... 301

## ***ምሥጋና***

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና አዛኝ በሆነው

ምስጋና የተባለ በአጠቃላይ ለዓለማቱ ጌታ ለአሏህ ይገባው። የአሏህ ውዳሴ እና ሰላምታ በነብያችን ሙሐመድ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም በተከታዮች እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን። በድጋሜ ይህን ኪታብ (መጽሐፍ) ለህትምት እንዲበቃ ላድረው ምስጋና ይድረሰው፡፡ እንዲሁም ከአላህ በታች ሰበብ በመሆን፤ በገንዘብ፣ በሞራላዊ ድጋፍ፤ እንቅልፍ አጥታችሁ፤ ጊዜአችሁን መሰዋዕት አድርጋችሁ ከጎኔ በመቆም፤ ድጋፍና ትብብር ላደረጋችሁልኝ ሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ አላህ (ሱ.ወ) ከፍ ያለ ምንዳ ይከፈላችሁ፡፡

بسم الله الرحمن الرحيم

الحمد لله والصلاة والسلام على نبينا محمد الذي أرسل رحمة للعامين وعلى آله الطيبين الطاهرين ومن اقتفى أثرهم إلى يوم الدين. وبعد:-

فقد اطلعنا على الكتاب الذي ألفه الأخ الفاضل/ سلمان كاسا (غبر إغزيابهير) حول مقارنة الأديان - والذي بمعنى "شعاء من الضياء لمن يتشوق إلى ضياء الحق". فقد وجدنا الكتاب أنا ورفقة من أصدقائي وفير البراهين والحجج في بابه. وهو أمثل كتاب في كشف الأسرار المكنونة. والكتاب جدير بالطباعة والنشر. ونحن على يقين بأنه ساعد ظهير في مكافحة حملة التنصير في البلاد.

وجزى الله الأخ الفاضل خير جزاء وحفظه من كل سوء ونفع به الإسلام والمسلمين!

أخوكم/ أبو رحمة

## መቅድም

በአላህ ስም እጅግ ሩኅሩኅ እጅግ አዛኝ በሆነው።

ምስጋና ሁሉ ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ የተገባ ነው። የአላህ እዝነት፣ በረከቱ፣ እንዲሁም ሰላሙ እርሱ ለዓለም እዝነት አድርጎ በላካቸውና የነብያት መደምደሚያ በሆኑት በሆኑት በሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በንጹሐን ቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እና የእነርሱን መንገድ እስከ ዕለተ ትንሳኤ በተከተሉት ላይ ሁሉ ይስፈን። ሲቀጥል ወንድም ሰልማን ካሳ (ገ/እግዚአብሔር) ያጠናቀረውን "ከብርሃን ነፀብራቅ ብርሃንን ለሚናፍቅ ሁሉ" የተሰኘውን መጽሐፍ እኔ እና ባልደረቦቼ ቃኝተነዋል። መጽሐፉ በሁለቱ ሃይማኖቶች ንጽጽር ዘርፍ በብዙ ማስረጃዎች የወፈረ፣ የተደበቁ ሚስጥሮችን ገልጦ በማውጣት ረገድ ዓይነተኛ ሆኖ አግንተነዋል። ስለዚህም በመሰል ዘርፍ ላይ ለሚያደርጉ ተጨማሪ ጥናቶች ልዩ አጋዥ ነው ብለን እንመሰክራለን። በመሆኑም ለዚህ መጽሐፍ ሕትመትና ስርጭት ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደርግ ዘንድ ጥሪ እናቀርባለን። ወንድም ሰልማን ካሳ (ገ/እግዚአብሔርን) አላህ ይጠብቀው፣ ለሙስሊሙ ኡማ ጠቃሚም ያድርገው ብለን እንማጸናለን።

አቡ ረህማ!

بسم الله الرحمن الرحيم

تقديم الكتاب بقلم أبو عبد الله شيخ سعيد إمام وخطيب بالمسجيد السلف

الحمد لله رب العلمين أنزل القرآن بلسان عربي مبين وحفظه من كيد الظالمين وحماه من تحريف المفسدين **((إنا نحن نزلنا الذكر وإنا له لحافظون))** والصلاة والسلام على النبي المصطفى الأمين تركنا على المحجة ليلها كنهارها لا يزيغ عنها إلا هالك .

وبعد قد تصفحت هاذا الكتاب والذي بمعنى "شعاء من الضياء لمن يتشوق إلى ضياء الحق" ألفه الأخ المجاهد بقلمه الطالب سلمان كاسا (غبر إغزيابهير) فعرفت إنه بذل جهدا كبيرا في الدفاع عن الإسلام والمسلمين والرد على أكاذب النصارى واليهود واعتمد في ذالك على نصوص الكتاب والسنة وبين عقيدة النصارى وكشف أباطلهم وأكاذبهم فجزاه الله على عمله خير الجزاء وأثابه جزيل الثواب

وبهذه المناسبة يسرني أن أنبه إلى أن بعض العوام بل عالم في هاذا الزمان كجمال الدين الأفغاني يقول كلاما خطيرا مكفرا مخرجا عن الملة أن الأديان الثلاثة الموسوية والعيسوية والمحمدية من تمام الإتفاق في المبدء والغاية وإذا نقص في الواحد شيء من أوامره الخير إستكملته الثانية وعلى هاذا لاح لي بارق أن يتحد أهل الأديان الثلاثة نعوذ بالله من الكفر والضلال لكن بين المؤلف في هاذا الكتاب لأن عقيدة النصارى واليهود فيه كفر وأباطيل .........

فجزاه الله خير الجزاء على ماوضح وبين

وصلى الله وسلم على نبينا محمد وآله وصحبه

كتبه شيخ سعيد أبو عبد الله

١٤٣٩ / ٤ / ١٢هـ

## መቅድም

በአሏህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና አዛኝ በሆነው

በአህለል ሱና ወል ጀመዓ የመስጅደ ስሰለፍ ኢማም እና ኸጢብ በሆኑት በአቡ ዐብዱሏህ (ሸይኽ ሰዒድ)

ምስጋና የተባለ በአጠቃላይ ለዓለማቱ ጌታ ለአሏህ ይገባው። እርሱ አሏህ ግልፅ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ ቁርአንን አወረደ፤ ከበደለኞች ተንኮል እና ከአበ ላሽዎች ማጣመምም ጠበቀው።

﴿إنا نحن نزلنا الذكر وإنا له لحافظون﴾

**‹‹ቁርአንን ያወረድነው እኛ ነን ለእርሱም ( ለቁርአን ) ጠባቂወቹ እኛው ነን››**

የአሏህ ውዳሴ እና ሰላምታ ምርጥ እና እውነተኛ በሆኑት ነብያችን ሙሐመድ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም ላይ ይሁን። ነብያችን ሌሊቱ እንደ ቀኑ በሆነ ግልፅ ማስረጃ ላይ ነው ትተውን የሄዱት ከዚህም ግልፅ ማስረጃ ጠፊ የሆነ ሰው እንጅ አይርቅም።

ከዚህ በመቀጠል ይህን “ከብርሃን ነፀብራቅ ብርሃንን ለሚናፍቅ” የሚለ ውን መጽሐፍ በእርግጥም አገላብጬ ተመልክቸዋለሁ። ይህን መጽሐፍ ታጋይ የሆነው ወንድማችን ተማሪ ሰልማን ካሳ (ገ/እግዚአብሔር) ጽፎ ታል። ከኢስላም እና ከሙስሊሞች በመከላከል እንደዚሁም ውሸታም በሆኑት ክርስቲያኖች እና የሁዳኖች ላይ መልስ በመስጠት ትልቅ ትግል እንዳደረገ አውቂያለሁ። በዚህም ላይ በቁርአን እና በሐዲስ ማስረጃዎች ላይ ተደግፏል።

የክርስቲያኖችን እምነት ግልፅ አድርጓል የነርሱንም ከንቱ እምነት እና ውሸት ግልፅ አድርጓል። አሏህ በዚህ ስራው መልካም እና ብዙ የሆነን መንዳ ይመንዳው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ለማስታወስ የምፈልገው በዚህ ዘመን ከተራ ግለሰ ቦች አለፍ ስንል አዋቂ ከሚባሉት እንደ ጀማሉዲን አል አፍጋኒይን ይመ ስል አደገኛ ፣ ከህደት እና ከመንገድ የሚያስወጣ ንግግርን ይናገራል። እን ዲህም ይላል፡-"ሦስቱ ሃይማኖቶች ሙሳዊ (የየሁዳኖች) ፣ ዒሳዊ (የክርስቲ ያኖች) እና ሙሐመዳዊ (የእስልምና) ሃይማኖቶች ከመጀመሪያ እስከ መጨ ረሻ ሙሉ በሙሉ ይስማማሉ። ከአንዱ እምነት ከመልካም ትእዛዞች መካከል

የኅደለውን ሌላኛው ይሞላዋል በዚህም የተነሳ እነዚህ የሦስቱ እምነት ባለቤቶች አንድ መሆን አለባቸው የሚለው ሐሳብ ለእኔ ግልፅ ሆነልኝ" ይላል። አሏህ ከክህደት እና ከጥመት ይጠብቀን፡፡ ነገር ግን የዚህ መጽሐፍ አዘጋጅ በክርስቲያኖች እና በየሁዳኖች እምነት ውስጥ ክህደት እና ከንቱ እምነቶች እንዳሉ ግልፅ አድርጓል። ባብራራው እና ግልፅ ባደረገው አሏህ መልካም ምንዳን ይመንዳው።።

የአሏህ ውዳሴ እና ሰላምታ በነብያችን ሙሐመድ ሶለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም በተከታዮች እና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን።

አቡ ዐብዱሏህ (ሸይኽ ሰዒድ)

## መቅድም

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው

ከድቅድቅ ጨለማ ለወጣኝና እስልምናንም ለመራኝ ለዓለማቱ ጌታ ምስጋና ይገባው። ዛሬ ዓለማችን እንደ አንድ መንደር በተገናኘበት ዘመን ማንኛውንም ማህበረሰብ ከሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ተገንጥሎ ለብቻው መኖር አይችልም። ግሎባላይዜሽን (ሉላዊነት) በሸቀጥ ብቻ ሣይሆን በአስተሳሰብ ጭምር የእያንዳንዱን ቤት እያንኳኳ ነው። ‹የእነ ገሌን እምነትም ሆነ አመለካከት መስማትም ማወቅ አልፈልግም፤ የራሴን ለእነርሱ አላካፍልም ‹ብሎ መቀመጥ ፈፅሞ የማይታሰብበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። አንድ ሰው የራሱን ለሌሎች መግለጽ ባይፈልግ እንኳ ሌሎች በሩን አንኳኩተው መምጣታቸው አይቀርም። ታዲያ ይህ ግለሰብ ያለው አማራጭ አንድም የመጡበትን ወገኖች በአግባቡ ማስተናገድ አሊያም በግልምጫና በቁጣ (ጨኸት) መሸነት ነው። በአገራችን ያለውን ተጨባጭ ስንመከት የየትኛውም ሃይማኖት ተከታይ የሌሎች ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ ሰዎች ቀርበውት ስለሃይማኖታቸው ለማስረዳት ሲሞክሩ በቅንነት ከማዳመጥ ይልቅ ለስድብና ዱላ መጋበዙ ሲበዛ የተለመደ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ሌላ ሣይሆን የሁሉም ሃይማኖት ተከታዮች ማለት ይቻላል ስለራሳቸው እምነት ይሁን ስለሌሎች እምነት በደንብ አለማወቃቸው ነው። ስለዚህ እነዚህ ወገኖች ረጋ ብለው የሁለቱን ሃይማኖቶች ልዩነት አስረድተው እነሱ የያዙትን እምነት ለምን እንደመረጡትና ከሌሎች የቀረበላቸውን ለምን እንደማይከተሉት ምክንያታዊ በሆነ መልኩ በማስረዳት ፈንታ አምባጓሮ ፈጥረው ሰዎቹን ከአጠገባቸው ማራቅን ይመርጣሉ። ይህ ዓይነቱ አካሄድ አሁን ባለንበት ተጨባጭ ምን ያህል ያስኬደናል የሚለው ግን አጠያያቂ ነው።

ዛሬ የተለያዩ የመረጃ ምንጮች ሳንወድ በግድ በራችንን እንኳ ማንኳኳት ሳያሻቸው ጓዳችን ድረስ ዘልቀው መግባት እያቻሉ ነው። በሌላው ዓለም ያሉት እንቅስቃሴዎች አገር ላይ ባለው ተጨባጭ ላይ የራሣቸው የሆነ አሉታዊም ይሁን አዎንታዊ ተፅዕኖ ማሣደራቸው የማይቀር ነው። ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት የሁሉንም ሃይማኖት ተከታዮች እንቅስቃሴን ዘልቀን ብንመለከት የተለያዩ ሃይማኖታዊ መረጃዎችን መጀመሪያ ከተዘጋጁባቸው ቋንቋዎች ወደ አገረኛ ቋንቋ በመመለስ የተከታዮቻቸውን እምነት ለማጠናከርና ሌሎችን ወደራሳቸው እምነት ለመሳብ

የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርጉ እናገኛለን። ስለዚህ ወደድንም ጠላንም የሌላውን ዓለም ተፅዕኖ መቀበላችን የግድ ነው። ይህን ስንል ደግሞ ከሌላው የሚመጣውን ነገር ሁሉ አግበስብሰን እንቀበል ማለት አይደለም። እነርሱም እንደኛው ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ጠንካራና ደካማ ጎን ይኖራቸውልና ጠንካራ ተሞክሮዎቻቸውን በመውሰድ ደካማውን መተው እንችላለን። በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች ውስጥ ከምናገኛቸው ጥሩ ተሞክሮዎች ውስጥ የተለያዩ የሃይማኖት ምሁራንን በማዘጋጀት ለህብረተሰቡ ሠላማዊ በሆነ መልኩ ስለሃይማኖታቸው ገለፃ የሚሰጡበትንና ከህብረተሰቡ የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች በአግባቡ የሚመልሱባቸው መድረኮችን ማመቻቸት ነው። ለዚህ አይነቱ ተሞክሮ አገራችን ባዕድ ብትሆንም በሁሉም ሃይማኖት አባቶች ዘንድ ቅንነቱ ካለ መድረኩን ማመቻቸት ቀላል ነው። ይህ ደግሞ የአገራችን የሃይማኖት መቻቻል ተምሳሌትነት ይበልጥ ያጠናክረዋል እንጂ አያጠፋውም።

ዛሬ በአገራችን ስላለው የሃይማኖት መቻቻል ብዙ ይነገራል። ነገር ግን እስካሁን ያለው የሃይማኖት መቻቻል በምን ላይ የተመሰረተ ነው? ብሎ የሚጠይቅ ወገን ብዙም የለም። የአገራችን የሃይኖማት መቻቻል መሰረት ካየነው በአስቂኝ ነገሮች የተገነባ ነው። ለምሳሌ ሁለት ፍፁም ተቃራኒ የሆኑ ሃይማኖቶች እንከተላለን የሚሉ ወገኖች «እኛም እናንተም ልክ ነን! እናንተ አላህ ትላላችሁ! እኛ ደግሞ እግዚአብሔር እንላለን! ያው ነው እኮ! ቢለዋ ብቻ ነው የሚለየን! አንድ ነን!»----- ወዘተ የሚሉ የሃይማኖት አባቶች በማይቀበሏቸው አባባሎች ላይ የተመሰረተ ነው። በእንዲህ አይነቱ መሰረት ላይ የተገነባ መቻቻል አንደኛው ወገን ትክክለኛውን ሃይማኖት ለማወቅና ለመከተል ብሎ የተነሳ ዕለት ብትንትኑ ይወጣል። ስለዚህ አንድነታችን፣ አብሮነታችንና መቻቻላችን ለሌላው ተምሳሌት ሆኖ ይቀጥል ዘንድ መቻቻላችንን በጥሩ መሰረት ላይ መገንባት ግድ ይለናል። ይህ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የሁሉም ሃያማኖት ተከታዮች የራሳቸውንና የተቃራኒዎቻቸውን ሃያማኖት በአግባቡ ሲያውቁና ሲረዱ ብቻ ነው:: ነገር ግን «አንተም የራስህን ጠብቅ! እኔም የኔን በልቤ ልያዝ! በዚህ ጉዳይ እኔም አንተም ምንም ነገር ባናነሳ ይሻላል!» ተከድኖ ይብሰል! አይነት ከሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ይገነፍልና ወደአላስፈላጊ አቅጣጫ ያዞራል። ይህ ደግሞ ለማንም አይበጅም። ስለዚህ ተቀራርቦ መወያየትና መነጋገር የበለጠ ያቀራርባል እንጂ አያራርቅም። አጉል በአትንኩኝ ባይነት ተኮፍሶ መቀመጥ ለማንም አያዋጣም።

በዚህ ረገድ በአሁኑ ሰዓት በአንዳንድ የሃይማኖት ተከታዮች መካከል የምናየው ሠላማዊ የሆነ ሃይማኖታዊ ውይይት (ክርክር) ለሚያጠኑ ተምሳሌት ሊሆነን ይችላል ብለን እንገምታለን። እንዲህ አይነቱን ሠላማዊ የሆነ ውይይት እንደ ድፍረትና የሰውን ሃይማኖት እንደ መንካት አድርገው የሚቆጥሩ አንዳንድ ወነኖችም አይጠፉም። እነዚህ ወገኖች የያዙት አቋም አንድም የሃይማኖታቸውን መመሪያ በጥልቀት ካለማወቅ አሊያም የሚቀርብላቸውን ጥያቄዎች ‹በአግባቡ መመለስ አንችልምና ከሰው ፊት መዋረድ አለ!› ከሚል ከንቱ ስጋት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ለእነዚህ ወገኖቻችን የምንላቸው ነገር ቢኖር የሃይማኖታችሁ መመሪያ (መጽሐፍ) በዚህ ጉዳይ ላይ ምን እንደሚል በአግባቡ እንድታዩት፤ እንደትፈትሹትና ራሳችሁን ጥሩ ተወያይ አድርጋችሁ እንደትሞክሩ ነው። አንዳንዶች ደግሞ የራሳቸውን ድክመት ለመሸፋፈን ሲሉ ለተራው ሰው ሃይማኖቱ እንደ ተነካና እንደ ተዘለፈ አድርገው በማቅረብ ሆን ብለው ሕዝቡን ለዱላና ለአላስፈላጊ ግጭት እንዲጋበዝ የማድረግ ስራ ሲሰሩ ይታያል። ይህ አይነቱ ድርጊት በፈጣሪም ሆነ በፍጡራን ዘንድ ያሰወቅሳልና ስለዚህ ሁላችንም እናስብበት።

# <u>መግቢያ</u>

የሰው ልጅ የተላቀና የተከበረ ፍጡር ነው። ነገር ግን እንደ እንሰሳ በዘፈቀደ ያለ ዓላማ ሲኖር እንደ እንሰሳ አሊያም ከእነርሱ በታች ዘቀጠ። በእርግጥም ማሰብ፣ ማስተንተን፣ ማገናዘብ፣ ማስተዋልና መረዳት ካልቻለ ከእንሰሳት በታች ማሽቆልቆሉ አይቀሬ ነው። በመጽሐፈ መዝሙር 42፡12 «***ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም፤ እንደሚጠፉ እንሰሳዎች መሰለ***» በማለት የሰዎችን ሁኔታ ይገልፃል። ማሰብ አለመቻል ለሰው ልጅ ትልቁ የውድቀት እና የጥፋት መንስኤ ነው። ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል 12፡24 «***መጽሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ስለዚህ የምትስቱ አይደላችሁምን***? በማለት አለማወቅ የጥፋት ምክንያት መሆኑን ይጠቁመናል። ጳውሎስ በ2ኛ ቆረንቶስ 4፡3 እና በ2ኛ ጢሞቲዎስ 3፡13-17 «***ወንጌላችን የተከደነ ቢሆንም እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉት ነው***» ይላል። ስለዚህ አለማንበብ ወደ ጥፋት የሚያመራ ነው። ለዚህም ነው በትንቢ.ተ.ሆሴዕ 4፡6 «***ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል***» በማለት የጥፋታቸው ዋናው ምክንያት አለማንበብ መሆኑን ያስገነዝበናል። ማንበብ ፅድቅን ለተጠሙ ልቦች እርካታና ጥም ቆራጭ ነው። ማንበብ የመንፈሳዊነት ምልክትና የአዕምሮ ጂምናስቲክ ነው። ማንበብ ፈጣሪን የምናውቅበት አገናኝ መስመር ነው። ከእውቀቶች ሁሉ የላቀው እውቀት እውነተኛውን አምላክ ያስተዋወቀና እርሱን እንድንፈራው፤ እንዲሁም እርሱን በብቸኝነት እንድናምልከው የሚያደርግን ነው። አልፎም በሰዎች ላይ የእውቀት ትርጉምና ተግባርን ተንፀባርቆና ድምቀትን ተላብሶ ሲታይ ነው። ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 24፡45 «***መጽሐፍትን ያስተውሉና ያውቁ ዘንድ አዕምሮአቸውን ከፈተላቸው።***» በመጽሐፈ ኢያሱ 34፡16 «**የእግዚአብሔርን መጽሐፍ ፈልጉ፤ አንብቡም**» በማለት መጽሐፍን እንድናነብ አምላክ ያዘናል።

## <u>በእምነት ላይ ሚስጢር የሚባል ነገር የለም</u>።!!!

ሚስጢር ከእምነት ጋር ምንም ግንኙነትና ተዛማጅነት የለውም። ሲጀመር ባልገባንና በላወቅነው ነገር እንዴት ልናምን እንችላለን? እምነት ማለት ከጥርጣሬ የራቀና የፀዳ ነው። ስለዚህ በአንድ ነገር ለማመን ማንነቱን በጥልቅ መረዳትና ማወቅ አለብን። ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 10፡17 «***እምነትም ከመስማት ነው፤ መስማትም የእግዚአብሔርን ቃል ነው።***» ከዚሁ ምዕራፍ 10፡14 «***ባልሰሙት ነገር***

***እንዴት ያምናሉ?***» በማለት አታንብብ ሚስጢር ነው፤ ጌታን መፈታተን ነው ለሚሉ ሰዎች ጥያቄ ያቀርባል።

## ***ፈጣሪን ማወቅ እርሱን መፈታተን አይደለም***።!!!

አንዳንድ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ላንብብ ብሎ ሐሳብ ለሚያቀርብላቸው ሰው፡- የሚሰጡት መልስ "ፈጣሪን አትፈታተን" በማለት ይመልሳሉ። ይልቁንም አለማንበብ ትልቁ ፈተናና ፈጣሪን መፈታተን ነው። የሰው ልጅ ቢያነብ ኖሮ እውነተኛ ፈጣሪውን ባወቀ ነበር። ካለማንበቡ የተነሳ ፈጣሪውን ማወቅ ተስኖታል። በመጽሐፈ ሲራክ 5፡27«***ፈጣሪህ እግዚአብሔር ስለ አንተ ይከራከርሃልና ለሞት እስክትደርስ ድረስ ስለ እውነት ተከራከር***» ይላል። ተጨማሪ በትንቢተ.ኢሳይያስ 41፡21«***ክርክራችሁን አቅርቡ፤ ማስረጃችሁን አምጡ***» በማለት በደፈናው ሳይገባን በማለት ጭፍን መከተልን አውግዟል።

## አንብቡ ማለት ምክር እንጂ ትችት አይደለም።!!!

ፈጣሪን እወቁ፤ አንብቡ ብሎ የሚመክር ሰው እውነተኛ የመዳኛ መገድን የሚያመላክት ነው። አንብቡ ማለት ትችት፣ ወቀሳ አሊያም ስድብ አይደለም። በመጽሐፈ ተግሣጽ 4፡23«***በምላሱ ከሚሸነግል ሰው ይልቅ፤ የሰውን መንገድ (ሃይማኖት) የሚነቅፍ እጅግ ክብርን ያገኛል***።» በመጽሐፈ መዝሙር 16፡7 «***የሚመከረኝን እግዚአብሔር ይባርከው***» ይላል። በመጽሐፈ ምሳሌ 12፡1 «***ተግሣጽን የሚወድ እውቀትን ይወዳል፤ ዘለፋን የሚጠላ ግን ደንቆሮ ነው።***» የ1993 ዕትም «***ምክርን የሚጠላ ደነዝ ነው***» ይላል። እኔ እናንተን በምላሴ ለምሸነግል በውስጤ የነደፍኩት የሰይጣን ተልዕኮ የለኝም። ነገር ግን ለእናንተ ካለኝ ጥሩ ጎንና መልካም አስተሳሰብ የመነጨ ነው።

## ***ሁሉንም ፈትኑ፤ መልካሙንም ያዙ***።!!!

ሁሉንም ማየት አዋቂነት ነው። አዋቂነትም ደግሞ የተሸለውን መምረጥና መልካሙን መያዝ ነው። በሰቆቃው.ኤርሚያስ 3፡40-41«***ኑ፤ መንገዳችንን (ሃይማኖታችንን) እንመርምርና እንፈትን፤ ወደ እግዚአብሔርም እንመለስ። ልባችንን ከእጃችን ጋር በሰማይ ወዳለው ወደ እግዚአብሔር እናንሣ።***»

ክርስቲያኖች ለዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ንግግር ቅድሚያ ሚዛን እንስጥ። በትንቢተ.ኢሳይያስ «***እውነትን መንገድ (ሃይማኖት) ላይ ቆማችሁ ፈልጉ።***» በ1ኛ ተሠሎንቄ 5፡21«***ኩሉ አበክሩ ወዘ ሰናይ አጽኑ፤ (ሁሉንም ፈትኑ፤ መልካሙን ያዙ)።***»

## የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ።!!!

ውድ አንባቢያን የመጨረሻ ውሳኔአችሁ የምታመልኩትን መምረጥና ማምለክ ነው። አምላክ ፍጥረታትን በሙሉ የፈጠረው እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በሁሉም የሰው ልጆች ላይ የተጣለ ኃላፍትና ነው። በመጽሐፈ ኢዮብ 34፡4«***የሚበጀንን እንምረጥ፤ መልካሙንም አብረን እንወቅ***» እላለሁ። በመጨረሻም በመጽሐፈ ኢያሱ 24፡15«***የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤***» መልካም ምርጫ ተመኘቻለሁ።

# ምዕራፍ አንድ

## ኢየሱስ ማን ነው?

ኢየሱስ ሰውና ነብይ እንደ ነበረ ከውልደቱ ጀምሮ እስከ አረገበት ጊዜ እንዲሁም እስከ መጨረሻ የሰው ልጅ እንደ ሆነ ያስረዳል። አራቱ ወንጌሎች ለዚህ ማስረጃ ናቸው። በመጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ምዕራፎች እንዲሁም በጳውሎስ መልእክት ውስጥም ሰው እና ነብይ እንደ በብዙ ቦታ ላይ ተገልጿል። ለምሳሌ ከውልደቱ ስንጀምር፡- በሉቃስ ወንጌል 1፡26-38 ‹‹*በስድስተኛውም ወር መላኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ሄዶ ወደ ታጨች አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ የድንግሊቱ ስም ማርያም ነበር። መላአኩም ወደ እርሷ ገብቶ ደስ ይበልሽ፤ ጸጋ የምላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት። እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መላአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ፀጋ አግኝተሻል፤ አትፍሪ፤ <u>እንሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ</u>። ምንም ሰለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መላአኩን መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል። የልዑል ኃይልም ይፀልይሻል። መላአኩም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም እንሆ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይሁንልኝ አለችው።*›› በማቴዎስ ወንጌል 1፡23‹‹*እንሆ ድንግል ፀንሳለች፤ <u>ወንድ ልጅም ትወልዳለች</u>።*›› በሉቃስ ወንጌል 1፡31 ‹‹*እንሆ ትፀንሳለች፤ <u>ወንድ ልጅም ትወልዳለች፤ ስሙንም ኢየሱስ ትዩዋለሽ</u>*›› ይላል። ስለዚህ ማርያም ፀንሳ የምትወልደው አምላኳን ሳይሆን ወንድ ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ነው። በዮሐንስ ወንጌል 12፡2 ላይ ‹‹*እርሷም <u>ፀንሳ</u> ነበር፤ <u>ምጥም</u> ተይዛ ተጨንቃ ነበር።*›› በሉቃስ ወንጌል 2፡6-7‹‹*በዚያም እንዳሉ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ። የበኩር ልጅ የሆነውን <u>ወንድ ልጅ ወለደች</u>*›› ይላል። ከዚህ ላይ ሐሳቡ ግልጽ ነው። እዚህ ላይ አንድ ሎጂክ ላንሣ እኔ አባትና እናቴን መውለድ እችላለሁ? መልሳችሁ መቼም "አትችልም" ነው። ያ ከሆነ ታዲያ ማርያም ኢየሱስን እንደ ወለደችው ግልጽ አይደል። ታዲያ እንዴት ነው ኢየሱስ እናቱን ፈጠራት የሚባለው? ሲጀመር ፈጣሪ የሁሉ ነገር አስገኚ ነው ሁሉንም ነገር የፈጠረ ነው። ፍጡር ፈጣሪን ሊፈጥረው (ሊወልደው) አይችልም።

ክርስቲያኖች ኢየሱስን ፈጣሪ ነው ካሉ እናቱ ማርያምን የማርያምን እናት ጨምሮ ማን ፈጠራቸው? ጥቅሱ ይቀጥልና እንዲህ ይላል፡- ***«በጨርቅም ጠቀለለችው፤ በእንግዶች ማረፊያ ቦታ ስላገኘች በግርግር አስተኛችው»*** ይላል። በሌላ ቦታ በከብት በረት ተወለደ ይላል። ከዚያም በሉቃስ ወንጌል 2፡21***«ሊገርዙት ስምንት ቀን በሞላው ጊዜ በማህፀን ሳይገረዝ በመላኩ ስሙም ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ።።»*** ኢየሱስ እውን አምላክ ከሆነ የዓለማቱን ጌታ ሰው ሊገረዝ ሊባል ነውን? በሉቃስ ወንጌል 2፡40***«ሕፃኑም ጥበብ ተሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ»*** ይላል። አምላክ የሚያድግ ሕፃን ነውን? በሉቃስ ወንጌል 2፡52***«ኢየሱስ ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር»*** ይላል። ኢየሱስ አምላክ ነው ከተባለ የሚያሳድገው ሌላ አምላክ አለ ማለት ነው? በሉቃስ ወንጌል 9፡56***«የሰው ልጅ የሰው ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ።።»*** በማቴዎስ ወንጌል 11፡19 ***«የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቷል»*** ይላል። ከበላና ከጠጣ ምን ያስከትላል? መልሱን ለእናንተ ልተው። በሉቃስ ወንጌል *2፡41-48****«ዮሴፍና ማርያም በየዓመቱ ለፋሲካ በዓል ወደ እየሩሳሌም ይሄዱ ነበር። ከዚያም ኢየሱስ አሥራ ሁለት (12) ዓመት በሆነው ጊዜ እንደተለመደው በዓሉን ለማክበር ሄደ፤ እነርሱም ተመለሱ፤ እሱም በዚያው ቀረ፤ ፈለጉት አጡት።---------ዮሴፍና ማርያም በቤተ-መቅደስ ባዩት ጊዜ ተደነቁ። ከዚያ እናቱ ልጄ ምነው እንዲህ አደረከኝ! አባትህ እና እናትህ ተጨንቀን ስንፈልግህ ነበር እኮ! አለችው።።»*** ኢየሱስ አባት አለው እንዴ? የዓለማት ፈጣሪ ኢየሱስ ነው ብላ ማርያም የምታምን ከሆነ ለምን ተጨንቃ ፈለገችው? በዚያ ላይ አምላክ ጠፍቶ ሰው ሲፈልገው? ማርያም ኢየሱስ የዓለማት ፈጣሪ ነው ብላ የምታምን ከሆነ ለምን ተጨንቃ ፈለገችው? አምላክ ጠፍቶ ሰው ሊፈልገው? ኢየሱስ ለማርያም አምላኳ ከሆነ ለምን ልጄ አለችው? በሉቃስ ወንጌል 11፡27 ***«ይህንንም ሲናገር ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማኅፀንና የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው።።»*** የዓለማት ጌታ የሆነው በሰው ልጅ ማኅፀን ተረግዞ ተወለደ ማለት ምን ማለት ነው? ለአዕምሮ አይከብድም? የዓለማትን አምላክ በሰው ልጅ ማኅፀን ተረገዞ መወለድን አስቡት። ከዚህ የበለጠ የአምላክን ክብር የሚያዋርድ አለን? የዓለማት ጌታ ጡት ጠባ ማለት ከማስገረምም አልፎ ያሳዝናል። የዓለማትን ጌታ የሚበላና የሚጠጣ ነው ማለት ተገቢ ነውን? ኢየሱስ ሰብዓዊ ባሕሪትን የተላበሰ ለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎችን እናገኛለን። ለምሳሌ፡- እንደ ራበው፣ እንደ ተከፋ፣ እንደ አዘነ፣ እንደ ታወከ፣ እንደ ደከመውና

በአጠቃላይ በርካታ ሰብዓዊ ባሕርያትን እንደ ተላበሰ መጽሐፍ ቅዱስ በስፋት ያስረዳል። እንደ ተራበ፡- በማቴዎስ ወንገል 21፡18 ‹‹***ኢየሱስ ጠዋት ወደ ከተማ ተመልሶ ሲሄድ ራበው።***›› በማርቆስ ወንጌል 11፡12 ‹‹***በማግስቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ፤ ቅጠልም ያለት በለስ በሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደሆነ ብሎ መጣ። ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘበትም።***›› ምን ነው ኢየሱስ በለሷ የምታፈራበትን ወቅት እንኳ አያውቅምን? የዓለማት አምላክ ይቅርና እንስሳት እንኳ የአዝመራ ወቅትና አዝመራው የሚያፈራበትንና የማያፈራበትን ወቀትና ጊዜ ለይተው ያውቃሉ። የዓለማት አምላክ ከእነርሱ እንኳ አይሻልም ማለት ነው በለሷ የምታፈራበትን ወቅት ያላወቀው? በማቴዎስ ወንጌል 4፡12 ‹‹***አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጾመ በኋላ ራበው።***›› በዮሐንስ ወንጌል 19፡28 ‹‹***ኢየሱስ ተጠማሁ አለ።***›› በዮሐንስ ወንጌል 4፡6 ‹‹***ኢየሱስ መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጉደጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ። ጊዜውም ስድስት (6) ሰዓት ነበር።***›› ከዚህ ላይ ጊዜው ተጠቅሷል። አጋጣሚ ሆኖ ፀሐይ አድክሞት ይሆናል። ምክንያቱም በዚህ ወቅት ፀሐይ የበለጠ የምትሞቅበት ጊዜ ነው። አንድ ሰው ከደከመው መቼም ማንቀላፋቱና መተኛቱ አይቀርም። ለዚያም ነው በሚከተሉት ምዕራፍ የእነዚህ ውጤት የሚነገረን። በሉቃስ ወንጌል 8፡23 ‹‹***በባህሩ ላይ እየቀዘፈ ሲሄዱ ሳሉ ኢየሱስ አንቀላፋ።***›› በማርቆስ ወንጌል 4፡38 ‹‹***እርሱም በስተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር። አንቅቶውም መምህር ሆይ! ስንጠፋ አይገድህምን አሉት።***›› በማቴዎስ ወንጌል 8፡24‹‹***እርሱ ግን ተኝቶ ነበር።***›› ከዚህ ላይ ኢየሱስ ተኝቷል። እውነተኛ አምላክ የሆነው ግን ፈፅሞ አይተኛምም አያንቀላፋምም። በመጽሐፈ መዝሙር 121፡4 ‹‹***እነሆ እስራኤልን የሚጠብቅ አምላክ እግዚአብሔር አይተኛም፤ አያንቀላፋምም።***›› ስለዚህ የማይተኛውን የማያንቀላፋውን የኢየሱስንና የዓለማት ጌታ የሆነውን ብቸኛ አምላክ ተገዙ ማለት ቀና ምክራችን ነው። በዮሐንስ ወንጌል 11፡33 ‹‹***በመንፈሱ አዘነ በራሱ ታወከ።***›› ከዚሁ ምዕራፍ ቁጥር 35 ‹‹***እንባውን አፈሰሰ***›› ይላል። ከሰው ልጆች ባሕሪያቶች ውስጥ ማዘንና መከፋት ያጋጥማሉ። የዓለማት አምላክ ነው የተባለው ደግሞ እንደ ሰው ልጅ ያዘንና ይተከዝ ነበር። በማቴዎስ ወንጌል 26፡38 ‹‹***ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች።***›› በማርቆስ ማርቆስ 138 ‹‹***ሊደነግጥም፣ ሊተክዝም፣ ጀመረና፤ ነፍሴ እስከሞት ድረስ እጅግ አዘነች አለ***›› ይላል። እነዚህ የኢየሱስን ሰብዓዊ ባሕርያቶች እንጂ የዓለማትን አምላክን ባሕርያትን የሚገልጽ አይደሉም። አምላክ እንዲህ ባለ ተራ ንግግር አይገለጽም።

አምላክ እንደዚ ካለ ጉድለት ሁሉ የጠራ ነው። አንድ ሰው የሚደነግጠው የሚያስደነግጠው ነገር ሲኖር ነው። እንዲሁም የሚደክመውና የሚያታክተው አድካሚና አታካች ነገር ሲኖር ነው። ታዲያ ኢየሱስ የዓማለት ጌታና አምላክ ከሆነ ማን ያስተክዘዋል? ማን ያስደነግጠዋል? ማን ያደክመዋል? የዓለማትን ጌታና አምላክ የሚያደክም፣ የሚያስደነግጥ፣ የሚያስተክዝ፣ የሚያታክት ሊኖር? እንዲህ ባለ እሳቤ ማመን እጅግ አይከብድምን? አሁንም ኢየሱሰ በሰይጣን እንደ ተፈተነ ይነግረናል። በማርቆስ ወንጌል 1፡12-13 «***ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው። በምድረ በዳም <u>በሰይጣን ሲፈተን አርባ ቀን ሰነበተ</u>***» ይላል። ኢየሱስ አምላክ ከሆነ በሰይጣን እንደሚፈተን አስቀድሞ አያውቅምን? የፈጠረው ፍጡርስ እንደሚፈትነው አያውቅም? አምላክ ደግሞ እንደ ማይፈተን በ1ኛ የያዕቆብ መልእክት 1፡13-14 «-------***<u>እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና</u>***-----።» ሌላው ደግሞ ኢየሱስ እንደ ደከመው፣ እንደ ታከተው በዮሐንስ ወንጌል 4፡6«***ኢየሱስ መንገድ ከመሄድ <u>ደክሞ</u> እንዲህ <u>ተቀመጠ</u>***» ይላል። አምላክ ደግሞ እንደማይደከመው እንደማይታከተው በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 40፡28«***እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው፤ <u>አይደክምም፤ አይታክትምም</u>፤ ማስተዋሉም አይመረመርም***» ይላል። ከደከመው፣ ከታከተው፣ አምላክ ከሰው በምንም ተለየ? የዓለማት ጌታና አምላክ ሰው አይደለም፤ ሰውንም አይመስልም። በዮሐንስ ወንጌል 8፡40«***ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኳችሁን <u>ሰው</u> ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?***» ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለምን ከራሱ አይናገርም? አምላክ ከሆነ ከሌላ እገዛ ይፈልጋል እንዴ? በማቴዎስ ወንጌል 8፡20«***ኢየሱስም፣ <u>ለሰው ልጅ ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም አላቸው</u>።***» ምን ነው ይህ የአምላክ መግለጫ ነው? እርሱ አምላክ ድሃ ከሆነ የፈጠራቸው ፍጥረታት በሙሉ ማን ይመግባቸዋል? ከየትስ ያገኛሉ? ታዲያ ለራሱ መጠጊያ ያጣ ለሌላ ይተርፋል? መልሱን ለመጽሐፉ ሰዎች ትቻለሁ። በማቴዎስ ወንጌል 15፡7-9«***ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከኔ በጣም የራቀ ነው። <u>የሰው የሆነ ትምህርት እያስተማርኩ በከንቱ ያመልኩኛል</u>።***» ኢየሱስ ያስተማረው የሰው ትምህርት ነው ማለትም እኔን አምልኩኝ አይደለም ያለው። ነገር ግን ሰዎች በከንቱ ያመልኩታል። በማቴዎስ ወንጌል 10፡32«***ስለዚህ <u>በሰው</u> ፊት ለሚመሰክርልኝ፤ እኔም ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ።***» ይህችን ምዕራፍ በደንብ ማጤን ያሻል። ኢየሱስ ሰው ብሎ የሚመሰክርልኝ አለ እንጂ መች አምላክ ብሎ የሚመሰክርልኝ አለ? ሲቀጥል አሁንም ኢየሱስ

በአምላኩ ፊት እርሱ አምላክ እንዳልሆነ ይመሰክራል፤ በሰዎችም ላይ ይመሰክርባቸዋል። እስካሁን እንዳየነው ኢየሱስ ከውልደቱ ጀምሮ የሰው ልጅ እንደነበር አንቀፆቹ በሙሉ ዋቢ ማስረጃ ናቸው፡፡

## የሃይማኖት አባቶች ኢየሱስ ፍጡር ስለመሆኑ ምን እምነት ነበራቸው?

ሃይማኖት አበው በሚባለው የኦርቶዶክስ መጽሐፍ ኢየሱስ ፍጡር እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል፡፡ ተከታዩን ጥቅስ እንመልከት፡- ሃይማኖተ አበው ዘመጠሊጎን 44፡3 «**ዘመጠሊጎን አለ፡- ወለሊሁ ሐነፀ ሥጋሁ ውስጠ ከርሰ ድንግል ወኢተሳተፎ መኑሂ በፈጠረ ሥጋሁ አለ ለሊሉሁ ባሕቲቱ ፈጠሮ፡፡**» ትርጉም፡- “እርሱ ሥጋውን በድንግል ማሕፀን ፈጠረ፤ ሥጋውን በመፍጠር ማንም አጋዥ አልሆነውም፤ እርሱ እራሱ ፈጠረው እንጂ፡፡” ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ 124:19 ቄርሎስም አለ፡- «**ንብሎ ፍጡረ እስመ ውእቱ ተወልደ በስጋ እምብእሲት፤**» ትርጉም፡- “ከሴት በሥጋ ስለተወለደ ፍጡር ነው እንላለን” ሃይማኖተ አበው ዘጎርጎርዮስ 35:6 ጎርጎርዮስም አለ፡- «**ወዓዲመ ይትበሀል ፍጡረ በእንተ ዘኮነ ስጋ፤**» ትርጉም፡- “ስጋ ስለሆነ ፍጡር ይባላል” አንዱ እግዚአብሔር እንደ ተስፋው ቃሉ ከዳዊት ዘር ለእስራኤል መድኃኒትን ኢየሱስን ካለመኖር ወደ መኖር አመጣ፤ ይህም የተስፋ ቃል ኢየሱስ በማኅፀን የተፈጠረ ፍጡር መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡- በሐዋሪያት ሥራ 13፥23 «***ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደ ተሰፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ።***» በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 49፥5-6«***ያዕቆብን ወደ እርሱ እንድመልስ እስራኤልንም ወደ እርሱ እንድሰበስብ ባሪያ እሆነው ዘንድ ከማኅፀን ጀምሮ *የሠራኝ* እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡— እርሱም፡— የያዕቆብን ነገዶች እንድታስነሣ ከእስራኤልም የዳኑትን እንድትመልስ ባሪያዬ ትሆን ዘንድ እጅግ ቀላል ነገር ነውና እስከ ምድር ዳር ድረስ መድኃኒት ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌ ሰጥቼሃለሁ***» ይላል። "ከማኅፀን ጀምሮ የሠራኝ" ኢየሱስ ስለ መሆኑ የተለያዩ ጥንታዊ ማብራሪያ ማየት ይቻላል፤ ከዚህ መካከል ሃይማኖተ አበው ላይ ቄርሎስ ነግሮናል፡- ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ 76:19 ቄርሎስም አለ፡-«**ወዓዲ ይቤ መድኅን በአፈ ዝንቱ ነብይ ኢሳይያስ በእንተ ልደቱ እምድንግል ወበእንተዝ ተፀነስኩ፤ እምከርሥ ከመ ዐቅም ምግባራተ ብዙኅ ወአቅም ነገደ ያዕቆብ ወአስተጋብእ ዘርዋነ እስራኤል ወበእንተዝ ግብር ተፈጥረ እምከርሰ ድንግል፡፡**»

ትርጉም፦ “ዳግመኛም መድኀን ክርስቶስ ከድንግል ስለመወለዱ በኢሳይያስ አፍ "ብዙ ሥራ እሠራ ዘንድ የያዕቆብንም ወገን አጸና ዘንድ አስራኤልንም አንድ አደርግ ዘንድ በማሕጸን ተፈጠርኩ አለ፡፡” ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ 76፡21 ቄርሎስም አለ፦‹‹**ወካዕበ ይቤ ከመዝ ይቤ እግዚአብሔር ዘፈጠረኒ እምከርሰ እኩኖ ገብረ ለአስተጋብኦተ ሕዝበ ያዕቆብ ወለአንሥኦተ እስራኤል እስመ ለሊሁ የአምረኒ፡፡**›› ትርጉም፦ “ዳግመኛም የያዕቆብን ወገን አንድ ለማድረግ፤ እስራኤልን ለማዳን አገልጋይ እሆነው ዘንድ በማሕጸን የፈጠረኝ እግዚአብሔር እርሱ ይወደኛልና፡፡” ኢየሱስ ማርያም ማኅፀን ውስጥ የተፈጠረ ከሆነ በምን ተፈጠረ? ሁሉን ነገር በቃል የተፈጠረ ነው፤ ከተፈጠረ ነገር ያለ ቃል ምንም የተፈጠረ ነገር የለም፦ ዮሐንስ 1፥3‹ሁሉ ነገር በእርሱ ተፈጥሯል፥ ከተፈጠረውም ሁሉ ያለ እርሱ የተፈጠረ ምንም የለም።› (ኢ.መ.ት) የክርስትና ውስብስብ ትምህርት ተመልሰው ይህ ድንግል ማርያም ማኅፀን ውስጥ የተፈጠረው ስጋ አምላክ ነው፤ ይመለካል ይሉናል፦ ሃይማኖተ አበው ዘቄርሎስ 78፥31 ቄርሎስም አለ፦ ‹‹**ወዓዲ ንቤ እስመ ሥጋሁ ለእግዚእነ ክርስቶስ አምላክ ውእቱ፡፡**›› ትርጉም፦ "ዳግመኛ የጌታችን የክርስቶስ ስጋ አምላክ እንደሆነ እንናገራለን፡፡›› አንድ ኑባሬ ከተፈጠረ አምላክ አይሆንም። ምክንያቱም አምላክ ከጊዜ በኃላ አይሰራምና፡፡ በኢሳይያስ 43፥10‹‹*ከእኔ በፊት አምላክ አልተሠራም ከእኔም በኋላ አይሆንም።*››

በሐዋርያት ሥራ 3፡26፣ 4፡27፣ እና 4፡30 ላይ የእንግሊዝኛዎቹን መጽሐፍ ቅዱሳት ብንመለከት ኢየሱስን «የአምላክ ባሪያ» በማለት ይገልጻሉ። ነገር ግን የአማርኛዎቹ ይህን ትርጉም እንዳይዙ ሆነው «ባሪያ፣ አገልጋይ» በሚለው ምትክ «ብላቴና፣ ልጅ» በሚለው ተተክቷል። በማስከተል ከእንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሚከተሉት ሰባቱ ኢየሱስን «የአምላክ ባሪያ» ብለው መግለጻቸውንና «ባሪያ» በሚለው ቃል ላይ በማሥመር እንመለከታለን፦ «እግዚአብሔር ብላቴናውን ባስነሳ ጊዜ፣ እያንዳንዳችሁን ከክፉ መልሶ ይባርካችሁ ዘንድ አስቀድሞ ወደ እናንተ ላከው።» (የሐዋርያት ሥራ 3፡26) “When God raised up his servant, he sent him first to you to bless you by turning each of you from your wicked ways.” (Acts 3:26, New International Version, NIV)

“To you first, God, having raised up **his servant Jesus**, sent him to bless you in turning away every one of you from your iniquities.” (Acts 3:26, New King James Version, NKJV)

“For you first, God raised up **His Servan**t and sent Him to bless you by turning every one of you from your wicked ways.” (Acts 3:26, New American Standard Bible Updated edition, NASU)

“Unto you first God, having raised up **His Servant**, sent him to bless you, in turning away every one of you from your iniquities.” (Acts 3:26, American Standard Version, ASV)

“For you first, God raised up **His Servant**, and sent Him to bless you by turning every one of you from your wicked ways.” (Acts 3:26, New American Standard, NAS)

“God, having raised up **His Servant,** sent Him to you first, to bless you in turning every one of you from your wickedness.” (Acts 3:26, Revised Standard Version, RSV)

“And as soon as God had Brought **His Servan**t to life again, he sent him first of all to you men of Israel, to bless you by turning you back from your sins.” (Acts 3:26, The Living Bible, TLB) ሰባቱም **«ባሪያውን ኢየሱስን»** ይላሉ።

«ለመፈወስ እጅህን ዘርጋ፤ በቅዱስ ብላቴናህም በኢየሱስ ስም ድንቅና ታምራትን አድርግ» (የሐዋርያት ሥራ 4፡30)

“Stretch out your hand to heal and perform miraculous signs and wonders may be done through the name of **your holy Servant Jesus**.” (Acts 4:30, New International Version, NIV)

“By stretching out your hand to heal, and that signs and wonders may be done through the name of your holy Servant Jesus.” (Acts 4:30, New King James Version NKJV)

“And send your healing power, and may miracles signs and wonders be done by the name of **your holy Servant Jesus**.” (Acts 4:30, The Living Bible, TLB)

“While Thy Stretchest forth thy hand to heal; and that signs and wonders may be done through the name of **thy holy Servant Jesus**.” (Acts 4:30, American Standard Version, ASV)

“While you extend your hand to heal, and signs and wonders take place through the name of **your holy Servant Jesus**.” (Acts 4:30, New American Standard Bible Updated edition, NASU)

“While thou stretchest out thy hand to heal, and signs and wonders are performed through the name of **thy holy Servant Jesus.**” (Acts 4:30, Revised Standard Version, RSV)

While thou dost extend Thy hand to heal, and signs and wonders take place through the name of **Thy holy Servant Jesus.**” (Acts 4:30, New American Standard, NAS) ሰባቱም«**አገልጋይ ኢየሱስ**» ይላሉ።

ሐ) «በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥንዮስ ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚች ከተማ አንተ ባቀባኸው በቅዱስ ብላቴናህ ላይ ከንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈጸም ነው።» (የሐዋርያት ሥራ 4፡27) “Indeed Herod and Pontius Pilate met together with the Gentiles and the people of Israel in this city conspire against Your holy Servant Jesus, Whom you anointed.” (Acts 4:27, New International Version, NIV)

“For truly against **Your holy Servant Jesus,** Who you anointed, both Herod and Pontius Pilate, with the Gentiles and the people of Israel, were gathered together” (Acts 4:27, New King James Version, NKJV)

“For truly in this city there were gathered together against **Your holy Servant Jesus**, Whom you anointed, both Herod and Pontius Pilate , along with the Gentiles and the peoples of Israel, (Acts 4:27, New American Standard Bible Updated Edition, NASU)

“For of a truth in this city against the **holy Servant Jesus**, Whom thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, with the Gentiles and the people of Israel, were gathered together.” (Acts 4:27, American Standard Version, ASV)

“For truly in this city there were gathered together against **Thy holy Servant Jesus**, Whom Thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, along with the Gentiles and the peoples of Israel.” (Acts 4:27, New American Standard, NAS)

“For truly in this city there were gathered together against **Thy holy Servant Jesus**, Whom Thou didst anoint, both Herod and Pontius Pilate, along with the Gentiles and the peoples of Israel, (Acts 4:27, Revised Standard Version, RSV)

“That is what is happening here in this city today! For Herod the king, and Pontius Pilate the governor, and all the Romans-as well as the people of Israel-are united against Jesus, your anointed Son, **Your holy Servant**.” (Acts 4:27, The Living Bible, TLB) ሰባቱም «አገልጋይ ኢየሱስ» ይላሉ። ከላይ የጠቀስናቸው የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ጥቅሶች በሙሉ ስለ ኢየሱስ የአምላክ አገልጋይነት አንጂ ስለ አምላክነቱ አይደለም የሚገልጹት!!! ይህ እንግሊዝኛው ሲሆን የ1980 ቀላል ትርጉም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከበፊቱ በተለየ መልኩ ልክ እንደ እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስን

አገልጋይ ይለዋል፡- «በእርግጥም ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአረማውያንና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች ከተማ ተሰብስበው መሲህ ባደረግኸው በቅዱስ አገልጋይህ በኢየሱስ ላይ ተነሱ፤» (የሐዋርያት ሥራ 4፡27) እንግሊዝኛው መጽሐፍ ቅዱስ «Your Servant Jesus» «አገልጋይህ ኢየሱስ» ይላል። ለምን አማርኛው ይህንን «አገልጋይህ» የሚለውን በ«ብላቴናህ» ቀየረው? ኢየሱስ የአምላክ ባሪያና አገልጋይ ከሆነ እንዴት አምላክ ሊሆን ይችላል? የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎችስ ምነው «የአምላክ አገልጋይ» የሚለውን በ«ብላቴና» መለወጣቸው? ኢየሱስ አምላክ እንዲሆን ፈልገው ይሆን?

## <u>የኢየሱስ የአምላክ ባሪያነት በአዲስ ኪዳን</u>

ወደ ኢየሱስ ስንመጣ ፈጣሪ ኢየሱስን "አብዲ" עַבְדִּי ማለትም "ባሪያዬ" በማለት ፈጣሪ ተመላኪ ኢየሱስ አምላኪ መሆኑን ቁልጭ አድርጎ ያሳያል፡- ኢሳይያስ 42፥1 እነሆ ደግፌ የያዝሁት "**ባሪያዬ**" עַבְדִּי፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አድርጌአለሁ፥ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል። ይህንን በኢሳያያስ በኩል "ባሪያዬ" የሚለውን ትንቢት ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ተርጓሚዎች "ብላቴና" ማለትም "ልጄ" ብለው ለመለወጥ ቢዳዱም ግሪኩ ግን **"ፔይስ ሞዩ" παῖς** ማለትም **"ባሪያዬ"** ብሎ አስቀምጦታል፤ "ፔይስ" παῖς ማለት "ባሪያ" ማለት ነውና፡- ማቴዎስ 12፥17-18«***በነቢዩ ለአሕዛብ በኢሳይያስ የተባለው ይፈጸም ዘንድ እንዲህ ሲል፡-እነሆ የመረጥሁት <u>"ባሪያዬ" παῖς μου</u> ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፥ ፍርድንም ያወራል።***» በትርጉም ኢየሱስን "ልጅ" ብለው ቢቀይሩትም ግሪኩ ግን "ባሪያ" ብሎ ያስቀመጠበት ጥቅስ በቁና ነው፣ በተጨማሪም የአማርኛው ትርጉም እና KJV ትርጉም "ልጅ" እያሉ ቢለውጡም NIV ትርጉም በትክክል የግሪኩን ትርጉም ይዞ "ባሪያ" ብሎ አስቀምጦታል፡- በሐዋሪያት ሥራ 3:13«***የአብራሃምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥ የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት የካዳችሁትን <u>"ባሪያዬውን" παῖς ኢየሱስን አከበረው</u>።***»

በሐዋሪያት ሥራ 3:26«ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር <u>"ባሪያዬውን" παῖς</u> አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።»

በሐዋሪያት 4:27-28« በቀባኸው በቅዱሱ “ባሪያህ” παῖς በኢየሱስ ላይ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር፥ እጅህና አሳብህ እንዲሆን አስቀድመው የወሰኑትን ሁሉ ሊፈጽሙ፥ በዚች ከተማ በእውነት ተሰበሰቡ።» በሐዋሪት ሥራ 4:29-30«አሁንም፥ ጌታ ሆይ፥ ወደ ዛቻቸው ተመልከት፤ ለመፈወስም እጅህን ስትዘረጋ በቅዱስ “ባሪያህም” παῖς በኢየሱስ ስም ምልክትና ድንቅ ሲደረግ፥ ባሪያዎችህ በፍጹም ግልጥነት ቃልህን እንዲናገሩ ስጣቸው።» "ባሪያ" ማለት ለፈጣሪ ሲሆን "አምላኪ" ማለት ስለሆነ ስለ አማኞች በሚናገርበት አውድ ላይ፡- "ባሪያዎቹም ያመልኩታል" በማለት ተናግሯል፡- ራእይ 22፥3 «ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፡፡» ራእይ 22፥6 «እርሱም፡- እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞች ናቸው፥ የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር *ለባሪያዎቹ* እንዲያሳይ መልአኩን ሰደደ።» ራእይ 22፥9«እርሱም፡- እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ *ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ*፤ ለእግዚአብሔር ስገድ አለኝ።» መላእክት፣ ነብያት፣ ቃሉን የሚታዘዙ ሁሉ ለፈጣሪ ባሮች የተባሉት አንዱን አምላክ ስለሚያመልኩ ነው፤ ለፈጣሪ ባርነት አርነት ነው፤ የፈጣሪ ባሪያ መሆን ፍጹምና እውነተኛ ነጻነት ነው፡፡ ፲ኛ ጴጥሮስ 2፥16«አርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ሁኑ* እንጂ ያ አርነት ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ።»

## ምዕራፍ ሁለት

## ኢየሱስ የሰው ሥጋ ለብሶ አምላክ ሆኖ አልመጣም፤ እንዲሁም አምላክ ሰው አይደለም፤ ሰውንም አይመስልም።

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሁለት አይነት ባሕርያትን ተላብሶ ነው የመጣው ይላሉ። ኢየሱስ “ፍፁም ሰው”፤ “ፍፁም አምላክ” ነው። ይህ ማለት ፍፁም ሰው ነው ማለት ፍፁም አምላክ አይደለም ማለት ነው። ፍፁም አምላክ ነው ማለት ደግሞ ፍፁም ሰው አይደለም ማለት ነው። በኦሪት.ዘኁልቁ 23፡19«***ሐሰትም ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም። ሰለዚህ አምላክ እግዚአብሔር ይዋሽም ይፀፀትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም***» ይላል። አምላክ እግዚአብሔር ይዋሽም ይፀፀትም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም። ኢየሱስ ደግሞ አምላክ ሳይሆን ሰው ሆኖ ነው የመጣው። አምላክ እግዚአብሔር ደግሞ ሰው አይደለም። አሁንም አምላክ ሰው እንደማይመስል በሚከተሉት ምዕራፎች ተጨማሪ ጥቅሶች እናገኛለን። በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 15፡29 «***የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር አይዋሽም፤ አይፀፀትም። እርሱም ይፀፀት ዘንድ የሰው ልጅ አይደለምና።***» ክርስቲያን ወገኖቻችን ሆይ በኦሪት.ዘኁልቁ ከተገለጸው ንግግር በምን ይለያል? ደግሞስ ይህ ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል? እውቀትን መረዳት ለፈለገ እውነቱ ይህና ይህ ብቻ ነው። ነገሩ ሚስጢር አይደለም። ተመሳሳይ መልእክት በትንቢ.ተ.ሆሴዕ 11፡9 ላይ እናገኛለን። «***እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁምና በቁጣም አልመጣም***» ይላል። አንዳንድ ክርስቲያን ወገኖቻችን አምላክ ሰው የሆነው የሰው ባሕሪ ተላብሶ ነው ይላሉ። አምላክ አንዴ ሰው ሌላ ጊዜ የሰው ባሕሪያትን እንደማይላበስና እንደማይቀያየር በትንቢ.ተ.ሚልኪያስ 3፡6 ላይ «***እኔ እግዚአብሔር አልለዋወጥም***» ብሏል። እውነቱ ይህ ነው፤ አላህ ሐቅን በሐቅነቱ የሚቀበል አዕምሮ ይስጠን። እንዴት አምላክ ሰው ይሆናል? እሱን የሚመስል ሰው አለን? ያ ማለት እኮ አምላክን እንደሰው ልጅ ቀይ፣ ጥቁር፣ ጠይም፣ ፈረንጅ፣ ሐበሻ ወ.ዘ.ተ.ይመስላል እያልን ልንገልጸው ማለት ነው። ከላይ ያየናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ምዕራፍ ቁጥሮች ወንጌልና ሌሎችንም ጨምሮ ኢየሱስ ከውልደቱ ጀምሮ እስከ አረገበት ጊዜ እንዲሁም ከአረገ በኋላም የሰው ልጅ ብቻ ነው። በትንሳኤ ቀን በሚመጣበትም ጊዜ ኢየሱስ አምላክ ሳይሆን

ሰውና የሰው ልጅ ብቻ ነው። ቀለል እናድርገውና ከውልደቱ ጀምሮ እስከ አረገበት ጊዜ በርካታ ሰብዓዊ ባሕሪያትና ችግሮችን እንዳሳለፈ፤ ባጠቃላይ የሰው ልጅ የሆነውን እንደሆነ ነው የሚያስረዳው። ጳውሎስ ራሱ ስለ ኢየሱስ ማንነት ሲናገር፡- በ1ኛ ጢሞቶዎስ 2፡5«***አንድ እግዚአብሔር አለና፤ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል አንድ አስታራቂ አለ። እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው***» ይላል። አምላክ አንድ እግዚአብሔር ነው፤ ኢየሱስ ደግሞ ሰውና የሰው ልጅ ነው። ኢየሱስ ካረገ በኋላም ሰው ነው። በዮሐንስ ወንጌል 3፡13«***ከሰማይ ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም። እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።***» በተጨማሪም ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 8፡34«***የሰው ልጅ በአብ ቀኝ ይቀመጣል።***» ስለዚህ ኢየሱስ ካረገ በኋላም የሰው ልጅ ነው። ተጨማሪ በሐዋሪያት ሥራ 2፡22«***የእስራኤል ሰዎች ሆይ! ይህን ቃል ስሙራሳችሁ እንደምታውቁት፤ የናዝሬቱ ኢየሱስ እግዚአብሔር በመካከላችሁ ባደረገው ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው*** *ነበር።*»

# ምዕራፍ ሦስት

## ስለ ኢየሱስ የአምላክ መልእክተኛነት አራቱ ወንጌሎች ምን ይላሉ?

ለመልእክተኝነቱ አራቱ ወንጌሎች ስለሱ ምን ይላሉ የሚለውን ማስረጃ በማስቀደም እናያለን። ስለ ኢየሱስ በእውነት መመስከር በሁላችን ግዴታ ነው።

## የማቴዎስ ወንጌል

በማቴዎስ ወንጌል 10፡32-33 ‹‹***ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ፤ እኔም በሰማዩ ባለው አባቴ (አምላኬ) ፊት እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት ለሚከዳኝ ሁሉ፤ እኔም በሰማዩ ባለው አባቴ (አምላኬ) ፊት እከዳዋለሁ።***›› እዚህ ላይ እንደምንረዳው ኢየሱስ ‹**ሰው**› ብሎ የሚመሰክርልኝ አለ እንጂ መቼ አምላክ ብሎ የሚመሰክርልኝ አለ? ደግሞ በሰው ፊት የሚከዳውን ነገ በአምላኩ ፊት ይከዳዋል። ከዚህ የበለጠ ውርደት የለም። ኢየሱስም በካሃዲያን ላይ የሚመሰክርበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ስለማንነቱ በእውነቱ መመስከር የሕይወት መንገድ ነው። በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41 ‹‹***እናንተን የሚቀበል (ሐዋሪያቶችን ማለት ነው።) እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል፤ የነብይን ዋጋ ያገኛል***›› ይላል። ኢየሱስ እኔን የሚቀበል የላከኝንም ይቀበላል ብሏል። ታዲያ እናንተ ተቀብላችሁታል? ኢየሱስ ያለው፤ ነብይ በነብይ ስም የሚቀበል አለ እንጂ ነብይን በአምላክ ስም የሚቀበል መቼ አለ? እኛ ሙስሊሞች አልሐምዱሊላህ ይህን የኢየሱስን ንግግር እውነት ብሎ በማመን እንቀበለዋለን። ‹‹**ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል፤ የነብይን ዋጋ ያገኛል። ፃድቁን በፅድቅ ስም የሚቀበል፤ የፃድቁን ዋጋ ያገኛል**›› ይላል። ኢየሱስን በነብይነቱ ስላልተቀበላችሁት የፅድቅን ዋጋ አታገኙም። በማቴዎስ ወንጌል 12፡30 ‹‹***ከኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይቃወመኛል፤ ከእኔ ጋር ያልሆነ ሁሉ ይበተናል***›› ይላል። በዚህ ጥቅስ መሰረት ከኢየሱስ ጋር ያልሆነው ማን ነው? ነብይነቱን ካለመቀበል ጋር በቃል ብቻ እንወደዋለን፤ እንቀበለዋለን፤ የሚለው አባባል ለአዕምሮ አይጎረብጥም? በማቴዎስ ወንጌል 13፡ 57-58 ‹‹***በዚህም ምክንያት ተሰናከለውበት ሳይቀበሉት ቀሩ፤ ኢየሱስ ግን ‹‹ነብይ›› የሚናቀው በገዛ ሀገሩና በገዛ ቤተሰቡ ነው እንጂ በሌላ ቦታስ ይከበራል አላቸው። ባለማመናቸው ምክንያት ኢየሱስ ብዙ ተዓምር አላደረገም።***››

ኢየሱስን ያከበረው "ነቢይ ነው" ብሎ ያመነ ነው ወይስ ያልሆነውን "አምላክ" ብሎ በውሸት ያመካሸው? በማቴዎስ ወንጌል 15፡24 ‹‹***እርሱም እኔ የተላኩት ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች ብቻ ነው ሲል መለሰላቸው።***›› እዚህ ላይ ደግሞ ኢየሱስ በነብይነቱ እንኳ የተላከው ለእስራኤል ሕዝቦች ብቻ እንጂ ለዓለም እንዳልሆነ እራሱ ተናግሯል። በመልእክተኛነቱ እንኳ ለዓለም ሳይላክ እንዴት "የዓለማት ጌታ" ነው የሚባለው እንዴት ነው? በማቴዎስ ወንጌል 21፡10-11 ‹‹***ኢየሱስ ወደ እየሩሳሌም በገባ ጊዜ የከተማ ሰዎች በሙሉ ይህ ማን ነው? በማለት ታወኩ። ሕዝቡም ይህ በገሊላ ክፍለ ሀገር ከሚገኝ ከናዝሬት ከተማ የመጣ ነብዩ ኢየሱስ ነው አሉ።***›› ክርስቲያኖች! እናንተ በጊዜው ከኢየሱስ ጋር አብረው ከነበሩት ሰዎች የዓይን ምስክርነት ትበልጣላችሁን? መቼም ቢሆን ከሐዋሪያቶችና በጊዜው ከነበሩ ሰዎች የሚቀድም ክርስቲያን በፍፁም አይኖርም። በጊዜው አብረውት የነበሩት ሰዎች የዓይን ምስክረ ሙስሊሞች ነበሩና እንደ እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን በነብይነቱ አምነዋል። ሐዋሪቱ ሙስሊሞች ነበሩ። ምክንያቱም ኢየሱስን በነብይቱ የሚያምን እኛ ሙስሊሞች ሐዋሪያቶችና በጊዜው አብረው የነበሩ የዓይን ምስክር የነበሩ ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚህ ሰዎች ኢየሱስን ነብይ ነው አሉ። እናንተ ደግሞ ክርስቲያን ነን የምትሉ ኢየሱስን "አምላክ" ነው ትላላችሁ። ታዲያ ከእነርሱና ከእናንተ የማን ንግግር ይታመን? እነርሱ በቦታው ተገኝተው መስክረዋል። ‹**ማየት ማመን ነው**› ይባል የለ!!!

## በማርቆስ ወንጌል

በማርቆስ ወንጌል 1፡38‹‹***እንዲህም አለ፡- እኔ የመጣሁት ለማስተማር ስለሆነ በቅርብ ወደ አሉት ሰዎች እንሂድ አላቸው።***›› ስለዚህ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የተላከው አምላኩ ያለውን ለማስተማር እንጂ እኔን በብቸኝነት አምልኩ ብሎ ለመጣራት አይደለም። በማርቆስ ወንጌል 3፡31-34‹‹***የኢየሱስ እናትና ወንድሞቹ ወደ እርሱ መጡ እንደሚፈልጉትም ነገሩት። እርሱም እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? ሲል መለሰ። በዙሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩት እየተመለከተ ‹‹እነሆ›› እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው። ‹‹የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈፅሙ ሁሉ እርሱ ወንድሜም እህቴም እናቴም ነው›› አለ።***›› በጥቅሱ መሰረት እናንተ የኢየሱስ እናት ወንድምና እህት ናችሁ? የኢየሱስ እናት ማርያም መሆኗስ ግልፅ አይደለምን? እዚህ ላይ ኢየሱስ የእምነት ወንድምና እህት

ለማለት ፈልጎ እንጂ የስጋ እናት፣ ወንድም እህት ማለቱ አይደለም። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ የሚፈፅም በሙሉ የሚፈፅም ኢየሱስ የእምነት እናት፣ ወንድምና እህት ነው። በዚህ መሰረት እኛ ሙስሊሞች የኢየሱስ የእምነት ወንድሞች ነን። በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41*«__ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል፤ የነብይን ዋጋ ያገኛል። ፃድቁን በፅድቅ ስም የሚቀበል፤ የፃድቀን ዋጋ ያገኛል__»* ስላለ ለዚህ መስፈርት ደግሞ ቀዳሚዎቹና ተጋባዦቹ ሙስሊሞች ብቻ ነን። በማርቆስ ወንጌል 6፡4*«ኢየሱስ በናዝሬት ብዙ ተቃውሞ ደረሰበት፤ __ኢየሱስም ነብይ__ በሌሎች ዘንድ __ይከበራል__፤ በገዛ አገሩና ዘመዶቹ ግን __ይናቃል__።»* እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን እናከብረዋለን፤ እንወደዋለን።

## __በዮሐንስ ወንጌል__

በዮሐንስ ወንጌል 5፡23-24 *«ወልድን የማያከበር፤ __የላከውንም አያከብርም፤ እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ፤ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።__»* ኢየሱስ “አምላክ” ነው የሚል በኢየሱስም ሆነ በላከው አላመነም። እንዴት የዘላለም ሕይወት የሚያገኘው? የሰው ልጅ እኮ ደካመና አቅመ ቢስ ነው። እሳትን የሚችል አንድም ፍጥረት የለም። ስለ ኢየሱስ ማንነት በተለያዩ ዓመታት የሚታተሙ የመጽሐፍ ቅዱስ እትሞች የኢየሱስን ማንነት አጉልተው ያሳያሉ። ለምሳሌ፡- በቅርብ ጊዜ ከታተሙት ውስጥ የሚከተሉትን ምዕራፎች እንመልከታቸው፡- 1). የ1993 እና የ1997 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30 *«__እኔ ብቻዬን ከራሴ ምንም ማድረግ አልችልም። የምፈርደው የምሰማውን ብቻ ነው።__»* 2). የ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30*«__እኔ በራሴ ስልጣን ምንም ማድረግ አልችልም፤ ነገር ግን ከአብ የሰማሁትን እፈርዳለሁ። የላከኝን ፈቃድ እንጂ የራሴን ፈቃድ ስለማላደርግ ፍርዴም ትክክል ነው።__»* 3). የ1954 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30*«__እኔ ብቻዬን አንዳች ማድረግ አይቻለኝም።__»* ጥያቄ ኢየሱስ አምላክ ነው ከተባለ ለምንድ ነው ከራሱ ምንም ማድረግ የማይችለው? ደካማ አምላክ አለ ሊባል ነውን? ለአምላክ የሚሳነው ምን አለ? ደግሞ ኢየሱስ ከአብ የሰማሁትን ነው ይላል። አምላክ ከሌላ አምላክ ይሰማልን? በዮሐንስ ወንጌል 5፡31 ላይ ኢየሱስ ስለ ራሱ ሲናገር፡- *«እኔ __ስለራሴ ብመሰክር__ ምስክርነቴ __እውነት አይደለም__»* ይላል። በመቀጠል ስለ ኢየሱስ ነብይነት የሚመሰክርለት አምላኩ እንደሆነ ተናግሯል። በዮሐንስ ወንጌል 5፡32 *«ነገር ግን*

***ስለእኔ የሚመሰክርልኝ ሌላ አለ፤ እርሱም ስለእኔ የሚመሰክረው ምስክርነት እውነት እንደሆነ አውቃለሁ።***» በእርግጥም ከአምላክ የበለጠ የማን ንግግር ይታመናል? ስለዚህም ነው፦ በዮሐንስ ወንጌል 5፡36-37«***እኔ ግን ከዮሐንስ የበለጠ ምስክር አለኝ፤ ምስክሬም እንድሰራው የሰጠኝ ሥራ ነው። ይህም የምሰራው ሥራ አብ እንደላከኝ ስለእኔ መሰክሯል።***» እዚህ ላይ አንድ ነገር መገንዘብ አለብን። ስለኢየሱስ ነብይነት 1ኛ ራሱ ኢየሱስ፤ 2ኛ ዮሐንስ፤ 3ኛ አምላክ መስክረዋል። ለአብነት ያክል እነዚህን ጠቀስኩ እንጂ ስለ ኢየሱስ ነብይነት በጊዜው የነበሩ ሰዎች፤ ሐዋሪያት እንዲሁም ሌሎችም የዓይን ምስክር የነበሩት ሰዎች በነብይነቱ መስክረዋል። ስለዚህ እናንተም ምስክሩን ከሰማችሁና ካወቃችሁ በኋላ እናንተም ስለ ኢየሱስ ነብይነት መመስከር ይገባችኋል እላለሁ። ይህ ካልሆነ ግን የነብይን ነብይነት ያልተቀበለና ያልመሰከረ ቅጣት እንደሚጠብቀው መለኮታዊ መጽሐፍት ይጠቁማሉ። በዮሐንስ ወንጌል 5፡37 ላይ እንዲህ ይላል፦ «***እናንተ ግን ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፤ መልኩንም አላያችሁም።***» በዮሐንስ ወንጌል 5፡38-42«***እርሱ የላከውን ስለማታምኑ የእርሱ ቃል በእናንተ ዘንድ አይኖርም። እናንተ የእግዚአብሔር ፍቅር የሌላችሁ መሆኑን አውቃለሁ***» ብሏል። በከንቱ እንወደዋለን ማለት መሰረተ ቢስ አባባል ነው። በዮሐንስ ወንጌል 5፡43-44 «***እኔ በአባቴ ስም መጣሁ እናንተ ግን አልተቀበላችሁኝም፤ እርስ በርሳችሁ ከሰው ክብር የምትፈልጉ። ነገር ግን ከአንዱ አባቴ ከእግዚአብሔር የሚገኘው ክብር ግን የማትፈልጉ እናንተ እንዴት በእኔ ልታምኑ ትችላላችሁ?***» የሙስሊሞች ጥያቄ ይህ ነው። ኢየሱስን ካልተቀበላችሁት እንዴት በላከው ልታምኑ ትችላላችሁ? በእሱ ማንነት ማመን ማለት የላከውን ማመንና መቀበል ማለት ነው። በዮሐንስ ወንጌል 5፡46-47 ደግሞ እንዲህ ይላል፦ «***ሙሴን ብታምኑ ኖሮ እርሱ ስለእኔ ጽፏልና እኔንም ባመናችሁ ነበር። እርሱ የፃፈውን ቃል ካላመናችሁማ የእኔን ቃል እንዴት ታምናላችሁ?*** ይላል። ምስጋና እስልምናን ለቸረን ለዓለማቱ ጌታ ይገባው። እኛ ሙስሊሞች በሁሉም ነብያት እናምናለን። በዮሐንስ 6፡14 እንዲህ ይላል፦ «***ሰዎችም ኢየሱስ ያደረገውን ተአምር ባዩ ጊዜ ወደ ዓለም የሚመጣው ነብይ ይህ ነው አሉ።***» ከዚህ በተፃራሪ ክርስትና እምነታችን ነው የሚሉ የአሁን ሰዎች ደግሞ ወደ ዓለም የሚመጣው አምላክ ይህ ነው አሉ። የነበሩት የዓይን ምስክሮች ያዩትን ተአምር እንኳ አይተው ከነብይነት ውጪ ሌላ ማዕረግ አልሰጡትም። እንዲውያም ‹***ማየት ማመን ነው***› ይባል የለ። በዮሐንስ ወንጌል 6፡28-29 ‹***ሰዎችም ታዲያ***

***የእግዚአብሔር ሥራ ለመስራት ምን ማድረግ ይገባናል አሉት? ኢየሱስም የእግዚአብሔር ሥራማ እግዚአብሔር በላከው ማመን ነው ሲል መለሰላቸው።»*** በአሁኑ ሰዓት በኢየሱስ ነብይነትና በላከው ብቸኛ አምላክ የሚያምኑ ሙስሊሞች ብቻ ናቸው። በዮሐንስ ወንጌል 6፡38 እንዲህ ይላል፡- ***«እኔ ከሰማይ የወረደኩት የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ እንጂ የራሴን ፈቃድ ለማድረግ አይደለም።»*** በዮሐንስ ወንጌል 6፡39***«የላከኝም ፈቃድ ከሰጠኝ ሁሉ አንድ እንኳ ስለጠፋ በመጨረሻ ቀን እንድነሳ ነው።»*** በዮሐንስ ወንጌል 6፡40***«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲያገኝ ነው።»*** እዚህ ላይ በእርሱ የሚያምን አለ እንጂ መች በእኔ አምላክነት የሚያምን አላለም። ስለዚህ ትኩረት መስጠት ያሻል። በዮሐንስ ወንጌል 6፡44 ***«የላከኝ አብ የሳበው ካልሆነ በስተቀር ወደኔ መምጣት የሚችል ማንም የለም።»*** በዮሐንስ ወንጌል 6፡57 ***«ኅያው አብ እንደላከኝ፤---»*** በዮሐንስ ወንጌል 7፡16 ***«የሚያስተምረው ትምህርት ከላከኝ አብ የመጣ ነው፤ እንጂ ከእኔ አይደለም።»*** በዮሐንስ ወንጌል 7፡17***«የላከኝን ፈቃድ ማድረግ የሚፈልግ ቢኖር ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር የተገኘ ወይም እኔ የተናገርኩት መሆኑን ለይቶ ያውቃል።»*** እኛ ሙስሊሞች መጽሐፍን ቅዱስ ተንተርሰን እንጂ የምንከራከራችሁ በራሳችን ሐሳብ አፍልቀን አለመሆኑ ሊታወቅልን ይገባል። በዮሐንስ ወንጌል 7፡18 እንዲህ ይላል፡-***«ከገዛ ራሱ የሚናገር የገዛ ራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እውነተኛ ነው፤ ሐሰትም አይገኝበትም።»*** እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስ የላከውን እናከብራለን፤ ክርስቲያኖች ግን ኢየሱስንም ሆነ የላከውን አያከብሩም። በዮሐንስ ወንጌል 7፡28 ***«ኢየሱስ በቤተ መቅደስ ሲያስተምር ድምጹን ከፍ አድርጎ እንዲህ አለ፡- እኔን ታውቁኛላችሁ አዎ ከወዴትም እንደመጣሁ ታውቃላችሁ። ነገር ግን እኔ በራሴ ስልጣን አልመጣሁም የላከኝ እውነተኛ ነው።»*** ጥያቄ፣ ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ለምን በገዛ ስልጣኑ አልመጣም? በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 7፡28***«መጨረሻው የላከኝን አታውቁም እኔ ግን እርሱ ስለላከኝ አውቀዋለሁ»*** ብሏል። ኢየሱስ አላህ እንደላከው ጠንቅቆ ያውቃል። በዮሐንስ ወንጌል 7፡40 ***«ከሕዝቡ አንዳቸው ይህን ቃል በሰሙ ጊዜ ይመጣል የተባለው ነብይ በእርግጥ ይህ ነው አሉ።»*** በጊዜው የነበሩ ሰዎች እውነታውን አልካዱም። ኢየሱስ ያስተማረው ከጌታ የታዘዘውን አምለክ የላበትን መልእክት ነው። በጊዜው የነበሩ ሰዎች በእርግጥ ይህ “ነብይ” ነው ብለዋል። ሙስሊሞች በዓይን ካዩት ሰዎች ጋር ተመሳሳይ አቋም አላቸው። ኢየሱስም አምላክ መባሉን አይፈልግም። አምላክ

ነው ማለት ውዴታን አይገልጽም ጥላቻን እንጂ። በዮሐንስ ወንጌል 8፡14«*ማንም እንኳ እኔ ስለራሴ ቢመሰክር ከየት እንዳመጣሁ ወደየትም እንደምሄድ ኢታውቁም። የላከኝ አብ ከኔ ጋር ነው።*» በዮሐንስ ወንጌል 8፡17-19«*የሁለት ሰዎች ምስክርነት እውነት እንደሆነ በሕጋችሁ ተጽፏል። ስለዚህ እኔ ራሴ እመሰክራለሁ፤ የላከኝ አብ ስለኔ ይመሰክራል። እርሱም አባትህ የት አለ? ሲሉ ጠየቁት እኔንም ሆነ አባቴን ኢታውቁም። እኔን ብታውቁ አባቴን ባወቃችሁ ነበር ሲል መለሰላቸው።*» በዮሐንስ ወንጌል 8፡26 «*ይሁን እንጂ የላከኝ እውነተኛ (ታማኝ) ነው።*» በዮሐንስ ወንጌል 8፡42 «*ኢየሱስም አለ፡- እኔ እዚህ ያለሁት ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቼ ነው። የላከኝ እርሱ ነው እንጂ እኔ በራሴ ስልጣን አልመጣሁም።*» በዮሐንስ ወንጌል 8፡43 «*ስለምን ንግግሬ አይገባችሁም? ቃሌን መቀበል ስለማትፈልጉ ነው*» ይላል። ስለምን ንግግሩ አይገባችሁም? እኔ መልእክተኛ ነኝ እያለ፤ ማን እንደላከው እየተናገረ፤ በእሱ ማንነት አለማመን ምን ይባላል? በዮሐንስ ወንጌል 8፡44-45 «*እናንተ የአባታችሁ የዲያቢሎስ ልጆች ናችሁ፤ ፍላጎታችሁም የአባታችሁን ምኞት መፈፀም ነው። እርሱ ከመጀመሪያ አንስቶ ነብሰ ገዳይ ነበር፤ እውነት ከእርሱ ሌላ ከእውነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም፤ እርሱ ከሐሰተኛና የሐሰት አባት ስለሆነ ሐሰት በሚናገርበት ጊዜ ከራሱ አውጥቶ ይናገራል። እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለሆንኩ ኢታምኑኝም።*» በዮሐንስ ወንጌል 8፡46-47 «*ለመሆኑ ከእናንተ ኃጢአተኛ ነህ ብሎ የሚወቅሰኝ ማን ነው? እውነት የምናገር ከሆንኩ ታዲያ ለምን ኢታምኑኝም? ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል። እንግዲህ እናንተ የእግዚአብሔርን ቃል የማትሰሙት ከእግዚአብሔር ስለሆናችሁ ነው።*» ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል። በዮሐንስ ወንጌል 8፡54-55«*ኢየሱስ እንዲህ ሲል መለሰ፡- እኔ የራሴን ክብር ብፈልግ ክብሬ ዋጋ የለውም። እኔን የሚያከብረኝ አባቴ ነው። እርሱም አምላካችን የምትሉት ነው። እናንተ ግን እርሱን አላወቃችሁትም፤ እኔ አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንኩ ነበር። ነገር ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ።*» ኢየሱስ የላከውን ያውቃል፤ ቃሉንም ይጠብቃል። እናንተ ክረስቲያኖች ደግሞ በተቃራኒው ናችሁ የሚያሳዝን ጉዳይ ነው። በዮሐንስ ወንጌል 9፡4«*ቀን ሆኖ ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ፤ ማንም ሊሰራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣል።*» እዚህ ላይ ኢየሱስ ምን ያክል አምላኩን ፈሪና ታዛዥ መሆኑን ይነግረናል። በዮሐንስ ወንጌል 9፡17«*ሰዎች ዓይነ ስውር ወደ ነበረው ሰው ተመልሰው*

***ዓይንህን ስለከፈተልህ ሰው ምን ትላለህ? አሉ። ሰውየውም እርሱ ነብይ ነው አለ።»*** ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ብዙ ተአምር አድርጓል። ስለዚህ አምላክ ነው ይላሉ። ነገር ግን በጊዜው አብሮት የነበረውና ዓይኑንም ያዳነለት ሰው ኢየሱስን ነብይ ነው ብሎ ነው የመሰከረው። ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ያ አብሮት የነበረው የዓይን ምስክር ይሆን ነበር። ኢየሱስ ተአምር የሚያደርገው በአምላክ ፈቃድ ነው እንጂ በእራሱ ኃይል አይደለም። በማስረጃ እንመልከት፡- በዮሐንስ ወንጌል 10፡25 ***«በአባቴ ስም የማደርጋቸው ተአምራትም ስለእኔ ይመሰክራሉ።»*** ለዚህ አይደል ተአምር ያየው ሰው ኢየሱስን ነብይ ነው ያለው። በዮሐንስ ወንጌል 10፡18 ***«ይህን ትእዛዝ የተቀበልኩት ከአባቴ ነው።»*** እዚህ ላይ ኢየሱስ ትእዛዝን እንደሚፈፅምና የተቀበለው ትእዛዝ ከአባቱ (ከአምላኩ) ነው። በዮሐንስ ወንጌል 10፡25 ***«ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡- «እኔ ነግሬአችሁ፤ እናንተ ግን አታምኑም በአባቴ ስም የምሰራቸው ሥራ ስለኔ ይመሰክራሉ።»*** በዮሐንስ ወንጌል 10፡29 ***«የሰጠኝ አባቴ ከሁሉም ይበልጣል።»*** በእርግጥም አምላክ ከሁሉ በላጭ ነው፤ የሚወዳደረው የለምና። በዮሐንስ ወንጌል 14፡15 ***«ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ።»*** በዮሐንስ ወንጌል 14፡21 ***«ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ይወደኛል። እኔን የሚወደን አባቴን ይወደዋል፤ እኔም እወደዋለሁ።»*** እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን እንወደዋለን፤ እርሱን በመውደዳችን ከላይ በጥቅሱ እንደተወሳው አምላካችንም ይወደናል። በዮሐንስ ወንጌል 14፡24 ***«የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙት ቃል የላከኝ አብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።»*** ኢየሱስን የማይወድ ቃሉን አይጠብቅም። በዮሐንስ ወንጌል 14፡31 ***«ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድ ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን ሁሉ እፈፅማለሁ።»*** ኢየሱስ የአምላኩን ትእዛዝ ይጠብቃል። ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ሰው የሚድነው በእምነት እንጂ ትእዛዝን በመፈፀም አይደለም ይላሉ። በከንቱ ጽድቀናል ብለው ራሳቸውን የሚያታልሉ በአጉል ምኞት የተሸነገሉ ናቸው። በዮሐንስ ወንጌል 15፡9-10***«አብ እኔን እንደሚወደኝ እኔም እናንተን ወደድኳችሁ እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደፈፀምኩና በፍቅሩ እንደኖርኩ እናቴም የእኔን ትዕዛዝ ብትፈፅሙ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።»*** በዮሐንስ ወንጌል 17፡3***«የዘላለም ሕይወትም፤ ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውን አንተንና የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው።»*** የዘላለም ድነት የሚገኘው ዮሐንስ 17፡3 ላይ በተጠቀሰው መሰረት ነው። ኢየሱስ ለሐዋሪያቶች ሲናገር፡- በዮሐንስ ወንጌል 17፡6-8 ***«እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል፤***

***የሰጠኸንም ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ፤ አንተ እንደላከኸም አምነዋል።»*** እነማን ናቸው ቃሉን የጠበቀና በኢየሱስ መላክተኛነት የሚያምን? እንዲሁም አላህን የሚውቅ ማን ነው? ክርስቲያኖች ወይስ ሙስሊሞች ፈርዱን ለእምነቱ ተከታዩች ለሆኑት ትቻለሁ። ሐዋሪያቶች በኢየሱስ ነብይነት ስለሚምኑ ነው ***«አንተ እንደላከኸ አምነዋል»*** ያለው። በዮሐንስ ወንጌል 17፡25 ***«ፃድቅ አባት ሆይ! ዓለም ባያውቅህም እኔ አውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደላከኸ አውቀዋል።»*** ክርስቲያኖች እንጂ አላህን የማያውቁት ሐዋሪያቶችና ኢየሱስ ግን ያውቁታል። ለምን ቢሉ ሙስሊሞች ናቸውና። በኢየሱስ መልእክተኛነት የሚያምን ሁሉ ሙስሊም ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል 18፡37 ***«ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል።»*** ሐቅን የፈለገ ሁሉ ሐቅን ይቀበላል። በዮሐንስ ወንጌል 20፡17 ***«እኔ ወደ አባታችሁና ወደ አባቴ ወደ አምላካችሁና ወደ አምላኬ አላረኩም።»*** ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ወደ አምላኬ ይል ነበር?

## በሉቃስ ወንጌል

በሉቃስ ወንጌል 4፡43-44 ***«ሰዎች ኢየሱስን አትለየን አሉት፤ እርሱ ግን እኔ የተላኩበት ለዚህ ነው ወደ ሌሎች ከተሞች ሄጀ የእግዚአብሔርን መንግስት ማብሰር ይገባኛል አላቸው።»*** በሉቃስ ወንጌል 6፡16 ***«ታላቅ ነብይ በመካከላችን ተነስቷል፤ እግዚአብሔር ሕዝቡን ሊያድን መጥቷል እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።»*** ስለዚህ መመስገን ያለበት የላከው ነው። ከዚያም ሰዎች ኢየሱስን ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው በማለት ጠየቁት መልሱንም በሚቀጥለው ምዕራፍ እናገኛል። በሉቃስ ወንጌል 9፡46-48 ***«ደቀመዛሙርቱ ከሁላችን የሚበልጥ ማን ነው? ብለው ክርክር አንስተው ነበር። ኢየሱስ አንድ ሕፃን አመጣና ከአጠገቡ አቆመው፤ እንዲህም አላቸው፡-«ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል የላከኝንም ይቀበላል።»*** ከዚህ ላይ ጥያቄ ክርስቲያኖች ሕፃናት ሲወለዱ ከነወንጀላቸው (ከነኃጢአታቸው) ነው ትላላችሁ። ኢየሱስ ግን ከሁሉ የሚበልጡ መሆናቸውን ተናግሯል። እንዲያው የውርስ ኃጢአት አለ የሚለው ከዚህ ዘንድ ለአዕምሮ አይጎረብጥምን? በሉቃስ ወንጌል 10፡16 ***«እንደገናም ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቶቹ እንዲህ አለ፡- እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናንተን የማይሰማ የማይቀበል እኔን አይቀበልም፤ እኔን የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም።»*** አሁን እውነቱ ግልጽና ግልጽ ነው። ስለ

ኢየሱስ ማንነት አራቱ ወንጌሎች ማለትም ማቴዎስ፣ ማርቆስ፣ ዮሐንስና ሉቃስ ስለ ኢየሱስ ማንነት የነበራቸውን እምነት አስረድተዋል። ጳውሎስ በኢየሱስ ላይ ምን አቋም ነበረው ወደሚለው ስናመራ ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው መልእክት 4፡4‹‹***የዘመኑ ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግ በታች የተወለደውን ልጁን ላከ።›› በማለት በኢየሱስ ላይ የነበረውን አቋም ተናግሯል።

## ትኩረት አድርጉ!!!

ወደ ሌላ ርዕስ ከመግባቴ በፊት ለማስታወስና ሐሳቡን ለማጠናከር ያክል ስለ ኢየሱስ ነብይነት ከአራቱ ወንጌሎች አንዳንድ ምዕራፍና ቁጥር በመጥቀስ በኢየሱስ ነብይነት ላይ እምነት ግልጽ እንዲሆን እፈልጋለሁ። በማቴዎስ ወንጌል 15፡24‹‹***ኢየሱስም አለ፡- እኔ የተላኩት ለእራኤል ቤት ለጠፉ በጎች ብቻ ነው።***›› ከዚህ ላይ ‹**ብቻ**› የሚለው ለአለም እንዳልተላከ ያሳያል። በመቀጠል ከዚሁ ምዕራፍ 21፡10-11‹‹***ኢየሱስም ወደ እየሩሳሌም በገባ ጊዜ የከተማው ሕዝቦች ይህ ማነው? በማለት ታወኩ። ሕዝቡም ይህ ከገሊላ ከምትገኝ ክፍለ ሀገር ከናዝሬት ከተማ የመጣው ነብዩ ኢየሱስ ነው አሉ።***›› በአባባል እንኳ ‹**ማየት ማመን ነው**› ይባል የለ!!! ስለዚህ ኢየሱስን በአካል ያዩት ሰዎች የዓይን ምስክሮች ነብይ ነው አሉ እንጂ ከነብይነት አውጥተው ወደ አምላክ ደረጃ አላሸጋገሩትም። በማርቆስ ወንጌል 9፡37‹‹***እንደነዚህ ካሉት ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔንም የሚቀበል ሁሉ እኔን ብቻ ሳይሆን የላከኝንም ይቀበላል።***›› በማርቆስ ወንጌል 6፡4‹‹***ኢየሱስ በናዝሬት ብዙ ተቃውሞ ደረሰበት፤ ኢየሱስም ነብይ በገዛ ሀገሩና በዘመዶቹ ይናቃል፤ በሌሎች ግን ይከበራል አላቸው።***›› ኢየሱስ ስለ ራሱ ‹***ነብይ***› በማለት ማንነቱን ገልጿል። እንዲሁም በነብይነቱ የሚያከብረውንና የሚንቀውንም ጨምሮ ገልጿል። አልሐምዱሊላህ እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን እናከብረዋለን። በዮሐንስ ወንጌል 5፡23-24‹‹***እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።***›› ከዚሁ ምዕራፍ 17፡3 ‹‹***ብቻህን እውነተኛ አምላክ የሆንከውና የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይቸ የዘላለም ሕይወት ናት።***›› ከዚህ ላይ ብቸኛው የመዳኛ መንገድ ተገልጿል። በሉቃስ ወንጌል 9፡46-48‹‹***ኢየሱስ እንዲህ አላቸው ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።***›› በሉቃስ ወንጌል 10፡16‹‹***እንደገናም ኢየሱስ ደቀመዛሙርቱን እናንተን የሚሰማ እኔን ይሰማል፤ እናንተን የማይቀበል እኔን***

***አይቀበልም፤ እኔን የማይቀበል የላከኝን አይቀበልም አላቸው።»*** የኢየሱስ መቀበል የሚረጋገጠው በአላህ ስታምኑ ነው። በአላህ ካላመናችሁ በኢየሱስም አታምኑም ማለት ነው። በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41«***ኢየሱስ ለሐዋሪያቶቹ እንዲህ አላቸው፡- እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል። ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ያገኛል። ፃድቅን በፅድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ያገኛል።»*** ታዲያ ይህ ንግግር ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል? ነብይን በነብይ ስም የሚቀበሉ ሙስሊሞች በመሆናቸን የነብይን ዋጋ እናገኛለን። እንዲሁም ኢየሱስን ፃድቅ ነው ብለን ስለምናምን የፃዲቅን ዋጋ እናገኛለን። ክርስቲያኖች ግን በነብይነቱም ሆነ በፃድቅነቱ ስለማያምኑ በጥቅሱ መሰረት የነብይን ዋጋ ሆነ የፃድቅን ዋጋ አያገኙም።

## ድምዳሜ ኢየሱስ ነብይ ነበር።

ነብይ ማለት በዕብራይስጥም ተናጋሪ ወይም ነጋሪ ማለት ነው። ለአንድ ነብይ ነብይ የሚያሰኘው የሚመጣለትን ‹**ነበእ**› ማለትም ወሬ ነው። ይህንን አንድ ናሙና ከመጽሐፍ ቅዱስ ማየት እንችላለን። በኦሪት.ዘጸአት 7፡1«***እግዚአብሔር ሙሴን አለው፡- እይ፤ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለው፤ ወንድምህም አሮን ነብይ ይሆንሃል።»*** ነቢአከ ማለት ነብይክ ወይም የአንተ ነብይ ማለት ነው። አሮን ለሙሴ ነብይ ነበር ማለት የሙሴን ንግግር ይናገርለታል ማለት ነው። ነብይ ማለት የሌላ ማንነት ንግግርን ተቀብሎ የሚያስተላልፍ አፈ ቀላጤ ወይም ቃል አቀባይ ማለት ነው። በዚህ ስሌት መሰረት ከአምላክ ወሬ የሚመጣላቸው የአምላክ ነብይ ይባላሉ። አምላክ ደግሞ ያንን ነብይ በተለያየ መንገድ ያናግረዋል። በሕልም በመግለጥ ማናገር፡- በኦሪት.ዘኍልቁ 12፡6«***እርሱም። ቃሌን ስሙ፤ በመካከላችሁ ነብይ ቢኖር፤ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፤ ወይንም በሕልም አናግረዋለሁ።»*** በራእይ በመገለጥ፡- በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 9፡9«***ዛሬ ነብይ የሚባለው ቀድሞ ባለ ራእይ ይባል ነበርና አስቀድሞ በእስራኤል ዘንድ ሰው እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ሲሄድ፡- ኑ፤ ወደ ባለ ራእይ እንሂድ ይባል ነበር።»*** በመጽሐፈ ኢዮብ 33፡14-15«***እግዚአብሔር በአንድ መንገድ በሌላም ይናገራል፤ ሰው ግን አያስታውልም። በሕልም በሌሊት ራእይ አፍላ እንቅልፍ በሰዎች ላይ ሲወድቅ፤ በአልጋ ላይ ተኝተው ሳሉ፤----»*** ቃሉን በአፉ በማድረግ፡- አምላክ ነብይን ሲያስነሳ ቃሉን በነብዩ አፍ አድርጎ “በል” ሲለው ያ ነብይ የተባለውን

መልእክት ብቻ ያስተላልፋል። በኦሪት.ዘኊልቊ 23፥16«*እግዚአብሔር በለዓምን ተገናኘ፤ ቃሉንም በአፉ አድርጎ ወደ ባላቅ ተመለስ፤ እንዲህም በል አለው።*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 51፥16«*ሰማያትን እዘረጋ ዘንድ፤ ምድርንም እመሰረት ዘንድ፤ ጽዮንንም፦ አንቺ ሕዝቤ ነሽ እል ዘንድ፤ ቃሌን በአፍህ አድርጌአለሁ፤ በእጄም ጥላ ጋርጀሃለሁ።*» በትንቢተ.ኤርሚያስ 1፥9«*እግዚአብሔርም እጁን አፌን ዳሰሰ፤ እግዚአብሔርም፦ እነሆ ቃሌን በአፍህ ውስጥ አኑሬአለሁ።*» ይህን ሐሳብ ይዘን ወደ ኢየሱስ ስንመጣ ኢየሱስም አምላክ ነብይ ነው ብለው ክርስቲያኖች ይህን ጥቅስ ይጠቅሳሉ። በኦሪት.ዘዳግም 18፥18«*ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሣላቸዋለሁ፤ ቃሌንም በአፉ አደርጋለሁ፤ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራቸዋል።*» እኛ ነጥባችን ይህን ጥቅስ ለማን ነው የሚናገረው? ሳይሆን ይህ ጥቅስ ለኢየሱስ ነው ካላችሁ ኢየሱስን ነብይ አድርጎ ያስነሳው አምላክ ቃሉን በአፉ አድርጎ “በል” እያለው ያናገረው እንደ ነበር ፍንትው ያለ መረጃ ነው። ኢየሱስ ከላከው ከአምላክ እየሰማ ሲናገር የነበረ ሰው ብቻ ነው። ከእራሱ ምንም ነገር አልተናገረም፤ ነገር ግን የሚናገረውን ትዕዛዝ ሰጠው። በዮሐንስ ወንጌል 8፥40 «*ነገር ግን አሁን ከአምላክ የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብራሃም እንዲህ አላደረገም።*» ከዚሁ ምዕራፍ 8፥26 «*የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው።*» አሁንም ከዚሁ ምዕረፍ 12፥49«*እኔ ከራሴ አልተናገርኩምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ።*» አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 14፥24«*የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።*» ኢየሱስ ከራሱ ምንም ማድረግ የማይችል ሰው ነው። ከላከው እየሰማ ይናገራል፤ ይህንን በል እያለ የሚያናግረው እራሱ ሳይሆን ከላከው የመጣ የአምላክን ቃል ነው። በዮሐንስ ወንጌል 5፥30-32«*እኔ ከእራሴ አንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ፤ ፍርዴም ቅን ነው፤ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና። እኔ ስለእራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም፤ ስለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው፤ እርሱም ስለ እኔ የሚመሰክረው ምስክር እውነት እንደ ሆነ አውቃለሁ።*» ከዚሁ ምዕራፍ 7፥16 «*ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው፦ ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤ ፈቃዴን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፤ እርሱ ይህ ትምህርት ከአምላክ ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ለይቶ ያውቃል።*» ኢየሱስ የማን ነብይ ነው? መልሱ የአንድ አምላክ ነብይ ይሆናል። ኢየሱስ ነብይ ከሆነ ፊሽካው ተነፋ፤ ከዚያ በኋላ አምላክ ነው አሊያም

የአንዱ አምላክ ሁለተኛው አባል ነው ማለት ተውኔትና ቁማር ነው የሚሆነው። ነብያት በአንዱ አምላክና ሕዝቦች መካከል ሆነው እግዚአብሔር እንዲህ ይላል በማለት ያስተላልፉ ነበር። በመጽሐፈ መሣፍንት 6፡8 ‹‹***እግዚአብሔር ወደ እስራኤል ልጆች <u>ነብይ ላከ</u>፤ እርሱም አለ፦ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ ከግብፅ ምድር አወጣኋችሁ፤ ከባርነት ቤት አስለቀቅኋችሁ።***›› በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ 21፡13‹‹***<u>እነሆም፦ነብይ ወደ እስራኤል</u> ንጉሥ ወደ አከዓብ ቀርቦ፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ይህን ብዙ ጭፍራ ሁሉ ታያለህን? እነሆ፦ ዛሬ በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደ ሆንሁ ታውቃለህ አለ።***›› በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 20፡1‹‹***በዚያም ወራት ሕዝቂያስ እስከ ሞት ድረስ ታመመ። <u>ነብዩም የአሞጽ</u> ልጅ ኢሳይያስ ወደ እርሱ መጥቶ፦ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል አለው።***›› በተመሳሳይ መልኩ ነብዩ ኢየሱስ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል ብሎ ከአንዱ አምላክ የሰማውን አስተምሯል።

## <u>ኢየሱስ የተላከው ለእስራኤል እንጂ ለዓለም አይደለም።</u>

የኢየሱስ ነብይነት ለእስራኤል ሕዝቦች ብቻ ነው። ማለትም ለዓለም አልተላከም። ለዚህ ንግግሬ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24 ያለው ጥቅስ እውነታውን ያረጋግጣል። 15፡24‹‹***<u>ኢየሱስም አለ፦ እኔ የተላኩት ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች ብቻ ነው።</u>***›› ከዚሁ ምዕራፍ 10፡5-7‹‹***<u>ኢየሱስ እነዚህን አሥራ ሁለቱን ሐዋሪያት ላካቸው እንዲህም ብሎ አዘዛቸው፦ ወደ አረማውያን አትሂዱ፤ ወደ ሰምዲያውያንም ከተማ አትግቡ፤ ነገር ግን እንደ በጎች ወደ ጠፉት ወደ እስራኤል ሕዝቦች ሂዱ። ሄዳችሁም መንግስተ ሰማያት ቀርባለች እያላችሁ ስበኩ።</u>***›› እዚህ ላይም ኢየሱስ ራሱ ለእስራኤል ሕዝብ ብቻ እንደተላከ ሁሉ ሐዋሪያቶችንም ወደ እስራኤል ብቻ እንዲሄዱ ማዘዙን እንረዳለን። በማርቆስ ወንጌል 1፡38‹‹***<u>ኢየሱስም እኔ የመጣሁት ለማስተማር ስለሆነ እንዳስተምር በቅርብ ወዳሉት መንደሮች እንሂድ አላቸው።</u>***›

# ምዕራፍ አራት

# ኢየሱስ እምነት ምን ነበር? ምንስ አስተማረ ክርስትናን ወይንስ እስልምናን?

በሁሉም የክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ኢየሱስ ክርስትናን አስተምሯል፤ ሰብኳል የሚል እምነት አላቸው። ነገር ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሮ ከሄድን ኢየሱስ ሙስሊም ነበር። ያስተማረውም ኢስላምን ነው። ይህን ስል በማስረጃ ነው፤ ጉዳዩ ለእናንተ ክርስቲያኖች ከማስገረም አልፎ የሙብረቅ ነጎድጓድ ያክል እንደሚያያስደነግጥ አልጠራጠርም። ከአራቱም ወንጌሎች የምስክርነት ማስረጃ እናገኛለን። የእያንዳንዳቸውን ወንጌሎች ገጽና ቁጥር እንዲሁም የአሳታሚውን ድርጅት፤ ዓመተ ምህረቱን ጨምሬ እገልፃለሁ።

## በማቴዎስ ወንጌል

በማቴዎስ ወንጌል 4፡23 «*ኢየሱስ የአይሁድ ጸሎት ቤቶች በሆኑት <u>መስጊዶች</u> እያስተማረና የእግዚአብርሔን መንግስት የምስራች ቃል እያበሰረ በገሊላ ሁሉ ይዘዋወር ነበር።*» በማቴዎስ ወንጌል 6፡2 «*ስለዚህ አንተ ለድኃ በምትሰጥበት ጊዜ ግብዞች ድኃ ሰዎች ምስጋና ለማግኘት ብለው <u>በየመስጊዱና</u> በየመንገዱ እንደሚያደርጉት ለታይታ አታድርግ።*» በማቴዎስ ወንጌል 6፡5«*በምትጸልዩበት ጊዜ እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ እነርሱ ሰው እንዲያይላቸው ብለውና <u>በየመስጊዱና</u> በየመንገዱ ዳር ቆመው መጸለይ ይወዳሉ።*» በማቴዎስ ወንጌል 9፡23 «*ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ወደ <u>መስጊድ</u> አለቃው ቤት በደረሰ ጊዜ የሐዘን እንቢልታ ነፊዎችና እየተራወጡ በመጮኽ የሚያለቅሱትን ሰዎች አየ።*» በማቴዎስ ወንጌል 9፡35 «*እንዲሁም ኢየሱስ <u>በመስጊዶች</u> እያስተማረ የእግዚአብሔርን መንግስት መልካም ዜና እያበሰረ ሕዝቡን ከበሽታና ከደዌ ሁሉ እየፈወሰ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዘዋወር ነበር።*» በማቴዎስ ወንጌል 10፡17«*<u>በየመስጊዳቸውም</u> ይገርፏችዋል፤ ስለዚህ ተጠንቀቁ።*» በማቴዎስ ወንጌል 12፡9 «*ኢየሱስ ከዚያ ስፍራ ተነስቶ ወደ <u>መስጊዳቸው</u> ገባ።*» በማቴዎስ ወንጌል 13፡54 «*ኢየሱስ ወደ ገዛ ሀገሩ ወደ ናዝሬት ከተማም መጣ ከዚያም <u>በየመስጊዳቸውም</u> ያስተምር ነበር።*» በማቴዎስ ወንጌል 23፡6«*በግብዣ ላይ የከበሬታ ቦታን፤ <u>በመስጊድም</u> የመጀመሪያን ስፍራን*

***መያዝ ይወዳሉ።»*** በማቴዎስ ወንጌል 23፡34 ***«አንዳንዶቹንም <u>በመስጊዳቸው</u> ትገርፋላችሁ።»***[1]


የማቴዎስ፡ ወንጌል። ፲፫፡ ፲፱፡

1 ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ ከተተረጎመው። አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 6-30

# በማርቆስ ወንጌል

በማርቆስ ወንጌል 1፡21 ***‹‹ኢየሱስ የአይሁድ የጸሎት ቤት ወደሆነም ወደ <u>መስጊድ</u> ገብቶ ማስተማር ጀመረ።››*** በማርቆስ ወንጌል 1፡23***‹‹<u>በመስጊዳቸውም</u> በርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበር።››*** በማርቆስ ወንጌል 1፡29***‹‹በዚያን ጊዜ ኢየሱስ <u>ከመስጊድ</u> ወጥቶ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ስምዖንና እንድሪያስ ቤት ገባ።››*** በማርቆስ ወንጌል 1፡38-39 ***‹‹ኢየሱስም፡- እኔ የመጣሁት ለማስተማር ስለሆነ እንዳስተምር በቅርብ ወዳሉት መንደሮች እንሂድ አላቸው። ስለዚህ <u>በመስጊዶቻቸውም</u> እያስተማረና አጋንንትን እያስወጣ በገሊላ ሁሉ ይዘዋወር ነበር።››*** በማርቆስ ወንጌል 3፡14***‹‹ኢየሱስ ወደ <u>መስጊድ</u> እንደገና ገባ፤ እዚያውም አንድ እጁ ሽባ ሰው ነበር።»*** በማርቆስ ወንጌል 5፡22***‹‹እነሆ <u>ከመስጊድም</u> አለቆች አንድ ሰው መጣ ኢያኢሮስ የሚሉት።»*** በማርቆስ ወንጌል 5፡35***‹‹ኢየሱስ ገና ይህን በመናገር ላይ ሳለ <u>ከመስጊድ</u> አለቃው ቤት የመጡ ሰዎች <u>የመስጊዱን</u> አለቃውን ልጅህ ሞታለች፤ እንግዲህ ስለምን መምህሩን ታደክመዋለህ? አሉት።››*** በማርቆስ ወንጌል 5፡36***‹‹ኢየሱስ ግን የተባለውን ሰምቶ <u>የመስጊዱን</u> አለቃ ‹‹እመን እንጂ አትፍራ›› አለው።››*** በማርቆስ ወንጌል 5፡38***‹‹ወደ <u>መስጊድ</u> አለቃው ቤት በደረሱ ጊዜ ኢየሱስ ሰዎች ሲንጫጩና ሲያለቅሱ ሲጮኹ ተመለከተ።››*** በማርቆስ ወንጌል 6፡1-2***‹‹ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ------<u>በመስጊድ</u> ማስተማር ጀመረ።››*** በማርቆስ ወንጌል 8፡22***‹‹<u>ወደ ቤተ ሳይዳም</u> ---።››*** በማርቆስ ወንጌል 13፡9***‹‹እናንተ ራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ምክንያቱም ሰዎች ለፍርድ አሳልፈው ይሰጧችኋል <u>በየመስጊዱም</u> ይገርፏችኋል---።››***[2]

[2] ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ ከተተረጎመው። አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 38-53

## በሉቃስ ወንጌል

በሉቃስ ወንጌል 4፡15*‹‹ኢየሱስ በመስጊዶቻቸውም ያስተምር ነበር።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡16 *‹‹ከዚያ በኋላ ኢየሱስ ወደ አደገበት አገር ወደ ናዝሬት ሄደ፤ እንደልማዱም ወደ መስጊድ ገባ፤ ሊያነብም ተነሳ።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡20 *‹‹ኢየሱስ መጽሐፉን አጥፎ ለአስተናባሪው ሰጠውና ተቀመጠ በመስጊድ የነበሩትንም ሁሉ ትኩር ብለው ወደ እርሱ ይመለከቱ ጀመር።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡28 *‹‹በመስጊድ የነበሩትም ሁሉ ይህን በሰሙ ጊዜ እጅግ ተቆጡ።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡33 *‹‹ከዚያም በመስጊድ ርኩስ መንፈስ ያደረበት ሰው ነበር።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡38 *‹‹ኢየሱስ ከመስጊድ ተነስቶ ወደ ስምዖን ቤት ሄደ።››* በሉቃስ ወንጌል 4፡44 *‹‹ኢየሱስ በይሁዳም መስጊዶች ሁሉ እየተዘዋወረ ያስተምር ነበር።››* በሉቃስ ወንጌል 6፡6 *‹‹በሌላም ቀን ኢየሱስ ወደ መስጊድ ገብቶ ያስተምር ነበር።››* በሉቃስ ወንጌል 8፡41*‹‹በዚያን ጊዜ አንድ የመስጊድ አለቃ የሆነ ኢያኢሮስ የተባለ ሰው መጣ።››* በሉቃስ ወንጌል 11፡43*‹‹እናንተ ፈረሳዊያን ወዮላችሁ! ምክንያቱም በመስጊድ ውስጥ በክብር ወንበር ላይ መቀመጥ ትወዳላችሁ።››* በሉቃስ ወንጌል 12፡11 *‹‹ሰዎች በየመስጊዱ ሲወስዷችሁ ---።››* በሉቃስ ወንጌል 13፡10*‹‹ኢየሱስ በሰንበት ቀን በመስጊድ ያስተምር ነበር።››* በሉቃስ ወንጌል 13፡14*‹‹ኢየሱስ በሰንበት ቀን ስለፈወሰ የመስጊዱ አለቃ---።››* በሉቃስ ወንጌል 20፡46*‹‹--- በየ መስጊዱ----።››* በሉቃስ ወንጌል 21፡12*‹‹ነገር ግን ይህ ሁሉ ከመሆኑ በፊት እናንተን ይይዟችኋል፤ ያሳድዷችኋል፤ ወደ መስጊዱና ወደ ወህኒ ቤትም አሳልፈው ይሰጧችኋል።››*[3]

## በዮሐንስ ወንጌል

በዮሐንስ ወንጌል 6፡59*‹‹ኢየሱስ ይህን የተናገረው በቅርናሆም በመስጊድ።››* በዮሐንስ ወንጌል 9፡22*‹‹--ኢየሱስ ‹‹መሲህ›› ነው የሚል ሰው ቢኖር ከመስጊድ ሲያስወጡት አይሁዳውያን ባለስልጣናት ተስማምተው ስለ ነበር ነው።››* በዮሐንስ ወንጌል 12፡42*‹‹ሆኖም ከአይሁዳውያን አለቆች እንኳ ብዙዎች በኢየሱስ አምነዋል። ነገር ግን ከመስጊድ እንዲያስወጧቸው ፈረሳዊያን በመፍራት በግልጽ*

[3] ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ ከተተረጎመው። አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 68-87

*አልመሰከሩለትም።»* በዮሐንስ ወንጌል 16፡3-4*«ቀጥሎም ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- እንሆ ይህን ሁሉ የነገርኳችሁ እምነታችሁ እንዲናወጥ ነው፤ ከመስጊዶች አስወጥተው ያባሯችኋል። እንዲያውም እናንተን የሚገድሏችሁ ሁሉ፤ እግዚአብሔርን የሚያገለግል የሚመስልበት ጊዜ ይመጣል። ይህንንም የሚያደርጉት አብንም ሆነ እኔን ስላላወቁ ነው። ይህንን ለእናንተ መናገሬ ግን ጊዜው ሲደርስ ምን እንዳሏችሁ እንድታስታውሱ ነው።»* በዮሐንስ ወንጌል 18፡20 *«ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት፡- እኔ ለሰው ሁሉ በግልጽ ተናገርኩ አይሁዳውያን ሁሉ በሚሰበሰቡበት ዕለት ዕለት በመስጊድም ሆነ በቤተ መቅደስ ሁልጊዜም አስተማርኩ በስውር የተናገርኩት ምንም ነገር የለም።»*[4]

## በሐዋርያት ሥራ

በሐዋርያት ሥራ 1፡14*«እነዚህ ሁሉ ዘወትር ለጸሎት በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ ከእነርሱም ጋር ሴቶች ኢየሱስ ማርያም እንዲሁም የኢየሱስ ወንድሞች ነበሩ።»* በሐዋርያት ሥራ 9፡20*«"ወዲያውም ሳውል በደማስቆ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው" እያለ በየመስጊዱ ማስተማር ጀመረ።»* በሐዋርያት ሥራ 13፡5*«ወደ ሰልማናም በደረሱ ጊዜ በአይሁዳውያን መስጊዶች የእግዚአብሔርን ቃል አስተማሩ።»* በሐዋርያት ሥራ 13፡14-15*«በሌላ ቀን ወደ አንድ መስጊድ ገብተው ተቀመጡ፤ የሙሴና የነብያትን መጽሐፍት ካነበቡ በኋላ የመስጊዱ አለቆች ወንድሞች ሆይ! ሕዝቡን የሚያጽናና የምስክር ቃል (ዳዓዋ) ካላችሁ ተናገሩ አሉ።»* በሐዋርያት ሥራ 15፡20-21*«ይልቅስ ለጣዖት በመሰዋዕት ምክንያት የረከሰ ምግብ አትብሉ፤ ከዝሙት ራቁ፤ ሳይታረድና ደሙ ሳይፈስ ታንቆ የሞተ እንስሳ አትብሉ፤ ደሙንም አትብሉ፤ ብለን እንፃፍላቸው፤ ምክንያቱም ከጥንት ጀምሮ የሙሴ ሕግ በየሰንበቱ በየመስጊዶቹ ይነበብ ነበር፤ ቃሉም በየከተማው ይሰበካል።»* በሐዋርያት ሥራ 17፡17*«ስለዚህ በመስጊድ ከአይሁዳውያንና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩት ሰዎች ጋር ይከራከሩ ነበር።»* በሐዋርያት ሥራ 18፡7-8*«ስለዚህም ከእነርሱ ተለይቶ ቲቶስ ኢዮስጦስ ወደ ተባለው ሰው ቤት ሄደ፤ ይህ ሰው እግዚአብሔርን የሚያመልክ ሰው ነበር፤ ቤቱም በመስጊድ አጠገብ*

---

[4] ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተጻፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ ከተተረጎመው፡፡ አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 102-117

***ነበር። ቀርጶስ የሚባል <u>የመስጊድ</u> አለቃ፤ ከቤተሰቡ ጋር አመነ።*›› በሐዋርያት ሥራ 22፡19‹‹ ***<u>በየመስጊዱ</u>***---›› ጳውሎስ ኢየሱስንና በኢየሱስ ነብይነት ያመኑትን ሙስሊሞችን እንዲህ ያስቃያቸው እንደ ነበር በሚከተለው የመጨረሻው የዚህ ምዕራፍ መጠቃለያ የእርሱን ንግግር እናገኘዋለን። በሐዋርያት ሥራ 26፡9-11‹‹***<u>እኔ (ጳውሎስ) ራሴ የናዝሬቱን ኢየሱስንስም የተቻለኝን ያህል መቃወም አለብኝ ብየ አስብ ነበር። በኢየሩሳሌም ያደረኩትም ይህንኑ ነበር፤ ከካህናት አለቆች በተቀበልኩት ሰልጣን ከአማኞች ብዙዎችን ወደ ወህኒ ቤት እንዲገቡ አደርጌአለሁ፤ ሲገድሏቸውም ከገዳዮች ጋር ተስማምቻለሁ። ብዙ ጊዜ በየመስጊዱ እንዲቀጡና ከእምነታቸውን እንዲክዱ አደርጌአለሁ፤ በእነርሱ ላይም በጣም ተቆጥቼም ወደ ሌሎች ከተሞች እንኳ ወጥቼ እየሄድኩ አሳድዳቸው ነበር</u>*።››[5]

---

[5] ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ የተተረጎመው፡፡ አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 121-152



## ማጠቃለያ ለግንዛቤ ያክል!!

እስካሁን ያየናቸው አራቱም ወንጌሎች ኢየሱስ ሙስሊም እንደ ነበርና እስልምናንም በአብያተ ክርስቲያን ሳይሆን በመስጊድ እንዳስተማረ ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተቀምጧል። እውነቱ ተቀብሮና ተዳፍኖ ቢኖርም ነገር ግን እውነት ምንጊዜም ቢቀብሯት አትበሰብስም። አሁንም በድጋሜ ከእያንዳንዳቸው አንዳንድ

ምሳሌዎችን በመጥቀስ ሀሳቤን አጠናክረዋለሁ። በማቴዎስ ወንጌል 4፡23«***ኢየሱስ የአይሁድ ጸሎት ቤቶች በሆኑት <u>መስጊዶች</u> እያስተማረና የእግዚአብሔርን መንግስት የምስራች ቃል እያበሰረ በገሊላ ሁሉ ይዘዋወር ነበር።***» በማቴዎስ ወንጌል 12፡9«***ኢየሱስ ከዚያ ስፍራ ተነስቶ ወደ <u>መስጊዶቻቸው</u> ገባ።***» ከዚሁ ምዕራፍ 13፡54« ---- ***ከዚያ <u>በየመስጊዶቻቸው</u> ያስተምር ነበር።***» በማርቆስ ወንጌል 1፡21«***ኢየሱስ የአይሁድ ጸሎት ቤት ወደ ሆነውም ወደ <u>መስጊድ</u> ገብቶ ማስተማር ጀመረ።***» ከዚሁ ምዕራፍ በማርቆስ ወንጌል 6፡1-2«***ኢየሱስ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ፤ <u>በመስጊድ</u> ማስተማር ጀመረ።***» ከዚህ ላይ የዮሐንስ ወንጌል ላስቀድምና የሉቃስ ወንጌልን የንግግር መጨረሻ ላድርገው። በሉቃስ ወንጌል ላይ ትንሽ ትንታኔ መስጠት ስለፈለኩ ነው። በዮሐንስ ወንጌል 18፡20 «***ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰለት እኔ ለሰው ሁሉ <u>በግልጽ ተናገርኩ</u> አይሁዳውያን ሁሉ በሚሰበሰቡበት <u>በመስጊድም</u> ሆነ በቤተ-መቅደስ ሁልጊዜም <u>አስተማርኩ፤ በስውር የተናገርኩት ምንም ነገር የለም</u>።***» በሉቃስ ወንጌል 4፡15 «*ኢየሱስ* ***<u>በመስጊዶቻቸውም</u> ያስተምር ነበር።***» በሉቃስ ወንጌል 4፡44«***ኢየሱስ በይሁዳም <u>መስጊዶች</u> ሁሉ እየተዘዋወረ <u>ያስተምር</u> ነበር።***» ከዚሁ ምዕራፍ 6፡6 «***በሌላም ቀን ኢየሱስ ወደ <u>መስጊድ</u> ገብቶ <u>ያስተምር</u> ነበር።***» እስኪ ከላይ ጀምሮ ያየቸው ምዕራፍና ቁጥሮች ምንን ያስረዳሉ? መቼም ይህን እውነታ መደበቅና ማስተባበል አይቻልም። ቃል በቃል ከመተርጎም ቀጥታ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ነው ያስቀመጥኩት። ስለዚህ ኢየሱስ እምነቱ ሙስሊም እንደ ነበርና እስልምናን በመስጊድ እንደ አስተማረ አይተናል። አሁንም ደግሞ በመስጊድ እንደ ሰበከ (ኹጥባ) ንግግር እንደ አደረገ በቀጣዩ ምዕራፍ እናያለን።

## <u>ኢየሱስ ንግግር (ኹጥባ) ያደርግ ነበር</u>።

በመስጊድ ውስጥ ከሚነገሩ ከሚሰበኩ ትምህርቶች አንዱ በጁምዓ ቀን የሚደረገው ነው።ኢየሱስም እንደ ሙስሊምነቱ ይህን ስብከት እንደ አደረገና እንደ አስተማረ እውነታው በግልፅ አጉልቶ ያሳየናል። በ1879 የመጽሐፍ ቅዱስ ዕትም ላይ በሉቃስ ወንጌል 4፡16 እንዲህ ይላል፡- «***<u>ከዚያም በኋላ ኢየሱስ ወደ አደገበት አገር ወደ ናዝሬት ሄደ እንደልማዱም ከዚያ ወደ መስጊድ ገባ፤ ሊያነብም ተነሳ</u>።***» ከዚህ ላይ «**ሊያነብም**» የሚለው ሊኾጥብ ማለቱ ነው። ያ ማለት ጁምዓ ጁምዓ የሚደረገውን የሙስሊሞች ስብከት ማለት ነው። በዚህ ቀን ደግሞ ሰዎች

የሚባለውን ነገር በጥሞና ሰዎች መከታተላቸውን በቀጣዩ ምዕራፍ ይነግረናል። በሉቃስ ወንጌል 4፡20 «***ኢየሱስ መጽሐፉን አጥፎ ላስተናባሪው ሰጠውና ተቀመጠ በመስጊዱ የነበሩትም ሁሉ ትኩር ብለው ወደ እርሱ ይመለከቱ ጀመር።***» ይህ እምነት ሙስሊሞች በተግባር የሚያሳዩት ስለሆነ ምስክርነቱ የጎላ ነው። ታዲያ በዚህ መሰረት ኢየሱስ ሙስሊም ነው ስንል አይደለም ክርስቲያን ነው ክርስትናንም ነው ያስተማረው የሚል ጥያቄ መፈጠሩ አይቀሬ ነው። በጭራሽ አይገመትምም፤ አይታሰብምም። ምክንያቱም ኢየሱስ ሙስሊም ነበር እስልምናን አስተምሯል። ያስተማረውም በመስጊድ ውስጥ ነበር። ክርስትናን እንዳላስተማረና ክርስትያን ሁኑ እንዳላለና እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያን እንዳላስተማረም ሁሉም ክርስቲያን ሊያውቀውና ሊረዳው የሚገባ እውነታ ነው።[6]

[6] ምንጭ፡- ለመጀመሪያ በቁም ጹሑፍ በተፃፈው መጽሐፍ ቅዱስ ከ1886 እንግሊዘኛው ዕትም ወደ አማርኛ የተተረጎመው፡፡ አሳታሚ፡- የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር ዕ፤ የ1879 ዕትም ገጽ፡- 68

# ምዕራፍ አምስት

# ኢየሱስን በትክክል ማን ይወደዋል? እኛ ሙስሊሞች ወይስ ክርስቲያኖች?

ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ሙስሊሞች የኢየሱስ ጠላት ናቸው ብለው ያስባሉ። ነገር ግን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ካየነው ለኢየሱስ ጠላት የሆኑት ሙስሊሞች ሳይሆን እራሳቸው ክርስቲያኖች ናቸው። ለምሳሌ በዮሐንስ ወንጌል 14፡15 «***ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ***» ብሏል። ስለዚህ ውዴታ የሚረጋገጠው የእሱን ትእዛዝ በመፈፀም ነው። ታዲያ ትእዛዙን የሚጠብቅ ማን ነው? ፍርዱንና መልሱን እንወደዋለን ለምትሉ ሰዎች ትቻለሁ። ነገር ግን ኢየሱስ የሚወደው ክርስቲያን ሳይሆን ሙስሊሞች መሆናቸውን በዚሁ ምዕራፍ ይነግረናል። 14፡24 «***የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙት ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም***» ይላል። አሁንም ጥያቄ እንጠይቅ ኢየሱስ የአላህ መልእክተኛ መሆኑን የሚያምን ማን ነው? ክርስቲያኖች ወይንስ ሙስሊሞች? እንዲሁም ቃሉን የሚሰማና የሚጠብቀውስ? ሙስሊሞች ኢየሱስ የአላህ መልእክተኛና ነብይ መሆኑን እናምናለን እንመሰክራለን። ክርስቲያኖች ግን አያምኑም ቃሉንም አይጠብቅም። የአንድ ሰው ውዴታ የሚረጋገጠው በተግባር ነው። ይህም ትልቁ መመዘኛ መስፈርት ነው። ለዚህም ነው ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 14፡21 «***ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ይወደኛል***» ያለው። አሁንስ ይህን ትእዛዝ የሚቀበሉና በስራ ላይ የሚያውሉ እነማን ናቸው? ክርስቲያኖች ወይንስ ሙስሊሞች? የክርስቲያኖች ውዴታ ምኑ ላይ ነው? ውዴታ ማለት በክርስቲያኖች በቃልና በንግግር ብቻ ነው። ነገር ግን በ1ኛ በዮሐንስ መልእክት 3፡18 «***ፍቅራችን እውነትና በሥራ ላይ የሚገለጽ ይሁን እንጂ ወይንም በንግግር ብቻ አይሁን***» ይላል። ተሰቀለ፣ ሞተ፣ በሰይጣን ተፈተነ ማለታችሁ ውዴታን ይገልፃል? ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ተሰቅሎ ሞቷል ይላሉ። ይህ አባባላቸው ደግሞ ለኢየሱስ ያላቸውን ውዴታ ሳይሆን የሚገልጸው ጠላትነታቸውን ነው። በኦሪት.ዘዳግም 21፡22 ላይ «***አንድ ሰው ለሞት የሚያበቃ ወንጀል ቢሰራ እንኳ በእንጨት ላይ እንዳትሰቅለው። በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ የተረገመ ነውና***» ይላል። ታዲያ በዚህ አባባል ኢየሱስ የተረገመ ነውን? ተረገመ ማለትስ ውዴታና ከበሬታን ይገልፃል? ደግሞስ

ምን ኃጢአት አለበት? ኃጢአተኛ ነው ብሎ መፈረጅስ አሁንም ለእሱ ያላችሁን ውዴታ ይገልፃል? እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስን ከኃጢአት ንፁህ ነው ወንጀል የለበትም ማለታችን ክፋት ነውን? ከዚሁ ምዕራፍ 13፡5«***ሌሎች አማልዕክትን እንዲያመልኩ ሕዝቦችን የሚያዝ፤ ሐሰተኛ ሐልም አላሚ ነብይ ይገደል***» ይላል። ታዲያ በእናንተ አባባል ኢየሱስ ሐሰተኛ ነብይ ነው ማለት ነው? ባይሆንማ ኖሮ ባልተገደለና ባልተሰቀለ ነበር። እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስ እውነተኛ ነብይ ነው ሐሰት አይናገርም ማለታችን ክፋት ነውን? በመጽሐፈ መዝሙር 32፡6«***ቅኖች ወደ እግዚአብሔር ይጸልያሉ፤ ይጮኻሉ፤ እርሱም ይሰማቻዋል፤ ከችግራቸውም ያድናቸዋል***» ይላል። በጥቅሱ መሰረት ኢየሱስ ቅን ስላልሆነ ነው ጸሎቱን ያልሰማውና ያልዳነው? ኢየሱስ ግን አምላክ እንደሚሰማው በዮሐንስ ወንጌል 11፡41-42«***አባት ሆይ! ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ***» በማለት ልመናው ተቀባይነት እንደሚያገኝና አምላክ እንደሚሰማው ተናግሯል። ታዲያ ኢየሱስ አምላኩ እንደ ሰማውና ለወደፊትም እንደሚሰማው ከተገለጸ ለምን ማመን አቃታችሁ? እሱ የተናገረው ውሸት ነው ማለት ነው? ሌላው ደግሞ በሰይጣን ተፈተነ ስትሉ። እንደ እናንተ አባባል፡- በማርቆስ ወንጌል 1፡13«***በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ሰነበተ።***» እኛ ሙስሊሞች <u>ኢየሱስም</u> ሆነ እናቱ <u>ማርያም</u> ከሰይጣን ተንኮል አምላክ ጠብቋቸዋል በማለትና ለእነሱ እና ለእናቱ የተለየ ጥበቃ አድርጎላቸዋል፤ ማለታችን ለእነርሱ ያለንን ከበሬታ ይገልፃል። ኢየሱስ እናቱን እንዳመናጨቃት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በዮሐንስ ወንጌል 2፡2«***ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?***» አስቡት ያውም እናትን በአሁኑ ሰዓት እንኳ ይህን ያክል እናቱን የሚያመናጭቅና በዚህ ቃል ተጠቅሞ ይጠራል የሚል ግምት የለኝም። አምላክ የረገመው ካልሆነ በስተቀር ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች ይህን የተከበረ የአላህ ነብይ ይህን ቃል ይናገረዋል ብለን አንደፍርም። በፍፁም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለፃ እኛ ነፃ ነን። ምክንያቱም ኢየሱስን ስለምነወደውና ስለ ምናከብረው ይህን ንግግር እርሱ ይናገረዋል ብለን እኛ ሙስሊሞች አንደፍርም። ቁርኣን ለኢየሱስ ጥብቅና ቆማል።

# ኢየሱስ የሙስሊሞች የእምነት ወንድም ነው።!!!

ኢየሱስ የሙስሊሞች የእምነት ወንድም ነው። ይህን እውነታ በማርቆስ ወንጌል 3፡31-32 ላይ እናገኘዋለን። እንዲህ ይላል፡- «***የኢየሱስ እናትና ወንድሞች ወደ እርሱ መጡ።*** ***በውጭ ቆመው ሰው ልከው አስጠሩት፤ በዚያም ተቀምጠው የነበሩ ሰዎች «እነሆ እናትህ ወንድሞችህና እህትህ በውጭ ቆመው ይፈልጉሃል» ብለው ነገሩት።*** ***እርሱም እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ ማን ናቸው? ሲል መለሰ። በዙሪያው ተቀምጠው ወደነበሩት ሰዎች እያመለከተ እንሆ እናቴና ወንድሞቼ እነዚህ ናቸው፡- «የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚፈፅም ሁሉ እርሱ ወንድሜም፣ እህቴም፣ እናቴም ነው» አለ።*** » ይህ ጥቅስ ማንን ብቻ ያመለክታል? በነብይነቱ አታምኑም የአምላኩንም ትእዛዝ አትፈፅሙም። አሁን ግልፅ የኢየሱስ ጠላቱና ወዳጁ ተለየ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ (ትእዛዝ) የሚፈፅሙ ሙስሊሞች ብቻ ናቸው። ለዚህም ነው ኢየሱስ «***ወንድሜም እህቴም እናቴም ናቸው***» ያለው። ይህን እውነታ ደግሞ ቁርኣን በሱረቱል አል-ሑጁራት ቁጥር 10«***አማኞች ወንድማማቾች ናቸው***» ሲል ያብራረዋል። ስለዚህ ኢየሱስ የሙስሊሞች የእምነት ወንድም ነው፤ እምነቱም ኢስላም ነበር፤ ያስተማረውም እስልምናን ነው። ሁሉም ሙስሊሞች በተራራቁ ሀገራት ቢኖሩም የሚተዋወቁና የማይተዋወቁ ቢሆኑም የእምነት ወንድማማቾች ናቸው። ከሙስሊሞች የእምነት ወንድማማቾች መካከል ኢየሱስ አንዱ ነው። እኛ ሙስሊሞች የእምነት ወንድማችን ስለሆነ ኢየሱስን እንወደዋለን። በዮሐንስ መልእክት 4፡8«***ወንድሙን የማይወድ ከእግዚአብሔር አይደለም***» ይላል። እንዲሁም ከዚሁ ምዕራፍ 4፡20«***ማንም እግዚአብሔርን እወዳለሁ ያለ ወንድሙን ቢጠላ እርሱ ሐሰተኛ ነው።*** ***ያየውን ወንድሙን ያልወደደ ያላየውን እግዚአብሔርን መውደድ አይችልምና።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 5፡21«***እርሱ እግዚአብሔርን የሚወደድ ሁሉ ወንድሙን መውደድ ይገባዋል የሚለውን ትእዛዝ ሰጥቶናልና።***» ሙስሊሞች የኢየሱስ የእምነት ወንድሞች ነን፤ እንወደዋለንም። ምክንያቱም እንደ ክርስቲያኖች ነብይነቱን አልተቃወምንም እንዲሁም ለመስቀል አልሞከርንም። ለመስቀልን ለመግደል ያሰቡት የክርስቲያን የካህናት አለቆች ናቸው እንጂ ሙስሊሞችና የሙስሊም መሪዎች አይደሉም።

# ኢየሱስን ጌታ የሚሉ ሁሉ መንግስተ ሰማያት (ገነት) አይገቡም።

ኢየሱስ ከተከበሩት የአላህ መላእክተኞች አንዱ ነው እንጂ እሱ የዓለማት አምላክና ጌታ እንዲሁም ሁሉን ነገር የፈጠረ አይደለም። በመሆኑም በእርሱ በነብይነቱ መላክተኛነቱን የሚያምኑ እንጂ ጌታ ነው፤ አምላክ ነው፤ የሚሉት ሁሉ መንግስተ ሰማያት እንደማይገቡ እራሱ ኢየሱስ በአንክሮ ተናግሯል። በማስከተልም እሱን ጌታ በማለትና በማምለክ ሳይሆን ቃሉን በመስማትና የላከውን በማመን ገነት እንደሚገባ ተናግሯል። በዮሐንስ ወንጌል 5፡23-24 ‹‹***እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው***›› ብሏል። እዚህ ላይ የተገለጸው የላከውን በማመን እንጂ እሱን ጌታ በማለትና በማምለክ አይደለም። በመቀጠል በማቴዎስ ወንጌል 7፡21-23 ***‹‹በሰማያት ያለው የአባቴን (የአምላኬን) ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።››*** ኢየሱስ አምላክ ላለመሆኑ ይህ አንቀጽ ብቻ በቂ ነው። መንግስተ ሰማያት የሚገቡት በኢየሱስ አምላክነት ያመኑ ሳይሆን በኢየሱስና በሁላችንም አምላክ ያመነና የእርሱን ፈቃድ የሚያደረግ ብቻ መሆኑን በግለፅና በማያሻማ ቋንቋ ገልጿል። አንቀጹ ይቀጥላል፡- ***በዚያን ቀን (በትንሳኤ በፍርዱ ቀን) ብዙዎች ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርኩምን? በስምህ አጋንንትን አላወጣህምን? በስምህ ብዙ ተአምራቶችን አላደረከምን ይሉኛል? በዚያን ጊዜ አላውቃችሁም እናንተ ከፉዎች (አመፀኞች) ከእኔ እራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።››*** ይህ አገላለጽ ደግሞ እጅግ የሚደንቅ ነው። ኢየሱስን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለው ማን ነው? እኛ ሙስሊሞች ወይንስ ክርስቲያኖች? አላውቃችሁኻም የተባሉትስ? መቼም ሙስሊሞችን እንዳልሆኑ ለሁሉም ክርስቲያን ግልፅ ነው። ሙስሊሞች ኢየሱስን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! አይሉትም። በማቴዎስ ወንጌል 15፡79 ***‹‹ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፤ ልቡ ግን ከእኔ የራቀ ነው። የሰው የሆነ ትምህርት እያስተማርኩኝ በከንቱ ያመልኩኛል።››*** አሁንስ በከንቱ የሚያመልኩት እነ ማን ይሆኑ? በመቀጠል በማርቆስ ወንጌል 10፡13-15***‹‹ሕፃናትን ኢየሱስ እንዲዳስሳቸው ሰዎች ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀመዛሙርቱ ግን ተቆጡ። ኢየሱስም ይህን በማየት ተቆጥቶ ደቀመዛሙርቱን እንዲህ አላቸው፡- የእግዚአብሔር መንግስት እንደነዚህ ሲሉትና ስለዚህ ሕፃናትን ወደ እኔ ይምጡ አትከልክሏቸው፤ እውነት እላችኋለሁ የእግዚአብሔር መንግስት እንደ ሕፃናት ሆኖ የማይቀበሉት ከቶ አይገባበትም።››***

ጥያቄ ለክርስቲያኖች ሕፃናት ወንጀለኛ (ኃጢአተኛ) ናቸው ስላልተጠመቁ ትላላችሁ፡፡ ለዚህ ንግግራችሁ ማስረጃቸሁ ምንድን ነው? ኢየሱስ ግን ሕፃናት ወንጀለኛ (ኃጢአተኛ) ሳይሆኑ የመንግስተ ሰማያት እንደሆኑ ነው የነገረን፡፡ ከኢየሱስ ንግግር የበለጠ የማን ንግግር ይታመናል? እንዲሁም ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ደግሞ እንደ ሕፃናት ካልተሆ እንደማይገባም በማስከተል ተናግሯል፡፡ ሕፃናት ምንድን ናቸው እምነታቸው ከተባለ? አጭሩና ትክክለኛ መልሱ ሙስሊሞች ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደ እኛ ሙስሊሞች እንደ ሕፃናት ሙስሊም ካልሆናችሁ መንግስተ ሰማያት በክርስቲያኖች ላይ እርም ነው፡፡ እኔ አይደለም ያልኳችሁ ኢየሱስ የተናገረውን ነው፡፡ ኢየሱስ ይህን ሲናገርና ሲያረግ በምድር ላየው ነገር ነበር፡፡ እንዲሁም ሞተ፣ ተሰቀለ ሳይባል በሕይወት ሳለ ነበር የተናገረው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ላይ የውርስ ኃጢአት እንደሌለና ኢየሱስም ለሰው ልጆች ኃጢአት ቤዛ እንዳልሆነና ተስቅሎ እንዳልሞተ ንግግሩ ይጠቁሟል፡፡ ምክንያቱም ተሰቀለ ሞተ ከመባሉ በፊት በምድር ላይ ሳለ ነው የተናገረው፡፡ በሉቃስ ወንጌል 6፡46«***የምነግራችሁን አትፈፅሙም፤ ታዲያ ለምን ጌታ ሆይ ትሉኛላችሁ?***» ይላል፡፡ ብቸኛ የመዳኛው መንገድ በዮሐንስ ወንጌል 5፡23-24 እና ከዚሁ ምዕራፍ 17፡3 ላይ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪ በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41 ያለውን ስንመለከት እንዲህ ይላል ኢየሱስ፡- ለሐዋሪያቶች«***<u>እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል የላከኝ ይቀበላል፤ ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ያገኛል</u>፡፡ <u>ጻድቁንም በጽድቁ የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ያገኛል</u>***፡፡» ከዚህ ላይ ነብይን በነብይ ሰም የሚቀበል አለ እንጂ መች ነብይን በአምላክ ስም የሚቀበል አለ?

## <u>ኢየሱስን ጌታ ማለት ሳይሆን ትእዛዛትን መጠበቅ (መፈፀም) መንግስተ ሰማያት (ገነት) ያስገባል፡፡</u>

ትእዛዛትን መፈፀምና መጠበቅ ወደ መንግስተ ሰማያት ያስገባል፡፡ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 14፡12«***<u>እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የምሰራውን ሥራ ይሰራል</u>፡፡ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ <u>ከዚህ የበለጠ ሥራ ይሰራል</u>***፡፡» ልብ ብለን ይህን ጥቅስ ካየነው ኢየሱስ በእኔ አምላክነት የሚያምን ሳይሆን ያለው በእርሱ ነብይነት የሚያምን ሁሉ የእሱን ስራ መስራት እንደሚችል ነው የገለፀው፡፡ አይደለም በአምላክነቱ የሚያምን ነው የምትሉ ከሆነ

ታዲያ እናንተ ከአምላክ የበለጠ ስራ መስራት ትችላላችሁ ማለት ነው? ምክንያቱም ከዚህ የበለጠ ስራ ይሰራል ስለሚል ጥቅሱ። በኢየሱስ ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከላይ ያሳለፍነው የማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41 ላይ የተጠቀሰው ጥቅስ መልስ ይሰጠናል። «***እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል፤ ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ያገኛል። ፃድቁንም በፅድቅ ስም የሚቀበል፤ የፃድቁን ዋጋ ያገኛል***» በማለት ስለ ራሱ ማንነት አስረድቷል። ስለዚህ መንግስተ ሰማያት ለመግባት በኢየሱስ ነብይነት ማመንና የአምላክን ትእዛዝ መፈፀም ግድ ይላል። በዮሐንስ ወንጌል 14፡15«***ብትወዱኝስ ትእዛዜን ጠብቁ***» ብሷል። አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 14፡21«***ትእዛዜን የሚቀበልና በሥራ ላይ የሚያውለው ይወደኛል***።» ስለዚህ መንግስተ ሰማያት የሚገቡት ትእዛዛቱን የሚጠብቁት ብቻ ናቸው። በ1ኛ ዮሐንስ መልእክት 3፡18«***ፍቅራችን እውነተኛና በሥራ ላይ የሚገለጽ ይሁን እንጂ በቃል ወይንም በንግግር ብቻ አይሁን***» ይላል። በዮሐንስ ወንጌል 14፡24«***የማይወደኝ ቃሌን አይጠበቅም***» ያለው ለዚህ ነው። ቃሉን የሚጠብቅ ሁሉ ሙስሊም ነው። በማቴዎስ ወንጌል 19፡16-18«***አንድ ቀን አንድ ሰው ወደ ኢየሱስ መጥቶ መምህር ሆይ! የዘላለም ሕይወትን ለማግኘት ምን ማድረግ አለብኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? ብሎ ጠየቀው ኢየሱስም ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቃለህ? መልካም የሆነ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ወደ ሕይወት ለመግባት ብትፈልግ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ (ፈጽም) አለው።***» አስተውሉ ኢየሱስ ምን እንዳለ መልካም የሆነው አንድ አምላክ ነው። በመቀጠል ወደ መንግስተ ሰማያት መግባት የፈለገ ደግሞ ትእዛዛትን መጠበቅና መፈፀም እንዳለበት ለጠይቀው ሰው መልሷል። በሉቃስ ወንጌል 6፡46«***የምነግራችሁን አትፈፅሙም ታዲያ ለምን ስለምን ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! ትሉኛላችሁ?***» ይላል። አራቱም ወንጌሎች ትእዛዛትን በመፈፀም ላይ ፅኑ ምክር አላቸው። ነገር ግን ኢየሱስን አምላክ ነው የሚሉ ሰዎች ለዚህ ነገር ቦታ አይሰጡትም። ሌሎችም ምዕራፍና ቁጥሮች በዚሁ ጉዳይ ላይ ወደ አንድ አቅጣጫ ያቀስራሉ። ለምሳሌ በትንቢተ.ኢሳይያስ 13፡15-16፣ 18፡10፣ 26፡13፣ በትንቢተ.ኤርሚያስ 44፡7፣ በትንቢተ.ሶፎንያስ 1፡14፣ 2፡3፣ በትንቢተ.ሕዝቄኤል 11፡9-12፣ 20፡5-9፣ 20፡18-19፣ በኦሪት.ዘሌዋውያን 20፡7፣ 26፡14 እና ሌሎች ምዕራፎች አሉ። በተለይ ዘዳግም፣ ዘኁልቁ ሌሎችም ምዕራፎች ትእዛዛትን እንድጠብቅና እንድንፈፅም በፅኑ ይመክራሉ። በመቀጠል ደግሞ ትዕዛዝን አለመጠበቅ ከባድ ቅጣት እንዳለው

ያስጠነቅቁናል። ለምሳሌ፡-በኦሪት.ዘሌዋውያን 25፡14-18 ላይ እርሱ “ራሱ አለመታዘዝ የሚያስከትለው ቅጣት” ይላል። በቅርብ ጊዜ ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ በ1993 ዕትም በገጽ 124 መመልከት ይቻላል። 26፡14-18«*ነገር ግን ባትሰሙም፤ እነዚህን ትእዛዞችን ባትጠብቁ ስርአቴንም ብትንቁ፤ ሕጌን ብታቃልሉ፤ ትእዛዜንም ሁሉ ባትፈፅሙ፤ ቃል ኪዳኔንም ብታፈርሱ፤ እኔም ይህን አደርግባችኋለሁ። ድንገተኛ መቅሰፍትና ድንጋጤን አመጣባችኋለሁ።*» ስለዚህ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ትእዛዛትን መጠበቅ በሁሉም ፍጥረታት ላይ የተጣለ ግዴታ ነው።

## ትእዛዛትን የሚፈፅሙ እነ ማን ናቸው?

በመጽሐፈ መዝሙር 25፡10«*ቃል ኪዳኑን የሚጠብቁትንና ትእዛዛቱን የሚፈፅሙትን ሰዎች እግዚአብሔር በእውነትና በፍቅር ይመራቸዋል*።» በትንቢ.ተ.ዮናስ 3፡3 (ዮናስ)«*የእግዚአብሔርን ቃል ታዘዘ*።» በመጽሐፈ መቃብያን ቀደማይ 36፡15-16«*ከሞት ወደ ሕይወት ትሻገሩ ዘንድ መልካም ማድረግና የደኅነት መንገድን ቻል አትበሉ። በጎ ሥራ የሚሰሩትን እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቃቸዋል*።» በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 10፡28«*ከሞት ወደ ሕይወት ከምታልፍ ከዚች አለምም ወደ ላይኛዋ መንግስተ ሰማይ ከዚች ምድራዊ ብርሃን ወደ ሰማያዊ ብርሃን ትሻገሩ ዘንድ መልካም ሥራን አዘጋጁ*።» ከዚሁ ምዕራፍ 9፡20«*በእግዚአብሔር ፊት በቆማችሁ ጊዜ ሥራችሁ በጎ ይሆን ዘንድ ነፍሳችሁ ከሥጋችሁ ስትለይ የፈጣሪያችሁን የእግዚአብሔርን ፈቃድ (ትእዛዝን) ጠብቁ*።» እነዚህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ኢየሱስ ለኃጢአታችን ተሰቅሎ በመሞት መሰዋዕት ሆኗል በሚለው የተሸሩ አይደሉም።

## ኢየሱስ ራሱ ሙስሊም፣ ትእዛዝን ተቀባይና ፈፃሚ ነበር።

ኢየሱስ ትእዛዝን የሚፈፅም እንደነበር ይናገራል። ትእዛዝን የሚቀበልና በስራ ላይ የሚያውል ደግሞ ሙስሊም ነው። ኢየሱስም ሙስሊም ነበር፤ ትእዛዝን እንደ ፈፀመና እንደ ተቀበለ፤ በዮሐንስ ወንጌል 10፡18«*ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኩ*» በማለት ይናገራል። ከዚሁ ምዕራፍ 12፡49-50«*እኔ የምለውንና የምናገረውን ትእዛዝ የሰጠኝ የላከኝ አብ ነው። የእርሱም ትእዛዝ የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረው አብ የነገረኝን ትእዛዝ*

***ነው።»*** አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 14፡31«***ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድ ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን ሁሉ እፈፅማለሁ።»*** አሁንም በድጋሜ በዚሁ ምዕራፍ 9፡4«***ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- ቀን ሆኖ ሳለ የላከኝን ሥራ መሥራት አለብኝ፤ ማንም ሰው ሊሠራ የማይችልበት ሌሊት ይመጣልና።»*** እኛም የምንላችሁ ቀን ሆኖ ሳለ የአላህን ትእዛዝ ፈፅሙ፤ ኢየሱስ እንደፈፀመው። ትእዛዝን የሚፈፅሙ ሁሉ ብፁአን (ፃዲቅ) መሆናቸውንም ጠቁሟል። በሉቃስ ወንጌል 11፡28 «***ብፁዓንስ (ፃድቃን) የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው።»*** እንዲሁም በትዕዛዝ ላይ የሚፀና እንደሚድን ተገልጿል። በማርቆስ ወንጌል 13፡13 «***እስከ መጨረሻ የሚፀና ይድናል።»*** በተቃራኒው ደግሞ መልካም ስራ የማይሰራ ትእዛዝን የማይጠብቅ ፍርዱ ምን እንደሆነ በሚቀጥለው ምዕራፍ ምላሹን ይሰጠናል። እንዲህ በማለት፡- በሉቃስ ወንጌል 3፡9«***መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል።»*** የሰው ልጅ መልካም ካልሰራ ገነነም ተገቢ ደመወዙ ነው። በመቀጠልም በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 6፡14«***እግዚአብሔርን የማይወዱ ሰዎች ግን ቃሉን አይጠብቁም፤ ልቦናቸውም የቀና አይደለም።»*** አምላካችን ሆይ ልቦናችንን የቀናና መልካም ስራ የምንሰራና ከክፉ ስራ አንተ ጠብቀን።

# ምዕራፍ ስድስት

## ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው አዳምና ሔዋን እንዲሁም የሰው ልጆች በሙሉ በሰሩት ወንጀል (ኃጢአት) እርሱ ተሰቅሎ በመሞት ቤዛ (መሰዋዕት) ለመሆን ነው? ወይንስ ለሌላ?

እንደ ክርስትና አስተምሮ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው አዳምና ሔዋን በሰሩት ኃጢአት እና እንዲሁም የሰው ልጆች በሙሉ በሰሩት ወንጀል እርሱ ለእኛ ቤዛ (መሰዋዕት) ለመሆን ነው ይላሉ። ነገር ግን ኢየሱስ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል ወደዚህ ምድር የመጣው ለሌላ ዓላማ እንደ ሆነ ተከታዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ይናገራል። ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበት ዋናው ዓላማ በማቴዎስ ወንጌል 10፡34-35«*__እኔ የመጣሁት ሰላምን ልሰብክ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። እኔ የመጣሁት ወንድ ልጅን በአባቱ ላይ ሴት ልጅን በእናቷ ላይምራትን በአማትዋ ላይ በጠላትነት ለማስነሳት ነው።__*» ታዲያ ይህን ንግግር ማን ነው የተናገረው? ይህ እውነታ ተደብቆ ኢየሱስ የመጣው ለኃጢአታችን ሲል ተሰቅሎ ለመሞት ቤዛ ለመሆን ነው ለምን ይባላል? ይህን ሐሳብ የማይገድፉና እውነታውን አጉልተው የማያሳዩ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ሰፍረው ይገኛሉ። ለምሳሌ፡- በብሉይ ኪዳን በትንቢተ.ሕዝቂኤል 9፡5-6«*__በከተማይቱ በመዘዋዋር ሁሉንም ግደሉ፤ ለማንም በመራራት ሐዘኔታ አታድርጉ፤ ወጣት ሽማግሌ ኮረዳም ሆነ ሕፃናትን ሳይቀር ሁሉንም ግደሉ__*» ይላል። ይህ ብቻ አይደለም። በሌሎች ምዕራፎችም በጭራቃዊ ድርጊት ተሞልተው ይነበባሉ። በትንቢተ.ኢሳይያስ 4፡22፣ ከዚሁ ምዕራፍ 8፡18፣ ኦሪት.ዘኁልቊ 31፡1-18፣ ኦሪት.ዘዳግም 20፡4-14፣ በመጽሐፈ መሳፍንት 21:10-12 እና ሌሎችም ምዕራፎች አሉ። ነገር ግን ይህን ሁሉ ከመዘርዘር ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን የተናገረውን ማስቀደሙ የተሻለ ነው። ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 12፡49-51«*__እነሆ እኔ በምድር ላይ እሳት አምጥቻለሁ፤ ታዲ ያቶሎ ቢቀጣጠልልኝ በወደድኩ፤ እኔ በምድር ላይ ሰላምን ያመጣሁ ይመስላችኋልን? እኔ ያመጣሁት መለያየትን እንጂ ሰላምን አይደለም እላችኋለሁ።__*» ይህ ትንቢት ይፈፀም ዘንድ ከዚሁ ምዕራፍ ሳንወጣ በሉቃስ ወንጌል 19፡27«*__እነዚህን ጠላቶችን ግን እዚህ አምጥቻለሁ በፊት ግደሏቸው።__*» ታዲያ ይህ ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል? በትንቢተ.ሕዝቄል 9፡5-6 ያለውን ስንመለከት ደግሞ ሁሉንም

ግደሉ በማለት ይመክራል። ለህፃናትና ለአሮጊቶች እንዳትራራ በማለት። አሁን የትኛው የሰይፍ ሃይማኖት እንደ ሆነ ንጹህ አዕምሮና ህሊና ያለው ይፍረደው። የእኔ ብዙ ማለት አያስፈልግም። ኢየሱስ ለኃጢአተኞች እንዳልመጣና ለወንጀላቸውም ተሰቅሎ እንዳልሞተ በሚቀጥለው ርዕስ ይብራራል።

## እውን ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል ነው ተሰቅሎ የሞተው? እንዲሁም ተሰቅሎ ሞቷልን?

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃአጢት ሲል ተሰቅሎ እንዳልሞተና ለኃጢአታቸውም ሲል ወደዚህ ምድር እንዳልመጣ ካሳለፍነው ርዕስ ላይ እውነቱን አይተናል። አሁንም የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖረን ኢየሱስ ተሰቅሎ እንዳልሞተ ማስረጃዎችን በመጥቀስ ይህን የሐሰት ብዝሃ ግልጽ ይሆንልናል። ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል ተሰቅሎ እንዳልሞተ በዮሐንስ ወንጌል 7፡33-34 በሰፈረው አንቀጽ መልስ ይሰጠናል። የሐሰት ብዥታውን በማጥፋት እውነታውን የበለጠ ያጎለዋል። ‹‹***ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- እኔ ከአናንተ ጋር የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደላከኝ እሄዳለው፤ ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም፤ ወዳለሁበትም ልትመጡ አትችሉም።***›› ከዚህ ላይ ወደላከኝ እሄዳለሁ አለ አንጂ መች ተሰቅየ እሞታለሁ አለ? እንዲሁም ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝም ብሏል። ታዲያ እንዴት ተይዞ ተሰቀለ ይባላል? ማን ፈልጎ ይዞ ሰቀለው? ጥቅሱ ዋሸ ወይንስ እናንተ? ግልፅ እኮ ነው ወዳለሁበት ለትመጡ አትችሉም እያለ ተይዞ ተሰቀለ ማለት ምን ማለት ነው? አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 8፡21‹‹***እኔ እሄዳለሁ እናንተ ግን እኔን ትፈልጉኛላችሁ ነገር ግን ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ እኔ ወዳለሁበት ለትመጡ አትችሉም።***›› እንዲያውም ከዚህ ላይ ለኃጢአታችን ተሰቅሎ ቤዛ ሆነልን የሚለው አባባል ለአዕምሮ ከመጐርበጥ አልፎ ትርጉምና ቦታ ያጣል። ከዚሁ ምዕራፍ 8፡24 ‹‹***ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ ያልኩት ስለዚህ ነው፤ እኔን ማንነት አውቃችሁ ብታምኑ ከነኃጢአችሁ ትሞታላችሁ።***›› የእርሱን ማንነት ማመን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ከዚሁ ምዕራፍ በዮሐንስ ወንጌል 5፡23-24‹‹***እውነት እውነት አላችኋላሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው***›› በማለት መልሱን ይሰጠናል። አይሁዶች ኢየሱስን ለመስቀል ቢያስቡም እንኳ ሀሳባቸውም እንዳልተሳካ አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ ስንወጣ መልስ ይሰጠናል። በዮሐንስ ወንጌል 7፡30‹‹***በዚያን ጊዜ ሊያዩት ፈልገው ነበር። ነገር ግን ማንም***

***አልያዘውም***» ይላል፡፡ ታዲያ እንዴት ተይዞ ተሰቀለ? ማን ያዘው ጥቅሱ ማንም አልያዘውም ካለ ተይዞ ተሰቀለ የሚለው የማን ንግግር ነው? የ1993 ዕትም ላይ «***ማንም እጁን አላሳረፈበትም***» ይላል። አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 8፡59 «***አይሁደዊያን ድንጋይ አንስተው ሊወግሩት አሰቡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወረባቸው ከቤተ መቅደሰም ወጥቶ ሄደ።***» ከቤተ መቅደስም ከተሰወረባቸው የት አግኝተው ሰቀሉት ከተናጋሪው የበለጠ የማን ንግግር ይታመናል? የአሁኖቹ ክርስቲያኖች በዓይን ካዩት የበለጣችሁ ታማኝ ናችሁን? እንዲያውም በአባባል እንኳ ‹**ማየት ማመን ነው**› አይደል የሚባለው።

## ኢየሱስ ተሰቅሎ እንደሚሞት ሳይሆን ወደ አምላኩ እንደሚያርግ (እንደሚወሰድ) ነው የተናገረው።

ኢየሱስ ተሰቅሎ እንደሚሞት ሳይሆን ወደ አምላኩ እንደሚያርግ ተናግሯል። በዮሐንስ ወንጌል 7፡33-34«***ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- ከእናንተ ጋር የምቆየው ጥቂት ጊዜ ነው፤ ከዚያም ወደላከኝ እሄዳለሁ***» አለ። ከዚህ ላይ ተሰቅሎ እንደሚሞት ሳይሆን ለወደፊት እንደሚያርግ ነው የሚያስረደው። ከዚሁ ምዕራፍ 20፡17«***እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ፤ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው***» ነው ያላት ለማሪያም። ተጨማሪ በማቴዎስ 26፡24«***የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄደል***፤-----» ይላል፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እንደሚያርግ በተደጋጋሚ በአፅንዖት ተናግሯል። ጳውሎስ

## አምላክ ግን አይሞትም፤ ዘላለማዊና ኅያው ነው።

ክርስቲያኖች “አምላክ ሞቷል” ይላሉ። ነገር ግን አምላክ የማይሞት፤ ኅያውና ዘላለማዊ አምላክ ነው። የዘላለሙ አምላክ ቀርቶ ኢየሱስም አምላክ ባይሆንም ተሰቅሎ አልሞተም። አምላክ እንደማይሞት መጽሐፍ ቅዱስ በአዲስ ኪዳንና በብሉይ ኪዳን ሰፍሮ ይገኛል። በትንቢተ.ሕዝቄኤል 14፡16«***እግዚአብሔር በኅያውነቴ እምላለሁ***» ይላል። በትንቢተ.ኤርሚያስ 10፡10«***እግዚአብሔር ግን እወነተኛ አምላክ፤ ዘላለማዊ ንጉሥ ነው።***» በኦሪት.ዘዳግም 32፡40«***እጄን ወደ ሰማይ እዘረጋለሁና፤ እንዲህም እላለሁ፡- ለዘላለም እኔ ኅያው ነኝና።***» ስለዚህ አምላክ ዘላለማዊ ንጉስና ኅያው ከሆነ እንዴት ሞተ ይባላል? ሞተ፣ ተሰቀለ ብሎ የሰበከው ጳውሎስ እራሱ አምላክ እንደማይሞት ተናግሯል። 1ኛ ቆሮንቶስ 6፡16

*«የተባረከውና ብቻውን ገዥ የሆነው የነገሥታት ንጉሥ የጌቶች ጌታ እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ የሚያሳየው ነው፤ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ሊቀርብ በማይችል ብርሃን ውስጥ ይኖራል፤ እርሱን ያየ ማንም የለም፤ ሊያየውም የሚችል የለም፤ ለእርሱ ክብርና ኃይል ከዘላለም እስከ ዘላለም ይሆን አሜን።»* ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 1፡1*«ብቻውን አምላክ ለሚሆን ለማይሞተው ለማይታየው ለዘመናት ንጉሥ ለሆነው ምስጋናና ክብር ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይሆን አሜን።»* ከዚህ ላይ ኢየሱስ አምላክ ነው የምትሉ ሰዎች አምላክ ተብሎ በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጸው ግን እንደማይሞት፣ ዘላለማዊ ንጉስ፣ ኃያልና ኅያው አምላክ እንደ ሆነ ነው አንቀጹ የሚያስረዳው። ታዲያ ብቻውን አምላክ ለሚሆን ሲል አምላክ ብቸኛ መሆኑን አያሳይምን? ሲቀጥል የሞተው ሌላ አምላክ ነው ማለት ነው? ኢየሱስ አምላክ እንደማይሞት አሁንም በሉቃስ ወንጌል 20፡38 *«እግዚአብሔር የኅያው አምላክ እንጂ የሙታን አምላክ አይደለም።»* በማለት አምላክ የማይሞት መሆኑን ያስረደል። ሞተ፣ ደከመ፣ ተከዘ፣ ወ.ዘ.ተ. የሚባሉት ባሕሪያቶች የሰው ባሕሪ እንጂ የአምላክ ባህሪያቶች አይደሉም። በበለጠ ደግሞ የአምላክ ባሕሪያቶች ከሚለው ርዕስ ይመልከቱ። ለኃጢአታችን ኢየሱስ ሞቶ ተሰቅልናል የሚሉት አባባሎችን እስካሁ ካየናቸው ጥቅሶች ጋር ተዛማጅነት የላቸውም። ኢየሱስም ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል ተሰቅሎ እንዳልሞተና እያንዳንዱ ሰው በገዛ ኃጢአቱ እንደሚጠየቅ መጽሐፍ ቅዱስ በፅኑ ያስረዳል። ኃጢአት የሚሰራ የኃጢአት ደመወዝን እንደሚቀበል፤ መልካም የሰራ የመልካም ደመወዝን እንደሚቀልና በጥቅሉ የውርስ ኃጢአት እንደሌለ በአንክሮ ይናገራል።

## ኢየሱስ ሞተ፣ ተሰቀለ የምትሉን ከሆነ እኛ ሙስሊሞች ጥያቄ አለን።

ኢየሱስን ተሰቅሎ ሞቷል የሚሉን ከሆነ ለክርስቲያኖች የምንጠይቃቸው ጥያቄዎች አሉ። ይኸውም በሉቃስ ወንጌል 22፡3-5*«ሰይጣንም ከአሥራ ሁለቱ ጋር ከተቆጠረው አንዱ በነበረው የአስቆሮቱ በተባው በይሁዳ ገባበት፤ ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንደሚሰጣቸው ከካህናት አለቆችና ከመቀደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ፤ እነርሱም ደስ አላቸው። ገንዘብም ሊሰጡት ተዋዋሉ፤ እርሱም (ሰይጣን) በነገሩ ተስማማ።»* ጥያቄ ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ካደረገውና ክርስቲያኖች እንደሚሉት ኢየሱስም ተይዞ ከተሰቀለ ሰይጣን የክርስቲያኖች ባለውለታ ነው ማለት ነው። ለምን ቢሉ ክርስቲያኖች እንደሚሉት

በኢየሱስ መሰቀል ነውና ከኃጢአት ነፃ የወጡት። ገነትም ወራሽ የሆኑት። ይህ ነው የክርስትና የመዳኛ መንገድ። ስለዚህ ሰይጣን በይሁዳ ገብቶ ኢየሱስን አሳልፎ እንዲሰጥ ካደረገው ከዚያም ክርስትና እንደሚለው ኢየሱስ ተይዞ ከተሰቀለ በጥሞና ካስተዋልነው ክርስቲያኖች ድነናል ያሉበት ስቅት እንዲሳካ ሰይጣን ግንባር ቀደም አስተዋፅኦ አድርጓል። እንዲሁም የመዳኛ መንገድ ዘርግቷል ማለት ነው። ታዲያ ክርስትና መዳኛው ዋናው ምክንያት ሰይጣን ሊሆን አይደለም!!! ምክንያቱም ሰይጣን ኢየሱስን እንዲሰቀል አሳልፎ ባይሰጥ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ስቅለቱ መች ይሳካ ነበር። ታዲያ ለክርስቲያኖች እንደ ሰይጣን ማን መልካም ባለውለታ አለ? ኢየሱስን አሰቅሎ ክርስቲያኖችን አድኖ የለ። ሌላው ጥያቄ ኢየሱስ ተሰቀለ ሞተ የምትሉን ከሆነ እየረገማችሁት ማለት ነው። ምክንያቱም በኦሪት.ዘዳግም 21፡22«***ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ወንጀል (ኃጢአት) ቢሠራ እንዲሞትም ቢፈረድበት በእንጨት ላይ አትስቀለው፤ ምክንያቱም የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር አምላክ ዘንድ የተረገመ ነው።***» ታዲያ ኢየሱስ በጥቅሱ መሰረት የተረገመ ነውን? ደግሞስ ምን ኃጢአት አለበት? እኛ ሙስሊሞች ኢየሱስ ወንጀል (ኃጢአት) የለበትም እንዲሁም የተረገመ አይደለም ማለታችን ክፋት ነውን? ሞተ ተሰቀለ ስትሉ እያከበራችሁትና እየወደዳችሁት ነው ማለት ነው? እንደ ክርስቲያኖች ለኢየሱስ ማን ጠላት አለ? ለመስቀል የሞከሩት የካህናት አለቆች እንጂ ሙስሊሞች አይደሉም። አሁንም ኢየሱስ ሞቷል የምትሉትን ከሆነ ሐሰተኛ ነብይ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም ከዚሁ ምዕራፍ 13፡5«***ሕልም አላሚና ሐሰተኛ ነብይ ይገደል***» ይላል። ታዲያ በጥቅሱ መሰረት ኢየሱስ ሐሰተኛ ነብይ ነው ማለት ነው? ባይሆንማ እንደ እናንተ አባባል ተሰቅሎ ባልሞተ ነበር።ሲቀጥል በመጽሐፈ መዝሙር 34፡17«***ቅኖች ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ፤ እርሱም ይሰማቸዋል፤ ከችግራቸውም ያድናቸዋል።***» አሁንም ይህን ጥቅስ በመንተራስ ጥያቄ አለን። ኢየሱስ ቅን ስላልሆነ ነው ተሰቅሎ የሞተው? እንዲሁም ከችግሩ ያላዳነው? ኢየሱስ ግን ቅን ነበር ኃጢአት የሌለበት ነብይም ነው ጸሎቱም የተሰማለት ነበር። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 7፡7-10«***ለምኑ ይሰጣችኋል፤ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችኋል፤ የሚለምን ሁሉ ይቀበላል፤ የሚፈልገውንም ያገኛል። መዝጊያም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።***» ታዲያ የኢየሱስ ጸሎት ተቀባይነት የለውም የተባለው ለምንድን ነው? ኢየሱስ ጸሎቱ እንደተሰማለትና ተቀባይነት እንዳገኘም ጳውሎስ እራሱ ወደ ዕብራውያን በላከው መልእክት 5፡7«***እርሱም በሥጋው ወራት ከሞት ሊያድነው***

*ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ምልጃን አቀረበ። እግዚአብሔርንም ስለ መፈራቱ ተሰማለት።*» ስለዚህ የኢየሱስ ጸሎት በከንቱ አልቀረም ማለት ነው። ተጨማሪ በያዕቆብ መልእክት 5፡16«*ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱም ስለሌላው ይጸይ፤ የፃድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።*» አሁንም በድጋሜ ኢየሱስ ጸሎቱን አምላኩ እንደሰማው ሲናገር፡- በዮሐንስ ወንጌል 11፡211-12 «*ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- አባት ሆይ! ስለሰማኸኝ አመሰግናለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ።*» አዎ የኢየሱስ ጸሎት ይቅርና የፃድቃን ሰዎች ጸሎትም እንደሚሰማ ተናግሯል። እውነቱ ይህ ነው ለሚያነበውና ለሚረደው ሰው። ሌላው ኢየሱስ ለሰው ልጆች ሲል መሰዋት አልሆነም። በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳንም ሰፍሮ ይገኛል። በትንቢተ.ሆሴዕ 6፡6«*ከመሰዋዕት ይልቅ ምህረትን እወዳለሁኝ፤ ከሚያቃጥል መሰዋዕት ይልቅ እግዚአብሔርን ማወቅ እወዳለሁና።*» ኢየሱስም በማቴዎስ ወንጌል 9፡13«*ነገር ግን ሂዳችሁ መሰዋዕትን ሳይሆን ምህረትን እወዳለሁ፤ መሰዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ተማሩ።*» ከዚሁ ምዕራፍ 12፡7«*ምህረትን እወዳለሁ መሰዋዕትንም አይደለም። ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኮነናችሁ ነበር*» ይላል። ስለዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስን ኃጢአተኛ ነው ብላችሁ አትኮንኑት። እርሱ እራሱ ቤዛነትን ሳይሆን የአምላኩን ምህረት ነው የፈለገው። ሌላው ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ሞቷል ብላችሁ ታምናላችሁ። ሞተ እንኳ ቢባል ስቃይን ፈተናን ለመግለጽ ነው። እንጂ ተሰቅሎ እንዳልሞተ ባሳለፍነው ርዕስ ላይ ያየነው እውነታ ነው። ለምሳሌ ጳውሎስ ‹**ሞት**› ማለት ስቃይና ፈተና መሆኑን ሲገልጽ፡- በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡31«*ወንድሞች ሆይ! ዕለት ዕለት እሞታለሁ*» ይላል። ታዲያ ዕለት ዕለት እሞታለሁ ሲል በየቀኑ ነው የሚሞተው? ስንቴስ ነው የሚሞተው? የሰው ልጅ ስንት ጊዜ ይሞታል? ለማንኛውም ዕለት ዕለት እሞታለሁ ማለቱ በየቀኑ እሰቃያለሁ ለማለት ነው። «*ኢየሱስም ነብሴ እስከ ሞት ድረስ ታውካች*» ያለው የደረሰበትን ፈተና ለመግለፅ ነው።

## አዳምና ሔዋን እንዲሁም የሰው ልጆች በሙሉ በሰሩት ኃጢአት ኢየሱስ ለኃጢአታችን ሲል ተሰቅሎ በመሞት ቤዛ ሆነ ከሚለው ሐሳብ ጋር አብረው የማይሄዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል ተሰቅሎ ሞተ ከሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ጋር አብረው የማይሄዱና ተዛማጂነት የሌላቸው በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች አሉ። ለአብነት የሚከተሉትን እንመልከት፡-

- *እስከ መጨረሻ የሚጸና ይድናል።*
- *መጥፎ የሰሩ ወደ ሲዖል ይገባሉ።*
- *መልካም የሰሩ ገነት ይገባሉ።*
- *ከነኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ።*
- *መሰዋዕት ከሞት፣ ከኃጢአትም ታድናለች፡፡*
- *እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደማይሰማ የታወቀ ነው።*
- *ሐብታሞችና ባለጸጎች ወደ መንግሰተ ሰማያት ከሚገቡ ግመል በመርፌ ቀዳዳ መግባት (መሹሎክ) ይቀላል።*
- *ወደ ሕይወት የሚወስደው መንገድ የጠበበ (የቀጠነ) ነው፤ጥቂቶች እንጂ አያገኙትም።*
- *ጽዳቃችሁ ከሙሴ ሕግና ከፈረሳዊያን ሕግ ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም።*
- *ወደ ፈተና እንዳትገቡ በርቱና ጸልዩ።*
- *እኔ ወደዚህ ዓለም የመጠሁት ሰላምን ልሰብክ ይመስላኋልን አይደለም እኔ የመጣሁት ሰይፍን እንጂ ሰላምን ልሰብክ አይደለም።*
- *ንሰሓ የማይገባ ሁሉ ይጠፋል።*

## የውርስ ኃጢአት አስተምሮቱ የማን ነው? የኢየሱስ ወይንስ የጳውሎስ?

በመጀመሪያ የውርስ ኃጢአት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የለም፡፡ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ያላስተማረውና እንዲሁም በብሉይ ኪዳን የሌለ ነው። ለዚህ መረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ወደሚለው ስናመራ አስተምሮቱ የጳውሎስ ሆኖ

እናገኘዋለን። ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 5፡12 ላይ «*በአንዱ አዳም ምክንያት ሞት ወደዚህ ዓለም ገባ*» ይላል። ምክንያቱም አዳም ኃጢአት ሰርቷል የኃጢአት ደመወዝ ደግሞ ሞት ነው። ሞት ደግሞ ወደዚህ ዓለም የገባው በአንዱ አዳም ምክንያት ነው። የውርስ ኃጢአት አለ እንኳ ብለን ብንስማማ ለመስማማት ያክል፡ - በኦሪት.ዘፍጥረት 2፡17«*እግዚአብሔር ከፉና መልካሙን የማያስታውቀውን ዛፍ አትብሉ ባላቸው ጊዜ*--- ።» ከዚሁ ምዕራፍ 3፡1«---*ጀምሮ ቀጥፋ የበላችው ሔዋን ናት በእባብ አሳሳችነት ቅጠሉን ቀጥፋ የበላችው ሔዋን ናት*።» ስለዚህ ሞት ወደዚሁ ዓለም የገባው በአንዱ አዳም ምክንያት ሳይሆን በሔዋን ምክንያት ነው። በአንዱ አዳም ምክንያት የሚለው ከላይ ከተጠቀሰው ጋር አብሮ አይሄድም ይቃረናል። እራሱ ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡17«*የተታለለው ወንዱ (አዳም) አይደለም፤ ሴቷ (ሔዋን) ተታላ ሕጉን በመተላለፍ ወንዱን አሳሳተችው*» ይላል። ይህ ብቻ አይደለም ሔዋን የኃጢአት ምንጭ እንደሆች ሌሎች ምዕራፎችም በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ አሉ። በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 3፡6«*የበለሰ ፍሬውን ከበላች በኋላ መጥታ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍጥረቱን አዳምን አሳሳተችው። የፈጣሪዋን ትእዛዝ ስለተዳፈረች፤ በእርሱም (በአዳም) በልጆቹም ሞትን አመጣች*።» ታዲያ ሴቶች በአመጡት ሞት ነው አዳምና የሰው ዘር በሙሉ የሚሞቱት? በመጽሐፈ ሲራክ 42፡13-14«*ከልብስ ብል ይገኛል፤ ኃጢአትም ሁሉ ከሴት ልጅ ይገኛል። ስለ እርሷም ሁላችንም እንሞታለን*።» ይህን አያይዘው አንዳንድ የክርስቲያን ምሁራን በሴቶች ላይ ወቀሳና እርግማን አቅርበዋል። ለምሳሌ፡- የቀድሞው የአሜሪካ ፀረ ሠቆቃ ማኅበር መሪ የነበረችው ማልቲዳ ጆስሊን ጌጅ እንዲህ ስትል ጽፋለች፡- *“‹ቅዱስ ተርተሊንን (155-255 ኢ.ኤ) የመሳሰሉት ታላላቅ ምሁራን ሴት ሔዋንም ሆነ ሌላዋ ሴት ያው የኃጢአት ጀማሪ፤ ሞትን ያመጣችብን፤ የጌታችንንም ልጅ ለሞት የዳረገችና ልንጠነቀቃት የምትገባን የሰይጣን መግቢያ በማለት በሰፊው ማስተማራቸውን እንገነዘባለን።›፣ በዚህ ጉዳይ ላይም ቤተ ክርስቲያን ለሴት ፆታ ባላቸው የጥፋተኝነት እይታ የበላይና የበታች ፆታዎች እንዳሉም ቤተ ክርስቲያን ታስተምር ነበር።›2”* ”ከዚህ ላይ ደግሞ ሞት ያመጣችና የኃጢአት ምንጭ ሔዋን እንደሆነችና ስለእርሷም ሁለታችንም እንደምንሞት ተጠቅሷል። እንዲሁም ጳውሎስ በአንዱ አዳም ምክንያት ሞት ወደዚህ ዓለም ገባ የሚለውም ተጠቅሷል። ከሁለቱ ጥቅሶች የትኛው ትክክል በአዳም? ወይንስ በሔዋን? ሌላው እናንተ እንደምትሉት ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም የመጣው አዳም ሔዋን በአጠቃላይ የሰው ልጆች በሙሉ በሰሩት

ወንጀል (ኃጢአት) እርሱ ስለ እኛ ተሰቅሎ ቤዛ በመሆን ከገኃነም ነፃ ለማውጣት ነው ይላሉ። ያ ከሆነ በኦሪት.ዘፍጥረት 3፡16 ላይ ሔዋን የተከለከለችውን ዛፍ በመብላቷ አምላክ ቅጣት አዘዘባት። በወሊድ ጊዜ ሴቲቱ በስቃይ እንድትወልድ «***ሴቲቱንም እንዲህ አላት፡- በምጥ ጊዜ ስቃይሽን፤ ጭንቅሽን አበዛለሁ፤ በስቃይም ትወልጃለሽ፤ ፍላጎትሽም ወደ ባልሽ ይሆናል***» አላት። በዚህ ጥቅስ መሰረት ሔዋንና ሴቶች በጭንቅና በስቃይ እንዲወልዱ ተፈርዶባቸዋል። ስለዚህ ኢየሱስ ከመጣ በኋላ ይህ ጭንቅና ስቃይ መቆም ነበረበት ታዲያ እስካሁን ለምን ቀጠለ? ምክንያቱም ኢየሱስ ለውርስ ኃጢአት ስለመጣና በሰሩት ወንጀል ቤዛ ከሆነ እርሱ ከመጣ በኋላ መቆም ነበረበት። ድንገት እናንተ ሙስሊሞች ስለሆናችሁ ኢየሱስን ስላልተቀበላችሁ ነው እንዳትሉ የክርስቲያን ሴቶች በጭንቅና በስቃይ ነው የሚወልዱት። እንዲሁም ምድራዊ ሞት ለምን ቀጠለ? ታዲያ ኢየሱስ ለእኛ ሲል ቤዛ ሆነ የሚለው ጥቅስ ውሸት ነው ማለት ነው?

## የውርስ ኃጢአት የለም፤ አንዱ ባጠፋው ሌላው ያላጠፋው አይቀጣም።

የሚያሳዝነውና የሚያስገረመው ክርስቲያኖች ከምን ተነስተው እንደሆነ አይገባኝም የውርስ ኃጢአት አለ ብለው የሚያምኑት። እንደ መጸሐፍ ቅዱስ ከሆነ ጉዳዩን ሰፋ አድርጎ የውርስ ኃጢአት እንደሌለ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን በግልፅ ተቀምጧል። አዳምና ሔዋን በሰሩት ወንጀል ኃጢአት ወንጀል ተላልፏል፤ ተዋርሷል፤ ብለው ያምናሉ። ከእነሱ ጋር አብሮ የነበረው ክርስቲያን አለን ብለን ብንጠይቅ የሁሉም ክርስቲያኖች መልስ የለም ነው። ታዲያ አዳምና ሔዋን ኃጢአት ሲሰሩ ካላየን ለኃጢአታቸው ተጠያቂነት የምንወስደው ኃላፊነት ከምን የተነሳ ነው? ለማንኛውም የውርስ ኃጢአት የለም። አንዱ ባጠፋው ሌላው ያላጠፋው አይቀጣም። በኦሪት.ዘዳግም 24፡16«***ልጆቻቸው በሠሩት ወንጀል ወላጆች መቀጣት የለባቸውም። ወላጆች በፈፀሙት ወንጀል ልጆች መቀጣት የለባቸውም፤ እያንዳንዱ ሰው በራሱ ወንጀል በሞት ይቀጣል***።» ይህ ከፍትሕ አንፃር ሲታይ ለአዕምሮም የሚስማማ ነው። ዛሬ እንኳ ፍርድ ቤት አንዱ ባጠፋው ሌላውን አይቀጣም። ድንገት ለወንጀሉ ተባባሪ ካልሆነ በስተቀር አይቀጣም። እንደዚሁም ፈጣሪ ደግሞ ፍርደ-ገምድል አይደለም። በተለይ በዚህ ዙሪያ በትንቢተ.ሕዝቄኤል በሰፊው ይህንን ሁኔታ ይገልጸዋል። በ1993 ዓ.ም በቅርብ ጊዜ ከታተመው መጽሐፍ ቅዱስ በገጽ 795 ላይ ርዕሱ ራሱ «***ኃጢአት***

*የምትሰራ ነፍስ ትሞታለች›* ይላል። ትንቢተ.ሕዝቄኤል 18፡1-28‹‹*አባቶች ጐምዛዛ የወይን ፍሬ በሉ፤ የልጆችንም ጥርስ አጠረሱ እያላችሁ የምትመስሉት ተምሳሌት ምን ማለት ነው*?›› የእኔ ጥያቄ ይህ ነው። አሁን ብዙ ማለት አልችልም። ምክንያቱም ሁሉን ነገር አንቀጹ በዝርዝር ያስረዳል። ‹‹*እነሆ ነፍስ ሁሉ የኔ ናት፤ የአባት ነፍስ የእኔ እንደ ሆነችው ሁሉ፤ የልጆችም ነፍስ የኔ ናት። ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች። በቅንነትና በትክክል የሚሰራ ነብስ ቢገኝ በኮረብታ ባሉ አብያተ ጣዖት የቀረበውን አይበላም፤ በእስራኤ ቤት ወደ አሉት ጣዖት አይመለከትም፤ የባልንጀራውን ሚስት አይነካም፤ ከሴት ጋር በወር አበባዋ ጊዜ አይተኛም፤ ማንንም አይያስጨንቅም፤ ነገር ግን በመያዣ የወሰደውን እንኳ ለተበዳሪው ይመልሳል፤ ለተራብ የራሱን እንጀራ ለተራቆቱትም ልብስ ይሰጣል እንጂ በጉልበቱ አይቀማም፤ በአራጣም ወለድም አይቀበም፤ እጅን ከበደል ይሰበስባል፤ በሰውና በሰው መካከል በትክክል ይፈርደል፤ ሥርዓቴን ይከተላል፤ ትእዛዜንም በቅንነት ይጠብቃል፤ ይህ ሰው ፃድቅ ነው በሕይወት ይኖራል ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ነገር ግን አሁን ደግሞ ከላይ በመልካም ሥራ ከተጋና የፈጠረውን ሕሊና ትእዛዝ ባይጠብቅ ደግሞ . . . እንዲህ አይነቱ ሰው በሕይወት ይኖራል? ከቶ አይኖርም! እነዚህን አፀያፊ ነገሮች አድርጓልና በእርግጥ ይሞታል። ደሙም (ኃጢአቱም) በገዛ እራሱ ላይ ይሆናል። ልጅ የአባቱን ወንጀል አይወርስም፤ አባትም በልጁ ኃጢአት አይቀጣም፤ ልጁ በሕይወት ይኖራል እንጂ በአባቱ ኃጢአት አይሞትም፤ አባት ግን የሰውን መብት ሰለ ተዳፈረ፤ በገዛ ኃጢአቱ ይሞታል። እናንተ ግን ልጅ ሰለ አባቱ ኃጢአት ለምን አይቀጣም? ትላላችሁ ልጅ ቅንና ትክክለኛውን ነገር ሰላደረገ ሥርዓቴንም ሁሉ በጥንቃቄ ሰለ ጠበቀ በሕይወት ይኖራል፤ መሞት የሚገባት ኃጢአት የምትሰራ ነፍስ ናት። ልጅ በአባቱ ኃጢአት አይቀጣም፤ አባትም በልጁ ኃጢአት አይቀጣም ፃድቁ የፃድቅን ፍሬ ያገኛል። ኃጢአተኛውም የኃጢአቱን ዋጋ ያገኛል*» ይላል። ታዲያ ይህ ምን ማብራሪያ ያስፈልገዋል?

## የውርስ ኃጢአት በአዲስ ኪዳንም የለም፤ ኢየሱስም አላስተማረም።

ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት እንደሌለ ሲነግረን፡- በዮሐንስ ወንጌል 9፡1-4 ‹‹*ኢየሱስ በመንገድ ሲያልፍ እውር ሆኖ የተወለደውን ሰው አየ፤ ደቀ*

***መዛሙርቱም "መምህር ሆይ ይህ ሰው እውር ሆኖ የተወለደው በማን ኃጢአት ምክንያት ነው? ወይንስ በወላጆቹ ነው? ሲሉ ጠየቁት ኢየሱስም እንዲህ፡- ሲል መለሰ ይህ ሰው የታወረው በእርሱ ወይንም በወላጆቹ ኃጢአት አይደለም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው አለ፡፡*** » ታዲያ ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት ቢኖርና ካለ ለምንድ ነው ኢየሱስ እናቱና አባቱ እንዲሁም አዳምና ሔዋን በሰሩት ወንጀል ነው ብሎ ያልመለሰው? የውርስ ኃጢአት አለ ሲባል ጉድዩ በጣም ያስደነግጣል። ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 8፡34«***እውነት እውነት እላችኋለሁ ኃጢአት የሚሠራ ኃጢአት ባሪያ ነው፡፡***» ተጨማሪ በማርቆስ ወንጌል 4፡24-25«***ስለምትሰሙት ነገር ተጠንቀቁ በምትሰፉበት መሥሪያ ለእናንተም ይሠፈርላችኋል ባይበልጥም ይጨመርላችኋል። ከሌላው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል፡፡***» ስለዚህ የኃጢአት ባሪያ ላለመሆንና በመትሰፉበትም መስሪያ እንደይሰፈርባችሁ የፈጣሪን ትዕዛዝ መስራትና ከከለከለው ነገር መከልከል አለባችሁ። ጳውሎስም የውርስ ኃጢአት እንደሌለ ሲናገር፡- በሐዋሪያት ሥራ 3፡23 «***ያንን ነብይ የማትሰውን ነፍስ ሁሉ በሕዝብ ተለይታ ትምታለች***» ይላል። ብዙ ጊዜ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ለውርስ ኃጢአት መሰዋዕት ለመሆን ነው ይባላል። ኢየሱስ ግን ለውርስ ኃጠአት እንዳለመጣ በሉቃስ ወንጌል 5፡31-32«***ደቀማዛሙርቱ ሲያጉረመረሙ ሲሰማ ኢየሱስ እንዲህ፡-በማለት መለሰላቸው በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም። እኔም ኃጢአተኞችን ወደ ንሳሓ እንዲመለሱ እንጂ ፃድቃንን ልጣራ አልመጣሁም አላቸው፡፡***» ከዚህ ላይ ኢየሱስ የውርስ ኃጢአት ለመደምሰስ ነው የመጣሁ ብሎ ሳይሆን የመለሰው ኃጢአተኞች ወደ ንሳሓ (እንዲገቡ) እንዲመለሱ ልጣራ ነው የመጣሁት ያአላቸው።

## ለኃጢአተኛ ሰው ወዮለት! ለኃጢአትም ምክንያት ለሚሆን ለሚያሰናክል ሰው ወዮለት!

ክርስቲያኖች ቆም ብላችሁ ራሳችሁን ልትፈትሹና ልትመረምሩ ይገባል። ‹**ፅድቁ ቀርቶ በወጉ በተኮነናችሁ**› የሚስብል ነው ጉዳዩ። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያወራው ሌላ የአናንተ አባባል ሌላ ነው። ክርስቲያኖች ኃጢአታችን ተምሯል ትላላችሁ። ነገር ግን ይቅርና መማር ማንም ጽድቅ ሰው እንደሌለ አልፎ ተርፎ በገኃነም እሳት ውስጥ ዘውታሪ መሆናችሁን ነው መጽሰሐፍ ቅዱስ

የሚያስረዳው፡፡ ማስረጃውም በመሐፈ ሲራክ 2፡12-13«*ለሚጠራጠር ሰው ወዮለት! ለጠማሞች እጆችም ወዮላቸው! ሥራው ሁለት ለሆነ በሁለቱም መንገድ ለሚሄድ ለኃጢአተኛ ሰው ወዮለት! ለሚጠራጠርና ለማያምን ልብ ወዮለት! ስለዚህም (ከገኃነም) አያመልጥምና፡፡*» ከዚሁ ምዕራፍ 3፡24-26«*ጥፋትን የሚወዳት በእርሷም ይሞታል። ክፉ ልቦና በመከራ ይገረፋል፤ ኃጢአተኛ ሰው በኃጢአቱ ላይ ይጨመራል፤ ለትዕቢተኞች ጥፋት ፈውስ የላትም፤ ክፍ ተክል በውስጣቸው ሥር ሰዷልና፡፡*» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 8፡10«*በኃጢአታቸው እንድትቃጠል፤ የኃጢአተኞችን ሰዎች እሳት አትጫር፡፡*» በመጽሐፈ ኢዮብ 4፡8-9 «*ክፋትን የሚያርሱ መከራም የሚዘሩ ያንኑ ያጭዳሉ። በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ። በቁጣው ወላፈን ይደመሰሳሉ፡፡*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 13፡9«*እነሆ ምድሪቱን ባድማ ሊያደርግ፤ ኃጢአተኞቿንም ከእርሷ ዘንድ ሊያጠፋ፤ ጨካኝ ኾኖ በመዓትና በፅኑ ቁጣ ተሞልቶ የእግዚአብሔር ቀን ይመጣል*፡፡» ከዚሁ ምዕራፍ 30፡1«*ለአመፀኞች ልጆች ወዮላቸው" ይላል እግዚአብሔር፤ የእኔ ያልሆነውን ሐሳብ ይከተላሉ ከመንፈሴ ያልሆነውን ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራሉ፡፡*» በመጽሐፈ መዝሙር 50፡22«*እናንተ እግዚአብሔርን የምትረሱ ይህን ልብ በሉ፤ አለበለዚያ ግን ብትንትናችሁን አወጣለሁ። የሚያድናችሁ የለም፡፡*» በመጽሐፈ ምሳሌ 8፡36«*የሚያጣኝ ሁሉ ግን ራሱን ይጐዳል፤ የሚጠሉኝ ሁሉ ሞትን ይወዳሉ፡፡*» ከዚሁ ምዕራፍ 15፡10 «*ከመንገድ የሚወጣ ሰው ጥብቅ ቅጣት ይጠብቀዋል*፡፡» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 15፡28-29«*የክፉ ሰው አፍ ግን ክፊትን ያጐርፋል፤ እግዚአብሔር ከክፉዎች እሩቅ ነው፡፡*»

## ኃጢአተኞች ኃጢአታቸው ሊደመሰስ ይቅርና ምንም ምክንያት የላቸውም፤ ኢየሱስም ለውርስ ኃጢአት ለመሸከም አልመጣም።

ሌላው ይቅርና ሁለት ሰዎች ዝሙት በመስራታቸው ምክንያት ወንጀላቸው እንደማይማር መጻሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በመጽሐፈ ኩፋሌ 23፡39«*በሕዝቡ መካከል ሁለቱ ሁሉ በአንድነት ይጠፋ ዘንድ ይህችን ኃጢአት በሠሩበት ቀን ይገድላቸው ዘንድ ነው እንጅ ለኃጢአታቸው ምንም ሥርየት የለውም፡፡*» ሰው ሁሉ በሚሰራው ስራ ይጠየቅበታል እንጅ ለኃጢአቱ ማንም ዋስትና ኃላፍትና

አይወስድለትምም። ስለዚህ ኃጢአት እየሰሩ ኃጢአቴ በኢየሱስ መሰዋትነት ተደምስሷል የሚል እምነትን አያስይዝም። ተጨማሪ በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 10፡9-11«*ተነስተህ በፊቱ እንደምትቆም እወቅ። እንደ ሐሳብም በመቀብር የምትቀር አይምሰልህ፤ እንዲህ አይደለም፤ በምድር እንደሰራኸው ሥራ በጐም ቢሆን ክፉም ቢሆን ተነስተህ ዋጋህ ትቀበላለህ። ይህች የፍርድ ቀን ናትና በትንሳኤም ጊዜ በሥራኸው ኃጢአትህን ሁሉ ፍዳህን ቅተበላለህ፤ ከሕፃንነትህ ጀምሮ እስከ ዚያን ጊዜ ድረስ የተፃፈ እዳህን ትጨርሳህ። ኃጢአትህንም ትኪድ ዘንድ እንደዚህ ዓለም ሥራ ለኃጢአትህ የምታመካኘው ምክንያት የለህም።*» አሁንስ ግልፅ አልሆን ብሎ ይሆን? ክርስቲያኖች እስኪ ምን ምክንያት ይኖራችሁ ይሆን? ምክንያታችሁስ ተቀባይነት ያገኛልን? ክርስቲያኖች ራሳችሁን ፈትሹ መርምሩ አሁንም በተጨማሪ በመጽሐፈ ሲራክ 5፡5-6«*የእግዚአብሔር ምህረቱ ብዙ ነው እያልህ ኃጢአቴም ይቅር ይለኛል እያለህ ኃጢአቱ ላይ ኃጢአት አትጨምር። መቅሰፈቱም በኃጢአተኛ ሰው ላይ ይሆናል።*» በኦሪት.ዘፀአት 20፡7 «*የእግዚአብሔር የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ ከበደል ወይም ከተጠያቂነት አታመለጥምና።*» “አለማወቅ ኃጢአት አይደለም” የሚለው አባባል ከዚህ ላይ ቦታ የለውም። በመጽሐፈ መክብብ 5፡6«*በአግዚአብሔር ፊት ባለማወቅ ነው፤ አትበል እግዚአብሔር ስለቃልህ እንዳይቆጣ፤ የእጅህንም ሥራ እንደያጠፋብህ።*» በትንቢተ.ኤርሚያስ 10፡1-3«*እግዚአብሔር የሚላችሁን ስሙ፤ የአሕዛብን መንገድ አትከታተሉ፤ የአሕዛብ መንገድ ከንቱ ናትና።*» ከዚሁ ምዕራፍ 11፡11«*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እነሆ ሊያመለጡት የማይችሉትን ክፉ ነገር በነዚህ ሕዝብ ላይ አመጣሁ። ወደ እኔ ይጮኻለሁ፤ እኔ ግን አልሰማቸውም ኃጢታቸውም ይቅር አይባልም።*» በመጽሐፈ መቃብያን 10፡24«*ኃጢአታቸውን ያሳሰባቸው ዘንድ ባለማወቅ ኃጢአት የሠሩ ሰዎች በትንሳኤ ጊዜ ፈፅመው ያዝናሉ።*» የኔ ብዙ ማለት አያስፈልግም። ክርስቲያኖች የእራሳችሁ መጽሐፍ የሚመክራችሁን ስሙ።

## ኃጢአተኞች በገኃነም (በሲዖል) እሳት ውስጥ ዘወትር ሲቃጠሉ ይኖራሉ።

ክርስቲያኖች ሆይ ነፍሳችሁን ከእሳት አድኑ። እሳት ማለት ቸለል ሊባል የማይገባው ጉዳይ ነው። መጽሐፈ ቅዱስም በዚህ ዙሪያ በብዙ ቦታ ላይ ያስጠነቅቃል። በመጽሐፈ መቃብያን ቀደማይ 23፡6-7 «*በዚያን ጊዜ*

*የእግዚአብሔርን ፈቃድ ያላደረጉት ከሐዲዎችንና አመፀኞች ያፍራሉ፤ እስከ ዘላለም ድረስ መውጫ የሌለው በገኃነም እሳት ጨምሯቸው የሚል አስደንጋጭ ቃል ይሰጣቸዋል*።» ታዲያ በዚያ መውጫ በሌለው የገኃነም እሳት ከመቃጠል አሁን ላይ አንድ አላህን ተገዝታችሁ ከሲዖል መዳን አይሻላችሁም ነበር? እሳት ማለት አኮ ይቅርና የሰው ልጆች ብረትንና ድንጋይን ያቃጥላል። ታዲያ የሰው ልጅ ይህ ደካማ ፍጡር ማን ሊቋቋመው ይችላል? በመጽሐፈ መቃብያን 7፡1-2 «*የፈጠራቸው እግዚአብሔርን የማታውቁ ትእዛዙንና ቃሉንም የማትጠብቁ አንተና እንደ አንተ ያሉት ወዮላችሁ! ፀፀት ትፀፀቱ ዘንድ አላችሁና። . . . እስከ ዘላለም ድረስ ከርሷ መውጫ የላችሁም*።» በመጽሐፈ ኢዩብ 4፡8-9«*ክፋትን የሚያርሱ መከራንም የሚዘሩ ያንንኑ ያጭዳሉ። በእግዚአብሔር እስትንፋስ ይጠፋሉ። በቁጣው ወላፈን ይደመሰሳሉ*።» በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 9፡36 «*ኃጢአታቸውን በጫንቃቸው ይሸከማሉ። ጥቂትም ቢሆን ብዙም ቢሆን ኃጢአትን ቢሰሩ እንደ ሠሩት ሥራቸውን ይቀበላሉ*።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 1፡28 «*አመፀኞችና ኃጢአተኞች ግን በአንድነት ይደቃሉ፤ እግዚአብሔርን የሚተው ይጠፋሉ*።» ከዚሁ ምዕራፍ 66፡14-16«*የእግዚአብሔር ቁጣ ግን በጠላቶቹ ይገለጣል፤ እነሆ እግዚአብሔር በእሳት ነበልባል ይመጣል፤ ሰረገሎቹም እንደ አውሎ ነፋስ ናቸው፤ በእሳትና በሰይፍ እግዚአብሔር ፍርዱን በሰው ሁሉ ላይ ያመጣል፤ በእግዚአብሔር ሰይፍ የሚታረዱት ብዙ ይሆናሉ*።» በትንቢተ.ናሆም 1፡3 «*እግዚአብሔር በደለኛውን ሳይቀጣ አያልፍም*።» በመጽሐፈ መዝሙር 34፡21 «*ኃጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል*።» ኢየሱስም በሉቃስ ወንጌል 3፡9«*መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 20፡47 «*የመበለቶችን ቤት የሚበሉ፤ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ፤ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ*።» በማቴዎስ ወንጌል 21፡43-44«*ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ትወሰዳለች፤ ፍሬዋንም ለሚደርግ ሕዝብ ትሰጣለች። በዚህም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፤ ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨል*።»

## ከክርስቲያኖች ፃድቅ የሌለና፤ ሁሉም ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ።

ክርስቲያኖች ሁሉም ኃጢአተኞችና ፃድቅ እንዳልሆኑ ጳውሎስ እንዲህ ይናገራል። በሮሜ መልእክት 3፡9-18 «*ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኞች መሆናቸውን*

***ቀደም ብየ አስረዳቸዋለሁ፤ አንድ እንኳ ፃደቅ ሰው የለም፤ አንድ እንኪ አስተወይ የለም፤ እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም። ሁሉም ከእውነት መንገድ ወጥተዋል፤ ተሳስተዋል፤ ደግ ሥራ የሚሰራ አንድ እንኳ የለም።ሰውን የሚጐዳ ክፉ ቃል ለመናገር አፋቸው እንደመቃብር የተከፈተ ነው። አፋቸው በመራራ እርግማን የተሞላ ነው፤ እግራቸው ሰውን ለመገደል የፈጠነ ነው። በመንገዳቸው የሚገኘው ጥፋትና መከራ ነው፤ የሰላም መንገድ አያውቁም፤ እግዚአብሔርን ከቶ አይፈሩም።***» ይህ ነው የክርስቲያኖች ሁኔታ በጥቅሉ ለመልካም ስራ የታደሉ አይደሉም። ለዚህ ነው በዚህ መልኩ የገለፃቸው። በመጽሐፈ መዝሙር 12፡1 «***እግዚአብሔርን የሚፈራ ደግ ሰው የለምና።***» ከዚሁ ምዕራፍ 14፡1«***ተግባራቸው ጸያፍ ነው፤ በጐ ነገር የሚሰራ አንድም የለም።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 14፡3 «***ሁሉም ከመንገድ ወጥተዋል፤ በአንድ ላይም ብልሹ ሆነዋል፤ አንድ እንኳን መልካም የሚያደርግ የለም።***» አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 143፡2«***ሰው ሆኖ አንድ እንኳ ፃድቅ የለም።***» በመጽሐፈ መቃብያን ካልዕ 7፡2«***እንደ እግዚአብሔር የምትሰውላቸውና የምትሰግዱላቸው፤ እናንተና ካህናቱ እስከ ዘላለም (ከሲያል) ከእርሷ መውጫ የላቸውም።***» በትንቢተ.ኢሳይያስ 6፡12-13«***እግዚአብሔርም ሰዎች እስኪያርቅ ምድሪቱንም ጨርሦ ባዶ እስከትሆን ከአሥር አንድ ሰው እንኳ በምድሪቱ ቢቀር እርሱም ደግሞ ይጠፋል።***» እሰካሁን ያየናቸው በሙሉ ተስፋ አስቆራጭ ንግግሮች ናቸው። ሰለዚህ ሁሉም ክርስቲያን በመጀመሪያ ያለበትን ይፈትሽ የመጨረሻ የሕይወቱ ፍፃሜ የት እንደሚደርስ ያስቡ በማለት እመክራለሁ።

# ምዕራፍ ሰባት

## መዳን እንዴት ይቻላል? የሚያድነውስ ኢየሱስ ነው? ወይንስ እግዚአብሔር?

መዳን የሚቻለው በኢየሱስ ተሰቅሎ መሞት ሳይሆን በመልካም ስራ ነው። መልካም የሰሩትን ሰዎች ማዳን የሚችለው ደግሞ ኢየሱስ ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ ነው። አንድ ምሳሌ እንውሰድ በመጽሐፈ ጦቢት 1፡8«*ምጽዋት ከሞት ታድናለች፤ ከኃጢአትም ሁሉ ታነፃለች፤*» እንዲያውም ከዚህ ላይ በስቅለት ድኅነት እንደማይገኝና ስቅለቱንም ከንቱ ሞትን ነው የተናገረው፡፡ በመጽሐፈ መቃብያን 21፡26-28«*በጎ ሥራ ብንሠራም በጎ ሥራ ከሠሩ ጋር መንግሰተ ሠመያት እንወርሳለን፡፡ የሚወዱትን አይለያይምና፤ በንጹህ የሚለምኑትን ሰዎች እጅግ ይወዳቸዋልና፤ ጸሎታቸውንም ይሰማቸዋል፡፡ ቆርጠው ንሰሓ የሚገቡትንም ንሰሐቸውን ይቀበላቸዋል፡፡ ሕጉንና ሥርዓቱን፤ ትእዛዙንም ለሚጠብቁ ሰዎች ኃይል ፅናቱን ይሰጣቸዋል፤ ፈቃዱንም ያደረጉ ሰዎች ለዘላለሙ በመንግስቱ ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል፡፡ ፊተኞችም ቢሆኑ ኋለኞችም ቢሆኑ*፡፡» ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 1፡16«*የሚያምኑትን ሰዎች ማዳን የሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል ነው*።» ከዚሁ ምዕራፍ 6፡16«*ለእግዚአብሔር ብትታዘዙ ፅድቅን ታገኛላችሁ*።» በዚህ ዙሪያ ኢየሱስ የፀናና ተመሳሳይ አቋም አለው። በማቴዎስ ወንጌል 24፡13«*እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 6፡13«*መንግስት ያንተ ናትና*።» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 5፡20 «*ፅድቃችሁ ከፃፎችና ከፈረሳውያን ፅድቅ ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም*።» አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 19፡13-14«*ሰዎች ሕፃናትን እንዲዳስሳቸውና እንዲጸልይቸው ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀመዛሙርቱ ግን ገሰጹአቸው። ነገር ግን ኢየሱስ ሕፃናትን ተውአቸው ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግስተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና*።» በሉቃስ ወንጌል 18፡ 18-27«*ከአለቆች አንዱ፡- ቸር መምህር ሆይ! የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው፡- ኢየሱስም ሰለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ቸር የለም። ትእዛዛቱን ታውቃለህ፡- አታመንዝር፣ አትግደል፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትና እናትህን አክብር አለው። እርሱም፡- ይህን ሁሉ ከሕፃንነቴ ጠብቄአለሁ አለ። ኢየሱስም ይህን ሰምቶ አንዲት ግን*

*ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ በሰማይ መዝገብ ታገኛለህ። መጥተህም ተከተለኝ አለው። እርሱ ግን ይህን ሰምቶ እጅግ ባለጠጋ ነበርና ብዙ አዘነ። ኢየሱስም ብዙ እንዳዘነ አይቶ፡- ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንገስት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል። ባለጠጎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊገባ ይቀላል። የሰሙትም ሰዎች እንግዲህ ማን ሊድን ይቻላል? አሉ። እርሱ ግን ኢየሱስ በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ።»* በማቴዎስ ወንጌል 18፡3«*እንደ ሕፃናት ካልተለወጣችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት ከቶ አትገቡም*» ብሏል።

# ምዕራፍ ስምንት

# የአምላክ ባሕሪያቶች

አምላክ ያልተወለደና እንዲሁም ሁሉን ነገር የፈጠረ ነው። አምላክ ሁሉንም ነገር አዋቂ፤ የወደፊቱን የሚያወቅ፤ እንደ ፍጥረታት የማይተኛ፤ የማያንቀላፋ፤ በማንም የማይፈተን፤ መኃሪ የሆነ፤ ጥፋተኛውንም የሚቀጣ፤ ዘላለማዊ ንጉስ፤ ሁሉን የሚገዛ፤ ሊሰገድለት የሚገባውና ባጠቃላይ የአምልኮ ዘርፎች በሙሉ በሙሉ ለእሱ የሚገቡ ናቸው። ለእያንዳንዳቸው መረጃ በመጥቀስ በቻልኩት መጠን እውነቱን ለእናንተ ለማድረስ እሞክራለሁ። በዚህ ርዕስ ላይ በዋናነት የእግዚአብሔር አምላክንና የኢየሱስን ነብይነትን የሚብራራ ነው። ሁለታቸውንም በንጽጽር መልኩ የምናያቸው ይሆናል።

## 1) አምላክ የሁሉ ነገር ፈጣሪና አስገኝ እንጂ ተፈጣሪ አይደለም።

ክርስቲያኖች አምላክ የተፈጠረና ከሰው የተገኘ ነው ብለው ያምናሉ። ያ ማለት ኢየሱስ ከማርያም መወለዱን አይክዱም። ያም ሆኖ ግን ፍጡር መሆኑን እያወቁ ዓለማትን ብቻውን ከፈጠረው ከአንድ አምላክ ጋር እኩል ተርታ ሲያሰልፉት ይታያል። አንድ አምላክ ሁሉነ ነገር የፈጠረ ለመሆኑ ለዋቢነት እንመልከት፡- በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 45፡1*«__ሠሪው እግዚአብሔር__ እንዲህ ይላል፡----»* ከዚሁ ምዕራፍ 45፡9*«__ከሠሪው ከእግዚአብሔር__ ጋር ለሚታገል ወዮለት!።»* ተጨማሪ አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 40፡28 ላይ ይመልከቱ። በመጽሐፈ መዝሙር 121፡2*«ዕርዳታዬ የሚመጠው __ሰማይና ምድርን ከፈጠረ ከእግዚአብሔር ነው__።»* ከዚሁ ምዕራፍ 24፡17፣ 81፡1፣ 89፡11፣ 90፡2፣ በመጽሐፈ መቃብያን ቀዳማይ 27፡1 በሌሎችም። ጳውሎስ ወደ ዕብራውያን ሰዎች በላከው መልእክት ላይ ሁሉን የሚገዛና የፈጠረ መመለክ ያለበት እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን ይገልፃል። ዕብራውያን 2፡10*«__ሁሉም ነገር ለእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው__።»* ከዚህ ምዕራፍ 3፡10 *«__ሁሉን ነገር የሠራ ግን እግዚአብሔር ነው__።»* ተጨማሪ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 1፡20 በሰፊው ይገኛል። ስለዚህ ሁሉን ነገር የሰራና የፈጠረ እግዚአብሔር መሆኑን እንጂ ሦስት አምላክ ወይንም ኢየሱስ ተጋሪ አለመሆኑን ተገልጿል። ሁሉም ነገር የፈጠረ አንድ አምላክ ብቻ ነው። በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡1 ሌሎች ምዕራፍችምና ቁጥሮችም አሉ። በተለይ

በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡11 ላይ ይህ ምዕራፍ ከስሙ እንደምንረዳው አንድ አምላክ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን በአጠቃላይ አለሙን በሙሉ አንድ እግዚአብሔር ብቻ እንደ ፈጠረ ይናገራል። ያ ማለት ኢየሱስን አይጨምርም። በትንቢ.ተ.ኤርሚያስ 10፡12 *«__እግዚአብሔር ግን ምድርን በኃይሉ ፈጠረ፤ ዓለሙንም በጥበቡ መሰረተ፤ ሰማያትንም በማስተዋሉ ዘረጋ።__»* አንዱ አምላክ እግዚአብሔር ብቻ ሰማይና ምድርን እንዲሁም ዓለሙን በሙሉ ከፈጠረ ኢየሱስ ምን ፈጠረ? ኢየሱስ ይህን መስፈርት ያሟላል ወይ? ሌላው ይቅርና እናቱ ማሪያምን ራሱን ኢየሱስን ጨምሮ ማን ፈጠራቸው? ይህን የተረዳ ክርስትያን ካለ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ሊያሳየኝና ሊነግረን ይገባል። ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው ተፀንሶ እንደ ተወለደ ሰው ሁሉ የሆነውን ሁሉ ሆኗል። እርሱም የዚህ ሰብዓዊ ባሕርያት ተጋሪ ነበር። ለምሳሌ፡- እንደ ተፀነሰ በማቴዎስ ወንጌል 1፡23፤ እንደ ተወለደ በሉቃስ ወንጌል 1፡31፤ እንደ ተገረዘ በሉቃስ ወንጌል 2፡21 ሌሎችም እንደ አደገ ምግብ እንደ በላ እንደ ጠጣ፤ አሁን ይህ አገላለጽ ለአምላክ ይገባዋል? አምላክ በሰው እጅ ሲገረዝ? መወለድ፣ መፀነስ፣ ማደግ እነዚህ ባሕሪያቶች ከሰብዓዊ ባሕሪ በፍፁም አይዘሉም። አምላክ ግን ከዚህ ሁሉ የፀዳ፣ የራቀና የማይገባው ነው። ለአምላክ ይበላል ይጠጣል ብሎ መግለጽ ክብሩን ማሳጣት እንጂ ሌላ አይደለም።

## 2) __አምላክ የማይደክመው፤ የማይታክተው ነው።__

አምላክ ከሰብዓዊ ባሕሪያቶች ከሚለይባቸው መካከል፡- የማይደክመው፤ የማይታክተው መሆኑ ነው። መድከም፣ መታከት፣ መተከዝ፣ ማዘን፣ መከፋት ወ.ዘ.ተ. እዚህ በሙሉ የፍጡራን የሰብዓዊ ባሕሪያቶች ናቸው። ምክንያቱም የሚደክም ካለ፤ ሌላ አድካሚ ኃይል አለ፤ የሚከፋ ካለ ሌላ አስከፊ ነገር አለ ማለት ነው። ፈጣሪን ግን ማን ያደክመዋል? ማን ያስተክዘዋል? ማን ያታክተዋል? እስኪ ራሳችን አምላክን ግምት ውስጥ በማስገባት አዕምሮአችን ተጠቅመን መልስ እንስጥ። ከዚያ ከክርስቲያንና ከሙስሊም ማን ለአምላክ ክብር እንደሚሰጥ መልሱን እናገኛለን። ለማንኛውም በዚህ ጉዳይ አምላክ ምን እንዳለ እንመልከት፡- በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 40፡28 *«__አላወቅህምን? አልሰማህምን? እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ ነው። አይደክምም፤ አይታክትም።__»* አምላክ እንደማይደክመው እንደማይታክተው ናግሯል። ኢየሱስ ግን በዮሐንስ

ወንጌል 4፡6 ‹‹*መንገድ ከመሄድ ደካም በጉድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት (6፡00) ነበር*።›› ከዚህ ላይ ጊዜው ተጠቅሷል፤ የአጋጣሚ ነገር ሆኖ ፀሐይ አድክሞት ይሆናል። ደከመ ሲባል አድካሚ ነገር አለ ያልኳችሁ ለዚህ ነው።

## 3) አምላክ የማያንቀላፋና የማይተኛ ነው።

በ1980 ዕትም በመጽሐፈ መዝሙር 121፡21‹‹*እግዚአብሔር የእስራኤል ጠባቂ ከቶ አያንቀላፋም፤ ፈፅሞ አይተኛም*።›› ዓለማትን የሚጠበቅና የሚቆጣጠር አምላክ ፈፅሞ አይተኛም፣ አያንቀላፋምም። ኢየሱስ ደግሞ እንዳንቀላፋ በሉቃስ ወንጌል 8፡23‹‹*ሲሄድ አንቀላፋ*።›› ተጨማሪ በማቴዎስ ወንጌል 8፡24‹‹*ኢየሱስ ግን ተኝቶ ነበር*።›› እርግጥ ነው ኢየሱስ የሰው ልጅ ስለሆነ ይደክማል፣ ያንቀላፋል፣ ይተኛል። ኢየሱስም የሰው ልጅ ስለሆነ ነው የደከመው፣ የተኛውና ያንቀላፋው።

## 4) አምላክ በማንም አይፈተንም።

በ1980 ዕትም በ1ኛ የያዕቆብ መልእክት 1፡13-14‹‹------ *እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና------*።›› እስኪ እናስታውል ፈጣሪ ተፈተነ ስንል የፈጠረውን ፍጡር እንደሚፈተነው ቀድሞ አያውቅም ነበር ማለት ነው? ማን ድፍረትና ብርታት አግኝቶ ነው ፈጣሪን የሚያክል ነገር የሚፈትን? ከፈጣሪ የበለጠ ፍጡር ፈጣሪን መፈተን የሚችል ኃይል ያለው ፍጡር አለን? መልሱን ፈጣሪ ይፈተናል የምትሉ ሰዎች መልሱልን። ኢየሱስ እንደ ተፈተነ በሉቃስ ወንጌል 1፡12-13‹‹*ኢየሱስም ወዲያውም በምድረ በዳም በመንፈስ ወደ ምድረ በዳም አወጣው፤ በምድረ በዳ በሰይጣን ሲፈተን አርባ ቀን ሰነበተ*።›› ኢየሱስ ፈጣሪ ከሆነ ሰይጣን እንደሚፈትነው አያውቅም ነበር? ለአርባ ቀን ያክል መጨዋቻ ሲያደርገው እንዴትስ ራስን ጣል ሲለው ሰነበተ? ፈጣሪ ግን ከዚህ ሁሉ የጠራ ነው።

## 5) አምላክ ሁሉን አሸናፊ፤ ብርቱና ኃያል ነው።

ከአምላክ ባሕሪያቶች ውስጥ ብርቱ፣ ኃያልና አሸናፊነት የአምላክ መለያ ናቸው። በመጽሐፈ መዝሙር 89፡8-9‹‹*ሁሉን የምትችል እግዚአብሔር ሆይ! እንደ አንተ ያለ ኃያል የሆነ የለም። እግዚአብሔር ሆይ! አንተ በሁሉ ነገር*

***እውነተኛ ነህ። አንተ የኃይለኛውን ባህር በስልጣንህ ታዛለህ፤ የማዕበሉንም ቁጣ ጸጥ ታደርጋለህ።***» ከዚሁ ምዕራፍ 89፡13«***ክንድህ እጅግ የበረታ ነው፤ ኃይልህም እጅግ ታላቅ ነው።***» ክርስቲያኖች መንፈስ ቅዱስን ሦስተኛ አምላክ ነው ብለው የሚያምኑበት ስለ አምላክ አሸናፊነት፣ ኃያልነትና ብርቱነቱን ሲገልጽ፡- በሉቃስ ወንጌል 1፡35«***መልአኩም እንዲህ ሲል መለሰ፡- ---የልዑል የእግዚአብሔር ኃይል በአንቺ ላይ ይሆናል***።» ከዚሁ ምዕራፍ 1፡37«***ለእግዚአብሔር እኮ የሚሳነው ነገር የለም።***» ኢየሱስ ስለ አምላክ ኃያልነት ሲናገር፡- በማርቆስ ወንጌል 12፡24 «***ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- እናንተ እንዲህ የምትሳሳቱት መጻሐፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል ባለማወቃችሁ አይደለም?***-----።» ኢየሱስ ራሱ ኃይል እንደሌለው ሲናገር፡- የ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30«***እኔ በራሴ ስልጣን ምንም ማድረግ አልችልም***» ብሏል። ኢየሱስ አምላክ ነው ከተባለ ለምን ምንም ማድረግ ተሳነው? ደካማ አምላክ አለ ሊባል ነው? ይህ ደግሞ ለአምላክ ፈፅሞ የማይገባ ነው።

## 6) አምላክ ሰው አይደለም፤ ሰውም አይመስልም።

አምላክ ከፈጠረው ፍጥረት ማንንም አይመስልም። ለእርሱም አምሳያ የለውም። በኦሪት.ዘኁሉቁ 23፡19«***ሐሰትም ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም፤ ይፀፀት ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።***» በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 15፡29 «***የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር አይዋሽም፣ አይፀፀትም፤ እርሱም ይፀፀት ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም።***» ተጨማሪ በትንቢተ.ሆሴዕ 11፡9«***እኔ በመካከላችሁ ያለው ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ የሰው ልጅ አይደለሁምና። እግዚአብሔር ይዋሽም ዘንድ የሰው ልጅ አይደለም***» ይላል። ስለዚህ አምላከን ሰው ብለው የዋሹት የሰው ልጆች ናቸው። አምላክ ግን አይዋሽም፤ አይፀፀትም፤ ይፀፀት ዘንድም የሰው ልጅ አይደለም። እርሱን የሚመስለው ፍጡር እንደሌለ በትንቢተ.ኢሳይያስና በሌሎች ምዕራፎች ተናግሯል። ኢየሱስ ደግሞ በተቃራኒ የሰው ልጅ ሆኖ ነው የመጣው። በጊዜ ያዩትና የነበሩ ሰዎች ከሰብዓዊነት ደረጃ አውጥተው የአምላክነትን ደረጃ አልሰጡትም። ኢየሱስ ስለ እራሱ ሰው መሆን ሲናገር በማቴዎስ ወንጌል 11፡19«***የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣና መጥቷል።***» በዮሐንስ ወንጌል 8፡40«***ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኳችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?***» ይላል። ለበለጠ መረጃ "ኢየሱስ

ማን ነው” ከሚለው ርዕስ በሰፊው ይመልከቱ። ለማጠቃለል ያክል በሁለት ምዕራፎች ኢየሱስ ስለ ራሱ ምን እንዳለ እናያለን። በማቴዎስ ወንጌል 10፡32 «*ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ፤ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ።*» ይህች ምዕራፍ ብቻ ለሚገነዘባት ስለ ኢየሱስ ማንነት ለማወቅ በቂ ማስረጃ ናት። ኢየሱስ “ሰው” ብሎ የሚመሰክርኝ አለ እንጂ አምላክ ብሎ ለሚመሰክርልኝ አላለም። ጳውሎስ ራሱ ስለ ኢየሱስ ሰው መሆን ሲናገር፡- በ1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5«*አንድ እግዚአብሔር አለና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው*» ብሏል።

## 7) አምላክ ሁሉን ነገር አዋቂ ነው።

በመጽሐፈ መዝሙር 11፡14«*እግዘአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ዙፋኑም በሰማይ ነው፤ በየትኛውም ከፍታ ያሉትን ሰዎች ሁሉ የመከታተል የሚሰሩትንም ሁሉ መርምሮ ያውቃል።*» አምላክ የፈጠራቸውን ፍጥረታት በሙሉ ያውቃል። ኢየሱስ ደግሞ ምንም ነገር እንደማያውቅ ሲናገር፡- በዮሐንስ ወንጌል 8፡26-28 «*የላከኝ እውነተኛ ነው፤ እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ። ስለ አብ እንደ ነገራቸውም አላስተዋሉም፤ ስለዚህ ኢየሱስ የሰውን ልጅ፤ ከፍ፣ ከፍ፣ ባደረጋችሁበት ጊዜ እኔ ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ በራሴ አንዳች ነገር እንደማላደርግ በዚያን ጊዜ (በትንሳኤ ቀን) ታውቃላችሁ።*» እንዲሁም ኢየሱስ ስለ ትንሳኤ ቀን መቸ እንደሚሆን አያውቅም። በማርቆስ ወንጌል 13፡32 «*ነገር ግን ከዚያች ሰዓት ከአብ በቀር ማንም የሚያውቅ የለም። የሰማይ መላአከትም (ገብርኤል) ቢሆን ወልድም (ኢየሱስ) ቢሆን የሚያውቅ የለም።*» በሉቃስ ወንጌል 8፡45«*ኢየሱስ የነካውን ሰው አላወቀም።*» እንዲሁም ኢየሱስ ምን ነገር እንደማያውቅ አምላክ እግዚአብሔር ግን ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ ሲያብራራ፡- በሉቃስ ወንጌል 16፡15«*እናንተ በሰዎች ላይ እራሳችሁን የምታመፃድቁ ናችሁ፤ እግዚአብሔር ግን የልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የተከበረ በእግዚአብሔር ዘንድ የረከሰ ነው*» በማለት ኢየሱስ የራሱን ሳይሆን የአምላኩን አዋቂነት ገልጿል።

## 8) አምላክ ኅያውና ዘላለማዊ ነው።

በትንቢተ.ኤርሚያስ 10፡10‹‹*እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱም ኅያው አምላክ ዘላለማዊ ንጉሥ ነው።*›› በትንቢተ.ሕዝቄኤል 14፡16 ‹‹*እግዚብሔር በኅያውነቴ እምላለሁ*›› ይላል። በመጽሐፈ መክብብ 12፡13 ‹‹*እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ነው።*›› ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቲዎስ 1፡17‹‹*ዘላለማዊ ንጉሥ ለሆነው ለማይሞተው ለአንዱ አምላክ ክብርና እና ምስጋና ይሁን።*›› ከዚህ ምዕራፍ 6፡16‹‹*እርሱ ብቻ የማይሞት ነው።*›› ተጨማሪ በ1ኛ ጴጥሮስ 1፡23‹‹*እኛ ከማይጠፋው፤ ኅያውና ዘላለማዊ ከሚሆን ከእግዚአብሔር ተወለድን።*›› አምላክ የማይሞት፤ ኅያውና ዘላለምዊ ነው። ኢየሱስ ደግሞ “ሞቷል” ትላላችሁ። ስለዚህ የማይሞተውንና ኅያው የሆነውን አምላክ ተቀበሉ። በኢየሱስ ሰብዓዊነትና ነብይነት እንዲሁም በእግዚአብሔር አምላክነት ያለው ልዩነት የጎላ ነው።

## 9) አምላክ ንግስናው ወሰን የለውም።

በመጽሐፈ መዝሙር 19፡6‹‹*ከአንዱ የሰማይ ዳርቻ ተነስቶ ወደ ሌላዉ ሰማይ ይነግሳል።ከእውቀቱም ኃይል ሊያመልጥ የሚችል ምንም ነገር የለም።*›› ከዚሁ ምዕራፍ እግዚአብሐር *ከአንዱ ሰማይ ሄዶ ሌላኛዉ ሰማይ ሥልጣን ይነግሳል።*›› ከዚሁ ምዕራፍ 11፡4‹‹*እግዚአብሔር በተቀደሰ መቅደሱ አለ፤ ዙፋኑም በሰማይ ነው፤ በየትኛውም ክፍል ያሉትን ሰዎች ሁሉ ይመለከታል፤ የሚሰሩትንም ሁሉ መርምሮ ያውቃል።*›› ሁሉን አዋቂና በዙፋኑ በስልጣኑ ወሰን የሌለው አንዱ እግዚአብሔር ብቻ ነው። ከዚሁ ምዕራፍ 10፡16‹‹*እግዚአብሔር ለዘላለም ንጉሥ ሁኖ ይኖራል።*›› ከዚሁ ምዕራፍ 22፡27-28‹‹*መንግስታት ሁሉ እግዚአብሔርን ያስታውሳሉ፤ በዓለም ዙሪያ ያሉት ሁሉ ወደ እርሱ ይመለሳሉ፤ የአረማውያን ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ፤ መንግስታዊ ሥልጣን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው።*›› ስለዚህ መንግስታትን ሁሉ የሚያስተዳድር እርሱ አንዱ አምላክ እግዚአብሔር ነው። ከዚሁ ምዕራፍ 24፡7-10‹‹*ታላቁ ንጉሥ እንዲገባ ደጃችንን እንክፈት፤ ይህ ታላቁ ንጉሥ ማን ነው? ብርቱና ኃያል የሆነዉ እግዚአብሔር ነው፤ በጦርነት አሸናፊ የሆነዉ እግዚአብሔር ነው፤ ይህ ታላቅ ንጉሥ የሠራዊት አምላክ እግዚአብሔር ነው።*›› ከዚሁ ምዕራፍ 29፡4-6፣ 29፡10፣ 32፡1-45፣ 41፡13፣ 47፡7፣ 47፡14፣ 50፡6-7፣ 83፡18 95፡3-6 እና 96፡3-6 ወደ ሌሎች ምዕራፍ እንሸጋገር

በትንቢተ.ኢሳይያስ 32-22‹‹***<u>እግዚአብሔር ዳኛችን ነው፤ እግዚአብሔር ሕግ ሰጪአችን ነው፤ እግዚአብሔር ንጉሣችን ነው፤ የሚያድነን እርሱ ነው</u>***፡፡›› ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 1፡20‹‹***<u>የእግዚአብሔር ባሕሪ ይኸውም ዘላለማዊ ኃይሉና አምላክነቱ እርሱ በፈጠራቸዉ ነገሮች ግልጽ ሆኖ ታይቷል</u>***፡፡›› ከዚህ ላይ አምላክ ዘላለማዊ ነው፡፡ ደግሞም ዘላለማዊነት የአምላክ ባሕሪ ነው፡፡ ስለዚህ ከጊዜ በኋላ የተፈጠረ ነገር ዘላለማዊ ነው አይባልም፡፡ ምክንያቱም ጊዜ ራሱ ፍጡር ነው፡፡ ኢየሱስ የውልደት ጊዜው የታወቀ ነው፡፡ የነበረበት ጊዜ የታወቀ ነው፡፡ በምድር ላይ 33 በምድር ላይ ሲያስተምር ቆይቷል፡፡ ስለዚህ ከጊዜ በኃላ የመጣን ፍጡር ዘላለማዊ ነው ማለት አያስኬድም፡፡ ሌላው ይቅርና በእድሜ እንኳ የሚበልጡት ሰዎች ስንትና ስንቶች አሉ፡፡ ለምሣሌ፡- ነብየ ኑህ 950 ዓመት ኖሯል፡፡ አስቡት እርሱ እንኳ ዘላለማዊ አምላክ ነው አልተባለም ከጊዜው መርዘም የተነሳ፡፡

## 10) <u>አምላክ ሁሉን የሚገዛ ነው፡፡</u>

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 10፡5‹‹***<u>እግዚአብሔር ሁሉን የሚገዛ አምላክ ነው</u>***፡፡›› በትንቢተ.ሐጌ 2፡10 ‹‹***<u>ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ነው</u>***፡፡›› ጳውሎስ በ1ኛ የያዕቆብ መልእክት 1፡9 ‹‹***<u>እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ</u>***፡፡›› ከዚህ ምዕራፍ 2፡6 ‹‹***<u>ለፈጠረ ጌታ ተገዙ</u>***፡፡›› እኛ ሙስሊሞች የምንላችሁ ይህንኑ ነው፡፡ ኢየሱስ ራሱ ለፈጠረው አምላክ ይገዛል፡፡ አንድም ቦታ ላይ እኔን ተገዙ ያለበት ቦታ የለም፡፡ ይልቁንም ኢየሱስ ሰይጣንን ለአምላክ እንዲሰግድ ሲያዘው በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና በሉቃስ ወንገል 4፡8‹‹***ኢየሱስ ለሰይጣኑ እንዲህ አለው፡-ሂድ ለጌታህ ለእርሱ ስገድ፤ እርሱን ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል አለው***፡፡›› ኢየሱስ ለእግዚአብሔር የማይገዛ የኃጢአት ባሪያ እንደሆነ በዮሐንስ ወንጌል ሲነግረን 8፡3 ‹‹***<u>እውነት እውነት እላችኋለሁ፡- ኃጢአት የሚሠራ የኃጢአት ባሪያ ነው</u>***፡፡›› ጳውሎስ ይህን ሐሳብ ገድፎ ሲናገር፡- በሮሜ መልእክት 8፡7‹‹***<u>ለኃጢአት የተገዛ አዕምሮ ከእግዚአብሔር ጋር ጠበኛ ነው፤ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛም፤ መገዛትም አይችልም</u>***፡፡›› ስለዚህ ኃጢአት የሚሰራ የኃጢአት ባሪያ ነው፡፡ ኢየሱስ እራሱ ለአምላኩ ይገዛል፡፡ የ1980 ዕትም በ1ኛ ቆረንቶስ 15፡28‹‹***<u>ሁሉም ከተገዛለት በኋላ እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ እንዲሆን ወልዱ (ኢየሱስ) ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ለእርሱ (ለእግዚአብሔር) ይገዛል</u>***፡፡›› ታዲያ ኢየሱስ ተገዙኝ ካላለና

ለአምላኩ ከተገዛ ምኑ ላይ ነው አምላክነቱ? ፈጣሪ ሆይ ፍጡርን ከመገዛት ጠብቀን፡

## 11) አምላክ በሁሉም ነገር፤ በስልጣን የበላይ ነው።

በመጽሐፈ መዝሙር 22፡27-29 ‹‹*መንግስት ሁሉ እግዚአብሔርን ያስታውሱታል፤ በዓለም ዙሪያ ያሉት ሁሉ ወደ እርሱ ይመለሳሉ፤ የአረማዊያን ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ፤ መንግስታዊ ሥልጣን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው፤ ስለዚህ መንግስት ሁሉ የሚያስተዳድረው እርሱ ነው። በዓለም የሚኖሩ ባለጸጋዎች ሁሉ በዓል በማድረግ ለእርሱ ይሰግዳሉ፤ ከሞት የማያመልጡት ሰብዓዊ ፍጡሮች ሁሉ በፊቱ ይንበረከካሉ።*›› በ1980 ዕትም ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር በ1ኛ ቆሮንቶስ 11፡3‹‹*በክርስቶስም ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር አብ መሆኑን እንድታውቁ እፈልጋለሁ*›› ይላል። እኛም ይህን እንድታውቁ እንፈልጋለን። ኢየሱስ እንደሆነ በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30‹‹*እኔ በራሴ ሥልጣን ምንም ማድረግ አልችልም*›› ብሏል።

## 12) አምላክ ሊሰገድለት የሚገባ ነው።

በመጽሐፈ መዝሙር 22፡27-29 ‹‹*የአረማውያን ነገዶች ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይሠግዳሉ። ከሞት የማያመልጡ ሰብዓዊ ፍጡሮች ሁሉ በፊቱ ይንበረከካሉ።*›› አልሐምዱሊላህ በዓለም ላይ ያሉ ሙስሊሞች በሙሉ ለአላህ ይሰግዳሉ። እናንተ ክርስቲያኖችስ ለማን ነው የምትሰግዱት? በዮሐንስ ራእይ 7፡11 ‹‹*በግንባራቸው ተደፍተው ለእግዚአብሔር ይሰግዳሉ።*›› ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 11፡16፣ 15፡3፣ 22፡9፣ በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 18፡39‹‹*ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ በግንባራቸው ተደፍተው አምላክ እግዚአብሔር እርሱ እውነተኛ ነው አሉ።*›› ወደ ሮሜ ሰዎች 14፡11‹‹*ጉልበት ሁሉ ለእግዚአብሔር ይንበረከካል።*›› እራሱ ጳውሎስ በ2ኛ ኤፌሶን 3፡14‹‹*እኔ ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እምበረከካለሁ።*›› በዮሐንስ ራእይ 15፡3-4‹‹*የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዲህ እያለ ይዘምር ነበር፡- "ሁሉን የምትችል ጌታ አምላክ ሆይ! የሕዝቦችህ ንጉሥ ሆይ! መንገድህ ትክክለኛ እውነት ነው፤ ጌታ ሆይ! አንተን የማይፈራ ማን ነውና ስምህንም የማያከብር ማን ነው? ምክንያቱም ቅዱስ አንተ ብቻ ነህ፤ ሕዝቦችህ ሁሉ መጥተው በፊትህ ይሰግዳሉ።"*›› ኢየሱስ ለሰይጣኑ ማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና ሉቃስ ወንጌል 4፡8

«*ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱን ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል አለው።*» ኢየሱስም ለአምላኩ እንደ ሰገደ በማቴዎስ ወንጌል 26፡39«*ጥቂት ወደ ፊት አለፍ አለና በፊቱ ወደቀና (ሰገደና) ሲጸልይ አባት ሆይ! ቢቻልህስ ይህቺ ጽዋ ከኔ ትለፍ አለ*።» ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ለአምላክ ይሰግድ ነበር? ለአምላክ ይሰገዳል እንጂ አምላክ ለማን ይሰግዳል? እኛ ሙስሊሞች ለአምላክ (ለአላህ) ስገዱ ማለታችን ጥፋት አይደለም። ኢየሱስ ለአምላኩ እንደሰግደው እናንተም ስገዱ። ይህ የዘወትር ምክራችን ነው።

## 13) አምላክ ሊመሰገን ይገባዋል።

ለአምላክ ከሚገቡ ነገሮች ምስጋና፤ ሁሉም ፍጥረታት አምላክ ለለገሳቸውና ለቸራቸው ፀጋ አምላካቸውን ማመስገን ግዴታቸው ነው። የሚመሰገነውም አንድ ፈጣሪ ብቻ ነው። መጽሐፈ መዝሙር 30፡12«*እንግዲህ ነፍሴ ታመሰግንህ ዝምም አትበል፤ እግዚአብሔር ሆይ! አንተ አምላኬ ነህ፤ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።*» ከዚህ ምዕራፍ 33፡2 «*እግዚአብሔርን አመስግኑት።*» ከዚሁ ምዕራፍ 52፡9፣ 57፡7፣ 63፡3-4፣ 67፡5፣ 68፡19፣ 69፡18፣ 69፡30፣ 69፡34፣ እና 89፡52 ተጨማሪ ---- በመጽሐፈ ነህምያ 9፡5 «*ከዘላለም እስከ ዘላለም የሚያኖረው አምላካችን አወደሱት (አመስግኑት)።*» በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 1፡48 «*ዓይኔ እንዲያይ የፈቀደ የእስራኤል አምላክ ምስጋና ይድረሰው።*» ከዚሁ ምዕራፍ 5፡7 «*ይህ ታላቅ ሕዝብ አንድ መሪ ለዳዊት ጥበበኛ ልጅ ሰጥቶታልና ዛሬ ምስጋና ለእግዚአብሔር ይገባ።*» ለአብነት ያክል ይህን ካየን አሁን ደግሞ ጳውሎስ ማን እንደሚመሰገን በሚከተሉት ምዕራፎች ተናግሯል። በዮሐንስ ራእይ 15፡3-4 «*የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዲህ በማለት ፈጣሪውን ያመሰግናል፡-"ሁሉን ቻይ ጌታ አምላክ ሆይ ሥራህ ታላቅ እና አስደናቂ ነው። የዘመናት ንጉሥ ሆይ! መንገድህና ጽድቅህ እውነት ነው፤ አንተን የማይፈራስ ማን ነው? የሚያከብርህስ ማን ነው? የጽድቅ ሥራህ ስለተገለጠ ሕዝቦች ሁሉ ይመጣሉ፤ በፊትህም ይሰግዳሉ።*»" በሐዋሪያት ሥራ 28፡15 «*ጳውሎስም ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።*» በዮሐንስ ራእይ 11፡17 «*ያለህና የነበርከ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ አመሰግንሃለሁ። ምክንያቱም አንተ ታላቅና ኃይልህን ይዘህ ነግሰሃልና።*» ወደ ሮሜ ሰዎች 1፡21 «*እግዚአብሔርን ቢያውቁትም እንኳ እንደ አምላክነቱ አላከበሩትም ምስጋናም አላቀረቡለትም።*» ከዚሁ ምዕራፍ 1፡25 «*የእግዚአብሔርን እውነት በሐሰት*

***ለወጡ፤ በፈጣሪ ፋንታ ፍጡር አመለኩ፤ እና ለእነሱም ፈጣሪ ለዘላለም የተመሰገነ ነው።»*** ኢየሱስም ፈጣሪውን አመስጋኝ ነበር። በሉቃስ ወንጌል 19፡38 ***«እግዚአብሔርንም እያከበሩ ኢየሱስን ተከትለው ሕዝቡም ሁሉ ይህን ሲያዩ እግዚአብሔርን አመሰገኑት። ድምፃቸውን ከፍ በማድረግ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።»*** በሉቃስ ወንጌል 5፡25***«የዳነው ሰውዬም እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ።»*** በሉቃስ ወንጌል 5፡26 ***«በዚያን ጊዜ ሁሉም በመገረም እግዚአብሔርን አመሰገነች።»*** ከዚህ ላይ ተአምር ያዩ ሰዎች ያመሰገኑት እግዚአብሔርን ነው። ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስን ባመሰገኑት ነበር። ተአምር ያላዩ ሰዎች ተነስተው ፍጡርን ማመስገናቸው ምክንያታቸው ምን ይሆን? ለነገሩ ጳውሎስ በፈጣሪ ፈንታ ፍጡር አመለኩ ብሏል። ኢየሱስ ራሱ አምላኩን ያመሰግናል። በዮሐንስ ወንጌል 11፡41 እንዲህ ማለት ፈጣሪውን ኢየሱስ ያመሰግናል። ***«አባት ሆይ! ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ፤ ይህን መናገሬ ግን በዚህ የቆሙ ሰዎች አንተ እንደላከኝ ያምኑ ዘንድ ነው።»*** (የ1980 ዕትም) ***«ነገር ግን ይህን ያልኩት እዚህ የቆሙት ሰዎች አንተ እንዳልከኝ እንዲያምኑ ብዬ ነው።»*** ኢየሱስ አምላክ ከሆነ ማንን ነው ያመሰገነው? አምላክ መመስገን ነው ያለበት ማመስገን?

## 14) አምላክ አዳኝ ነው።

በመጽሐፈ መዝሙር 3፡8 ***«ማዳን በእግዚአብሔር ነው፤ የማዳን ኃይል የእግዚአብሔር ነው።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 5፡1-5፣ 5፡11-5፣ 7፡10፣ 13፡5፣ 14፡6፣ 23፡1-6፣ 30፡1-24፣ 31፡10፣ 33፡20፣ 34፡2-4፣ 36፡6፣ 37፡38፣ 46፡1፣ 50፡23፣ 60፡17፣ 98፡13፣ 112፡1፣ 118፡4፣---በትንቢ.ተ.ዮናስ 2፡9***«ድኅነት ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።»*** በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 45፡5***«አዳኙ የእስራኤል አምላክ ሆይ!----።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 45፡17 ***«ከእግዚአብሔር ዘንድ ዘላለማዊ ደኅነት ይገኛል።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 45፡24***«ጽድቅና ኃይል በእግዚአብሔር ብቻ ነው።»*** በትንቢ.ተ.ኤርሚያስ 17፡7 ***«ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን፤ መታመኛውም በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 17፡14 ***«እግዚአብሔር ሆይ! ፈውሰኝ፤ እኔም እፈወሳለሁ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 31፡18 በሰቆቃው.ኤርሚያስ 3፡26***«ሰው የእግዚአብሔርን ማዳን ዝም ብሎ ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው።»*** በትንቢ.ተ.ኢዩኤል 2፡31-32***«ታላቁና የሚያስፈራው የእግዚአብሔር ቀን ከምጣቱ***

***በፊት ፀሐይ ትጨልማለች፤ ጨረቃም ወደ ደመና ትለወጣለች። የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ እርሱ ይድናል።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 4፡5«***አሕዛብ ሁሉ በአማልክቶቻቸው ስም ይሄዳሉ፤ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከዘላለም እስከ ዘላለም እንሄዳለን።»*** በትንቢተ.ሚልኪያስ 7፡7«***እኔ ግን እግዚአብሔርን ተስፋ አደርጋለሁ፤ አዳኜ የሆነውን አምላክ እጠይቃለሁ፤ እርሱም ይሰማኛል።»*** በትንቢተ.እንባቆም 3፡18«***እኔ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል፤ በደኅነቴ አምላክ ሐሴት አደርጋለሁ።»*** እስካሁን ባየናቸው ምዕራፍና ቁጥሮች አዳኝ ማን እንደ ሆነ በግልጽ ቋንቋ በሚገባን መልኩ ተቀምጧል። እርሱም እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ። ጳውሎስ ደግሞ ማን እንደሚያድን ወደ ሮሜ ሰዎች 1፡16«***የሚያምኑ ሰዎች ሁሉ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር ነው።»*** የሐዋሪያት ሥራ 2፡21«***የእግዚአብሔርን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል።»*** ከዚህ ላይ ትኩረት አድርጉ፤ለሚያምኑት ሰዎች ሁሉ ነው የተባለው እንጂ ለኃጢአታችሁ አይደለም። ሲቀጥል ደግሞ ማዳን የሚችለው እግዚአብሔር መሆኑ ተገልጿል። ታዲያ የኢየሱስን ስም የሚጠራ መች አለ? ኢየሱስ ሌሎችን ሰዎች ሊያድን ቀርቶ ራሱን እንኳን ማዳን አይችልም። በማቴዎስ ወንጌል 8፡20«***ኢየሱስ ለቀበሮዎች ጉድጓድ፤ ለሰማይ ወፎች መስፈሪያ አላቸው፤ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም።»*** ለምን ይህን አለ ብትሉኝ በዮሐንስ ወንጌል መልስ ይሰጠናል። 5፡8 «***እኔ ምንም ማድረግ አልችልም እንደሰማሁ እፈርዳለሁ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና»*** ብሏል። ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ እኔ አድናችኃለሁ ይል ነበር። ነገር ግን እሱም መዳን ስለፈለገ«***የሰው ልጅ ራሱን የሚያስጠጋበት የለውም»*** ብሏል። ከዚህ ላይ ኢየሱስ ድሃ ነው ማለት ነው? ሲቀጥል ማን ማዳን እንደሚችል በሉቃስ ወንጌል 3፡6«***የሰው ዘር ሁሉ የእግዚአብሔርን ማዳን ያያሉ።»*** የሚያድነው ኢየሱስ አይደለም።

## 15) አምላክ ሊመለክ ይገባዋል።

በመጽሐፈ ኢያሱ 24፡14«***እግዚአብሔርን ብቻ አምልኩ።»*** የሚመለከው ማን እንደ ሆነ ምዕራፍ ግልጽ ያደርግልናል። ከዚህ ምዕራፍ 24፡15«***የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔንና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።»*** አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 24፡18«***ሕዝቦቹም እንዲህ አሉ እኛም እግዚአብሔርን እናመልካለን።»*** ድንገት የምታመልኩትን ካላወቃችሁና ሌላን አምላክ ካመለካችሁ

ኢያሱ እንዳለው እግዚአብሔርን አምልኩ በማለት እንደመከራችሁ እኛ ሙስሊሞችም የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ አላህ (ሱ.ወ) አምላክ በማለት ቀና ምክራችንን እንመክራችኋለን። ኢያሱ ባስተማራቸው መሰረት የሕዝቦች መልስ "ጌታ አምላካችን እግዚአብሔር ነው" አሉ። የእናንተም መልስ ይህ እንዲሆን እንመኛለን። ምክንያቱም ከአንድ አምላክ ውጪ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም። በ2ኛ በመጽሐፈ ሳሙኤል 7፡22«***ልዑል እግዚአብሔር እንዴት ታላቅ ነህ! ከቶ የሚመሰገን ማንም የለም። በጆሮአችን እንደሰማነው ሁሉ ከአንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም።***» በየትኛው የክርስትና ክፍል ያለ ሰው ይህን ጥቅስ ልብ ሊለው ይገባል። ኦርቶዶክስ በቀላሉ አርባ አራት ታቦትን ያመልካል። እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ከሄድን ግን ከአንድ አምላክ ውጭ እንዲመለክ አያዝም። ለምን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለን ባዕድ አማልዕክት ትገዛላችሁ? አርባ አራት ታቦቶች ሁሉ የዓለም ፈጣሪ ናቸውን? ክርስቲያኖች ሰይጣን ያታለላችሁ ጊዜ ይበቃል ተመለሱ። እናንተን እንዲሁም ሁሉን ነገር የፈጠረን ጌታ አምልኩ። ቄሶችም ቢሆን ይህን ጥቅስ ሳያውቁት አይቀርምና ልታስተምሯቸውና እንናንተም ልትገነዘቡት ይገባል። ***(ኢት አምልኩ ባይደ አማልክትን ዘኢንበሌ)*** ይህ ማለት «***ከእኔ በስተቀር ሌላ አምላክ ኢታምልኩ ነው***» የሚለው እንጂ ሦስት አምላክ ወይንም አርባ አራት ታቦትን አያመለከትም። በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 12፡24«***ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍፁም ልባችሁ በታማኝነት አምልኩት።***» መመለክ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ጳውሎስም ያስተምራል። በያዕቁብ መልእክት 1፡27«***ንጹህ የሆነ ነውር የሌለበት አምልኮ ለእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነው።***» ኢየሱስ ሰይጣን ለኔ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ ሐብት እሰጥሃለሁ ሲለው በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና በሉቃስ ወንጌል 4፡8«***ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለው፡- ሂድ ለእግዚአብሔር ስገድ፤ እርሱ ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል አለው።***» ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ለኔ ስገድልኝ እኔን ብቻ አምልክ ባለው ነበር።

## 16) አምላክ ሁሉን ቻይ ነው።

አምላክ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው የሚሳነው አንድም ነገር የለም። በመጽሐፈ ኢዮብ 37፡22-23«***ሁሉን የሚችል አምላክ ከአዕምሮአችን በላይ ነው። በኃይልና በፍርድ ቀን ታላቅ ነው።***» በዮሐንስ ራእይ 11፡17«***ያለህና የነበርክ ሁሉን ቻይ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን። ምክንያቱም አንተ***

*ታላቅና ኃይልህን ይዘህ ነግሰሃል።»* ከዚህ ምዕራፍ 15፡3«*የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ እንዲህ በማለት ይዘምራል፡- ሁሉን ቻይ ጌታ ሆይ! አምላክ ሆይ! ሥራህ ታላቅና አስደናቂ ነው።»* ኢየሱስም አምላክ ሁሉን እንደሚችልና ራሱ ደግሞ ምንም ነገር እንደማይችል ሲነግረን፡- በሉቃስ ወንጌል 18፡27«*ኢየሱስ በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ይቻላል።»* ኢየሱስ ራሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 5፡30«*እኔ በራሴ ሥልጣን ምንም ማድረግ አይቻለኝም*» ብሏል።

## 17) አምላክ ሊለመን ይገበዋል፡፡

አምላክ ለሁሉም ፍጥረታት እንደፈለጉት ስለሚሰጥ ለእኛም የምንፈልገውን ነገር ከእሱ ለማግኘት እርሱን ብቻ መለመን አለብን። በትንቢተ.ሚልኪያስ 1፡9 «*አሁን ግን እንዲራራልን እግዚአብሔርን ለምኑ።»* በትንቢተ.ዘካሪያስ 8፡21 «*እግዚአብሔርን ለመለመን እግዚአብሔር ጸባዖትን ለመፈለግ፤ ኑ፤ በፍጥነት እንሂድ፤ እኔም እሄዳለሁ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡22«*ብዙ ሕዝብና ኃያላን መንግስትም እግዚአብሔርን ለመፈለግና ለመለመን ወደ ኢየሩሳሌም ይመጣሉ።»* በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 3፡5«*እንዲሰጥህ የምትፈልገውን ለምን አለው።»* ከዚሁ ምዕራፍ 3፡10«*ሰለምን ይህን በመለመኑ ደስ አለው።»* ኢየሱስ ማን መለመን እንዳለበት በማቴዎስ ወንጌል 20፡20-23«*የዘብዲዎስ ልጆች እናት ኢየሱስን ጠየቀች እርሱም ምን ትፈልጊያለሽ አላት? እነዚህ ሁለት ልጆች አንዱ በቀኝህ አንዱ በግራህ በመንግስትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው። ኢየሱስ ግን መልሶ የምትለምኑትን አታውቁም አላት። እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠምቀውን ጥምቀት ትችላላችሁ? አለ። እንችላለን አሉት፤ እርሱም ጽዋዬን ትጠጣላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን በአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም።»* ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ የተለመነው ይሰጥ ነበር።

## 18) ወደ አምላክ መጸለይ ይገባል።

አምላክ ጸሎትን ሰሚና ተቀባይ ነው። የምንጸል የውም ለአንድ አምላክ ብቻ ነው። በመጽሐፈ መዝሙር 63፡4«*ለጸሎትም እጆቼን ወደ አንተ እዘረጋለሁ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 65፡2«*አንተ የሰዎችን ጸሎት ስለምትሰማ ሰዎች ወደ አንተ*

***ይመጣሉ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 65፡5 ***«ጸሎታቸውን ሰምተህ ድል ታጎናጽፋለህ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 66፡17***«ድምጼን ከፍ አድርጌ ወደ እርሱ ጸለይሁ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 69፡16***«እግዚአብሔር ሆይ! ቸርነት በተሞላበት ፍቅርህ ጸሎቴን ሰማ፤ በታላቅ ምህረት ወደኔ ተመለሰ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 77፡2 ***«በችግር ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ፤ ሌሊቱን በሙሉ ያለ እረፍት እጆቼን ወደ እግዚአብሔር እጸልያለሁ።»*** ኢየሱስ ወደ አምላኩ ይጸልይ እንደ ነበርና የሚጸለየው ለእግዚአብሔር እንደ ሆነ አስተምሯል። በማርቆስ ወንጌል 11፡25 ***«ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲልላችሁ በማንም ላይ አንዳች ነገር ቢኖርባችሁ ይቅር በሉ።»*** ከዚህ ላይ የምንረዳው ነገር አለ። ይኸውም ኃጢአትን ይቅር የሚለው ኢየሱስ ሳይሆን የኢየሱስ አምላክ ነው። ጳውሎስ ኢየሱስ ወደ አምላክ መጸለዩን ወደ ዕብራዊያን ሰዎች በላከው መልእክት 5፡7***«እርሱ (ኢየሱስ) በሥጋው ወራት ከሞት ሊድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርን ስለመፍራቱ ተሰማለት»*** ይላል። ኢየሱስ ራሱ ጸሎት እንዳደረገና አምላኩን ይፈራ ነበር። በሉቃስ ወንጌል 6፡12***«ከዚያ በኋላ አንድ ቀን ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጣ፤ እዚያ ሌሊቱን ሙሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 22፡39-42***«----ከዚ በኋላ የድንጋይ ውርወራ ያህል ከእነርሱ ራቅ ብሎ ሄደ፤ ተንበርክኮም እንዲህ ሲል ጸለየ፤ "አባት ሆይ! ፈቃድህ ቢሆን ይህን የመከራ ጽዋ ከእኔ አርቅልኝ፤ ግን የአንተ ፈቃድ ይሁን እንጂ የእኔ ፈቃድ አይሁን።»"*** በማቴዎስ ወንጌል 14፡23***«ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ለመጸለይ ብቻውን ወደ አንድ ተራራ ላይ ወጣ።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 18፡18-19***«"እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ በምድር የምታስሩት በሰማይ የታሰረ ይሆናል፤ በምድር የምትፈቱትም በሰማይ የተፈታ ይሆናል። ደግሞም እላችኋለሁ ከእናንተ ሁለቱ በምድር ላይ ማናቸውንም ነገር ለመለመን በጸሎት ቢተባበሩ በሰማይ ያለው አባቴ ይፈጽምላቸዋል።"»***

## 19) አምላክ ሊፈራ ይገበዋል።

አምላክ መፈራት ያለበት ኃያል ንጉስ ነው። ስለዚህ ፍጥረታት በሙሉ እርሱን ብቻ መፍራት አለባቸው። በኦሪት.ዘፀአት 14፡13***«አትፍሩ ዛሬ የምታዩአቸው ግብፃውያን ለዘላለም አታዩአቸውምና።»*** በመጽሐፈ ምሣሌ 3፡7***«በራስህ***

*አስተያየት ጠቢብ ነኝ አትበል፤ እግዚአብሔርን ፍራ፤ ከክፍት ምዕራቅ፤ እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ነው።»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡13 «*እግዚአብሔርን መፍራት ክፋትን መጥላት ነው።»* ከዚሁ ምዕራፍ 10፡27 «*እግዚአብሔርን መፍራት እድሜን ያረዝማል፤ የክፉዎች እድሜ ግን በአጭር ይቀጫል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 14፡26-27«*እግዚአብሔርን የሚፈራ ጥኑ አንባ አለው፤ ልጆቹም መጠጊያ ይኖራቸዋል። እግዚአብሔርን መፍራት ሕይወት ምንጭ ነው። ሰውን ከሞት መጥመድ ያድነዋል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 15፡16 «*እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር ያለ ጥቂት ነገር ሁከት ካለበት ትልቅ ሐብት ይበልጣል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 22፡4-5«*ትሕትናና እግዚአብሔርን መፍራት ሐብት፣ ንብረትን ያስገኛል። በክፉዎች መንገድ ላይ እሾህና መጥመድ አለ፤ ነፍሱን የመጠብቅ ግን ከእነዚህ ይርቃል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 38፡14 «*እግዚአብሔርን ዘወትር የሚፈራ ሰው ብሩክ ነው፤ ልቡን የሚያደነድን ግን በመከራ ላይ ይወድቃል።»* በመጽሐፈ መዝሙር 19፡9«*እግዚአብሔርን መፍራት ንጹሕ ነው ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 33፡8«*ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍረው፤ በዓለም የሚኖሩ ሕዝብ ሁሉ በፊቱ ይንቀጥቀጡ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 76፡11«*መፈራት ለሚገባው ለእግዚአብሔር ለአምላካችሁ የተሳላችሁትን ሥለት ፈፅሙ።»* በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 12፡24‹ ‹*ብቻ እግዚአብሔርን ፍሩ፤ በፍፁም ልባችሁ በታማኝነት አምልኩት።»* በትንቢተ.ኤርሚያስ 10፡2-5«*እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡-የአሕዛብን መንገድ አትማሩ፤ ከሰማይ ምልክትም አትፍሩ፤ አሕዛብ ይፈሩታልና የአሕዛብ ልማድ ከንቱ ነውና፤ ዛፍ ከዱር ይቆረጣል፤ በሠራተኛውም እጅ በመጥረቢያ ይሰራል። በብርና በወርቅ ያስጌጡታል፤ እንዳይናወጥም በችንካርና በመዶሻ ይቸነክሩታል። እንደ ተቀረጸ አመድ ናቸው፤ እነርሱም አይናገሩም፤ መራመድም አይቻላቸውምና ይሸከሙአቸዋል። ክፉ መስራትም አይቻላቸውምና ደግሞም መልካም ስራ ይሠሩ ዘንድ አይቻላቸውምና አትፍሩአቸው።»* በመጽሐፈ ሲራክ 1፡13«*እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ፍፃሜው ያምራል፤ በሚሞትበትም ቀን ይከበራል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 2፡1-3«*እግዚአብሔርን የሚፈሩ ቃሉን አይረሱም፤ የሚወዱትም ትእዛዙንና መንገዱን ይጠብቃሉ። እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች ፍቃዱን ይሻሉ፤ የሚወዱትም በሕጉ ይረካሉ፤ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ልቦናቸውን ያዘጋጃሉ፤ በፊቱም ሰውነታቸውን ያዋርዳሉ።»* ኢየሱስ ማንን መፍራት እንዳለብን ሲነግረን፡- በማቴዎስ ወንጌል 10፡28«*ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል*

*የማይችሉትን አትፍሩ፤ ይልቁንስ ነፍስንም፣ ሥጋንም፣ በገሃነም ሊያጠፋ የሚችለውን አምላክ ፍሩ*» በማለት የሚፈራው አምላክ እንጂ ኢየሱስን እንዳል ሆነ እራሱ ይነግረናል። በተጨማሪ በሉቃስ ወንጌል 1፡50«*እግዚአብሔርን ለሚፈሩ ሰዎች ሁሉ ከትውልድ እስከ ትውልድ ምህረቱን ያደርጋል።*» ኢየሱስም እንደ ማንኛውም ፍጡር እግዚአብሔር አምላክን ይፈራ ነበር። ጳውሎስ ወደ ዕብራዊያን ሰዎች በላከው መልእክት 5፡7«***እርሱ (ኢየሱስ) በሥጋው ወራት ከሞት ሊድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትና ምልጃን አቀረበ፤ እግዚአብሔርን ስለ መፍራቱ ተሰማለት***» ይላል።

## 20) በአንድ አምላክ መታመን አለብን።

ፍጥረታትን በሙሉ አንድ አምላክ ስለ ፈጠራቸው እነሱም በአንድ አምላክ መታመን አለባቸው። አምላክም በዚህ ዙሪያ የሚለን ነገር አለ። በመጽሐፈ መዝሙር 84፡12«*ሁሉን የምትችል አምላክ ሆይ! በአንተ የሚታመኑ የታደሉ ናቸው።*» በትንቢተ.ኤርሚያስ 17፡5-7«*በሰው የሚታመን በሥጋ ለባሽ የሚመካ ልቡንም ከእግዚአብሔር የሚያርቅ የተረገመ ነው።ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚታመን መታመኛውም እግዚአብሔር የሆነ ሰው ብሩክ ነው።*» በትንቢተ.ናሆም 1፡7«*እግዚአብሔር መልካም ነው፤ በጭንቅ ጊዜ መሸሸጊያ ነው፤ ለሚያምኑበት ይጠነቀቅላቸዋል።*»

## 21) መንግስተ ሰማያት የሚያስገባው ኢየሱስ ሳይሆን የኢየሱስ አምላክ ነው።

ሁሉም ክርስቲኖች ገነት በኢየሱስ ነው ብለው ያምናሉ። ነገረ ግን ኢየሱስ ራሱ መንግስተ ሰማያት ገነት መግባት ይፈልጋል። በማቴዎስ ወንጌል 20፡20-23 «***የዘብዲዎስ ልጆች እናት ኢየሱስን ጠየቀች እርሱም ምን ትፈልጊያለሽ አላት? እነዚህ ሁለት ልጆች አንዱ በቀኝህ አንዱ በግራህ በመንግስትህ እንዲቀመጡ አዝዝ አለችው። ኢየሱስ ግን መልሶ የምትለምኑትን አታውቁም አላት። እኔ ልጣጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠምቀውን ጥምቀት ትችላላችሁ? አለ። እንችላለን አሉት፤ እርሱም ጽዋዬን ትጠጣላችሁ፤ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን በአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም።***» ስለዚህ

ኢየሱስ መንግስተ ሰማያት የሚያስገባ ካልሆነ ልፋታችሁ ከንቱ ነው ማለት ነው። ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ የተጠየቀውን ገነት እኔ አስገባሃለሁ ባለ ነበር። ልፋታችሁ ከንቱ እንዳይሆን መንግስተ ሰማያት እንድትገቡ የኢየሱስን እንዲሁም የሁላችን አምላክ የሆነውን ተገዙ። መንግስተ ሰማያት በሰላም ትገባላችሁ። ኢየሱስ ራሱ መንግስተ ሰማያት መግባት ይፈልጋል።በማቴዎሰ ወንጌል 26፡29 ‹‹***በአባቴ መንግስት (ገነት) አዲሱን የወይን ፍሬ ጭማቂ ከእናንተ ጋር እስከምጠጣበት ቀን ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ የወይን ጭማቂ ዳግመኛ አልጠጣም እላችኋለሁ***።›› ተጨማሪ በሉቃስ ወንጌል 22፡18‹‹***ኢየሱስ ገነት ይገባል***›› ያውም ከእኛ ጋር። ኢየሱስ አምላክ ነው የምትሉን ሰዎች አምላክ ገነት ያስገባል? ወይንስ ይገባል? ለነገሩ ገነት ቢገባ አይደንቅም ገና በዚህ በምድራዊ ሕይወት ሳለ ሲበላና ሲጠጣ ነበር። ጳውሎስ በ1ኛ ቆረንቶስ 4፡5 ‹‹***በዚያን ጊዜ እያንዳንዱ ሰው ደመወዙን ከእግዚአብሔር ይቀበላል***።›› ስለዚህ ደመወዝ የሚገኘው ከኢየሱስ ሳይሆን ከእግዚአብሔር አምላክ ብቻ ነው።

## 22) ሁላችንም ወደ አምላክ መጮህ አለብን ከጭንቅ ለመገላገል።

አምላክ ከሁሉም የምድራዊም ሆነ ከሲዖል ጭንቀት እንዲያነሳልን ሁላችንም ወደ አምላክ መጮህ አለብን። ታላላቅ የአምላክ ነብያት እንኳ ሳይቀሩ ወደ አምላክ ይጮሁ ነበር። ሰለሞን በ1ኛ መጽሐፍ ሳሙኤል 12፡17‹‹***እኔ ነጎድጓድ ዝናብ እንደሚጥል ወደ እግዚአብሔር እጮኻለሁ***።›› ከዚሁ ምዕራፍ 12፡23-25፣ በመጽሐፈ ነህምያ 9፡4‹‹***ወደ አምላካቸው ወደ እግዚአብሔርም በታላቅ ጮኹ***።›› በመጽሐፈ ኢዮብ 30፡20‹‹***እግዚአብሔር ሆይ! ወደ አንተ ጮኹ***።›› ከዚህ ምዕራፍ 30፡24፣ በመጽሐፈ መዝሙር 3፡4‹‹***ወደ እግዚአብሔር ድምፄን ከፍ አድርጌ እጮኻለሁ***።›› ከዚህ ላይ እንደምንረዳው ነብያት በጭንቅ ጊዜ ወደ አምላክ ጮኸዋል፣እናንተስ ለማን ነው የምትጮኹት? ኢየሱስ ሳይቀር ለአምላኩ ከጭንቅ እንዲገላግለው ጮኋል። በማቴዎስ ወንጌል 27፡46‹‹***ኢየሱስ በዘጠኝ ሰዓት (9፡00) ገዳማ ድምጹን ከፍ አድርጎ ኤሎሄ ኤሎሄ ለማ ሰበቀታኒ እያለ በታላቅ ድምጽ ጮኸ***።›› ትርጉም ‹አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ› በማለት አምላኩን ተማፅኗል። ኢየሱሰ አምላክ ቢሆን ኖሮ ተጨንቆ ባልጮኸ ነበር። ተነሱ ክርስቲያች እንደ ኢየሱስ ወደ አምላካችሁ ወደ አላህ ጩኹ።

## 23) ሁሉንም ነብያቶች በአንድ አምላክ ያምናሉ።

ሁሉም ነብያት አምላክ አንድ መሆኑን ብቻ ነው የሚያምኑትና ያስተማሩት። በትንቢተ.ዘካሪያስ 14፡9«***እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ይነግሳል፤ በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስሙም አንድ ብቻ ይሆናል***።» በኦሪት.ዘዳግም 6፡4 «***እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው***።» በመጽሐፈ መዝሙር 104፡1 «***ነፍሴ ሆይ! እግዚአብሔርን ባርኪ፤ አቤቱ አምላኬ ብቻህን ታላቅ ነህና***።» ከዚሁ ምዕራፍ 105፡7«***እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው***።» በመጽሐፈ ሳሙኤል 2፡2«***እንደ እግዚአብሔር ታላቅ የለም፤ እንደ አምላካችን ፃዲቅ የለም፤ ከንተ በቀር ቅዱስ የለም***።» ጳውሎስ 1ኛ ቆረንቶስ 8፡5-7«......***አንድ አምላክ አብ ነው***።» ከዚሁ ምዕራፍ 1ኛ ቆረንቶስ 2፡5«***አንድ አግዚአብሔር አለና***--------።» ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል 12፡29«***እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ አምላክ ነው***» በማለት አስተምሯል።

## 24) እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር እንጂ ኢየሱስ አይደለም።!!!

በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 18፡39«***እግዚአብሔር እሱ እውነተኛ አምላክ ነው***።» በመጽሐፈ መዝሙር 83፡18«***ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ በምድር ሁሉ አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንክ ይወቁ***።» እውነተኛ አምላክ እግዚአብሔር እንደሆነ እወቁ። በመጽሐፈ መዝሙር 105፡7«***እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው***።» በትንቢተ.ሐጌ 2፡10«***ሁሉን የሚገዛ እግዚአብሔር ነው***።» እናንተም በ1ኛ የያዕቆብ መልእክት 1፡9«***እራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ***።» ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 7፡21-23«***በሰማያት ያለው የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፤ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም***» ብሏል። ኢየሱስ አውነተኛ አምላክ ሳይሆን እውነተኛ ነብይ ነው። በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41 «***እናንተን የሚቀበል፤ እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል፤ የላከኝን ይቀበላል። ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይ ዋጋ ያገኛል። ፃድቅንም በፃድቅ ስም የሚቀል የፃድቅን ዋጋ ያገኛል***።» ስለዚህ ኢየሱስ ነብይ ነው።

## 25) <u>የዓለማት ጌታ አንድ (1) ብቻ እንጂ ሦስት (3) አምላክ አይደለም።!!!</u>

ሁሉም ነብያቶች ስለ አንድ አምላክ አስተምረዋል፤ በአንድ አምላክም ያምናሉ። ሦስት አምላክ የሚባል በመጽሐፍ ቅዱስ በአንድም ቦታ የለም። ከዚህ ቀጥሉ የተዘረዘሩትን ምዕራፍና ቁጥሮች ተመልከትን ከስህተታችን እንመለስ። አባይን በጭልፋ እንዲሉ ለአብነት ያክል ስለ አምላክ አንድነት የሚከተሉትን ምዕራፎች የሚያሰጨብጡን ቁም ነገር አለ። በመጽሐፈ መዝሙር 71፡19«*<u>አምላኬ ሆይ! አንተን የሚመስል ማንም የለም።</u>*» ከዚሁ ምዕራፍ 83፡18«*<u>ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ በምድር ሁሉ ይነግሳል፤ አንተ ብቻ ልኡል እንደ ሆንክ ይወቁ።</u>*» ከዚሁ ምዕራፍ 86፡10«*<u>አቤቱ አንተ ድንቅ የምታደርግ አንተ ብቻ ታልቅና አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህ።</u>*» ከዚሁ ምዕራፍ 104፡1«*<u>ነፍሴ ሆይ! እግዚአብሔርን ባርኪ፤ አቤቱ አምላኬ ብቻህን ታላቅ ነህና።</u>*» ከዚሁ ምዕራፍ 135፡5«*<u>እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም።</u>*» በኦሪት.ዘዳግም 4፡25‹‹*<u>አምላካችሁ እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር የተስማማውን ቃል ኪዳን እንዳትረሱ፤ አምላክህም እግዚአብሔር</u> የተከለከለውን የማናቸውንም ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል አታድርጉ፤ <u>አምላክህ እግዚአብሔር ቀናተኛ አምላክ ነውና።</u>*» ከዚሁ ምዕራፍ 6፡4-9«*<u>እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።</u> አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ፤ በፍፁም ነፍስህና ኃይልህም ውደድ።*» በመጽሐፈ ነገሥት 3፡22«*<u>የእስራኤል አምላክ አባቴ! በላይ በሰማይም በታች በምድርም አንተን የሚመስል አምላክ የለም።</u>*» በመጽሐፈ መክብብ 12፡13 «*<u>እግዚአብሔር የዘላለም አምላክ የምድር ዳርቻ ነው።</u>*» በኦሪት.ዘፀአት 18፡11 «*<u>እግዚአብሔር ከአማልክት ሁሉ እንደሚበልጥ አሁን አወኩ።</u>*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 43፡10-11«*<u>እኔም እንደሆንኩ ታስታውሉ ዘንድ እናንተን የመረጥኩትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር። ከእኔ በፊት አምላክ አልተሰራም፤ ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ፣ እኔ፣ እግዚአብሔርነኝ፤ ከእኔ ሌላ የሚያድን የለም።</u>*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 44፡6«....*<u>እኔም ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኋለኛ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም።</u>*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 45፡5-6«*<u>እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔ ሌላ ማንም የለም። ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤ በፀሐይ በውጫና በምዕራቡ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስጠነቀቅኩ፤ አንተ ግን አላውከኝም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ ማንም የለም።</u>*»

በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 45፡18«***ሰማያትን የፈጠረ እግዚአብሔር እርሱ ምድርን የሠራና ያደረገ ያጸናትም መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላል፦እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም።***» በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 46፡9«***እኔ አምላክ ነኝና፤ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።***» በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 48፡12«---***እኔ ነኝ እኔም ፊተኛው ነኝ፤ እኔም ኋለኛው ነኝ፤ እጄም ምድርን መሰርታለች፤ ቀኝም ሰማያትን ዘርግታለች።***» ለአብነት ያክል፦ በትንቢ.ተ.ኢይሳያስ 44፡6 ላይ «---***እኔም ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኋለኛ ነኝ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም***» ብሏል። ታዲያ እንዴት ሦስት አምላክ ይባላል? ጳውሎስ በ1ኛ ቆረንቶስ 8፡6«***አንድ አምላክ አብ ነው።***» በድጋሜ በ1ኛ ጢሞቲዎስ 1፡17«----***ብቻውን አምላክ ለሚሆን፤ ለማይታየውና ለማይጠፋው ለዘመናት ምስጋናና ክብር ለሚሆን ለዘላለም ይሁን።***» ከዚሁ ምዕራፍ 2፡5«***አንድ አምላክ አለና፤ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።***» ኢየሱስ በሚከተሉት ምዕራፎች አምላክ አንድ መሆኑን ተናግሯል። በማቴዎስ ወንጌል 17፡3«***አንተ ብቻ እውነተኛ አምላክ የሆንከውንና የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።***» በሉቃስ ወንጌል 18፡19«***ስለምን ቸር ትለኛለህ ከአንዱ አምላክ በቀር ቸር የለም።***» የማጠቃለያ ንግግሩ በማቴዎስ ወንጌል 12፡29 «***ከትእዛዛት ሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ፦ እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።***» ከላይ ባየናቸው ምዕራፍና ቁጥሮች አምላክ አንድና አንድ ብቻ ነው። ነገር ግን ክርስቲያኖች እንደ ሸቀጥ እቃ አምላክን እየጨመሩ መጥተዋል። መጽሐፍ ቅዱስን ተንተርሰው ሳይሆን በራሳቸው የፈጠሩት ነው። አንዳንዶች ፎቶ ግራፍ አምላኪዎች ናቸው። በተለይ ኦርቶዶክሶች ለዚህ ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ባሳለፍነው ምዕራፍ ላይ ከአንደ አምላክ ውጭ ማምከን አጥብቆ ይከለክላል። በትንቢ.ተ.ሕዝቄል 27፡15«***ሰአሊ የተረገመ ነው***» ብሏል። ክርስቲያኖች መረገም ፈልጋችሁ ነው ሦስት ሰዎች ስላችሁ የዓለማትን አምላክ በሰው መስላችሁ ሦስት አምላኮች ናቸው የምትሉት? አምላክ ግን በማንም አትመስሉ በማለት የተናገረውን አሳልፈናል። አንዳንድ ክርስቲያኖች “ሦስት አምላክ” አለ ብለው ለማስረዳት ሲሞክሩ **‹እግዚ- አብ -ሔር›** ብለው ሦስት ቃላቱን በመተንተን ሦስት አምላክ ለማድረግ ይሞክራሉ። እንዲያውም እግዚአብሔር የሚለውን የ1980 ዕትም የግርጌ ማስታዎሻ እግዚአብሔር ማለት

የሁለት ውቅር ቃላት ነው። ትርጉሙም የብሔር አምላክ ማለት ነው በማለት ለብሔር ብቻ ወስኖታል። ታዲያ እግዚአብሔር የብሔር አምላክ ከሆነ የዓለማት አምላክ ማን ነው? በትንቢተ.ዘካሪያስ 1፡9«***እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ይነግሳል፤ በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስሙም አንድ ብቻ ይሆናል***።» ሦስት የሚለው ከየትኛው የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት እንደተገኘና እንዳለ አሳዩን። ኢየሱስ ስለ አንድ አምላክ አስተምሯል። ሦስት አምላክ አይታወቅም በማስከተልም ከአንድ አምላክ ውጭ ማልገልና ማምለክ እንደማይቻል በሉቃስ ወንጌል 16፡13«***አንድ ሰው በጊዜ ሁለት ጌቶችን ማገልገል የሚችል የለም፤ አንዱን ጠልቶ ሌላውን ይወዳል፤ አንዱን ንቆ ሌላውን ያከብራል***።» ሌላው ይቅርና ሶስት አምላክ ማምለክ ሁለት አምላክ ማምለክ እንደማይቻል ኢየሱስ ተናግሯል። እኛ ሙስሊሞች የምንመክራችሁ ኢየሱስ የመከራችሁን ነው፤ አንድ አምላክ አምልኩ በማለት ነው። በሉቃስ ወንጌል 4፡8«***ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ሥገድ እርሱን ብቻ አምልክ***» ብሎ እንደተናገረው። በመጽሐፈ ኢያሱ 24፡15«***እግዚአብሔርን እናመልካለን አምላካችን ነውና አሉ***።» የእናንተም መልስ ተመሳሳይ ይሁን፤ እኛም ሙስሊሞች ግዚአብሔርን እናመልካለን። እናንተ ክርስቲያኖችስ ማንን ታመልካላችሁ?

## 26) ወደ አምላክ በንስሓ ፈጥነን መመለስ አለብን።

ክርስቲያኖች የምንመክራችሁ ትልቁ ምክር ሞት ሳይቀድማችሁ ወደ ንሰሓ ግቡ በማለት ነው። በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ 10፡14«***በዚያም ስለሠራኸው ኃጢአት ታፍራለህ፤ በመልካም ሥራቸው ከሚመሰገኑት ትመሰገን ዘንድ ነው እንጂ በፍርድ ቀን በመላክትና በሰዎች ፊት እንዳታፍር ወደዚያ ሳትደርስ በዚህ ንሰሓ ለመግባት ፍጠን***።» ከዚሁ ምዕራፍ *በዚህ (በምደር ሳለን በሕይወት) ንሰሓ ካላዘጋጀን በዚያ (በትንሣኤ ቀን) የማይረባና የማይጠቅም ጩኸትና ለቅሦን እናዘጋጃለን*።» በመጽሐፈ መክበብ 12፡7«***ነፍስም ወደ ሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ***።» በመጽሐፈ መዝሙር 51፡13«***ዳዊት እንዲህ ይላል፡- እኔም ለሕግ ተላላፊዎች መንገድህን አስተምራለሁ፤ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ***።» በትንቢተ.ሕዝቄኤል 18፡13«***የእስራኤል ቤት ሆይ!፤ እግዚአብሔር። እንግዲህ ንሰሓ ግቡ! በኃጢአት እንዳትጠፉ ከኃጢአታችሁ ሁሉ ተመለሱ***።» ተጨማሪ በትንቢተ.ኤርሚያስ 8፡6-8፣ በትንቢተ.ዘካርያስ 1፡3፣1፡7፣ እና 8፡21 ---

እንዲሁም በትንቢተ.ኢዩኤል 2፡21«***"አሁንም ቢሆን፤ በጾም፣ በለቅሶ ንባ፣ በሐዘን፣ በፍፁም ልባችሁ ወደ እኔ ተመለሱ" ይላል እግዚአብሔር፡፡***» በትንቢተ.ሦፎንያስ 2፡2-3«***የተወሰነው ጊዜ ሳይደርስ ቀኑ እንደ ገለባ ይጠራቸዋል፤ የእግዚአብሔር ጽኑ ቁጣ በእናንተ ላይ ሳይመጣ፤ የእግዚአብሔር የመዓት ቀን ሳይደርስባችሁ ተሰብሰቡ። እናንተ የምድር ትሑሐን ሁሉ ትእዛዛትን የምትፈፅሙ እግዚአብሔርን እሹ (ፈልጉ)፡፡***» የ1980 ዕትም አዲስ ኪዳንና መዝሙረ ዳዊት ቀለል ባለ አማርኛ ከተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ በገጽ 174 ላይ ርዕሱ ራሱ ‹**ንሰሓ የማይገባ ሁሉ ይጠፋል**› እያለ ያስጠነቅቃል። ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 13፡3-4«***በኃጢአታችሁ ተጸጽታችሁ ንሰሓ ባትገቡ፤ እናንተም እንደ እነርሱ ትጠፋላችሁ እላችኋለሁ። በሰሊሆም ግንብ ተደርምሶባቸው ስለሞቱት አሥራ ስምንት ሰዎች ምን ታስባላችሁ እነርሱ ከኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሰዎች ሁሉ የባሱ ኃጢአተኞች ይስላችኋልን አይደለም! በኃጢአታችሁ ተጸጽታችሁ ንሰሓ ባትገቡ እንናተም እንደ እነርሱ ትጠፋላችሁ እላችኋለሁ፡፡***» በማርቆስ ወንጌል 2፡16-17«***"ከፈረሳዊያን ወገን የሆኑ የሙሴ ሕግ መምህራን ኢየሱስ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተው" ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላውና የሚጠጣው ለምንድን ነው" በማለት ደቀመዛሙርቱን ጠየቁአቸው። ኢየሱስም ይህን "ለበሽተኞች እንጂ ለጤነኞች ሐኪም አያስፈልጋቸውም፤ እኔም የመጣሁት ኃጢአተኞችን ወደ ንሰሓ ለመጥራት እንጂ ፃድቃንን ወደ ንሰሓ ለመጥራት አይደለም" አላቸው፡፡***» ተጨማሪ በማቴዎስ ወንጌል 9፡9-13፣ በሉቃስ ወንጌል 5፡ 27-32 ይመልከቱ፡፡

## 27) ንሰሓ መግባት ከአምላክ ዘንድ ያለው ጥቅም

ኃጢአተኞች ወደ አምላካቸው ሲመለሱ ወንጀላቸው ተምሮና ጸጸታቸው ወደ መልካም ስራ ተቀይሮ ያገኙታል። ስለዚህ እኛም ይህን ዕድል ለማግኘት ካለንበት ወንጀል መመለስና ወደ ንሰሓ መፍጠን አለብን። በትንቢተ.ሕዝቄኤል 18፡27-28 «***ኃጢአተኛው ግን ከክፉ ሥራው ተመልሶ በታማኝነትና በቅንንት ቢኖር ሕይወቱን ያድናል። የፈፀመውን በደል ሁሉ ተገንዝቦ ካደረገው ክፋት ሁሉ ስለተመለሰ ፈፅም በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም፡፡***» በሉቃስ ወንጌል 15፡10 «***ንሰሓ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ ምክንያት በሰማይ መላእክት ዘንድ እንዲሁ ደስታ ይሆናል፡፡***» አምላክ ሁላችንም ንሰሓ ገብተው ከሚደሰቱት ያድርገን።

## ምዕራፍ አሥር

## ኢየሱስን ወደ አምላክነት ደረጃ ያደርሰዋል ብለው የሚያነሷቸው መሰረተ ቢስ ሐሳቦች

ክርስቲያኖች ኢየሱስን ወደ አምላክነት ደረጃ አድርሰውታል ብለው የሚያነሷቸው አብይት ምክንያቶች፡-

- ያለ አባት መወለዱ
- ሙታንን ማስነሳቱ (አላዓዛርን)
- ወደ ሰማይ ማረጉ (መወሰዱ)
- ለአርባ ቀን ያለ ምግብና ያለ ውሃ መቆቱ
- ተአምራትን በራሱ ፈቃድ ያደረገ ስለመሰላቸው
- ተሰቅሎ የሰው ልጆችን ኃጢአት የተሸከመ ስለመሰላቸው
- እኔና አብ አንድ ነን ስላለ (ከአምላክ ጋር እኩል ስለመሰላቸው)
- የአምላክ ልጅ ስለተባለ
- የሕይወት እንጀራ ነኝ ስላለ (ገነት የሚያስገባ ስለመሰላቸው)
- አዳኝ ስለሆነ (ዓይን ለምጽን) ስላዳነ
- ማንም ያልሰራውን ኢየሱስ ብቻ የሰራ ስለመሰላቸው
- ጌታ ተብሎ መጠራቱ
- አምላክ ተብሎ መጠራቱ
- በትንሽ እንጀራ ብዙ ሰዎችን ስለመገበ
- ሰው ስለሰገደለት
- በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ
- ኢየሱስ ከእግአብሔር ጋር አብሮ ስለነበር
- በባህር ላይ ስለተራመደ --------- እነዚህንና መሰል ተግባሮቹ ወደ አምላክነት ያደርሰዋል ብለው ያምናሉ።

ከላይ በተዘረዘሩት ዋና ዋና ነጥቦች ላይ በመመርኮዝ ኢየሱስን አምላክ ነው እንዲሉ ምክንያት ሆኗቸዋል። ሁሉም የክርስትና እምነት ተከታዮች በዋናነት ኦርቶዶክስ፣ ፕሮቴስታንት፣ ጆቫና ካቶሊክ በእነዚህ ነጥቦች ላይ ተንተርሰው

ኢየሱስን አምላክ ነው የአምላክነት ደረጃ አግኝቷል ብለው ያምናሉ። በየቦታውና በየቤተ ክርስቲያኑ ለኢየሱስ የሚያ ደርጉት ጸሎትና አምልኮ ትልቅ ምስክር ነው። እውነታውን ለማረጋገጥ በእያንዳንዳቸው ላይ መረጃ በመጥቀስ በቅደም ተከተል እናያቸዋለን።

## 1) <u>ያለ አባት መወለዱ</u>

ያለ አባት መወለድ አምላክ የሚያሰኝ ከሆነ አዳም ያለ አባት እና ያለ እናት ስለተወለደ ከኢየሱስ የበለጠ ቀዳሚ ድርሻ ይኖረው ነበር። የሌለን ነገር ማስገኘት ነው የሚከብደው ወይንስ ካለ ነገር ማስገኘት? የኢየሱስ አፈጣጠርም ካለ ነገር የተገኘ ነው ከማርያም ማለት ነው። አዳም ግን ከሌለ ነገር የተገኘ ነው። ታዲያ ኢየሱስን ከማርያም ማስገኘቱ ነው የሚገርመው ወይንስ ያለ እናትና አባት አዳምን ማስገኘቱ? ለበለጠ መረጃ ‹የሰው ልጅ አፈጣጠር› በሚለው ርዕስ ስር ይብራራል ከዚያ ላይ ይመልከቱ።

## 2) <u>አላዓዛርን ከሞት ስላስነሳ</u>

አላዓዘር የሚባለውን ሰው ኢየሱስ እንዴት ከሞት እንዳስነሳው የ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 11፡41 ላይ መልስ ይሰጠናል። «***<u>ኢየሱስ ዓይኑን አንስቶ (ለመነ አምላኩን) አባት ሆይ! ስለሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ሁልጊዜም እንደምትሰማኝ አውቃለሁ። ነገር ግን ይህን መናገሬ አንተ እንደላከኝ በዚህ የቆሙ ሰዎች እንዲያምኑ ነው።</u>***» ጥያቄ ኢየሱስ ጌታ ከሆነ ለምን መለመን አስፈለገው? ሌላ አምላክ አለን? አንዱ አምላክ ሌላውን አምላክ ከለመነ ምኑን አምላክ ሆነው? ነው የሌላውን አምላክ ኢየሱስ ያለ አስመስሎ ለመነ? ተአምር ያደረገው በመጀመሪያ አምላኩን ለምኖ ነው፤ ልመናው እንደተሳካለት ደግሞ ሁልጊዜም እንደሚሰማኝ አውቃለሁ ብሏል። ይህ እኮ አያስገርምም ኢየሱስ ለሐዋሪያት እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ሂድ ብትሉት ይሆንላችኋል ብሏል። ምክንያቱም ለአምላክ የሚሳነው ነገር የለምና። ስለዚህ ኢየሱስ አላዘርን ከሞት ያስነሳው መጀመሪያ ለአምላኩ ጸሎት ልመና አቅርቦ ነው እንጂ በራሱ ኃይል አይደለም። ከእሱ የበለጠ ተአምር ያደረጉ ሌሎች ነብያቶችና ተራ ሰዎችም አሉ። ለምሳሌ፡-

## 3) ኢየሱስ ብቻ አይደለም፤ ሌሎች ተራ ሰዎች ከሞት አስነስተዋል።

ጳውሎስና ሐዋርያው ጴጥሮስ ከሞት እንዳስነሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በሐዋሪያትሥራ 20፡9 ***«ጳውሎስ ከሞት ያስነሳው ሰውም <u>አውጤከስ</u> ይባላል።»*** ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 9፡4 ***«ሐዋሪያው ጴጥሮስ ከሞት ያስነሳት ሴት <u>ጣቢታ</u> ትባላለች።»*** ሐዋርያው ጴጥሮስና እንደ ሌሎች "ሐዋሪያ" ነኝ የሚለው ጳውሎስ ሰውን ከሞት ስላስነሱ አምላክ ይባላሉ ማለት ነው? ጳውሎስ ሳይቀር ሐዋሪያ ነኝ እያለና ደግሞ ሰውን ከሞት አስነስቻለሁ በማለት ራሱን ከተመረጡ የአምላክ ባሪዎች ጋር ራሱን ያወዳድራል።!!

## 4) ከኢየሱስ የበለጠ ነብዩ ሕዝቄኤል የሞተ አጥንትን አስነስቷል።

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 37፡1-10 ***‹<u>የእግዚአብሔር እጅ በላየ ላይ ነበር፤ እግዚአብሔርም በመንፈሱ አወጣኝ፤ አጥንቶች በሞሉባት ሸለቆ ውስጥ አኖረኝ፤ በእነሱም አንፃር በዙሪያቸው አሳለፈኝ፤ እነሆ በሸለቆው ውስጥ እጅግ ብዙ ነበሩ፤ እነሆም እጅግ ደርቀው ነበሩ፤ እነርሱም የሰው ልጅ ሆይ! እነዚህ አጥንቶች በሕይወት ይኖራሉን? አለኝ። እኔም ጌታ እግዚአብሔር አንተ ታውቃለህ አልኩ። እርሱም እንዲህ አለኝ፡- በእነዚህ አጥንቶች ላይ ትንቢት ተናገር አለኝ፤እንዲህም በላቸው እናንተ የለቀቃችሁ አጥንቶች ሆይ! የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል፡- እነሆ ትንፋሽን አግባባችኋለሁ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ ጅማትም እሰጣችኋለሁ ስጋም እመግባችኋለሁ በእናንተ ላይ ቁርበትን እዘረጋለሁ፤ ትንፋሽንም አገባባችኋለሁ፤ በሕይወትም ትኖራላችሁ፤ እኔም እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ</u>»*** ይላል። ይህን አንቀጽ ልብ ብለን ስንመለከተው ነብዩ ሕዝቄኤል ከኢየሱስ የበለጠ ብዙ ተአምራቶችን ማድረጉንና ብዙ አጥንቶችን በአምላክ ፈቃድ በህይወት ዘርቷል። ቢሆንም ግን የአምላክነት ደረጃ አልተሰጠውም። ስለዚህ ኢየሱስን ብቻ ነጥለን የምናይበት አንድም ምክንያት የለም።

## 5) ኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረጉ (መወሰዱ)

ወደ ሰማይ ማረግ (መወሰድ) አምላክ የሚያስብል ከሆነ ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ነብያት አሉ። ለምሳሌ በኦሪት.ዘፍጥረት 5፡24 ***«<u>ሔኖክም አረጓል፤</u>***

***ሔኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረገ አልተገኘም፤ እግዚአብሔር ወስዶታልና።***» ተጨማሪ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 2፡11-12«***ኤሊያስም ወደ እግዚአብሔር በመንፈስ አርጓል።***» ኤሊያስ፣ ኢየሱስና ሔኖክ ስንት አምላክ ሊሆኑ ነው? ያረጉ ነብያት አምላክ የሚያሰኛቸው ከሆነ በጥቅሱ መሰረት ኤሊያስንና ሔኖክን ለምን አምላክ ልንላቸው አልደረፈርንም? ስለዚህ ኢየሱስን ብቻ መነጠሉ ኢ ፍትሀዊነትና ፍርደ ገምድልነት ነው። ምክንያቱም በማረግ ደረጃ ካየነው ኤሊያስና ሔኖክም መስፈርቱን ያሟላሉ። ኢየሱስ ካረገ በኋላም እስከ መጨረሻው አምላክ እንደማይሆን በዮሐንስ ወንጌል 3፡13«***እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው***» በማለት ለራሱ ሰው መሆኑን መልስ ሰጥቷል። ቢያርግም የአምላክነት ሹመት አላገኘም። እንዳላገኘም ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 3፡34«***የሰው ልጅ በአብ ቀን ይቀመጣል***» በማለት ከሰውነት ደረጃ ወደ አምላክነት ደረጃ አላሸጋገረውም።

## 6) ***ያለ ምግብና ያለ ውኃ ያለ አርባ ቀን መቆየቱ***

ኢየሱስ ያለ ምግብና ያለ ውኃ አርባ ቀን መቆየቱ አምላክ የሚያስብለው ከሆነ ሙሴም የዚህ ዕድል ተካፋይ ሊሆን ነው ማለት ነው። ምክንያቱም በኦሪት.ዘፀአት 34፡27-28«***ሙሴ በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፤ እንጀራም አልበላም፤ ውኃም አልጠጣም።***» ታዲያ ጥቅሱን ተንተርሰን ሙሴን ለምን አምላክ አንለውም ምክንያቱም እንደ ኢየሱስ ያለ ምግብና ያለ ውኃ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ስለተቀመጠ። አሁንም በዚህ ጉዳይ ላይ አምላክ የሚያስብል ከሆነ *"፡**በሰይፉ ፈንታሁን ሾው በመጋቢት ወር 2009 ዓ.ም አንድ አስደንጋጭ ክስተት ታይቷል። ይኸውም ለ11 ዓመት ያለ ምግብ የቆየች መሆኗ በህክምና ማስረጃ የተረጋገጠ ነው እያለ ያቀረባት ሴት ልጅ ነበረች።፡**"* ስለዚህ ይህች ሴት ልጅ ለአሥራ አንድ (11) ዓመት ያለ ምግብ ከቆየች ከኢየሱስና ከሙሴ የበለጠች አምላክ ልትሆን አይደል!? ያም ሆነ ይህ ኢየሱስ ያለ ምግብ እና ያለ ውኃ መቆየቱ አዲስና የሚገርም አይደለም። ምክንያቱም ከእርሱ በፊት ሙሴ ያለ ምግብ እና ያለ ውኃ ለአርባ ቀን ስለሰነበተ ማለት ነው።

## 7) ኢየሱስ ብቻ አይደለም፤ ሙሴም በባህር ተራምዷል።

በኦሪት.ዘፀአት 14፡22‹‹***የእስራኤል ልጆች በባህሩ መካከል ገቡ፤ ውኃውም በቀኛቸውና በግራቸው እንደ ግድግዳ ሆነላቸው***›› ይላል። ሙሴም እንደ ኢየሱስ እጁን በባህሩ ላይ ዘርግቶ ተአምር ሰርቷል፤ አሳይቷል።

## 8) ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢአት የተሸከመ ስለመሰላቸው

ይህች አባባል ቅጥፈቱ ከሁሉም የጎላና መረጃ አልባ መሰረተ ቢስ ከንቱ ምኞት ነው። ኢየሱስ በዚህ ዙሪያ አንድም ቦታ ላይ ያላስተማረውና በእርሱ ላይ የተቀጠፈበት መረጃ አልባ ውሸት ነው። ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው እንደማንኛውም ነብይ ለማስተማር ነው።ለዚህም ነው በማርቆስ ወንጌል 1፡38 ***‹‹ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- እኔ <u>የመጣሁት ለማስተማር</u> ስለሆነ እንዳስተምር በቅርብ ወደአሉ ሰዎች እንሂድ አላቸው።››*** የውርስ ኃጢአት የሌለ ለመሆኑ ቁኣርንም ሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ተመሳሳይ አቋም አላቸው። በትንቢተ.ሕዝቅኤል 18፡20-23 ***‹‹<u>ኃጢአት የምትሰራ ነፍስ እራሷ ትሞታለች</u>። ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፤ አባትም የልጅን ኃጢአት አይሸከምም፤ የፃድቁ ፅድቅ በራሱ ላይ ይሆናል። ኃጢአተኛ ካደረጋት ኃጢአት ሁሉ ቢመለስ ትዛዜን ሁሉ ቢጠብቅ ፍርድንና ቅንን ነገር ቢያደርግ ፈፅሞ በሕይወት ይኖራል እንጂ አይሞትም። የበደለውም በደል አይታሰብበትም፤ ጽድቁም በሰራሱ ላይ ነው በሕይወት ይኖራል። <u>ባደረገውም አመፅና ኃጢአት በዚያች ይሞታታል</u>።››*** እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ ሌላ ሐሳብ ማፍለቁ ለምን አስፈልጎ ይሆን? ይህ ጥቅስ ብሉይ ኪዳን ነው ያለው ስለዚህ ተሽሯል አይባልም። ምክንያቱም ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 5፡7-20 ላይ የሙሴን ሕግና የነብያትን ትምህርት ለመሻር እንዳልመጣ ተናግሯል። በተለይም በ2007 ዓ.ም በታተመው በሰማኒያ አሐዱ ርዕሱ ራሱ "የኦሪት ሕግ ስለመጽናት" ይላል። ከዚሁ ምዕራፍ 5፡17-20 ‹‹***<u>እኔ ኦሪትንና የነብያትን ትምህርት ለመሻር አልመጣሁም</u>***›› በማለት ኢየሱስ ሕግን ሊፈፅም እንደ መጣና እንደ ፈፀመ ተናግሯል። አንቀጹ ይቀጥልና ቁጥር 20‹‹***<u>ፅድቃችሁ ከሙሴ ሕግና ከፈርሳውያን ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት አትገቡም</u>***›› ብሏልና ለእኛ ሲል ለኃጢአታችን ሞተ፣ ተሰቀለ ማለት ከዚህ ላይ ቦታ ያጣል። መልካም ከሰራ የመልካም ደመወዝ ይከፈለዋል። ክፍ ከሰራ የክፉ ደመወዝ ይከፈለዋል። የውርስ ኃጢአት የሚባል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በፍፁም የለም። ኢየሱስ አሁንም በድጋሚ በዮሐንስ

ወንጌል 9፡31 «***እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን እንደማይሰማ የታወቀ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔርን የሚፈራና ፈቃዱንም የሚፈፅም ሲኖር እርሱን እግዚአብሔር ይሰማዋል***።» ስለዚህ ለኃጢአተኞች ምክንያት የላችውም አምላክም አይሰማቸውም። ጳውሎስ በ1ኛ ቆረንቶስ 3፡8«***ኢያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል***» በማለት የውርስ ኃጢአት እንደሌለ በግልፅ ተናግሯል።

## 9) ኢየሱስ ተአምር ያደረገው በራሱ ፈቃድ ስለመሰላቸው

ተአምር ማድረግ በኢየሱስ ብቻ የተገደበ አይደለም። ለምሳሌ፡- ለነብዩ ዳዊት ብረትን አግርቶለታል። ለነብዩ ሰለሞን ጥበብን፣ ወፎችና ጉንዳኖችን የማናገር ታአምር በአጠቃላይ ብዙ ተአምራትን ሰጥቷቸዋል። ሆኖም ግን እነዚህን ታዓምራት መሰጠታቸው ወደ አምላክነት ደረጃ አያደርሳቸውም። እስኪ ለአብነት ያክል የሙሴን ከኢየሱስ ጋር እናወዳድረው ለመሆኑ ሙሴ በአንዲት በትር ስንት ተአምራት እንዳሳየ፤ በእጁም ምን እንደሰራ በቀጣዩ ምዕራፍ እንመልከት። በኦሪት.ዘፀአት 4፡3-4«***ሙሴ በትሩን መሬት ላይ ጣላት አለው፤ እባብም ሆነች፤ ከአጠገቧም ሸሸ። እግዚአብሔር (ያህውዌ) ሙሴን በል እጅህን ዘርጋና ጅራቱን ያዝ አለው፤ ሙሴም እጁን ዘርግቶ ሲይዛት ወደ እባብ ተለወጠ፤ በእጁ ላይ እንደገና በትር ሆነች***።» ሁለተኛ ተአምር ከዚሁ ምዕራፍ 4፡6«***እግዚአብሔርም ደግሞ እጅህን በብትህ ውስጥ አስገባ አለው፤ ሙሴም እጁን በብብቱ ውስጥ አስገባ፤ ከብብቱ ውስጥ ባወጣበት ጊዜ እጁ እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች***።» አሁንም በድጋሜ 4፡7«***አሁንም ደግሞ እጅህን ወደ ብብትህ መልሰህ አስገባ አለው፤ ሙሴም እጁን መልሶ በብብቱ ውስጥ አስገባ እጁን ከብብቱ ውስጥ ባወጣበት ጊዜ ተመልሶ እንደሌላው የሰውነቱ ክፍል ሆነች***።» በመጀመሪያ በትሯ እባብ ሆነች፤ ከዚያ ተመልሳ በትር ሆነችለት፤ ባህርን የሚያክል ነገር ለሁለት ተሰነጠቀለት። ፈርዖንና ጭፍሮቹን በሙሉ ደመሰሰችለት። ምድረ እስራኤልን ሙሴ ነገሰባት። ከዚያም ሙሴ እጁን እንደ ብርሃን እያበራ ይጠቀምባት ጀመር። ባህሩን ለሁለት የሰነጠቀው በአንዲት በትር ነበር። ይህን ሁሉ ተአምር ሙሴ ያከናወነው በእግዚአብሔር ፈቃድ ነው እንጂ በእርሱ ፈቃድ አይደለም።

## 10) ኢየሱስ ብቻ አይደለም ሌሎች አማኝ ያልሆኑ ሰዎችም እንኳ ብዙ ድንቅ ነገርና ተአምር ያሳያሉ።

ኢየሱስ አማኝ ያልሆኑ ሰዎችም ተአምር እንደሚያደርጉ በሚከተለው ምዕራፍ ተናግሯል። በማቴዎስ ወንጌል 24፡24‹‹***ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነብያቶች ይነሳሉና፤ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ተአምራትና ድንቅ ነገር ያሳያሉ***።›› ዋናው ቁም ነገር ግን ተአምር ቢያሳዮም አምላክ መሆን አለመቻላቸው ነው።

## 11) ኢየሱስ ብቻ አይደለም ሌሎች ነብያትም ዓይን አብርተዋል።

በመጽሐፈ ነገሥት 6፡17‹‹***ኤልሳዕም አቤቱ ያይ ዘንድ ኣይኖቹን እንዲያይ እባክህ ግለጥ ብሎ ለየ። እግዚአብሔርም የብላቴናውን ኣይኖች ገለጠ***።›› ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ኤልሳዕም በእግዚአብሔር ፈቃድ የብላቴናውን (የባሪያውን) ዓይን እንዲበራ አድርጓል። ተአምር ማሳየት አምላክ የሚስብል ከሆነ ኤልሳዕም በአምላክነት ላይ ተጋሪ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም እንደ ኢየሱስ ዓይን ስላበራ። ከዚሁ ምዕራፍ 6፡18‹‹***ኤሌሳዕም ይህን ሕዝብ እውር ታደርገው ዘንድ እለምንሃለሁ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ***።›› ኤልሳዕም እንደ ተናገረው ቃል እውር አደረጋቸው። ‹‹***ኤልሳዕም ወደ ማርያም በገቡ ጊዜ ኤልሳዕም አቤቱ ያዩ ዘንድ የነዚህን ሰዎች ኣይኖች ግለጥ አለ፤ እግዚአብሔርም ዓይኖቻቸውን ገለጠ እነርሱም አዩ***።›› ኤልሳዕም እንዲያዩ ብቻ ሳይሆን እንዲታወሩም አድርጓል። ሆኖም ግን አሁንም ወደ አምላክነት ደረጃ አያሸጋግርም።

## 12) ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ነብያትም አድነዋል።

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ 17፡22‹‹***እግዚአብሔርም የኤሊያስን ቃል ሰማ፤ የብላቴናም ነፍስ ወደ እርሱ ተመለሰች እርሱም ዳነ***።›› ተጨማሪ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 4፡33-34‹‹***ኤልሳዕም ወደ ቤቱ በገባ ጊዜ እነሆ ሕፃኑ ሞቶ በአልጋ ላይ ተጋድሞ ነበር፤ ገብቶም በሩን ከሁለቱ በኋላ ዘጋ ወደ እግዚአብሔር ጸለየ፤ መጥቶም በሕፃኑ ላይ ተኛ። አፍን በአፉ ኣደረገበት፤ በዓይኑ እጁንም በእጁ ላይ ኣድርጎ ተጋደመበት፤ የሕፃኑም ገላ ሞቀ። ተመልሶም በቤት ውስጥ አንድ ጊዜ ወዲህ ወዲያ ተመለሰ፤ ደግሞ መጥቶም ሰባት ጊዜ በሕፃኑ ላይ ተጋደመበት***

*ሕፃኑም ዓይኖቹን ከፈተ።*» ኤልሳዕም እንደ ኢየሱስ አምላክ ባይባልም ሕፃኑን ከሞት ቀስቅሶታል። ከዚሁ ምዕራፍ 13፡20-21 «*ኤልሳዕም ሞተ ቀበሩትም፤ ከዓምብ ሊደጋ ጣዩች በየዓመቱ ወደ አገሩ ይገቡ ነበር። ሰዎችም አንድ ሰው ሲቀብሩ ሊደጋ ጣዮች ሬሳውንም በኤልሳዕ መቃብር ጣሉት። የኤልሳዕም አጥንት በነካ ጊዜ ሰውየው ድኖ በእግሩ ቆመ።*» ከዚህ ላይ ደግሞ በጣም የሚደንቅ ነው። የኤልሳዕም አስክሬን የሞተውን ሰው በነካው ጊዜ ድኖ በእግሩ ቆመ። ኤልሳዕም ሞቶ እንኳ ተአምር አሳይቷል። ኢየሱስ ካደረገው ጋር ሲነፃፀር ኤልሳዕ ያሳየው እጅግ ከባድ ተአምር ነው። አስቡት የሞተን ሰው አጥንት ሲነካ የሞተውን ሰው አድኖ በእግሩ አቆመው።

## 13) ኢየሱስ ብቻ አይደለም ሌሎች ነብያትም ለምጻሞችን ፈውሰዋል።

በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 5፡14« --- *የእግዚአብሔር ሰው እንደተናገረው በዮርዳኖስ ወንዝ ሰባት ጊዜ ብቅ ጥልም አለ፤ ሥጋውም እንደገና እንደ ትንሽ ብላቴና ሥጋ ሆኖ ተመለሰ ንፁሕም ሆነ።*» ሰለሞን የብላቴናውን ለምጽ አንፅቶታል ነገር ግን ለአምላክነት ደረጃ ከኢየሱስ እኩል አልተሰለፈም።

## 14) ኢየሱስ ብቻ አይደለም ሐዋሪያትም አጋንንትን አውጥተዋል።

በመጀመሪያ ደረጃ ኢየሱስ አጋንንትን ያወጣው በራሱ ኃይል ሳይሆን በአምላኩ ፈቃድ ነው። እንዴት እንዳወጣም የሉቃስ ወንጌል መልስ ይሰጠናል። በሉቃስ ወንጌል 11፡20«*እንግዲህ እኔ አጋንት በእግዚአብሔር ኃይል የማስወጣ ከሆነ የእግዚአብሔር መንግስት ወደ እናንተ መምጣቷን ዕወቁ*» በማለት ኢየሱስ አጋንንትን ያስወጣው በእግዚአብሔር ኃይል እንደ ሆነ እራሱ ኢየሱስ ተናግሯል። በመቀጠል ኢየሱስ ሐዋሪያትም ሳይቀር እንደሚያድኑና እንደሚፈውሱ በማርቆስ ወንጌል 16፡18«*እጃቸውን በበሽተኞች ላይ ሲጭኑ በሽተኞች ይድናሉ*» በማለት ሐዋሪያት በሽተኞችን እንደፈወሱና አጋንንትን እንዳስወጡ የማርቆስ ወንጌል ይናገራል። በዚህም ብቻ አልተገደበም። ጳወሎስም "አጋንንትን አስወጥቻለሁ"፤ "ሙታንንም አስነስቻለሁ" በማለት በራሱ መልእክት አስፍሮት እናገኛለን።

## 15) ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ስለተባለ ከሦስቱ አማልክት አንዱ ነው ብለው ስላሰቡ።

**‹ልጅ›** የሚለውን በጥሬ የምንተረጉመው ከሆነ ትልቅ ስህተት ነው። ምክንያቱም በተለያዩ ዘመናት ይኖሩ የነበሩ ነብያት እና የሰው ልጆች የእግዚአብሔር ልጅ ተብለዋልና። መጽሐፍ ቅዱስ **‹ልጅ›** የሚለውን እንዴት እንደ ተረጎመው አንድ በአንድ እንመልከት፡-

1- **«ልጅ»** ማለት ፃድቅ (የእግዚአብሔር ወዳጅ)
2- **«ልጅ»** የተቀባ (የተሾመ) ማለት እንደሆነ
3- **«ልጅ»** አገልጋይ ማለት እንደሆነ
4- **«ልጅ»** ማለት ባሪያ በማለት ይተረጉመዋል።

### 1.1) «ልጅ» ማለት ፃድቅ ማለት እንደ ሆነ

በማርቆስ ወንጌል 15፡39«***በዚያ አንፃር የቆመው የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሠጠ ባየ ጊዜ ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበር አለ።***» ይህን ቃል በሉቃስ ወንጌል 7፡47 ፃድቅ ብሎ ይተረጉመዋል። «***የመቶ አለቃውን የሆነውም ባየ ጊዜ ይህ ሰው በእውነት ፃድቅ ሰው ነበር ብሎ እግዚአብሔርን አመሰገነ።***» ከላይ እንደተመለከትነው መቶ አለቃ የተናገረው አንድ ቃል ሆኖ ሳለ ያ ቃል ምን እንደ ነበረ በማርቆስ ወንጌል ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ነው በማለት ገልፆታል። የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ደግሞ ፃዲቅ የሚለውን ትርጉም ሲነግረን በሉቃስ ወንጌል ፃዲቅ ሰው ነበር ብሎታል። ስለዚህ በሁለቱም አንቀፆች መካከል የትርጉም ስምምነት እንዳለ ግልፅ በሆነ በማስረጃ ያሳየናል። ያም ልጅ ማለት ፃድቅ ማለት እንደሆነ ይነግረናል።

### 1.2) «ልጅ» ማለት የተቀባ፣ የተሾመ ማለት እንደ ሆነ

በማቴዎስ ወንጌል 16፡16«***ሰምዖን ጴጥሮስም መልሶ፡- አንተ ክርስቶስ የኅያው የእግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።***» ልጅ የሚለውን ቃል የተቀባ፣ የተሾመ ማለት እንደሆነ ሲመተርጎም በሉቃስ ወንጌል 9፡20«***ጴጥሮስም መልሶ፡- ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ አለ።***» ጴጥሮስ የተናገረው አንድ ቃል ነው። ስለዚህ ይህን ቃል በማቴዎስ ወንጌል ኢየሱስን የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ሲለው የእግዚአብሔር ልጅ

ማለት ደግሞ የተቀባ (የተሾመ) ማለት እንደሆነ በሉቃስ ወንጌል የተቀባ በማለት ልጅ የሚባለውን ተርጉሞታል።

## 1.3) «ልጅ» ማለት አገልጋይ ማለት እንደ ሆነ

ሁሉም የሰው ልጆች በሙሉ የአምላክ አገልጋይ ናቸው እንጂ አምላክ ከሰው አስረግዞ የወለዳቸው ነው ለማለት አይደለም። የአምላክ ልጅ መሆን ደግሞ በኢየሱስ ብቻ የተገደበ እንዳልሆነ በሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንመልከት። በትንቢ.ተ.ሕዝቄኤል 16፡20«***ይላል ጌታ እግዚአብሔር፡- ለእኔም የወለድሻቸውን ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽን ወለድሽ***----» ይላል። ታዲያ በዚህ መሰረት እግዚአብሔር ሴቶችና ወንዶች ልጆች አለውን? ብለን ብንጠይቅ ክርስቲያኖች ሳይቀር የሚሰጡት መልስ የለውም ነው። ስለዚህ ልጅ ማለት አገልጋይ ማለት ነው። ኢየሱስም ልጅ ማለት አገልጋይ ማለት መሆኑን ሲገልፅ በሚከተለው ምዕራፍ የተናገረውን እናገኛለን። በዮሐንስ ወንጌል 8፡44«***እናንተ የአባታችሁ የዲያብሎስ ልጆች ናችሁ፤ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ ለላቸው።***» ከዚህ ላይ ኢየሱስ የአይሁድ አለቆችን ሲወቅሳቸው ከአባታችሁ ማለቱ ከእርሱ (ከሰይጣን) ተወልዳችሁ ማለቱ ሳይሆን ስራችሁና ባህሪያችሁ እርሱን ትመስላላችሁ ለማለት ፈልጎ ነው። ያ ካልሆነማ የአይሁድ አለቆች ከሰይጣን ተረግዘው የተወለዱ፤ እናትና አባታቸው ሰይጣን ነው ማለት ነው? አይደለም፤ የባህሪና የስራ መመሳሰል ለመግለጽ ነው።

## 1.4) «ልጅ» ማለት ባሪያ ማለት እንደ ሆነ

በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 42፡1«***እነሆ ደግፌ የያዝኩት ባሪያዬ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አደርጋለሁ፤ እርሱም ለአሕዝብ ፍርድን ያወጣል።***» ከዚሁ ምዕራፍ 57፡13«***እነሆ ባሪያዬ በማስተዋል ያደርጋል፤ ከፍ ከፍም ይላል እጅግም ታላቅ ይሆናል።***» ሁሉም የክርስትና እምነት ተከታዮች እነዚህ ትንቢቶች የተነገሩት ለኢየሱስ ነው ብለው ያምናሉ። ኢየሱስን እንደማይመለከተው በሌላ ርዕስ እመጣበታለሁ። ለመስማማት ያክል ግን ለእሱ ነው እንበልና ታዲያ ባሪያ በማለት ስለተገለጸ ኢየሱስ የአምላክ ባሪያ መሆኑን ለምን አላመናችሁበትም? ለኢየሱስ ነው ብትሉም በነብይነቱና የአምላክ ባሪያ በመሆኑ አላመናችሁም። ይህ

ትንቢት ለነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በቀጥታ እርሳቸውን ብቻ ነው የሚመለከተው።

## 1.1.5) <u>**እውን ኢየሱስ ብቻ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነውን?**</u>

እውን ኢየሱስ ብቻ "አንድያ ልጅ" ነውን ብለን በምንጠይቃችሁ ጊዜ ሁሉም የክርስትና የእምነት ቡድኖች በአንድነት የምትሰጡት መልስ በአንድ ድምጽ "አዎ" ነው። በዚህ ማስረጃ በመንጠልጠል፡- በዮሐንስ ወንጌል 3፥16«<u>***በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው***</u> ---- <u>***እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪ ሰጥ ድረስ ዓለሙን ወዶልናል***</u>» ስለሚል በዚህ ጥቅስ በመንተራስ ነው ክርስቲያኖች ኢየሱስን የአምላክ አንድ ልጅ ነው ብለው ያመኑት። ኢየሱስን ብቻ አንድያ የእግዚአብሔር ልጅ አድርገን የምንወስድ ከሆነ በሚከተሉት ምዕራፍና ቁጥሮች ላይ የተጠቀሱትን አንድያ የእግዚአብሔር ልጆች ማስወገድ አለብን። አለበለዚያ ግን ጥቅሱ ይቃረናል።

አንድያ ማለት የመጀመሪያ የበኩር ልጅ ማለት ነው። ነገር ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ነብያቶች የእግዚአብሔር አንድያ (የበኩር) የመጀመሪያ ልጅ ተብለዋልና። ታዲያ እነርሱም እንደ ኢየሱስ አምላክ ይባሉ ይሆን? አይሆኑም የምትሉን ከሆነ ኢየሱስ ብቻ ተነጥሎ እንዴት አምላክ ተባለ? ከኢየሱስ የቀደሙ ነብያት የዚህ ድርሻ ተካፋይ አይሆኑምን? ምክንያቱም በእናንተ አባባል አንድያ ልጅ መባል ወደ አምላክነት ደረጃ ስለሚያደርስ ማለት ነው። ካልሆነ ግን ለሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች መልስ ያሻቸዋል። መልሱንም ከክርስቲያን ምሁራን እንጠብቃለን። በኦሪት.ዘፀአት 4፥23«<u>***እስራኤል የበኩር***</u> ***(አንድያ)*** <u>***ልጄ***</u> ***ነው።***» ያዕቆብ የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነው። በመጽሐፈ መዝሙር 89፥26-27 «***አንተ*** <u>***አባቴ***</u> ***ነህ አምላኬ መድኃኒቴም መጠጊያ እኔም ደግሞ*** <u>***የበኩር ልጅ***</u> ***(አንድያ) አደርገዋለሁ፤ ከምድር ነገሥታትም ከፍ ከፍ ይላል።***» ዳዊትም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነው። በትንቢተ.ኤርሚያስ 31፥9«***እኔ ለእስራኤል አባት ነኝና ኤፍሬምም*** <u>***በኩሬ***</u> ***ነው (አንድያ) ነው።***» ኤፍሬምም የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ነው። ከላይ እንደ ተመለከትነው፡- ያዕቆብ፣ ኤፍሬም፣ ዳዊትና ኢየሱስ የእግዚአብሔር አንድያ ልጆች ናቸው። አራቱም ነብያት በአንድ ቃል "የበኩር" የመጀመሪያ አንድያ ልጅ በማለት ተገጸዋል። ከቋንቋ አንፃር ስናያቸው

ሁሉም የበኩር አንድያ ልጅ ያስብላቸዋልን? እግዚአብሔር አራቱንም በአንድ ጊዜ ነው የወለዳቸው? ነው እንዳትሉን ሁሉም ነብያት በዘመን በጣም ይራራቃሉ። የበኩር ማለት የመጀመሪያ አንድያ ልጅ ማለት ነው። ታዲያ ሁሉም ነብያት እንዴት የበኩር ይባላሉ? አንዱን አንዱ የሚቀድም ነብይ የለም? ክርስትያኖች ኢየሱስን ጌታ ነው ያሉት በኒቃየው ጉባኤ ነበር በምርጫ የጸደቀው። ታዲያ እነዚህ ነብያት እጩ ተወዳዳሪ አልነበሩም? ወይንስ ኢየሱስ በምርጫ አሸንፎ ነው? መልሱን የተረዳ ሰው ካለ ይመልስልን።

## 1.1.6) ኢየሱስ ብቸኛ የእግዚአብሔር ልጅ ከተባለ አዳም ከሁሉም ይቀድማል።

ኢየሱስ ብቸኛ ልጅ ነው በሚባለው ከወሰድነው እውን ኢየሱስ ብቸኛ ልጅ ያደረገዋልን? በሉቃስ ወንጌል 3፡38 የ1980 ዕትም‹‹***አዳም የእግዚአብሔር ልጅ ነው።***›› ስለዚህ አዳምም የእግዚአሔር ልጅ ተብሏል። በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 7፡13-14‹‹***እርሱ በስሜ ቤት ይሠራል፤ የመንገስቱንም ዙፋኑ ለዘላለም አጸናዋለሁ፤ እኔም አባት እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።***›› ሰለሞንም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል። በመጽሐፈ መዝሙር 2፡7‹‹***ትእዛዙን እናገራለሁ እግዚአብሔር አለኝ፦ አንተ ልጅ ነህ ዛሬ ወለድኩህ።***›› ዳዊትም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል። በመጽሐፈ ዜና ቀዳማይ 22፡10‹‹***እርሱ ለስሜ ቤት ይሠራል፤ ልጅም ይሆንኛል፤ እኔም አባት እሆነዋለዋሁ።***›› ሰለሞንም የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል። በኦሪት.ዘዳግም 14፡1‹‹***እናንተ የአምላካችሁ ልጆች ናችሁ።***›› አሁንም ሙሴና የሙሴ ተከታይ ሕዝቦች የእግዚአብሔር ልጆች ተብለዋል። የአምላክ ልጅ ስለተባለ ብቻ እንደ አምላክ የሚቆጠሩ ከሆነ አዳም፣ ዳዊት፣ ሰለሞን፣ ሙሴና የሙሴ ሕዝቦች በሙሉ አምላክ ይሆናሉ ማለት ነው? ያ ከሆነማ በአለም ላይ ስንት አምላክ አለ? ከብዛቱ አንፃር ቁጥሩስ ይታወቃልን? እግዚአብሔር ለኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ነብያትም አባት ሆኗቸዋል፤ እነርሱም ልጅ ሆነውታል። ያ ማለት “ልጅ” ፃድቅና ባሪያ አገልጋይ ለማለት እንጂ አምላክ ከሰው አርግዞ የወለዳቸው ለማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። አምላክ ሚስትና ልጅ ከመያዝ ከነዚህ ሰብዓዊ ባሕሪያቶች ሁሉ የጠራ ነው። ኢየሱስ ለሕዝቦቹ ሊያስተምር በማቴዎስ ወንጌል 23፡9‹‹***አባታችሁ አንዱ የሰማዩ ነውና በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ።***›› ከዚሁ ምዕራፍ 5፡45‹‹***ይህንን ብታደርጉ***

***በሰማይ ላለው አባታችሁ ልጆች ትሆናላችሁ።»*** አሁንም በድጋሜ ቁጥር 48 ላይ «***ስለዚህ የሰማዩ አባታችሁ ፍፁም እንደሆነ እናንተም ፍፁማን ሁኑ»*** ይላል። ታዲያ በዚህ መሰረት ሁሉም የክርስቲያን ሕዝቦች አምላክ ናቸው ማለት ነው? በምድር ላይ ማንንም አባት ብላችሁ አትጥሩ ስለሚል ስለዚህ ሁሉም ክርስቲያኖች የአምላክ ልጆች ናቸው ማለት ነው? ይህ ከሆነ ታዲያ ኢየሱስን ብቻ መነጠሉ ለምን አስፈለገ? የሌለን ትርጉም መተርጎም የትም አያደርስም። ተጨማሪ በመጽሐፈ ኩፋሌ 1፡22-23«***ትእዛዜንም ሁሉ ይፈጽማሉ፤ አባትም እሆናቸዋለሁ፤ እነርሱም ልጆች ይሆኑኛል፤ ሁሉም የኀያው የአምላክ ልጆች ይባላሉ፤ መልአክት ሁሉ ሰውም ሁሉም ያውቃቸዋል፤ እነርሱም ልጆቼ እንዲሆኑ እኔም በሚገባ በእውነት እንዲሆኑ እንደምወዳቸውም ያውቋቸዋል።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 14፡32 «***እግዚአብሔር አምላክ አባት ይሁንህ አንተም ልጅ ሁነው።»*** አብርሃም ልጁን ያዕቆብን የእግዚአብሔር ልጅ በማለት ገልፆታል የራሱ መሆኑን እያወቀ።

## 1.1.7) ከኢየሱስ የበለጠ መልከ ጼዴቅ ያለ አባትና ያለ እናት የተገኘ ነው፤ እርሱም ዘላለማዊ ኗሪ ነው ይለናል።

ከኢየሱስ የበለጠ ተአምራዊ አፈጣጠር ያለው ሰው እንደ ነበረ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። ወደ ዕብራውያን መልእክት 7፡1«***አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም። ለዘመኑም ጥንት ለሕይወቱም ፍፃሜ የለውም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።»*** ኢየሱስ እናት አለው፤ መልከ ጼዴቅ ግን እናትም አባትም የሉትም። ስለዚህ መልከ ጼዴቅ ከኢየሱስ የበለጠ አፈጣጠር ስላለው ለምን አምላክ ልትሉት አልደፈራችሁም? እንዲሁም መልከ ጼዴቅም የአምላክ የእግዚአብሔር ልጅ ተብሏል። አንዳንድ ሰዎች ይህ ሰው ኢየሱስ ነው ይላሉ ነገር ግን ይህ አባባል ከአንቀጹ ጋር ይቃረናል። ምክንያቱም ኢየሱስ የትውልድ ዘመን እንዳለው በዮሐንስ ወንጌል 3፡23 እንደተገፀው ኢየሱስ የትውልድ ዘመን አለው። ነገር ግን በዕብራውያን መልእክት ላይ የተገለጸው ሰው የትውልድ ዘመን የለውም። እናት አባት የለውም። ኢየሱስ ደግሞ እናት አለው፤ ማርያም ማለት ነው።

## 1.1.8) ማጠቃለያ ኢየሱስ የአምላክ ልጅ ሳይሆን የሰው ልጅ ነው።

ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 9፡56«***የሰው ልጅ የሰውን** ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ።*» በማቴዎስ ወንጌል 11፡19«***የሰው ልጅ** እየበላና እየጠጣ መጥቷል።*» ከዚሁ ምዕራፍ 10፡32-33«***በሰው** ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔም በሰማዩ ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤ **በሰው** ፊት ለሚከዳኝ ሁሉ ግን እኔም በሰማዩ ባለው አባቴ ፊት እክደዋለሁ*» ብሏል። በእናንተ በክርስቲያኖች ላይ ኢየሱስ ያላለውንና ያላስተማረውን ስለተከተላችሁ ነገ በአላህ ፊት ይክዳችኋል። እኛ ሙስሊሞች አልሐምዱሊላህ ኢየሱስን ሰውና ነብይ ብለን ስለመሰከርን ነገ በአላህ ፊት እውነተኞች መሆናችንን ይመሰክራል፤ እንደ እናንተ አይክደንም። ጳውሎስም ስለ ኢየሱስ ሰው መሆኑን ሲመሰክር በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡5«***አንድ እግዚአብሔር አለና በሰውና በእግዚአብሔር መካከል አንድ አስታራቂ አለ፤ እርሱም** ሰው የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ **ነው***» በማለት እራሱ ተናገሯል።

እስካሁን ያየናቸው በሙሉ ኢየሱስን ወደ አምላክነት ደረጃ የሚያደርሱት ከሌሎች የተለየ አንድም ምክንያት የለም። የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው የተጠሩ ነብያቶችና ሰዎች በሙሉ ፃድቃኖች አገልጋዮችና ባሪያዎች መሆናቸው ለመግለጽ ነው እንጂ የአምላክ ልጆች እንዳልሆኑ አንክሮ ሊሰጥበት ይገባል። ስለዚህ ኢየሱስ ከባሪያዎች ከአገልጋዮችና ከፃድቃኖች አንዱ ነው ማለት ነው። በዚህ አጋጣሚ ኢየሱስ ያለ አባት ከእናት ስለተገኘ ብቻ በቀጥታ የእግዚአብሔር ልጅ የሚያስብል ከሆነ እግዚአብሔር አዳምን ያለ አባት ያለ እናት አስገኝቶታልና አዳም አምላክ በሆነ ነበር የሰው አምላክ አይሆንም እንጂ። ስለዚህ አንድ ሰው ጽድቅ ስራ ሲሰራ የአምላኩን ትዕዛዝ ሲፈፅም የአምላክ ልጅ ነው ማለት ባሪያ ፃድቅ አገልጋይ ማለት ነው። ለዚያ ነው ጳውሎስ በሮሜ መልእክት ላይ 8፡14 «***በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው***» ያለው። በመቀጠልም ጳውሎስ የእግዚአብሔር ልጅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1፡17«***ለማንም ሳያዳላ በእያንዳንዱ ላይ እንደየሥራው የሚፈርደውን እግዚአብሔር «አባታችን» ብላችሁ የምትጠሩትን ከሆነ በዚህ አለም በአንድነት አመፀኞች ሆናችሁ ሳትኖሩ እርሱን በመፍራት ኑሩ***» በማለት ያስተምራል። ትርጉሙ ይህ ሆኖ ሳለ ያለ ቦታ ለማስገባት መጣጣሩ ከእውነት የራቀ ለመሆን ካልሆነ በስተቀር ለሌላ አይደለም። የአምላክ ልጅ ማለት ከዚህ

ላይ እንደ ተገለጸው አምላክን በመፍራት መኖር መሰዋት መስጠት እንጂ ኢየሱስ ለእኔ ወንጀል ቤዛ ሆኗልና የፈለኩትን ኃጢአት ልስራ የሚያስብል አይደለም። በሉቃስ ወንጌል 15፡29 «*__ስለ አመጹ ደስ አይለውም፤__*» 1ኛ ቆረንቶስ 13፡6 «*__መናፍስት ስለተገዙለት ደስ አይለውም፤ ስሙ በሰማይ ስለተፃፈ እንጂ።__*» ተጨማሪ ሉቃስ ወንጌል 10፡20 ተመልከቱ።

## 1.1) __ኢየሱስ ጌታ ተብሎ መጠራቱ አምላክ አያደርገውም።__

‹*__ጌታ__*› የሚለው ቃል የባለቤነትን አመልካች እንጂ የኢየሱስን አምላክነት አይገልጽም። ይገልፃል የምትሉ ከሆነ ሀገራችንና ሌሎች ሀገሮችን ጨምሮ በብዛት ክርስቲያኖች ይህን ስም ይጠቀሙበታል። በተለይ በተለይ ክርስቲያኑ ሕዝብ ለምሳሌ ሙሉ ጌታ፣ መሪ ጌታ፣ ጌታ ሰው፣ ጌታቸው፣ ጌታሁን፣ ተስፋሁን፣ ቅዱስ... እንዲሁም በሴቶች ተስፋነሽ፣ ቅድስት ወ.ዘ.ተ. ታዲያ እነዚህ ስሞች በሙሉ ወደ አምላክነት ያሸጋግራሉን? መልሳችሁ አዎ ከሆነ የነዚህ ሰዎች መጠሪያ ያላቸው ክርስቲያን ሰዎች እድለኛ ያደርጋቸው ይሆን? ደግሞ የሰው ጌታ አለን? ያ ከሆነ ምድር በሙሉ የሰው አምላክ ልትሆን አይደል? ሲቀጥል ኢየሱስ ጌታ መባልን አይፈልግም። በማቴዎስ ወንጌል 21-23 «*__ኢየሱስ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም__*» በማለት የጌትነት ደረጃ አለመፈለጉን ራሱ ተናግሯል። ከቋንቋ አንፃር ‹*__ጌታ__*› የተባለም ሰው እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ ይገኛል። በ1980 እትም በማቴዎስ ወንጌል 27፡62-63 «*__በማግስቱ ቅዳሜ የካህናት አለቆችና ፈረሳውያን በአንድነት ወደ ጲላጦስ ሄዱና እንዲህ አሉት፡- ጌታ ሆይ ------__*» ብለውታል። ታዲያ ጲላጦስም አምላክ ነው ማለት ነው ጌታ ስለተባለ? ከኢየሱስ የበለጠ እውነት ተናጋሪ ክርስትያን መቼም የለም። ኢየሱስ እኔ የአለም አምላክ ነኝ እኔን ብቻ አምልኩ ያለበትን ቦታ የአለም ክርስቲያን ተሰባስቦ ማምጣትና በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማሳየት የሚችል አንድም ክርስቲያን የለም። በእርግጠኝነት በፍፁም አንድም ቦታ የለም። ኢየሱስ ለሰይጣኑ ምን እንዳለው በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና በሉቃስ ወንጌል 4፡8«*__ጌታ እግዚአብሔርን እርሱ ብቻ አምልክ፤ ለእርሱ ብቻ ስገድ__*» በማለት የሚሰገድለትና የሚመለከው አምላክ ማን እንደሆነ ነግሮታል። ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ለሰይጣኑ ለኔ ስገድልኝ ባለው ነበር። ተጨማሪ በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41 ያለውን ስንመለከት የእርሱን ማንነት የበለጠ

አጉልቶ ያሳየናል። «***እኔን የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል፤ ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይን ዋጋ ያገኛል። ፃድቁንም በጽድቅ ስም የሚቀበል የፃድቁን ዋጋ ያገኛል***» ይላል። ስለዚህ ኢየሱስ ከነብይነት ውጭ ሌላን ነገር አምላክነትን አይፈልግም።

## 1.2) ኢየሱስ አምላክ ተብሎ ስለተጠራ አምላክ አያደርገውም፡፡

ኢየሱስ ይቅርና የዓለማት አምላክና ጌታ የባለቤት አመልካች የሆነን ስም እንኳ እንዲባል አልፈለገም። አምላክ የሚለውን ስም መጽሐፍ ቅዱስ ለባለቤት አመልካችነት እንደሆነ ይገልፃል። ለምሳሌ፡- በኦሪት.ዘጸአት 7፡1«***እግዚአብሔር ሙሴን አለው፡- እይ፤ እኔ ለፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ፤ ወንድምህም አሮን ነብይ ይሆንሃል***» ይላል። ከዚህ በመነሳት ሙሴ ፈርዖንን የፈጠረው አምላኩ ነው ማለት ነውን? ያ ከሆነ ደግሞ ሙሴ የዓለማት አምላክ ነው። ጣዖታትም እኮ አማልክት ተብለዋል። ስሙ ስለተባለ ብቻ አይደለም ማየት ያለብን። እውነተኛውን አምላክ ለይቶ ማወቅ ነው። እውነተኛ አምላክ አንድ እግዚአብሔር እንጂ ሙሴ፣ ጣዖታት፣ አማልክትና ኢየሱስ አይደሉም። በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 18፡39«***እግዚአብሔር እሱ እውነተኛ አምላክ ነው፡፡***» በመጽሐፈ መዝሙር 83፡18 «***ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ በምድር ሁሉ አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንክ ይወቁ፡፡***» በመጽሐፈ መዝሙር 105፡7«***እርሱ እግዚአብሔር አምላካች ነው፡፡***» ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 7፡21-23«***በሰማያት ያለው የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ፤ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም***» ብሏል። ኢየሱስ አውነተኛ አምላክ ሳይሆን እውነተኛ ነብይ ነው። በማቴዎስ ወንጌል 10፡40-41«***እናንተን የሚቀበል፤ እኔን ይቀበላል፤ እኔን የሚቀበል፤ የላከኝን ይቀበላል። ነብይን በነብይ ስም የሚቀበል የነብይ ዋጋ ያገኛል። ፃድቅንም በጽድቅ ስም የሚቀል የፃድቅን ዋጋ ያገኛል፡፡***» ስለዚህ ኢየሱስ ነብይ ነው።

## ማጠቃለያ

ሁሉም ነብያት አምላክ አንድ መሆኑን ብቻ ነው የሚያምኑትና ያስተማሩት። በትንቢተ.ዘካሪያስ 14፡9«***እግዚአብሔር በምድር ሁሉ ይነግሳል፤ በዚያ ቀን እግዚአብሔር አንድ ብቻ ስሙም አንድ ብቻ ይሆናል፡፡***» ሙሴ በኦሪት.ዘዳግም 6፡4«***እስራኤል ሆይ! ስማ! ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፡፡***» ዳዊት በመጽሐፈ

መዝሙር 104፥1«***ነብሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ አቤቱ አምላኬ ብቻህን ታላቅ ነህና፡፡***» ከዚሁ ምዕራፍ 105፥7«***እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው፡፡***» ሰለሞን በመጽሐፈ ሳሙኤል 2፥2«***እንደ እግዚአብሔር ታላቅ የለም፤ እንደ አምላካችን ፃዲቅ የለም፤ ከንተ በቀር ቅዱስ የለም፡፡***» ጳውሎስ 1ኛ ቆረንቶስ 8፥5-7«......***አንድ አምላክ አብ ነው፡፡***» ከዚሁ ምዕራፍ 1ኛ ቆረንቶስ 2፥5 «***አንድ አግዚአብሔር አለና-------፡፡***» ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል 12፥29«***እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ አምላክ ነው***» በዮሐንስ ወንጌል 17፥20«***ወደ አምላኬና ወደ አምላከችሁ----፡፡***» በማለት አስተምሯል፡፡

## 1.3) ለኢየሱስ ሰዎች ስለሰገዱለት

‹**ስግደት**› የሚለው ቃል በዕብራይስጥ ሻቻህ ሲሆን በግሪክ ደግሞ ፕሮስካኒአስ ይባላል፡፡ እንዲሁም አምልኮ ማለት ደግሞ ላቲዮስ ይባል፡፡ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ ለተለየየ ምንነት እና ማንነት የሚለየው በንያ (በሐሳብ) የሚቀርብ *intention* አምልኮን *adrotion* ወይም አክብሮትን *prostration* ነው ለማመልከት የተጠቀመበት፡፡ የአምልኮ ስግደት በባሕርይ የአንድ አምላክ ሐቅና ገንዘብ ሲሆን የአክብሮት ስግደት ደግሞ በፀጋ ለህያዋን ማንነት ማክበርን ያመለክታል፡፡ ለአብነት ያክል፡- ሰው ለሰው ይሰግድ ነበር፡፡ ለነብዩ ዮሴፍ ወንድሞቹ እንደሰገዱለት፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 37፥9-10«***ደግሞም ሌላ ሕልም አለመ (ዮሴፍ)፤ ለወንድሞቹም ነገራቸው፤ እንዲህም አለ፡- እነሆ ደግሞ ሌላ ሕልምን አለምሁ፤ እነሆ ፀሐይና ጨረቃ አሥራ አንድ ከዋከብትም ሲሰግዱልኝ አየሁ፡፡ ለአባቱና ለወንድሞቹም ነገራቸው፤ አባቱም ገሠጸው፤ እንዲህም አለው፡- ይህ የለምኸው ሕልም ምንድር ነው? በውኑ እኔና እናትህ ወንድሞችህ መጥተን በምድር ላይ እንሰግድልህ ይሆን?***» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥6«***ዮሴፍም በምድር ላይ ገዥ ነበር፤ እርሱም ለምድር ሕዝብ ሁሉ ይሸጥ ነበር፤ የዮሴፍም ወንድሞች በመጡ ጊዜ በምድር ላይ በግንባራቸው ሰገዱለት፡፡***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 43፥26 «***ዮሴፍም ቀደ ቤቱ በገባ ጊዜ በእጃቸው ያለውን እጅ መንሻ በቤት ውስጥ አቀረቡለት፤ ወደ ምድርም ወድቀው ሰገዱለት፡፡***» ለአባታቸው ለያይዕቆ እንደ ሰገዱ በኦሪት.ዘፍጥረት 43፥28«***እነርሱም አሉት፡- ባሪያህ አባታችን ደኅና ነው፤ ገና በሕይወት አለ፡፡ አጎንብሰውም ሰገዱለት፡፡***» አብራሃም ለሰዎች እንደ ሰገደ፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 23፥7«***አብራሃምም ተነሣ፤ ለምድሩ ሕዝብም፤ ለኬጤ***

***ልጆች፤ ሰገደ።»*** ለይስሐቅ ሰዎች እንዲሰግዱለት አባቱ ያዕቆብ መርቆታል። በኦሪት.ዘፍጥረት 27፡29 ***«ሕዛብ ይገዙልህ ሕዝቡም ይሰገዱልህ፤ ለወንድሞችህም ጌታ ሁን፤ የእናትህም ልጆች ይሰገዱልህ፤---።»*** ለዳዊትም ሰዎች እንደሚሰግዱለት፡- በ1ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል 29፡20 ***«ዳዊትም ጉባኤውን ሁሉ፡- አምላካችሁን እግዚአብሔርን ባርኩ አላቸው። ጉባኤውም ሁሉ የአባታቸውን አምላክ እግዚአብሔርን ባረኩ፤ ራሳቸውንም አዘንብለው ለእግዚአብሔርና ለንጉሡ (ለዳዊት) ሰገዱ።»*** ኢአማንያን ለአማንያን እንደሰገዱ፡- በዮሐንስ ራእይ 3፡9 ***«እነሆ አይሁድ ሳይሆኑ፡- አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፡- መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ---።»*** ለመላአክት እንደሚሰገድ፡- በመጽሐፈ ኢያሱ 5፡14 ***«እርሱም፡- አይደለሁም፤ እኔ የእግዚአብሔር ሠራዊት አለቃ ሆኜ አሁን መጥቼአለሁ አለ። ኢያሱም ወደ ምድር በግንባሩ ተደፍቶ ሰገደና፡- ---።»*** ተጨማሪ በኦሪት.ዘፍጥረት 19፡1 ***«---ሁለቱም መላእክት በመሸ ጊዜ ወደ ሰዶም ገቡ፤ ሎጥም ባያቸው ጊዜ ሊቀበላቸው ተነሣ፤ ፊቱንም ደፍቶ ወደ ምድር ሰገደ።»*** ለባለስልጣን እንደሚሰገድ፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 33፡1-3 ***«---እርሱም (ያዕቆብ) በፊታቸው አለፈ፤ ወደ ወንድሙ እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ።»*** ታዲያ እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት በሙሉ እያመለኩ ነው ማለት ነውን? መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም የክብር ስግደትን እንጂ የአምላኮን (ላቲዮስን) እንዳልሆነ ትኩረት ሊሰጥበት ይገባል። ለግኡዛን ነገሮችም ቢሆን አምልኮ ተከልክሏል። ኢየሱስም ቢሆን አምልኩኝ አላለም፤ ስግደትንም እንደማይገበው ለሰይጣኑ ነግሮታል። በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና በሉቃስ ወንጌል 4፡8 ***«ጌታ እግዚአብሔርን እርሱ ብቻ አምልክ፤ ለእርሱ ብቻ ስገድ»*** በማለት የሚሰገድለትና የሚመለከው አምላክ አንደ እግዚአብሔር መሆኑን አስረድቶታል። ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ለሰይጣኑ ለኔ ስገድልኝ ባለው ነበር። በመጽሐፈ ኢያሱ 24፡14 ***«እግዚአብሔር ብቻ አምልኩ።»*** የሚመለከው ማን እንደ ሆነ ምዕራፉ ግልጽ ያደርግልናል። ከዚህ ምዕራፍ 24፡15 ***«የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ፤ እኔንና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።»*** አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 24፡18 ***«ሕዝቦቹም እንዲህ አሉ እኛም እግዚአብሔርን እናመልካለን።»*** ድንገት የምታመልኩትን ካላወቃችሁና ሌላን አምላክ ካመለካችሁ ኢያሱ እንዳለው እግዚአብሔርን አምልኩ በማለት እንደመከራችሁ እኛ ሙስሊሞችም የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ አላህ (ሱ.ወ) አምላክ በማለት ቀና ምክራችንን

እንመክራችኋለን፡፡ ኢያሱ ባስተማራቸው መሰረት የሕዝቦች መልስ ጌታ አምላካችን እግዚአብሔር ነው አሉ፡፡ የእናንተም መልስ ይህ እንዲሆን እንመኛለን፡፡ ምክንያቱም ከአንድ አምላክ ውጪ ሌላ የሚመለክ አምላክ የለም፡፡ በ2ኛ በመጽሐፈ ሳሙኤል 7፡22«***ልዑል እግዚአብሔር እንዴት ታላቅ ነህ! ከቶ የሚመሰገን ማንም የለም፡፡ በጆሮአችን እንደሰማነው ሁሉ ከአንተ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም፡፡***» በየትኛው የክርስትና ክፍል ያለ ሰው ይህን ጥቅስ ልብ ሊለው ይገባል፡፡ ኦርቶዶክስ በቀላሉ አርባ አራት ታቦት እንዲመለክ ኢያዝም፡፡ ለምን ከመጽሐፍ ቅዱስ የሌለን ባዕድ አማልዕክት ትገዛላችሁ? አርባ አራት ታቦቶች ሁሉ የአለም ፈጣሪ ናቸውን? ክርስቲያኖች ሰይጣን የተጫወተባችሁ ጊዜ ይበቃል ተመለሱ፡፡ እናንተን እንዲሁም ሁሉን ነገር የፈጠረን ጌታ አምልኩ፡፡ መመለክ ያለበት እግዚአብሔር ብቻ መሆኑም ጳውሎስም ያስተምራል፡፡ በያዕቁብ መልዕክት 1፡27«***ንጹህ የሆነ ነውር የሌለበት አምልኮ ለእግዚአብሔር አብ ዘንድ ነው፡፡***» ኢየሱስ ለሰይጣኑ ምን እንዳለው በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 እና በሉቃስ ወንጌል 4፡8«***ጌታ እግዚአብሔርን እርሱ ብቻ አምልክ፤ ለእርሱ ብቻ ስገድ***» በማለት የሚሰገድለትና የሚመለከው አምላክ ማን እንደሆነ ነግሮታል፡፡ ታዲያ ኢየሱስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ለሰይጣኑ ለኔ ስገድልኝ ባለው ነበር፡፡

## 1.4) በመንፈስ ቅዱስ መሞላቱ

ከዚህ ላይ የምንረዳው ነገር አለ፡፡ ማለትም ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ከመሞላቱ በፊት ጎደሎ ነበር ማለት እንደ እናንተ አባበል፡፡ ለማንኛውም ወደ መልሱ ስናመራ ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ሰዎችም በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ እንዳሉ መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል፡፡ በሐዋሪያት *ሥራ* 11፡24«***በርናባስ ደግ፣ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረ፡፡***» ከዚሁ ምዕራፍ 5፡32«***ስለዚህ ነገር እኛም ምስክሮች ነን፤ ደግሞም እግዚአብሔርን ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈስ ቅዱስ ምስክር ነው፡፡***» ከዚሁ ምዕራፍ 6፡5«***ይህ አባባል ሁሉንም ደስ አሰኘ፤ ቀጥሎም ያሉትንም ሰዎች መረጡ፤ በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ እስጢፋኖስ፣ ፊልጶስ፣ ጵሮኮኖስ፣ ኒቃሮና ጢሞና፣ ጳርሜናና ወደ አይሁድነት ገብቶ የነበረው የአንጾኪያው ኒቆላዎስ፡፡***» ተጨማሪ በ2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 1፡21፣ በ2ኛ ጢሞቲዎስ 1፡14፣ በ1ኛ ቆረንቶስ 2፡16 እና በሉቃስ ወንጌል 1፡41 ላይ ይመልከቱ፡፡ አንዳንዶች ኢየሱስን ከሌሎች ነብያት ነጥሎ ወደ አምላክነት ለማድረስ ሲሉ

ኢየሱስ እኮ ገና በእናቱ ማኅፀን እያለ ነው "በመንፈስ ቅዱስ" የተሞላው ይላሉ። ነገር ግን መጥምቁ ዮሐንስ እንደ ኢየሱስ ገና በእናቱ ማህፀን እያለ ነበር መንፈስ ቅዱስ የሞላበት። በሉቃስ ወንጌል 1፡13-15«***መልአኩም እንዲህ አለው፡- ዘካርያስ ሆይ! አትፍራ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልዳለች፤ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለች----በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና። የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥአይጠጣም። <u>ገና በእናቱ ማህፀን ሳለ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ይሆናል</u>***» ይላል።

## <u>ማጠቃለያ</u>

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት በአጭሩ በመልካም ሥነ ምግባር መታነጽ ማለት ነው። አንድ ሰው መንፈስ ቅዱስ የተሞላበት ነው ከተባለ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለፃ በመልካም ስራ የዳባረ ምግባር ያለው፤ መልካም የአምላክ ባሪያ የሆነ ማለት ነው። ለዚህ ንግግሬ ይልጥ ማሳያ የሚሆነን የሚከተለው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነው። በሐዋርያት ሥራ 6፡3-4«***<u>በመልካም ጠባያቸው የተመሰገኑ፤ በመንፍስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ</u>፤ ሰባት ሰዎችን መረጡ፤ እነርሱን ኃላፊነት እንሽማቸዋለን። እኛ ግን በመጸለይ የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር እንተጋለን።***» በተጨማሪ ጳውሎስ የመንፈስ ፍሬ ማለት ትዕግስት፣ መልካም ስራ፣ የዋህነት፣ ራስን መግዛት ነው በማለት ገልፆታል።

## 1.5) <u>ኢየሱስ በትንሽ እንጀራ ብዙ ሰዎች ስለመገበ</u>

በትንሽ እንጀራ ብዙ ሰዎችን መመገብ በኢየሱስ ብቻ የምንገድበውና ለእኛ እንግዳ ሊሆንብን አይገባም። ምክንያቱም ሌሎች የአምላክ ነብያት ይህን ታአምር አሳይተዋል። እንደ ኢየሱስ በነብዩ ኤልሳዕና ኤልያስም ተመሳሳይ ታአምር አሳይተዋል። ኤልሳዕ በሃያ የገብስ እንጀራ እና እሸት መቶ ሰዎቸን መግቧል። በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 4፡43-44«***ሎሌውም፡- ይህን እንዴት አድርጌ <u>ለመቶ ሰው እሰጣለው</u>? አለ። እርሱም፡- ይበላሉ ያተርፋሉም ብሎ እግዚአብሔር ተናግሮአልና ይብሉ ዘንድ ለሕዝቡ ስጣቸው አለ። እንዲሁም በፊታቸው አኖረው፤ እንደ እግዚአብሔርም <u>በሉ</u>፤ <u>አተረፉም</u>።***» ኤልሳዕ ተጨማሪ 2ኛ ታአምር ባሏ የሞተባትን ሴት በቤቷ ከነበረው ትንሽ የወይራ ዘይት ማሰሮ ያለባትን ዕዳ እንድትከፍልና ዕዳዋን ከፍላ እንደሚተርፋትም በደስታ

አስከሯታል። በመጽሐፈ ነገሥት ካልእ 4፡7«***ሄደሽ ዘይቱን ሽጪ ለባለ ዕዳውም ክፈዩ፤ አንቺና ልጆችሽም ከተረፈው ተመገቡ።***» ነብዩ ኤልያስ ተመሳሳይ ታአምር መስራቱን ቀጣዩ ምዕራፍ ይነግረናል። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፡16 «***በኤልያስም እጅ እንደ ተናገረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ዱቄቱ ከማድጋው አልተጨረሰም፤ ዘይቱም ከማሰሮው አልጎደለም።***» ተጨማሪ የኤልያስ 2ኛ ታአምር ለየት ያለና አስደናቂ ታአምር አድርጓል። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 17፡6 «***ቁራዎቹም በጥዋትና በየማታው እንጀራና ሥጋ ያመጡለት ነበር፤ ከወንዙም ይጠጣ ነበር።***»

## 1.6) ሐዋሪያት ከኢየሱስ የበለጠ ብዙ ተአምርና ድንቅ ነገር ይደረግ እንደ ነበር።

ከኢየሱስ የበለጠ ተአምር ያሳዩ ነብያት እንዳሉ ሁሉ ሐዋሪያትም ብዙ ድንቅ ነገርና ተአምር ይደረግ ነበር። በሐዋሪያት ስራ 5፡12«***ብዙ ተአምራትና ድንቅ ነገሮች በሕዝቡ መካከል በሐዋሪያቶች እጅ ይደረጉ ነበር።***» ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 2፡43 ላይ ይመልከቱ እንዲያውም በጥቅሱ መሰረት ሐዋሪያት ከኢየሱስ የበለጠ ብዙ ተአምርና ድንቅ ነገር አሳይተዋል። ኢየሱስ ያሳየው ተአምር ጥቂት ስለሚል ያም ሆኖ ግን አምላክ አያስብላቸውም። የሚያስኛቸው ቢሆን ሐዋሪያት ከኢየሱስ የበለጠ ቀዳሚ ቦታ ይይዙ ነበር። ተአምር ማሳየት በሌሎች ሰዎችም በአላህ ፈቃድ ጂኒ (ኢጋንንት) ያስወጣሉ፤ ይፈውሳሉ። ለምሳሌ ጂኒ ሰይጣን የያዘው ሰው በቁርአን ሙስሊሞች በአላህ ፈቃድ ያድናሉ። ግን ወደ አምላክነት ደረጃ አያደርሳቸውም። ምክንያቱም ኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ ይቻላቸዋል ብሏል። በመቀጠል ሐዋሪያው አንተ የረገምካት በለስ ደረቀች ሲለው ኢየሱስም በማቴዎስ ወንጌል 21፡21«***እውነት እውነት እላችኋለሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ሂድ ብትሉት ይሆንላችኋል***» ብሏል። እንዲሁም ለሐዋርያው «***እምነት ቢኖርህ ሳትጠራጠር ይህን ተራራ ተነቅለህ ሂድ ብትለው ይሆናል***» በማለት ተናግሯል። እውነተኛ ተአምር ለማድረግ መስፈርቱ በአምላክ ማመን ነው። ምክንያቱም ለአምላክ ደግሞ የሚሳነው ነገር የለምና።

## 1.7) <u>ከኢየሱስ የበለጠ ስራ መስራት እንደሚቻል</u>።

በዮሐንስ ወንጌል 14፡12«***እውነት እውነት እኔን የሚምን እኔ የምሰራውን ሥራ ይሰራል፤ እንዲያውም እኔ ወደ አብ ስለምሄድ <u>ከዚህ የበለጠ ሥራ ይሰራል</u>።***» ጥያቄ ኢየሱስ አምላክ ነው ካላችሁ ከእሱ የበለጠ መስራት ትችላላችሁን? ምክንያቱም ከዚህ የበለጠ ይሰራል ስለሚል ማለት ነው።

## 1.8) <u>ኢየሱስ "የሕይወት እንጀራ ነኝ" ስላለ አምላክ ስለመሰላቸው</u>።

ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ነብያት የሕይወት እንጀራ ናቸው። ማለትም ሁሉንም ነብያት ከተከተልናቸው ትእዛዛቸውን ከፈፀምን የሕይወት እንጀራ ማግኘታችን የሚያጠራጥር አይደለም። ነብያትን በመከተል ትእዛዝ የፈፀመ ሁሉ ትክክለኛ የሕይወት እንጀራ ያገኛል። ኢየሱስ ግን በዮሐንስ ወንጌል 6፡32 «***<u>እውነተኛ እንጀራ የሚሰጣችሁ ግን የሰማዩ አባቴ ነው</u>።***» ታዲያ ኢየሱስ የሚሰጠው ሐሰተኛ እንጀራ ነው ማለት ነው? ምክንያቱም እውነተኛ እንጀራ የሚሰጣችሁ የሰማዩ አባቴ ነው ስላለ።

## 1.9) "<u>ኢየሱስ እኔና አብ አንድ ነን" ስላለ ከአምላክ ጋር እኩል ስለመሰላቸው</u>።

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 10፡30«***<u>እኔና አብ አንድ ነን</u>***» ያለው ትምህርቱን እንጂ በስልጣን በመፍጠር በሁሉም ነገር እኩል እንደማይሆን ደግሞ ከዚሁ በዮሐንስ ወንጌል 14፡28«***<u>የምትወዱኝ ብትሆኑስ ከኔ አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላቸው ነበር</u>።***» ስለዚህ ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ነው ከተባለ ለምን ኢየሱስ ከእኔ አብ ይበልጣል አለ? ንግግሩ አይቃረንምን? ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ነኝ እኔ የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነኝ በሁሉም ነገር ስልጣን አለኝ መች አለ? የ1980 ዕትም በ1ኛ ቆረንቶስ 11፡3«***በክርስቶስም ላይ <u>ስልጣን</u> ያለው <u>እግዚአብሔር አብ መሆኑን እንድታውቁ እወዳለሁ (እፈልጋለሁ)</u>***» ይላል። ታዲያ ኢየሱስ ከአብ ጋር በስልጣን እኩል የሆነው የቱ ጋር ነው? ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 10፡29 ደግሞ«***<u>የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል</u>***» በማለት ያስተምራል። እግዚአብሔር አብ ከሁሉ እንደሚበልጥ ኢየሱስ በአንደበቱ ተናግሯል። ከኢየሱስ የበለጠ የማን ንግግር ይታመናል? አሁንም ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 5፡30 የ1980 ዕትም «***<u>እኔ</u>***

*በራሴ ስልጣን ምንም ማድረግ አይቻለኝም*» ብሏል። አምላክ ደግሞ ሁሉን ቻይ ነው አይደል። ኢየሱስ ግን እኔ በራሴ ስልጣን ምንም ማድረግ አልችልም ካለ በጥቅሱ መሰረት ኢየሱስ ደካማ አምላክ ነው ማለት ነው? በመጽሐፈ መዝሙር 22፡27-29 «----- *ስልጣን ሁሉ የእግዚአብሔር ነው።*» በዚህ ላይ ምንም ማብራራት የሚያስፈልገውና ግልፅ በሆነ ቋንቋ ተቀምጧል። ኢየሱስ እኔና አብ አንድ ነን ያለው ትምህርቱን ነው። ያ ማለት አምላክ አስተምር ያለው ትምህርት ኢየሱስ ያስተምራል ትምህርቱ የራሱ ሳይሆን የአምላኩ ንግግር የአምላኩን ትምህርት እንዲያስተምር አምላክ አስተምር ያለውን ብቻ ስለሚያስተምር ነው እኔና አብ አንድ ነን ያለው። ነገር ግን በስልጣን በመፍጠር በአምላክነት በፍፁም አይደለም። እኩል እንዳልሆነ ካሳለፍነው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አይተናል። የሚያስተምረው ትምህርት ከአብ እንደሆነ ደግሞ በዮሐንስ ወንጌል 7፡16 «*የሚያስተምረው ትምህርት ከላከኝ ከአብ የመጣው እንጂ ከእኔ አይደለም።*» ስለዚህ "እኔና አብ አንድ ነን" ማለቱ የሚያስተምረው ትምህርት ነው።

## 10) ኢየሱስ እኔ ሕይወት ነኝ ስላለ እርሱ አምላክ ስለመሰላቸው።

በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 12፡49-50 «*እኔ በራሴ ስልጣን አልተናገርኩም እኔ የምለውንና የምናገረውን ትእዛዝ የሰጠኝ የላከኝ አብ ነው። የእርሱም ትእዛዝ የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረው አብ የነገረኝን ነው።*» ጥቅሱን ተንተርሰን ጥያቄ አለን። ኢየሱስ የሚሰጠው ጊዜያዊ ሕይወት ነው ማለት ነው? የእግዚአብሔር ትእዛዝ ዘላለማዊ ሕይወት ለማግኘት ሲጠየቅ ምን እንደመለሰ እንመልከት፡- በማቴዎስ ወንጌል 19፡16 «*እነሆ አንድ ሰው ቀርቦ፡- የዘላለም ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ አለው? ኢየሱስም ስለመልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው። ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።*» መልካም የሆነ አንድ አምላክ ብቻ ነው እርሱም የዘላለም ሕይወት ነው። ትእዛዛቱን ለሚጠብቅ ሰው ይህን ጥያቄ አሁንም በሉቃስ ወንጌል 18፡18 ተጠይቆ መልስ ተሰቶበት እናያለን። «*ከአለቆችም አንዱ ቸር መምህር ሆይ! የዘላለም ሕይወትን እንድወርስ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው። ኢየሱስም ሰለምን ቸር ትሆናለህ? ከአንዱ እግዚአብሔር በቀር ማንም ቸር የለም። ትእዛዛቱን ታውቃለህ፡- አታመንዝር፣ አትግደል አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትና እናትህን*

***አክብር***።» አሁንም ኢየሱስ ስለ ዘላለም ሕይወት ሲጠየቅ የሰጠው መልስ ትእዛዛትን እንዲጠብቅና እንዲያከብር መከረው እንጂ እኔ አምላክህ ነኝ፤ በኔ እመን ወይንም እኔ እሞትልሃለሁ፤ የአንተን ኃጢአት እሸከምልሃለሁ፤ አንተም የዘላለም ህይወት ታገኛለህ አላለውም። በተጨማሪ «***የዘላለም ሕይወትን***» ቃላዊ ሌላ ትርጓሜ በመስጠትም ሆነ በመሰለን ከምንተረጉመው ይልቅ ኢየሱስ በአንደበቱ ግልጽና አጭር በሆነ መልኩ ትርጉሙን አስቀምጦታልና ሐቅን ላለመቀበል ከምናደርገው ዳርዳርታ ውጭ ሌላ ምክንያት የለንም። ትርጉሙ ምን እንደ ሆነ በዮሐንስ ወንጌል 17፡3 ላይ መልስ ይሰጠናል። «***እውነተኛ አምላክ ብቻህን የሆንከውን የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት***።» ኢየሱስ እንደ ገለጻልን የዘላለም ሕይወት የሚገኘው አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ በማምለክ እንጂ በሌላ አይደለም። እንዲሁም እንደ ሙስሊሞች ኢየሱስን የአምላክ መልእክተኛ መሆኑን በማመን ብቻ ነው። ስለዚህ ክርስቲያኖች ወደዚህ ቀጥተኛ መንገድ (ወደ እስልምና) እንድትገቡ በአክብሮት እንጋብዛችኋለን።

## 11) ***“«ቃልም ሥጋ ሆነ»” ስለሚል ኢየሱስ ከሦስቱ አምላክ አንዱ ስለመሰላቸው።***

ይህ አባባል በክርስቲያኖች ዘንድ ስር የሰደደ የሐሰት ማምታቻ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ ስጋ የለበሰ ሰው አምላክ ነው ማለት ትልቅ ስህተት ነው። ምክንያቱም አምላክ ሰው አይደለም፤ ሰውም አይመስልም። አምላክ ሰው አለመሆኑና ሰው አለመምሰሉ ተገልጿል። ወደ ርዕሳችን ስንመለስ እንደ መከራከሪያ ነጥብ አድርገው የሚወስዱት በዮሐንስ ወንጌል 1፡1 እና 1፡14 ያለውን ነው። በ1980 ዕትም ስናነብ የምናገኘው ይህን የመከራከሪያ አጀንዳ ውድቅ አድርጎት እናገኘዋለን። በዮሐንስ ወንጌል 1፡1«***ቃል በመጀመሪያ ነበረ፤ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ፤ ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ***።» በጥቅሱ መሰረት እኛ ሙስሊሞች የምናነሳቸው ጥያቄዎች አሉ። ጥቅሱ የሚለው “ይህም ቃል እግዚአብሔር ነበረ” ነው። ታዲያ «***ቃል ሥጋ ሆነ***» የሚሉትን አንቀፆች በመንተራስ ኢየሱስ እራሱ እግዚአብሔር ነው የምንል ከሆነ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከክርስቲያኖች መልስ አንፈልጋለን። ለምሳሌ በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡3 «***እግዚአብሔርም፡- ብርሃን ይሁን አለ፤ ብርሃን ሆነ***» ይላል። ስለዚህ «***ብርሃን***

***ይሁን***» የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ብርሃን አስገኝቷል ወይንስ ቃሉ ራሱ ወደ ብርሃን ተቀይሯል? ተቀይሯል የምንል ከሆነ ብርሃን አምላካችን ሆነ ማለት ነውን?! ይህ አባባል ደግሞ ግልጽ የሆነ ስህተት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። ሲቀጥል በሐዋሪያት ሥራ 12፡24 «***የእግዚአብሔር ቃል እየሰፋ ሄደ***» ይላል። እንዲህ ከሆነማ ገና ለወደፊት ለሚወለዱት ሰዎች ሁሉ አምላክ ሊሆኑ አይደል። ስለዚህ በኢየሱስ ብቻ መገደቡ የሚያዋጣ አይደለም። የሰው ዘር በሙሉ ለዚህ እድል ተጋሪ ናቸው የሚል ሐሳብ ስለሚያዝ ማለት ነው። ለማንኛውም ወደ እውነት ስንመጣ እግዚአብሔር በቃሉ ብቻ የሻውን ፍጥረት ይፈጥራል እንጂ ቃሉ አይቀየርም። ምክንያቱም ቃሉ ድርጊት ፈፃሚ ነውና። ቃሉ ይቀየራል እንዳይባል በትንቢተ.ሚኪያስ 3፡6«***እኔ እግዚአብሔር አልቀያየርም***» ብሏል። ስለዚህ ቃል ድርጊት ፈፃሚነትን እንጂ የኢየሱስን አምላክነትን አያመለክትም። በትንቢተ.ኢሳይያስ 55፡10-11«***ዘርንም ለሚዘራ፤ እንጀራንም ለሚበላ እንዲሰጥ እንጂ ወደ ሰማይ እንደማይመለስ ከአፌ የሚወጣ ቃል እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውን ያደርጋል የላኩትንም ይፈፅማል፤ እንጂ እኔ በከንቱ አይመለስም።***» ስለዚህ ኢየሱስ በቃሉ የተገኘ እንጂ እራሱ ያቃል ኢየሱስ አይደለም። ለዚያ ነው ጳውሎስ በ1ኛ ቆረንቶስ 3፡23«***ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።***» ስለዚህ በዚህ መሰረት «**ቃል**» የሆነው ክርስቶስ አምላክ ቢሆን ኖሮ ክርስቶስ እግዚአብሔር እንጂ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው ባልተባለ ነበር። ስለዚህ ኢየሱስ ከፍጡራን መካከል አንዱ ነው። አፈጣጠሩም ደግሞ እንደማንኛውም ሰው ነው። ያ ማለት በማሪያም ማኅፀን ተረግዞ እንደተወለደ ግልጽና የማይካድ ሐቅ ነው። ተጨማሪ በመጽሐፈ ኩፋሌ 10፡33«***ሰማይን የፈጠረ በምድር ላይ ዝናብን ጠለልን ያወርደውን በምድር ላይ ሁሉን የሚያደርገውን ሁሉንም በቃሉ የፈጠረውን ሕይወትንም ሁሉ ከእርሱ የሚገኘውን የሰማይን አምላክ አምልኩ።***» ስለዚህ ሁሉን ነገር እግዚአብሔር የፈጠረው በቃሉ ብቻ ነው። በዚህ መሰረት ኢየሱስ በቃሉ የተገኘ ነው ማለት ነው።

## 12) **"እግዚአብሔር ሰውን በመልካችን በአምሳላችን እንፍጠር" ስላለ ኢየሱስ ከሦስቱ አምላክ አንዱ ነው ብለው ስለሚያምኑ፡፡**

በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡26 «***እግዚአብሔርም አለ፡- ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር።***» «***እንፍጠር***» የሚለው አባባል ሦስትነትን ያመላክታል

ብለው ሁሉም የክርስትና ቡድኖች ያምናሉ። በመጀመሪያ ተናጋሪው ማን ነው? እግዚአብሔር ነው እንዳንል እሱ እንደሚናገር ጥቅሱ አያስረዳም። ምክንያቱም “እግዚአብሔርም አለ” ብሎ የተናገረው ሌላ ተራኪ ነው እንጂ የእግዚአብሔር ንግግር አይደለም። ለምሳሌ ራሱ ተናገረ ተብሎ የሚገመተው እንዲህ ብሎ ስለራሱ ሲገልጽ ነው። በትንቢተ.ሆሴዕ 11፡4‹‹***እኔ በመካከላችሁ ያለሁ ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለሁም።***›› ይህን ጥቅስ ስንመለከት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻው ተናጋሪው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን እንረዳል። ነገር ግን በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡26 ያለውን በምናይበት ጊዜ ‹‹**እግዚአብሔርም አለ፡-**›› በማለት የሚተርከው ሌላ ተራኪ ተናጋሪ መሆኑን ነው። ስለዚህ ይህን የአምላክ ንግግር ብለን አንደፍርም የተራኪው (የተናጋሪው) ንግግር ነው። ንግግሩም ስህተት ነው። ሲጀምር አምላክ አልወለደም አልተወለደም። ይወልዳል የምትሉ ከሆነ እግዚአብሔር ነው ሁለት አምላኮችን የወለደው? ምክንያቱም ‹‹**እግዚአብሔር አለ**፡-›› ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር ስላለ። ሲቀጥል ከዚህ ላይ የሚፈጥረው እግዚአብሔር እንጂ ሦስት አምላኮች አይደሉም። እግዚአብሔርም አለ ስለሚል ሦስቱ አምላኮች ቢሆኑ ኖሮ ‹‹**እግዚአብሔሮችም አሉ**›› ነበር የሚባለው። ሲቀጥል እግዚአብሔር ሰውን ከመሰለ ያ ማለት ደግሞ ጥቁር፣ ቀይ፤ ጠይም፣ ሐበሻ፣ ፈረንጅ ቀ.ዘ.ተ እያልን ልንገልጸው ነው ማለት ነው? ያ ከሆነ ከሚከተሉት ምዕራፍና ቁጥሮች ጋር ሐሳቡ አብሮ የማይሄድና የሚቃረን ነው። ምክንያቱም አምላክ ሰው እንደማይመስል በኦሪት.ዘኁልቁ 23፡19 ‹‹***ሐሰትም ይናገር ዘንድ እግዚአብሔር ሰው አይደለም።***›› አሁንም በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 15፡29 ‹‹***የእስራኤል ክብር የሆነው እግዚአብሔር አይዋሽም፤ አይፀፀትም፤ እርሱም ይፀፀት ዘንድ የሰው ልጅ አይደለምና።***›› አሁንም በድጋሚ በትንቢተ.ሆሴዕ 11፡9 ‹‹***እኔ በመካከላችሁ ያለው ቅዱስ አምላክ ነኝ እንጂ ሰው አይደለም***›› በማለት እግዚአብሔር ሰውና ሰውም እንደማይመስል ተናግሯል። ሌላው ‹‹**እንፍጠር**›› የሚለው እውን ቃሉ በሦስት ብቻ የተገደበ ነው? የተገደበ ነው የምትሉን ከሆነ በአሃዛዊ መገለጽ ነበረበት። ነገር ግን አልተገለጸም። ‹‹**እንፍጠር**›› የሚለው ይቅርና ሦስት አንድ ሚሊዮንና ከዚያ በላይ ቢሆንስ? ምክንያቱም በሦስት ስላልተገደበ ቃሉ ከሦስት በላይ መሆኑን የሚያሲዝ ስለሆነ ማለት ነው። በድጋሜ የሚከተሉትን ምዕራፎችና ቁጥሮች እንመልከታቸው በዚህ ጉዳይ አምላክ አንድ እንደሆነ እና ሦስት አምላክ እንደሌለ መልስ ይሰጡናል። በትንቢተ.ኢሳይያስ 43፡10-11‹‹***እኔም እንደሆንኩ ታስታውሉ ዘንድ እናንተን***

የመረጥኩትም ባሪያዬ ምስክሮቼ ናችሁ ይላል እግዚአብሔር። ከእኔ በፊት አምላክ አልተሰራም፤ ከእኔም በኋላ አይሆንም። እኔ፣ እኔ፣ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔ ሌላ የሚያድን የለም።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 44፡6«....እኔም ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኋለኛ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 45፡5-6«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔ ሌላ ማንም የለም። ከእኔም በቀር አምላክ የለም፤ በፀሐይ በውጫና በምዕራብ ያሉ ከእኔ በቀር ማንም ሌላ እንደሌለ ያውቁ ዘንድ አስጠነቀቅሁ፤ አንተ ግን አላውከኝም። እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም ሌላ ማንም የለም።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 45፡18«ሰማያትን የፈጠረ አግዚአብሔር እርሱ ምድርን የሰራና ያደረገ ያጸናትም መኖሪያም ልትሆን እንጂ ለከንቱ እንድትሆን ያልፈጠራት አምላክ እንዲህ ይላል፡- እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ የለም።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 46፡9«እኔ አምላክ ነኝና፤ ሌላም የለምና የቀድሞውን የጥንቱን ነገር አስቡ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ እንደ እኔም ያለ ማንም የለም።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 48፡12«---እኔ ነኝ እኔም ፊተኛው ነኝ፤ እኔም ኃይለኛው ነኝ፤ እጄም ምድርን መሰርታለች፤ ቀኝም ሰማያትን ዘርግታለች።» በትንቢተ.ሆሴዕ 13፡4 «እኔ ከግብጽ ምድር ጀምሬ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ አታውቅም፤ ከእኔም በቀር ሌላ መድኃኒት የለም።» በኦሪት.ዘዳግም 32፡39 «አሁንም እኔ ብቻዬን እንደ ሆንሁ፤ ከእኔ በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ፤--» ከዚሁ ምዕራፍ 4፡35«እግዚአብሔርም አምላክ እንደ ሆነ ታውቅ ዘንድ ይህ ለአንተ ተገለጠ፤ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም።» በትንቢተ.ኢዩኤል 2፡27«እኔም በእስራኤል መካከል እንዳለሁ፤ እኔ አምላካችሁ እንደ ሆንሁ፤ ከእኔም በቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ታውቃላችሁ።» ጥያቄ ለምሳሌ በትንቢተ.ኢሳይያስ 44፡6 «---እኔም ፊተኛ ነኝ፤ እኔም ኋለኛ ነኝ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለም» ብሏል። ታዲያ ሦስት አምላክ መኖሩ ለምን አልተገለጸም? በድጋሜ ከእኔ በፊት አምላክ አልተሰራም ለወደፊትም አይሆንም ካለ ኢየሱስ ከጊዜ በኋላ መምጣቱ ግልፅ አይደለምን? ኢየሱስም ከጊዜ በኋላ አምላክ እንደማይሆን በትንቢተ.ኢሳይያስ 43፡10-11 ላይ «ከእኔም በኋላ አይሆንም» ለምን አለ? አምላክ አንድ ከሆነ ታዲያ እንዴት ሦስት አምላክ ሊባል ቻለ? በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሱ ከሌለ ከየት መጣ? ወንይስ አዲስ መጽሐፍ ቅዱስ ወርዶ ይሆን? ጥያቄውን ከዚህ ላይ ላቁመውና ወደ እውነታ ስንገባ አምላክ አንድ አምላክ ብቻ ነው። በትንቢተ.ኤርሚያስ 10፡ 10-11«እግዚአብሔር ግን እውነተኛ አምላክ ነው፤ እርሱም ሕያው አምላክና የዘላለም ንጉሥ ነው።» በትንቢተ.ሆሴዕ 13፡4«አምላክህ እግዚአብሔር እኔ ነኝ።»

ነብያት ኢየሱስን ጨምሮ አንድ አምላክ እንደ ሆነ ብቻ ነው የሚያውቁት። ለአብነት ያክል፡- በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 8፡22 ***(ሰለሞን) «እንዲህ አለ፡- የእስራኤል አምላክ አቤቱ በላይ በሰማይ በበታችም በምድር አንተን የሚመስል አምላክ የለም።»*** ተጨማሪ 1ኛ ሳሙኤል 2፡2 ***«እንደ እግዚአብሔር ቅዱስ የለምና፤ እንደ አምላካችንም ፃድቅ የለምና ከአንተ በቀር ቅዱስ የለም።»*** በመጽሐፈ መዝሙር (ዳዊት) 86፡10 (ዳዊት) ***«አቤቱ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህ፤ አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና።»*** በኦሪት.ዘዳግም 6፡4 (ሙሴ) ***«እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው።»*** ኢየሱስም በማርቆስ ወንጌል 12፡29***«ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።»*** ለአብነት ያክል ያለፉ ነብያት የሚያውቁት አንድ አምላክ ብቻን ነው። አምላክ ራሱ እንዲህ ይላል፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 17፡1***«እኔ አልሻዳይ (ታላቅ) ነኝ።»*** በኦሪት.ዘሌዋውያን 19፡3-4***«እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፤ ወደ ጣዖታትም ዘወር አትበሉ፤ ቀልጠው የተሰሩትም የአማልዕክት ምስሎች ለእናተ አታድርጉ እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ።»*** በኦሪት.ዘፀአት 20፡2***«እግዚአብሔርም ይህን ቃል ሁሉ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡- ከግብፅ ምድር ከባርነት ቤት ያውጣውህ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ።»*** ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 20፡3-5***«ከኔ በቀር ሌሎች አማልዕክት አይሁንልህ። በላይ በሰማይ ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ፤ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፤ አትስገድላቸው፣ አታምልካቸውም።»*** እውነቱ ይህ ነው ሐቅን ለፈለገና እውነተኛውን ሃይማኖት ለመከተል ምርጫውን ለማስተካከል ማስረጃው ይኸው ነው።

## 13) ኢየሱስ ከእግዚአብሔር አብሮ ስለነበረ

ኢየሱስ ብቻ ሳይሆን ሌሎች ነብያትም ከእግዚአብሔር ጋር ነበሩ፡፡ ለአብነት እስማኤል በኦሪት.ዘፍጥረት 21፡20***«እግዚአብሔር ከብላቴናው ጋር ነበረ፤ አደገም፣ በምድረ በዳም ተቀመጠ፤ ቀስተኛም ሆነ፡፡»*** ዮሴፍ በኦሪት.ዘጸአት 39፡2 ***«እግዚአብሔር ከዮሴፍ ጋር ነበረ፤»*** ሙሴ በኦሪት.ዘጸአት 34፡28***«በዚያም አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከእግዚአብሔር ጋር ነበረ፡፡»*** ኢያሱ በመጽሐፈ ኢያሱ 6፡27 ***«እግዚአብሔርም ከኢያሱ ጋር ነበረ፤»*** ሰለሞን በመጽሐፈ ሣሙኤል 3፡19 ***«ሣሙኤልም አደገ፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፡፡»*** ዳዊት በመጽሐፈ ሣሙኤል 18፡14***«ዳዊት በአካሄዱ ሁሉ አስታውሎ ያድግ ነበር፤ እግዚአብሔርም***

***ከእሱ ጋር ነበረ።»*** ልብ በሉ! እስካሁን ያየናቸው የአምላክ ነብያት ከእግዚአብሔር ጋር ነበሩ፡፡ ኢየሱስም በዚህ ስሌት ካየነው በትንቢተ.ኢሳይያስ ትርጉሙም፡- እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው ማለት ነው» ይላል፡፡

## 14) ማጠቃለያ ትኩረት ማድረግ ያሻል።!!!

ሁሉም ነብያት ተአምር የሚያደርጉት በአምላክ ፈቃድ እንጂ በራሳቸው ኃይልና ፈቃድ አይደለም። አምላክ ለተለያዩ ነብያት ተአምራትን የሚሰጣቸው ሕዝቦቻቸው ትምህርቱን እንዲቀበሉና በነብይነታቸውም እንዲያምኑባቸው እንጂ ለሌላ ዓላማ አይደለም። ተአምር ማድረግ ለአንድ ነብይ እንግዳ ነገር አይደለም። ለምሳሌ፡- ለነብዩ ዳዊት ብረትን አገራለት፤ ለነብዩ ሰለሞን ንግስናን ሰጠው፤ አዕዋፋትን እንዲያናግሩትና ቋንቋቸውንም እንዲያውቅ አደረገው። እንዲሁም ለነብዩ ሙሴ በአንዲት ብትር ባህሩን ለሁለት እንዲከፈልለትና እጁን እንደመብራት እንዲጠቀምበት አደረገ። ስለዚህ እነዚህና መሰል ተአምራቶች በሌሎች ነብያትም ታይተዋል። በኢየሱስ የታየው በሌሎች ነብያትም ታይተዋል። ተአምር የሚያደርግ አምላክ እግዚአብሔር እንጂ ነብያት አይደሉም። ለዚህም ነው በመጽሐፈ መዝሙር 72፡18 ***«ይህን ሁሉ ተአምራት የሚያደርግ እርሱ ብቻ ስለሆነ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 77፡14 ***«ተአምራትን የምታደርግ አምላክ አንተ ነህ፤ አንተ በመንግስትህ መካከል ኃይልህን አሳይተኸኛል።»*** ተጨማሪ በመጽሐፈ ኢዮብ 34፡14***«ቁም! የእግዚአብሔርን ተአምር አስብ»*** አሁን የበለጠ ግልጽ ይሆንልናል። ሁሉን ተአምራት የሚያደርገው አንድ እግዚአብሔር (አንድ አላህ) መሆኑን ነግሮናል። ኢየሱስ ያደረገው ተአምር የራሱና በራሱ ኃይል እንዳልሆነ በዮሐንስ ወንጌል 10፡25 ***«በአባቴ (በአምላኬ) ስም የማደርጋቸው ተአምራቶች ስለኔ ይመሰክራሉ»*** ብሏል። ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ የ1980 ዕትም 10፡22 ***«ከአብ የሆኑ ብዙ ተአምራቶችን አሳያችኋለሁ።»*** ስለዚህ ኢየሱስ ያደረገው ታዓምር በአምላኩ ስም ነው እንጂ በእራሱ ኃይል እንዳልሆነ በእራሱ አንደበት የምስክር ቃል እናገኛለን። በመቀጠል የ1993 ዕትም በማርቆስ ወንጌል 6፡4***«ኢየሱስ ግን ነብይ በሌሎች ዘንድ ይከበራል፤ በገዛ ሀገሩ፣ በዘመዶቹና በቤተሰቡ ግን ይናቃል ሲል መለሰላቸው። በዚያም በጥቂት ሕመምተኞች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር ሌላ ታዓምር ማድረግ አልተቻለውም»*** ይለናል። "‹አሳ ጎርጓሪ ዘንዶ ያወጣል›"

አሉ። ክርስቲያኖች ኢየሱስን ብቻ የተአምር ባለቤት አድርጋችሁ ስታቀርቡልን ነበር። ነገር ግን መጽሐፉ አውነቱን አጋለጠው። አላህም እውነትን ያነግሳል፤ ሐሰትን ያረክሳል፤ በጣም የሚገርመው ደግሞ ቀጥሎ ያለው ነው።

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

# ኢየሱስ (ዒሳ) በኢስላም ዕይታ

ኢየሱስ ከተከበሩት ነብያት አንዱ ነው። አፈጣጠሩም ከሰው የተለየ አይደለም። በአጠቃላይ እኛ ሙስሊሞች ለኢየሱስ ካለን ውዴታና ትልቅ ቦታ የተነሳ በነብይነቱ እናምንበታለን፤ እናከብረዋለንም። ለእስራኤል ሕዝቦች የተላከ መላክተኛ መሆኑን እናምናለን፤ እንመሰክራለን። አፈጣጠሩም በተአምር ከመርየም እንደተወለደ ሙሉ እምነት አለን። ያ ማለት በተአምር መወለዱ አምላክ ያደርገዋል ብለን አንደፍርም። ምክንያቱም አላህ በተአምር ከፈጠራቸው ፍጥረቶች ኢየሱስ የተለየ አይደለም። ለምሳሌ፡- አደም ያለ አባት እና ያለ እናት ተፈጥሯል። ኢየሱስን አላህ እንዴት እንዳስገኘው ከውልደቱ እንጀምር፡- አላህ (ሱ.ወ) የሰውን ልጅ በተለያየ መንገድ ፈጥሯል። ይህን አስመልክቶ አላህ (ሱ.ወ) ሰዎችን በአራት (4) መንገዶች ፈጥሯል።

1. ያለ ወንድና ሴት አንዲትን ነፍስ (አደምን) ፈጠረው
2. ከወንድ ብቻ ከአደም የጎን አጥንት (ሔዋንን) ፈጠራት
3. ከሴት ብቻ ከመርየም ያለወንድ ዒሳን (ኢየሱስን) ፈጠረ
4. ከወንድና ከሴት ከአደምና ከሐዋ ቀሪዎችን ፍጥረታት ተፈጠሩ እነዚህን አራቱን የሰው ልጅ አፈጣጠር ሰፋ ባለመልኩ በዝርዝር የምንመለከታቸው ይሆናል።

## 1) <u>ያለ ወንድና ያለ ሴት አደምን ፈጠረ</u>።

የአደም አፈጣጠር ከኢየሱስ አፈጣጠር ጋር ስናወዳድረው የአደም አፈጣጠር ይደንቃል። ኢየሱስ ካለ ነገር የተገኘ ነው። ማለትም ከእናቱ ከመርየም በተአምር የተገኘ ነው። አደም ደግሞ ከለለ ነገር የተገኘ ነው። የአደም እናትም ሆነ አባት የሉትም። አደም እንዴት እንደተፈጠረ ቁርኣን በሚከተለው ምዕራፍ መልስ ይሰጠናል። በሱረቱል አል-ኒሳእ 4፡1 ‹‹**እናንተ ሰዎች ሆይ ያንን ከአንዲት ነፍስ የፈጠራችሁን አላህን ፍሩ**።›› ተጨማሪ በሱረቱል አል-አዕራፍ 7፡189‹‹**እርሱ የአንዲት ነፍስ (አደምን) የፈጠራችሁ ነው**።›› በእነዚህ የቁርኣን ጥቅሶች መሰረት አላህ (ሱ.ወ) የሰውን ልጅ መፈጠር ሲጀምር ያለ ወንድ ያለ ሴት አንዲትን ነብስ አደምን መፍጠሩን እንረዳለን። ወደ ሁለተኛው የአፈጣጠር መንገድ ምንድ ነው

ወደሚለው ነጥብ ከመግባቴ በፊት ይህ አንዲት ነፍስ አደም እንዴት ሆኖ እንደተፈጠረ እንዴት ሆኖ ወደ ሕይወት እንደመጣ በአፈጣጠሩ ሂደት ያሳለፋቸውን የሕይወት ኡደት (life cycle) እንመለከት፡-

## ለምሳሌ ከአፈር

አላህ (ሱ.ወ) በሱረቱል አል-ኢምራን 3፡59‹‹**አላህ ዘንድ (በአፈጣጠር) የዒሳ (የኢየሱስ) ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው። አላህ አደምን ከአፈር ፈጠረው። ከዚያ ለእርሱ (ሰው) ኹን አለው ሆነም።**›› ተጨማሪ በሱረቱል አል-ከሐፍ 18፡ 37‹‹**ጓደኛው (አማኙ) እርሱ ለእርሱ የሚመላሰለው ሲሆን፤ ከዚሁ ከአፈር በፈጠር ከዚያም ሰው ባደረገህ አምላክ ካድክን?**›› አለው። አሁንም በሱረቱል አል-ሐጅ 17፡5፣ በሱረቱል ጧሐ 20፡55፣ በሱረቱል ሩም 30፡20፣ በሱረቱል ፋጢር 35፡11 እና በሱረቱል አል-ጋፊር 40፡67 ላይ ተመልከቱ።

## ከጭቃ

የሰው ልጅ መጀመሪያ ላይ አፈር ነበር፤ ከዚያም ውኃ ሲጨመር ወደ ጭቃነት ተቀየረ።ስለዚህም አደም ከጭቃ ተፈጠረ በሚል አገላለጽ ተጠቀመ። በሱረቱል አል-አንዓም 6፡2 ‹‹**እርሱ (አላህ) <u>ያ ከጭቃ የፈጠራችሁ</u>፤ ከዚያም (የሞት) ጊዜ የወሰነ ነው። እርሱም ዘንድ (ለትንሳኤ) የተወሰነ ጊዜ አለ። ከዚያም እናንተ (በመቀስቀሳችሁ) ትጠራጠራላችሁን?** በሱረቱል አል-አዕራፍ 7፡12‹‹**አላህ ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው፤ (ኢብሊስን) እኔ ከርሱ የበለጥኩኝ ከእሳት የፈጠርከኝ እርሱን ግን (አደምን) <u>ከጭቃ ፈጠርከው አለ</u>።**›› በሱረቱል አል-ኢስራዓ 15፡61 ‹‹**ለመላእክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ አስታውስ ወዲያውኑም ሰገዱ። ኢብሊስ ብቻ ሲቀር <u>ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው</u> እሰግዳለሁን? አለ።**›› ተጨማሪ ሱረቱል ሷድ 38፡71፣ በሱረቱል አል-ሙዕሚኑን 23፡12፣ በሱረቱል አል-ሰጅዳህ 32፡7፣ በሱረቱል አል-ሷፋት 31፡11 ላይ ተመልከቱ።

## ከሚገማ የሆነ ጥቁር ጭቃ

ጭቃው በደንብ ቦኩቶ ሲተው መልኩ ይጠቁራል፤ ጠረኑም ይገማል። ስለዚህ አደም ከሚገማ የሆነ ጥቁር ጭቃ እንደተፈጠረ በቀጣዩ አንቀጽ ተገልጿል።

በሱረቱል አል-ሒጅር 15፡26‹‹**እኔ ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው፡፡**›› ከዚሁ ምዕራፍ 15፡33 ‹‹**ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከግም ጭቃ ለፈጠረው ሰው (ለአደም) ልሰግድ አይገባኝም አለ (ኢብሊስ)፡፡**››

## ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ

የተበካው ጭቃ እስኪደርቅ ድረስ ሲተውና ከአንድ ነገር ጋር ሲጋጭ ኪል ኪል የሚል ድምፅ ስለሚሰጥ (አደም) ከሚቅጨለጨል ጭቃ እንደተፈጠረ ተገልጿል፡፡ በሱረተል አል-ረህማን 55፡14‹‹**ሰውን እንደሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠርነው፡፡**››

## የሕይወት መንፈስ በመንፋት

በሱረቱል አል-ሒጅር 15፡29‹‹**ፍጥረትን ባስተካከልኩበትና በውስጡ መንፈሴ በነፋሁበት ነፍስ በዘራሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሆናችሁ ውደቁ፡፡**›› በሱረቱል አል-ሰጂዳህ 32፡9‹‹**ከዚያም (ቅርጹን) አስተካከለው በእርሱ ውስጥም ከመንፈሱ ነፋበት (ነብስ ዘራበት) ለእናንተም ጆሮዎችን አይኖችንና ልቦችን አደረገላችሁ በጣም ጥቂትን ብቻ ታመሰግናላችሁ፡፡**››

## 2) አደምን አላህ በእጁ ፈጠረው፡፡

በሱረቱል ሷድ 38፡75‹‹**አላህም ኢብሊስን አለው በሁለት እጆቼ በፈጠርኩት ከመስገድ ምን ከለከለህ? አሁን ኮራህ ወይስ (ፊትኑ) ከትዕቢተኞች ነበር አለው፡፡**›› ከላይ ባሳለፍነው ርዕስ ላይ ሰፋ ባለ ትንታኔ አደም የተፈጠረበትን መንገድ አይተናል፡፡

## 3) ከወንድ ብቻ ከአደም የጎን አጥንት ያለ ሴት (ሔዋንን) ፈጠረ፡፡

በሱረቱል አል-ኒሳእ 4፡1‹‹**እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ ከ (አደም) የፈጠራችሁን ከእርሷም መቆናጀዋን (ሔዋንን) የፈጠረውን ፍሩ፡፡**›› በሱረቱል አል-አዕራፍ 7፡89‹‹**እርሱ ያ ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁ ከርሷም መቀናጀዋን (ሔዋን) ወደ እርሷ ይረካ ዘንድ ያደረግነው፡፡**›› አሁንም በሱረቱል አል-ዙመር 39፡6‹‹**ከአንዲት ነፍስ ለፈጠራችሁ ከዚያም መቀናጀዋን (ሔዋንን) አደረገ፡፡**››

## 4) <u>ከወንድና ከሴት ከአደምና ሔዋን የተፈጠሩ ብዙ ፍጥረታት አስገኘ</u>።

በሱረቱል አል-ሑጁራት 49፡13 ‹‹**እናንተ ሰዎች ሆይ! ከአንዲት ነፍስ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁ ጎሳዎችን ነገዶች አደረጋችሁ አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪ ነው። አላህ ግልጽና አዋቂ ውስጡንም አዋቂ ነው**።›› በሱረቱል አል-ኒሳእ 4፡1‹‹**እናንተ ሰዎች ሆይ! ያንን ከአንዲት ነፍስ አደም የፈጠራችሁን ከእርሱዋም መቀናጀዋን (ሔዋን) የፈጠረው ከእነርሱ (ከአደምና ከሐዋ) ብዙ ወንዶችና ሴቶች የበተነውን (ያበዛውን) ጌታችሁን ፍሩ**።››

### ሀ) <u>ከፍትወት ጠብታ</u>፡-

በሱረቱል ካህፍ 18፡37‹‹**እርሱ (አማኙ) እርሱ የሚመሳሰለው ሲሆን፤ በዚያ ከአፈር ከዚያምከፍትወት ጠብታ ከፈጠረህ---**።›› በሱረቱል አል-ነጅም 53፡ 45-46 ‹‹**እርሱ ሁለቱን አይነቶች ወንድና ሴትን ፈጠረ። ከፍትወት ጠብታ (በማኅፀን ውስጥ) በምትነፍስበት ጊዜ**።›› በሱረቱል አል-ኒሳእ 4፡76‹‹**እኛ ሰውን በሕግ ግዳጅ የምንሞክረው ስንሆን ቅልቅሎች ከኾኑት የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው ሰሚና ተመልካችም አደረግነው**።›› በተጨማሪ በሱረቱል አል-ሙዕሚኑን 23፡12-13፣ በሱረቱል ፋጢር 35፡11፣ በሱረቱል ያሲን 36፡77፣ በሱረቱል አል-ጋፊር 40፡67፣ በሱረቱል አል-ቂያማህ 75፡35፣ በሱረቱል አል-ነህል 16፡4 እና በሱረቱል አል-ሙርሰላት 77፡20 በበለጠ ይመልከቱ።

### ለ) <u>ከረጋ ደም</u>፡-

የፍትወት ጠብታ ከ40 ቀን በኋላ የረጋ ደም ይሆናል። በሱረቱል አል-አለቅ 96፡1-2 ‹‹**አንብብ በዚያን ሁሉን በፈጠው ጌታ ስም ሰውን ከረጋ ደም በፈጠው (ጌታ ስም)**።›› በሱረቱል አል-ሙዕሚኑን 23፡12-14‹‹**በእርግጥም ሰውን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያም በጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው። ከዚያም ጠብታዋን በአርባ (40) ቀን የረጋ ደም አደረገን ፈጠርን**።›› በተጨማሪም በሱረቱል አል-ጋፊር 40፡67፣ አል-ሐጅ 25፡5 እና በሱረቱል አል-ቂያማህ 75፡36-38 ላይ ይመልከቱ።

### ሐ) <u>**የሚላመጥ የሆነ ቁራጭ ስጋ**</u>፡-

በሱረቱል አል-ሐጅ 22፡5‹‹**ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም ከዚያም ቁራጭ ስጋ** ---፡፡›› በሱረቱል አል-ሙዕሚኑን 23፡12-14‹‹**ከዚያም በጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው፡፡ ከዚያም ጠብተዋን (በ40 ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርነው፡፡ የረጋውን ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን**---፡፡››

### መ) <u>**በሦስት ጨለማ ውስጥ**</u>፡-

(ከሀ-ሐ) የተመለከትናቸው ክስተቶች ሁሉ በሶስት ጨለማዎች ውስጥ ከሆድ በማህፀንና በእንግዴ ልጅ ከመፈጠሩ በኋላ (ሙሉ) መፈጠርን ይፈጥራቸዋል፡፡ በተለይም ይህ አውነታ የዘመናችን ሳይንስ የደረሰበትና ያረጋገጠው ነው፡፡ በሱረቱል አል-ዙመር 39:6‹‹**በእናቶቻችሁ ሆድ ውስጥ በሦስት ጨለማዎች ውስጥ <u>በሆድ በማኅፀንና በእንግዴ ልጅ</u> ከመፈጠሩ በኋላ ሙሉ ፍጥረትን ይፈጥራችኋል፡፡ ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም ከቁራጭ ስጋ ለጥቆ ሰው ያደርጋችኋል፡፡**››

### በ) <u>**ከሴት ብቻ ከመርየም ያለ ወንድ ዒሳን (ኢየሱስን) አስገኘ፡፡**</u>

ከሴት ብቻ ያለ ወንድ (ኢሳን) ኢየሱስን አስገኘ፡፡ በሱረቱል አል-ኢምራን 3፡ 45-7 **‹‹መላአክት ያሉትን (አስታውስ) መርየም ሆይ! አላህ በርሱ ከሆነው ቃል ስሙ (አል መሲህ ዒሳን) የመርየም ልጅ በዚህ አለምና በመጨረሻው ቀን (አለም) የተከበረ ባለሟሎችም በሆነ (ልጅ) ያበስራሻል፡፡ በሕፃንነቱና በሕፃንነቱ (እድሜው 30/40) የሆኑ ሰዎችን ያነጋግራል፤ ከመልካሞችም ነው (አላት) ፡፡ (መርየምም) ጌታ ሆይ! ሰው ያልነካኝ (በግንኙነት) ስሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች፡፡ አላህም የሚሻን ይፈጥራል፤ አንዳች በሻ ጊዜ ለእርሱ ኹን ይለዋል፤ ወዲያውም ይሆናል አላት፡፡**›› ዋናው የመነጋገሪያ ነጥባችን ይህ ይሆናል ማለት ነው፡፡ በዚህ በቅዱስ ቁርኣን ጥቅስ መሰረት ዒሳ (ኢየሱስ) (ዐ.ሰ) ከሴት ብቻ ያለ ወንድ መፈጠሩን እንረዳለን፡፡ እስኪ ጥቅሱን ሰፋ አድርገን እንመልከት፡፡ ‹‹<u>**መላአክት ያሉትን አስታውስ›› የሚለው ቃል መርየም ዘንድ ተልኮ የመጣው መልአኩ ጅብሪል (ገብርኤል) መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ‹‹መላአክት›› በማለት ብዙ ቁጥሩን መጠቀሙ ለነጣላ አካል የብዙ ቁጥርን ስሜ መስጠት በሚለው ሕግ መሰረት ለጅብሪል የተሰጠ የክብር ስያሜ ወይም ደግሞ አብሳሪዎች መላከቶች**</u>

**<u>ሆነው ወደ እርሷ ዘንድ በመምጣት የተናገረው ግን ጅብሪል (ገብርኤል) ብቻ መሆኑን ያሳየናል</u>።**» ይህም የመላክት አለቃ በመሆነው ጅብሪል (ገብርኤል) በዚህ አጠራር መጠራቱን ያሳየናል እንጂ ብዙ መላክቶች እሷዘንድ መምጣታቸውን አያሳይም። ለማንኛውም አላህ (ሱ.ወ) የሚሳነው ነገር የለምና ዒሳም (ኢየሱስ) ሆነ ሌሎች ፍጥረታትንመፍጠር የአላህ የይሁን ቃል ብቻ ነው የሚያስፈልገው። ለዚህም ማስረጃ በሱረቱል አል-ነሕል 16፡40«**ለማንኛውም ነገር መኾን በሻ ጊዜ ቃላችን ለእርሱ ኹን ማለት ብቻ ነው። ወዲያውኑም ይሆናል።**» በሱረቱል አል-በቀራህ 2:117«**ሰማያትንና ምድርን ያለ ብልጫ የፈጠረ ፈጣሪ ነው ነገርንም (በማስገኘት) በሻ ጊዜ ለርሱ የሚለው። ኹንነው ወዲውም ይሆናል።**» ተጨማሪ በሱረቱል ያሲን 36፡82፣ በሱረቱል አል-ጋፊር 40፡68 --- ይመልከቱ። ይህን ካየን በመጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ እንዴት እንደ ተፈጠረ ደግሞ ለግንዛቤ ያክል እንመልከት። በሉቃስ ወንጌል 1፡26-38«***በስድስተኛውም ወር መላኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ገሊላ ከተማ ከዳዊት ወገን ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰው ሄዶ ወደ ታጨች አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ የድንግሊቱ ስም ማርያም ነበር። መላአኩም ወደ እርሷ ገብቶ ደስ ይበልሽ፤ ጸጋ የምላብሽ ሆይ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው። ከሴቶች መካከል የተባርክሽ ነሽ አላት። እርሷም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች። መላአኩም እንዲህ አላት፡- ማርያም ሆይ! በእግዚአብሔር ፊት ፀጋ አግኝተሻል፤ አትፍሪ፤ <u>እንሆ ትፀንሻለሽ፤ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፤ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ</u>። ምንም ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው። መላአኩም መልሶ እንዲህ አላት፡- መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል። የልዑል ኃይልም ይፀልይሻል። መላአኩም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና። ማርያምም እንሆ የጌታ ባሪያ እንደቃልህ ይሁንልኝ አለችው።***» ከዚያም በሉቃስ ወንጌል 1፡31 «***<u>እንሆ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ</u>።***» ከዚህ ላይ ኢየሱስ እንደማንኛውም ሰው ተረግዞ እንደሚወለድና ወንድ ልጅ እንደሚሆን ተገልጿል። ቀጣይ ያለው ምዕራፍ በበለጠ ያብራራልናል። በዮሐንስ ወንጌል 12፡2«***<u>እርሷም ፀንሳ ነበር፤ ምጥም ተይዛ ተጨንቃ ጮኸች</u>።***» ፣ በሉቃስ ወንጌል1፡6-7«***<u>በዚያም እንዳሉ የምትወልድበት ጊዜ ደረሰ፤ የበኩር ልጅ የሆነውን ወንድ ልጅ ወለደች</u>።***» ከዚህ ላይ ጥቅሱ እንደሚያስረዳን ማርያም አርግዛ የምትወልደው አምላኳን ሳይሆን ወንድ ልጅ የሆነውን ኢየሱስን ነው። ቁኣንም ተረግዞ እንደተወለደ በሱረቱል መርየም 19፡22-23«**ወዲያውኑም አረገዘች፤**

**በርሷም (በሆድዋ) ይዛው ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች፤ ምጡም ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት።›› ዒሳ (ኢየሱስ) እንደማንኛውም መልእክተኛ እንጂ የተለየ ነብይ አልነበረም። በሱረቱል አል-ኢምራን 3፡59‹‹**አላህ ዘንድ (በአፈጣጠር) የኢሳ (የኢየሱስ) ምሳሌ እንደ አደም ብጤ ነው። ወዲያውም አደምን ከአፈር ፈጠረው፤ ከዚያም ለርሱ (ሰው) ኹን አለው ሆነም።**›› ከዚህ ላይ በመጽሐፍ ቅዱስም ***ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ነው ያላት መላአኩ ለማርያም።*** በሉቃስ ወንጌል ላይ ‹‹**ኹን**›› የሚለው ቃልም በመጽሐፍ ቅዱስ በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡3 ‹‹***እግዚአብሔርም ብርሃን ይሆን አለ፡- ብርሃንም ሆነ።***›› ‹‹***ብርሃን ይሁን***›› የሚለው የእግዚአብሔር ቃል ብርሃንን አስገኘ? ወይንስ ቃሉ ብርሃን ሆነ? ብለን ማንኛውንም ክርስቲያን ብንጠይቅ የሚመልሱልን መልስ በቃሉ አማካኝነት ብርሃን ተገኘ እንጂ ሌላ አይሉም። ምክንያቱም ይህንን ሀሳብ ሊደግፍ የሚችል ሌላ ጥቅስ አለና። በትንቢተ.ኢሳይያስ 55፡11‹‹***ከአፌ የሚወጣው ቃሌ እንዲሁ ይሆናል፤ የምሻውንም ያደርጋል። የላኩትንም ይፈፅማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም***›› ይላል። በዚህ መሰረት እንግዲያውስ ቃሉ ድርጊትን ፈፃሚ ከሆነ ዒሳ (ኢየሱስ) በአላህ ቃል የተገኘ ነው ማለት ያለብን ወይንስ ቃሉ ራሱ ኢሳ (ኢየሱስ) ሆነ? ‹**ኢማሙ አህመድ ኢብኑ ሀንበል እንዲህ ይላሉ፡- ኢሳ (ኢየሱስ) ኹን በሚል ቃል ተፈጠረ። ሻዚ ኢብኑ ያህያ (ረ.ዐ) እንዲህ ይላሉ፡- ቃሊቱ ራሷ ኢሳ (ኢየሱስ) አልሆነችም። ነገር ግን በቃሊቱ ኢሳ (ኢየሱስ) ተገኘ።**› ለዚህ ማጠናከሪያ በሱረቱል አል-ተውባ 9፡5‹‹**ከአጋሪዎች አንዱ ጥገኝነት ብጠይቅህ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው።**›› ስለዚህ ዒሳ (ኢየሱስ) በአላህ የይሁን ቃል የተገኘ ነው። ከዚያም ኢየሱስ እንደማንኛውም ሰው ጡት መጥባቱና ምግብ መብላቱ መጠጥ መጠጣቱ ለምሳሌ ጡት መጥባቱ በሉቃስ ወንጌል 11፡27 ‹‹***ይህንን ሲናገር ከሕዝቡ አንዲት ሴት ድምጿን ከፍ አድርጋ የተሸከመችህ ማኅፀንና** **<u>የጠባኸቻው ጡቶች ብፁአን ናቸው አለችው</u>***።›› መመገቡን በማቴዎስ ወንጌል 11፡19 ‹‹***የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ።***›› በተጨማሪም በማርቆስ ወንጌል 11፡12፤ እንዲሁም በሉቃስ ወንጌል 24፡42‹‹***በዚህ አንዳች የሚባላ አላችሁን አላቸው። እርሱም ከተጠበሰ አንድ ቁራጭ ዓሳ ከማር ወለላም ሰጡት ተቀብሎም በፊታቸው በላ።***›› አላህ (ሱ.ወ) በሱረቱል አል-ማኢዳህ 5፡75 ‹‹**የመርየም ልጅ አል መሲህ ከፊቱ መልክተኞች በእርግጥ ያለፉ የሆነ መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት ሁለቱም <u>ምግብን የሚበሉ</u> ነበሩ።**›› ከተበላ ከተጠጣ በኋላ ምን ይከተላል? የማይነገር ነገር አለ አይደል?

በአጭሩ ይህን ካየን ማለትም ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ሰው ምግብና መጠጥ ከበላና ከጠጣ ከዚህ በፊት እንደ አለፉት ነብይ ነው። ኢየሱስ ነብይነቱም ወደ በኒ እስራኤል ብቻ ነው የተላከው። በማቴዎስ ወንጌል 10፡5«***ኢየሱስ እነዚህን አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያቶች ኢየሱስ ሲልካቸው እንዲህም አለ፡- በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ። ወደ ሳምራዊያንም ከተማ አትግቡ፤ ይልቅስ ወደ እስራኤል ቤት ወደ ሆኑት ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 15፡24«***እርሱም መልሶ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች ብቻ አልተላኩም አለ።***» ከተደበቁት አውነታዎች መካከል በ1816 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ አራቱ ወንጌሎች ከታተሙት ውስጥ በማቴዎስ ወንጌል ካለይ ከተቀሰኩት ምዕራፍ 15፡24 በገፅ 40 ላይ እንዲህ ይላል፡- «***እኔ የተላኩት ለእስራኤል ሕዝቦች ነው፤ እንዲሁም ስሙ አህመድ በሆነው የማበሰር ነኝ***» ይላል። ተጨማሪ በስንክ ሳር በሚባለው መጽሐፍ «***ኢት ይትመፅ ምድረ አረብ ካዓባ እስሙሁ አህመድ፤ ሙሐመድ አማኑኩም ይባልኩም***» በማለት ይናገራል። ከዚህ እንደምንረዳው ኢየሱስ የተላከው ለበኒ እስራኤል ሕዝቦች ብቻ ነው የሚያመለክተው። ቁርኣን በሱረተል አል-ኢምራን 3፡9 «**ወደ እስራኤል ልጆችም መላክተኛ ያደረገዋል።**» በድጋሜ በሱረተል አል-ሦፍ 61፡6«**የመርየም ልጅ ኢሳ (ኢየሱስ) የእስራኤል ልጆች ሆይ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልእክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማብሰር ሲሆን ወደ እናንተ የተላኩ የአላህ መልእክተኛ ነው ባለ ጊዜ አስታውስ። በግልጽ ተአምራቶችን በመጣቸውም ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ።**» ኢየሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለአለም እንደሚላኩ ተናግሯል። ኢየሱስ እንደ ሆነ ለአለም እንዳልተላከ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24 ላይ አይተናል። እንዲሁም ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24 ላይ የተናገረውን ቁርኣን በሱረቱል አል-ሦፍ 61፡6 ያለውን አዛምዱ ምን ያክል የትርጉም ተመሳሳይነት እንዳለ በግልጽ እንረዳለን። በዩሐንስ ወንጌል 14፡16«***ብትወዱኝ ትዕዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን አምናለሁ፤ ለዘላለም ከእናንተ ጋር እንድኖር ሌላ አፅናኝ ይሰጣችኋል።***» ከዚሁ ምዕራፍ 16፡7«***እኔ እውነት እነግራችኋለሁ እኔ እንድሄድ ይሻለኛል። እኔ በልሄድ አፅናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን ይልክላችኋል።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 16፡13«***እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት መንፈስ ይመራችኋል። የሚሰማውንም ሁሉ ይናገራል እንጂ ከራሱ አይናገርም። የሚመጣውንም ይነግራችኋል።***» በመጽሐፍ ቅዱስ ይህን ካየን የበለጠ ለማረጋገጥ በቁርኣን እንመልከት። በሱረቱል አል-ሦፍ 61፡6«**የመርየም**

**ልጅ ኢሳ (ኢየሱስ) የእስራኤል ልጆች ሆይ! እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መላዕክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ሲሆን ወደ እናንተ የተላከ የአላህ መላዕክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ አስታውስ።»** ኢየሱስ ወደ ፊት የሚመጣውን ነብይ ከስሜቱ እንደማይናገር ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራ ተናግሯል። ይህን ንግግሩን በሚከተለው የቁርኣን አንቀጽ እናዛምድ። በሱረቱል አል-ነጅም 93፡2-5«**ነብዩ (ሙሐመድ) አልተሳሳተም፤ አልጠመመም፤ ከልብ ወለድ አይናገርም። እርሱ (ንግግሩ) መለኮታዊ የሚወርድ ራዕይ እንጂ ሌላ አይደለም**» በማለት ቁርኣን ይነግረናል። ለበለጠ መረጃ ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሳቸው በሚለው ርዕስ ላይ ይመልከቱ።

## ዒሳ (ኢየሱስ) አልተሰቀለም፤ ተሰቅሎ አልሞተምም።

በዮሐንስ ወንጌል 20፡17 «***ኢየሱስ እኔ ወደ አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላክና ወደ አምላካችሁ አርጋለሁ ብለሽ ንገሪያቸው***» ብሎ ለማርያም ኢየሱስ ተናግሯል። ከዚህ ላይ ተሰቅሎ እንደሚሞት ሳይሆን እንደሚያርግ ነው። ክርስቲያኖች ኢየሱስ ሞቷል፤ ተሰቅሏል፣የምትሉን ከሆነ፡- በኦሪት.ዘዳግም 21፡22 «***ማንም ሰው ለሞት የሚያበቃውን ኃጢአት ቢሠራ እንዲሞት ቢፈረድበት በእንጨት ላይ አትሰቀለው፤ በእንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአሔር ዘንድ የተረገመ ነው***» ይላል። ስለዚህ ኢየሱስ የተረገመ ነው ማለት ነው? እንደ እናንተ አባባል ኢየሱስ ባይረገምማ መች ተስቅሎ ይሞት ነበር። አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 13፡5 ላይ«***ሕዝቦችን ጣዖት እንዲያመልኩ ያዘዘ፤ ሕልም አላሚና ሐሰተኛ ነብይ ይገደል***» ይላል። ስለዚህ ኢየሱስ ሐሰተኛ ነብይና ኃጢአተኛ ነው። እኛ ሙስሊሞች ግን ኢሳን (ኢየሱስን) ኃጢአት የሌለበትና በኃጢአቱ ምክንያት ያልተሰቀለ፤ ያልተወገረና ያልሞተ እንዲሁም ሐሰተኛ ነብይ አይደለም በማለት እናምናለን። ለምሳሌ፡- ኢየሱስ ተሰቅሎ እንዳልሞተ በሱረተል አል-ኒሳእ 4፡157-150 «**እኛ የአላህ መላዕክተኛ የመርየምን (የማርያም) ልጅ አል መሲህ ዒሳን (ኢየሱስን) ገደልን በማለታቸው ረገምናቸው፤ አልገደሉትም። ግን ለእነርሱ የተገደለውን ሰው በኢሳ (በኢየሱስ) ተመሰለ። እነዚያም ከእርሱ (መገደል) በመጠራጠረ ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በርሱ ነገርም ምንም እውቀት የላቸውም፤ በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ አላህ ወደርሱ አነሳው፤ አላህም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።ከመጽሐፉም ሰዎች ከመሞቱ በፊት በርሱ በዒሳ**

**(በኢየሱስ) በእርግጥ የሚያምን እንጂ አንድም የለም። በትንሳኤ ቀን በእርሱ ላይ መስካሪ ይሆናል**።» ስለዚህ ዒሳ (ኢየሱስ) እንደሚያርግ (ወደ አምላኩ እንደሚወስድ) ነው የሚያሳው እንጂ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሲል ተሰቅሎ እንደሚሞት አይደልም።

## ዒሳ (ኢየሱስ) በአላህ ፈቃድ ተአምራትን እንዳአደረገ እናምናለን።

እኛ ሙሰሊሞች አላህ በቅዱስ ቃሉ እንደ ነገረን ኢየሱስ ብዙ ተአምራቶችን በአላህ ፈቃድ ማድረጉን እናምናለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በማቴዎስ ወንጌል 13፡58 «*ኢየሱስ በዚያም ብዙ ተአምር ማድረግ አልቻለም*» ይለናል። ኢየሱስ በኢስላም ግን አላህ (ሱ.ወ) ለየት ያለ ተአምር እንደ አደረገ ይነግረኛል። ለምሳሌ፡- ለምጽን እንደ አዳነ፤ ሙታንን እንደ አስነሳ፤ እነዚህን ሁሉ ተአምራት በአላህ ፈቃድ እንዳደረገ ቁርኣን ይነግረናል። በሱረቱል አል-ኢምራን 3፡49«**ወደ እስራኤል ልጆችም መላክተኛ ያረገዋል፤ ዒሳ (ኢየሱስ) ይላልም፡- እኔ በጌታዬ ዘንድ በተአምር መጠኋችሁ። እኔ ለእናንተ ከጭቃ እንደ ወፍ ቅርጽ እፈጥራለሁ፤ በእርሱም እተንፍስበታለሁ።በአላህ ፈቃድም ወፍ ይሆናል፤ በአላህ ፈቃድ እውር ሆኖ የተወለደውን ለምጽንም አድናለሁ፤ሙታንንም በአላህ ፈቃድ አስነሳለሁ**» በማለት ቁርኣን ለዒሳ (ለኢየሱስ) ይመሰክራል። አላህ (ሱ.ወ) ለዒሳ (ለኢየሱስ) እነዚህን ተአምራት እንዲያደርግ አላህ ለእሱ ተአምር ሰጥቶታል።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የዒሳ (የኢየሱስ) ተልዕኮ

የዒሳ (የኢየሱስ) ተልዕኮው ሕዝቦች አንድ አምላክን እንዲያመልኩ ማድረግና ማስተማር ነው እንጂ እሱን እንዲያመልኩት አልተጣራም አላስተማረምም። ሰይጣን ዒሳን (ኢየሱስን) ለእኔ ብትሰግድልኝ ባለው ጊዜ፡- ዒሳ (ኢየሱስ) ለማን መስገድ እንዳለበት በማቴዎስ ወንጌል 4፡10‹‹*ኢሳ (ኢየሱስ) ሂድ አንተ ሰይጣን ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏል አለው።*›› ከዚህ ላይ አምላክ በብቸኝነት እንዲያመልክ ኢሳ (ኢየሱስ) ለሰይጣኑ ነግሮታል። እንዲሁም አምላክ ቸር እንደሆነ በሉቃስ ወንጌል 18፡19‹‹*ዒሳ (ኢየሱስ) ቸር መምህር ሲባል ስለምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም*›› በማለት ተናገረ። እንዲሁም አምላክ አንድ አምላክ እንደሆነ በማርቆስ ወንጌል 12፡29‹‹*ከትዕዛዘቱ ሁሉ ፊተኛይ፡- እራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው።*›› በተለይ ደግሞ በማቴዎስ ወንጌል 7፡21-23‹‹*በሰማያት ያለው የአምላኬን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም።*›› በተጨማሪ በዮሐንስ ወንጌል 17፡3‹‹*እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንከውን አንተን የላከውንም ኢየሱስ ክርስቶስ ያውቁ ዘንድ ይች የዘላለም ሕይወት ናት*›› በማለት የነብይነቱን ኃላፍትናውንና አድርስ የተባለውን መልክት ግዴታውን ተወጧል።

## ሁሉም ነብያቶች ስለ አንድ አምላክ ሰብከዋል።

ሁሉም ነብያቶች ኢየሱስን ጨምሮ የአላህ ሰላምና እዝነት በሁላቸውም ላይ ይሁንና ስለ አላህ አንድነትና እሱን ብቻ በብቸኝነት እንዲያመልኩ ሕዝቦችን አስተምረዋል። እንዲሁም ማጋራት ጣዖት አምለኮን አስጠንቅቀውና አስከፊነቱንም ጠቅሰዋል። በሱረቱል አል-ኒሳእ 4፡116‹‹**አላህ በእርሱ ማጋራትን አይምርም፤ ከዚያ ወዲያ ያለውን ለሚሻው ሰው ይምራል።በአላህም የሚያጋራ ሰው በእውነት በእርግጥ የራቀ መሳሳት ተሳሳተ**።›› በሱረቱል አል-ማኢዳህ 5፡72-76 ‹‹**እነዚያ እርሱ የመርየም ልጅ አል መሲህ ዒሳ (ኢየሱስ) ነው ያሉ ሰዎች በእርግጥ ክደዋል። መሲህም ኢሳ (ኢየሱስ) አለ፡- የእስራኤል ልጆች ሆይ ጌታየንና ጌታችሁ አላህን ተገዙ። እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ ጀነት በእርሱ**

**ላይ እርም ናት መኖሪያም እሳት ነው። ለበዳዮችም ምንም ረዳቶች የላቸውም። እነዚያ አላህ የሦስት ሦስተኛ ነው (ከሦስቱ አማልክት አንዱ ነው) ያለ በእርግጥ ካዱ። ከአምላክም አንድ አምላክ እንጂ ሌላ የለም።ከሚሉትም ነገር ባይከለከሉ ከእነርሱ እነዚያን የካዱትን አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። ወደ አላህ አይመለሱምና ምህረትን አይጠይቁምን? አላህ መሐሪ አዛኝ ነው። የመርየም ልጅ አል-መሲህ ዒሳ (ኢየሱስ) ከበፊቱ መላዕክተኞች በእርግጥ ያለፈ የሆነ መላአክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት። ሁለቱም ምግብ ይበሉ ነበር። አንቀፆችን ለእርሱም እንዴት ለከሐዲዎች እንደምናብራራ ተመልከት፤ ከዚያም ከእውነት እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት። ከአላህ ሌላ ለአንተ መጉዳትና መጥቀምን የማይችል ትገዛላችሁን? በላቸው። አላህ እርሱ ሰሚና አዋቂ ነው። <u>ጌታዬን ጌታችሁን ተገዙ ነው ያልኩ</u>**።» የሚለው በወንጌል ላይ ያለው የተጠቀሰው በድጋሜ በሱረቱል አል-ኢምራን 3፡51 ኢሳ (ኢየሱስ) «**አላህ ጌታዬና ጌታችሁ ነው ስለዚህ ተገዙት ይህ ቀጥተኛው መንገድ ነው።**» ዮሐንስ ወንጌል 17፡3 ላይ ያለውን፤ እንዲሁም በማቴዎስ ወንጌል 4፡10 ያለውን ነው ቁርአን ላይ ንግግሩን የደገመው። ስለዚህ ዒሳ (ኢየሱስ) የአላህ መልእክተኛ ነው እንጂ የዓለማት ጌታና አምላክ አይደለም። <u>የዓለማት ጌታና አምላክ ግን አላህ ብቻ ነው</u>። አላህ (ሱ.ወ) አንድ ብቻ እንደሆነ ነብያቶች ለሕዝቦች በመላክ እርሱ ብቻ እንዲመለክ አዟል። እያንዳንዱም ነብይ ተአምር ይዘው ወደ ሕዝቦቻቸው ልኳቸዋል። ለዚህም ማስረጃ በሱረቱል አል-ጋፊር 40፡78«**<u>ለማንኛውም መላእክተኛ በአላህ ፈቃድ ካልሆነ ተአምርንም ሊያመጣ አይገባውም። የአላህም ትዕዛዝ በመጣ ጊዜ በእውነት ይፈርዳል። እዚያ ዘንድም አጥፊዎች ይከስራሉ</u>**።» በሱረቱል አል-ሐዲድ 57፡25«**<u>መላአክተኞቻችንን በግልጽ ማስረጃዎች በእርግጥ ላክን</u>**።» አሁን እንዳየነው አላህ (ሱ.ወ) እያንዳንዱ <u>ነብይ</u> ሲልክ ከተአምራት ጋር ነው። ማንኛውም ነብይ ከራሱ የሚያደርገው አንድም ተአምር ምንም የለም። ስለዚህ ሁሉም ነብያት ዒሳ (ኢየሱስን) ጨምሮ በነብይነታቸው ሙስሊሞች ያከብሯቸዋል፤ ይወዷቸዋል። ነገር ግን እነዚህን የአምላክ ነብያቶች አያመልኳቸውም። ነብያቶችም ኢየሱስን ጨምሮ ከአላህ ውጭ እንዲመለኩ አይወዱም። ተአምር በማድረግ አንፃር ስናይ ለምሳሌ፡- ነብዩላህ ዳውድ (ዳዊት)፣ ለሙሳ (ለሙሴ)፣ ለሱለይማን (ለሰለሞን) --- ለሌሎችም ነብያቶች ተአምርን ሰጥቷቸዋል። አላህ ለምንድ ነው ይህን ተአምር ለነብያቶች የሰጣቸው ቢባል? መልሱ ሕዝቦች ያን ተአምር አይተው በነብይነታቸው እንዲያምኑባቸውና ይህን

ተአምር የሰታቸውን አምላክ እንዲያመልኩ እንጂ ነብያቶችን እንዲያመልኳቸው አይደለም። ለሙሳ (ለሙሴ) (ዐ.ሰ) በሱረቱል ጧሐ 20፡12-20 «**<u>አላህም ሙሳ ሆይ ዘንጓን ጣላት አለው፤ ጣላትም፤ ወዲውም እርሷ የምትሮጥ እባብ ሆነች። ያዛት አትፍራ፤ ወደ መጀመሪያ ጸባይዋ (ወደ ዘንግነት) እመልሳታለሁ አለ</u>**።» 2ኛ **<u>ተአምር እጅህንም ወደብብትህ አግባ አለው ሌላ ተአምር ስትሆን</u>**።» በሱረቱል አል-ነምል 16«**<u>ሱለይማንም (ሰለሞን) ዳውድን (ዳዊትን) ወረሰ፤ አለም፡- ሰዎች ሆይ! የበራሪን ንግግር የወፍ ቋንቋ (የጉንዳንዋን ቋንቋ) ተስተማርን፤ ነገሩም ሁሉ ተሰቶናል</u>**።» ለምሳሌ ይህን ለአብነት ያክል በቁርአን ካየን በመጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሌሎች ነብያቶችና ተራ ሰዎች እንኳ ተአምር እንዳደረጉ እንመለከታለን። በማቴዎስ ወንጌል 10፡8«ሐዋሪያቶች ሙታንን እንደሚያስነሱ፤ ለምጽ እንደሚያድኑ፤ አጋንንትን እንደሚያስወጡ» የ1980 ዕትም ይነግረናል። ለበለጠ “ኢየሱስን ወደ አምላክነት ደረጃ ያደርሰዋል ብለው ከሚያነሷቸው መሰረተ ቢስ ሀሳቦች” ከሚለው ርዕስ ይመልከቱ።

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት

## ጳውሎስ ማን ነው?

በሁሉም የክርስትና ተከታዮች ጳውሎስ ‹“**ሐዋሪያ**”› ነው የሚል እምነት አላቸው። ያውም “**ቅዱስ**” በማለት ይገልጹታል። ሐዋሪያ ማለት ኢየሱስን በዓይን ያዩና የረዱ ናቸው። ነገር ግን በወቅቱ ጳውሎስ ኢየሱስን ያየና የረዳ አልነበረም። ኢየሱስ ለሐዋሪያቶች ሹመት እንዲሰጣቸው በሉቃስ ወንጌል 9፡1 ላይ ለአሥራ ሁለቱ የሐዋሪያቶች ሹመት ሰጥቷቸዋል። ሹመት ከተሰጡት ሐዋሪያቶች ውስጥ እሱ አልነበረም፤ በጊዜውም ኢየሱስን አያውቀም አላየውምም። ታዲያ ኢየሱስ ሐዋሪያ ነህ ብሎ ሹመት ካልሰጠው ማን ሾመው? በገዛ ስልጣኑ ይሆን? ጳውሎስ ስለራሱ ሹመት የሚለን ነገር አለ። ወደ ቲቶ ሰዎች በላከው መልእክት 1፡1-2 «***የእግዚአብሔር አገልጋይና የኢየሱስ ክርስቶስ <u>ሐዋሪያ ከሆነው፤</u> የእግዚአብሔርም ምርጦች በእምነት ለመርዳትና የሃይማኖቱንም እውነት እንዲያውቁ <u>ከተሾመው ጳውሎስ፤</u> ይህም ሃይማኖት በዘላለም ሕይወት ተስፋ ላይ የተመሰረተ ነው፤ የማዋሸው አምላክ ይህን ሕይወት <u>ለመስጠት ከዘመናት በፊት ቃል ገባልን</u>***።» የት ላይ ነው እግዚአብሔር ለጳውሎስ የሐዋሪያነት ሹመት እንደሚሰጠው ቃል የገባለት? ተጨማሪ በ2ኛ ቆረንቶስ 10፡5«***<u>“እኔ ታላላቅ ሐዋሪያቶች ከሚባሉት የማንስ አይመስለኝም</u>”***።» እንዴት ነው ከታላላቅ ሐዋሪያቶች ጳውሎስ እኩል የሚሆነው? በዚያ ላይ ራሱ “**የማንስ አይመስለኝም**” በማለት ጥርጥር ውስጥ እየገባ ሌሎች ሰዎች እንዴት እርግጠኛ ሆኑ? ለመሆኑ ምን ማስረጃ ኖሮት ነው ከሐዋሪያቶች እራሱን ያወዳደረ? ብዙ ጊዜ ክርስትኖች የሚሰጡት መልስ “በሕልሙ አይቶ ነው” የሚል ነው። ነገር ግን ሕልም የሚያዩ ሁሉ ውሸታም እንደሆኑ ይገልፃል። በትንቢተ.ዘከሪያስ 10፡2«***<u>“ሕልምም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል፤ ከንቱ ይጽናናሉ</u>”***» ይላል። ስለዚህ ያ በህልሙ ያየው ነገር ስህተት ለመሆኑና በከንቱ መፅናናቱን ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ነገረን። ይህ ብቻ አይደለም። በኦሪት.ዘዳግም 9፡5«---***<u>ያ ሕልም አላሚ ይገደል</u>***» ይላል። ከዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ በመነሳት ጳውሎስ ውሸትን ተናግሮዋል። ሐዋሪያም ነኝ እያለ በከንቱ ተፅናንቷል። ሌላው ጥያቄ ላየው ሕልም እውነተኛነት ምን ማስረጃ አለን? ከሐዋሪያነት የበለጠ “ጌታ ነህ” የሚል ሕልም ቢያይስ ሊታመን ነው ማለት ነው? እራሱ ከራሱ ሐሳብ አፍልቆ ኢየሱስን አንዴ ሰው ነው ይለዋል፤ አንዴ

አምላክ ነው ይለዋል። ሲቀጥል ደግሞ ራሱ ጳውሎስ ንግግሩን ያፈርሰዋል። የቱ ተይዞ የቱ እንደሚተው ክርስቲያኖች መልስ ይኖራቸው ይሆን?

## 1) ኢየሱስ ጳውሎስን አላከውም፤ የእርሱም ሐዋሪያ አልነበረምም።

ኢየሱስ የመረጣቸው አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት (ደቀመዝሙሮች) ብቻ መሆኑን በማርቆስ ወንጌል 3፡13-19«***ኢየሱስ ወደ ተራራ በወጣ ጊዜ የፈለጋቸውን ወደ እርሱ ጠራ፤ እነርሱም ወደ እሱ ቀረቡ። ከእርሱ ጋር እንዲሆኑ ለማስተማር፤ እንዲልካቸው አሥራ ሁለቱን መርጦ "ሐዋሪያት" ብሎ ሰየማቸው።-----የተመረጡትም የአሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት እነዚህ ናቸው፡- ጴጥሮስ ብሎ የሰየመው ሰምዖን፣ በአኔርጌስ ወይም የነጎድጓድ ልጆች ብሎ የሰየማቸው የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስ፤ እንደርያስ፣ ፊልጶስ፣ በርቶሎሜዎስ፣ ማቴዎስ፣ ቶማስ፣ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብ፣ ታዴዎስ፣ ተቀናቃኙ ሰምዖንና አስቆሮታዊ ይሁዳ ናቸው።***» ጳውሎስ ሐዋርያ ከነበር ለምን ከእነርሱ ጋር ስሙ አብሮ አልተጠቀሰም? በጊዜውስ አብሮ ነበርን? ሲቀጥል ኢየሱስ ሐዋርያቶችን የላካቸው መሆኑን በሉቃስ ወንጌል 22፡29«***<u>አባቴ እኔን እንደላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ</u>***» ብሏል። ስለዚህ ጳውሎስን ኢየሱስ እንዳላከው ግልፅና ግልፅ ነው። ነገር ግን ጳውሎስ ሐዋርያ ነኝ አብሬ ተልኪያለሁ ብሎ ሲናገር፡- በ1ኛ ቆረንቶስ 1፡17 «***<u>ክርስቶስ የላከኝ ወንጌል እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም</u>።***» ኢየሱስ ጳውሎስን እንዲያጠምቅም ሆነ ወንጌል እነዲሰብክ በፍፁም አላከውም። ኢየሱስ ጳውሎስ የት ያውቀዋልና ነው የሚልከው? ጳውሎስ ኢየሱስ እንዳጠምቅ አላከኝም ብሏል። ታዲያ ለምን አንዲት ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት እያለ አስተማረ? ወደ ዕብራውያን መልእክት 10፡22«***<u>ስለዚህ ከክፉ ኅሊና እንነፃ ለባችንን ተረጭተን፤ ሰውነታችንንም በንጹሕ ውኃ ታጥበን፤ ቅን ልብና እውነተኛ እምነት ይዘን ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ</u>።***» ፍርዱን ለእናንተ! የሱን አቋም የሚያውቀው አለን? እንኳን ለእናንተ ለራሱም ግራ የተጋባው ነው። የሚገርመው እራሱ ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 10፡15«***<u>ካልተላኩ እንዴት ይሰብካሉ</u>?***» ይላል። እኛም የምንለው ይህን ነው ካልተላከ ለምን ይሰብካል? መልሱን ሐዋሪያ ነው ለምትሉ ሰዎች ትቻለው።

## 2) ጳውሎስ በኢየሱስ ነብይነት ያመኑትን አሳዳጅና ጠላት ነበር።

ጳውሎስ ይቅርና ቅዱስነትና ሐዋሪያነት ስም ሊሰጠው ተራ አማኝ እንኳ አልነበረም። ይልቁንም ያመኑትን ሰዎች ያሳድድ የነበረ ሰው ነው። ማሳደዱንና ክፉ ስራውን በራሱ መልእክት ይናገራል። ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው መልእክት ላይ 1፡13 «*"በአይሁድ ሥርዓት እንዴት እንደ ነበርኩ ሰምታችኃል፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን አሳድድና አጠፋ ነበር"*።» ታድያ ጳውሎስ ቅዱስ ሰው ነው? ቅዱስነት ያመኑትን ሰዎች ማሳደድና ቤተ ክርስቲያንን ማጥፋት ነው እንዴ? በሐዋሪያት ሥራ 26፡9-11«*እኔ (ጳውሎስ) ራሴ የናዝሬቱን ኢየሱስን ስም የተቃለኝን ያህል መቃወም አለብኝ ብየ አስብ ነበር። በኢየሩሳሌም ያደረኩትም ይህንኑ ነበር፤ ከካህናት አለቆች በተቀበልኩት ስልጣን ከአማኞች ብዙዎችን ወደ ወህኒ ቤት እንዲገቡ አድርጌአለሁ፤ ሲገድሏቸውም ከገዳዮች ጋር ተስማምቻለሁ። ብዙ ጊዜ በየምኩራቡ እንዲቀጡና ከእምነታቸውን እንዲክዱ አድርጌአለሁ፤ በእነርሱ ላይም በጣም ተቆጥቼም ወደ ሌሎች ከተሞች እንኳ ወጥቸ እየሄድኩ አሳድዳቸው ነበር*።» በ1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9«*"እኔ ከሐዋሪያት ሁሉ የማንስ ነኝና የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን ስለአሳደድሁ ሐዋሪያ ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ"*።» ድሮስ ማን ሐዋሪያ ነህ አለው? ራሱን አይደል በኩራት "ከታላላቅ ሐዋሪያት የማንስ አይደለሁም" በማለት ራሱን የሾመ። አሁን ደግሞ "ሐዋሪያ ተብሎ ልጠራ የማይገባኝ ነኝ" ይላል። የትኛው ንግግር እውነት የትኛው ንግግር ሐሰት ነው? ለነገሩ ከላይ ከታላላቅ ሐዋሪቶች የማንስ አይመስለኝም ስላለ እርግጠኛ ስላልሆነ ይመስለኛል። አሁን ሐዋሪያ ተብዬ ልጠራ አይገባኝም ያለው። ይህ ብቻ አይደለም መጽሐፍ ቅዱስም እርስ በራሱ ይቃረናል ጳውሎስ ከዛ ያየውን ይሆናል ንግግሩ የሚያቃርነው።

## 3) ጳውሎስ ጋብቻን ይቃረናል፤ ፈጣሪ ያላዘዘውን ቃል በመሻር የራሱን ሐሳብ ይናገራል።

ፈጣሪ ያለውን ሳይሆን የራሱን ሐሳብ ከስሜቱ አፍልቆ ይናገራል። ባሳለፍነው ርዕስ ላይ "**የማንስ አይመስለኝም**" እያለ እየተጠራጠረ እንደ ተናገረ ሁሉ አሁንም የራሱን ሐሳብ ሲያንፀባርቅ እናገኘዋለን። በ1ኛ ቆረንቶስ 7፡7-26«*"ሰው ሁሉ እንደኔ ሚስት ሳያገባ ቢኖር በወደደሁ። ላላገቡና ባሎቻቸው ለሞቱባቸው ሴቶች*

***የምላው እንዲህ ነው፤ .....ሳያገቡ እንደኔ ቢኖሩ መልካም ነው፤ ላገቡት ግን የምሰጠው ትእዛዝ ይህ ነው። ይህም ትእዛዝ ከጌታ ነው እንጂ የኔ አይደለም"። ያገባች ሴት ከባሏ አትለያይ ብትለይም ሳታገባ ለብቻዋ ትኑር። ...... ለሌሎች ግን ጌታ ሳይሆን እኔ እራሴ የምለው እንዲህ ነው። ....... ላላገቡት ሰዎች ግን ከጌታ የተቀበልኩት ትእዛዝ የለኝም። ነገር ግን በእግዚአብሔር ምህረት እምነት የሚጣልብኝ እንደመሆኔ መጠን የራሴ ሐሳብ ከዚህ ቀጥሎ ያለው ነው፦ አሁን ያለንበት ጊዜ የችግር ጊዜ ስለሆነ ሳያገቡ በብቸኝነት መኖር መልካም ይመስለኛል።"»*** ኧረ መልካም አይደለም። አምላክ በዘፍጥረት ላይ «**ብዙ ተባዙ ወምልዋ ለምድር**» ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት ነው ያለው። አምላክ በዘፍጥረት 2፡18«***ሰው ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚበጀውን ረዳት እንፍጠርለት***» በማለት አምላክ ጋብቻን ያዛል። ጳውሎስ ደግሞ ጋብቻን ተቃውሞ ምንኩስናን አዟል። ታዲያ በአምላክ ምህረት እምነት የሚጣልበት ሰው የራሱን ሐሳብ ነው የሚናገረው? የተፈጥሮን ስርዓት ለምን ይቃወማል? ይቅርና ለሰው ልጆች በሙሉ ለአዳም እንኳ አምላክ ሔዋንን ከግራ ጎኑ ፈጥሮለታል። ሲቀጥል "**እንደኔ**" በማለት የራሱን ሐሳብ ሲያስቀድምና ከአምላክ የተሻለ ለመሆን ይጥራል። "«**ጌታ ሳይሆን እኔ እራሴ የምለው እንዲህ ነው**»" የሚሉት አባባሎች ከስሜቱ የመጣለትን ነው እንጂ የአምላክ ትዕዛዝ እየፈፀመና እየተቀበለ አይደለም። "**አምላክ የከፈተውን ጉሮሮ ሳይዘጋው አያድርም**" ይባላል በአባባል እንኳ። የዱር አራዊቶች ወፎች ማን ይመግባቸዋል አርሰውና አዝምረው ወይንስ ሸምተው ነው? ኢየሱስ እምነት ቢኖራችሁ ይህች ወፍ በባዶ ሆዷ ወጥታ ሆዷን ሞልታ እንድምትመለስ የሰማዩ አባታችሁ ይመግባቸዋል ነበር ያለው። አምላክ ለፈጠረው ፍጥረት በሙሉ መጋቢ ነው። ለዚያ ነው በትንቢተ.ኤርሚያስ 29፡5-6 «***ቤት ሰርታችሁ ተቀመጡ አትክልት ተክላችሁ ፍሬውን ብሉ። አግቡታችሁ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ውለዱ። ወንዶች ልጆቻችሁንና ሴቶች ልጆቻችሁን አጋቡ። እነርሱም ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ይውለዱ ቁጥራችሁ ይብዛ እንጂ አይነስ።»*** ተጨማሪ በመጽሐፈ መዝሙር 81፡10«***ከግብፅ ምድር ያወጣውህ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ እኔ ነኝ፤ አፍህን በሰፊው ክፍት እኔ እመግብሃለሁ።»*** ኢየሱስ የተናገረውን አሁንም እናስከትል በሉቃስ ወንጌል 12፡24«***ቁራዎችን ተመልከቱ አይዘሩ አያጭዱ እቃ ቤትም ጎተራም የላቸውም፤ እግዚአብሔር ይመገባቸዋል።»*** እውነታው ይህ ሆኖ ሳለ ራስን ከፈጣሪ ሕግ ውጭ መደረግ

አያዋጣም፡፡ "‹‹**አሁን ያለንበት የችግር ዘመን ነው**›› " በማለት ጋብቻን ለመቃረን የሚያደርገው ዳርዳርታ ጉድ ያስብላል፡፡

## 4) ጳውሎስ የሙሴን ሕግ ተቃርኗል (ሽሯል)፡፡

ትእዛዝን መፈፀም መንግስተ ሰማያት እንደሚያስገባ አጠራጣሪ ጉዳይ አይደለም፡፡ ለአብነት ብንጠቅስ በማቴዎስ ወንጌል ኢየሱስ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባት ምን ማድረግ አለብን ተብሎ ሲጠየቅ በማቴዎስ 19፡17‹‹***"ወደ ሕይወት መግባት ብትፈልግ ትእዛዛቱን ፈጽም አለው"***፡፡›› ይህ ቃል አዲስ ነው፡፡ ጳውሎስ ደግም ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው መልእክት 2፡16‹‹***ሰው የሚጸድቀው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ነው እንጂ የሙሴን ሕግ በመፈፀም አይደለም"***›› በማለት ያስተምራል፡፡ ከዚሁ ምዕራፍ 3፡10‹‹***"ሕግን በመፈፀም እንድናለን የሚሉ ሁሉ የተረገሙ ናቸው"***፡፡›› አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 5፡4‹‹***"እናንተ በሕግ አማካኝነት ለመፅደቅ የምትፈልጉ ሁሉ ከክርስቶስ ተለይታችኋል"***፡፡›› ሕግን መፈፀምና መከተል ወደ መንግስተ ሰማያት እንደማያስገባ ኢየሱስ አስገንዝቧል፤ ጳውሎስ ደግሞ የተረገሙ ናቸው ይላል፡፡ የትኛውን እንመን ጳውሎስ የተናገረውን ወይስ ኢየሱስ የተናገረውን? በ1980 ዕትም በማቴዎስ ወንጌል 5፡17-20 ያለውን ስንመልከት፡- ‹‹***"እኔ የሙሴን ሕግና የነቢያትን ትምህርት ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ እኔ ፍፁም እንዲሆኑ ላደረጋቸው መጣሁ እንጂ ለመሻር አልመጣሁም"፡፡ እውነት እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ ሁሉ ይፈፀማል እንጂ ከሕግ አንዲት ጭረት ወይንም አንዲት ነጥብ አትሻርም፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ትዕዛዞች አነስተኛ የሆነችውን አንዷን አንኳ የሚያፈርስና ሌሎችንም ሰዎች እንዲያደርጉ የሚያስተምር ሰው በመንግስተ ሰማያት አነስተኛ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ትእዛዞችን ሁሉ የሚፈፅምና ሌሎችም ሰዎች እንዲሁ እንዲፈፅሙ የሚያስተምር ሰው በመንግስተ ሰማያት ታላቅ ይሆናል፡፡ የእናንተ ፅድቅ ከሙሴ ሕግ መምህራንና ከፈረሳውያን ፅድቅ ካልበለጠ ወደ መንግስተ ሰማያት ከቶ አትገቡም እላችኋለሁ"***፡፡›› ከዚህ ላይ እውነቱ ተደብቆ ሰው የሚድነው ዝም ብሎ በእምነት ነው የሚሉ በርካቶች ናቸው በተለይ የፕሮቴስታንት እምነት ተከታይነን ባዮች፡፡ ከዚህ ላይ ግን ይህ አባባል ቦታ አያገኝም፡፡ አሁን የጳውሎስ ትምህርት ውጤቱና ወደ የትኛው መንገድ እንደሚያስተምር ጉዳዩ በመረጃ ግልፅ ሆኗል፡፡ የሙሴን ሕግ በመፈፀም

እንድናለን የሚሉ የተረገሙ መሆናቸውን ሲገልፅ ኢየሱስ ደግሞ የሙሴን ሕግ የሚፈፅሙ ፃድቃን መሆናቸውን መስክሯል። በመቀጠል ሕግ እንዲፈፅም የሚያስተምር በመንግስተ ሰማያት ታላቅ መሆኑን እንዲሁም ሕግን እንዳይፈፅሙ የሚያስተምሩ ታናሽ መሆናቸውን ጨምሮ ገልጿል። ጳውሎስም ሕግን ስለተቃረነ በመንግስተ ሰማያት ታናሽ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። እሱ የሙሴን ሕግ ብቻ አይደለም የአምላክን ቃል ሽሯል። ወደፊትም ኢየሱስ የተናገረውን ሽሮ እናገኘዋለን። አሁንም የሻረውን የተቃረነውን አይተናል። ሕግ ከክብደቱ የተነሳ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ሕግ አይሻርም። አንዲት ነጥብና አንዲት ጭረት ብትሆን ነበር ያለው። አሁንም በመጽሐፈ ባሮክ 4፡1 ***«የዘላለም ሕግ የሆነው የእግዚአብሔር ትእዛዙ መጽሐፍ ይህ ነው፤ የሚጠብቁትም ሁሉ ይኖራሉ፤ የሚተውት ግን ይሞታሉ።»*** አሁንም በድጋሜ በመጽሐፈ ኩፋሌ 23፡39 ***«ስለዚህም <u>ሕግ የዘመን ፍፃሜ የለውም</u>።»*** በትንቢተ.ኢሳይያስ 40፡8 ***«ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ <u>የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች</u>።»*** ያ ማለት አይሻርም ማለት ነው። ጳውሎስ ግን ይቅርና አንዲት ነጥብ ሙሉ ለሙሉ ነው የሻረው ይህ ድርጊቱ ይቅርና ሐዋሪያት ተራ ሰው ያስበዋል? ጳውሎስ ሕግ ለማን እንደሚያስፈልግ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡8-10 ***«ሰው በሚገባ ከሰራበት ሕግ መልካም መሆኑን እናውቃለን፤ እንዲሁም ሕግ የተሰራው ለደጋግ ሰዎች እንዳልሆነ እናውቃለን፤ ሕግ የተሰራው ለአመፀኞችና ለወንጀለኞች፤ ለካሐዲዎችና ለኃጢአተኞች፤ ቅድስና ለለላቸና መንፈሳዊ ነገርን ለሚንቁ፤ ሰውን ለሚሸጡ ነጋዴዎችና ለውሸተኞች፤ በሐሰት ለሚምሉና የእውነተኛ ትምህርት ተቃራኒ የሆነውን ነገር ለሚያደርጉ ነው።»*** ታዲያ በአሁን ሰዓት የተዘረዘሩትን ወንጀሎች የሚሰራ የለም? የለም ብንል እውነታውን ማስተባበል አይሆንምን?

## 5) <u>የጳውሎስ ቃል እርስ በርሱ ይቃረናል።</u>

ጳውሎስ በእምነቱ አቅም የለሽ ከመሆኑ የተነሳ በየዘመናቱ ከሚታተሙት መጻሓፍት ንግግሩ ተቃርኖ እናገኘዋለን። ለምሳሌ በ1980 እና ከ 1993 ዕትም ላይ ጳውሎስ ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው ደብዳቤ ላይ ንግግሩን እንመልከት። ገላቲያን 3፡12 እና 3፡10 ላይ ንግግሩ ከላይ ካሳለፍነው ጋር በ1993 ዕትም ***«<u>በሕግ በመጽሐፍት የተፃፈውን የማያደርግ የተረገመ ነው</u>።»*** ይህ አባባሉ ኢየሱስን

የገደፈ ይመስላል። ነገር ግን አሁንም ይህን ንግግር ከዚህ ምዕራፍ ላይ ከተቀመጠው ጋር ቃረናል። የ1980 ዕትም ወደ ገላቲያን ሰዎች 3፡10 ‹‹*“ሕግን በመፈጸም እንጸድቃለን” የሚሉ ሁሉ የተረገሙ ናቸው፤*›› ይህ ቃል በአንድ ምዕራፍና ቁጥር መቃረኑ ለሁሉም ግልፅ አይደለምን? ከዚህ አንፃር ጳውሎስ እምነቱ ምንድን ነው? ሁሌም ንግግሩ ስለሚቃረን አቋሙን መለየት እጅግ በጣም ይከብዳል።

## 6) ጳውሎስ ኢየሱስ ያልሻረውን ብሉይ ኪዳንን ሙሉ በሙሉ ሽሯል፡፡

ጳውሎስ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ሽሮና ሲቃወም መጽሐፍ ቅዱስን ንግግር ውድቅ ሲደርግ ለሱ ሁሌም አዲስ አይደለም። ከላይ ባሳለፍነው ርዕሳችን ላይ መቃረኑን ግልፅ ነው። ነገር ግን ይህ መቃረን አንድ አንዴ ሳይሆን ሙሉ አዲስ ኪዳንን መሻሩን ነው የሚያስረዳው። ይህ የተቃውሞ ንግግሩም በሮሜ መልእክቱ 7፡4-6 በግልፅ ሰፍሮ ይገኛል። እንዲህ በማለት፡- ‹‹***ወንድሞቼ ሆይ! .... እናንተ ክርስቶስ አካል ስላልሆናችሁ በሞት የመለየት ያህል ከሙሴ ሕግ ተለይተናል።..... ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ የምናገለግለው በአዲሱ መንፈሳዊ መመሪያ እንጂ አስቀድሞ በተፃፈው በአሮጌው ..... የሕግ መመሪያ አይደለም።***›› ወደ ዕብራዊያን ሰዎች በላከው 7፡18-19‹‹***ሕጉ ምንም ፍፁም አላደረገምና ስለዚህ የምታደከም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች።***›› ብሉይ ኪዳንን የሻረው ድንገት አዲስ ኪዳን ስለሚል ከስሙ ተነስቶ የአሁኑ ኢደስ የዱሮው አሮጌ መስሎት ይሆን? የሚያገናዝብ አዕምሮ የለውም። ወደነፈሰበት መንፈስ የተለመደ ባሕሪው ነው። ስለ ሕግ ክብደት በኦሪት.ዘዳግም 4፡2 እንዲህ ይላል፡- ‹‹***እኔ ያዘዝኳችሁን የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትጠብቃላችሁ እንጂ ባዘዝኳችሁ ቃል ላይ አትጨምሩም፤ አታጓድሉም።***›› በመጽሐፈ ባሮክ 4፡1‹‹***የዘላለም ሕግ የሆነው የእግዚአብሔር ትእዛዙ መጽሐፍ ይህ ነው፤ የመጠብቁትም ሁሉ ይኖራሉ። የሚተውት ደግሞ ይሞታሉ።***›› በመጽሐፈ ኩፋሌ 23፡39 ‹‹***ስለዚህም ሕግ የዘላለም ፍፃሜ የለውም።***›› ስለዚህ ሕግ የሚሻር አለመሆኑ ግልፅና ግልፅ ነው። ኢየሱስ በማቴዎስ 5፡17-20 ያለውን አሁንም በድጋሜ እንመልከት፡- ‹‹***እኔ የሙሴን ሕግና የነብያትን ትምህርት ለመሻር አይምሰላችሁ ልፈፅመው እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።***›› ጳውሎስ ነብያት በሔዱበት እርሱ አልሔደም የእነሱን ፈለግ አልተከተለም። ከዚህ የበለጠ

ለኢየሱስ እንኳን ያልተሰጠውን ስም “ቅዱስ” ተብሏል። ጳውሎስ በኢየሱስ ነብይነት ላመኑት ጠላጥ ነው። ጳውሎስ ኢየሱስን ተቃውሞ ሰዎችን ከእምነት መንገድ ስላስወጣ ነው። በራሱ መልእክት “እኔ አማኞችን አሳድድና የእግዚአብሔርን ቤት አቃጥል ነበር” ብሏል።

## 7) <u>ጳውሎስ የአምላክን ሕግ ለሰው ዘር በሙሉ ያዘዘውን የመገረዝን ቃል ኪዳን ሽሯል።</u>

በኦሪት.ዘፍጥረት 17፡9-14 ያለውን ስንመለከት ስንመለከት፡- ‹‹*“እግዚአብሔር አብራሃምን እንዲህ አለው በእናንተም በኩል፤ አንተንና ከአንተ በኋላ የሚመጡ ዘርህ ከትውልድ እስከ ትውልድ ኪዳኔን ትጠብቃላችሁ። አንተንና ከአንተም በኋላ የሚወጣው ዘርህ የምትጠብቁት ኪዳኔ ይህ ነው፤ በመካከላችሁ ያለ ወንድ ይገረዝ። ስለዚህ ሸለፈታችሁን ትገረዛላችሁ፤ ይህም በእኔና በእናንተ መካከል ላለው ኪዳን ምልክት ይሆናል። የሚመጣውም ትውልድ ሁሉ፤ማንኛውም ወንድ ልጅ፤ ስምንት ቀን ሲሞላው ይገረዛል። እንዲሁም በቤትህ የተወለደውና ከውጭ በገንዘብ የተገዛ ባዕድ ሁሉ መገረዝ አለበት፤ በሥጋችሁ የሚፈፀም ይህ ኪዳኔ የዘላለም ኪዳን ይሆናል። የሥጋ ሸለፈቱን ያልተገረዘ ማንኛውም ወንድ ኪዳኔን በማፍረሱ ከወገኖቹ ይወገዳል”*።›› አብራሃም ከእግዚአብሔር ጋር ከተነጋገረ በኋላ መገረዙን በኦሪት.ዘፍጥረት 17፡25 ‹‹*“በዚያችም እለት አብራሃም እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ልጁን እስማኤልን፣ በቤቱ ውስጥ የተወለዱትንና ከውጭ በገንዘብ የገዛቸውን <u>ወንዶች በሙሉ ገረዟቸው</u>”*።›› እግዚአብሔር ለዘላለም የሰጠው ቃል ኪዳን የማይሻር ለመሆኑ ሙስሊሞች በተግባር የሚያሳዩት ነው። ዳግሞም መገረዝ ለወንድ ልጅ ያለውን ጠቀሜታ ሳይንስ እንኳን ሳይቀር እውነታውን አረጋግጧል። ኢየሱስ እራሱ ለዚህ ህግ ተገዥና የአምላኩን ቃል ኪዳኑን አክባሪ እንደ ነበር በሉቃስ ወንጌል 2፡21‹‹***<u>ኢየሱስ ሲገርዙት ስምንት</u> ቀን በሞላው ጊዜ ......***›› ይላል። እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት ኢየሱስ ሲወለድ ሊገርዙት ሰዎች እንዳሰቡ በሉቃስ ወንጌል የምስክርነት ቃል አግኝተናል። ጳውሎስ ግን ይህን ድርጊት ተቃርኗል። ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከውም መልእክት 5፡2 ‹‹*“እነሆ እኔ ጳውሎስ የምላችሁ ይህ ነው፡- <u>“መገረዝ ያስፈልገናል”</u> ብላችሁ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም”*።›› በማለት ኢየሱስንና አምላክ የዘላለም ቃል ኪዳን አድርጎ የዘዘውን እንደተቃወመ በራሱ ደብዳቤ አስፍሮት ይገኛል። በማስከተልም ወደ ፍልጵስዮስ ሰዎች በላከው መልእክት 3፡2‹‹***<u>እንደ</u>***

***ውሻ ከሚልከፈከፉ ከክፉ ሰዎች አስተማሪዎች ተጠንቀቁ፤ እነርሱ ሰለ መገረዝ የሚያስተምሩ ናቸው።»*** ከዚህ ላይ ደግሞ ለሌሎች ሰዎች ማስፈራራት የተቀለቀለበት ማስጠንቀቂያ ሰንዝሯል። አብራሃም፣ እስማኤልና ኢየሱስ አምላክ ባዘዛቸው መሰረት ተገርዘዋል። ታዲያ እነዚህ የተከበሩ የአምላክ ነብያቶች የሚለከፈከፉ ውሻ ናቸውን? የተከበሩና ለአምላካቸው ታዛዥ የሆኑትን ነብያት ክብራቸውን ማራቆት ጤነኛ ንግግር አይደለም። የሚገርመው ጳውሎስ ለሌች ተመቅኘ እንጂ እራሱ እንደ ተገረዘ አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 3፡5 ላይ ***«እኔ በስምንተኛው ቀን ተገርዣለሁ»*** ይለናል። እሱ ከተገረዘ ሌሎችን መከልከል ለምን አስፈለገ? ጳውሎስ አይተገበረውም እንጂ አንድ ሰው ለራሱ የወደደውን ለሌሎች መውደድ እንዳለበት አስተምሮ ነበር። እንዲህ በማለት በ1ኛ የዮሐንስ መልእክት 3፡14-15 ***«እኛ ወንድሞቻችን ስለምንወድ ከሞት ወደ ሕይወት መሻገራችን እናውቃለን፤ ወንድሙን የሚጠላ ነብሰ ገዳይ ነው»*** ብሎ አስተምሮ ነበር። ወንድሞችን ቢወድ አያሳድድም ነበር። ነገሩ በአፍ ብቻ ሆነ እንጂ። ሌላው ጳውሎስ አምላክ ያዘዘውን እንደማይሰራ እንዲህ ይነግረናል፡- በ2ኛ ቆረንቶስ 11፡17 «እንግዲህ ታምኜ ስመካ "የምናገረው፡- በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም"፡፡» ተጨማሪ በ1ኛ ቆረንቶስ 7፡12«***ሌሎችንም "እኔ እላለሁ፡- ጌታም አይለም፡፡"»*** ይህ ነው የጳውሎስ አቋም፡፡

## 8) የኢየሱስና የሙሴ ተከታይ የነበሩት ጳውሎስን ተቃውሙት፤ የሙሴንና አምላክ ያዘዘውን የመገረዝ ቃል ኪዳኑን በመቃረኑና በመሻሩ።

በጊዜው አብረውት የነበሩት ሰዎች የሚያደርገው ድርጊት ከኢየሱስ እምነት ያፈነገጠ በመሆኑ የተለዩ ሐሳቦች ተሰንዝሮበታል። እጅግ በጣም ብዙ ተቃውሞ እንደደረሰበትም እራሱ ይናገራል። በሐዋሪያት ሥራ 21፡20-21«***"ጳውሎስን እንዲህ አሉት፡- ወንድም ሆይ! ብዙ ሺህ የሚቆጠሩ አማኞች በአይሁዳዊያን መካከል እንዳሉና ሁሉም ለሙሴ ሕግ ቀናተኞች (ታዛዦች) እንደሆኑ ታውቃለህ? አንተ በአረማውያን መካከል ያሉትን አይሁዳዊያን ሁሉ "ልጆቻችሁን አትግረዙ ወይንም ስርዓተችን አትፈፅሙ እያልክ በማስተማር የሙሴን ሕግ እንዲሽሩ ታደርጋለህ አሉት።"»*** ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 5፡17-20 ላይ የሙሴን ሕግና የነብያትን ትምህርት ሊሽር እንዳልመጣና ሊፈፅመው እንደመጣ ተናግሯል። ጳውሎስ ግን የአምላክን ቃል ኪዳንና ኢየሱስ ያስተማረውን ተቃርኖ የራሱን ሐሳብ ብቻ ያራምዳል። በጊዜው ለሙሴ ሕግ ታዛዥ የነበሩት እንዲሁም በኢየሱስ ነብይነት

ያመኑት ሰዎች ጳውሎስን ተቃርነውታል። ያሁኖቹ ክርስትያኖች ግን አልተቃወሙትም። ጳውሎስ ኢየሱስንና አምላክ ያዘዘውን መቃወሙ አግባብ ሆኖ አግንተውት ይሆን? ከአምላክ ንግግር የበለጠ የሚታመን አለን? በዚያ ላይ የእምነት ሰው አይደለም። እንደ እሱ ያለ እምነት ለመኖር አስባችሁ ይሆን? ያ ማለት ኢየሱስ ያስተማረውንና የአምላክን ቃል እናንተም ሽራችኋል ማለት ነው ልክ እንደ ጳውሎስ።

## 9) ጳውሎስ የኢየሱስን የመጀመሪያ ትእዛዝ ተቃርኗል።

ጳውሎስ የመጀመሪያቱ ትእዛዝ በማለት ያስተማረው ኢየሱስን በመቃረን ነው። ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክት 6፡2‹‹***ፊተኛይቱ ትእዛዝ እናት አባትህን አክብር የሚል ነው***›› ይለናል። ለኢየሱስ ደገሞ የመጀመሪያቱ ትዕዛዝ ምንድን ናት ተብሎ ሲጠየቅ በማቴዎስ ወንጌል 22፡38-40 መልስ ሰጥቷል እንዲህ በማለት፡- ‹‹***ጌታ አምላክህን በፍፁም ልብህ በፍፁም ነፍስ በፍፁም ሐሳብህ ውደድ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ይች ናት።***›› ሲጀመር አምላኩን ያልፈራ ሰው እንዴት ነው እናት አባቱን ያከብራል ተብሎ የሚታሰበው? አምላክን ትቶ እናት አባትን ማክበር ግንዱን ትቶ ቅርንጫፉን እንደ መያዝ ማለት ነው። ደግሞም እርግጥ ነው አምላኩን ያልፈራ ሰው እናት አባቱን ያከብራል ማለት ዘበት ነው።

## 10) ጳውሎስ በእምነቱ አቋም የለሽ እንጂ አማኝ የአምላክም ባርያ አልነበረም።

ጳውሎስ "**ሐዋሪያ**" ነው ተብሎ የሚታመንበት ሰው ስለራሱ ማንነት ሲመሰክር በ1ኛ ቆረንቶስ 9፡19-22 ላይ መልሱን ይሰጠናል። ‹‹"***እኔ እኮ የማንም ባሪያ ሳልሆን ነፃ ሰው ነኝ፤ ይሁን እንጂ በተቻለኝ መጠን ብዙዎችን በማዳን ለመጥቀም ብዬ የሁሉም ባሪያ ሆኛለሁ። ከአይሁዳውያን ጋር ስሆን አይሁዳውያን ሆንሁ። ምንም እንኳን ከሙሴ ሕግ በታች ባልሆንም ከሙሴ ሕግ ያሉትን ለማዳን ስል ከሙሴ ሕግ በታች እንዳሉት ሆንሁ። ምንም እንኳ እኔ የእግዚያብሔር ሕግ ያለኝንና ከክርስቶስ ሕግ ስር ብሆንም፤ ሕግ የሌላቸውን አረማውያን ለማዳን ስል እንደ አቅመ ደካሞች ሆንሁ፤ በተቻለኝ መጠን አንዳንዶችን ለማዳን ከሁሉምጋር ሁሉን ነገር ሆንሁ።***"›› "‹‹**ከሁሉም ጋር ሆንሁ**››" ሲል ምን ለማለት እንደፈለገ ግልፅ ነው። ከላይ ያየነውን ንግግር በ2ኛ ኤፌሦስ 3፡14 ላይ ይቃረናል። ‹‹***እኔ***

***ጳውሎስ ለእግዚአብሔር እምበረከካለሁ*»** ካለ ታዲያ ለእግዚአብሔር ከተንበረከከ እኔ የማንም ባርያ ሳልሆን ነፃ ሰው ነኝ ለምን አለ? ንግግሩን ራሱ ተናግሮ እራሱ ንግግሩን ያፈርሰዋል።

## 11) ጳውሎስ ለራሱ ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል ይላል።

ጳውሎስ በ1993 ዕትም በ1ኛ ቆረንቶስ 6፥12«***ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል፤ ይሁን እንጂ ሁሉ ነገር አይጠቅምም፤ ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል ይሁን እንጂ ምንም ነገር በእኔ ላይ አይሰለጥንም።***» ከንግግሩ በመነሳት ሁሉንም ነገር ለራሱ ከተፈቀደለት የፈለገውን ኃጢአት ቢሰራ ነፍስ መግደል፤ ዝሙት ስርቆት ማጭበርበር በአጠቃላይ የፈለገውን ኃጢአት ማግበስበስ ይችላል ማለት ነው? ለጳውሎስ ማን ነው? ሁሉን ነገር የፈቀደለት? ሌላ መጽሐፍ ቅዱስ ወርዶለት ነው? አምላክ ፈቅዶለት ነው እንዳይባል አምላክን በመቃረን ጳውሎስን የሚያክል ሰው የለም። ጳውሎስ የሚፈልገውን ነገር ሳይሆን የማይፈልገውን ነገር እንሚያደርግ የታወቀ ነው። በመቀጠልም የማይፈልገውን ነገር የማደርገው በውስጤ ያለው ኃጢአት ነው በማለት ጳውሎስ የራሱን አቋም አንፀባርቋል።

## 12) ጳውሎስ በአንድ አፍ ሁለት ምላስ ስለአረማውያን ኃጢአተኛነትና ጽድቀት

ጳውሎስ የሁሉም ባሪያ ነኝ አረማውያን ለማዳን አረማውያን ሆንሁ እያለ ያስተምር እንደ ነበር ባለፈው ርዕስ ላይ አይተናል። አሁን ደግሞ ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው መልእክት 2፥15«***"በእርግጥ እኛ በትውልዳችን አይሁዳውያን ነን እንጂ እንደ ኃጢአተኞች አረማውያን አይደለንም።"***» ወደ ሮሜ መልእክት 3፥30 «***እግዚአብሔር አንድ ነው፤ አይሁዳዊያንም ሆነ አረማውያን በእምነት የሚያጸድቀው እረሱ ነው፡፡***» ከዚህ ሌላ ደግሞ ጳውሎስ ዘረኛ መሆኑን እንረዳለን። አረማውያን ለማዳን እንደ አረማውያን ከሆነ አሁን ለምን አረማውያንን ኃጢአተኛ ናቸው ብሎ ኮነናቸው? አረማውያን መስሎ ሳለ እንደ እርሱም ኃጢአተኛ ነበር ማለት ነው? ተጨማሪ ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች በላከው መልእክት ደግሞ 3፥5«***በትውልዴም ከብያንም ዘር የሆንሁ እስራኤላዊ ነኝ፤ ከዚያም በቀር ጥርት ያልሁ ዕብራዊ ነኝ። የአይሁዳውያንን ሕግ ለመጠበቅ ፈረንሳዊ ነበርሁ።***» ይህ ሰው ያልሆነው የለም። በዚያ ላይ የፈለገውን እየሆነ

“ጥርት ያልሁ ዕብራዊ ነኝ” ማለቱ እውነተኛ አያስብለውም። ጳውሎስን በጊዜው ያዩትና አብረው የነበሩት ሰዎች እብድ ብለውታል። በሐዋሪያት ሥራ 26፡24 ‹‹***ጳውሎስ እንዲህ ብሎ ለራሱ ሲመልስ ፊስጦስ በታላቅ ድምፅ፦ ወንደም አብደሃል እኮ አለው።***›› መጀመሪያ ከዚያ ከዚህ ሲል የነበረው በእብደቱ ምክንያት ነው። አንዴ አይሁዳውያን አንዴ ከሙሴ ሕግ በታች አንዴ አረማውያን የሆነው። የእብድ ሰው ቃል ተይዞ ያስተማረውን መቀበል እንደ እሱ እብድ መሆን ነው።

## 13) ጳውሎስ ከአምላክ ጋር እኩል ስራ እሰራሉሁ በማለት እራሱን ከአምላክ ጋር ያወዳድራል።

“‹**ሰው ከቆየ ከሚስቱ ይወልዳል አሉ**›” አሁን ደግሞ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር አምላክ ጋር እኩል ስራ እሰራለሁ በማለት ከሐዋሪያነት አልፎ እራሱን ወደ አምላክነት ደረጃ አሸጋግሯል። የ1980 ዕትም በ1ኛ ቆረንቶስ 3፡9‹‹***እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሰራ ነን***›› በማለት እራሱን ሁሉን ነገር ከፈጠረ አምላክ ጋር እራሱን ማወዳደሩ እሱ ምን ሰርቶና ፈጥሮ ይሆን? ይቅርና አምላክ የሰረውን ሰው የሰረውን ያልሰራ መሆኑ የምናውቀው ጉዳይ ነው። በዚያ ላይ ኃጢአተኛ ሰው እንደ እግዚአብሔር ስራ እሰራለሁ ተብሎ መናገሩ ከማስገረም አልፎ በጣም ያሳዝናል። “‹‹**የምፈልገውን ትቼ የማልፈልገውን አደርጋለሁ። ያም በውስጤ ያለው ኃጢአት ነው።**››” ታዲያ እንዲህ አይነቱ ሰው ነው ከእግዚአብሔር ጋር አብሮ የሚሰራው?

## 14) ጳውሎስ ከኃጢአተኞች የባሰ ኃጢአተኛ እንደ ነበር።

ጳውሎስ የፈለገውን ነገር እንደማያደርግ አምላክ ባዘዘው ነገር ላይ እንደማይቆም እንዲሁም መልካም ስራ እንደማይሰራ በራሱ እራሱን ይገልፃል። ወደ ሮሜ ሰዎች በላከው መልእክት 7፡15-20‹‹“....... ***እኔ የማደርገውን አላውቅም፤ ምክንቱም የምወደውን ትቼ የምጠላውን አደርጋለሁ። እንግዲህ ማድረግ የማልፈልገውን ነገር የሚያደርገው በኔ ውስጥ ያለው ኃጢአት ነው እንጂ እኔ አይደለሁም። ማድረግ የምፈልገውን መልካም ነገር አላደርግም። ዳሩ ግን የማልፈልገውን ክፉ ነገር አደርጋለሁ።***”›› ከዚህ የበለጠው ቀጥሎ ያለው ነው። በ1ኛ ጢሞቲዎስ 1፡15 ‹‹***እኔ ከኃጢአተኞች የባሰኩ ኃጢአተኛ እኔ ነኝ።***›› በመጀመርያ ቆም ብላችሁ እራሳችሁ ፍርዱን ፍረዱ። እኛ በትውልዳችን

አይሁዳውያን ነን እንጂ እንደ ኃጢአተኞች አረማውያን አይደለንም ነበር ያለው። ታዲያ ከዚህ ጋር ንግግሩ ይስማማል? አሁን ደግሞ ኃጢአተኛ እንደሆነ ራሱ ነገረን፤ የማይፈልገውን ነገር እንደሚሰራ ይህንን እንደዲያደርግ የገፋፋው በውስጡ ያለው ኃጢአት እንደሆነም ራሱ ተናግሯል። አቅሉን የሳተ ሰው ነው የሚያደርገውን የማያውቅ። ጳውሎስ ታድያ አቅሉን ከሳተ ሰው በምን ይለያል? ጳውሎስን መቀበል ምን የሚሉት እብደት ነው? ኃጢአተኛን ሰው መልካም የማያደርገን ያውም የኢየሱስንና የአማኞችን ጠላትና የእግዚአብሔርን ቤት አጥፊ የነበረ ሰውን የሚለውን መቀበል በተዘዋዋሪ የሱን ኃጢአተኛነት መቀበል ነው። ወደ ፊልጵስዮስ ሰዎች በላከው መልእክት 3፡6«*ስለ ሃይማኖት መቅናትም ቢሆን በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምኑትን የማሳድድ ነበርሁ።*» የጳውሎስ አቋም ይህ ነበር፤ የእምነት ሰዎችን የሚያሳድድ ሰው ሐዋርያ" መባሉ ለሁሉም ሰው ይገርመዋል። ክርስቲያኖች ከጳውሎስና ከኢየሱስ ንግግር እውነተኛነቱ የትኛው ሚዛን እንደሚደፋ ራሳችሁ ገምቱ ከንግግራቸው የተነሳ። እንዲሁም ያላችሁበትን ፊትሹ፤ እውነተኛውን ኢየሱስን ፈልጉ እንደኛ ሙስሊሞች ውደዱት።

## 15) ለጳውሎስና ለመሰሎቹ የተሰጠ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስጠንቀቂያ!!

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 13፡10 «*ሰላም ሳይኖር ሰላም አለ እያሉ ሕዝቤን ያታልላሉ።*» ከዚሁ ምዕራፍ 13፡17 «*ሰላም ሳይኖር የሰላም ራእይ የሚያዩላት የእስራኤል ነብያቶች ጠፍተዋል።*» አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 13፡23 «***...እኔ ያላዘዝሁትን ጽድቅ በውሸት ስላሳዘናችሁ ኃጢአተኛውም ከኃጢአቱ ተመልሶ ከክፉ መንገዱም ተመልሶ ሕይወቱን እንዳያድን በኃጢአቱ ስላበረታታችሁት፤***» ለዚህ አድራጎታችሁ አምላክ ተገቢ የሆነ ቅጣት ይቀጣችኋል። በትቢተ.ኤርሚያስ 23፡16 «*ከእግዚአብሔር አፍ የወጣ ሳይሆን ከገዛ ልባቸው የሆነውን ራእይ ይናገራሉ።*» ከዚሁ ምዕራፍ 29፡9«*በስሜ ሐሰተኛ ትንቢት ይነግሯችኋል እንጂ እኔ አላኳቸውም።*» በት-ዘካሪያስ 10፡2«*ሕልምም የሚያዩ በሐሰት ተናግረዋል፤ በከንቱ ይጽናናሉ።*» በትንቢተ.ኢሳይያስ 30፡1 «*"ለአመፀኞች ልጆች ወዮላቸው" ይላል እግዚአብሔር፤ የእኔ ያልሆነውን ሐሳብ ይከተላሉ ከመንፈሴ ያልሆነውን ቃል ኪዳን ያደርጋሉ፤ በኃጢአት ላይ ኃጢአት ይጨምራሉ።*» የእነዚህን ውጤት ደግሞ በኦሪት.ዘዳግም 9፡5«*ሕልም አላሚና ሐሰተኛ ነብይ ይገደል*» ስለሚል አምላክ ትልቅ ቅጣት የሚጠብቀው መሆኑን አምላክ ነግሮናል።

## ምዕራፍ አሥራ አራት

## በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ክርስቲያኖች የማይተገብሯቸው ሙስሊሞች እየተገሯቸው ያሉ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች

አንዳንድ ክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ሁሉም ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቲያን ሁኑ ብሎ አስተምሯል ይሉናል። ይህን አባባል ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወንጌልን ጠቅሰው በማስረጃ አይናገሩም። ይልቁንስ ኢየሱስ ሙስሊም ነበር። ኢስላማዊ ተግባራትንም ይስራ ነበር። በአጠቃላይ ህይወቱ በሙሉ በእስልምና ስርዓቶች ላይ መሰረት ያደረገ ነበር። ለምሳሌ፡- አንድ ሙስሊም ለአላህ ይሰግዳል፤ ኢየሱስም ይሰግድ ነበር። በማቴዎስ ወንጌል 26፡39‹‹***ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ <u>በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ</u>፡- አባቴ ሆይ! ቢቻልህስ ይህቺ ጽዋ ከኔ ትለፍ›አለ።***››

## <u>ያለፉት ነብያት በአንድ አምላክ (በአላህ) ያምኑና ለእርሱም ይሰግዱና የአሰጋገድ ሥርዓታቸው ተመሳሳይ ነበር፡፡</u>

ነብያት ለአምላካቸው ይሰግዱ እንደ ነብርና የአሰጋገድ ሥርዓታቸውም አንድ አይነት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳል። ኢየሱስም ልክ እንደ ሌሎች ነብያት ይሰግደ ነበር። ለአብነት ያክል፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 17፡33‹‹***<u>አብራሃምም በግንባሩ ወደቀ</u>።***›› በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ 18፡42‹‹***ኤልያስም ወደ ቀርሜሎስ አናት ወጣ፤ <u>ፊቱንም በጉልበቱ መካከል አድርጎ ተደፍቶ ሰገደ</u>***›› ይላል። በመጽሐፍ ኢያሱ 5፡14‹‹***ኢያሱም ወደ ምድር <u>በግንባሩ በምደር ላይ ሰገደ</u>።***›› በመጽሐፍ ኩፋሌ 1፡17‹‹***<u>ሙሴ በግንባሩ ተደፍቶ ጸለየ (ሰገደ)</u>።***›› በተጨማሪ በኦሪት.ዘፍጥረት 20፡6‹‹***ሙሴና አሮን ከጉባኤው ፊት ወደ መገኛው ድንኳን ደጃፍ ሄደው <u>በግንባራቸው ወደቁ</u>፤ እግዚአብሔር ክብር ተገለጠላቸው።***›› በመጽሐፈ ነህምያ 8፡6‹‹***ዕዝራም "ታላቅ አምላክ የሆነ እግዚአብሔር ይመስገን!" አለ፡፡ ሕዝቡም ሁሉ እጃቻቸውን ወደ ላይ በማንሳት "አሜን! አሜን!" ሲሉ መለሱ፤ ወደ ምድርም ለጥ ብለው <u>ፊታቸውን መሬት በማስነካት ለእግዚአብሔር ሰገዱ</u>፡፡››*** ከሕዝቡ ከፍ ብሎ በተሠራኢየሱስ በዚህ የአሰጋገድ ሥርዓት ተመሳሳይ ድርጊት እንዳከናወነ ይነግረናል። በማቴዎስ ወንጌል 26፡39‹‹***ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ <u>በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ</u>፡- አባቴ ሆይ! ቢቻልህስ ይህቺ ጽዋ ከኔ ትለፍ›አለ።***››

ከላይ ካየናቸው የኢየሱስ የተለየ ነገር የለም። ያ ማለት ሁሉም ነብያት ለአምላክ ይሰግዱ ነበር። ኢየሱስም ለአምላኩ ይሰግድ ነበር።

## በሕብረት መስገድ (የጀማዓ ሶላት)

በሕብረት (በጀማ) መስገድ የጋራ ጥምረትና የአንድነት ምልክትን አንጸባርቆ የሚያሳይ ነው። በህብረት (በጀማዓ) መስገድ የጋራ ጸሎት ይባላል። በመጽሐፈ መዝሙር 95፡6‹‹***ኑ፤ እንስገድ፤ ለእርሱም እንገዛ፤ እርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ***።›› ስለዚህ በሕብረት (በጀማ) መስገድ እንግዳ ነገር አይደለም። የሚገርመው ሙስሊሞች የነብያትን ፈለግ በመከተል በሕብረት (በጀማዓ) በሚሰግዱበትና በጋራ ጸሎት በሚያደርጉበት ሰዓት ለሌላ ዓላማ የሚሰበሰቡ አድርገው ይቆጥሩታል። በጋራ በሕብረት (በጀማዓ) መስገድ በነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተመሰረተ ሃይማኖታዊ ሥርዓት አይደለም። ከእሳቸው በፊት የነበሩት ነብዩ ዳዊት ተግብሮታል። ኑ እንስገድ በማለት። ኑ እስገድ ማለት የአረበኛ ትርጉሙ (ሐያ ዐለ ሦስት) ማት ነው። ያ ማለት ደግሞ ኑ በጋራ በሕብረት (በጀማ) እንስገድ ማለት እንጂ ሌላ ትርጉም የለውም። በኢየሱስም ጊዜ በሕብረት (በጀማ) ይሰገድ ነበር። በሐዋርያት ሥራ 1፡14‹‹***እነዚህ ሁሉ ዘውትር ለጸሎት በአንድነት ይሰበሰቡ ነበር፤ ከእነርሱም ጋር አንዳንድ ሴቶችና ኢየሱስ፣ ማርያም፣ እንዲሁም የኢየሱስ ወንድሞች ነበሩ***።›› ከዚህ ላይ ኢየሱስ ራሱ በሕብረት (በጀማ) ለመስገድ ይሰበሰብ እንደ ነበር እንቀጽ ያስረዳል።

## የስግደት አቅጣጫ (ቂብላ)

የስግደት አቅጣጫ (ቂብላ) የአምላክ ትእዛዝ እንጂ ጣዖት ማምለክ አይደለም። አምላክ ዙሩ ወደ አበለት አቅጣጫ መዞር ታዛዥነትን ያመለክታል። ነብያትም ለአምላካቸው ታዛዥ ነበሩ።ወደ ታዘዙበት አቅጣጫም (ቂብላ) ዙረው ይሰግዱ ነበር። በትንቢተ.ዳንኤል 6፡10‹‹***ዳንኤል ጽፈቱ (የአቅጣጫው ትእዛዙ) (ቂብላው) እንደ ተጻፈ ባወቀ ጊዜ ወደ ቤቱ ገባ፤ የእልፍኙም መስኮቶች ወደ እየሩሳሌም አንፃር ተከፍተው ነበር፤ ቀድሞም ያደርግ እንደ ነበረ በየዕለቱ ሦስት ጊዜ በጉልበቱ ተንበርክኮ በአምላኩ ፊት ጸለየ፤ አመሰገነም***።›› ከዚህ ላይ ዳንኤል ሦስት ዕለታዊ ስግደቶችን መፈጸሙን እንዲሁም ወደ እስራኤል ሕዝብ የተላከ መሆኑን እንረዳለን። ሲሰግድ የነበረው ወደ ኢየሩሳሌም እንደ ነበር አንቀጹ

ያስታውሰናል። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ 8፡329 *«በስሜ ይሆናል ወደ አልኸው ሥፍራ ወደዚህ ቤት ዓይኖችህ ሌሊትና ቀን የተገለጡ ይሁኑ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡30*«"ባርያህና ሕዝብሕ እስራኤል ወደዚህ ስፍራ የሚጸልዩትን ልመና ስማ፤ በማደሪያህ በሰማይ ስማ፤ ሰምተህም ይቅር በል"።»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡35 *«አንተን ስለ በደሉ ሰማይ የተዘረጋ ጊዜ፤ ዝናብም ባልዘነበ ጊዜ፤ ወደዚህ ሥፍራ፤ ስምህንም ቢያከብሩ፤ ባስቸነቅሃቸውም ጊዜ ከኃጢያታቸው ቢመለሱ አንተ በሰማይ ስማ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡38-39*«"ማናቸውም ሰው የልቡን ሕመም አውቆ ጸሎትና ልመና ቢጸልይ፤ እጆቹንም ወደዚህ ሥፍራ ቢዘረጋ፤..."»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡42-43*«"አሕዛብም ከእስራኤል ወገን ያልሆነ እንግዳ፤ ታላቆቁን ስምሕን፤ ብርቱይቱንም እጅህን፤ የተዘረጋውንም ክንድህን ሰምቶ ስለስምህ ከሩቅ አገር በመጣ ጊዜ፤ መጥቶም ወደዚህ ቤት በጸለየ ጊዜ፤ አንተ በማደሪያህ በሰማይ ስማ፤ የምድርም አሕዛብ እንደ እስራኤል ይፈሩ ዘንድ፤ በዚህም በሰራሁት ቤት ስምህ እንደ ተጠራ ያውቁ ዘንድ፤...."»* ከዚሁ ምዕራፍ 8፡44*«"ሕዝብሕም ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት አንተ በምትልካቸው መንገድ ቢወጡ፤ አንተ ወደ መረጥሃት ከተማ፤ እኔም ስለ ስምህ ወደ ሰራሁት ቤት ለእግዚአብሔር ቢጸልዩ፤ ጸሎታቸውንና ልመናቸውን በሰማይ ስማ፤ ፍርድህንም አድርግላቸው።"»* መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃው እንደሚያሳየው ይሄ የአምልኮ አቅጣጫ በነብዩ ዳንኤል ብቻ ሳይሆን በሰለሞንና በአባቱ በዳዊት ጊዜም እንደ ነበር ቀጣዩ ምዕራፍ ይተርክልናል። በመጽሐፈ ነገሥት 8፡42-44 ላይ ባለው አንቀጽ ሰለሞንና ሕዝቦቹ እርሱ በእየሩሳሌም ለአምላክ ወደ ሰራው ቤት ዞረው ይሰግዱና የስግደት አቅጣጫቸው እንደ ነበር ነው የሚያሳየው። በአዲስ ኪዳንም ይህ የአምልኮ አቅጣጫ (ቂብላ) እንዳለም ኢየሱስ በተከታዩ ጥቅስ ይነግረናል። በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 4፡19-23*«ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፡- "ጌታ ሆይ! አንተ ነብይ እንደሆንህ አሁን ዐወቅሁ፤ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ ግን ሰዎች መስገድ የሚገባቸው በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ።" ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "አንቺ ሴት! ለእግዚአብሔር አብ በዚህ ተራራ ላይ ወይም በኢየሩሳሌም ስለ መስገድ የማትጨነቁበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ፤ እናንተ ለማታውቁት አምላክ ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን-------ለምናውቀው አምላክ እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለእግዚአብሔር አብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ እንዲያውም አሁን መጥቶአል፤ እግዚአብሔር አብም የሚፈልገው እንደዚህ የሚሰግዱለትን ነው።»*

## ከመስገዳቸው በፊት የሚያደርጉት ትጥበት (ውዱዕ)

አካላዊ ትጥበት ማድረግ ለጤና ወሳኝ ሚና አለው። ንጽህና ባለመጠበቅ የተነሳ የሚመጡ በርካታ በሽታዎች አሉ። ነገር ግን አንዳንድ ክርስቲያን ወገኖች ተቃራኒ አመለካከት አላቸው። እንዲህም ሲሉ ይደመጣሉ፡- በቀን አምስት ጊዜ ለምን ትጣጠባላችሁ? ያለ ትጥበት ያለ (ውዱዕ) ብትሰግዱ አምላክ አይሰማችሁምን? በማለት ይቃወማሉ። አንዴ የገጠመኝን ልንገራሁ ጎንደር ዙሪያ አዲስ ዘመን ከተማ ከተወለድኩበት አካባቢ ነው። አጋጣሚ ሆኖ እኔ ከክርስትና እምነት ወደ እስልምና መግባቴን አላወቀም ነበር። ከዚያ ሰዎች ሲነግሩት በርቀት እየተመለከተኝ አትኩሮቱ ከኔ ጋር ነበር። እኔም ታክስ ለመያዝ ወደ አውቶብስ ተራ ገባሁ። እሱ ያለበት ታክስ ትንሽ ሰው ቀርቶ እስኪሞላ ይጠባበቅ ነበር። በመስኮት ብቅ አለና ሽሜው ቂጥ ማጠብ አስደስቶህ ነው ሽማኔ የሆንከው? እያለ በተደጋጋሚ ሲናገር በታክሲው ውስጥ ያሉ ሰዎች በሳቅ አደመቁት። እኔም ከመሃይም ሰው ጋር መነጋገር ልክ ከዝንብ ማር እንደ መጠበቅ ማለት ነው ብየ ለንግግሩ ምላሽ አልሰጠሁትም። ከዚያም ታክሲው ሞልቶ ሲወጣ ከዚያ ንግግሩ አልተቆጠበም። በድጋሞ ሲናገረኝ እኔም ሁኔታዎቹ ምላሽ እንድሰጥ አስገደዱኝ። ጢጋ አልኩና ሰማህ ወንድም ንጽህና የሚያስጠላው ዝንብ ነው አልኩት። እንደገና ሰዎች በእሱ ላይ በሳቅ አጠፌተውን መለሱለት። ዋናው ቁም ነገሩ ንጽህና የሚሰጠውን ጥቅም የግድ የህክምና ባለሞያዎች ብቻ መናገር የለባቸውም። ጠቀሜታው የጎላ ስለሆነ ማንም ያውቀዋል። ወደ አምላክ ሲቀረብ ደግሞ አካላዊ ጽዳትና የልብ ጽዳት የግድ ነው። በኦሪት.ዘጸአት 40፡30-32‹‹***እግዚአብሔርም ሙሴን እንዳዘዘው የመታጠቢያውን ሰን በመገናኛው ድንኳንና በመሰዊያው መካከል አኖረ፤ በመጣጠቢያው ውን ጨመረበት። በእርሱም <u>ሙሴና አሮን ልጆችም እጆቻቸውን፤ እግሮቻቸውን ታጠቡ፤ ወደ መገናኛው ድንኳን በገቡ ጊዜ ወደ መሰዊያውም በቀረቡ ጊዜ ይታጠቡ ነበር</u>***።›› ሙሴን ያዘዘው አምላክ ነው እኛን እንድንታጠብ ያዘዘን።

## የጀናባ (በግብረ ሥጋ ግንኙነት የረከሰ ሰው) ትጥበት

በኢስላም አንድ ሰው የግብረ ሥጋ ግኑኝነት ሲያደርግ ገላውን መታጠብ ግዴታ ይሆንበታል። ካልታጠበ ጀናባ (ርኩስ) ነው። ለጀናባ (ለርኩስ) ትጥበት ከእስልምና ሃይማኖት ውጭ በሌሎች ዘንድ የለውም። ይህን ስል መቼም ማጋነን

አይሆንም። መጽሐፍ ቅዱስም ተሰሚነት ባይኖረውም እንድንታጠብ ያዛል። በኦሪት.ዘዳግም 23፡10-11«*በእናንተ መካከል ሌሊት በሚሆነው ርክሰት የረከሰ (የግብረ ሥጋ ግንኙነት) ሰው ቢኖር፡- ከሰፈር ወደ ውጭ ይውጣ፤ ወደ ሰፈር አይመለስ። በመሸም ጊዜ በውኃ ይታጠብ።*» ተጨማሪ በኦሪት.ዘሌዋውያን 15፡18 «*ወንዱ በሴቲቱ ቢደርስባት (ቢገናኛት) በውኃ ይታጠቡ፤ እስከ ማታም ድረስ ችኩሶች ናቸው።*» እኛ ሙስሊሞች የግብረ ሥጋ ግኑኝነት አድርገን ይቅርና በህልማችን እንኳ ከሴት ጋር የተገናኘን መስሎን የዘር ፈሳሽ ቢፈስን እንታጠባለን።

## ንጽህናን (ጡሐራን) መጠበቅ መጠበቅ እንዳለብን

አንድ ሰው ወደ ስግደት በሚቀርብበት ጊዜ በውሃ እንደሚታጠብ ሁሉ ንፅህናውን (ጡሐራውን) ይጠብቃል። ያ ማለት ከአካሉ ጀምሮ እስከሚለብሳቸው ልብሶች እንዲሁም የሚሰግድበትም ቦታ ንጹህ (ጡሐራ) መሆን አለበት። አለበለዚያ ግን ስግደቱ ትክክል አይሆንም። በኦሪት.ዘጸአት 3፡5 «*እርሱም (ሙሴ)፡- እነሆኝ አለ። (እግዚአብሔርም) ወደዚህ ሥፍራ አትቅረብ፤ አንተ የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ።*» ተጨማሪ በሐዋሪያት ሥራ 7፡23«*ጌታም የቆምህባት ሥፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው።*» ከላይ በሁለቱም ጥቅሶች ማለትም በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የመስገጃ ቦታው ንጹህ (ጡሐራ) ስለሆነ በቆሻሻ ጫማ እንዳያቆሽሹ አምላክ ትዕዛዝ ማስተላለፉን እንረዳለን። እኛ ሙስሊሞች ይህን የምንተገብረው ቀደምት ነብያትን ባዘዘበት መንገድ ስለታዘዝን ነው።

## ጾም

ጾም ማለት ሰውነትን ከሙብል ከመጠጥና ከክፉ ስራ ከሐሜት ከመጥፎ ንግግርና ከኃጢአት ሁሉ መከልከል ማለት ነው፡፡ በመጽሐፈ ነህምያ 1፡4«*ይህንም ቃል በሰማሁ ጊዜ ተቀምጬ አለቀስሁ፤ ኣያለ ቀንም አዝን ነበር፤ በሰማይም አምላክ ፊት እጾምና እጸልይ ነበር፡፡*» በመጽሐፈ ዕዝራ 8፡21«*እግዚአብሔር ጉዞአችንን እንዲያቀናልን፤ እኛንና ልጆቻችንን፤ እንዲሁም ንብረታችንን ሁሉ እንዲጠብቅልን በእርሱ ፊት ራሳችንን ዝቅ አድርገን እንለምነው ዘንድ በዚያው በአህዋ ወንዝ አጠገብ ጾም ዐውጅሁ፡፡*» በመጽገፈ አስቴር 4፡16«*ሂደህ በሱሳ ያሉትን አይሁድ ሁሉ ሰብስብ፤ ለኔም ጹሙ፤*» በትንቢተ.ዮናስ 3፡5«*የነነዌ ሕዝብ*

***የእግዚአብሔርን ቃል አመኑ፤ ጾምም ዐወጁ፤»*** ኢየሱስም በማቴዎስ ወንጌል 4፡2 ***«እዚያ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ከጾመ በኋላ ራበው፡፡»*** እዚህ ላይ ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ነብያት መጾሙን እንረዳለን፡፡

## አሥራት ግብር (ዘካ) ማውጣት መስጠት ግዴታ እንደሆነ

አሥራት ግብር (ዘካ) በሁሉም የሰው ልጆች ላይ ግዴታ ነው። ግዴታነቱም በሐብታሞች ላይ ነው። ሆኖም ግን ከሙስሊሞች ውጭ የሌላ እምነት ተከታይ ምንም ቦታ አይሰጠውም ብል ማጋነን አይሆንም። ሙስሊሞች በአጠቃላይ በሚችሉት ያክል የአምላክን ትዕዛዝ ለመፈፀም ወደ ኋላ አይሉም። አሥራት ግብር (ዘካ) ማውጣት ትልቅ ኃላፊነት መሆኑንና ሰዎችም የተጣለባቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው መጽሐፍ ቅዱስ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ተቀምጧል። ለአብነት እነሆ፡- በኦሪት.ዘፍጥረት 28፡20-22 ***«ያዕቆብ እንዲህ አለ፡- እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ቢሆን፤ በምሄድባትም በዚያች መንገድ ቢጠብቀኝ፤ የምበላውን እንጀራ የምለብሰውን ልብስ ቢሰጠኝ፤ ወደ አባቴ ቤትም በጤና ቢመልሰኝ፤ እግዚአብሔር አምላኬ ይሆናል። ለሀውልት የቆምኂት ይህች ድንጋይ የእግዚአብሔር ቤት ትሆናለች፤ ከሰጠኸኝም ሁሉ ለአንተ ከአሥር እጅ አንዱን እሰጥሃለሁ»*** በማለት አምላክ ግዴታ ያደረበትን አሥራት ግብር (ዘካ) ማውጣቱን ይነግረናል። አብርሃምም የተጣለበትን አሥራት ግብር (ዘካ) እንደ አወጣ ከዚሁ ምዕራፍ 14፡20 ***«አብርሃም ከሁሉ አሥራት ሰጠሁ፡፡»*** ሙሴም በኦሪት.ዘዳግም 14፡22 ***«ከእርሻህ በእየ ዓመቱ ከምታገኘው ከዚህ ፍሬ ሁሉ አሥራት ታወጣለህ፡፡»*** ተጨማሪ በኦሪት.ዘሌዋውያን 27፡30***«የምድርም አሥራት የምድር ዘርም የምድርም ፍሬ ቢሆን ለእግዚአብሔር የተቀደሰ ነው፡፡»*** ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 12፡17 እና 14፡23 ላይ በሁሉም ነገር አሥራት ግብር (ዘካ) እንደሚወጣበት አፅኖትና ትኩረት ሰጥቶበት እናገኘዋለን። በመቀጠልም የሰው ልጅ የተጣለበትን አሥራት አለማውጣት አምላክን እንደስረቅ ይቆጠራል። በትንቢ.ተ.ሚልኪያስ 3፡ 8-10 ***«ሰው እግዚአብሔርን ይሰርቃልን?እናንተ ግን እኔን ሠርቃችኋል፤ የሰረቃችሁት አሥራት በኩራት ነው፡፡»*** ኢየሱስም ለዚህ ተግባር ተካፋይና ገዳፊ እንደ ነበረም በሉቃስ ወንጌልና በዮሐንስ ወንጌል ይናገራል። በሉቃስ ወንጌል 18፡12 ***«ከማገኘው ሁሉ አሥራት እሰጣለሁ፡፡»*** ኢየሱስ እንደ ማንኛውም ነብያት ስለሆነ አሥራት (ዘካ) ማውጣቱን እራሱ መናገሩን እንገነዘባለን።

## ምጽዋት (ሰዶቃ) መስጠት እንዳለብን

አሥራት ቀርቶ በማንኛውም ጊዜ ግዴታ የሆነው ምጽዋት መስጠት እንዳለበት በአንክሮ ይናገራል። በመጽሐፈ ጦቢት 1፡8«***ምጽዋት*** ***ከሞት ታድናለች፤ ከኃጢአትም ሁሉ ታነፃለች፤ ወርቅና ብር ከማድለብ ይልቅ ምጽዋት መሰጠት ይሻላል።***» በመጽሐፈ ሲራክ 3፡28«***ውኃ የሚነዳውን እሳት እንደሚያጠፋ ሁሉ*** ***ምጽዋት*** ***ደግሞ የኃጢአትን ብዛት ታጠፋለች።***» ኢየሱስም በዚህ ጉዳይ ላይ በርካታ ንግግሮችን ተናግሯል። በማቴዎስ ወንጌል 6፡4«***አንተ ግን ምጽዋት ስታደርግ በሰውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሰራውን ግራህ አትወቅ በሰውር የሚያይህ በግልጽ ይሰጥሃልና።***» በዚሁ ምዕራፍ 6፡19-20«***ገንዘባችሁን ብልና ዝገት ከሚያጠፋው ሌባም ሰብሮ በሚሰርቀው በምድር ላይ አትሰብስቡ። ነገር ግን ብል ሊበላው፤ ዝገት ሊያበላሸው ሌባም ቆፍሮ ሊሰርቀው በማይችልበት በዚያ በሰማይ ለራሳችሁ ሐብት አከማቹ።***» ኢየሱስ በሉቃስ ወንጌል 6፡38«***ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መስፈሪያም ተመልሶ ይሰፈርላችኋል።***» ከዚሁ ምዕራፍ 12፡28«***ያላችሁንም በመሸጥ ምጽዋትንም ስጡ።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 12፡33-34«***ያላችሁን ሸጡና ለድኾች ስጡ ሌባ በማይሰርቅበት ብል በማይበላበት በማያረጅም ከረጡት የማያልቅ ንብረት በሰማይ አከማቹ።***» በሐዋሪያት ሥራ 20፡35«***ከሚቀበል ይልቅ*** ***የሚሰጥ ብፅዱ*** ***ነው።***» በ2ኛ ቆረንቶስ 9፡6«***በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ያጭዳል፤ በበረከትም የሚዘራ በበረከትም ደግሞ ያጭዳል።***» ወደ ሮሜ ሰዎች 12፡8«***የሚሰጥ በልገሰና ይሰጥ።***» እስካሁን ያየናቸውን በሙሉ በክርስቲያኖች ዘንደ የተሻሩ ሕጎች አስመስለው ያዩአቸዋል። ነገር ግን በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዲስ ኪዳን እንዳልተሸሩ ግልፅ ነው። ክርስቲያኖች ግን “በኢየሱስ ስቅለት እመን” መልካም ስራ አያስፈልግም በሚለው መሰረተ ቢስና ከንቱ ምኞት ተቀየረ እንጂ።

## ልብስን በአግባቡ መልበስ እንዳለብን

ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ እራቁትን መሄድ ፈጣሪን የሚያስደስት አድርገው ይቆጥሩታል። ይህ ብቻ አይደለም፤ እንደስልጣኔና እንደዘመናዊነት ያዩታል። ይህ አድራጎት ግን ስልጣኔነት ሳይሆን ሰይጣንነት ነው። የሚገርመው ፈጣሪን ያስቀይማል ብለው አያስቡም። እስኪ በዚህ ጉዳይ ላይ የሚከተለው የመጽሐፍ

ቅዱስ ጥቅስ የሚነግረን ነገር አለ። በኦሪት.ዘሌዋውያን 19፡19‹‹***ከሁለት ዓይነት ነገር የተሰራ ልብስ አትልበስ***።›› በዚህ መሰረት ሁለት ዓይነት ልብስ መልበስን አምላክ ከልክሏል። ያ ማለት የወንድንና የሴት ልብስ አንድ ሰው መልበስ እንደ ሌለበት ያስረዳል። ምክንያቱም የሴት ልብስ ለሴት ነው መልበስ የተፈቀደው እንደዚሁ የወንድም ልብስ ለወንድ ልጅ ነው የተፈቀደው። ከዚህ ውጭ ከተከለከልነው ነገር ነበር የማከለከል ከሆነ አምላካችን እናስቀይማለን፤ አምላክም እንዲህ ብሏል። ከዚሁ ምዕራፍ 22፡5 " ***ሴት የወንድ ልብስ አትልበስ፤ ወንድም የሴት ልብስ አይልበስ፤ እንዲህ የሚያደርገውን አምላክ እግዚአብሔር አምላክ እግዚአብሔር ይጸየፈዋል***።"››

## ሴት ልጅ ገላዋን ሸፍና መልበስ እንዳለባት

አምላክ የሴትን ልጅ ገላ የተለየና አስውቦ ነው የፈጠራት። ስለዚህ ውብ ገላዋ እንዲሸፍን ያዘዘበት ምክንያት ዝርዝሩ ብዙ ነው። ቀላል ምሳሌ እንውሰድ አንዲት ሴት ልጅ ተገላልጣ ስትሄድና ተሸፋፍና ስትሄድ መስመር ላይ ያሉ ሥርዓት ያጡ ወንዶች የሚለክፉት ለከፋ የትኛዋን ነው? ሁላችሁም በአንድ ድምጽ የተገላለጠችው ነው እንደምትሉኝ አልጠራጠርም።የተላጠውን ሙዝ ዝንቦች ይወሩታል አይደል።!! አሁን ሚስጥሩ ጎልቶ ይታየናል። በ1ኛ ቆረንቶስ 11፡5-6 እና 11፡13‹‹***ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለች፤ እንደ ተላጨች ያህል አንድ ነውና። ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ፀጉሯን ትቆረጥ፤ ለሴት ግን ፀጉሯን መቆረጥ ወይም መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን።... በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታል?***›› ፍርዱን ለእናንተ ስለ ቀረበ እራሳችሁ ፍረዱ።

## ሴት ልጅ ዓይነ ርግብ (ኒቃብ) መልበስ እንዳለባት

ሴት ልጅ ዓይነ ርግብ (ኒቃብ) መልበሷን ከሃይማኖት ትእዛዝ ብቻ ሳይሆን ከጤና አንፃርም የመንመለከተው ይሆናል። የክርስቲያን ሴቶች የዓይን ኩል ተቀባብተው አካላቸው ወደ ዝሙት እየተጣራ ይሄዳል። በዚያ ላይ የተላያየ ቀሻሻን የሚስቡ የዓይን ኩሎች አሉ። ነገር ግን ከዚ ሁሉ ቢሸፈኑ ከሚያደርጉት ሰው ሰራሽ (አርቴ) ይልቅ አምላክ የለገሳቸው ፀጋ ይበቃቸዋል። ከሚመጣባቸው

ቆሻሻና ብሽታም ይጠብቃቸዋል። በመጽሐፈ መኃልይ ዘሰለሞን 4፡1«***በዓይነ ርግብ (ኒቃብ) መሸፈኛሽ* ውስጥ ዓይኖችሽ እንደ ርግቦች ናቸው፡**» ከዚሁ ምዕራፍ 5፡6«***ከተማይቱን የሚዞሩት ጠባቂዎች አገኙኝ መቱኝ፤ አቆሳሰሉኝኝም ቅጥር ጠባቂዎችም *የዓይነ ርግብ (ኒቃብ) መሸፈኛዬን* ወሰዱት፡፡***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 6፡7«***በዓይነ ርግብ (ኒቃብ ) መሸፈኛሽ* ውስጥ ጉንጭና ጉንጭሽ እንደ ተከፈለ ሮማን ናቸው፡፡**» በኦሪት.ዘፍጥረት 24፡66«***እርሷም *መሸፈኛ (መነቀቢያ)* ወሰዳ ተከናነበች፡፡***»

## ወንድ ልጅ ሱሪውን አሳጥሮ መልበስ እንዳለበት

እንደ አለመታደል ሆኖ ክርስቲያኖች በሙስሊሞች ላይ ሱሪአቸውን አሳጥረው ስለለበሱና አምላካቸውን ስለታዘዙ ያሾፉባቸዋል። የሚያሳዝነው ይህ ሹፈታቸው በሙስሊሞች ብቻ መስሏቸዋል። ነገር ግን በእራሳቸውም መጽሐፍ ቅዱስም ነው የሚያሾፉትና የሚሳለቁት። አንዳንዶች ከሙስሊሞች ሱሪውን አሳጥሮ ሲያዩ ልብስ ጨርሰው ነው ከቁርጭምጭሚትህ በታች ያልወረደው? ይላሉ። ምክንያቱም ለክርስቲያኖች ይህ ነገር ልክ "‹**ለአህያ ማር አይጥማትም**›" ነው ነገሩ። ለማንኛውም መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ዙሪያ ምን እንደሚል እንመልከት፡- በትንቢተ.ሚልኪያስ 2፡16«***የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር *ልብሱን በግፍ ድርጊት የሚሸፍነውን (የሚጎትተውን) ሰው* እጠላለሁ ይላል እግዚአብሔር (ፀባዖት)፡፡***» በግፍ ድርጊት መሸፍን ማለት ልብስን አሳጥሮ በአግባቡ አለመልበስ ማለት ነው። ክርስቲያኖች ቆም ብላችሁ አስቡት ከንጽህና አንፃር ምን ያክል ጠቀሜታ እንዳለው መቼም ይህን እውነታ ማንም አይክደውም። ኢየሱስም ይህን ሐሳብ ደግፎ ሲናገር፡- በማቆርስ ወንጌል 12፡38-40«***ሲያስተምርም እንዲህ አለ፡- *ረጃጅም ልብስ ለብሰው መዞርን* በገቢያም ሰላምታን በእየ ምኩራውም የከበሬታን ወንበር፤ በግብርም የከበሬታን ስፍራ ከሚወዱ ከፃፎች የጠበቁ። የጸሎቶችን ቤት የሚበሉ፤ ፀሎታቸውን በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ፡፡***» በጸሎት በማመካኘት ሕዝቡን የሚያጭበረብር እነ ማን ናቸው? ቢባል በእርግጠኝነት የሚደረገውን አሳፋሪ ተግባር አምላክን በእጅጉ የሚያስቀይም ስራ የሚሰሩ እነ ማን እንደሆኑ ሀገር ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ነው። እንዲሁም የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ያስተማረውን በመቃረን ደረጃም ቢሆን ከአይሁዳውያን የማይሻሉ ናቸው። ኢየሱስ ሙስሊም ነበር፤ ሱሪን አሳጥሮ

ብሏል። ሙስሊሞችም የኢየሱስን ምክር ይሰማሉ፤ ልባሳቸውን ያሳጥራሉ። ልብሳቸውን ሳያሳጥሩ አስረዝመው የሚለብሱ ሰዎችን በምንመለከትበት ጊዜ ከተረከዛቸው በታች ያለው ክፍል ሌላ ልብስ ይመስላል። አንዳንዴም ከመቆሸሹ የተነሳ ሌላ ልብስ ተቆርጦ የተቀጠለ ያስመስለዋል። ስለዚህ ልብሳችሁን አሳጥራችሁ አምላክ ባዘዘው መልኩ እንደ ሙስሊሞች መልበስ አለባችሁ፤ ትርፍ መጫን ይቅርባችሁ። መቼም መኪና ትርፍ ከጫነ መቀጣቱ እንደማይቀረው ሁሉ እናንተም አምላክ እንዳይቀጣችሁ ትእዛዙን ጠብቁ በማለት ካለኝ መልካም ጎን እመክራለሁ።

## ጺምን ማሰደግ እንጂ አለመቁረጥ እንዳለብን

ፂም አምላክ ለሰው ልጆች የለገሰው ታላቅ ፀጋ ነው። እንዲሁም ወንዶች ከሴቶች ከሚለዩበት አንዱ ተፈጥሮአዊ መለያ ባሕሪ ነው። አምላክ ለወንዶች ፂማቸውን እንዲያሳድጉ አዟቸዋል፤ እንዲሁም እንዳያሳጥሩም ከልክሏቸዋል። በ1993 ዕትም በኦሪት.ዘሌዋውያን 19፡27«***የእራስ ፀጉራችሁን ዙሪያውን አትከርከሙ፤ <u>ጺማችሁንም አሳጥራችሁ አትቁረጡ</u>።***» ለዚህ የአምላክ ትዕዛዝ ሙስሊሞች ብቻ ናቸው ተገዥና ተቀባይ የሆኑት። ክርስቲያኖችን በምንመለከትበት ጊዜ እንዲያውም ፂሙን በሚያሳድግ ሰው ላይ ያላቸው አመለካከት ሌላ ነው።

## ምዕራፍ አሥራ አምስት

## በመጽሐፍ ቅዱስ ተቀብረው ካልበሰበሱት እውነታዎች መካከል

ክርስቲያኖች በመጽሐፍቸው ውስጥ በርካታ እውነቶችን ተቀበረዋል። ቢሆንም ግን ተቀብረው አልበሰበሱም። ከእነዚህም መካከል ስለ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻ ነብይ እንደሚሆኑ የተተነበዩ ትብቢቶች፤ የማይጽፉና የማያነቡ መሆናቸውን፤ በመካ እንደሚነሱ፤ እንድሁም ቁርኣን እንዴት እንደሚወርድላቸው፤ ቁርኣን በሁለት ቦታዎች እንደ ወረደ በመካና በመዲና፤ መካ የሚለው ስም መኖሩ፤ ወደ መካና መዲና ሐጅና ዑምራ ስለ ማድረግ፤ ስለ ዐረብ የተነገረ ሸክም፤ ስለ ካዕባ እና ሌሎችም እውነቶች ለመደብቅ ቢሞክሩም አላህ አጋልጧቸዋል። እያንዳንዳቸውን በዝርዝር በማስረጃ እንመልከታቸው።

## ስለ መካ መጠቀስና ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከዐረብ ምድር ከመካ እንደ ሚላኩ የተተነበዩ ትንቢቶች

መካ ሌላ ስሟ በካ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በሚከተለው ጥቅስ እንዲህ ይገልፃታል። ከኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን ከተወሰደው መጽሐፍ ቅዱስ በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6«***እነርሱ የበካ ሸለቆ ውስጥ ሲያልፉ፤ የምንጮች ሥፍራ ኢደረጓት፤ የመከር ዝናቦችም በኩሬዎች ይሸፍኗታል***።» የአራማይክ መጽሐፍ ቅዱስ በቀላል እንግሊዝኛ ከሚለው የተወሰደ በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6 «***በለቅሶ ሸለቆ አጠገብ አለፉ፤ የመኖሪያ ሥፍራም ኢደረጓት፤ እንደዚሁም የሕግ መምህርን በረከት ይሸፍናል***።» King James Verision since 1798 Page 307 Plasma 84:4«Who Passing Through The Valley of Baka Make it awell The Rain also FilleTh The Pools.»የ1954 ዕትም ላይ በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6«***በለቅሶ ሸለቆ ውስጥ በተወሰነው ሥፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጠናል***።» የ1980 ዕትም በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6«***በካ በተባለው ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ የምንጭ ሥፍራ ይሆናል***።» ይህ የሕግ መምህር ከበካ (ከመካ) የተነሳው ለዓለም የሚላክ ነብይ ማን ነው ቢባል ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ክርስቲያኖችም ሳይቀሩ በአንድ ድምፅ ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው ብለው እንደሚመልሱ ጥርጥር የለኝም። ለምን ቢሉ ከመካ የተነሳ የሕግ መምህር እሳቸው ብቻ ናቸው።

## <u>ነብያችን ሙሐመድ ከመላካቸው በፊት የማይጽፉና የማይነቡ መሆናቸው መጠቀሱ</u>

በትንቢተ.ኢሳይያስ 29፡11-12‹ ‹*ራእዩም እንደ ታተመ መጽሐፍ ቃል ሆኖባቸዋል። ማንበብንም <u>ለሚያውቅ</u>* ☾1879 ዕትም› *(<u>ለማያውቅ</u>) ይህንን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ታትሟልና አልችልም ይላቸዋል። ደግምም መጽሐፍን ምንባብ ለማያውቅ ይህንን አንብብ ብለው በሰጡት ጊዜ እርሱ ማንበብ ይላቸዋል።*›› ከዕለታት አንድ ቀን መላአኩ ጅብሪል (ገብርኤል) በድንገት በመምጣት ወደ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አንብበ አላቸው። እሳቸው የሚጽፉና የሚያነቡ ስላልነበሩ አልችልም አሉት። አሁንም እየደጋገመ መልአኩ አንብብ ሲላቸው ማንበብ አልችልም አሉት። ማንበብና መፃፍ ያልቻሉበት ምክንያት ለምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ አሁንም ይህ ምዕራፍ መልስ ይሰጠናል። በትንቢተ.ኢሳይያስ 42፡18-19‹‹*<u>እናንተ ደንቆሮዎች ስሙ፤ እናንተ ዕውሮች ታዩ ዘንድ ተመልከቱ፤ ከባሪያዬ በቀር ዕውር የሆነ ማን ነው? እንደምልከው መልእክተኛዬስ በቀር ደንቆሮ የሆነ ማን ነው? እንደ ፍፁም ወይንስ እንደ እግዚአብሔር ባሪያ ዕውር ማን ነው</u>?*›› ዕውር ማለት ማንበበና መፃፍ የማይችል ማለት ነው። የኔ ብዙ ማለት አያስፈልግም። ምክንያቱም አንቀጽ የበለጠ የማስረዳት አቅም አለው። ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቁርኣንን ማንበብና መፃፍ ከመላካቸው በፊት እንደማይችሉ በትንቢተ.ኢሳይያስ የተተነበየውን እውነታ አላህ ሲያረጋግጥልን፡- በሱረቱል አል-አንከቡት 29፡48‹‹**ከርሱ (ከመላካቸው በፊት) በፊትም መጽሐፍን፣ የምታነብ በቀኝህም የምትጽፍ አልነበርክም**›› ብሏል።

## <u>ቁርኣን ለነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመካና በመዲና እንደሚወርድላቸው</u>

በትንቢተ.ኢሳይያስ 28፡10-12‹‹*<u>ትእዛዝ በትእዛዝ ሥርዓት በሥርዓት ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ነው። በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን ለዚህ ሕዝብ ይነገራል። እርሱም እርፍት ይህች ናት የደከመውን አሳርፍ ይህችም ማረፊያ ናት አላቸው። እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ።</u>*›› የቁርኣን አንቀጻት ትዕዛዝ ስርዓት በስርዓት በባዕድ አፍ በልዩም ልሳን (በአረበኛ ቋንቋ) ከእስራኤል ቋንቋ ውጭ በባዕድ አፍ

በልዩ ልሳን ጥቂት (በመካ) ጥቂት (በመዲና) በመውረድ ትልቁና ዓለም አቀፋዊ ሃይማኖታዊ መጽሐፍ ሆኖ በመውረዱ ትንቢቱ ተፈጻሚነቱ በተግባር ታይቷል። በመቀጠል በልዩ ልሳን በባዕድ አፍ ይህችን ጥቅስ እንመልከታት ይህ ልዩ ልሳን የሆነውና ዓለም አቀፋዊ ቋንቋ ምንድን ነው? አረበኛ ቋንቋ አይደለምን? ሁሉም የዓለም ሙስሊሞች አረቡም፣ ሐበሾችም ሌላውም በአጠቃላይ ሁሉም ሕዝብ የሚጠቀምበት የጋራ የአምልኮ ቋንቋ አረበኛ ቋንቋ ነው። ለስግደት (ለሶላት) በምቆምበት ሰዓት "አለሁ አክበር" በማለት ስግደታችን እንጀምራለን። ክርስቲያኖችን በምመለከትበት ጊዜ ለአምልኮ የሚጠቀሙበት የጋራ ቋንቋ የላቸውም። በአገራችን እንኳ በተለያየ ቋንቋ ነው የሚጠሩት። አማራውም በአማርኛ ኦሮሞውም በኦሮሚኛ ጉራጌውም በጉራጊኛ ሌላውም በሌላ ነው። በጣም የሚገርመው ደግሞ *"‹‹**እነርሱ ግን መስማትን እንቢ አሉ**››"* የሚለው ሐረግ ቁርኣንም እንዲህ ነው የገለጸው በሱረቱን 17፡18‹‹**በዚህም ቁርኣን ውስጥ ከምሳሌው ሁሉ ለሰዎች በእርግጥ መላለስን <u>አብዛኛዎቹም ሰዎች ክደትን እንጂ ሌላ እንቢ አሉ</u>**።›› አንቀጹ ሲቀጥል *"‹‹**ለዚህ ሕዝብ ይናገራል**››"* ይላል። ላለፉት ሕዝቦች ቢሆን ለዚህ ሕዝብ ይናገራል ተብሎ አይፃፍም። ለዚህ ሕዝብ የተናገሩ ደግሞ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ናቸው። ስለዚህ ምርጫችን አስተካክለን ያለንን ዕድል እንጠቀምበት።

## <u>ወደ መካ ኢስላማዊ የሐጅና ዑምራ ሥነ ሥርዓቶች</u>

ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ የሙስሊም ሐጃጆችን ለጣዖት አምልኮ እንደሚሄዱ አድርገው ያስባሉ። ነገር ግን ይህ ሃይማኖታዊ የሐጅና የዑምራ ሥነ ሥርዓት በመጽሐፍ ቅዱስም ይገኛል። በትንቢተ.ሕዝቅኤል 40፡1-3‹‹***በተማረክን በሃያ አምሥተኛው ዓመት በዓመቱ መጀመሪያ ከወሩ <u>በአሥረኛው ቀን</u> ከተማይቱ ከተመታች በኋላ በአሥራ አራተኛ ዓመት፤ በዚያው ቀን የእግዚአብሔር እጅ በእኔ ላይ ነበር እርሱም ወደዚያ ወሰደኝ።***›› የዚህ የጉዞ ወቅት የሐጅና ዑምራ ጊዜ በዓመቱ መጀመሪያ ከወሩ በአሥረኛው ቀን ነው። ይህም ከኢስላማዊ በዓል ጋር ተዛማጅት አለው፤ አይሁዶች ልክ እንደ እንደ ሙስሊሞች የጨረቃ ዘመን አቆጣጠር ይጠቀሙ ነበር። ስለዚህም የመጨረሻው ወር አሥረኛ ቀን ***<u>የዒድ አል ሐድሃ በዓል</u>*** ነው። በዚህ ጊዜ ወደ መካ ሐጅ የሚደረግበት ዓመታዊ ወቅት እንደሆነ በሚገባ ይታወቃል።

## ሐጅ የሚደረግበትን ቦታ ጠንቅቆ ማወቅ እንደሚገባ

በትንቢተ.ሕዝቅኤል 44፡6-8‹‹*እግዚአብሐርም እንዲህ አለኝ፡- የሰው ልጅ ሆይ፤ ልብ አድርግ ስለእግዚአብሔርም ቤት ሥርዓትና ሕግ ሁሉ የምነግርህን ሁሉ በዓይን ተመልከት በጆሮህም ስማ፤ የቤቱን መግቢያ የመቅደሱንም መውጫ ሁሉ ልብ አድርግ*።›› በሐጅ ወቅት ሐጅ የሚደረግበትን ቦታ ለይቶ ማወቅ ሐጁ ትክክል እንዲሆን ከሚያግዙት ነጥቦች አንዱ ነው። ምክንያቱም ሐጃጆች ከሌላ ሀገር ወደ መካ የሐጅ ቦታ ስለሚሄዱ የሚያውቁት ሀገር ስላልሆነ ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል። ለዚህ ነው አምላክ ነብዩ ሕዝቅኤልን ባሳለፍነው ምዕራፍ ላይ ስፍረውንና ልኬቱን ልብ ብሎ እንዲመለከት አስጠንቅቆ የነገረው። የቤቱንም መግቢያ የመቅደሱንም መውጫ ሁሉ ልብ አድርግ በማለት።

## ሐጅ የሚደረገው ወደ መካ መሆኑና የሐጅ ሥነ ሥርዓቱም በሶፋና በመርዋ ተራሮች እንደሚከናውን

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 40፡2-3‹‹*በእግዚአብሔር ራእይ ወደ እስራኤል ምድር አመጣኝ፤ እጅግም በረዘመ ተራራ ላይ አኖረኝ፤ በዚያም ላይ በደቡብ ወገን እንደ ከተማ ሆኖ የተሠራ ነገር ነበር*።›› ከተማዋ ከእስራኤል ምድር በስተ ደቡብ ናት። በዚያ በዙሪያዋ በተራሮች የታጠረች ከተማ ናት። እነዚህም ተራሮች ሶፋና መርዋ ናቸው። በደቡብም ወገን እንደ ከተማ ሆኖ የተሰራው ነገር ካዕባ ነው። አሁንም ይህን ቦታ በመግለጽ ረገድ የነብዩ ሕዝቅኤል ተጨማሪ ማስረጃዎች አሉ። ‹ካዕባ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መጠቀሱ› ከሚለው ርዕስ ዝርዝሩን ይመልቱ።

## የሐጃጆች የኢሕራም ልብሶችና ከሐጃጆች የሚጠበቁ ሕግጋቶች

በትንቢተ.ሕዝቅኤል 44፡17‹‹*ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በር በገቡ ጊዜ የተልባ እግር ልብስ ይልበሱ፤ በውስጠኛው አደባባይ በርና በቤቱ ውስጥ ባገለገሉ ጊዜ ከበግ ጠጕር አንዳች ነገር በለያቸው አይሁን*።›› ከዚሁ ምዕራፍ 44፡18 ‹‹*በራሳቸው ላይ የተልባ እግር መጠምጠሚያ ይሁን፤ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን፤ የሚያወዛም ነገር አይታጠቁም*።›› ከዚሁ ምዕራፍ 44፡19-20 ‹‹*ወደ ውጫኛውም አደባባይ ወደ ሕዝብ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፤ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውጥ ያኑሩ፤ ሕዝቡን በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ሌላውን ልብስ ይልበሱ*።›› ከዚሁ ምዕራፍ 44፡14‹‹...*ሌላም ልብስ*

***ለብሰው ወደ ሕዝብ ይወጣሉ፡፡***» ማብራቱቱ ቃል በቃል መተርጎም ስለሚሆን የተወሰነ ብቻ ነካ አድርጌ ልለፍ፡፡ ስለ ሐጃጆች አልባሰት ተጠቃሏል፡፡ በውስጠኛውም አደባባይ በርና በቤቱ ውስጥ ባገለገሉ ጊዜ ከበግ ጠጉር መጠምጠሚያ ይሁን፤ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን፡፡ ወደ ውስጠኛውም አደባባይ በር በገቡ ጊዜ የተልባ እግር ልብስ ይልበሱ፤ እነዚህን በሙሉ የሙስሊም ሐጃጆች አልባሳት ናቸው፡፡ እንዲሁም ከሐጃጆች የሚጠበቁ ሥርዓቶችን ነው፡፡ አሁንም ተጨማሪ ማብራሪያ አለ፡፡ ወደ ውጭኛውም አደባባይ ወደ ሕዝብ በወጡ ጊዜ ያገለገሉበትን ልብሳቸውን ያውልቁ፡፡ በተቀደሰውም ዕቃ ቤት ውስጥ ያኑሩ፤ ሕዝቡን በልብሳቸው እንዳይቀድሱ ሌላውን ልብስ ይልበሱ፡፡ ....ሌላ ልብስ ለብሰው ወደ ሕዝብ ይወጣሉ፡፡ ሐጃጆች ሌላ ልብስ በሐጅ በውስጠኛውም አደባባይ በርና በቤቱ ውስጥ ባገለገሉ ጊዜ ከበግ ጠጉር መጠምጠሚያ ይሁን፤ በወገባቸውም ላይ የተልባ እግር ሱሪ ይሁን፡፡» የሐጃጆች ሌላ ልብስ በሐጅ ጊዜ የሚለብሱት ልብስ **የኢሕራም ልብስ** በመባል ይታወቃል፡፡

## በተራሮች ላይ ሆነው ሐጃጆች የሚያቀርቡት የምስጋና ጸሎት

በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 42፡10-11«***ለእግዚአብሔር አዲስ መዝሙር ከምድርም ዳርቻ ዘምሩ፤.....በተራሮችም ራስ ላይ ሆነው ይጮኹ፡፡***» አዲስ መዝሙር ማት በፊት ከነበረው ዝማሬ የተለየ ዝማሬ ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም በአምልኮ ጊዜ የሚዘመረው ዝማሬ ሁሉ ዓለም ዓቀፋዊና በአረበኛ ቋንቋ የሚደረግ ነው፡፡ ስለዚህ በዚያ ተራራ ራስ ላይ ለአላህ ምስጋና በማድረግ ትንቢቱ ለወደፊትም እየተፈጸመ በተግባር ይገኛል፡፡ እነዚም ተራሮች የሚገኙት በመካ ነው፡፡

## ሐጃጆች ከሐጅ ሥነ ሥርዓት በኋላ የሚያደርጓቸው መስዋዕቶች (እርዶች)

በትንቢ.ተ.ሕዝቄኤል 42፡13«*እንዲህም አለኝ፡- በልዩ ሥፍራ አንፃር በሰሜንና በደቡብ በኩል ያሉ ዕቃ ቤቶች፤ እነርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚቀርቡ ካህናት ከሁሉ ይልቅ የተቀደሰውን ምግብ የሚበሉባቸው ቤቶች ናቸው፡፡ ሥፍረው ቅዱስ ነውና በዚያ የተቀደሰውን ነገር የእህሉን ቁርባን **የኃጢአቱንና የበደሉን መስዋዕት ያኖራሉ፡፡*** ከዚህ ላይ እንደ ነብዩ ሕዝቅኤል የሐጅ ወቅት ሊጠናቀቅ ሲል

የሚደረገውን መሰዋዕት እየጠቆመን ነው። የእህሉን ቁርባን የኃጢአቱንና የበደሉን መሰዋዕት ያኖራሉ በማለት። ተጨማሪ በትንቢተ.ኢሳይያስ 60፡7 ***«የቄዳር መንጋዎች ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ፤ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፤ እኔን ደስ ሊያሰኙኝ በመሰዊያዩ ላይ ይወጣሉ፤ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ።»*** ይህ ትንቢት በዐረፋ ቀን የሚደረጉትን የእርድ ሥነ ሥርዓቶች ያመለክታል። ከዚህ ላይ ጥያቄ ከዐረብ ምድር የሆኑትን መንጋዎች አውራ በጎች ማንን ነው የሚያገለግሉት? መካን ወይንስ ጽዮንን? መካ እያገለገሉ መሆኑ እውነታው ሳይታለም የተፈታ ነው። ምክንያቱም በክርስቲያኖች ዘንድ “ኢየሱስ የመጨረሻ የኃጢአት መሰዋዕት ሆኖ ነው የመጣው” ብለው ስለሚያምኑ ነው። ስለዚህም ያን በብሉይ ኪዳን የተጠቀሰውን የእርድን አስፈላጊነት ከንቱ አድርጎታል። በኢስላም ደግሞ እንስሳትን ማረድ በሐጅ ጊዜ የተለመደ ዓመታዊ ተግባር ነው።

## <u>የዘምዘም ውኃ በመካ ውስጥ መጠቀሱ</u>

በ1879 ዕትም በበትንቢተ.ሕዝቂል 47፡9 ***«ሕያው ነፍስ ያለውም፤ የሚንቀሳቀሰውም ሁሉ ወንዙ የደረሰበት ሁሉ ይድናል፡፡-----ይህች ውኃ ከዚያ ስለ ደረሰች ይፈውሰማል፤ ይድንማል፡፡»*** ይህ የዘምዘም ውኃ በእጅጉ መድኃኒት ነው፡፡ ሌላው ውኃ እንደማይፈውስ ከዚሁ ምዕራፍ ቀጥር 11 ላይ ***«ረገረጉና አቋሪው ውኃ ግን አይፈውሱም፤ ጨው እንደሆኑ ይኖራሉ እንጂ፡፡»*** እየ1980 ዕትም በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6 ***«በካ (መካ) በተባለው ሸለቆ በሚያልፉበት ጊዜ የምንጭ ሥፍራ ይሆናል።»*** የ1954 ዕትም በመጽሐፈ መዝሙር 84፡6 ***«በለቅሶ ሸለቆ ውስጥ በተወሰነው ሥፍራ የሕግ መምህር በረከትን ይሰጠናል።»*** በለቅሶ ሸለቆ የተባው ነብዩ ኢብራሂም (አብርሃም) የመጀመሪያ ልጃቸውን ኢስማኤልን ከእናቱ ሐጀር ጋር ያሳረፈበት ምድረ በዳ ሲሆን እናትና ልጅ ያለቀሱበት ይሆኸው ሥፍራ ነበር። አምላካችን አላህ ለለቅሷቸው ምልሽ በመስጠት የምንጭ ውኃ አፈለቀላቸው። ይህ ምንጭ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይደርቅ ኅያው ሆኖ የቆየ ነው። ለወደፊትም ኢንሻአላህ ኅያው ሆኖ ይቆያል። የምንጩ ስምም <u>**ዘምዘም**</u> ይባላል።

## በመካ ውስጥ የሚገኘው ካዕባ መጠቀሱና ቅርጹም አራት ማዕዘን እንደሆነ

በሒጃዝ ግዛት በዐረቢያ ደቡባዊ ክፍል ከቀይ ባሕር እሩቅ ሳትሆን የምትገኝ የመካ ከተማ ናት። በዚህች ከተማ ላይ ከድንጋይ የተሠራ ትንሽ አራት ማዕዘን ግንባታ ይገኛል። የማዕዘኑ ርዝመት 60 ጫማ ርዝመት፤ 60 ጫማ ወርድ እና 60 ጫማ ቁመት ነው። ይህ አራት ማዕዘን ከጥንት ጊዜ ጀምሮ መኖሩ ይታወቃል። ወደዚያ ቤት የሚጓዙ ተጓዦችም ያውቁታል። ስሙም **በይቱላህ የአላህ ቤት** ይባላል። ቅዱስነቱና ጥንታዊነቱ ከታሪክ እራሱ የበለጠ ጥንት ነው። የቤቱ ስዕል የሚከተለው ነው።



## ነብዩ ሕዝቄኤል የዚያን ሥፍራ ቅርጽ ሲገልጽ

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 42፡15 ‹‹*ውስጠኛውንም ቤት ለክቶ በፈጸመ ጊዜ ወደ ምስራቅ በሚመለከት በር መንገድ አወጣኝ፤ እርሱንም በዙሪያ ለካው።*›› በአራቱም አቅጣጫ ለክቶ አራት ማዕዘን መሆኑን በሚከተሉት ምዕራፎች ይናገራል። በትንቢተ.ሕዝቄኤል 42፡16‹‹*የምስራቁን ወገን በመለኪያ ዘንግ አምስት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ። ዞሮም፤*.........›› ከዚሁ ምዕራፍ 42፡18 ‹‹*የደቡብኑም ወገን*

***<u>በመለኪያ ዘንግ አምሥት መቶ ክንድ አድርጎ ለካ።ዘረም፤</u>*......» ከዚሁ ምዕራፍ 42፡19-20«***<u>በአራቱ ወገን ለካው</u>። የተቀደሰውንና ያልተቀደሰውን ይለይ ዘንድ <u>ርዝመቱ አምሥት መቶ ክንድ</u>፤ <u>ወርዱ አምሥት መቶ ክንድ</u> የሆነ ቅጥር በዙሪያው ነበር።***» ከዚህ ቅርጽ አንፃር ይህ ቦታ አራት ማዕዘን ነው። በትንቢተ.ሕዝቅኤል 41፡4 «***በመቅደሱም ፊት <u>ርዝመቱን ሀያ ክንድ</u>፤ <u>ወርዱንም ሀያ ክንድ</u> አድርጎ ለካና፡- ይህ <u>ቅድስተ ቅዱሳን ነው</u> አለኝ።***» እንደዚህ ቅዱስ ቦታ አገላለጽ ቅርጹ አራት ማዕዘን ነው። እንዲሁም ካዕባም አራት ማዕዘን መሆኑ በሚገባ ይታወቃል። ጥያቄ ለመሆኑ በክርስትና ወይም በአይሁድ ከዚህ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይ ቅርጽ ያለው የተቀደሰ ቤት አለን? ነብዩ ሕዝቅኤል ከላይ ከተገለጸው በተጨማሪ ስለ መስፋት ተንብተዋል አብረን እንከታተል። በትንቢተ.ሕዝቅኤል 41፡6-7«***በመቅደሱም ግንብ ዙሪያ ደገፋዎች ይሆኑ ዘንድ እረፍቶች ነበሩ። በመቅደሱም ግንብ ውስጥ ደገፋዎች አልነበሩም። በቤቱም ዙሪያ ባለ ግንብ ውስጥ በነበሩት እረፍቶች ነበሩ። በመቅደሱም ግንብ ዙሪያ ደገፋዎች ይሆኑ ዘንድ እረፍቶች ነበሩ። በመቅደሱም ግንብ ውስጥ ደገፋዎች አልነበሩም። በቤቱም ዙሪ ባለ ግንብ ውስጥ በነበሩት እረፍቶች ምክንያት ላይኞቹ ጓዳዎች ከታችኞቹ ጓዳዎች ይበልጡ ነበር።***» ከዚሁ ምዕራፍ 47፡1«***ወደ መቅደሱም መዝጊያ መለሰኝ፤ እነሆም፤ <u>ውኃ</u>፤ ከቤቱ መድረክ በታች ወደ ምስራቅ ይወጣ ነበር፤ የቤቱ ፊት ወደ ምስራቅ ይመለከት ነበርና ውኃውም ከቤቱ ከቀኝ ወገን በታች በመሰዊያው በደቡብ በኩል ይወርድ ነበር።***» ከዚሁ ምዕራፍ 47፡2«***በሰሜኑም በር በኩል አወጣኝ፤ በስተ ውጭ ባለው መንገድ ወደ ምስራቅ ወደሚመለከት በስተ ውጭ ወዳለው በር አዞረኝ፤ እነሆም፤ <u>ውኃው</u> በቀኝ ወገን ይፈስ ነበር።***» ከዚሁ ምዕራፍ 47፡3«***ሰውዬውም ገመዱን በእጁ ይዞ ወደ ምስራቅ አንድ ሸህም ክንድ ለካ፤ <u>በውኃው</u> ውስጥ አሻገረኝ፤ <u>ውኃም</u> እስከ ቁርጭምጭሚት ደረሰ።***» ከዚሁ ምዕራፍ 47፡4«***ደግም አንድ ሺህም ለካ ላሻገረው የማይችለው <u>ወንዝ ነበር</u>።***» ከዚህ ላይ እነዚህ አንቀጾች በሙሉ የሚያስረዱት እውነታ አለ። ነብዩ ሕዝቄኤል ሐጅ ማድረጉን እንረዳለን። ከዚያም በቤቱ ዙሪያ ውኃ አግኝቷል። ይህ በጣም ትልቅ ውኃ ከቤት ስር ከቀኝ ወገንና ከመስዊያው ደቡብ በኩል የሚወርድ ነው። የዚህ ውኃ ማብሪያና እንዴት ትልቅ እንደ ነበር የተገለጸበት ሁኔታ በትክክል **<u>የዘምዘም ውኃን</u>** ነው።

ከላይ ያለው የአምላክን ቤት በይቱላህን ክ ርስቲያኖች እውነታን ለመደበቅ ሲሉ ሰለሞን የገነባው ቤተ መቅደስ ነው ይላሉ። ነገር ግን ሰለሞን የገነባው ከካዕባ ጋር እናነፃፅር። በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማይ 6:2«***ንጉሡ ሰለሞንም ለእግዚአብሔር የሠራው ቤት ርዝመቱ ስድሳ (60) ክንድ፣ ወርድም ሀያ (20) ክንድ፣ ቁመቱም ሠላሳ (30) ክንድ ነበር።***» ይህን ሰለሞን የሰራውን ከካዕባ ጋር ስናነፃፅር ያለውን ልዩነት እንመልከት ካዕባ ርዝመቱ 60 ጫማ 60 ወርዱ ጫማና ቁመቱም 60 ጫማ ነው። ታዲያ ሰለሞን ከሰረው ጋር ምን ዝምድና አለው? እንደ ሰለሞን ቤተ መቅደስ ገለፃ ፣ከዚያ በነብዩ ሕዝቂኤል ከቁጥር 40-43 ከተገለፀው እንደሚለይ በደንብ ግልፅ ነው። ነብዩ ሕዝቂኤል ማንኛውንም በኢሩሳሌም የሚገኘውን የአምላክ ቤት ነው ተብሎ የሚነሳውን ደረቅ ሙግት ከንቱ ያደርገዋል። ምክንያቱም ከካዕባ ውጭ አራት ማዕዘን የሆነ ሌላ የአምላክ ቤት አልነበረምና። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰውን አራት ማዕዘን የአምላክ ቤት ከካዓባ ውጭ በምድር ገጽ የት ይገኛል?

## “ስለ ዓረብ የተነገረ ሸክምና” ስለ በድር ጦርነት እንዲሁም ስለሰደተኞች (ሙሐጅሮች) ስለሰደተኞች አስጠጊዎችና ረጂዎች (አንሷሮች) መጠቀሰ

በትንቢተ.ኢሳይያስ 21፥13-17«***ስለ ዐረብ የተነገረ ሸክም፤ የድዳናዊያን ነጋዴዎች ሆይ በዓረብ ዱር ውስጥ ታድራላችሁ። በቴማን የምትኖሩ ሆይ ወደ ጠጠሙት ሰዎች ውኃ አምጡ እንጀራም ይዛችሁ የሸሹትን ሰዎች ተቀበሉአቸው። ከሰይፍ ከተመዘዘው ሰይፍ ከተለጠጠው ቀስት ከጽኑም ሰልፍ ሸሽተዋልና ጌታ እንዲህ ብሎናልና እንደ ምንደኛ ዓመት በአንድ ዓመት ውስጥ የቄዳር ክብር ሁሉ ይጠፋል። ከቀስተኞች ቁጥር የቀሩት የቄዳር ልጆች ኃያላን ያንሳሉ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ተናግሯልና።***» ይህ ትንቢት በትክክል ለመፈጸሙ በርካታ ተግባራቶች ትንቢቱን በሚመለከት መልኩ ተከናውነዋል። ቄዳር ማለት መካ ማለት ሲሆን ቴማን ደግሞ መዲና ማለት ነው። እንዲሁም መልካም በመስራት ወደር የለሽ የሆኑ ሰዎችንም አንቀጹ ያወሳል። በታዋቂ ስማቸው የቄዳር (የመካ) ስደተኞች (ሙሐጅሮች) እና ስደተኞችን አስጠጊ የሆኑት ረዳቶች የቴማን (የመዲና) (አንሷሮች) እንዲሁም ታሪክ ለሚያወሳው የበድር ጦርነት ያስቃኙናል። ይህ ትንቢት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እና በባልደረቦቻቸው ከመካ (ከቄዳር) ስደትና በመዲና (ቴማን) ሕዝቦች ተቀባይነት፤ እነዚያ ሁልጊዜ

በታዋቂ ስማቸው በሚታወሱት “ሙሐጂሩን (ስደተኞች)” እና “አንሷሮች (ረዳቶች)” በቅደም ተከተል ተፈጽሟል። በተጨማሪም ስለበድር ጦርነት፣ በኢስላም ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው ወሳኝ ስለሆነው ጦርነት ይናገራል። የመካ ሁኔታ በጣም አሰቃቂ፣ ከኢስላም ጠላትነቱ ጋር ሊመለስ የማይችልበት ደረጃ ላይ በደረሰ ጊዜ ወደ መዲና ስደት ታዘዙ። ቄዳር እና ቴማን የእስማኤል (ዐለይሂ ሰላም) ልጆች ስሞች ናቸው። ከኦሪት.ዘፍጥረት 25፡12-13 ማየት እንደሚቻለው። የመዲና ነዋሪዎች ነብዩን (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) እና ሙሽሪኮች በበድር ሜዳ ጦርነት ተካሂዷል። ሙስሊሞችም በመካ ሙሽሪኮች ላይ ድል በመቀዳጀት ጦርነቱ ተጠናቋል። “የበድር ጦርነት፣ ቅዳሜ ዕለት፣ ማርች 3፣ 624 ዓ.ል (ረመዷን 17፡2 ዓ.ሒ በኢስላማዊው አቆጣጣር) በምዕራባዊ ዐረቢያ ሒጃዝ ክልል (የዛሬዋ ሳዑዲ ዐረቢያ) በኢስላም የመጀመሪያው ቀናት ወሳኙ ጦርነት በነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ትግል መካ ውስጥ ካሉት ባላንጣ ቁረይሾች ጋር በአዲስ መልክ ነበር የተካሄደው። ጦርነቱ በኢስላም ታሪክ ውስጥ እንደወሳኝ ድል የሚታይ ሲሆን ለመለኮታዊ እገዛ ጣልቃ ገብነት መለያ ነበር። ወይም ከዓለማዊ ምንጮች አንፃር ለሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐላይሂ ወሰለም) ስትራቴጂያዊ ጉብዝና ትልቅ ማሳያ ነበር። በድር በተለይ በቁርኣን ውስጥ ከተጠቀሱት ጥቂት ጦርነቶች አንዱ ነው። ስለበድር ጦርነት ከፍተኛ ዕውቀት በጊዜው ከነበረው ኢስላማዊ ባህላዊ ዘገባዎች ከሁሉም፣ ከሐዲስና ከነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) የሕይወት ታሪክ፣ ከጦርነቱ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በጽሑፍ መልክ ከተመዘገቡት ይገኛል። ከጦርነቱ ቀደም ብሎ፣ በኋላኛው 623 እና መጀመሪያው 624፣ ሙስሊሞችና መካውያን በርካታ አነስተኛ ግጭቶችን አካሄደዋል። የሙስሊም ግዛት (በነብዩ የተመሩ ዘመቻዎች) በተደጋጋሚ እንደመከሰታቸው መጠን። ሆኖም ግን በድር በበሁለቱም ኃይላት መካከል ታላቅ ተሳትፎ የተደረገበት የመጀመሪያው ነበር። ጠንካራ የመከላከል ቦታ አያያዝ ላይ በሙብለጥ የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏህ ዐለይሂ ወሰለም) ኃይል፣ ያ በመልካም ስነ ምግባር የታነጸው፤ የመካውያን መስመሮች ሰበረ። በርካታ የቁረይሽ ወሳኝ ሰዎችን የተገደሉ ሲሆን ቀንደኛውን የነብዩ ሙሐመድ (ሰለሏሁ ዐለይሂ ወሰለም) ባላንጣ ዓምር እብን ሒሻም ጭምር ተገድሏል። ለቀደምት ሙስሊሞች እነርሱ በመካውያን መካከል ያሉ ጠላቶቻቸውን የኋላ ኋላ እንደሚያሸንፉ ጦርነቱ የመጀመሪያው ምልክት ነበር። መካ በዚያውን ጊዜ ዐረቢያ ውስጥ ካሉ ከተሞች በጣም ሐብታምና ኃያላን ከነበሩ ከተሞች አንዷ ነበረች። ከዚያ የሙስሊሙን

ሦስት እጥፍ የሚበልጥ ሠራዊት አሰማሩ። የሙስሊሞ ድልም ሌላ ኃይል በዐረቢያ መነሳቱን ለሌሎች ጎሳዎች ፍንጭ ሰጥቷል። እንደዚሁም የሙሐመድን (ሰለኋሁ ዐለይሂ ወሰለም) ለነዚህ በመዲና ብዙ ጊዜ ለተበታተነ ማህበረሰብ የመሪነት ቦታን አጠንክሯል የሚል የታሪክ ምስክርነት አስፍሯል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ መጽሐፍ ቅዱስ ስለመካ መከፈትና የሱሐቦች ብዛት አሥር ሺህ እንደ ነበር የሚከተለው ጥቅስ ይነግረናል፡፡

King James Verision since 1798 Page 117 33:2«—The Lord Come From Sina and Rose Up From Seir Unto Them. He Shined Forth From Mount Paran and He Come With Ten Thousands of Saitnts.» ትርጉም፡- ***«እግዚአብሔር ከሲና መጣ፤ በሴይርም መጣላቸው፡፡ ከፋራን ተራራ ተገለጠ፤ ከአሥር ሺህ ቅዱሳንም ጋር መጣ፡፡»*** ክርስቲያኖች እስኪ ከፋራን ተራራ ጋር የተያያዘ የአምልኮ ዘርፍ አለ? በእስልምና ግን የአንድ ሲደመር ወይንም የአንድ ሲቀነስ እንኳ ልዩነት የለውም፡፡!! የእነዚህን የሱሐባዎች ብዛት አሥር ሺህ ነበር፡፡ አላህ (ሱ.ወ) በሚከተለው ምዕራፍ ይነግረናል፡- በሱረቱል ነስር ምዕራፍ 110፡1-2«**የአላህ እርዳታና (መካን) መከፈት በመጣ ጊዜ፤ ሰዎችንም ጭፍሮች (አሥር ሺህ) እየሆኑ፤ በአላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤**» በማለት ቁርኣን እውነታውን ያረጋግጣል፡፡

## የነብያችን «አህመድ» የሚለው ስም መኖሩ

ነብያችን ስማቸው በሚከተለው ምዕራፍና ቁጥር እንዲሁም በሌሎች መጽሐፎች ሰፍሮ ይገኛል። ለመጀመሪያ ጊዜ በታተመው የአራቱም ወንጌሎች አዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ የ1812 እና የ1816 ዕትም በገጽ 40 ላይ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24«***ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- እኔ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም፤ እንዲሁም ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ነኝ።***» በሌሎች መጽሐፍም በሰፊው እንዲህ በማለት ይጠቅሳል፡- «ይት ይትመጽ ምድረ ዓረብ ካዕባ እስሙሁ አህመድ ሙሐመድ አማኑኩም ይባልኩም።» ከዚህ ላይ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከዐረብ ሀገር እንደሚነሱ ስማቸውም አህመድ እንደሆነ በመቀጠልም ሕዝቦች ታማኙ ሙሐመድ እንደሚሏቸው እውነታውን

ያስቀምጣል። እንዲሁም በታምረ ማሪያም መጽሐፍ ላይ በስፋት ስለ እሳቸው ያወራል።

## የዘውትን ጸሎት በሚባለው መጽሐፍ «አላህ አድነነ» በሚል የግዕዝ ጹሑፍ መኖሩ

በክርስቲያኖች መጽሐፍ የዘውትር ጸሎት በሚባለው "አላህ አድነነ" የሚል የግዕዝ ጹሑፍ እናገኛለን። «**አቡነዘ ዘበሰማያት ይትቀደስ ሰምከ፤ ትምጣ መንግስትከ፤ ----** ትንሽ ወረድ ይልና **እግዚአ ተመንሱት አላህ አድነነ**» ይላል። ስለዚህ አላህ የዓለማት አምላክ አዳኝ መሆኑን እኛ ሙስሊሞች እናምናለን።

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት

## ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት መጠቀሳቸው።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የመጨረሻ ነብይና የአላህ መልእክተኛ መሆናቸው በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ተጠቅሰው በግለፅ ይገኛሉ። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 21፡43-44«*ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- "ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን እራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፤ ለዓይኖቻችሁም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ ከመጽሐፍ አላነበባችሁምን"? ስለዚህ እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔር መንግስት ከእናንተ ትወሰዳለች፤ ፍሬዎን ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች። በዚህም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፤ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጫል።*» ይህ ትንቢት ጥሩ ጥቆማ ይሰጣል። ይህ ትንቢት በትክክል የሚያመላክተው የነብይነት ፀጋ ከእስራኤላውያን ወደ እስማኤላውያን እንደሚሰጥ ነው። ግድ የለም፤ ጉዳዩን እስከ ጥግ ድረስ በዝርዝር እንመልከተው። ያ ከእስማኤላውያን ዝርያ የመጣው ለዓለማት እንደ ማዕዘን ድንጋይ የሆነው ማን ነው? ኢየሱስ ነው እንዳይሉ እሱ ለዓለማት እንደማይላክ፡- በማቴዎስ ወንጌል 15፡24«*"ኢየሱስም መልሶ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም አለ"።*» ስለዚህ ኢየሱስ ወደ ዓለም እንደማይላክ እውነታውን ከእራሱ አንደበት የምስክር ቃል አግኝተናል። ታዲያ እነኚህ ምርጥ የዓለማት የማዕዘን ድንጋይ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ካልሆኑ ማን ናቸው? ወይንስ ገና ለወደፊት የሚላክ ነብይ በክርስቲያኖች ይኖር ይሆን? ለማንኛውም ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለዓለም የሚላኩ የመጨረሻው መልእክተኛ የሆኑና የነብያቶች አባት ከሆነው ከአብራሃም ዘር የተገኙ ናቸው። አምላክ በኦሪት.ዘፍጥረት 22፡18 «*"የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረክ"*» በማለት አምላክ ነብዩ አብራሃምን እንደባረካቸውና ዘሮቹን እንደዚሁም ባርኳቸዋል። አብራሃም የመጀመሪያ ልጁን **‹እስማኤልን›** አምላክ ለመሰዋትነት አቅርብ ተብለው አብራሃምም የታዘዙትን ባቀረቡበት ጊዜ ነበር ይህ ቃል ኪዳን የተገባላቸው። ነገር ግን ክርስቲያኖችና አይሁዶች ይህን እውነታ ላለመቀበልና ለመቅበር ሲሉ አብራሃምን ለመሰዋትነት አቅርብ ያላቸው **‹ይስሐቅን›** ነው ብለው አይሁዶች በመጽሐፋቸው ውስጥ አስገቡ። ትዕዛዙ ለይስሐቅ በተባለ ኖሮ "«*አምላክ አንድ ልጅህን አልከለከልህምና*

***በእውነት በረከትን እባርክሃለው***" አምላክ አይልም ነበር። ምክንያቱም ነብዩ አብራሃም በዚህ ጊዜ ሁለት ልጅ ነበራቸውና ይስሐቅና እስማኤል ማለት ነው። አይሁዶች ግን እስማኤል የሕጋዊ ጋብቻ ልጅ ስላልሆነ እስማኤል ተረግሟል ይላሉ። ይልቁንም **‹ለእራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ›** እንደሚባለው የተባረከው የይስሐቅ ዘር የሳራ ዘር እንጂ የእስማኤል ዘር አይደለም በማለት ካላቸው ምቀኝነት የተነሳ ሐቅን ለመደበቅ ይከራከራሉ። ለዚህ ለደበቁት ሐቅ መልሱን በተከታዩ ምዕራፍ እናገኛለን። በኦሪት.ዘፍጥረት 17፡20«***እግዚአብሔር "ስለእስማኤልም ሰምቻለሁ፤ እነሆ ባርኬዋለሁ፤ ፍሬያማ አደርገዋለሁ፤ እጅግም አበዘዋለሁ፤ አሥራ ሁለት አለቆችን ይወልዳል"*** » ይላል። ታደያ ይህ ቃል ኪዳን እርግማን ነውን? ተጨማሪ በኦሪት.ዘዳግም 21፡15-17«***ለአንድ ሰው አንዲቱ የተወደደችና አንዲቱ የተጠላች ሁለት ሚስቶች ቢኖሩት፤ ለእርሱም የተወደደችው፤ ደግሞም የተጠላችው ልጆችን ቢወልዱ፤ በኩሩም ከተጠላችው ሚስት የተወለደው ልጅ ቢሆን፤ ለልጆቹ ከብቱን በሚያወርስበት ቀን ከተጠላቸው ሚስት በተወለደው በበኩሩ ፊት ከተወደደችው ሚስት የተወለደውን ልጅ በኩር ያደርገው ዘንድ አይገባም። ነገር ግን ከከብቱ ሁለት እጥፍ ለእርሱ በመስጠት ከተጠላቸው ሚስት የተወለደው ልጅ በኩር እንደ ሆነ ያስታውቅ። የኃይሉ መጀመሪያ ነውና በኩርነቱ የእርሱ ነው።***» ክርስቲያኖች ሆይ! አብራሃም ያ የተከበረ የአምላክ ነብይ ‹**"ሕገ ወጥ ልጅ"**› ነበረው ብለው የሚከሱት ከሆነ ይህ የአምላክን ነብይና የበርካታ ነብያትን አባት መስደብና ክብሩን ማንቋሸሽ ነው። አምላክም አብራሃምን የሚረግሙትን አይሁዳንና ክርስቲያኖችን ረግሟቸዋል። በኦሪት.ዘፍጥረት 12፡3 «***የሚባርኩህንም እባርካለሁ፤ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፤ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።***» በዚህ መሰረት እኛ ሙስሊሞች በሁሉም ነብያቶች ስለምናምን "ተባረኩ" ናቸው እንላለን እንጂ እንደ ክርስቲያኖችና አይሁዶች "የተረገሙ" ናቸው የሚል እምነት የለንም። አብራሃምን እንደባረከው ሁሉ እስማኤልንም ባርኮታል። ከዚሁ ምዕራፍ 22፡18«***የምድር አሕዛብ ሁሉም በዘርህ ይባረካሉ፤ ቃሌን ሰምታሃልና።***» አምላክ እንደሚባርከውና ዘሩን እንደሚያበዛለት ቃል ገብቶለታል። ስለዚህ የእስማኤል ዘርም ተባርኳል፤ ተባዝቷል። በመሆኑም አረቦች በትውልድ የእስማኤል ልጆች ሲሆኑ እስራኤላውያን ደግሞ የይስሐቅ ዘሮች ናቸው። ሁለታቸውም የአባታቸው የነብዩ አብራሃም ልጆች ናቸው። ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከእስማኤል ዘር የሆኑና የመጨረሻ ነብይ የሆኑት ለሰው ልጅና ለፍጥረታት በሙሉ የተላኩና የነብያቶች መደምደሚያ ናቸው።

ስለእርሳቸውም የመጨረሻ ነብይ መሆናቸውን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተተነበየውን ትንቢት በቅደም ተከተል እንመልከት፦ በትንቢ.ተ.ዕንባቆም 3፡3 «***እግዚአብሔር ከቴማን ቅዱስም ከፋራን ተራራ ይመጣል። ክብሩም ሰማያትን ከድኗል፤ ምስጋናውም ምድርን ሞልቷል***።» ይህ ትንቢት ማን ያመለክታል ተብለው ቢጠየቁ ክርስቲያኖች የሚያቀርቡት መልስ የለም። ምክንያቱም በአንድም ቦታ ላይ የክርስትና ሃይማኖት የአምልኮ ሥርዓት ከፋራን ተራራ ጋር የሚያያይዘው የለም። ከዚህ ላይ የምንገነዘበው እውነታ ቴማን (መዲና) ፋራን ተራራ (መካ) ደግሞ የሚገኘው በዚያ በሚወደድ በነብያችን ሀገር በመካ ነው። በዐረፋ በዓል የዓለም ሙስሊሞች በሙሉ በዚሁ ተራራ ራስ ላይ ሆነው “**አላሁ አክብር፤ አላሁ አክብር**” በማለት የአምላካቸውን የአላህን ስም በሚያጠሩ በውዳሴና በጸሎት ይገልፃሉ። ከዚያም በኋላ “**አልሐምዱሊላህ**” ምስጋና ለዓለማቱ ጌታ ይሁን በማለት ለአላህ ምስጋና ያሰማሉ። በዚህ ትንቢት ከፋራን ተራራ እግዚአብሔር ይመጣል ሲል፦ የነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ነብይነት ከመካ ምድር እንደሚነሱ በማያጠራጥር መልኩ ይጠቁማል። ነብዩ እስማኤልም በዚህ ቦታ ላይ የሐጅና ዑምራ የአምልኮ ሥርዓቶችን መፈፀማቸውንም ይነግረናል። አሁንም ተጨማሪ ማስረጃ በኦሪት.ዘፍጥረት 21፡21«***“እስማኤል በምድረ በዳ ተቀመጠ፤ ቀስተኛም ሆነ፤ በፋራን ምድረ በዳ ተቀመጠ”***» ይለናል። ስለዚህ ቴማን መዲና ማለት ሲሆን ፋራን ተራራ የሚገኘው በመካ ከተማ ነው። ሙስሊሞች በዚህ መልኩ ትንቢቱን ከፈቱት፤ ክርስቲያኖች በምን ሊፈቱት ነው? ነው ትንቢቱ በከንቱ ነው የተተነበየው? በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 21፡7«***“በግመሎች የሚቀመጡትን ባየ ጊዜ በፅኑ ትጋት አስታውሎ ተግቶም ያደምጥ”***» ይላል። በግመል የተቀመጡት ነብይ ማን ናቸው? ኢየሱስ እንደሆነ በአህያ ውርጫ ነው የተቀመጠው። ስለዚህ በግመል የተቀመጡ ነብዩ ሙሐመድና ተከታዮቻቸው ነው። አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 42፡1-8«***እነሆ ድግፌ የያዝሁት ባሪያዬ፤ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ምርጤ፤ በእርሱ ላይ መንፈሴን አደርጋለሁ፤ እርሱም ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል። አይጮኽም፤ ቃሉንም አያነሳም፤ ድምጹንም በሜዳ አያሰማም። የተቀጠቀጠ ሸንበቆን አይሰበርም፤ የሚጤሰንም ክር አያጠፋም፤ በእውነት ፍርድን ያወጣል። በምድር ፍርድን እስኪያደርስ ድረስ ይበራል እንጂ አይጠፋም፤ አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ። ሰመያትን የፈጠረ የዘረጋቸውም፤ ምድርንና በውስጥዋ ያለውን ያፀና፤ በእርስዋ ላይ ለሚኖሩ እስትንፋስን የሚሰጥ፤ ለሚሔዱባትም መንፈስን የሚሰጥ አምላክ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ እኔ እግዚአብሔር በፅድቅ***

ጠርቸሃለሁ፤ እጅህንም እይዝሃለሁ፤ እጠብቅሃለሁ፤ የዕውሩንም ዓይን ትከፍት ዘንድ፤ የተዘጋውንም ከግዞት ቤት፤ በጨለማም የተቀመጡትን የተቀመጠትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ ለሕዝብ ቃል ኪዳን ለአሕዛብም ብርሃን አድርጌ እሰጥሃለሁ።» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥8-9«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜም ይህ ነው ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬን ለተቀረጹ ምስሎች አልሰጥም። እነሆ የቀደሞው ነገር ተፈፀመ፤ አዲስ ነገርንም እናገራለሁ። አስቀድሞም ሳይበቅል እርሱን አስታውቃኋለሁ።» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥10-11 «ወደ ባህርም የምተወርዱ በእርስዋም ውስጥ ያላችሁ ሁሉ ደሴቶችና በእነርሱም ላይ የምትኖሩ ሆይ! ለእግዚአብሔር አዲስ መዝሙር ከምድርም ዳርቻ ምስጋናውንም ዘምሩ። ምድረ በዳውና ከተሞቹ የቄዳርም ሰዎች የሚቀመጡባቸው መንደሮች ድምፃቸውን ያንሱ፤ በሌላ የሚኖሩ እልል ይበሉ። በተራሮችም ራስ ላይ ሆነው ይጨኹ።» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥12-13 «ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ። ምስጋናውንም በደሴቶች ይናገሩ፤ እግዚአብሔር እንደ ኃይል ይመጣል። እንደ ሰልፈኞችን ቅንዓትን ያስነሳል፤ ይጮኻል ድምጹንም ያሰማል፤ በጠላቶቹም ላይ ይበረታል።» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥16-17«ዕውሮቹንም በማያውቋት መንገድ አመጣቸዋለሁ፤ በማያውቋት ጎዳና እመራቸዋለሁ፤ በፊታቸውም ጨለማን ብርሃን አደርጋለሁ። ጠማማውንም አቀናለሁ፤ ይህን አደርግላቸዋለሁ አልተዋቸውም። በተቀረጹትም ምስሎች የሚታመኑ ቀልጠው የተሰሩትንም ምስሎች አምላኮቻችን ናቸው የሚሉ ወደኋላቸው ይመለሳሉ ፈፅመውም ያፍራሉ።» ከዚሁ ምዕራፍ 42፥18-19 «እንናንተ ደንቆሮዎች ስሙ፤ እናንትም ዕውሮች ታዩ ዘንድ ተመልከቱ። ከባሪያዬ በስተቀር እውር የሆነ ማን ነው? እንደፍፁም ወይንስ እንደ እግዚአብሔር ባሪያ ዕውር የሆነ ማን ነው?።» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 42፥20-22«ብዙ ነገር ታያላችሁ፤ ነገር ግን አትጠባበቁትም፤ ጆሮአችሁ ተከፍቶአል። እግዚአብሔር ስለጽድቁ ሕጉን ታላቅ ያደርግና ያከብር ዘንድ ወደደ።» በ1879 ዕትም በኦሪት.ዘፍጥረት 49፥10 «ሴሎ የሠላም ንጉሥ እስኪ መጣ ድረስ፤ ለእርሱም የአሕዛብ መታዘዝ ይሆናል» ይላል፡፡ ሴሎሃ ማለት የአላህ መልእተኛ ማለት ነው፡፡ ታዲያ ያ የሰላም ንጉስ ሴሎ ይህ ሕዝብ አልታዘዘውምን? እስካሁን ያየናቸውን ምዕራፍና ቁጥሮች ክርስቲያኖች ለኢየሱስ ነው ብለው ያምናሉ። አንድ በአንድ ለማን እንደሆነ በስንጠረዥ በመዘርዘር የምናያቸው ይሆናል።

| በትንቢ.ኢሳይያስ 42፡ 1- | ነቢዩ ሙሐመድ (ሰላለሁ ዓለይሂ ወሰለም) | ነቢዩ ዒሳ (ኢየሱስ) (ዐለሂ ሰላም) |
|---|---|---|
| ***‹‹ባሪያዬ››*** | ይህ ቃል ከአምስቱ የእስልምና ሃይማኖት መሰረቶች አንዱን ያሟላል። ለምሳሌ፡- ከአላህ ሌላ አምላክ የለም። ሙሐመድም (ሰ.ዐ.ወ) የአላህ መልክተኛ እና ባሪያው ናቸው በማለት እንመሰክራለን እናምናለንም። | “**ባሪያዬ**” የሚለው ቃል ደግሞ አሁን ክርስቲያኖቹ ከሚያመለክቱት ኢየሱስ ጋር በፍፁም አይጣጣምም። ምክንያቱም በክርስቲያኖች እምነት ኢየሱስ ጌታ፣ ስላሴና የእግዚአብሔር ልጅ ነውና ኢየሱስን ጌታ ነው እንጂ ባሪያ ነው አይሉም። |
| 42፡4‹‹***ለአሕዛብ ፍርድን ያወጣል፤***›› | ይህ ሐረግ እስልምና በትክክል ለዓለም ሁሉ የተመረጠ ሃይማኖት በመሆኑና እንዲሁም ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ለሰው ዘር በሙሉ የተላኩ ስለሆነ ይመለከታቸዋል። ይህም በቁርአን ውስጥ በግልፅ ተቀምጧል፡ ‹‹**አንተም ለሰዎች ሁሉ በመላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢኾን እንጅ አልላክንህም፤ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁምም።**›› 34፡28 | ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24‹‹***እኔ ለእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም***›› ብሏል። ለሐዋሪያቶቹም አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 10፡5-6‹‹***ወደ ሕዛብ መንገድ አትሂዱ፤***›› ካለ እንዴት እና መቼ ነው ለአሕዛብ ፍርድን የሚያወጣው? ኢየሱስ ለአሕዛብ ፍርድን አላወጣም፤ እራሱ አውጥቻለሁ አላለም። |
| ***‹‹በምድርም ፍርድን እስኪያደርግ ድረስ*** | በ23 ዓመታት ውስጥ በምድር ላይ ሰማያዊውን ሕግ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚዊ፣ | 1ኛ. ኢየሱስ በምድር ላይ ምህርታቸውን አልጨረሱም። ምክንያቱም በምድር ላይ |

| | | |
|---|---|---|
| ***ይበራል እንጅ አይጠፋም።»*** | ፖለቲካዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሕገ መንግስታዊ እና ወታደራዊ ደንቦችን ያሟላ ቋሚና ዘላለማዊ የሆነ ቁርአንን ለዓለም ያስተ ማሩትና እና በተግባር ያሳዩት ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ብቻ ናቸው። ይህም መመሪያ ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ ሳይጨመርበት እና ሳይቀነስበት እየተሰራበት ነው። | ፍርድን የሚያደርግ ከሳቸው በኋላ የሚመጣ አፅናኝ እንጂ ይህ ድርሻ እርሳቸውን አይመለከትም። 2ኛ. በዮሐንስ ወንጌል 16፥ 8«***እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል***» ይላል። 3ኛ. ኢየሱስ ግን በዮሐንስ ወንጌል 12፥47«***ዓለምን ላድን እንጅ በዓለም ላይ ልፈርድ አልመጣሁም***» ብሏል። |
| «***አሕዛብም በስሙ ይታመናሉ፤***» | በትክክል በሁሉም ዓለም የሚኖሩት ሙስሊሞች በሙሉ የአላህን አንድነት ከመሰከሩ በኋላ ቀጥሎ የሙሐመድን (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ነብይነት መመስከር አለባቸው። ይህንን ካልተቀበሉ ግን እስልምናን እንዳልተቀበሉ ይቆጠራል። የመጀመሪያው የእስልምና ግዴታ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም፤ ሙሐመድም (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) የአላህ ባርያና መልእክተኛ ነው በማለት መመስከር ነው። | በድጋሚ ለማስመዝገብ ያክል ኢየሱስ አሕዛብ በሙሉ በስሜ ያምናሉ ብለው አላስተማሩም። ይልቁንም«***እኔ ከእስራኤል ቤትለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም***» ብሏዋል። በማቴዎስ ወንጌል 15፥24 በሌላም ደግሞ በሉቃስ ወንጌል 1፡32 ላይ የተጠቀሰውን ስንመልከት«***የልዑል ልጅም ይባላል፤ ጌታ አምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብ ቤትም ላይ ይነግሳል***» ይላል እንጂ በአሕዛብ ላይ ይነግሳል አላለም። |

| | | |
|---|---|---|
| | አላህ (ሱ.ወ) የነብዩ ሙሐመድን (ሰ.ዓ.ወ) እጅ እንደጠበቃቸው በቁርኣን 22፡15 ላይ እንመልከት፡፡ «**(አላህ መልክተኛውን) በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም አይረዳውም ብሎ የሚያስብ ሰው ገመዱን ወደ ሰማይ ይዘርጋ፤ ከዚያም (ትንፋሹ እስኪቆረጥ) ይታነቅ ተንኮሉ የሚያስቆጨውን ነገር ያስወግድለት እንደሆነም ይመልከት**» ይላል፡፡ በተጨባጭ ያለፈውን ታሪክ ስንመለከት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ተቃዋሚዎች ነቢዩን ለመግደል ቢታገሉም እንዳልተሳካላቸው እንረዳለን፡፡ | እዚህ ላይ እጅን ይዞ ኢየሱስን የጠበቀ ቢሆን ኖሮ ለምንስ አይሁዶች ኢየሱስን በመስቀል ቸነከሩት? በክርስቲያኖች እምነት ኢየሱስ ከተገረፈ፣ ከተሰቀለ፣ሞቶም፣ ከተቀበረ፣ እጅህንም እይዛለሁ እጠብቅህ ማለሁ በተባለው መሠረት ስላልተጠበቀ ትንቢቱ ኢየሱስን አይመለከትም፡፡ ይህ አባባል ግን የኢየሱስን ሞትና ትንሳኤን ማፅደቅ አይደለም፡፡ ሙስሊሞቹ ይህ ሁሉ ድራማ በኢየሱስ ላይ እንዳልተፈጸመ ፅኑ እምነት አላቸው፡፡ ሌላ ሰው ነው የተሰቀለው፡፡ |
| ***«በጨለማ የተቀመጡትን ከወህኒ ቤት ታወጣ ዘንድ፤»*** | የእስልምና ሃይማኖት የመጀመሪያ እርምጃው ባሪያዎችን ነፃ ማውጣት ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ ነቢዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በተላኩበት ዘመን ሙሽሪኮች (አጋሪዎች) ባርያ ገዝተው እንደግል እቃቸው ይጠቀሙበት ነበር፡፡ ይህ ግፍና ጉዳይ እልባት ያገኝ ዘንድ ነብዩ አጥብቀው ይዋጉ ነበር፡፡ | ኢየሱስ ክርስቶስ ተላኩበት ጊዜ እስራኤላውያን ባርነት ስር ነበሩ፡፡ ልክ ኢየሱስ ሲመጡ ከአይሁዶች ጥያቄ ቀረበላቸው፡፡ ከአባቶቻችን እንደሰማነው ከዚህ ባርነት እስራኤልን ነፃ የሚያወጣው ይመጣል ስለተባለ አይሁዶች ከፍተኛ ጉጉት አደረባቸው፡፡ ኢየሱስ ግን መንግስቴ ከዚህ አይደለችም አለ፡፡ በዚህን ጊዜ |

| | | |
|---|---|---|
| | አንድን ባሪያ ነፃ ማውጣት ከመልካም ስራዎች ሁሉ የላቀ መሆኑን ለተከታዮቻቸው አስተምረዋል። | አይሁዶች ኢየሱስን ለማስዋሸት ብዙ ችግሮችን በእርሱ ሱ ላይ ለመፍጠር ሞክረዋል። ምክንያቱም እነሱ ከምድራዊ ባርነት ነፃ ለመውጣት ነበር። ኢየሱስ ግን እስራኤልን ወደ ፈጣሪ ለመመለስ ስለሆነ እሰራኤላውያን መልእክቱን ባለመቀበል ኢየሱስን ለመግደል ይከታተሉ ነበር። |
| 42፡8-9<br>*«እኔ እግዚአብሔር ነኝ፤ ስሜ ይህ ነው፤* | ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በማለት የአላህን ስም በመጥራት አስተምረዋል። “**ስሜ ይህ ነው**” የሚለውን ካድ ማስጠንቀቂያ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ. ወሰለም) እስከተላኩበት ድረስ ዓለም በሙሉ ዘንግተውት ነበር። ነገር ግን ትንቢቱ በትክክል የተፈፀመው በመጨረሻው ነብይ አማካይነት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። | ኢየሱስም ይህንን ነበር ያስተማረው። ነገር ግን ዛሬ የአለም ክርስቲያኖች “ኢየሱስ ጌታ ነው” የሚሉ ስለሆነ ይህንን ስህተት ለማረም ያህል ለሰው ልጅ<br>አስቀድሞ “ስሜ ይህ ነው” ማለቱ ያሳያል። አሁን እየተፈፀመ ያለው ከፍተኛ ስህተት ከኢየሱስ (ዓላይሂ ሰላም) እርገት በኋላ ስምህ እግዚአብሔር አይደለም “ሥላሴ ነው እንጂ” እያልን የፈጣሪውን ስም የምንቃወም ይመስላል። |
| *«ክብሬን ለሌላ ምስጋናዬን ለተቀረጹ* | ነብዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ከተላኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ትንሳዔ ቀን ድረስ “**አላሁ** | በአሁኑ ወቅት ክርስቲያኖች በተለይም ፕሮቴስታንቶች የእግዚአብሔርን |

| | | |
|---|---|---|
| ***ምስሎች አልሰጥም።»*** | **አክብር**” እየተባለ ነው ሰላት የሚሰገደው። የተቀረጹት ምስሎች ደግሞ በእስልምና ሃይማኖት በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው። ምስጋናውም የሚገባው ለዓለማት ጌታ ለአላህ ነው እንጅ ለሌላ አይደለም። “**አልሐምዱሊላህ**” ምክንያቱም በዚህ ትንቢት ውስጥ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ሁሉ የሚያሟሉት ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ብቻ ናቸው። | ክብር በፍፁም ሲናገሩ አይታዩም። ከጥቂት ጊዜ በኋላ እግዚያብሔር የሚለውን ቃል እንኳ ከጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዳያጠፉት ያሰጋል። “ክብር ለኢየሱስ” ኢየሱስ የተመሰገነ ይሁን” የሚሉ የተሳሳቱና ከዚህ ትንቢት ጋር የሚቃረኑ አምልኮዎች አሉ። የማርያምንና የኢየሱስን ምስል ለአምልኮ የሚቀርጹ የኢየሱስ ተከታዮች አይደሉንም? ስለዚህ ትንቢቱ ኢየሱስን አይመለከትም። |
| 42፡10-11 «***ለእግዚአብሔር አዲስ መዝሙር ከምድርም ዳርቻ ምስጋናውንም ዘምሩ።»*** | አዲስ መዝሙር ማለት ይህ የአላህ ባሪያ በሚላክበት ጊዜ ምስጋናውንም ሆነ ዝማሬውን በፊት ከነበረው በተለዬ ሁኔታ የቀደምት እስራኤል ነብያት ከሚዘምሩት የተለየ ነው። ምክንያቱም በአምልኮ ጊዜ የሚዘመረው ዝማሬ ሁሉ አለም ዓቀፋዊና በአረበኛ ቋንቋ የሚደረግ ነው። | ነብዩ ዒሳ (ዓለይሂ ሰላም) የተላኩት ለእስራኤል ወገን በመሆኑ የተለየ መዝሙር አላስተማሩም። በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት መካከል በአሁኑ ጊዜ ይህ የመዝሙር አዘማመር ከፍተኛ ልዩነት ጎልቶ ይስታዋላል። |
| ***የቄዳር ሰዎች የሚቀመጡባቸው*** | የአላህ ባርያ በሚላኩበት ጊዜ የቄዳር ሰዎች ተቃውሞ እንደፈሚያነሱ አላህ ስለሚውቅ | ይህ አባባል ነብዩ ዒሳን (ዓለሂ ሰላም) የሚመለከት አለመሆኑን በቀላሉ ለመገንዘብ |

| | | |
|---|---|---|
| ***መንደሮች ድምፃቸውን ያንሱ በሴላ የሚኖሩ እልል ይበሉ። በተራሮችም ራስ ላይ ሆነው ጩኹ"።›› *** | ድምፃቸውን እንዲያነሱ አስጠንቁሿል። በሴላ የሚኖሩ ደግሞ በእልልታ ይህንን ባርያ እንዲቀበሉ አስቀድሞ አዟል። በሰፉዋና መራዋ ተራሮች ራስ ላይ ሙስሊሙ ህብረተሰብ በትንቢቱ በታዘዘው መሠረት አላህን እየተገዛ ይገኛል። ተራሮችም የሚገኙት በመካ ነው። | እርሳቸው በመካና መዲና ትምህርታቸውን አላስተማሩም። በእግራቸውም እዚያ አልረገጡም። ቄዳር (መካ) ቴማን (መዲና) ማለት ነው። አንድ ብርቱ ጥያቄ አለ። ይኸውም በቄዳርና በሴላ የሚኖሩት ዛሬ በተራሮች ራስ ላይ ሆነው ወደ ፈጣሪያቸው የሚጮሁት እንደተባለው "ኢየሱስ ጌታ ነው" በማለት ነው ወይንስ የአላህ ባርያ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ባመጡት መመሪያ ነው? ስለዚህ የትንቢቱን በመካ መፈፀም ጉዳይ ግልፅ መሆኑን ማጤን ግድ ነው። |
| 42፡12-13‹‹***በጠላቶቹም ላይ ይበረታል፤››*** | ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በተላኩ ማግስት በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ጠላቶች ነብዩን ለመግደልና እስልምናን ለማጥፋት ሞክረዋል። ዳሩ ግን ለአንዴ እንኳን ወደ ኋላ ሳይመለሱ ተጋፈጧቸው። በአጭር ጊዜ ውስጥ ድል አድርገው ለቀው የወጡትን የመካን ከተማ ለመቆጣጠር ችለዋል። | ዒሣ ጠላቶቻቸው ላይ አልበረቱም። እንዲያም ጠላቶቻችሁን እንደራሳችሁ ውደዱ እያሉ ነበር ያስተማረው። ለዚህም "ቀኝህን ሲመቱህ ግራህን ስጥ" የሚለውን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበቡ ይበቃል። |

| | | |
|---|---|---|
| 42፡16-17«***በተቀረጹትም ምስሎች የሚታመኑ ቀልጠው የተሰሩትንም ምስሎች አምላኮቻችን ናቸው የሚሉ ወደኋላቸው ይመለሳሉ፤ ፈፅመውም ያፍራሉ።***» | ነቢዩ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) እንደ ሚከተለው አስተምረዋል "**ማንኛንም ምስል የሚሰራሰው በመጨረሻ ቀን ነፍስ እስኪሰራበት ድረስ በአላህ ይቀጣል። ነገር ግን ነፍሱን ሊዘራበት በጭራሽ አይችልም** " ስለዚህ ይህ የአላህ ባርያ ከተላኩ ወዲያ የተሰሩትን ምስሎች የሚያመልኩ ወደኋላቸው ይመለሳሉ የሚለው በእስልምና ተግባራዊ ይሆናል። | በክርስትና ሃይማኖት ግን ምስሎቹን መቅረጽ ክልክል አይደለም። በ7ኛ.ጉባዔ የኒቂያ 2ኛ ጉባዔ የደነገገውን እንመልከት። እ.ኤ.አ በ787 ዓ.ም ጳጳስ እድሪያኑስ 1ኛ አቡናት 300 ውሳኔ ፡- የቅዱሳን ምስሎችና ስዕሎች አክብሮት ክርስቲያናዊ እንጅ አረማ አይደለም ብለው ገለጹ። ዘላለማዊይ የሕይወት መንገድ ከሚለው መጽሐፍ የተወሰደ። |
| «***ከባሪያ በቀር ዕውር ማን ነው? እንደምልከው መልእክተኛዬስ ደንቆሮ የሆነ ማን ነው?***» | ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ማንበብና መፃፍ ስለማይችሉ እውርና ደንቆሮ የተባለውን በዚህ ምክንያት ነው። «**ከርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትጽፈው አልነበርክም፤ ያን ጊዜ አጥፊዎቹ በተጠራጠሩ ነበር።**» በሱረቱል አል-አንከቡት 29፡48 | ነቢዩ ዒሣ (ዓለሂ ሰላም) እንደተባለው እውርና ደንቆሮ አይደለም። ለምሣሌ ያክል በሉቃስ ወንጌል 2፡52ን እንመልከት «***ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።***» ኢየሱስ ጌታ ሆኖ ሳለ እንዴትስ ደንቆሮ ይሆናል? ይልቅስ "ኢየሱስ ሊቅ ነው እኮ!" |

| | | |
|---|---|---|
| 42፥20-22 «***እግዚአብሔር ስለ ጽድቁ ሕጉን ታላቅ ያደርግና ያከብር ዘንድ ወደደ።***» | ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ደግፎ የያዘውን ባሪያውን ከቋሚ የሃይማኖት መመሪያ ወይንም የሕጎች ሁሉ የበላይ ሕግ በሆነው ቁርኣን የላከው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ይህም ሕግ ታላቅ ከመሆኑም በላይ የዓለም ሙስሊሞች በሙሉ ይዳኙበ ታል። በእስልምና ሃይማኖት ሕግ ከፍተኛ ትኩረትና ጥበቃ ተደርጎለታል። «**እርሱ ያ (አላህ) አጋሪዎች ቢጠሉም መልክተኛን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከው ነው።**፡9፥33 | በክርስትና ሃይማኖት መሰረት ኢየሱስ ከተላከበት ጊዜ ጀምሮ ሕግ ተሸሯል የሚል ነው። ጽድቅ የሚገኘው በእምነት እንጅ ሕግን በማክበር አይደለም ይላሉ። ወደ ዕብራዊያን ሰዎች 7፥18፥19«***ሕጉ ምንም ፍፁም አላደረገምና ስለዚህ የምታደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሸራለች።***» ስለሆነም ከዚህ በላይ ያየነው የመጽሐፍ ቅዱስ መመሳሰል በሙሉ ከኢየሱስ ጋር ሳይሆን ከነብዩ ሙሐመድ ጋር መሆኑ ሀቅን ለማወቅና ለመቀበል ያለንን ዕድል እንጠቀምበት። |

# ሙሴን የሚመስለው ነብይ ማን ነው? ኢየሱስ? ወይንስ ሙሐመድ?

በኦሪት.ዘዳግም 18፡18‹‹***ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ፤ቃሌንም በአፉ ሊደርጋለሁ፤ ያዘዝኩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል፤ በስሜም የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ፡፡***›› ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች እውነትን መደበቅ የተለመደ ባሕሪያቸው ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሰውን ምዕራፍ ለነብዩ ሙሐመድ አይደለም ብለው ይከራከራሉ፡፡ ጉዳዩ "‹**የሌባ አይነ ደረቅ ባለቤቱን አይፈራም**›" ነው ነገሩ፡፡ እስኪ ሙሴ ኢየሱስን ይመስላል? ኢየሱስ እናት እንጂ አባት አልነበረውም፡፡ ሙሴ ግን እናትና አባት ነበረው፤ እንደ ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፡፡ ታዲያ ይህ ብቻ ከንቱ ክርክራቸውን ውድቅ አያደርገውምን? የሚገርመው ክርስቲያኖች ኢየሱስን አምላክ ብለው ይከራከራሉ እንጂ ነብይ ብለው አያምኑም፡፡ ጥቅሱ የሚለው ‹‹***እንደ አንተ ያለ ነብይ***›› ነው የሚለው፡፡ ታዲያ ለምንድን ነው ኢየሱስን አምላክ ነው የምትሉት? ሙሴ ነብይ ነው አይደል? አዎ ከሆነ መልሳችሁ ታዲያ ለኢየሱስ ነው ብላችሁ የምትከራሩ ከሆሱስም እንደ ሙሴ ነብይ መሆን አለበት፡፡ ለምን ብትሉ በጥቅሱ መሰረት "እንደ አንተ ያለ ነብይ" ስለሚል ማለት ነው፡፡ በኒው ኢንተርናሽናል ቨርዥን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ደግሞ በኦሪት.ዘዳግም 18፡18 ከላይ በርዕሱ የምናገኘው ጹሑፍ "‹ሙሴን የሚመስለው ነብይ›" ይላል፡፡ በመቀጠልም ከዚሁ ምዕራፍ 34፡10 ‹‹***እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነብይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሳም***›› ይላል፡፡ ስለዚህ ለኢየሱስ ነው የሚለውን የመከራከሪያ አጀንዳ ከዚህ ዘንድ ውድቅ ያደርገዋል፡፡ ምክንያቱም ሙሴ ኢየሱስን በምንም መልኩ እንደማይመስልና ትንቢቱም ለኢየሱስ እንዳልሆነ ይህ ጥቅስ ያመለክታል፡፡ ለማንኛው ተንቢቱን በመዘርዘር እንመለከተው፡፡

1ኛ ***በስሜ የሚናገረው፤*** የሚለው ‹‹**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩኅሩኅ እጅግ በጣም አዛኝ በሆነው**›› በማለት ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቁርአንን ያነቡ ነበር፡፡ እንዲሁም ማንኛውንም ነገር ሲጀምሩ "በአላህ ስም" በማለት ነበር፡፡

2ኛ ***ቃሌን በአፉ ሊደርጋለሁ፤*** እነኚህ የተከበሩና የተወደዱ የዓለማት ነብይ ከመላካቸው በፊት የሚጽፉና የሚያነቡ አልነበረም፡፡ ለዚህም በትንቢ.ተ.ኢሳይያስ 29፡11-12 ላይ ይመልከቱ፡፡ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ማንበብና መፃፍ

ስለማይችሉ በቃላቸው ብቻ "በል" እየተባሉ በመላአኩ (ገብሪኤል) አማካኝነት በአፋቸው ላይ ቃል በቃል ተደርጓል።

3ኛ ***በስሜ የሚናገረውን ቃሌን የማይሰሙትን እኔ እበቀልሊታለሁ።*** ይህ ትንቢትም ተግባራዊ ሆኗል። በብዙ ሺዎችን የሚቆጠሩ የጣዖት አምላኪዎች እስልምናን ለማጥፋት ያልሞከሩትና ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። በእየ ጊዜው እንቅልፍ የማይዛቸው ነብዩንና እስልምናን ለማጥፋት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም አላህ የዓለማት ጌታ የሆነው በነዚህ የብያችንና የእስልምና ጠላቶችን ድባቅ መቷቸዋል። በሚደርጉት ተንኮልም አላህ ተበቅሏቸዋል።

## ለማጠቃለል ያክልና ለውሳኔ ያደርሰን ዘንድ

ከላይ የተመለከትነው በብሉይ ኪዳን በኦሪት.ዘዳግም 18፡18 የተጠቀሰውን «***ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነብይ አስነሳላቸዋለሁ***» ተብሎ የተተነበየውን አይሁዶች ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀውን ነብይ ይጠባበቁ ነበርና ወደ መጥምቁ ዮሐንስ ማንነቱን ለማወቅ በፈለጉ ጊዜ "ነብዩ" ነህን በማለት ጠይቀውታል። መጥመቁ ዮሐንስም አይደለሁም በማለት መልሷል። የሰጠውንም መልስ በቀጥታ ምዕራፍና ቁጥሩን በመጥቀስ በአዲስ ኪዳን እንከታተል። የ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 1፡19-21«***አይሁዳውያን ባለስልጣኖች ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን ወደ ዩሐንስ ልከው "አንተ ማን ነህ"? ብለው ባስጠየቁት ጊዜ ዮሐንስ "እኔ መሲሕ አይደለሁም" ሲል መሰከረ እንጂ አልካደም። እነርሱም "ታዲያ አንተ ማን ነህ ኤሊያስ ነህን"? ሲሉ ጠየቁት። እርሱም "አይደለሁም" ሲል መለሰላቸው። እነርሱም "ይመጣል የተባለው ነብይ ነህን" አሉት። እርሱም "አይደለሁም "አለ።***» ከዚህ ላይ አይሁዶች በብሉይ ኪዳን የነብያችን ሙሐመድ እንደሚመጡ ስለሚያውቁና ሲጠባበቁ ስለነበር ነው በአዲስ ኪዳንም መጥምቁ ዮሐንስን ነብዩ ነህን ብለው የጠየቁት። በመቀጠል መጥምቁ ዩሐንስ ኤሊያስ አይደለሁም አለ እንጂ መች ነብዩ አይደለሁም አላለም እንዳትሉን ይመጣል የተባለው ነብይ ነህን ተብሎም ሲጠየቅ እርሱም መልሶ አይደለሁም በማለት መልሷል። ኢየሱስም የኤሊያስን መምጣት በማቴዎስ ወንጌል 11፡14«***ይመጣ ዘንድ ያለው ኤሊያስ ይህ ነው።***» ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 17፡12«***ኤሊያስ ከዚህ በፊት መጣ።***» አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 17፡12«***ስለ መጥምቁ ዮሐንስ እንደነገራቸው አስተዋሉ።***»

ከዚህ ላይ መጥምቁ ዮሐንስ፣ ኤሊያስና ኢየሱስ መጥተዋል። ስለዚህ ለወደፊት ይመጣል ተብሎ የሚጠበቀው ነብይ ነብያችን ሙሐመድ ናቸው። እሳቸው ግን መጥተዋል ክርስቲያኖችና አይሁዶች ባያምኑባቸውም። ኢየሱስ በአዲስ ኪዳንንም ነብያችን እንደሚመጡ በሚከተሉት ምዕራፍ እውነታውን አስቀምጧል። በዮሐንስ ወንጌል 16፡5-8«***ከእናንተ ጋር ስለ ነበርኩ መጀመሪያ ይህንን አልነገርኳችሁም። አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ፤ ከእናንተም ወዴት ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም። ነገር ግን ይህንን ስለ ነገርኳችሁ ሐዘን በልባችሁ ሞልቷል፤ እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ ብሄድ ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አፅናኙ ወደ እናንተ አይመጣምና፤ እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል***።» ይህ ትንቢት በቀጥታ ነብያችን ሙሐመድን ብቻ ነው የሚመለከተው። ክርስቲያኖች ብዙ ጊዜ ይህን ትንቢት ለኢየሱስ ነው ብለው በድርቅና ይከራከራሉ። ነገር ግን ኢየሱስ ነው ይህን ትንቢት ለወደፊት ስለሚመጠው ነብይ የተናገረው። ለኢየሱስ ቢሆን ኖሮ በብሉይ ኪዳን ነበር ሌላ ነብይ ስለኢየሱስ መምጣት መናገርና መተንበይ የነበረበት። ነገር ግን ይህን ትንቢት የተነበየውና የተናገረው ራሱ ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን ነው። ታዲያ እንዴት ትንቢቱ ለኢየሱስ ነው የሚባለው? በመቀጠል ያ የሚመጣው ነብይ ስለኃጢአት ስለጽድቅም ስለፍርድም አለምን ይወቅሳል። ኢየሱስ እንደሆነ ለዓለም እንዳልተላከ በማቴዎስ ወንጌል 15፡24«***እኔ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላኩም***» ብሏል። ታዲያ እንዴት ትንቢቱ ለኢየሱስ ነው ይባላል? ነገሩ ነጭን ጥቁር እንደ ማለት አይሆንምን? ስለዚህ ለአለም የተላኩና የመጨረሻው ነብይና ስለ ጽድቅ ስለኃጢአት ስለፍርድም ዓለምን በሙሉ የወቀሱ እነኚህ ነብይ ናቸው። አሁንም ደግሞ ለመንፈስ ቅዱስ ነው በለው አያ ሙግት አይታክቴዎች ይከራከራሉ። በአጭሩ መንፈስ ቅዱስ ስለጽድቅ ስለኃጢአት ስለፍርድም ዓለምን ሲወቅስ አልታየም። ይህን የውሸት የመከራከሪያ አጀንዳ ውድቅ የሚያደርገው የአዲስ ኪዳን ጥቅስ አለ። ይኸውም በማቴዎስ ወንጌል 3፡16«***ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃው እንደወጣ ሰማይ ተከፈተ፤የእግዚአብሔርም መንፈስ በእርግብ አምሳል ወርዶ በኢየሱስ ላይ ሲያርፍ አየ***» ይለናል። ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ጊዜ ነው የወረደው እንጂ ለወደፊት እንደሚመጣ አይደለም የሚያሳየው ጥቅሱ። ተጨማሪ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ እንዳደገም ይናገራል። ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 16፡12-14 «***የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፤ ነገር ግን አሁን ልትሸከሙት አትችሉም። ግን***

***እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከእራሱ አይናገርምና፤ የሚመጣውንም ይነገራችኋል። እርሱ ያከብረኛል፤ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና***።» አሁንም ይህን ጥቅስ ለመንፈስ ቅዱስ ነው ብለው የክርስቲያን አስተማሪዎች ያስተምራሉ። ሆኖም ግን ይህን ትርጉም መና የሚያስቀረው አንቀጽ አለ። ይኸውም "***የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከእራሱ አይናገርምና***" ይላል። በክርስትና አስተምሮ መንፈስ ቅዱስ ከሦስቱ አምላክ አንዱ ነው ይላሉ። ሦስቱ አምላክም፡- "አብ፣ ወልድና መንፈስ ቅዱስ በአንድነት፣ በስልጣን ዓለምን በመፍጠር፤ በአጠቃይ ዓለማትን በማስተዳደር እኩል ናቸው" ይላሉ። በሦስቱም አምላኮች በስልጣን አንዱ በአንዱ የበላይነት የለም ብለው የሚያምኑ ከሆነ ለሚከተለው ጥያቄ መልስ ያስፈልገዋል። እርሱም፡- "***የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከእራሱ አይናገርም***" ይላል። ታዲያ መንፈስ ቅዱስ የሦስቱ ስላሴ አካል የሆነው "***ከእራሱ መናገር የማይችል ከሆን ገና የሚሰማውን ብቻ የሚናገር***" ከሆነ እኩልነታቸው ምኑ ላይ ነው? ሲቀጥል የሦስቱ አምላኮች የስላሴ አካል የሆነውን መንፈስ ቅዱስ ዕውቀቱንና ስልጣኑን አዘቅት ውስጥ መክተት አይሆንምን? እንዲሁም ይህ የሚሆን ከሆነ ስላሴን በመደምሰስ የክርስትና እምነትን መጨረሻ የለለው ውድቀት ውስጥ ይከታል ማለት ነው። መንፈስ ቅዱስ የዓለም አምላክ ከሆነና በስልጣን ከአምላክ ጋር እኩል ከሆነ ከማን ነው የሚሰማው? መንፈስ ቅዱስ ከአምላክ ይሰማል የሚል መከራከሪያ ነጥብ ከተነሳ ይህ መንፈስ ቅዱስ የስላሴ አካል አለመሆኑን ያረጋግጣል። ወደ እውነታው ስናመራ ግን ትንቢቱ የተነገረው ለብያችን ሙሐመድ ብቻ ነው። ከኢየሱስ አስተምሮ ጋር የሚስማማ የቁርኣን ጥቅስም በቁርኣንም ሰፍሮ ማስረጃውን እውነታውን ሲያረጋግጥ እናገኘዋለን። ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 16፡12-15«---"***የሚሰማውን ሁሉ ይናገራል እንጂ ከእራሱ አይናገርምና***"» ያለውን ቁርኣንም በሱረቱል አል-ነጅም ከ3-4«"**እርሱ (ሙሐመድ) ከራሱ ስሜት አይናገርም፤ ነገር ግን ከአምላክ የሚወርድለት መለኮታዊ ራእይ እንጂ**»" በማለት እውነታውን አምላከችን አላህ ይነግረናል። በመቀጠል ኢየሱስ«"***ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል***"» ብሏል። በእርግጥም ነብያችን ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የዓለምን ሕዝብ ወደ እውነት መርተዋል።

## ወደ መካ የሐጅ ጉዞ ማድረግ ማስረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ

በትንቢተ.ኢሳይያስ 60፡1-22 በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት በመካ ስላለው የአላህ ቤት (ካዕባ) የተተነበየ ሲሆን ክርስቲያኖች ግን ለጽዮን እንደተነበዩ አድገው ይወስዳሉ። ምናልባት የየራሳችንን ውሳኔና ትርጉም ከመስጠታችን በፊት ትንቢቱን ሙሉ በሙሉ ማየት ተግባራዊነቱን ማጣራትና ማረጋገጥ ተግባራዊ ከሆነ የት ቦታ ማለትም በመካ ነው ወይንስ በጽዮን የሚለውን ጥያቄ መመለስ መቻል አለብን። ጠቀሜታውስ በአሁኑ ሰዓት ለክርስቲያኖች ምን ያህል ነው? ከተግባራዊነቱ አኳያ በመንፈሳዊ መሐጽፋችን ውስጥ የተጠቀሰ በመሆኑ ማመን፤ ካላመንን ደግሞ መንፈሳዊ መጽሐፋችንን እንዳልተቀበልን ይቆጠራል። ውጤቱም ምን እንደሚሆን መገመቱ መልካም ነው። ለማንኛውም የሚከተሉትን ምዕራፍና ቁጥሮች ልብ ብለን በማጤን ትንቢቱ ወደየት እንደሚያቀስር መመልከት እንችላለን። በትንቢተ.ኢሳይያስ 60፡1-3 ***«ብርሃንሽ መጥቶአልና የእግዚአብሔር ክብር ወጥቶልሻልና ተነሽ አብሪ። እነሆ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አሕዛብ ይሸፍናል ነገረት ግን በአንቺ ላይ እግዚአብሔር ክብሩም በአንች ላይ ይታያል አሕዛብም ወደ ብርሃንሽ ነገሥታትም ወደ ማውጫሽ ጸዳል ይመጣሉ።»***

ከዚሁ ምዕራፍ 60፡4-5***«ዓይኖችሽን አንስተሽ በዙሪያሽ ተመልከች እነዚህ ሁሉ ተሰብስበው ወደ አንች ይመጣሉ። ወንዶች ልጆችሽ ከሩቅ ይመጣሉ። ሴቶች ልጆችሽም በጫንቃ ላይ ይሸከሟቸዋል። በዚያን ጊዜ የባህሩ በረከት ወዳንች ስለሚመለስ የአሕዛብም ብልጽግና ወደ አንች ስለሚመጣ አይተሽ ደስ ይልሻል ልብሽም ይደነቃል ይሰፋልም።»***

ከዚሁ ምዕራፍ 60፡6-7***«የግመሎች ብዛት የምድያምና የጌፌር ግመሎች ይሸፍኑሻል፤ ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ። ወርቅንና ዕጣንን ያመጣሉ፤ የእግዚአብሔርንም ምስጋና ያወራሉ። የቄዳር መንጎች ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ፤ የነባዮትም አውራ በጎች ያገለግሉሻል፤ እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሠዊያዬ ላይ ይወጣሉ፤ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ።»***

ከዚሁ ምዕረፍ 60፡8-9***«እርግቦች ወደ ቤታቸው እንደሚበርሩ እነዚህ እንደ ደመና የሚበርሩ እነማን ናቸው? እርሱ አክብሮሻልና ለአምላክሽ ለእግዚአብሔር ስምና ለእስራኤል ቅዱስ ልጆችሽን ከሩቅ ከእነርሱ ጋርም ብራቸውንና***

*ወርቃቸውን ያመጡ ዘንድ ደሴቶች የቴርሴስ መርከቦችም አስቀድመው ይጠብቁኛል።»*

ከዚሁ ምዕራፍ 60፡10-12*«በቁጣዬ ቀስፌ በፍቅሬ ምሬሻለሁና መጻተኞች ቅጥርሽን ይሠራሉ። ነገሥቶቻቸውም ያገለግሉሻል በሮችሽም ሁልጊዜ ይከፈታሉ። ሰዎች የአሕዛብን ብልፅግና የተማረኩትንም ነገሥታቶቻቸውን ወደ አንቺ ያመጡ ዘንድ ሌሊተና ቀን አይዘጉም። ለአንችም የማይገዛ ሕዝብና መንግስት ይጠፋል። እነዚያ አሕዛብም ፈፅመው ይጠፋሉ።»* 60፡14-15*«የአስጨናቂዎችሽም ልጆች አንገታቸውን ደፍተው ወደ አንቺ ይመጣሉ። የናቁሽም ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ። ከሰው ማንም እስከማያልፍብሽ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ ነገር ግን የዘላለም ትምክሕትና የልጅ ልጅ ደስታ አድግልሻለሁ።»*

ከዚሁ ምዕራፍ 60፡17-22 *«አለቆችሽንም ሰላም የበላይ ገዥዎችሽንም ጽድቅ አደርጋለሁ፤ ከዚያ በኋላ በምድርሽ ውስጥ ግፍ በዳርቻሽም ውስጥ ጉስቁልና ቅጥቃጤ አይሰማም፤ ቅጥርሽን መዳን በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ አምላክሽ ክብርሽ ይሆናልና ፀሐይ በቀን ብርሃን አይሆንልሽ የጨረቃም ብርሃን በሌሊት አያበራልሽም። እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናልና የለቅሶሽም ወራት ታልቃለች፤ ፀሐይሽ ከዚያ በኋላ አትጠልቅም ጨረቃሽም አይቋረጥም። ሕዝብሽም ሁሉ ጻድቃን ይሆናል። እኔም እከብር ዘንድ የአትክልቴን ቡቃያ የእጅ ሥራ የምትሆን ምድሪቱንም ለዘላለም ይወርሳሉ። ታናሹ ለሺህ የሁሉም ታናሹ ለብርቱ ሕዝብ ይሆናል። እኔ እግዚአብሔር በዘመኑ ይህንን አፋጥነዋለሁ።»*

አሁንም ደግመን ደጋግመን በትንቢተ.ኢሳይያስ 42 እና 60፡17-22 ስለ ሁለቱ ትንቢቶች ማለትም ትንቢቱን በተመለከተ ክርስቲያኖችን በጥሞና የምንጠይቀው እውን ትንቢቶቹ ተፈፅመዋል? ከተፈፀሙ ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንፃር ሲታይ ምን ምን ጠቀሜታ አላቸው? አፈፃጸማቸው ደግሞ ከክርስቲያኖቹ እምነት አንጻር ሲታይምን ያህል በአምልኮ ስርዓት ውስጥ እየተሰራባቸው ነው? የማይሰራባቸውም ከሆነ ለምን? በተለይም ትንቢተ ኢሳይያስ 60 በመካ አስቀድሞ ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተተነበየው መሠረት ነቢዩ መሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) በተላኩ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ ከዚያን ጊዜ አንስቶ እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ እንደሚቀጥል በግልጽ የተቀመጠ

በመሆኑ ጥርጣሬ የለበትም። ለመሆኑ ለጽዮን የተባለው በመካ ሲፈጸም "ቀይ ጤፍ ቢዘሩት ነጭ ጠየፍ ይበቅላል" ካልሆነ በስተቀር ለመካ ተተንብዮ በመካ ተግባራዊ መሆኑን ማመን አለብን። እስካላመን ለመቀበል ዋና ማስረጃችን ቁርኣን ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱስም ይደግፈናል። ቀጥሎ ደግሞ አንፃራዊ በሆነ ዘዴ ርዕሱን ለመግለፅ እንሞክራለን። ቁርኣንም ያለፉትን መልዕክቶች ስለሚያረጋግጥልን ጉዳዩ ተጣጥሟል። ትንቢተ.ኢሳይያስ ምዕራፍ 60፡1-22 ያለው እንዳለ የሚያስረዳው በሳውድ አረቢያ በመካ ያለው የአላህ ቤት መከበርና ዘላለማዊ ሆኖ እንደሚቆይ አላህም እንደሚጠብቀው የገባውን ቃል ነው። ዛሬ ከክርስቲያኖቹ ወገን ስለ ትንቢተ.ኢሳይያስ 60፡1-22 ተግባራዊ መሆን አለመሆን። ከሆነ በየትኛም የዓለም ክፍል እንደሆነ ተግባራዊ ካልሆነ ደግሞ መቼ እንደሚሆን የሚገኝ እውቀት የለም። ከፊሎቹ የሰሙም ያነበቡም አይመስሉም። ሌሎቹ ደግሞ እያነበቡ ከማለፍ በስተቀር ስለተግባራዊነቱ እምብዛም አይጨነቁም። ቀሪዎቹ ደግሞ የብሉይ ኪዳን ህግ ስለተሻረ አይመለከተንም ይላሉ። ለምንስ መጽሐፍ ቅዱስ ተብሎ ከኦሪት ዘፍጥረት እስከ የዮሐንስ ራእይ ድረስ በአንድ መጽሐፍ ተጠቃለለ ቢባል መልስ የላቸውም።

በሌላ መልኩ ደግሞ እራሳቸውን ብርሃን ውስጥ እንዳሉ አድርገው በመቁጠር በተቃራኒ ደግሞ ሙስሊሙ ጨለማ ውስጥ እንዳለ የሚገምቱት ወንጌላዊያን ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ከእምነት ወደኋላ ለመመለስ ከሚጠቀሙበት ስልት አንዱ "ፈጣሪ ሁሉ ቦታ እያለ ለምንስ ወደ መካ ፊታችሁን አዞራችሁ ትሰግዳላችሁ?" በማለት ይከራከራሉ። በተለይም እውቀት የሌላቸውን ደካማ ሙስሊሞችን በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመደለል ወደ ተሳሳተ መንገድ ይመራሉ። ለእነዚህ ወንጌላዊያን ጥያቄ አዘል አስተያየቶች ከዚያው ከመጽሐፋቸው ውስጥ መልሶች የሚገኙ ስለሆነ ወደ መካ ፊታችንን በማዞራችንን የአላህን ትዕዛዝ ጠብቀናል እንላለን። ወንጌላዊያን ስለ ኦሪት.ዘዳግም 18፥18 ሲጠየቁ የብሉይ ኪዳን ሕግ ተሸሯል ስለሚሉ ከአዲስ ኪዳኑ ውስጥ በዮሐንስ ወንጌል 4፡19-22 ውስጥ ያሉትን አንቀፆች እንዲያስተነትኑ እንጋብዛቸዋለን። ቀጥሎ ደግሞ በመጽሐፉ የተጠቀሱትን ትንቢቶች አስመልክቶ ትንቢቶቹ በመካ እና በጽዮን ምን አይነት ግኑኙነትና ልዩነት እንዳላቸው አንድ በአንድ በዝርዝር እናያለን። በዮሐንስ ወንጌል 4፡19-22 ይህም ኢየሱስና ነቢዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) አመጣጣቸው ተከታታይ በመሆኑ ከኢየሱስ በኋላ በእየሩሳሌም መስገዱ ቀርቶ

ለአንድ ፈጣሪ ወይንም ለአላህ ወደ መካ በመዞር እንደሚሰገድ የተተነበየ ትንቢት መሆኑን በግልፅ ያስረዳል።

በ1980 ዕትም በዮሐንስ ወንጌል 4፡19-23*«ሴትዮዋም እንዲህ አለችው፡- "ጌታ ሆይ! አንተ ነብይ እንደሆንህ አሁን ዐወቅሁ፤ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ላይ ሰገዱ፤ እናንተ ግን ሰዎች መስገድ የሚገባቸው በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ።" ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "አንቺ ሴት! ለእግዚአብሔር አብ በዚህ ተራራ ላይ ወይም በኢየሩሳሌም ስለ መስገድ የማትጨነቁበት ጊዜ እንደሚመጣ እመኚኝ፤ እናንተ ለማታውቁት አምላክ ትሰግዳላችሁ፤ እኛ ግን-------ለምናውቀው አምላክ እንሰግዳለን። ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለእግዚአብሔር አብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል፤ እንዲያውም አሁን መጥቶአል፤ እግዚአብሔር አብም የሚፈልገው እንደዚህ የሚሰግዱለትን ነው።»*

"አንች ሴት እመኚኝ" የተባለው ለአብ (ለአላህ) እንጂ ለወልድ ወይንም ለመንፈስ ቅዱስ ወይንም ደግሞ ለስላሴ ይሰገዳል አልተባለም። እዚህ ላይ አንድ ብርቱ ጥያቄ የሚያስነሳ ጉዳይ አለ ይኸውም አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ አንድ ከሆኑ በምን ምክንያት ነው ታዲያ ኢየሱስ *"ለእግዚአብሔር አብ በኢየሩሳሌም የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል"* ያለው? ስግደት ሁሉ የሚገባው ለአብ እንጂ ለኢየሱስ አይደለም።

ለማንኛውም ይህንን ጥቅስ መንደርደሪያ በማድረግ ቀጥሎ በትቢተ.ኢሳይያስ ምዕራፍ የሰፈረውን በንጽጽራዊ ዘዴ እናያለን። በመካና በጽዮን መካከል ያለውን አንድነትና ልዩነት የሚያሳይ ሠንጠረዥ (በትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 60፡1-18)

| በትንቢተ.ኢሳይያስ ምዕራፍ 60፥1 | መካ | ጽዮን |
|---|---|---|
| ‹‹*በዚያን ጊዜ የባህሩ በረተከት ወደአንቺ ስለሚመለስ የአሕዛብ ብልጽግና ወደ አንቺ ስለሚመጣ፤ የግመሎች ብዛት የምድያምና የጌፈር ግመሎች ይሸፍኑሻል ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ፡፡*›› | የባህሩ በረከት በዚያን ጊዜ ማለትም ይህ ትንቢት በተግባር የሚተረጎምበት ጊዜ ማለት ነው። ታዲያ በመካ ዛሬ የሐብት ክምችት ስላለ ሰው ለስራ ፍለጋ ወደዚያው ቦታ ይሄዳል። | የባህሩ በረከት ወደ ጽዮን መጣ ማለት አያስደፍርም። ምክንያቱም ከጽዮን የሚገኘው የጦር መሳሪያ ብቻ ነው። |
| ሳባ የሚገኘው በየመን ነው። | ግመሎች ለሁለት ዓላማ መካ ላይ ይሰበሰባሉ። 1ኛ) ወርቅንና ዕጣን ወደ ተቀደሰው የአላህ ቤት ያመጣሉ። 2ኛ) ለመስዋትም ይቀርባሉ። በዓረፋ በዓል የሐጅ ጸሎተኞችም ያርዳሉ። እንደ እየ አቅማቸው መጠን ከበግ እስከ ግመል መሰዋዕት ያደርጋሉ። “ሁሉ ከሳባ ይመጣሉ” የሚለው በግልጽ ያስቀምጣል። ምክንያቱም ሳባ የመን ውስጥ የሚገኝ ከተማ ነው ዛሬ ከየመን ግመል ጭነው ወደ መካ ነው የሚሄዱት እንጅ ውደ | ይህንን እውነታ የሚያረጋግጥልን በጽዮን ግመል አይበላም። ወርቅንና ዕጣንንም የጫኑ ግመሎች ከየመን ወደ ጽዮን አይመጡም። ምክንያቱም የመን የሙስሊም አገር ናትና ከጽዮን ጋር ግኑኝነት የላቸውም። ጥያቄው መቼ ነው የመኖች ወደ ጽዮን ግመል ጭነው የሚሄዱት ነው? |

| | | |
|---|---|---|
| | ጽዮን አይደለም። የመን የሙስሊሞች አገር በመሆኗ ወደ መካ እንጅ ወደ ጽዮን ለአምልኮ አይኬድም። | |
| 60፡7<br>***«የቄዳር መንጎች ሁሉ ወደ አንቺ ይሰበሰባሉ። የነብዮት አውራ በጎች ያገለግሉሻል። እኔን ደስ ሊያሰኙ በመሰዊያዬ ላይ ይወጣሉ፤ የክብሬንም ቤት አከብራለሁ።»*** | ቀዳርና ነብዮት የእስማኤል ልጆች ናቸው። አሪት.ዘፍጥረት 25፡12 ላይ ተመልከቱ። ከእስማኤል ዝርያ ደግሞ አንድም መንጋ ወደ ጽዮን አይሄድም። በዓረፋ በዓልም ሆነ ሌላ ጊዜ በዚህ መካ ባለው የአላህ ቤት መሰዋዕትነት ይፈጸማል። | ቄዳርና ነብዮት የእስማኤል ልጆች ከሆኑ አረቦች መንጎ ቻቸውንና በጎቻቸውን ወደ ጽዮን እንደማያመጡ ሳይታ ለም የተፈታ ነው። ሌላው በክርስቲያኖች ትምህርት መሰረት ኢየሱስ ለዓለም ኃጢአት ቤዛ ከሆነ በኋላ መስዋዕት ቀርቷል። ከቀረ ደግሞ ለምን **“በመስዊያዬ ላይ ይወጣሉ”**ተባለ? የዓለም ህብረተሰብ ወደ ጽዮን ለመብረር ያለው ፈተናና ዕገዳ በጣም ከባድ ስለሆነ ከጽዮን ጋር አይመሳሰልም። ከመካና ከጽዮን ዓለም አቀፋዊ የአምልኮ ሥርዓት የሚታዪው በየትኛው ነው? |

| | | |
|---|---|---|
| 60፡11«***በሮችሽም ሁልጊዜ ይከፈታሉ። ሰዎች የአሕዛብን ብልጽግና የተማረ ኩትንም ነገሥታቶቻቸውን ወደ አንቺ ያመጡ ዘንድ ሌሊትና ቀን አይዘጉም።***» | በመካ ያለው የአላህ ቤት በሮች ሁልጊዜ ክፍት መሆና የትንቢቱን በመካ ተግባራዊ መሆን ያሳ ከሐጅና ከዑምራ ውጪ እን እነዚህ የአላህ ቤት በሮች ክ እንደ ሚሆኑ ግልፅ ነው። | ትንቢቱ በሙሉ የሚያመለክተው በ አሁኑ ጊዜ በመካ እየተፈጸመ ያለውን ሁሉ በመሆኑ ከጽዮን ጋር ከፍተኛ ልዩነት አለው። |
| 60፡14«***የናቁሽ ሁሉ ወደ እግርሽ ጫማ ይሰግዳሉ።***» | በመጀመሪያ ላይ እስልምናን ለመቀበል ፈቃደኞች ያልሆኑት በስተመጨረሻ በዚህ ቤት እግር ጫማ አልሰገዱምን? | መጀመሪያ ጽዮንን የናቀና ዛሬ ደግሞ ወደ ጽዮን እግር ጫማ የሚሰግድ የለም። አሕዛቦችና እስራኤሎች ምንጊዜም አይጣጣሙም።በኢየሱስ ክርስቶስ ዙሪያ በመካከላቸው ከፍተኛ ልዩነት ስላለ። |
| 60፡15«***ከሰው ማንም እስከ ማያልፍብኝ ድረስ የተተውሽና የተጠላሽ ነበርሽ፤ ነገር ግን የዘላለም ትምክሕትና የልጅ ልጅ ደስታ አደርግሻለሁ።***» | ከእስልምና በፊት በመካ ማንም አያልፍም ነበር። ነገር ግን ዛሬ ታላቅ ዓለም አቀፋዊ ከተማ መሆኗን ማንም አይክድም። እጅግ በሚያስደንቅ ሁኔታ ትንቢቱ ተግባራዊ ሆኗል። | የእስራኤል ከተማ ጽዮን ግን ብዙ መንግስታት ሲፈራረቁባት የቆየችና የፖለቲካ ማዕከል በመሆን እስራኤልን ለባርነት ያደረገች ናት እንጂ እንደ መካ የተረሳች አልነበረችም። |

| | | |
|---|---|---|
| 60፡18«*አለቆችሽንም ሰላም የበላይ ገዥዎችሽንም ጽድቅ አደርጋለሁ፤ ከዚያ በኋላ በምድ ርሽ ውስጥ ጉስቁልናና ቅጥቃጤ አይሰማም፤ ቅጥርሽን መዳን በሮችሽንም ምስጋና ብለሽ ትጠሪያለሽ።* | 1). ዛሬ በመካ ሰላም አለ።<br>2). ግፍም አይሰማም።<br>3). ጉስቁልና ቅጥቃጤ በመካ አይሰማም። | በጽዮን ሰላም የለም። በዓለም ላይ ግፍ የሚሰራው ከእስራኤል ነው፤ በጽዮን ዛሬ በዕየለቱ በዜና ማሰራጫ የሚተላለፈው ግፍና ቅጥቃጤ ነው። |
| *ሕዝብሽም ሁሉ ጻድቃን ይሆናል።"* | ከእስልምና ትምህርት አኳያ ነብዩ ሙሐመድ (ሰለላሁ ዓለይሂ ወሰለም) ይዘውት የመጡትን የአላህ መልእክት ተቀብለው እየሰሩበት ያሉ የመካ ሕዝቦች በሙሉ ፃድቃን ናቸው። አልሐምዱሊላህከዚህ በላይ የተዘረዘረው ሀሳብ በሙሉ ዛሬ ከመካ ሁኔታ ጋር በጣም የተጣ መመ ሆኖ አግኝተነዋል። በእርግጠኝነት የምናስቀም ጠው ቁም ነገር ማንኛውም ክርስቲያን የእስራኤል ሕዝቦች ፃድቃን ናቸው አይልም። | ነገር ግን ለክርስቲያኖች የምናቀርበው ትልቁ ጥያቄ ለመሆኑ «**ሕዝብሽም ሁሉ ፃድቃን ይሆናል**» የሚለው በክርስትና ትምህርት መሰረት እስራኤልን ይመለከታል? በፍፁም እስራኤላዊያን እኮ የኢየሱስን ነቢይነትም ሆነ እነርሱ እንደሚሉት ጌትነት ያልተቀበሉ በመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ መሰረት የተረገሙ ናቸው። በቁርኣንም ይህንኑ ሐሳብ ይደግፋል። አል-ማኢዳህ 5፡78 |

የትንቢተ ኢሳያይስ ምዕራፍ (60፡1-18) በመካ ተግባራዊነት ብዙ ሰዎችን ከማስገረምም አልፎ የብዙ ሰዎችን ልብ ወደ እስልምና ሃይማኖት ስቧል። በዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ (ሰላለሁ ዓለይሂ ወሰለም) ምን ይላል? ለሚለው መሠረታዊ ጥያቄ የክርስቲያኑ መልስ "ምንም አይልም" የሚል ይሆን ይሆናል። ይሁን እንጅ በቀረቡት መመሳሰል ወይንም መገጣጠም ላይ ምንም ዓይነት አስተያየት አይሰነዝሩም። ይህ ግን እውነትን ለማለባበስ ካልሆነ በስተቀር እስካሁን ያየናቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች ትንቢቱ ሙሉ በሙሉ መካን አይመለከትም ብሎ መከራከር ነጬን ጥቁር እንደ ማለት ነው።

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት

## ነብያቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ያላቸው ደረጃ

መጽሐፍ ቅዱስ የተከበሩ ነብያቶችን ሠካራም፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ዝሙተኛ እና ጣዖት አምላኪ.............. ሌላም ሌላም በማለት በመጥፎ ገጽታ ይገልፃቸዋል። የሚገርመው በእነዚህ እኩይ ተግባራት እየገለፃቸው መጽሐፉ "ቅዱስ" የሚለው ስም መሰጠቱ ለአዕምሮ እጅግ ይሰቀጥጣል። ለአብነ ኖህ ሰካራም ነብይ እንደ ነበረ በኦሪት.ዘፍጥረት 9፡20-25 ይናገራል። አጠር አድርጌ አቀርባለሁ። የአንባቢያን ድርሻ የሚሆነው ምዕራፍና ቁጥሩን እስከጠቀስኩላችሁ ድረስ ሙሉ ቃሉን ማንበብ ነው። በኦሪት.ዘፍጥረት 9፡20-25«***ከዕለታት አንድ ቀን ኖህ የወይን ጠጅ ጠጥቶ ሰከረ፤ ልብሱንም አውልቆ እራቁቱን በድንኳን ውስጥ እራቁቱን ተኛ***።» ነብያቶች ሰካራምና ከስካራቸው የተነሳ እራሳቸውን ስተው እራቆታቸውን የሚተኙ አይደሉም። ከዚሁ ምዕራፍ«***የኖህ ልጆች ሀፍረተ ገላውን ተገልጾ ሲያዩ እራቁቱን ሆኖ ሲያዩት ፊታቸውን አዙረው ሀፍረተ ገላውን ሸፈኑት***» ይላል። ለተራ ሰው እንኳን ሀፍረተ ገላውን መናገር በጣም ዘግናኝ ነው። በድጋሜ ሳኦልም ይህን ተግባር እንደ ፈፀመ በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 19፡23-24«***ሳኦልም.......... ልብሱን አውልቆ ጥሎ ድምጹን ከፍ አድርጎ በመዘመር ማሽብሸብን ቀጠለ። ቀኑንም ለሊቱንም ሁሉ ራቁቱን በዛው ተጋድሞ ዋለ***።» ዳዊትም የእዚህ እኩይ ተግባር ተካፋይ መሆኑን በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 6፡20-21«***ጥቂት ዘግየት በማለት ዳዊት ቤተሰቡን ሰላም በማለት ወደ ቤት ገባ፤ የሳኦልም ልጅ ሜልኮል ልትቀበለው ወጣችና "የእስራኤል ንጉሥ ዛሬ ትልቅ ስም አግኝቷል፤ በመኳንንቱ ነገዶች ፊት እንዳ አበደ ሰው እርቃኑን ገልጧል" አለችው።***» ዳዊት በመጽሐፈ መዝሙር ያበደ ሳይሆን የተከበረና ፈጣሪውን አመስጋኝ ነብይ በአጠቃላይ የመልካም ባሪያ ተምሳሌት እንደ ነበር ምዕራፍና ቁርጥሩ ይነግረናል። ከዚህ ላይ ደግሞ ከእብድ ጋር ያመሳስለዋል።

## 1) ነብዩ ሰለሞን ለጣዖት እንደ ሰገደና፤ እንዲሁም ሰባት መቶ ሚስቶች (700) እና ሦስት መቶ (300) ቁባቶች እንደ ነበሩት

በ1ኛ በመጽሐፈ ነገሥት 11፡11-13‹‹*ሰለሞን የነገሥታት ልጆች የሆኑ ሰባት መቶ (700) ሚስቶች እና ሦስት መቶ (300) ቁባቶች ነበሩት፤ እነሱም ከእግዚአብሔር እንዲርቅ አደረጉት። በተለይም በእድሜ እየሸመገለ በሔደ መጠን ለባዕድ አምልኮ እንዲሰግድ አደረጉት።የሲዶናአዊያንን ሴት አምላክ ለነበረችው ለዐስታሮትና ሚልኮም ተብለው ለሚጠሩ ለአፀያፊው ለአሞናውያን አምላክ ሰገደ። .............. እግዚአብሔር ሁለት ጊዜ ተገልጦለት ባዕድ አማልክትን እንዳያመልክ ያዘዘው ቢሆንም ሰለሞን ለእግዚአብሔር አልታዘዘም። ይልቁንም ከእግዚአብሔር እየራቀ ሔደ፤ ስለዚህም እግዚአብሔር በሰለሞን ላይ ተቆጣ።*›› ከዚህ ላይ ክርስቲያኖች ለእኛ ለሙስሊሞች አብዝታችሁ የምትጠይቁት ጥያቄ አለ። ይኸውም ከአንድ በላይ ማግባት በእኛ ክልክል ነው በእናንተ ግን ይፈቀዳል ንግድ አይሆምን ትላላችሁ? ከዚህ ላይ ሰለሞን ያገባው እንዴት አልታይ አለ? ታድያ አንድ ሺህ ነው ከአራት ሚስት የሚበልጠው ወይንስ ሚያንሰው ነው? ፍርዱን ለናንተ! መጽሐፍ ቅዱስ ሰለሞንን ለጣዖት እንደ ሰገደ ያውም አፀያፊ ለሆኑና በተጨማሪም ለአምላኩ ታዛዥ እንዳልነበር ተናግሯል። በኢስላም ነብያቶች የሚላኩት ሕዝቦች ለአምላካቸው እንዲሰግዱ ለማስተማር ነው እንጂ ጣዖት እንዲያመልኩና መጥፎ ተግባራት እንዲያስተምሩ አይላኩም። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ኃላፊነታቸውን እንዳልተወጡ ይናገራል።

## 2) ኃጢአተኛ፣ ነብሰ ገዳይ እና ዝሙተኛ የነበረው ነብዩ ሳምሶን

በመጽሐፈ መሳፍንት 14፡19-20‹‹............*ወደ አስቆሎናም ወርዶ ሰላሳ (30) ሰዎችን ገደለ። ውብ የሆነ ልብሳቸውን ሁሉ በመግፈፍ አምጥቶ የእንቆቅልሹን ፍች ላወቁ ሰዎች ሰጣቸው፤ በሆነው ነገር ሁሉ እጅግ ተቆጥቶ ወደ ቤት ተመለሰ፤ ሚስቲቱም (የሳምሶን) በሠርጓ ሚዜ ለነበረው ተዳረች።*›› አሁንም ይህ ነብይ በመጽሐፈ መሳፍንት 15፡15-16‹‹*በአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ሰው (1000) ገደለ።*›› አሁንም በድጋሜ በመጽሐፈ መሳፍንት 16፡1-3‹‹*አንድ ቀን ሳምሶን የፊሊስጤማውያን ከተማ ወደ ጋዛ ሔደ፤ ከዚያም አንዲት አመንዝራ ሴት አግኝቶ ከሷ ጋር ለማደር ወደ ቤትዋ ገባ። የጋዛ ሰዎች ሳምሶን መኖሩን ሰምተው ያንን*

***ቦታ በመከበብ በከተማይቱ በር ሌሊቱን ሙሉ ሲጠብቁ አደሩ። እስኪነጋ ጠብቀን እንገለዋለን በማለት ለሊቱን ሙሉ ጸጥ አሉ። ነገር ግን ሳምሶን ከሴቲቱ ጋር ተኝቶ የቆየው እስከ እኩለ ሌሊት ብቻ ነበር***።» ነብዩ ሳምሶንን በመጽሐፍ ቅዱስ ነብሰ ገዳይ ዝሙተኛ በማለት በውርደትና በአፀያፊ ተግባር ያወግዘዋል። ከዚህም በላይ ደግሞ እጅግ የሚያስደነግጠው ከአመንዝራ ሴት ጋር ዝሙት ለመስራት ማደሩን ይነግረናል። ይህ ማለት በሀገራችን ቋንቋ ጭፈራ ቤት እንዳደረ ማለት ነው። ብዙ ጊዜ ቡና ቤቶች ጭፈራና ባር ቤቶች የዝሙትና የመጥፎ ስራ ማሰራጫ ማዕከላት ናቸው። በእነዚህ ቤቶች ውስጥ እራሳቸውን የሚያረክሱና ለዝሙት እራሳቸውን የሚሸጡ ሰዎች አሉ። ነብዩ ሳምሶን በዚህ ጊዜ ነበር ከአመንዝራ ሴት ጋር ያደረው። ልክ በአሁኑ ሰዓት እንዳለው ጭፈራና ባር ቤት ማለት ነው። ይህ ደግሞ በየትኛውም የሀገራችን ክፍል ያለ ነው። በሙስሊም ሀገሮች ግን አንድ ቦታ ላይ አይገኝም። ምክንያቱም ከዚህ መጥፎ ስራ ይልቅ እስልምና በጋብቻ ያምናል። በአጠቃላይ እስልምና ከመጥፎ ነገሮች የሚከለክልና በመልካም የሚያዝ እንዲሁም በመልካም ነገር የተገነባ ነው። ለምሳሌ፡- በባዕላት ጊዜ በየሚዲያው የሚተዋወቁት መልካም ነገሮች ብቻ ነው። ነገር ግን በክርስትና በባዕላት ጊዜ ከመልካም ነገሮች ይልቅ አስካሪ መጠጦች ወደ መጥፎ ስራ የሚገፉፉ ነገሮች ሚዲያውን ይሞሉታል። ይህ ነብይ በመጽሐፈ መሳፍንት 15፡4-5 ታጭዶ የተከመረውን የአዝመራ ክምር እንዳቃጠለ ይነግረናል። «...... ***ከዚያም በኃላ በቹበዎቹ ላይ እሳት በማቀጣጠል ቀበሮዎችን ወደ አልታጨደው ወደ ፊልሲጤማውያን የስንዴ ሰብል ውስጥ ለቀቃቸው። በዚህ አይነት ሁኔታ ታጭዶ የተከመረውን ብቻ ሳይሆን ገና በማሳ ላይ ያለውን የስንዴ፣ የወይራና የወይን ተክል ጨምሮ አቃጠለ***።» ሰዎችን ለድህነት ለመጋበዝ የለፉበትን አዝመራ ማቃጠል ተገቢ ነውን?

## 3) በራሱ ልጆች ላይ ዝሙት የሰራና ሠካራም ነብይ (ሉጥ)

በኦሪት.ዘፍጥረት 19፡30-38«.......... ***አንድ ቀን ታላቂቱ ልጅ እህቷን እንዲህ አለቻት፡- "አባታችን ማርጀቱ ነው ልጆች እንድንወልድ እኛን የሚያገቡ ወንዶች በዙሪቻችን የሉም፤ ተኝተን ከርሱ ልጆች እንድናገኝ አባታችንን የወይን ጠጅ አጠጥተን እናስክረው"። በዚያን ምሽት አባታቸውን የወይን ጠጅ አተጥተው አሰከሩት ታላቂቱ ልጅም ከሱ ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት አደረገች። ሉጥ ግን***

*በጣም ሰክሮ ስለነበር ስትተኛም ሆነ ስትነሳ አላወቀም። በማግስቱ ታላቂቱ ልጅ እህቷን ትላንት ማታ እኔ ከርሱ ጋር ተኝቻለሁ። (የግብረ ስጋ ግንኙነት ኢድርጊያለሁ።) ዛሬም እንደገና የወይን ጠጅ አጠጥተን እናሰክረውና አንቺም አብረሽው ተኚ (የግብረ ሥጋ ግንኙነት ኢድርጊ)። በዚህ አይነት ሁለታችንም ከአባታችን ልጆች ወልደን ዘራችን እንዳይጠፋ አለቻት። ስለዚህ በዚያ ምሽት አባታቸውን የወይን ተጅ አጠጥተው አሰከሩት። ትንሽቱ ልጅም ከርሱ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ኢደረገች። አሁንም ኢጅግ ሰክሮ ስለነበር ስትተኛም ሆነ ስትነሳም አላወቀም። በዚህ ሁኔታ ሁለቱም የሎጥ ሴቶች ልጆች ከአባታቸው አረገዙ። ታላቂቱ ወንድ ልጅ ወለደች ታናሺቱም ወንድ ልጅ ወለደች*።» የመጠጥ መዘዝ አልፎ ተርፎ ከወለዳቸው ልጆች ላይ ዝሙት እንዲፈፅም አደረገው። ከዚያም ሲነሱም ሆነ አብረውት ሲተኙ አላሰስታወሰም። እርግጥ ነው ሱስ ከበዛ የሱስ ተገዢ መሆኑ አይቀሬ ነው። ሎጥ ተነሳ እንጂ አሁንም በሀገራችን በተለይ በክርስቲያኖች ዘንድ ይህ ነገር የተፈቀደ መስሎ ነው የሚታያቸው። ለዚህ አይደል ሁሌም አዲስ ዓመት በሆነ ጊዜ የምዕፉ መክፈቻ ሚሆነው አስካሪ መጠጥ ነው።

## 4) በልጁ ሚስት ላይ ዝሙት የፈፀመ ይሁዳ

በኦሪት.ዘፍጥረት 38፡15-24«*ፊቷን በሻሽ ሸፍና ስለነበር ይሁዳ ባያት ጊዜ አመንዝራ ሴት መሰለችው፤ ምራቱ እንደሆነች ሳያውቅ እርሷ ወደተቀመጠችበት ወደ መንገድ ዳር ወጣ አለና "እባክሽ ካንቺ ጋር እንድተኛ ፍቀጂልኝ ብሎ ጠየቃት" እርሷም ፈቃድህን ብፈፅም "ምን ትሰጠኛለህ አለችው"? እርሱም "ከመንጋዎቼ መካከል አንድ ፍየል ጠቦት እልክልሻለሁ አላት፤እርሷም "እንግዲያውስ ጠቦትህን እከምትልክልኝ ድረስ መያዣ የሚሆን ስጠኝ" አለችው። ስለዚህ የጠየቀችውን ሁሉ ሰጣትና ከርሷ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ኢደረገ። እርሷም አረገዘች፤ በሶስተኛው ወር ገደማ ሰዎች ምራትህ ትዕማር የዝሙት ስራ ፈፀመች ከዚያም የተነሳ አረገዘች ብለው ሰዎች ለይሁዳ ነገሩት። ይሁዳም "ወደ ውጭ አውጥታችሁ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት አለ"*።» ዝሙት ለመስራት የጠየቃት መጀመርያ እርሱ ነው። ምንም እንኳን ሁለታቸውም ወንጀለኛ (ኃጢአተኛ) ቢሆኑም። ታድያ ለምን እርሷን ብቻ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት አለ? ፍርዱ ፍትሐዊ ነውን? ክስተቱ ዘግናኝ ነው። በልጁ ሚስት ላይ የፈፀመው ሲገርመን አሁንም ሌላ አስደንጋጭ ሁኔታ ይገጥመናል።

## 5) <u>በጎረቤቱ ሚስት ላይ ዝሙት የፈፀመው ነብዩ ዳዊት</u>

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 11፡22-27«*አንድ ቀን ከቀትር በኋላ ዘግየት ብሎ ከቀን እንቅልፉ ነቅቶ ወደ ቤተ መንግስቱ ሰገነት ወጣ፤ እዚያም ወዲያና ወዲህ ሲመላለስ አንድ ገላዋን የምትታጠብ ሴት አየ፤ ሴትየዋም በጣም ውብ ነበረች። ስለዚህ ማንነቷን ለማወቅ ዳዊት አንድ መላዕክተኛ ልኮ ቤርሳቤህ ትብላ የምትጠራውን የኤልዳም ልጅ የሂታዊው የኦሪዮን ሚስት መሆኗን ተረዳ። እርሷንም ያመጡለት ዘንድ ዳዊት መልእክተኞችን ላከ፤ እነርሱም ሒደው አመጡለት፤ ከእርሷ ጋር <u>የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ</u>። በዚህም ጊዜ ሴትየዋ ወርሃዊ የመንፃት ሥርዓቷን የፈፀመች ጥብቅ ነበረች። ከዚያ በኋላ ሴትየዋ ወደ ቤቷ ተመልሳ ሔደች፤ከጥቂት ጊዜ በኃላ መፀነሷን ስለተገነዘበች መልእክት ልካ ለዳዊት ነገረችው፤ ዳዊትም ኦርዮንን እራት ጋበዘውና እስኪሰክር ድረስ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ አደረገው። ........ በማግስቱም ጠዋት ዳዊት ለኢዮአብ ደብዳቤ ፃፈና በኦርዮን እጅ ላከው፤ የፃፈውም ደብዳቤ ኦርዮንን ጦርነቱ በተፋፋመት ግንባር አሰልፈው። ከዚያም አንተ ወደ ኋላ አፈግፍገህ እርሱ እንዲገደል አድርገው የሚል ነበር። ........ ቤርሳቤህ ባልዋ እንደሞተ በሰማች ጊዜ በማልቀስ አዘነች፤ የሐዘኗን ጊዜ ሲፈፀም ዳዊት ሰው ልኮ ወደ ቤተ መንግስት አስመጣት፤ እርሷም (ለዳዊት) <u>ሚስት ሆና ወንድ ልጅ ወለደች</u>።*» ዳዊት የሰው ሚስት ለመቀማት ሲል ባሏን አስገደለው። እውነት ይህ የአምላክ ነብይ ይህን ስራ ይሰራል? በዚህ አድራጎቱ ዳዊትን አምላክ እንደቀጣው ይናገራል። በ2ኛው ሳሙኤል 12፡10-11 «........ *"አንተ እኔን ስላልታዘዝከና የኦርዮንን ሚስት ስለወደድክ እነሆ በየትውልዱ ከዘሮችህ አንድ አንድ በግፍ ይገደላሉ፤ ከቤተሰቦችህ አንዱ ተነስቶ ችግር እንዲፈጥርልህ የማድርግ መሆኔን በመሀላ አረጋግጥልሃለሁ። ሚስቶችህንም ወስጄ ለሌላ ሰው በምሰጥበት ጊዜ ይህ ነገር እንደሚፈፀም ትገነዘባለህ፤ እነርሱም ከሚስቶችህ ጋር በቀን ብርሃን በግልፅ <u>የግብረ ሥጋ ግንኙነት ይደረጋሉ</u>*።» ይህ እውን የአምላክ ቃል ነውን? ዳዊት በሰራው ኃጢአት ከዘሮቹ አንዳንዱን መግደሉ አምላክ ፍርዱ ፍትሐዊ ያሰኘዋልን? አምላክ በመጥፎ ነገር ያዛልን? ያውም በቀን ብርሃን የግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲፈፅሙ በማድረግ። መልሱን የፈጣሪ ቃል ነው ለምትሉ ሰዎች ትቻለሁ።

## 6) <u>የነብዩ ዳዊት ልጆች በዝሙት ላይ ስራ መሠማራታቸው</u>

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 13፡11-14‹‹*የዳዊት ልጅ አቤሴሎም ውብ የሆነች ታምር ተብላ የምትጠራ ገና ባል ያላገባች እህት ነበረችው። አምኖን ተብሎ የሚጠራው ከዳዊት ልጆች አንዱ ታምርን ወደዳት። እርሷዋንም ከማፍቀሩ የተነሳ ታመመ፤ ድንግል እንደመሆኗ መጠን ከወንዶች ጋር እንዳትገናኝ ተጠብቃ ስለ ነበር እርሷን ለማግኘት ከቶ አልተቻለም። ነገር ግን በጣም ዘዴኛ የሆነ ዮናዲብ ተብሎ የሚጠራ ወዳጅ ነበርው......... "ሰውነትህ ጠውልጎ የማየው ለምንድነው ሲል ጠየቀው"? አምኖንም "የወንድሜን የአቤሴሎምን እህት ስለወደድኩ ነው" ሲል መለሰለት። ዮናዲብ እንዲህ አለው "ይህ ከሆነ እንግዲህ የታመምክ መስለህ ከአልጋ ላይ ተኛ፤ አባትህ ሊጠይቅህ ሲመጣ እህቴ ታአምር መጥታ እንድታስታምመኝ እባክህ ንገራት፤ እዚህ በአጠገቤ እያየኋት ምግብ አዘጋጅታ እራስዋ ሰርታ እንድታጎርሰኝ እዘዝልኝ አለው። ....... " ስለዚህም ዳዊት በቤት ለምትገኘው ታምር ወደ አምኖን ቤት ሔደሽ ምግብ አዘጋጂ የሚል ትዕዛዝ ላከ። ...... የጋገረችውን እንጀራ ከመጋገሪያው አውጥታ እንዲበላ አቀረበችለት። እርሱ ግን መመገቡን እምቢ ብሎ "ሰዎችን ሁሉ አስወጡልኝ" አለ፤ ሁሉም ሰው ወጣ ከዚያም በኋላ "እንጀራውን ወደዚህ ወደ አልጋዬ አምጥተሽ አንቺ እራስሽ አጉርሽኝ!" አላት። እርሷም "አይሆንም ወንድሜ ሆይ እባክህ አታዋርደኝ!" ይልቅስ ለንጉሱ ብትነግረው እኔን ላንተ በሚስትነት እንደሚሰጥህ እርግጠኛ ነኝ። እርሱ ግን ሊያዳምጣት አልፈቀደም፤ <u>እርሷን በኃይል አስገድዶ ክብረ ንጽሕናዋን ደፈረ</u>።››* "‹**እናት ለልጇ ምጥ አስተማረች አሉ**›" ዳዊት የሰው ሚስት ሲደፍር አይተው ነው ልጆቹም እህትና ወንድም ዝሙት የሰሩት? ዮናዳብ ደግሞ ኃይለኛ ጀንጃኝ እና አቃጣሪ ነው። "የታመምክ መስለህ እያለ አምኖን" ይመክረዋል። መጽሐፍ ቅዱስ ተከድኖ ይብሰል ሆነና ነገሩ ክርስቲያኖች ይህን ጉድ እስከዛሬ ማየት ተስኗቸዋል። ጉድ አያስብልም ታድያ? ይህም ብቻ አይደለም። ዝሙትን እንደ መብት ይጠቀሙበታል። የያዕቆብ ልጆች በኦሪት.ዘፍጥረት 35፡22 ‹‹*<u>"ያዕቆብም በዚያ ምድር ሲኖር ሳለ ሮቤል (የያቆብ የመጀመርያ ልጅ) ከአባቱ ቁባት ከባላገር ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት አደረገ፤ ያዕቆብ ይህንን ነገር ሰማ"</u>።››* ይህ ደግሞ ከአባቱ ቁባዓት ዝሙት የፈፀመው ይህ ማለት ከእናቱ ጋር ማለት ነው። ከዚሁ ምዕራፍ 49፡4‹‹*"አባቱ ያዕቆብ ይህንን ድርጊት ከሰማ በኋላ ሮቤልን (ልጁን) በአሽሙር ሲወጋው እንዲህ አለው፡- ይሁን እንጂ እንደ ውኃ የምትዋልል*

*ስለሆንክ የበላይ አለቃነት ለአንተ አይገባም። ምክንያቱም ከቁባቴ ጋር ተገናኝተሃል የአባትህን መኝታ አርክሰሃል" አለው።››*

## 7) እግዚአብሔር ነብዩ ሆሴዕ ዝሙት እንዲሰራ አዘዘው።

በትንቢ.ተ.ሆሴዕ 1፡2‹‹*እግዚአብሔር በሆሴዕ አማካኝነት ለእስራኤል ሕዝብ ቃሉን ማስተላለፍ ሲጀምር ሆሴዕን እንዲህ አለው፡- ሕዝቤ ከእኔ ተለይቶ አፀያፊ የሆነ የዝሙት ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል። እንግዲህ አንተም ሒድና ዘማዊት ሴት አግባ፤ እንደ እርሷ ሴሰኞች የሆኑ ልጆችን ከርሷ ውለድ*።›› ፈጣሪ ከዝሙተኛ ሴት ዝሙተኛ ልጆችን እንዲወልድ ለነብዩ ሆሴዕ ያዘዋል። ታድያ አምላክ እንደ ሰይጣን በመጥፎ ነገር ያዘዋልን? ታድያ ይህ የአምላክ ቃል ነውን? እኛ ግን አምላክ ይህን ንግግር ይናገረዋል ብለን አንደፍርም። ምክንቱም አምላክ የሰይጣን ባሕሪ የለበትም፤ ሰይጣን ነው በመጥፎ ነገር የሚያዘው። እዚህ ላይ ሌላም ጉድ የሚያስብል ክስተት አለ። ክርስቲያኖች ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተሞርኩዘው ይሆን የሚከተለው ተግባር ተካፋይ የሆኑት?!! ያውም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የእምነት አስተማሪና መሪ የሆኑት ቄሶችና ዲያቆናል በዝሙት ስራ መሰማራታቸው እኔ ከምላችሁ በበለጠ ራሳቸው ባዘጋጁት መጽሐፍ ጉዳዩን በአጉሊ መነፅር እንመልከተው። “የእምነት አራማጅ ነኝ” ብለው በተነሱት በማህበረ ቅዱሳን ውስጥ አንድ የተከሰተ ክስተት አለ ዝሙት እንዴት እንደተስፋፋ እንደዚህ ይተርክልናል። ከዲያቆን ጽጌ ሥጦተው አንደበት፡-“

የማኅበሩ ምስረታ በ1982 እስከ 1983 ዓ.ል አካባቢ በሦስት ወንዶች በአሥር ሴቶች ጥንስሱ እንደተጣለ ጸሐፊው ይገልፃል። “ከሴቶች መካከል አንዷ በዛር መንፈስ የተሞላች ሆና ዛሩ ሲወርድ ሚካኤል ነኝ፣ ማርያም ነኝ፤ በማለት የተለያዩ ትዕዛዛትን ያዛል። ለምሳሌ በየመጽሐፉ ቅዱሳቸው ውስጥ ወርቅ፣ ብርና ሌላም ንብረት አስቀምጠው እንዲሔዱ ጥብቅ ትዕዛዝ ያስተላልፍላቸዋል። ሴቶች የተባሉትን ሁሉ ሳያጓድሉ ይፈጽማሉ። ሌሊት ላይ ገንዘብ በወንድ ዲያቆናት ይወሰዳል። አንሶ ካገኙት ሳይወስዱ ይተውታል። ገንዘቡ ለተወሰደላት ሴት፡- “ማርያም በስጦታዬ ደስ አልተሰኘችም” በማለት የደም እምባ ታነባለች። ዲያቆናቱ በዚህ አኳኋን ብዙ ገንዘብ ሰብስበዋል። ዛሩ በዚህ መልኩ ሲወርድ ከቆየ በኋላ አንድ ቀን እንግዳ ነገር ያዛል። ከመጽሐፉ በቀጥታ ልጥቀስላችሁ፡- “የዛር መንፈስ

ወረደና፡- እኔ ማርያም ነኝ፣ የማዛችሁን ሁሉ ማድረግ አለባችሁ። አትጠራጠሩ፣ ጥርጣሬ የመናፍቃን ባህሪ ነው፤ እናም የማዛችሁን ሁሉ በእምነት አድርጉት በማለት ከወዲህ ለነገሩ ክብደት ይሰጣል። በማስከተልም፡-ድንግልናችሁ በተአምር የጋብቻችሁ እለት ይመለስላችኋል። አሁን ለዲያቆኑ ድንግልናችሁን ስጡት ይባላሉ። እነርሱም ያዘዘችው እመቤታችን ሆነችና ለታዘዘለት ዲያቆን ድንግልናቸውን ለመስጠት ወረፋ ተመዘገቡ። ... ዲያቆን እሸቱ ድንግልናቸውን ለማስገሰስ የተመዘገቡትን ልጃ-ገረዶች ቅደም ተከተሉን በመጠበቅ የአራቱን ሴቶች ድንግልና ወሰደ። ከዚህም በኋላ ግን ዲያቆኑ ኩራት ተሰማውና የሌሎችን ሴቶች ድንግልና ቀጠሮ በማራዘም አዘገየው። በርግጥ ከርሱ እንደማያመልጡና የታዘዙትም ለእርሱ እንደሆነ አስረግጦ ስለሚያውቅ ሊኮራ ይገባዋል።” [1] ይህ ብቻም አይደለም። ሌሎች የሚያስገርሙ የሚያሳዝኑም ታሪኮች በማሕበሩ ምስረታ ወቅት ተፈጽመዋል፤ ዲያቆን ጽጌ ስጦታውን እንደተረከልን፡-

“ከእለታት አንድ ቀን ዛሩ ወረደና ሁሉንም ሰብስቦ እናንተ ለኔ እንደ አሥራ ሁለቱ ሐዋሪያት ናችሁ። ተሸከሙኝና ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስትያኔን አዙሩኝ ብሏቸው እነርሱም በቃሬዛ አድርገው ዛርን ተሸክመው ቤተ ክርስትኑን አዞረውታል።”[2] ሌላም አለ። ባለዛሯ አንድ ቀን ማርያም “ተገለጸችለት”። ከመካከላቸው አንዷንም ሕይወቷን እንድታጠፋ አዘዘቻት። ከሦስት ቀናት በኋላም እንደምትነሳ ገለጸችላት። ልጅቱም ትዕዛዙ የማርያም ነው ብላ ስላመነች ተቀበለችው። ሳታመነታም ወደ ድርጊቱ ተሸጋገረች። በመቀነት አንገቷን አስራ ተንጠለጠለች። ከዚያ በኋላ የሆነውን ዲያቆን ጽጌ እንዲህ ተርኮልናል፡-

“ልጅቷ በመቀነቷ አንገቷን ታስራ ተንጠለተለች፤ አረፋ ደፈቀች፣ እንባ በእንባ፣ ጣር በጣር ተሞላች። ጥቂት ደቂቃዎች በሲቃ አለፉ። ጭንቁ በዛባት፤ ቶሎ መሞት አቃታት። ከዚህ በኋላ ግን ወደ ልቧ ተመለሰች። መንፈስ ቅዱስ ሹክ አላት። እግዚአብሔር እንደዚህ እንደማይፈትን፤ በምህረት የተሞላ አምላክ መሆኑንና በክርስቶስ ደም የተዋጀሁ እንዴት በዚህ ጣርና ስቃይ እንድሞት ይፈልጋል? የሚል ትክክለኛ መንገድ አገነች። ከዚህ በኋላ መታገስ አልቻለችም። ግን በጣም ደክማለች። የተንጠለጠለችበትን ጨርቅ በእጇ ያዘችና ጉሮሮዋን ትንሽ አሳረፈችው። ከዚያም ያላትን ኃይል ሁሉ አሰባስባ የድረሱልኝ፣ አድኑኝ ጥሪዋን አስተጋባች። ይህን ሁሉ ጉድ ሰምቶ የማያውቅ ጎረቤት የተፈጠረውን ሁሉ በውል

ሳይገነዘብ ጩኸቱን ሰምቶ ብቻ እየዘለለ ገባ። እንድትሞት የፈረዱባት አባላት ሁሉም ስለርሷ በሌላው ክፍል ይጸልዩ ነበር። ከጎረቤት ያለው ሕዝብ ግን ዘው ብላ ሲገባ ወጣቷ ብቻዋን በሞት ጣር እየተሰቃየች ነበር። በርግብርቦሽ ከተሰቀለችበት ካወረዷት በኋላ ፖሊስ ጣቢያ በመደወል ሁኔታውን አሳወቁ። ፖሊስም ፈጥኖ በመምጣት ወጣቷን ወደ ህክምና ወሰዳት።…”[7]

ልጅቱ የማርያም መልእክት የምታደርሰው ባለዛር ትንሽ እህት ናት። እርሷን “በማርያም ትዕዛዝ” መግደል የተፈለገበት ምክንያት ዲያቆን ጽጌ ሲያስረዳ፡- “ባለዛሯና ታናሽ እህቷ ከእናት ከአባታቸው ተሰጣቸው መኖሪያ ቤት ነበር። ይህን መኖሪያ ቤት እህትማማቾቹ የጋራ አድርገው ይኖሩበት ነበር። አሁን ልዩ ዘዴ ተፈጠረና ታናሽ እህቷን ገድላ ዲያቆኑን አግብታ ቤቱን ብቻዋን ወርሳ ያን የተሰበሰበ ብርም አብረው ሁለቱ ሊጠቀሙበት ተማከሩ።”[8]

## 8) ለጸሎት ጣዖትን (የጥጃ ምስልን) የሰራ ነብይ አሮን

በኦሪት.ዘፀአት 32፡2-4«*“አሮንም” ሚስቶቻችሁ፣ ወንዶች እና ሴት ልጆቻችሁ የሚያጌጡበትን የጆሮ ወርቅ ሁሉ ሰብስባችሁ አምጡልኝ አላቸው። ስለዚህ ሕዝቡ ሁሉ ያላቸውን የወርቅ ጉትቻ ሁሉ አውልቀው ወደ አሮን አመጡለት፤ እርሱም የወርቅ ጉትቻቸውን ሁሉ ወስዶ በእሳት አቀለጠው ያቀለጠውን ወርቅ በቅርጽ መስሪያ ውስጥ አስገብቶ የወርቅ ጥጃ አድርጎ ሰራው፤ ሕዝቡም “እስራኤል ሆይ” ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣን አምላካችን ይህ ነው አሉ።*» በኢስላም አንድን ነብይ ለጣዖት አምልኮ የቀረጸ የለም። ሕዝቦችንም ወደ ጣዖት አምልኮ የተጣራ ነብይ የለም። ደግሞስ የጥጃ ምስል የዓለማት ጌታ ነውን? መጽሐፍ ቅዱስ ግን እነዚህ ነብያቶች በመጥፎ ነገር ሲገልፃቸውና ኃላፊነታቸውንም ያልተወጡ አድርጎ ያቀርባቸዋል።

## 9) ነብዩ ዳዊት እብድ ለመምሰል ሞከረ።

በ1ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 21፡12-13«……….. *ስለዚህም ዳዊት እነርሱ ባሉበት አካባቢ ያበደ ለመምሰል ሞከረ፤ ሊይዙትም በሚሞክሩበት ጊዜ እንደ እብድ ሆኖ*

[7] ዲያቆን ጽጌ ስጦታው፣ ይነጋል፣ አዲስ አበባ ኢትዮጲያ 1997 ዓ.ም፣ ገጽ 126 – 127
[8] ከዚሁ ገጽ 127

***አገኙት። የከተማይቱ ቅጽር በሮች እየሟጠጠ ለኸጩን በጺሙ ላይ ያዝረከረክ ነበር***።» ይህን ያክል አዕምሮው ቢስት ነው እብድ ለመምሰል የሞከረው? እውን ዳዊት እብድ ነበር? ይህ ብቻ አይደለም ለኸጩን (ልጋጉን) በጺሙ ላይ ያዝረከርክ ነበር በማለት ገልፆታል። ይህ አገላለጽ ለተከበረ ለምላክ ነብይ ይገባልን? በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 6፡5-21«***ነብዩ ዳዊት በእግዚአብሔር ፊት እራቁቱን ደነሰ***» ይለናል። ከላይ እብድ ለመምሰል ሞክሮ ከዚያም እብድ ሆኖ አገኙት። መቼም ያበደ ሰው ልብሱን ማውለቁ ስለማይቀር ነው እራቁቱን ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት ደነሰ ያለው።

## 10) ወደ ዝሙት የሚያዝ ይሁዳ

በኦሪት.ዘፍጥረት 38፡8«***"ይሁዳ የኤርን ወንድም ኦናንን "ኦናንን ከወንድምህ ሚስት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት በማድረግ በደንቡ መሰረት ለወንድምህ መጠሪያ የሚሆን ዘር አስቀርለት" አለው።***» በዝሙት ከሚያዘው ይልቅ ሌላ ሚስት ማግባት አይሻልም ነበር? ፈጣሪ ሰዎችን በዝሙት የሚያዝ ከሆነ ይህ "ቅዱስ" ንግግር ያስብለዋል ወይ?

# ምዕራፍ አሥራ ስምንት

## የሴት ልጅ ክብርና ደረጃ በመጽሐፍ ቅዱስ

ወንዶች ለሴቶች አስፈላጊ እንደሆኑት ሁሉ ሴቶችም ለወንዶች አስፈላጊ ፍጡሮች ናቸው። አብዛኛዎቹ ፍጥረታት የተፈጠሩት ከተቃራኒ ፆታ ጋር ነው። ይህም በፈጣሪ መደንገጉ የራሱ የሆነ ዓላማዎች አሉት። ለአብነት ያህል፡- ሴት ልጅ ከተቀራኒ ፆታ ጋር መፈጠሯን ካስታዋልን ለመዋለድ በተለይ ዘርን ለመተካት ያለ ሴት የማይሳካ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ሴት ልጅ ለመዋለድ፣ አብሮ ለመኖር፤ ለመረዳዳትና የሕይወት ዘይቤን አስተካክሎ ለመኖር ሴቶች ትልቅ አስተዋጽዖ አላቸው። ሴቶች ለወንዶች ታላቅ የፈጣሪ ስጦታ ናቸው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተቃራኒ ገጽታ ይገልፃቸዋል። ይህ ብቻ አይደለም፤ የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ በመንተራስ የሀገራችን ክርስቲያኖች አንገት የሚያስደፉና ቅስም የሚሰብሩ ምሳሊያዊ ንግግሮችና ብሂሎች ሲሰነዝሩ ይደመጣል። ይህም ሴቶች በማህበረሰቡ ውስጥ ተንቀውና ራሳቸውን ደካማ ፍጡር አድርገው እንዲያስቡ አስገድዷቸዋል። ከእነዚህም አሸሚጣጭ አባባሎች ለአብነት እነሆ፡-

- ሴት ከመምከር ደግሶ መስከር
- ሴት ልጅ ማገዶ቎ ቢቸግራት ምሰሶ ትነቅላለች
- ሴትና ዶሮ ሲሄዱ ቤታቸውን ይከዱ
- ወንድ የወለደ እንደ እግዜር ከበደ
- ቢጠሉት አይሆን ሞትና ሴት መሆን
- የሴት ትልቅ የጓያ ክምር የለውም
- የሴት ሩጫ ከአፍ እስከ አፍንጫ
- ከሴት ጎበዝ የወንድ ደካማ
- ከሴት የመከረ በሳር ያሰረ
- ማውራት ሴትነት መስራት ወንድነት
- ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ
- ተናዶ መቅረት ሴት የሆኑ እለት
- ሴት ከበዛ ጎመን ጠነዛ

- ሴት ካልወለደች ቋንጣ አትጠብስም
- ሴት የወደደ ገኃነም እሳት ወረደ
- ሴት ያመነ ጉም የዘገነ
- ሴት ያመጣው ጠብ አይበርድም
- የሴት ልባም የአህያ ቀንዳም
- የሴት ልብ መርፌ ታህላለች የነኳት እለት ትጠፋለች
- የሴት ዘመናይ የፊቷን እንጂ የኋላዋን አታይ
- ሴት የወለደ መቅ የወረደ ወንድ የወለደ እንደእግዜር ከበደ
- ሴት የወለደና ጉድ ያዘለ አንድ ናቸው
- ለሴት ዱላ ለአህያ ዳውላ
- ከሺ ሴት አንድ ወንድ ይበልጣል[9]

## 1) ‹‹ሴት›› የሚለው ስያሜ የድክመት ምልክት እንደሆነ

አንዳንዶች "‹**ሴት**›" የሚለውን ስያሜ ከወንዶች ጋር ያላቸውን እኩልነት ላለመቀበል ሲሉ ሴት ማለት የድክመትና የፍርሐት ምልክት አድርገው ይወስዱታል። ድክመትና ፍርሐት ያለበትን ወንድም ቢሆን "ሴታ ሴት" በማለት ይጠሩታል። መጽሐፍ ቅዱስም ይህን ሐሳብ ሲደግፍና አፅኖት ሲያደርግበት እናገኘዋለን። በተለያዩ ምዕራፎች ድክመትና ፍርሐት ያለባቸውን ወንዶች በሴት መስሎ ሲገልፃቸው እናያለን። ለአብነት ያክል የሚከተሉትን ምዕራፎች እናያለን። በትንቢተ.ኢሳይያስ 19፡16‹‹***በዚያን ቀን ግብፃውያን እንደ ሴት ይሆናሉ። የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ካነሳው ክንዱ የተነሳ በፍርሐት ይንቀጠቀጣሉ።***›› በትንቢተ.ኤርሚያስ 50፡37‹‹***ሰይፍ በፈረሰኞችና በሰረገሎች ላይ በመኳኳሏ ባሉት ባዕዳን ወታደሮች ላይ መጣ፤ እነርሱም እንደ ሴቶች ይሆናሉ። ሰይፍ በሁለት ንብረት ላይ መጣ፤ለዝርፊያም ይሆናሉ።***›› ከዚሁ ምዕራፍ 51፡3‹‹***የባቢሎን ጦረኞች መዋጋት ትተዋል፤በምሽጎቻቸው ውስጥ ተቀምጠዋል፤ ኃይሎቻቸው ተሟጧል፤ እንደ ሴት ሆነዋል።***›› በትንቢተ.ናሆም 3፡13‹‹***እነሆ ጥፍሮችህ ሁሉም ሴቶች ናቸው። የምድርህ በሮች ለጠላቶችህ ወለል ብለው ተከፍተዋል፤***

9 ምንጭ ፡- ጣዝመት ከተሰኘው የሙሉ ደቦጭና ሴቶች በኢትዮጵያ ከተሰኘው የቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ መጽሐፍ የተወሰደ።

***መዝጊያዎቻቸው በእሳት ተበልተዋል።»*** ከዚህ ላይ እንደምንረዳው ***«የምድር ሰራዊቶች <u>በሙሉ እንደ ሴት ሆነዋል</u>»*** በማለት የተገለጸው ያ ማለት ደካማና ፈሪ መሆናቸውን ለመግለጽ ነው። ጥያቄ ሁሉም ሴቶች ፈሪ ናቸው ወይ? አንዳድ ሴቶች ከወንድ የተሻሉ እንዳሉም መካድ የለብንም።

## 2) ***«<u>ሴት ልጅ» ገደለችው እንዳይባል ደካማና ፈሪ ከመሆኗ የተነሳ</u>***

ሴት ልጅ በምንም መልኩ ከወንድ ልትሻል አትችልም የሚል ኋላቀር አስተሳሰብ ለዘመናት ተንሰራፍቶ ቆይቷል። ሴት ወንድን ማሸነፍም ሆነ በየትኛውም አጋጣሚ ከወንድ ተሽላ መገኘቷን ላለመቀበል ሲባል በተለዩ ፈሊጣዊ አነጋገሮች ሞራላቸውንና ክብራቸውን ሲነኩ ይስተዋላል። ለምሳሌ፡- **‹ከሺ ሴት አንድ ወንድ ይበልጣል›** በማለት ለውድድር እንኳ እንደማይበቁ አድርገው በመቁጠር ወንድ ብቻ ለነገሩ ሁሉ የበላይ ነው እያሉ ክብራቸውንና መብታቸውን ረግጠዋል። ይህንንም በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በስፋት ተጠቅሶ እናገኘዋለን። በመጽሐፈ መሣፍንት 9፡52-54 ***«አቤሜሊክም ተዋግቶ ግንቡን ያዘ፤ ይሁን እንጂ እሳት ለመለኮስ ወደ ግንቡ መግቢያ አጠገብ እንደደረሰ፤ አንዲት ሴት ከላይ የወፍጮ መጅ በራሱ ላይ ለቀቀችበት፤ ጭንቅላቱንም አፈረሰችው። ወዲያው ጋሻ ጀግሬውን ጠርቶ “<u>‹‹ሴት ገደለችው እንዳይሉ እባክህን ሰይፍ መዘህ ግደለኝ»</u>” አለው። ስለዚህ አገሊጋዩም ሆነ እርሱም ሞተ።»*** ትኩረት! “ሴት ገደለችው እንዳይባል” የተባለው በሴት ተገድሎ መሞት ታላቅ ሐፍረት ስለሆነ ነው ሴት ገደለችው እንዳይሉ ያለው።

## 3) <u>በሕዝብ ቆጠራ ጊዜ «ሴቶች» ከቁጥር እንደማይገቡ</u>

በክርስትና ሃይማኖት መመሪያ በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ አግዚአብሔር በሕዝብ ቆጠራ ወንዶች ብቻ እንዲቆጠሩ አዟል። እነሆ ማስረጃውን በኦሪት.ዘኁልቁ 1፡1-2 ***«እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ በሁለተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር በመጀመሪያ ቀን በሲና ምድረ በዳ ሳሉ እግዚአብሔር ሙሴን በሚገናኝው ድንኳን ውስጥ ተናገረው፤ እንዲህም አለው፡- <u>የወንዶቹን ስም አንድ በአንድ በመዘርዘር መላውን የእስራኤል ማሕበረሰብ በየጎሣዎቹና በየቤተሰባቸው ቁጥራቸው</u>።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 3፡15 ***«እግዚአብሔር ሙሴን ሲና ምድር፤ ሉዋሁያን በየቤታቸውና በየጎሣቸው ቁጠር፤ <u>የምትቆጥረውም አንድ ወርና ከዚያ</u>***

*__በላይ የሆነውን ወንድ ሁሉ ነው፡፡__*» ይህንን ጥቅስ በመንተራስ አንዳንድ የክርስቲያን ምሁራን እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል። ከእነዚህም ውስጥ ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ ይገኙበታል። እንዲህ ሲሉም ጽፈዋል፡-“**ከታሪክ ማህደር እንደምንረዳው በጥንት ጊዜ (ዘመን) ሴቶች እጅግ ከመናቃቸው የተነሳ በስነ-ሕዝብ ቆጠራ እንኳ አይገቡም ነበር።**”› በማለት ሴቶች ከቀጥር አለመግባታቸውን አብራተዋል። የሀገራችን ሰዎችም ‹**ከሺ ሴት አንድ ወንድ ይበልጣል**›፤ ‹**ወንድ የወለደ እንደእዜር ከበደ**› በማለት ሴቶች ከቁጥር ውጭ መሆናቸውን ተናግረዋል።

## 4) «__ሴቶች__» __መጥፎ ከመሆናቸው የተነሳ ወንዶች ከእነርሱ ጋር አብሮ አለመቀመጥ እንዳለባቸው__

በመጽሐፈ ምሳሌ 21፡9«*__ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድ ላይ ከመቀመጥ በውጭ ቤት ማዕዘን መቀመጥ ይሻላል__*፡፡» ከዚሁ ምዕራፍ 21፡19«*__ከጠበኛና ከቁጡ ሴት ጋር ከመቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ ይሻላል__*፡፡» አሁንም በድጋሜ ከዚሁ ምዕራፍ 25፡24 «*__ከጠበኛ ሴት ጋር በአንድነት ከመቀመጥ በሰገነት ማዕዘን መቀመጥ ይሻላል__*፡፡» ከዚሁ ምዕራፍ አልወጣንም 27፡15 «*__በዝናብ ቀን የሚያንጠበጥብ ቤትና ጠበኛ ሴት አንድ ናቸው__*፡፡» በመጽሐፈ ሲራክ 19፡13 «*__ጠበኛም ሚስት እንደማያቋርጥ ነጠብጣብ ናት__*[10] ፡፡» የአምላክ ቃል ነው ተብሎ የሚታመነው መጽሐፍ ቅዱስ ሴቶችን ወንዶች አብረዋቸው እንዳይቀመጡና ከእነርሱ እንዲርቁ በምሳሌ በማስረዳት ይመክራቸዋል። ለእምነቱ ተከታዮች ጥያቄ አለኝ ሴቶች ብቻ ናቸው ከፉ? ከወንዶች ከፉ የለም? በአባባልም ‹**ጨቅጫቃ ሴት ያለበትና የሚያፈስ ቤት ያለው እንደልቡ አያድርም**› ይላሉ። ሴት ልጅ ፀረ ሰላም ነች ማለት ነው።

## 5) «__ከደረቅ ሴት__»__ጋር አብሮ ከመኖር ከዱር እንስሳት ጋር መኖር እንደሚቀል__

መጽሐፈ ሲራክ 25፡16 «*__ከደረቅ ሴት ጋር አብረህ ከምትኖር፤ ከዱር አውሬዎችና ከእንሰሳት ጋር አብሮ መኖር ይሻላል__*፡፡» ከላይ ባየነው ርዕስ ላይ ከጠበኛ ሴት ጋር አብሮ መቀመጥ በምድረ በዳ መቀመጥ እንደሚሻል

[10] መጽሐፈ ሲራክ የሚገኘው በኦርቶዶክሱ መጽሐፍ 81 ነው፡፡

ይመከራል። ጥያቄ ከሴቶች ጋር አብሮ ከመኖር ከዱር አውሬ ጋር መኖር እንደሚቀል ተነግሯል። ያ ማለት እኮ ጅብ፣ አንበሳ፣ ነብር ወ.ዘ.ተ ከእነዚህ የዱር አራዊት ጋር መኖር በእርግጠኝነት ይቀላል? ሴቶችስ ከእነዚህ የዱር አውሬዎች ያነሱና የበታች ናቸውን? ከአባባሎችም **‹ሴት የወደደ ገኃነም እሳት ወረደ›** ያሉት? አብሮ መኖር ከተከለከለ በበለጠ ውዴታ ካለማ ከላይ ካየነው ርዕስ አንፃር ሴትን ልጅ መውደድ ወደ ሲኦል እንደምታወርድ ትገልፃለች።

## 6) **«<u>ሴት ልጅን» ሚስጠረኛ አድርጎ አለመያዝ እንደሚገባ</u>**

በመጽሐፈ ሲራክ 25፡24«***<u>በቤትህ አጠገብ ለውሃ ፍሳሽ አታብጅለት፤ ለሴት ልጅም የልብህን ሚስጢር አታውጣላት።</u>***» ከዚሁ ምዕራፍ 42፡14«***<u>ከሴት ቸርነት የወንድ ንፉግነት ይሻላል። ባሏንና ውሽማዋን የምታቀና ሴት ሐፍረት ናት።</u>***» በትንቢተ.ሚኪያስ 7፡5«***<u>በእቅፍህ ለምትተኛዋ ሴት እንኳን ቢሆን ስለምትነግራት ነገር ተጠንቀቅ።</u>***» ከዚህ ላይ ትልቅ ትዝብት እውነታ አለ። ሁሉም ወንዶች ለሴት ሚስጢር ያላካፈለ ይኖር ይሆን? ሌላው ይቅር ለእናትና ለሚስት ሚስጥረኛ ያልተሆነ ለማን ይሆናል? ከሴት ደግነት የወንድ ንፉግነት መሻሉንም ተገልጿል። ያ ማለት ልክ ሴቶች መልካም ስራ እንደማያውቁ ማለት ነው። ከዝንብ ማር እንደማይገኝ ሁሉ ከሴት ልጅ መልካም ስራ የማይገኝ መሆኑን ለመግለጽ ነው በማነፃፀር የተገለጸው። ከፈሊጣዊ አባባሎችም ሰናይ **‹ሴት ያመነ ጉም የዘገነ›** ሚስጢረኛ አለማድረግ የሚገባ ከሚከተለው ጉዳት ለማምለጥ ይሆን? ከፈሊጣዊ አባባል **‹ሴትና በቅሎ ጊዜ አይታ ትጥላለች›** ስለሚሉ ማለት ነው።

## 7) **«<u>ሴት ልጅ» የኃጢአት መገኛና ምንጭ እንደሆነች</u>**

ሴቶች የኃጢአት መገኛና ምንጮች ስለሆኑ ነው የሚስጢር ጓደኛ አድርጎ አለመያዝን የመከረው። በመጽሐፈ ሲራክ 42፡13-14 «***<u>ከልብስ ብል ይገኛል፤ ኃጢአትም ሁሉ ከሴት ልጅ ይገኛል፤ ለእርሷም ሁላችንም እንሞታለን።</u>***» ይህን አያይዘው አንዳንድ የክርስቲያን ምሁራን በሴቶች ላይ ወቀሳና እርግማን አቅርበዋል። ለምሳሌ፡- የቀድሞው የአሜሪካ ፀረ-ሰቆቃ ማህበር መሪ የነበረችው ሚልቲዳ ጀስሊን ጌጅ እንዲህ ስትል ጽፋለች። ቅዱስ ተርቲሊንን (155-255 እ.ኤ.አ) የመሳሰሉት ታላቅ ምሁራን "**‹ሴት› ሔዋንም ሆነ ሌላዋ ሴት ያው የኃጢአት ጀማሪ፣ ሞትን ያመጣችብን፤ የጌታችንንም ልጅ ለሞት የዳረገችና**

**ልንጠነቀቃት የምትገባን የሰይጣን መግቢያ በማለት በሰፊ ማስተማራቸውን እንገነዘባለን**[11]**። በዚህ ጉዳይ ላይም ቤት ክርስቲያን እንዲሁ ለሴት ያታ ባላቸው የጥፋተኝነት እይታ የበላይና የበታች ያታዎች እንዳሉ ቤት ክርስቲያን ታስተምር ነው**[12]**።›** ወደ መጽሐፍ ቅዱስ በመመለስ ጥያቄ ላቅርብ ጳውሎስ በሮሜ መልእክት 5፡12 ላይ «*በአንዱ አዳም ምክንያት ሞት ወደዚህ አለም ገባ*» ማለት አስተምሮ ነበር። ከዚህ ላይ ደግሞ የኃጢአት ምንጭ ሔዋን እንደሆነችና ለእርሷ ሁላችንም እንደምንሞት ተጠቅሷል። የትኛው ነው ትክክል? ኃጢአተኛ ከመሆኗ የተነሳ ከፈሊጣዊ ንግግሮች **‹ሴት የወደደ ገኃነም እሳት ወረደ›** ቢሉ አይፈረድባቸውም። ምክንያቱም ከሴት ልጅ ኃጢአት ስለሚገኝ ነው ኃጢአተኛን ሰው መውደድ እንደሌለበት ነው መጽሐፍ ቅዱስም የመከረው።

## 8) **«ሴት ልጅ» እንደ ሰይጣን አሳሳችና ሞትን ያመጣች መሆኗ**

መጽሐፍ ቅዱስ ሔዋን አዳምን እንዳሳሳተችውና ሞትን ወደዚህዓለም ያመጣች መሆኗን ይናገራል። በመጽሐፈ መቃብያን ሳልስ 3፡6«*የበለሰ ፍሬውን ከበላች በኋላ መጥታ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ፍጥረቱን አዳምን አሳሳተችው፤ የፈጣሪዋን ትእዛዝ ስለተዳፈረች በሱም (አዳም) በልጆቹም ሞትን አመጣች።*» በሴቶች ምክንያት ነው ሞት ወደዚህ ዓለም የመጣው? ይህ ከሆነ ወንዶች የሚሞቱት ሴቶች ባመጡት ሞት ነው ማለት ነው? በጥቅሱ መሰረት ከፈሊጣዊ አባባልም እንጥቀስ **‹ቢጠሉት አይሆንም ሞትና ሴት መሆን›።**

## 9) **«ሴት ልጅ» ከሞት የከፋች መሆኗ**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ወንድ ከሞት የከፋ ነው ተብሎ አንድም ቦታ ላይ አልተጠቀሰም። ስለ ሴት ግን በሰፊው ተጠቅሶ ይገኛል። በመጽሐፈ መክበብ 7፡26 «***ከሞት የከፋች ሴት አገኘሁ፤ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሰው ከእጅ ያመልጣል፤ ኃጢአተኛውን ግን አጥምዳ ትይዘዋለች።***» ጥያቄ ለክርስቲያን ወንዶች ሴት ልጅ ከሞት የከፋች ከሆነች ለምን ታገቧታላችሁ? እግዚአብሔርን ለማስደሰት ሲባል መስፈረቱ ከሴት ልጅ ማምለጥና መራቅ ነው። ኃጢአተኛውን

---

[11] Karen Armstrong The Gospel according to Woman Christianity Creation of The Sex War in the West Elmtree Books 1486 Page (52-62)

[12] Joslyn Woman Church and State Page 55

ወንድማ አጥምዳ ትይዘዋለች። ሴት ልጅ ኃጢአተኛ ከሆነች ለምንድን ወንዶችን በምትወልድበት ጊዜ ለወንዶች እነርሱም ወንዶች አብረው እንደ ሴቶች ኃጢአተኛ የማይሆኑት?

## 10) ‹‹ሴት ልጅ›› ከባል ጋር ያላት እኩልነት

አንዳንድ የክርስቲያን ምሁራን ሴቶች ከወንዶች ጋር በምንም አይነት እኩልነት የሌላቸው መሆኑን ለመግለጽ ሲሉ፡- የመናገር፣ የመማር፣ የማስተማር፣ የማስተዳደር---መብት የላቸውም በማለት በቤተ ክርስቲያን ሲያስተምሩ ቆይተዋል። መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ ላይ በሴቶች ላይ ልዩ ቅጣት እንዳዘዘባቸውና አድሏዊነት እንዳለው በመጽሐፈ ሲራክ ‹‹**ከሴት ደግነት (ቸርነት) የወንድ ንፉግነት ይሻላል**›› እያለ ይበልጥ እኩል አለመሆናቸውን አጉልቶ ያሳያል። በ1ኛ ቆረንቶስ 11፡3‹‹*ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፤ የሴትም ሁሉ ራስ ወንድ፤ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደሆነ እንድታውቁ እፈልጋለሁ*›› ይላል። ሙሉ ደቦጭ በዚህ ጥቅስ በመመርኮዝ እንድህ በማለት ጽፋለች፡- “‹**ለመሆኑ ይህ ‹‹ራስ የሚለው›› ምንን ያመላክታል? አያሌ የክርስቲያን መሪዎች ‹ሴት›‹ተገዢዎች› መሆናቸውን ያስረዳሉ። እንደነዚህ ወገኖች አስተሳሰብ ሴቶች ፀጥና ለጥ ብለው ለወንዶች መገዛት እንጂ ስለ እኩልነት ማሰብ የለባቸውም።**”›[13] በሌላ ቦታም የክርስቲያናዊ ጹሑፍ እናገኛለን። ‹**የተፈጥሮ ሕግ ስለሆነ የወንድ ራስነት ወይም ስልጣን ፈቅደናል ወዶ መቀበልና መገዛት ብልህነትና መንፈሳዊነትም እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል**[14]**።› በመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ ላይ ወንዶችና ሴቶች እኩል እንዳልሆኑ በዚህ መልኩ ሰፍሯል። በቁጥር 16 ላይ እግዚአብሔር በሴቲቱ በሔዋን ፍርድን አዟል። ሁለት ፍርዶችን ምንም እንኳን ልጅ የመውለድ አስደሳች ልምምድ ቢኖራትም ልጅ የመውለድ ሂደት ከፍተኛ ጭንቅና የህመም ስቃይ ያስከትልባታል። ዛሬም ልጅ በሚወልዱበት ጊዜ ሴቶች ሁሉ ይህንን ፍርድ ይቀበላሉ። ሁለተኛ በባልና በሚስት መካከል በነበረው የእኩልነት ግንኙነት ይቀየራል። ከውድቀት በፊት ሚስት ለባል የምትገዛበት ምክንያት አልነበረም፤ አሁን ግን እንዲገዛትና እንዲያዛት የበላይነት ለባል ተሰጠ።**

---

13 ሙሉ ደቦጭ፣ ጠዝሙት፣ የሴቶች አገልግሎት ቤተሰባዊ ክርስቲያናዊና ማህበራዊ ገፅታው አሳታሚ አዲስ አበባ 1993 ዕትም፣ ገጽ 8

14 ዮናስ ኤሪክስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች ምን እንማራለን? አሳታሚ ግሎባል ስነ ጹሑፍ አገልግሎት የካቲት 1998 ዓ.ም ገጽ 6

**ኃጢአት በመስራቷ ሂደት ሔዋን ቀዳሚውን ሚና ስለተጫወተች እርሷና ከርሷ በኋላ የመጡ ሴቶች በወንዶች በሚገዙበት ግንኙነት ለመኖር ተገደዱ[15]።›** ከዚህ ላይ ጳውሎስ በአንዱ አዳም ምክንያት ሞት ወደዚህ ዓለም ገባ በማለት በሮሜ 5፡12 አስተምሮ ነበር። ነገር ግን በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡17‹‹***የተታለለውም ወንዱ (አዳም) አይደለም፤ ሴቷ (ሔዋን) ተታላ ሕጉን በመተላለፍ ወንዱን (አዳምን) አሳሳተችው***›› በማለት ንግግሩ እርስ በርስ ይጣረሳል። ከላይ ያሉት ምንጮች 1.2.3

## 11) ‹‹ሴቶች›› የመናገር መብት የሌላቸው መሆኑ

ሴቶች የመናገርም ሆነ አቤቱታ የማቅረብ መብት በመጽሐፍ ቅዱስ አልተሰጣቸውም። ለምሳሌ፡- 1ኛ ቆረንቶስ 14፡34‹‹***ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና፡፡***›› ስለዚህ ያላቸው ድርሻ ለባሎቻቸው መገዛትና ጥያቄ እንኳ ቢኖራት መናገር ስለማትችል መብቷ ተረግጦና ሐሳብ ፍላጎቷ ተነፍጎ መኖር ነው ያላት ብቸኛ አማራጭ ይህን መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ መነሻ በማድረግ የክርስቲያን ምሁራን ተመሳሳይ ሐሳቦችን ጽፈዋል፡- **‹“የቀድሞው የአሜሪካ የሴቶች ፀረ ሰቆቃ ማኅበር መሪ የነበረችው ማልቲዳ ጆስሊን ጌጅ ጳውሎስ ሴቶች ዝም እንዲሉ ባዘዘው መሰረት ሴቶች በአውሮፓና በክርስቲያኑ ዓለም የመናገር መብት አልነበራቸውም። ለምሳሌ በ1833 እ.ኤ.አ መጀመሪያ ከተቋቋመው ሴቶችና ወንዶች በአንድ በሚያስተምረው በአሜሪካ ኢብሪሊን ኮሌጅ (Obrlin College) ሴቶች በአብዛኛው ክፍል ውስጥ እንዲናገሩ አይፈቀድላቸውም ነበር። በመጽሐፍ ቅዱስ በሴቶች ላይ በጣለው እገዳ መሰረት ማለት ነው። እንዲሁም በእንግሊዝ እ.ኤ.አ በ1664 በሄንሊ ተምስ (Henli Tems) አንዲት ሴት በፓርላማ ተወገዘች። ምላሷ ወደ ውጭ ተስቦ በገበያ ቀን ከዛፍ ጋር ታስራ የተቀጣችበትን ምክንያት የሚገልፅ ወረቀት ተለጥፎባት ውሎ ነበር።[16]” በሌላ በኩል ኢትዮጵያዊቱ ሙሉ ደቦጭ እንዲህ ስትል ጽፋለች፡- “በኢትዮጵያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያኖች እስከ መቼ ድረስ እንደ ኦሪት ስርዓት ከወንጌል አግልለው ይኖራሉ? ሲሉ ጠይቀው የሚከተለውን አክለዋል። ቢያንስ ለውይይት ሴቶች ስለራሳቸው እንዲናገሩ መድረኩን ክፍት**

15 ቲም ፊሎስ፣ የኢዘፍ የጥናት ምርምርና ማብራሪያ፣ በትምህርት መስኮት ማስፋፊያ (ት.መ.ማ) መልክ የተዘጋጀ፤ ክፍል 1 ና 2 ጹሐፍ፡- ትርጉም በግርማዊ እርማት፣ በአባይ ደምሴና በዮናታን ብርሃኑ፣ የመጀመሪያዕትም 1987 ዓ.ም ገጽ 92

16 Maltida Joslin GegeWoman Church State 1893 Reprint Edltion 1972 308 -309

**ማድረግ ይኖርባቸዋል። ስለ ሴቶች በአግልግሎት መሳተፍ በምንነጋገርበት ጊዜ ‹ሾላ በድፍን› ለማድረግ ይሞክራሉ። ስለ መብታችሁ ጠየቃችሁን በማለት ሴቶችን አፍ ያስይዟቸዋል። ስለ መብት ጉዳይ መጠየቅም ሆነ መናገር ኃጢአት እንደሆነ ይቆጠራል። በመንፈሳዊያን ስም ሴቶች ዝም ብለው እንዲገዙ ቤተ ክርስቲያን ከማስተማር ሌላ የእግዜአብሔርን ቃል ለሰው ልጅ ነፃ የሆነ ተፈጥሮ አለ፤ ፍትህ አለ፤ እኩልነት አለ፤ ብለው የሚናገረውን በኢትዮጵያ ያሉት አብያተ ክርስቲያናት የሚያስተምሩት እምብዛም ነው ወይንም የለም ማለት ይቻላል።**[17]" ታዲያ በአሁኑ ሰዓት መናገር ማስተማር ማን መብት ሰጣቸው? ጳውሎስ እንዳይሉ ዝም ይበሉ ብሏል። ነው ወይስ ራሳቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ጥቅስ ሸረውት ነው? ተሸሯል እንዳይባል ደግሞ ጥቅሱ ያለው አዲስ ኪዳን ላይ ነው።

## 12) ‹‹<u>ሴቶች›› እውቀትን የመፈለግና የማስተማር መብት የሌላቸው መሆኑ</u>

በ1ኛ ቆረንቶስ 14፡34 ‹‹***<u>ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ አልተፈቀደላቸውምና ለሴት ማኅበር መካከል መናገር ነውር ነውና ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን ይጠይቁ።</u>***›› ሴቶች በተለያዩ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ክንዋኔዎች ከወንዶች እኩል ሊማሩ አልተፈቀደላቸውም። ሴት ልጆች በኢትዮጵያ ያለ መማር ምክንያትን በተመለከተ ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ ፕሮፔሰር ፓንክረስትን አጣቅሰው ሲናገሩ፡- **‹"በሌላ በኩል ሴት ከተማረች ዳዊቱን ደግማና ደፍታ ባሏን ልትረግመውና እድሜውን ልታሳጥር ስለምትችል መማር የለባትም።›**[18]" በሚል አጉል ኋላ ቀርነት የሆነ እምነት የተነሳ ሴት ልጆች ሊማሩ አለመቻላቸውን ገልጸዋል። ሀገራዊ ፈሊጦችም ተመሳሳይነት አላቸው። ለምሳሌ **‹የቄስ ሚስት አወቀች አወቀች ቢሏት ዳዊቱን ቀዳ አጠበች›፤ ‹ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ›** በማለት የሴቶችን ሞራል የሚያቋሽሹ ንግግሮችን ይሰነዝራሉ። ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡12-13‹‹***<u>ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይንም በወንድ ልጅ ላይ ልትሰለጥን አይፈቀድላትም። አዳም ቀድሞ ተፈጥሯልና</u>***

17 ሙሉ ደቦጭ፣ ጣዝሙት፣ የሴቶች አገልግሎት ቤተሰባዊና ማህበራዊ ገፅታው፣ ራዕይ አሳታሚ አዲስ አበባ 1993 ዓ.ም ገፅ 22

18 ቄሲስ ከፍ ያለው መራሒ፤ ሴቶች በኢትዮጵያ ገጽ 121

*በኃላም ሔዋን ተፈጠረች።»* ከምሁራን አንደበት ይህንን በመንተራስ ያሉትን ለአብነት ያክል፡- **‹“የሴት ልጅ ክብር በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ ሳይሆን ተገዥ መሆን ነው። ከወንድ ስልጣን ስር መሆንና በቤተ ክርስቲያን ፀጥ ማለት በፈጣሪ የተሰጠ ሥርዓት እንጂ የባህል ጉዳይ አይደለም። ይህንንም በትህትና መቀበል የሴት ልጅ ክብር ነው። ማመፅ ግን ውርደት ነው።**[19] **በማስከተልም እንግዲህ ሴቶች ወንጌላውያን እየመለመሉ በቤተክርስቲያን ማሰለፉ ዘመን አመጣሽ ጥራዝ ነጠቅ ሀሳብ ነው እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ድጋፍ ኖሮት አይደለም ይላሉ።**[20]” ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የሚያዝ ከሆነ የዘመናችን በተለይ የፕሮቴስታንት ሴቶች ወንጌል የሚያስተምሩት ምን ድጋፍ አግኝተው ነው? ያውም በወንጌል ሽፋን እየተባለ ወደ ዝሙት የሚገፋፋ ልብስ እየተለበሰ በስብከት ሽፋን ዘፈንና ጭፈራ እናያለን። ለበለጠ መረጃ በሲዲ የማቀርበው ይሆናል። የቪዲዮ ማስረጃው ምን መልእክት እንዳለው መረዳት ይቻላል። የሚገርመው ይህን ጥቅስ አላዩትም እንዳንል አዲስ ኪዳን ነው ያለውና ያዩት ይሆናል። ነው ወይስ አዲስ ኪዳንም ተሻረ? ጸሎት ጭፈራ ዳንስ በተመለከተ አምልኮ አይባልም። ያውም ወንድና ሴት በአንድ ላይ ሆነው ውጤቱን ምን እንደሚሆን ወደ የት እንደሚያመራ ራሳችሁ ገምቱ።

## 13) «ሴት ልጅ» የትዳር አጋሯን መምረጥ እንደማትችልና በግዴታ ሳትፈልግ እንደምታገባ

በመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ወንድማማቾች ቢኖሩና ከአንደኛው ጋር ፈለገችም አልፈለገችም አብራ በግዴታ መኖር እንዳለባት ያዛል። በኦሪት.ዘዳግም 25፡5 *«ወንድማማቾች በአንድ ላይ ቢቀመጡ፤ አንድም ልጅ ሳኖረው ቢሞት፤ የሞተው ሰው ሚስት ሌላ ሰው ታገባ ዘንድ ወደ ውጭ አትሂድ። ነገር ግን የባልዋን ወንድም ወደ እርሷ ገብቶ እርሷን ያግባ፤ ከርሷ ጋር ይኑር።»* ይህ ነው ያገሬ ገበሬ **‹ዋርሳ›** እያለ የሚተገብረው ከመጽሐፍ ቅዱስ የተማረውን ነው እንጂ ከቁርኣን የተገኘ አይደለም። ፈለገችም አልፈለገችም ከማግባት ውጭ አማራጭ የላትም። ከዚህ ምዕራፍ 22፡28-29 *«ማንኛውም ሰው ድንግልና ያላትን*

19 የቄስ ሀይለ መኮንን፤ የነኛና 2ኛ የቀረንቶስ የጥናት ማብራሪያና መምሪያ በትምህርት መለኮት ማስፋፍያ (ት.መ.ማ) ገጽ 69

20 የላይኛው ምንጭ ቁጥር 1 ገጽ 95

***ያልታጨች ልጃ አገረድ ቢያገኝ ወስዶም ቢደርስባት ቢያገኝበትም ያ የደረሰበት ሰው ሀምሳ (50) የብር ሰቅል ለብዕቴናይቱ አባት ይሰጥ፤ አስነውሯታልና ሚስትም ትሆነው በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ሊፈታት አይገባውም።***» ይህ አባባል በሀገራችን ያለውን ጠለፋ ያበረታተዋል። ምክንያቱም ጥፋቱን በገንዘብ ይዋጠዋልና። ሌላው ጥያቄ ሁለተኛ ሚስት ብትሆንም ታስራ መኖር ነው ያላት አማራጭ?

## 14) «ሴት ልጅ» የፍች ጥያቄ የመጠየቅ መብት የሌላት መሆኗ

ሴት ልጅ የትዳር አጋሯን የመረጠችውን ወንድ እንደማታገባና ያገባት ሰው የፍቺ መብት እንደማይሰጣት አይተናል። ብትፈታ እንኳ ሌላ እንዳታገባ ትደረጋለች። ከሌላ ሰው ወደ ሌላ ሰው ለማግባት አትሂድ የሚል ትዕዛዝ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሰጠ ማለት ነው። ከሴቶች መብቶች ውስጥ ፍቺ ይገኝበታል። ለዘላቂ ሕይወት ከወንድ ጋር በመጣመርና ጋብቻ በመመስረት ዘርን መተካት የሴት ልጅ ዲሞክራሴዊ መብት ነው። ነገር ግን ጋብቻው ሊሰምር ካልቻለ ያለው አማራጭ መፍታትና ሌላ ሰው ማግባት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከተፈታች ሌላ ሳታገባ መኖር እንዳለባት ነው የሚነግረን። በ1ኛ ቆረንቶስ 7፡10-12«***ሚስትም ከባሏ ጋር አትለያይ፤ ብትለያይ ግን ብትፈታ ሳታገባ ትኑር ወይንም ትታረቅ።***» ክርስቲያኖች ግን የተፈቱ ሰዎችን ሲያገቡ ይታያል ለምንድ ነው? አሁንም አዲስ ኪዳን ተሻረ? ነው ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ለመሸሽግ ፈልገው ይሆን?

## 15) «ሴቶች» የውርስ መብት የሌላቸው መሆኑ

ከዲሞክራሴዊ መብቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የውርስ መብት ይገኝበታል። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የውርስ መብት የሰጠው ለወንድ ብቻ ነው። በትንቢተ.ሕዝቄኤል 46፡16-18«***ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ርስቱም ለወንድ ልጅ ብቻ የሚተላለፍ ይሆናል፤ ገዥ ከንብረታቸው በማፈናቀል የትኛውንም የሕዝብ ርስት መውሰድ አይገባም፤ ለወንድ ልጅ ርስት መስጠት ያለበት ከራሱ ንብረት ነው።***» በቃ ሴቶች ምንም ነገር አያገኙም? ከቁጥር ስለማይገቡ ነው?

## 16) የተፈቱና ባሎቻቸው የሞቱባቸው «ሴቶች» መገባት እንደሌለባቸው

በኦሪት.ዘሌዋውያን 21፡7 «***ለአምላክ የተቀደሰ ነው ጋለሞታን ሴት ወይንም የረከሰችውን አያግባ ወይንም ከባልዋ የተፋታችውን አያግባ።***» በመጽሐፈ ምሳሌ 23፡27«***ጋለሞታ ሴት የበለጠች አዘቅት ናትና።***» ከዚሁም ምዕራፍ ***ልጄ ሆይ ስለምን ጋለሞታን ሴት ትወዳለህ?***» በዚህ ላይ ጳውሎስም ተመሳሳይ ሐሳብ ይመክራል። በ1ኛ ጢሞቲዎስ 5፡11«***ባል የሞተባቸውን ቆነጃጅት ግን አትቀበል፤ በክርስቶስ ላይ ተነስተው ሊቀማጠሉና ሊያገቡ ይወዳልሉና።***» አጋጣሚና የሰፈጣሪ ውስኔ ሆኖ ባል ሞተባት። ታዲያ ይህች ሴት ሌላ ባል ብታገባ ምንድ ነው ክፋቷ? ሲቀጥል ጋለሞታ ሴት መወደድ የለባትም እያለ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። አሁን እውን ይህ የአምላክ ቃል ነው?

## 17) የተፈታችን «ሴት» የሚያገባ ወንድ እንደ አመንዝራ መቆጠሩ

በሌላ ምዕራፍ መጽሐፍ ቅዱስ በዝሙት ምክንያት ብቻ መፈታት (ፍች) እንደሚቻልና ከዚህ ሌላ ምክንያት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ደንግጓል። በማቴዎስ ወንጌል 19፡9«***እኔ ግን እላችኋለሁ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሌላይቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል። የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።***» ያውም ኢየሱስ ነው የተናገረው ተብሎ ይታሰባል። ጳውሎስ ደግሞ ቆረንቶስ 7፡39«***ሴት በባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት።***» ጥያቄ ከሞተች በኋላ ትፈታለች ማለት ነው ወይንስ መቼ ነው የምትፈታው? ክርስቲያኖች የተፈታችን ሴት ስለሚያገቡ አመንዝራዎች ሆነዋል ማለት ነው። የተከለከላችሁትን ስለፈፀሙ ማለት ነው።

## 18) «ሴቶች» ለሚስትነት አለመፈለጋቸው

ጳውሎስ እንዲህ በማለት ያስተምራል፡- በ1ኛ ቆረንቶስ 7፡27«***በሚስትህ ታሰረህ እንደሆነ አትፍታት መፍታትን አትሻ። በሚስትህ ካሊታሰርክ እንደሆነ ሚስትን አትሻ (ሚስትን አትፈልግ)።***» ከዚሁ ምዕራፍ 32«***እኔስ ያለጭንቀት እንዳትኖሩ እወዳለሁ፤ ያላገባ ሰው ጌታን ደስ በማሰኘት ስለ ጌታ ነገር ያስባል። ያገባ ሰው ግን ስለሚስት ያስባል፤ ሚስቲቱን ደስ ለማሰኘት ስለዚህ አለም ነገር***

***ያሰባል***።» ከዚህ ላይ ሴቶች ወደ ፈጣሪ እንደማያደርሱ ነው የተገለጸው። ታዲያ ሁሉም ክርስቲያን ማለት ይቻላል ለምን ያገባሉ? ጌታን ደስ ለማሰኘት ያልፈለጉ ይሆን? ጳውሎስ የራሱን ሀሳብ በማንፀባረቅ አለማግባት ለጌታ ደስ ያሰኛል ብሏል።አምላክ ደግሞ በዘፍጥረት ላይ «***ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሏት***» ያለው። ታዲያ ጳውሎስ ለምን የአምላክን ንግግር ተቃረነ?

## 19) ኢትዮጵያውያን «ሴቶች» መግባት እንደሌለባቸው

መጽሐፍ ቅዱስ ሙሴ ኢትዮጲያዊት ሴትን በማግባቱ እንደተናገሩት እንዲህ ይገልፃል፡- በኦሪት.ዘኁልቁ 12፥1-2«***ሙሴም ኢትዮጲያይቱን አግብቷልና፤ ባገባት በኢትዮጵያይቱ ምክንያት ማሪያምና አሮን በእርሱ ላይ ተናገሩ***።» ምን ነው ኢትዮጵያዊ ሴቶች ተንቀው ነው ሙሴ በማግባቱ የነቀፉት? ስለዚህ የሀገራችን ሴቶች ዜግነት መቀየር አለባችሁ ማለት ነው?

## 20) «ሴት ልጅ» ባሏን «ጌታ» ብላ መጥራት እንዳለበት

ሴት ልጅ ከወንዶች የበታች ከመሆኗ የተነሳ ባሏን ጌታ ብላ መጥራ አለባት ይላል። መጽሐፍ ቅዱስ አስተምሯል፡- በ1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 3፥6 «***እንግዲህ ሳራ አብራሃምን ጌታ ብላ እንደጠራችውና እንደታዘዘችለት እናንተም ከሚያስደነግጥ ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈራ መልካም ብታደርግ፤ ባሎቻችሁን ጌታ ብላችሁ ብትጠሩ ልጆች ናችሁ***።» ስለዚህ ሴቶች ከፍርሀትና ከድንጋጤ ለመዳን የግድ ባሎቻቸውን ጌታ ብለው መጥራት ግድ ይሆንባቸዋል ማለት ነው።

## 21) «ሴት ልጅ» ባልዋን እንደ «ጌታ መገዛት» እንዳለባት

ትዳር ማለት በባልና በሚስት መካከል የተመሰረተና በእኩልነት የየራሳቸው የስራ ድርሻ ያላቸውና የጋራ ጥምረታቸውን የሚመሰርቱበት መንገድ እንጂ ሚስት ባልዋን እንደ ጌታዋ የምትገዛት ሁኔታ አይደለም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ሚስት ለጌታ እንዲሚገዙ ሁሉ ለባሎቻቸውም መገዛት አለባችሁ በማለት ጥብቅ መመሪያ ይሰጣል። ጳውሎስ ወደ ኤፌሶን ሰዎች በላከው መልእክት 5፥22 «***ሚስቶች ሆይ ለጌታ እንደምትገዙ ሁሉ ለባሎቻችሁም ተገዙ***።» ተጨማሪ ወደ ቆላይስያስ ሰዎች በላከው መልእክት 3፥18«***ሚስቶች ሆይ! ለጌታ እንደሚገባ***

<u>*ለባሎቻችሁም ተገዙ።»*</u>ቀላል እናድርገውና አንዲት ሴት ለአምላክ እንደምትፆመው፤ እንደምትሰግደው ለባሏም ይህን ማድረግ አለባት ማለት ነው? ይህ ከሆነ ደግሞ ወንዶች በሙሉ ለሴቶች አምላክ ሊሆኑ አይደል። ምክንያቱም ለጌታ እንደሚገባ ለባሎችም ይገባል ስለሚል በዚህ ጥቅስ ላይ በመንተራስ የክርስቲያን ምሁራን ምን እንዳሉ እንመልከት፡- **‹“ቅዱስ ጳውሎስ በእነዚህ ምዕራፎች ሕጎችን አረጋግጧል ሥርአቱ የማይለወጥ ነውና። የሴት ተገዥነት ዛሬም አልተሻረም ማለት ነው። ስለዚህ በቤተሰብ ውስጥ ራስ ገዥ ወንዱ እንደሆነ ሴቶች ይገንዘቡ[21]። ባሎቻቸውም እንኳ ሴቶች የሚገዙት ለጌታ ስለሆነ በትግስት መገዛት አለባቸው[22]። ቀጥሎም፡- እግዚአብሔር ባዘዛት ቦታ በታማኝነት ስታገለግል የእግዚአብሔር መንግስት በቤቱ ይሰፍናል። ልባም ሴት (በመጽሐፈ ምሳሌ 31፡10) *«ፈቃዷን ለባሏ ታስገዛለች፤ ውበቷ ማስገዛቷ ነው።›*› ይህንን ቅዱስ የእግዚአብሔር ሕግ ብትጥስ ግን የሰይጣን መንገድ ስለምትከተል ከጥፋት ልታመለጥ አትችልም። *ከባሏም ፈቃድ እንዳትወጣ አድርግ።›*› እንደ ክርስቲያን ምሁራን አገላለፅ ፡- እንደ እግዚአብሔር ቃል መሰረት አንዲት ሴት መልካም ሚስት የሚያደርጋት ምንድን ነው? መልሱ ራስዋን ለባልዋ ማስገዛት የምትችል ስትሆን ነው። በእርግጥ ይህንን ቃል ብዙ ሴቶች አይወዱትም። ስለሆነም ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ የሰጠውን ሐሳብ ለመለወጥ ብዙዎቹ የተለያዩ ትርጉም ሰጡት የሚሉ አሉ።[23]”**

## 22) **‹‹<u>ሴቶች</u>›› <u>የወርቅ ጌጣጌጥ መልበስ እንደሌለባቸው</u>**

ሴት ልጅ በወርቅ እንድታጌጥና እንድትለብስ መጽሐፍ ቅዱስ ይከለክላታል። በ1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡9-10«<u>*ሴቶች በሚገባ ልብስ በመልበስ በማፈርና በትሕትና ራሳቸውን ከማስገዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ (ይልበሱ)፤ እግዚአብሔርን እንፈራለን ለሚሉ ሴቶች እንደሚገባ መልካም በማድረግ እንጂ በሹርባና በወርቅ ወይም በእንቁ ወይም ዋጋው እጅግ በከበረ (ውድ በሆነ) ልብስ አይሸለሙ።*</u>» የ1980 ዕትም ደግሞ ፀጉሯን መሰራትን ይከለክላል። ዲያቆን አዲሱ ተፈራ ይህን

21 በመጀመሪያ የሐዋሪያው ጳውሎስ መልእክት ወደ ቆረንቶስ ሰዎች፣ ትርጉም 1954 ዓ.ም አ.አ ጎንደር ገፅ 90

22 ወርቁ ወልደ ዮሐንስ፣ ክርስቲያናዊ ጋብቻ 1985፣ ገፅ 118

23 ወርቁ ወልደ ዮሐንስ ክርስቲያናዊ ጋብቻ 1985፣ ገፅ 119፤ ቀሲስ ከፍ ያለው መራሒ ሴቶች በኢትዮጵያ 1988 ገፅ 2-3

ጥቅስ በመንተራስ እንዲህ በማለት ማብራሪያ ጽፈዋል፡- ‹“**ሴቶችም ልብሳቸው በሥርዓት የተያዘች አካላቸው በሚገባ የተሸፈነ ሊሆን ይገባል። እንዲሁም ደግሞ ሴቶች በሚገባ ልብስ በአፍረትና ራሳቸውን ከመግዛት ጋር ሰውነታቸውን ይሸልሙ። እግዚአብሔር እንፈራለን ለሚሉ ሰዎች እንደሚገባ መልካም በማድረግ እንጂ በሹሩባና በወርቅ ወይም በእንቁ ወይም ዋጋው እጅግ የከበረ ልብስ አይሸለሙ።› 1ኛ ጢሞቲዎስ 2፡9-10 ተብሎ እንደተነገረ የእግዚአብሔር የሆኑ ምዕመናን ቃሉን ያከበራሉ በማክበራቸውም በረከትን ይቀበላሉ። የእግዚአሔር ያልሆነ ግን ከዚህ ቃል በተቃኒም ለሰውነታቸው የማይገባ ልብስን በመልበስ በመገላለጥ እንስሳዊ ፀባያቸው ቢያንፀባርቁ አፍረት የሆነ ስራ በመስራታቸው ነፍሳቸውን ያጎሳቁታል።**[24]”› በተለይም በአሁኑ ሰዓት ይቅርና በሹሩባ መሰራት ጣጠው ሌላ ነው። ለምሳሌ፡- የጆር፣ የእጅ፣ ወ.ዘ.ተ. ወ.ዘ.ተ. በማለት እጅግ ዋጋው ውድ በሆነ ገንዘብ ያጌጣሉ። ይህቺ ጥቅስ እኮ የምትመለከተው እናንተን ክርስቲያን ሴቶችን ነው። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በማፈርና በትህትና እያለ ሴቶች ግን በተቃራኒው የሰይጣን መልእክተኛ በመሆን ሰውነታቸውን ገላልጠው በመሄድ የእንስሳነት ኑሮ የሚኖሩ በርካታ የክርስቲያን ሴቶች አሉ። በየቦታው እራሳችሁ ተመልከቱ ምን እንደሚመስሉ። አልፎ ተርፎም የሙስሊም ሴቶችን ለምን ተሸፋፈናላችሁ በማለት? የሚያፌዙና ስልጣኔ መስሏቸው የሚተቹ አሉ። ይህ ግን ስልጣኔ ሳይሆን ሰይጣንነት ነው። ሀፍረተ ገላውን ለማንም ማሳየትን በምሳሌ ብናየው ልክ የተላጠ ሙዝ የሆነ ቦታ ቢጣልና ያልተላጠ ሙዝ የሆነ ቦታ ላይ ቢጣል የትኛው ነው ዝንብ የሚወረው? የተላጠውን ሙዝ ዝንብ ብቻ አይደለም፤ ሁሉም ነፍሳት ይወረዋል። እንደዚሁ ራሷን ገላልጣ የምትሄድ ሴት ሁሉም ሥርዓት ያጡ ወንዶች ይወሯታል፤ በየመስመሩ ምን እንደሚባሉ ራሳቸው ያውቁታል። ስለዚህ ስልጣኔ ማለት ራስን መሸፈን ነው።

## 23) <u>የወር አበባ ያየች «ሴት» የረከሰች መሆኗ</u>

በኦሪት.ዘሌዋውያን 2፡2-8‹‹***<u>ሴት አርግዛ ወንድ ልጅ ብትወልድ በወር አበባዋ እንደሚሆን አይነት እስከ ሰባት (7) ቀን የረከሰች ትሆናለች።</u>***›› ከዚሁ ምዕራፍ

24 ከዲያቆን አዲሱ ተፈራ አለባባሳችን ከማንነታችን አንፃር------1998 ዓ .ም ገፅ 29

15፡19-22«*ሴት ጊዜውን እየጠበቀ የሚመጣው የደም መፍሰስ ቢኖርባት፤ የወር አበባዋ እርኩሰነት እስከ ሰባት ቀን ይቆያል። በዚህም ጊዜ ምንም ሰው ቢነካት እስከ ማታ ድረስ እርኩስ ይሆናል። የተቀመጠችበትም ማንኛውም ነገር የነካው ሰው ልብሱን ይጠብ፤ ሰውነቱንም በውኃ ይታጠብ፤ እስከ ማታ ድረስ እርኩስ ይሆናል*።» አንዳንድ የክርስቲያን ምሁራን በዚህ ጥቅስ በመንተራስ እንዲህ ጽፈዋል፡- “**ሴቶች በወር አበባ ጊዜ ውጫዊ የኃጢአት ምልክቶች ነበሩ። ስለዚህ ከዚህ ለመንፃት መስዋዕት ይፈልጉ ነበር።**[25]” ጥያቄ ሰውነቷ በሙሉ እንዴት በቁሟ የረከሰች ትሆናለችን? እርኩስነቷን የነካ ሰው እንዴት በፍጥነት በሌላኛው ሰው ተላለፈ? ቆይ እርኩስነታቸው የኤሌክትሪክነት ባሕሪ አለበት ማለት ነው? ከዚህም በላይ የተቀመጠችበት መሬትም እርኩስ መሆኑ ተጠቅሷል። ይህ ብቻ አይደለም፤ ወደ ምድርም ይተላለፋል። ብዙ ጥያቄ ማንሳት ይቻላል ነገር ግን መልስ ከሌለው ለአንባቢያ ትቶ ማለፍ የተሻለ ነው።

## 24) «ሴት» በመሆኗ በእናትነትም ቢሆን ክብር እንደሌላት

የሚገርመውና ኢየሱስ እናቱን እንዳመናጨቃት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል። በዮሐንስ ወንጌል 2፡2«*ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- አንቺ ሴት ከአንቺ ጋር ምን አለኝ?*» አስቡት ያውም እናትን በአሁኑ ሰዓት እንኳ ይህን ያክል እናቱን የሚያመናጭቅና በዚህ ቃል ተጠቅሞ ይጠራል የሚል ግምት የለኝም። አምላክ የረገመው ካልሆነ በስተቀር ነገር ግን እኛ ሙስሊሞች ይህን የተከበረ የአላህ ነብይ የአላህ ሰላም በእሱ ላይ ይሁንና ይህን ቃል ይናገረዋል ብለን አንደፍርም። በፍፁም እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ገለፃ ሙስሊሞች ነፃ ነን። ምክንያቱም ኢየሱስን ስለምነወደውና ስለ ምናከብረው ይህን ንግግር እርሱ ይናገረዋል ብለን እኛ ሙስሊሞች አንደፍርም።

## 25) ወንድ ባጠፋው «ሴት» የምትቀጣ መሆኗ

አንዱ ባጠፋው ሌላው መቀጣት የለበትም ምክንያቱም ከፍትህ አንፃር ሲታይ የዓለማት ፈጣሪ ፍርደ ገምድል ዳኛ አይደለም። ሆኖም ግን መጽሐፍ ቅዱስ አንዱ የሌላውን ሚስት ለመከጀል ሲል የራሱን ሚስት እህል እንድትፈጭ ያዛል።

[25] ቲም ፊሎስ የብሉይ ኪዳን የጥናት መምሪያን ማብራሪያ፤ ገፅ 297

በመጽሐፈ ኢዮብ 31፡9-10«***ልቤ ሴላዋን ሴት ከጀሎ ባልንጀራዬ ደጃፍ ገብቼ ከሆነ፤ ሚስቴ የሌላ ሰው እህል ትፍጭ፤ ሌሎች ሰዎችም ይተኗት (ይገናኟት)።***» ከፍርድ አንፃር ብንሄድ ወንዱ ነው ከሌላ ሚስት ለዝሙት የሄደው። ታዲያ የሚስቲቱ መቀጣት እንዴት አዕምኖ ይቀበለዋል? ከፍርድ አንፃር ስንሄድ ‹***አይጥ በበላ ዳዋ ተመታ***› አይሆንም?

## 26) «**ሴት ልጅ**» **በእሳት ተቃጥላ መሞት እንዳለባት**

ይህ ቅዱስ የተባለው መጽሐፍ እውን ቅዱስ የሚያሰኙ ነገሮች በውስጡ የሉበትም። ወንድ ባጠፋ ሴት መቀጣት እንደሌለባትና በእሳት ተቃጥላ መሞት የሴት ልጅ ብቸኛ እጣ ፈንታ ሆኗል። የእምነቱ ተከታዮች ሰዎች ለምን እንደማያገቡ አይገባኝም። ደግነት ይህን አስደንጋጭ ጉዳይ ማየት አሳፍሯቸው ይሆን እንዳንል እስልምና ሙስሊም ሴቶችን ይበድላል ይላሉ። ‹**ዝንጀሮ የራሷን ገጣባ ሳታይ በሰው ትስቃለች**› አሉ። ሚስጢር የሚባለው ሽፋን ከዚህ ላይ አይሰራም። በኦሪት.ዘሌዋውያን 21፡9 «***የካህን ሴት ዝሙት አዳሪ ሆና ራሷን ስታረክስ አባቷን ታረክሰዋለች፤ በእሳት ትቃጠል።***» ይህ ከሆነ በየቡና ቤቱና በየጭፈራ ቤቱ ራሳቸውን የሚያረክሱ ሰዎች ይህ አንቀጽ አላዩትም ይሆን? መልሱን ለዝሙተኛ ክርስቲያኖች ትቻለሁ። በኦሪት.ዘፍጥረት 38፡15-24 ያለውን ብንመለከት ይሁዳ በልጁ ሚስት ላይ ዝሙት እንደሰራ ይናገራል። ማርገዟን ሰዎች በነገሩበት ጊዜ፡- «***ወደ ውጭ አውጥታችሁ በእሳት አቃጥላችሁ ግደሏት***» አለ። ከፈሊጣዊ አባባሎች ‹**ለሴት ዱላ ለአህያ ዳውላ**› የሚሉት የአገራችን ክርስቲያኖች ይህን ጥቅስ ተመርኩዘው ይሆን? ይሁዳ በልጅ ሚስት ላይ የሰራው ራሱ ነው።

## 27) «**ሴቶችን**» **የሚያገቡ ወንዶች ገነት እንደማይገቡ**

ኢየሱስ እንደ ሉቃስ ወንጌል አባባል ከሙታን ትንሳኤና ገነት ሊገቡ ሊያገኙ ከሚገባቸው ሰዎች መካከል ሴቶችን የማያገቡ መሆናቸውን መስክሯል። በሉቃስ ወንጌል 20፡34-36«***የዚህ ዓለም ሰዎች ያገባሉ ይጋባሉ፤ ያን ዓለምና ከሙታን ትንሳኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አይገቡም፤ አይጋቡም፣ እንደመላክት ናቸው፤ ሲሞቱም ወደፊት አይቻላቸውም፤ የትንሳኤ ልጆች ስለሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።***» ጥያቄ ያልተጋቡ ሰዎች መንግስተ ሰማያት

የሚገቡ ከሆነ በዘፍጥረት ***«ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሏት»*** ያለው አምላክ ገነት እንዳትገቡ ፈልጎ ነው? ስለዚህ ያገቡ ክርስቲያኖች በሙሉ ከስረዋል ማለት ነው። ክርስቲያን ሆኖ ያላገባ ሚስት ያላገባ የለም። ኢየሱስ ለኛ ቤዛ ሆነ ያላችሁት አባባል ውሸት ሆኖ ተገኘ ማለት ነው።

## 28) ከዳኑት ወንዶች ውስጥ «ሴቶች» የሌሉ መሆናቸው

በመጽሐፍ ቅዱስ ሴቶች የኃጢአት ምንጭና መገኛ ናቸው ሲል በጣም ዲካ የዘለለ ክብራቸው ሲነካና በማንቋሸሸ በእሳትም ተቃጥላ እንድትሞት እንደፈረደበት እርሷም ገነት እንደማትገባ ይናገራል። በዮሐንስ ራእይ 14፡1-5 ***«አየሁም እነሆም በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፤ ከነሱ ጋር ስሙና የአባቱ ስም የመንፈስ ቅዱስ ስም በግንባራቸው የተፃፈባቸው መቶ አርባ አራት ሺህ (144,000) ነበሩ። ከምድር ከተዋጀች (ከዳኑት) ከመቶ አርባ አራት ሺ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም። ከሴቶች ጋር ያልረከሱና ከአፋቸውም ውሸት አልተገኘም።»*** ጥያቄ ከ144,000 የጸኑት ወንዶች ብቻ ከሆኑ ለሴቶች ቦታ የለም? ይህ ከሆነስ ያሁኖቹም ክርስቲያኖች የይዞታ ማረጋገጫ የላችሁም ምክንያቱም ቦታው ተይዟል። አሁን ያለው የዓለም ክርስቲያን የት ይገባ ይሆን ሲያል? ማጠቃለያ ሁሉም ክርስቲያን ነኝ የሚል ሰው ሁሉ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነበው ጥሪየን አስተላልፋለሁ። በመቀጠልም እያንዳንዱን ንግግሬን ማየት ትችላላችሁ፤ ይህ ንግግሬ ከመጽሐፍ ቅዱስ የተገኘ እንጂ እናንተን የመተቸት አባዜ ተጠናውቶኝ አይደለም። በእርግጠኝነት እናንተ ካነበባችሁት ከዚህ የበለጠ መረጃ እንደምታገኙ አልጠራጠርም። እንዲሁም ደግሞ ያላችሁበትንም ፈትሹ፤ መንግስተ ሰማያት እንድትገቡ እንጂ የሲያል ጓደኛ ለማድረግ ሐሳቡ የለኝም። አንብቡት፤ አንብቡት የሁልጊዜም ምክሬ ነው።

# ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

## መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ የፈጣሪ ቃል ነውን?

የሰው ልጅ የተፈጠረለትን ዓላማ ተገንዝቦ ለመረዳትና ትዕዛዝና ፍላጎት እንዲኖር ይጠበቅበታል። ፈጣሪን በሚገባ ለመረዳትና በትክክል እሱን ብቻ ለመገዛት ለሰው ልጅ መለኮታዊ ሥርዓትና ሕግጋት ያስፈለጉታል። ይህ መለኮታዊ መመሪያ ወይንም የፈጣሪ ቃል በየዘመኑና በየቦታው ለሚኖሩ ሕዝቦች ይጠቅም ዘንድ በአንድ ወጥ በሆነ መዝገብ ተዘግቦ መቀመጡ ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል። ይሁን እንጂ በአንድ ወጥ መዝገብ መጠረዙ ቅርብ ክትትልና አስተማማኝ ጥበቃ ካልተደረገለት በስተቀር የፈጣሪ ቃል በሰዎች ቃል ሊቀየር፤ሊጨመርበት ወይም ሊቀነስበት ይችላል። ይህ ከሆነ ደግሞ መለኮታዊ (ሰማያዊ) ሕግጋቱ ይቀርና ምድራዊ (የሰዎች) ሕግ ሆኖ ይቀራል። በጥቅሉ የሁሉ ነገር ፈጣሪና ተንከባካቢ የሆነው የዓለማት ጌታ ከክብርነቱ የተነሳ መዝገቡም "**ቅዱስ**" መሆን ይኖርበታል። አፀያፊ ዘግናኝና አስከፊ ቃላቶች ወይም ንግግሮች አይጠበቁበትም። የሰውን ልጅ በጾታ፣ በዘርና በሀገር የማይከፋፈል መሆን አለበት። የፈጣሪ ቃል የግለሰቦችን ፍላጎት አስተያየትና አመለካከትን ለማንፀባረቅ ነፃ መሆን ይኖርበታል። ሕጎቹና ደንቦቹ የግለሰቦችን ፍላጎት ለማርካት ሲባል በየቦታውና በየጊዜው የሚለዋወጡ መሆን የለባቸውም። በአጠቃላይ እነዚህንና ሌሎችንም መስፈርቶች ግምት ውስጥ በማስገባት "**መጽሐፍ ቅዱስ**" ሙሉ ለሙሉ የፈጣሪ ቃል ነው? ብለን እንጠይቅ ከዚያም መጽሐፉን እንመርምረው። ለመሆኑ የሚከተሉት ነጥቦች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መኖራቸውን ያውቃሉን?

- ✓ የሴትን ልጅ ጡት ለስሜት አነሳሽነት መጠቀም፤
- ✓ በሰዎች ዘንደ እንኳን ፊት ለፊት የማይነገሩ አፀያፊ ቃላቶችን መጠቀም፤
- ✓ ዲቃላ ወይም ብልቱ የተቆረጠ ሰው ለጸሎት ወደ ፈጣሪ ቤት እንደማይቀርብ፤
- ✓ ከግብረ ስጋ ግንኙነት (ሕጋዊ ባልና ሚስት መካከል) በኋላ የዘር ፍሬው የፈሰሰ ሰው ቢታጠብም ለተወሰነ ጊዜ የረከሰ መሆኑን፤
- ✓ የአንዲት ሴት ልጅ ባል ቢሞት ሴትየዋ ሌላን ሰው ማግባት እንደማትችልና የሟቹ ወንድም በግድ እንደሚያገባት፤ የሚወለደውም የመጀመሪያ ወንድ ልጅ በሟቹ መጠራት እንዳለበት፤ የሟች ወንድም

ለማግባት ፈቃደኛ ባይሆን የሚቹ ሚስት ህዝብ ፊት የእግሯን ጫማ በማውለቅ ምራቋን በፊቱ ላይ እንደምትተፋ፤

- ✓ አራማዊያን ኃጢአተኞች እንደሆኑና አይሁዳውያን ግን ፃድቃኖች እንደሆኑ፤
- ✓ የነቢዩ አብራሃም (ኢብራሂም) ልጆች አንዱን ማክበር (ማሞገስ) ሌላውን መንቀፍ (መናቅ)፤
- ✓ ነቢዩ እስማኤል=> የአገልጋዩቱ ልጅ የተወለደው በስጋ ልማድ፤
- ✓ ነቢዩ ኢስሐቅ=>የነፃይቱ ልጅ የተወለደው በተስፋ ቃል፤
- ✓ የአሕዛብ ሕዝብ በአይሁዳዊያን ዘንድ አገልጋይና የበታች መሆናቸውን፤
- ✓ ለእስራኤሎች የዕዳ ስረዛ እንደሚኖርና ከሌሎች ግን ወለድ መቀበል የግድ መሆኑን፤
- ✓ 144,000 ጽዮናዊያኖች ድንግል በመሆናቸው ምህረት እንዳገኙና ሴትን ባለመገናኘታቸው ያልረከሱ መሆናቸው እንደተመሰከረላቸው፤
- ✓ ፈጣሪ ያለምንም ርህራሄ ሽማግሌ፣ አሮጊት፣ ወጣት፣ ኮረዳና ህፃንም ጭምር እንዲገደሉ ትዕዛዝ ማስተላለፍን፤
- ✓ ሕዝብ በፈጣሪ ላይ ያለውን እምነት እንዲተው ያደረጉ ሴቶች መሆናቸውን፤
- ✓ ኢየሱስ የመጣው እሳትን፣ ሰይፍንና መለያየትን እንጂ ሰላምን ለማምጣት እንዳልሆነና ዘመድ ለዘመድ ለማጣላት እንደመጣ፤
- ✓ ኢየሱስ ጠላቶቹ በፊቱ ላይ እንዲረሸኑ ማመልከቱን፤
- ✓ ወንጌል የተፃፈው ስለ እምነቱም ሆነ ስለ ታሪኩ ሙሉ ዕውቀት ባላቸው ግለሰቦች ሳይሆን በራዕይና በግምት እንደተፃፈ፤
- ✓ መጽሐፍ ቅዱስ ተራ የግል ደብዳቤ (መልእክት) እንዳካተተ "... አንተ ዘንድ የተውካትን ካባ ይዘህልኝ ና..."
- ✓ ወንድም ሆነ ሴት ሳያገቡ መኖር መልካም እንደሆነ ጳውሎስ የራሱን አስተያየት መስጠቱን፤
- ✓ በክርስቶስ ማመን ብቻ ነው እንጂ ህግን መተግበር ትርፍ እርግማን እንጂ ጽድቅ እንዳልሆነ፤
- ✓ ጳውሎስ የሙሴን ሕግ በመሻሩ ሐዋሪያቶች እንደነቀፉት፤

✓ የጳውሎስ አስመሳይ ሆኖ መኖርና ክፍንና ደጉን መለየት እንዳቃተው፤

እነዚህንና ሌሎችም ተመሳሳይ አሳፋሪ ቃላቶች፣ ሐረጎችና ዓ/ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተካተው እናገኛቸዋለን። ለማስረጃ ይሆነን ዘንድ የሚከተሉትን አንቀፆች እንመልከት።

## አፀያፊ ንግግሮች

በ2ኛ መጽሐፈ ነገሥት 18፡27 ‹‹***ልክ እንደ እናንተ ኩሳቸውን ለመብላትና ሽንታቸውን ለመጠጣት***...።››

ወደ ዕብራዊያን መልእክት 12፡8 ‹‹***ልጆች የሆኑ ሁሉ የሚቀበሉትን ቅጣት እናንተ ካተቀበላችሁ ዲቃሎች እንጂ ልጆች አይደላችሁም***።››

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 23፡20 ‹‹...***ብልቶቻቸው እንደ አህያ ዘራቸውም እንደ አለሌ ፈረስ ሆኖ በፍትወት ለሚቃጠሉ ወንዶች ተማረከች***።››

## ሁለት ሰዎች ተጣልተው የአንደኛው ሚስት በምታግዘው ላይ የተሰጠ ፍርድ

በኦሪት.ዘዳግም 25፡11 ‹‹*ሁለት ሰዎች ተጣልተው በሚተናነቁበት ጊዜ የአንደኛው ሚስት ባሏን ለማገዝ የሌላን **ሰው ብልት ብትጠመዝዝ ምሕረት** ሳይደረግላት እጇ ይቆረጥ*።››

## የአምላክ ፍርደ ገምድል ዳኝነት

በኦሪት.ዘዳግም 23፡1-2 ‹‹***ቈላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ። ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ። በብልት መቀጥቀጥ ወይም በመቆረጥ ምክንያት ጃንደረባ የሆነ ሰው ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ ገብቶ አይቆጠር። ከጋብቻ ውጭ ዲቃላ ሆኖ የተወለደና የእርሱም ዘር ሆኖ የተወለደ ሁሉ እስከ አሥር ትውልድ እንኳ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ጉባኤ ገብቶ አይቆጠር***።›› ይህ ሰው የአምላክ ውሳኔ ሆኖ አጋጣሚ ብልቱ ተቆረጠ። ታዲያ ይህ ሰው ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ የማይገባበት ምክንያት

ምንድን ነው? ብልት እኮ የእጅ ጥፍር አይደለም። ስለዚህ የሰው ልጅ አካሉን ሆን ብሎ ቆርጦ አይጥልም።

## የሴት ልጅ ጡት ለስሜት አነሳሽነት

በመጽሐፈ መኃልይ መኃል ዘሰለሞን 1፡12-16 *‹‹ሙሽራይቱ፣ ንጉሱ በድንክ አልጋው ላይ አረፍ ብሎ ሳለ፤ የሽቶዬ መዓዛ ቤቱን ሁሉ ሞላው። ውዴ በጡቶቼ መካከል ሲያርፍ፤ መዓዛው እንደ ተቋጠረ ከርቤ ነው። … ውዴ ሆይ አንተ እኮ ውብ ነህ እጅግ ደስ ታሰኛለህ፤ አልጋችንም እንደ ለምለም ሳር ደስ የሚያሰኝ ነው፡››*

## ከግብረ ስጋ ግንኙነት በኋላ

በኦሪት.ዘሌዋውያን 15፡16-18 *‹‹ማንም ሰው ዘሩ ከአባላዘሩ ወጥቶ በሚፈስበት ጊዜ መላ ሰውነቱን ታጥቦ እስከ ማታ ርኩስ ይሆናል። ዘሩ የፈሰሰበትን ማንኛውም ልብስም ሆነ ቆዳ ውኃ ይታጠብ፤ እርሱም እስከ ምሽት ድረስ ርኩስ ይሆናል። ሴትና ወንድ አብረው ተኝተው በሚነሱበት ጊዜ ሁለቱም ሰውነታቸውን በውኃ ታጥበው እስከ ምሽት ድረስ የረከሱ ይሆናሉ፡፡››*

## የባሏን ወንድም ለጋብቻ ጠይቃ እንቢ ካላት የተሰጠ ፍርድ

በኦሪት.ዘዳግም 25፡4-6 *‹‹ሁለት ወንድማማቾች በአንድ ርስት ላይ ቢኖሩና አንደኛው ልጅ ሳይወልድ ቢሞት የሟቹ ሚስት ከቤተሰብ ውጭ ለሆነ ሌላ ሰው በጋብቻ ተላልፎ ልትሰጥ አይገባም። ምክንያቱም <u>የሟቹ ወንድም እርሷን የማግባት ግዴታ አለበት</u>። ይህም በሚሆንበት ጊዜ በመጀመሪያ የሚወለደው ወንድ ልጅ በሟቹ ሰም ይጠራል፡፡››* ከዚሁ ምዕራፍ 25፡7-9 *‹‹የሟቹ ወንድም ለማግባት ባይስማማ ግን፡- "ነገር ግን የሟቹ ወንድም እርሷን ለማግባት ባይፈልግ፤ ወደ ከተማይቱ መሪዎች ዘንድ ሄዳ "የባሌ ወንድም ግዴታውን ለመፈፀም ፈቃደኛ አልሆነም ለሟቹ ወንድም በእስራኤል ሕዝብ መካከል ዘር ማቆምን እምቢ ብሎ አለ" በማለት ታርዳ። ከዚህ በኋላ የከተማይቱ መሪዎች ሰውዬውን ጠርተው ያነጋግሩት፤ አሁንም እርሷን ለማግባት ፈቃደኛ አይደለሁም*

*ቢል የሟቹ ሚስት በከተማይቱ መሪዎች ፊት ወደ እርሱ ትቅረብ፤ ከእግሩ ጫማዎች አንዱን አውልቃ ምራቅዋን በፊቱ ላይ በመትፋት ...።»*

## የጳውሎስ ዘረኝነትና ስለ አብራሃም ልጅ የሰጠው የውንጀላ ፍርድ

ወደ ገላቲያን ሰዎች በላከው ደብዳቤ 2፡15 *«በእርግጥ እኛ በትውልዳችን አይሁዳዊያን ነን እንጂ እንደ ኃጢአተኞች አረማውያንም አይደለንም።»* ከዚሁ ምዕራፍ 4፡22-31 *«በሕግ መጽሐፍ "አብራሃም ሁለት ልጆች ነበሩት፤ አንደኛው የተወለደው ከአገልጋይቱ ሴት ሲሆን ሌላው የተወለደው ከነፃይቱ ሴት ነበር።" ተብሎ ተጽፏል። አገልጋይቱ ልጅ የተወለደው በስጋዊ ልማድ ሲሆን የነፃይቱ ልጅ የተወለደው ግን በተስፋው ቃል መሰረት ነበር... ነገር ግን መጽሐፍ የሚለው ምንድን ነው? መጽሐፍ "አገልጋይቱ ሴት የወለደችው ልጅ ነፃይቱ ሴት ከወለደችው ልጅ ጋር አብሮ ስለማይወርስ አገልጋይቱ ከነልጇ ወዲያ አስወጣት" ይላል። ስለዚህ ወንድሞቼ ሆይ እኛ የነጻይቱ ልጆች ነን እንጂ የአገልጋይቱ ልጅ አይደለንም።»* አስወጣት የሚለው የአምላክ ቃል ወይንስ የጳውሎስ ትእዛዝ?

## ስለ ብድር ማስመለስና ወለድ መብላት እንደሚቻል የተሰጠ ፍርድ

በኦሪት.ዘዳግም 15፡2-3 *«...ለእስራኤል ወገኑ ገንዘብ ያበደረ ማንኛውም ሰው ዕዳውን በመሰረዝ ይተውለታል። ዕዳውን እንዲተውለት ያዘዘ ራሱ እግዚአብሔር ስለሆን ገንዘቡን ለመሰብሰብ አይሞክር። ለውጭ አገር ባዕዳን ያበደራችሁትን ገንዘብ ብቻ መሰብሰብ ትችላላችሁ። ወገኖቻችሁ ለሆኑት እስራኤላዊን ያበደራችሁትን ገንዘብ ግን አትሰብስቡ። እስራኤላዊ ወገንህ ገንዘብ ብታበድረው ወይም ምግብ የሚሆንና ሌላም ነገር ብትሰጠው ወለድ አትጠይቀው። ወለድ መጠየቅ የሚገባህ ከውጭ ሀገር ተወላጅ እንጂ ከእስራኤላዊያን ወገንህ አይደለም።»* ምን ነው ዶላር ስለጨመረ ወይንስ የውጭ ሀገር ዜጋ ሀብታም ስለሆኑ?

## በአሕዛብ ሕዝብ ላይ የተሰጠ ፍርድ

በትንቢተ.ኢሳይያስ 49፡22-23 *«ልዑል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- እጄን በማንሳት ለአሕዛብ ሁሉ ምልክት እሰጣለሁ። ወንዶችና ሴቶች ልጆችሽን ታቅፈው ያመጡልሻል። ነገሥታት አሳዳጊ አባቶችሽ ይሆናሉ። እቴጌዎቻቸውም*

***ምግዚቶችሽ ይሆናሉ። ግንባራቸውንም ወደምድር ዝቅ አድረገው ይሰግዱልሻል። የእግርሽንም ትቢያ ይልሳሉ።*** ከዚሁ ምዕራፍ 61፡5-6 ***«-ሕዝቤ ሆይ! የባዕድ አገር ሕዝቦች አገልጋዮቻችሁ ይሆናሉ። ስለዚህም እነርሱ መንጎቻችሁን ይጠብቃሉ። ምድራችሁን ያርሳሉ፤ የወይን ተክሎቻችሁንም በመንከባከብ ይጠብቃሉ። የአሕዛብንም ሐብት ትበላላችሁ።»***

## ምህረት የተደረገላቸው (የተዋጁ) 144,000 ጽዮናዊያኖች ብቻ መሆናቸው

በዮሐንስ ራእይ 14፡1-4 ***«ከዛህ በኃላ እነሆ በጉ በጽዮን ተራራ ላይ ቆሞ አየሁ። ከእርሱ ጋር የእርሱ ስምና የአባቱ ስም በግንባራቸው ላይ የተፃፈባቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች ነበሩ። ከሰማይም የታላቅ ፏፏቴ ውሃ ድምጽና የታላቅ ነጎድጓድ የመሰለ ድምጽ ሰማሁ። የሰማሁትን ድምጽ በገና ደርዳሪዎች በገና እየደረደሩ የሚያሰሙትን ድምጽ ይመስል ነበር። በዙፋኑና በአራቱ እንሰሶች በሽማግሌዎችም ፊት መቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች አዲስ መዝሙር ዘመሩ። ይህ መዝሙር ከምድር ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ ሰዎች በቀር ማንም ሊማረው አልቻለም። እነርሱ ድንግሎች ስለሆኑ ከሴቶች ጋር በግብረ ሥጋ በመገናኘት ያልረከሱ ናቸው። ከሰዎች መካከል የተዋጁ ናቸው።»*** ለሌሎች ሰዎች ቦታ ተይዟል ማለት ነው?

## በሕፃናት፣ በአሮጊቶች በሌሎችም ሰዎች የተሰጠ የሞት ፍርድ

በትንቢተ.ሕዝቅኤል 9፡5-6 ***«እንደገናም እግዚአብሔር ሌሎቹን ሰዎች እንዲህ ሲላቸው ሰማሁ፡- "በሉ እናንተም እርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ ውስጥ በመዘዋወር ሁሉንም ግደሉ። ለማንም በመራራት ምህረት አታድርጉ። ሽማግሌ ሆነ ወጣት አሮጊት ሆነች ኮረዳ ሕፃናትም ሳይቀሩ ሁሉንም ግደሉ።»"*** ይህ ሐረግ ኢየሱስ ለሰው ልጆች ኃጢአት ብሎ ተሰቀለ ከሚለው ጽንስ ሐሳብ ጋር ይቃረናል። በተጨማሪ በኦሪት.ዘኅልቁ 31፡1-18 ***«እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፡- በእስራኤል ሕዝብ ላይ ስለፈፀሙት በደል ምድያማውንን ቅጣ! ይህንን ካደረግህ በኋላ አንተ ትሞታለህ። ስለዚህ ሙሴ ሕዝቡን እንዲህ አለ፡- ምድያማውያንን በእግዚአብሔር ላይ ስለ ፈጸሙት በደል በእነርሱ ላይ አደጋ ጥላችሁ ትቀጡአቸው ዘንድ ለጦርነት ተዘጋጁ። ከእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ***

*አንድ ሺህ ወንዶች መርጣአችሁ ወደ ጦርነቱ ላኩ። እነርሱም እግዚአብሔር ሙሴን ባዘዘው መሰረት በምድያማዊያን ላይ አደጋ ጥለው ወንዶችን በሙሉ ገደሉ። ሙሴ ግን ከጦርነቱ ከተመለሱ በጭፍራ አለቆች በሺህ አለቆችና በመቶ አለቆች ላይ ተቆጣ። እንዲህም ሲል ጠየቃቸው፡- ሴቶችን በሙሉ በሕይወት ያስቀራችሁት ለምንድ ነው? ሕዝቡ በእግዚአብሔር ላይ ያላቸውን፤ እምነት እንዲተው ያደረጉት ሴቶች መሆናቸውን ዘነጋችሁን? ስለዚህ አሁን እያንዳንዱ ወንድ ልጅና እያንንዲቱን ከወንድ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የሆኑትን ሴቶች በሕይወት እንዲኖሩ አድርጋችሁ ለራሳችሁ አስቀሩ።»* በመጽሐፈ መሣፍንት 21፡10-12 *«"ጉባኤው ወደ የቤሽ ሄዳችሁ ሴቶችንና ልጆችን ጭምር ሁሉንም ግደሉ፤ ወንዶችንና ድንግል ያልሆኑትን ሴቶች በሙሉ ግደሉ" የሚል መመሪያ በመስጠት ከመካከቸው ምርጥ የሆኑትን አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎችን ላኩ። ስለዚህም እነርሱን በከንዓን ምድር በሴሎ ወደሚገኘው ሰፈር ይዘው መጡ።»*

## ኢየሱስ ሰይፍና ጥል ለማስነሳት መምጣት

በማቴዎስ ወንጌል 10፡34-35 *«ኢየሱስ እንዲህ አለ፡- "እኔ የመጣሁት ሰለምን በምድር ላይ ለማምጣት አይምሰላችሁ። እኔ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም። እኔ የመጣሁት ወንድ ልጅን በአባቱ ላይ ሴት ልጅን በአባቱ ላይ ሴት ልጅን በእናትዋ ላይ ምርትን በአማትዋ ላይ በጠላትነት ለማንሳት ነው።»"*

## እርስ በእርሱ ተቃራኒ የሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች።

ለአንድ ዓላማ የሚፃፍ ጽሑፍ በመጽሐፍ መልክ ሲጠረዝ በተቻለ መጠን አንባቢያን በቀላሉ ሊረዱት በሚችሉ ጥልቀትና ስፋት መቅረብ አለበት። በውስጡም የሚካተቱ የጽሑፍ ይዘት (ጽንሰ ሐሳብ) እርስ በራሳቸው የሚቃረኑ መሆን የለባቸውም። ተራ ልብ ወለድ እንኳን ቢሆን የጽሑፍ ጽንሰ ሐሳብ ከመጀመሪያ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ ለአንባቢ ግልጽ በሆነ መልኩና በተቻለ መጠን ከተቃርኖ ፀድቶ መቅረብ ይኖርበታል። መለኮታዊ ሥነ ሥርዓትና ሕግጋን የሚያብራራና የፈጣሪን ቃል የያዘው መጽሐፍ ደግሞ ቅዱስነቱን ጠብቆ ከግዙፍም ሆነ ከተራ ስህተቶች ነፃ መሆን አለበት። ይሁን እንጂ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በርካታ ስህተቶችን እናገኛለን። በጥቂቱ የሚከተሉት ነጥቦች ይጠቀሳሉ።

- የኢየሱስ የዘር ሐረግ መለያየት፤
- የኢየሱስ ሐዋሪያቶች ስም መጻረር፤
- ስለ አንድ ጉዳይ የሚያብራሩ የተለያዩ አንቀጾች እርስ በራሳቸው መቃረን፤
- ለአብነት ያህል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እንመልከት፡-

## የሚፃረሩ የኢየሱስ የዘር ሐረግ

ሀ

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አብርሃም | 12 | ኢ.ዮቤድ | 23 | አካዝ | 34 | ሶዶቅ |
| 2 | ይስሃቅ | 13 | እሴይ | 24 | ሕዝቂያስ | 35 | አኪም |
| 3 | ያዕቆብ | 14 | ዳዊት | 25 | ምናሴ | 36 | ኤልዩድ |
| 4 | ይሁዳ | 15 | ሰለሞን | 26 | አሞን | 37 | ማታን |
| 5 | ፋሬስ | 16 | ሮብአም | 27 | ኢዮስያስ | 38 | ያዕቆብ |
| 6 | ሔጽሮስ | 17 | አቢያ | 28 | ዩአኪን | 39 | ዮሴፍ |
| 7 | ራም | 18 | አሳፍ | 29 | ሳላቲያል | 40 | ኢየሱስ |
| 8 | ዓሚናደብ | 19 | አዮሳፍን | 30 | ዘሩባቤል | 41 | |
| 9 | ነአሶን | 20 | ኢዮራም | 31 | አብዮድ | | |
| 10 | ሳልሞን | 21 | አዚያን | 32 | ኤልያቂም | | |
| 11 | ቦኤዝ | 22 | ኢዮአታም | 33 | አዞር | | |

ለ በማቴዎስ ወንጌል 1:1-16

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አብራሃም | 16 | ናታን | 31 | ኤልምዳም | 46 | ኤስሊም |
| 2 | ይስሃቅ | 17 | ማጣት | 32 | ቆላም | 47 | ናሆም |
| 3 | ያዕቆብ | 18 | ማይናን | 33 | ሐዲ | 48 | አምፅ |
| 4 | ይሁዳ | 19 | ሜልያ | 34 | ሚልኪ | 49 | ማታትዮ |
| 5 | ፋሬስ | 20 | ኤልያቄም | 35 | ኔሪ | 50 | ዮሴፍ |
| 6 | ሐጽሮስ | 21 | ዮናን | 36 | ሳልትያል | 51 | ዮና |
| 7 | አርኒ | 22 | ዮሴፍ | 37 | ዘሩባቤል | 52 | ሚልኪ |
| 8 | ራም | 23 | ይሁዳ | 38 | ሬስ | 53 | ሌዊ |
| 9 | አሚናደብ | 24 | ስምኦን | 39 | ዮናን | 54 | ማቲ |
| 10 | ነአሶን | 25 | ሌዊ | 40 | ዮዳ | 55 | ኤሊ |
| 11 | ሳልሞን | 26 | ማጣት | 41 | ዮሴፍ | 56 | ዮሴፍ |
| 12 | ሞኤዝ | 27 | ዮራም | 42 | ሴሜይ | 57 | ኢየሱስ |
| 13 | ኢዮቤድ | 28 | ኤሊኤዘር | 43 | ሜታትዮ | | |
| 14 | እሴይ | 29 | ዮሴዕ | 44 | ማአት | | |
| 15 | ዳዊት | 30 | ዔር | 45 | ናጌ | | |

በሉቃስ ወንጌል 3፡23-34

ሰ. <u>የኢየሱስ የሐዋርያቶች ስም መፃረር</u>

<u>ሀ</u> <u>ለ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| 1 | ስምዖን (ጴጥሮስ) | 1 | ስምዖን (ጴጥሮስ) |
| 2 | እንድሪስ | 2 | እንድሪስ |
| 3 | ያዕቆብ | 3 | ያዕቆብ |
| 4 | ዮሐንስ | 4 | ዮሐንስ |
| 5 | ፊልጶስ | 5 | ፊልጶስ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | በርቶሎሜዎስ | 6 | በርቶሎሚዎስ |
| 7 | ቶማስ | 7 | ማቴዎስ |
| 8 | ማቴዎስ | 8 | ቶማስ |
| 9 | ያዕቆብ (የእልፍየስ ልጅ) | 9 | ያዕቆብ (የእልፍየስ ልጅ) |
| 10 | ታዴዎስ | 10 | ሰምዖን (ተቀናቃኙ) |
| 11 | ሰምዖን (ተቀናቃኙ) | 11 | ይሁዳ (የያዕቆብ ልጅ) |
| 12 | ይሁዳ | 12 | ይሁዳ (አስቆርታዊው) |

በማርቆስ ወንጌል 3፡16-19 በሉቃስ ወንጌል 6፡14-16

በማቴዎስ ወንጌል 10፡2-4

## ሌሎች ተፃራሪ ጥቅሶች

## የዮሴፍ አባት ማን ነው?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡16‹‹*ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ፤…››*

በሉቃስ ወንጌል 3፡23… ‹‹*ይኸውም ዮሴፍ የዔሊ ልጅ …››*

## አሥራ አንድ ወይስ አሥራ ሁለት?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡16‹‹*አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እንዲሄዱ ወደ አመላከታቸው በገሊላ ወደሚገኘው ተራራ ሄዱ።››*

በኛ ቆረንቶስ 15፡4-5‹‹ … *በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ የሚል ነው። እንዲሁም ለጴጥሮስ ታዩ፤ ኋላም ለአሥራ ሁለቱ ታዩ።››*

## ምስክርነቱ እውነት ነው ወይስ አይደለም?

በዮሐንስ ወንጌል 5፡31‹‹*እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት አይደለም።››*

በዮሐንስ ወንጌል 8፡14‹‹*ምንም እንኳ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደመጣሁ ወዴት እንደምሄድ ስለማወቅ ምስክርነቴ እውነት ነው።››*

## አሥራ ሁለቱ ወይስ አንዱ ብቻ ዲያብሎስ?

በማቴዎስ ወንጌል 19፡28«*ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- "በእውነት እላችኋለሁ" የሰው ልጅ በክብር ዙፋን ላይ የሚቀመጥበት በአዲሱ ዘመን የኔ ተከታዮች ሆናችሁ እናንተም በአሥራ ሁለቱ ዙፋን ላይ ትቀመጣላችሁ። በአሥራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች ላይ ተሹማችሁ ትፈርዳላችሁ።*» በዮሐንስ ወንጌል 6፡ 70«*ኢየሱስም፡- "እናንተ አሥራ ሁለታችሁን መርጬአችሁ የለምን? ታዲያ እኮ ከእናንተ አንዱ ዲያቢሎስ ነው።" አላቸው።*»

## ሰባት መቶ ወይስ ሰባ ሺህ? አርባ ሺህ ፈረሰኛ ወይስ አርባ ሺ እግረኛ?

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 10፡18« ... *ዳዊትና ሠራዊቱ ሰባት መቶ የሶሪያውያን የሰረገላ ነጅዎችንና አርባ ሺህ ፈረሰኞችን ገደሉ።*»

በ1ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል 19፡18«... *ዳዊትና ሠራዊቱ ሰባት ሺህ ሰረገላ ነጅዎችን አርባ ሺህ እግረኛ ወታደሮችን ገደሉ።*»

## ዳዊትና ለመከራ ማን አነሳሳው? እግዚአብሔር ወይስ ሰይጣን?

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 24፡11«*እግዚአብሔር እንደገና በእስራኤል ላይ ስለተቆጣ በዳዊት አማካኝነት መከራ እንዲመጣባቸው አደረገ። እግዚአብሔር ዳዊትን "ሄደህ የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ ቁጠር" አለው።*»

በ1ኛ መጽሐፈ ሰዜና መዋዕለ 21፡1«*ሰይጣን በእስራኤል ሕዝብ ላይ መከራ ማምጣት ስለ አቀደ ዳዊትን የሕዝብ ቆራ እንዲያደርግ አነሳሳው።*»

## ሦስት ሰዓት ወይስ ስድስት ሰዓት?

በማርቆስ ወንጌል 15፡25«*ኢየሱስን ሲሰቅሉት ጊዜው ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነበር።*»

በዮሐንስ ወንጌል 19፡14-15«*የፋሲካ ዝግጅት ቀን ነበር፤ ጊዜውም ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ጲላጦስ አይሁዳውያንን "እነሆ ንጉሳችሁ"*

*አላቸው። እነርሱ ግን "ወዲያ ውሰደው! ወዲያ ውሰደው! ስቀለው!" እያሉ ጮሁ።›*

## መስቀሉን ማን ተሸከመ? ኢየሱስ? ወይንስ የቀሬና ሰው?

በማቴዎስ ወንጌል 27፡32‹‹*ከገዢው ግቢ ሲወጡ ስምዖን የተባለው የቀሬና አገር ሰው አገኙና የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም አደረጉት*።››

በሉቃስ 23፡26‹‹*በወደሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መሰቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት*።››

በዮሐንስ ወንጌል 19፡17‹‹*ከዚህ በኋላ ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ "የራስ ቅል" ወደ ሚባለው ስፍራ ወጣ*።››

## ሐሞት ወይስ ከርቤ?

በማቴዎስ ወንጌል 27፡34‹‹*በዚያም ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ለኢየሱስ አቀረቡለት*።››

በማርቆስ ወንጌል 5፡23‹‹*እዚያም በደረሰ ጊዜ ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት*።››

## መግደላዊት ማሪያም ብቻ ወይስ ሌሎችም?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡1 ‹‹*ሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ ዕሁድ ጧት በማዳ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃብሩን ለማየጥ ሄዱ*።›

በማርቆስ ወንጌል 16፡1-2 ‹‹*ሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ መቅደላዊት ማርያም ያዕቆብን እናት ማርያም ሰሎሜም ሆነው የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት ሽቶ ገዙ። ዕሁድ ጧት ልክ ፀሐይ ስትወጣ ወደ መቃብሩ ሄዱ*።››

በሉቃስ ወንጌል 24፡10 ‹‹*ከመቃብር ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሯቸው። ይህን ለሐዋሪያት የተናገሩት መቅደላዊት ማርያምና የሐናና የያዕቆብ እናት ማሪያም እንዲሁም ሌሎች ሴቶች ነበሩ*።››

በዮሐንስ ወንጌል 20፡1 *‹‹እሁድ ጧት በማለዳ ገና ጎህ ሳይቀድ መግሰደላዊት ማርያም ወደ ኢየሱስ መቃብር ሄደች፡፡››*

## መልአክ ወይስ ሰዎች?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡2-3 *‹‹እነሆ በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባለለና በላዩ ተቀመጠ። የመልአኩም ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር። ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር፡፡››* በሉቃስ ወንጌል 24፡3-4 *‹‹ወደ መቃብርም በገቡ ጊዜ ግን የጌታ ኢየሱስን አስከሬን አላገኙም፤ ስለዚህም ነገር በመገረም ላይ ሳሉ እነሆ የሚያንፀባርቅ ብሩህ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት መጥተው በአጠገባቸው ቆሙ፡፡››* በማርቆስ ወንጌል 16፡5 *‹‹ወደ መቃብሩም በገቡ ጊዜ ነጭ ልብስ የለበሱ ጎልማሳ በስተቀኝ በኩል ተቀምጦ በማየታቸው ደነገጡ፡፡››* በዮሐንስ ወንጌል 20፡12 *‹‹የኢየሱስም አስከሬን በነበረበት ስፍራ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መልአክት አንዱ በራስጌ አንዱ በግርጌ ተቀምጠው አየች፡፡››*

## ተናገሩ ወይስ አልተናገሩም?

በማርቆስ ወንጌል 16፡8 *‹‹ሴቶቹም በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ከመቃብር ወጥተው ሸሹ። እጅግ ፈርተው ስለ ነበር ምንም ነገር ለማንም አልተናገሩም፡፡››* በሉቃስ ወንጌል 24፡8-9 *‹‹ሴቶቹም የኢየሱስን ቃል አስታወሱ፤ ከመቃብር ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሩዋቸው፡፡››*

## የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ማን ነው? እስራኤል ወይስ ኤፍሬም?

በኦሪት.ዘጽአት 4፡22 *‹‹በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር ለፈርዖን የምለውን እንዲህ ብለህ ትነግረዋለህ፡- እስራኤል የበኩር ልጄ ነው፡፡››*

በትንቢተ.ኤርምያስ 31፡9 *‹‹… እኔ ለእስራኤል አባት ነኝ፤ ኤፍሬምም የበኩር ልጄ ነው፡፡››*

## <u>መጽሐፍ ቅዱስ የማን ቃል ነው?</u>

መጽሐፍ ቅዱስ የማን ቃል ነው? ሁልጊዜም ክርስቲያኖች የሚሰጡት መልስ አንድ ነው። እርሱም፡- "እግዚአብሔር ቃል" ነው የሚል ነው። በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ከ100 ዓይነት በላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች ይገኛሉ። ከእዚህ ከ100 በላይ ቅጂዎች ትክክለኛው "የእግዚአብሔር ቃል" የትኛው ይሆን? ከአማርኛ ትርጉሞች ውጪ ያሉትን መጽሐፍ ቅዱሳት እንተወውና በሀገራችን ያሉትን እንኳ ስንመለከት ከፊሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምኑበት ሰማንያ አሐዱን ሲሆን ከፊሎቹ የክርስትና እምነት ተከታዮች ደግሞ ሰማንያ አሐዱን አይቀበሉም። 66ቱንና እና 73ቱን ብቻ ነው የሚቀበሉት። ከዚህ አንፃር እንኳን ብናይ የእግዚአብሔር ቃል የትኛው ነው? 81፣ 73 ወይስ 66ቱ? በእነዚህ መጽሐፍ መካከል የአስራ አምስት (15) መጻሓፍት ልዩነት አለው። ሰማንያ አሐዱን የእግዚአብሔር ቃል ነው ብለው የሚቀበሉት አስራ አምስቱን ማለትም "የቀኖች" (ዲዩትሮካኖኒካል) መጽሐፍ የእግዚአብሔር ቃል ነው ካሉ ማስረጃ ሊኖራቸው ይገባል። እንዲሁም ስልሳ ስድስቱን የሚቀበሉት የእግዚአብሔር ቃል ለመሆኑ ማስረጃና 15 የቀኖች መጽሐፍት የእግዚአብሔር ቃል ላለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። ምክንያቱም ያለንበት "የተአምር ዘመን" ሳይሆን "የማስረጃ ዘመን" ነውና። መጽሐፍ ቅዱስን ካለው የንግግር ይዘት በአራት መልኩ ከፍለን እናየዋለን።

<u>የአምላክ ቃል</u>፡- በኦሪት.ዘዳግም 6፡4 ***«እስራኤል ሆይ! ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍፁም ልብህ ነፍስህ በፍፁም ኃይልህ ውደድ።»***

<u>የነብያት ቃል</u>፡- በማርቆስ መንጌል 12፡29 ***«ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለው፡- ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ፡- እስራኤል ሆይ! ስማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፤ አንተም በፍፁም ልብህ በፍፁምም ነፍስህ በፍፁምም አሳብህ በፍፁምም ኃይልህ ጌታ አምላክህን ውደድ የምትል ናት።»***

<u>የተራኪዎች (የጸሐፍያን) ቃል</u>፡- ጳውሎስ ወደ ቲቶ ሰዎች በላከው መልእክት 3፡15 «***<u>ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል፤ በእምነት ለሚወዱን ሰላምታ አቅርብልን</u>።***» በተለያዩ የክርስትና እምነት ዘርፎች መጽሐፍ ቅዱስ ያለ ጥርጥር

“የአምላክ ቃል” ለመሆኑ እንደ ዋቢ መረጃ አድርገው የሚያቀርቡትን አንቀጽ አለ፡- በ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት 1፡21 «***ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ***» የሚለውን አንቀጽ እንደ ማስረጃ በመጥቀስ መጽሐፍ ቅዱስ “የአምላክ ቃል” መሆኑን ለማስረዳት ይሞክራሉ። ይህ ግን ትልቅ ስህተት መሆኑን ልንጠቁማቸው እንወዳለን። ምክንያቱም አንቀጹ የሚለው እንዲህ ነውና። በ2ኛ ጴጥሮስ መልእክት 1፡21«***ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።***» ይህ አንቀጽ የሚናገረው ከመጽሐፍ ቅዱስ አካል አንዱ ስለሆነው “ትንቢት” እንጂ ስለ ጠቅላላው መጽሐፍ አይደለም። ምክንያቱም ትንቢት የመጽሐፍ ቅዱስ አንዱ አካል ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው የትንቢት ቃል አይደለም። በተጨማሪም ይህንኑ ትንቢት እንኳን ቢሆን “ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩት” እንጂ “ፃፉት” አይልም። መጻፍና መናገር ደግሞ የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ስለሆነም ይህ አንቀጽ መጽሐፍ ቅዱስ የአምላክ ቃል ለመሆኑ እንደ በቂ መረጃ ሆኖ ሊቀርብ መቻሉ አጠያያቂ ነው።

## እውን ማቴዎስ መንጌሉን ጽፎታልን?

በማቴዎስ መንጌል 9፡9«***ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየ፤ ተከተለኝ አለው፤ ተነስቶም ተከተለው።***» የማቴዎስ ወንጌልን ቀራጩ ማቴዎስ እንደፃፈው ነው የሚነገረው። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሰውን አንቀጽ የማቴዎስ መንጌል 9፡9 የተመለከትነው ከሆነ ማቴዎስ እየተረከ ያለው ስለ ኢየሱስና ቀራጩ ማቴዎስ ስለተባለው ሰው ነው። እንዲሁም ማቴዎስ የጻፈው ስለሌላ ሰው ነው የሚመስለው፣ ይህን አንቀጽ ሲፅፈው በራሱ አስታኮ መጻፍ ነበረበት። ምክንያቱም ኢየሱስ እያናገረ ያለው የዚህን አንቀጽ ፀሐፊ እራሱን ማቴዎስን እንጂ ሌላ ሰውን አይደለምና። ስለዚህ ማቴዎስ ይህን አንቀጽ ሲፈጽም “ኢየሱስም ከዚህ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና ተከተለኝ አለው። ተነስቶም ተከተለው።” ከማለት ፈንታ “ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጬ ሳለ አየኝና ተከተለኝ አለኝ። ተነስቼም ተከተልኩት፤” ብሎ መጻፍ ነበረበት። አለበለዚያ ግን ይህን አንቀጽ ማቴዎስ ጽፎታል ማለት አያስደፍርም፣ ሌላ ሰው የጻፈው ነው የሚመስለው።

## የሉቃስ ወንጌል 1፡1-

በሉቃስ መንጌል 1፡1- *«ከበርህ ቴዎፍሎሰ ሆይ! ከመጀመሪያው በዓይን ያዩትና የቃሉ አገልጋዮች የሆኑት እንዲያስተላልፉልን በእኛ ዘመን ስለ ተፈጸመው ነገር ብዙዎች ታሪክን በየተራው ለማዘጋጀት ስለ ሞከሩ እኔ ደግሞ ስለተማርከው ቃል እርግጡን እንድታውቅ በጥንቃቄ ሁሉን ከመጀመሪያው ተከትዬ በየተራው ልጽፍልህ መልካም ሆኖ ታየኝ።»*"

ከዚህ አንቀጽ ሶስት ነጥቦችን እናገኛለን፡-

- ሉቃስ "በዓይን ያዩ ሰዎች እናዳስተላለፉልን" ማለቱ እሱ የዓይን ምስክር እንዳልነበረ፣
- ወንጌሉንም (መጽሐፉንም) ለመጻፍ መንፈስ ቅዱስ ተገለጠልኝ ወይም ከአምላክ ዘንድ ታዝዤ ፃፍኩት ሳይሆን ያለው መልእክቱ ለቅርብ ወዳጅ ቴዋፍሎት እንጂ ለዓለም አለመሆኑ
- ስለዚህ ከላይ ባየነው መሰረት የሉቃስ ወንጌል የአምላክ ቃል ነው ለማለት አይስደፍርም።

እንዲሁም ጳውሎስ በመልእክቶቹ ላይ የሚከተሉትን እንቀጾች አስፍሯል። *«እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበር ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።»* በማለት ጳወሎስ ከአምላክ ዘንድ የተገለጠለትን መለኮታዊ ራዕይ መሆኑ ቀርቶ የራሱን ፍላጎትና ስሜት ከአምላክ ቃል ጋር አጣምሮ ለመናገር እንደሚፈልግ እንረዳለን። እንዲሁም በሌላ ቦታ ቃሉ የአምላክ ሳይሆን የእሱ እንደሆነ በግልጽ አስቀምጧል፡፡ በ1ኛ ቆሮንቶስ 7፡12 *«ሌሎችንም እኔ እላለሁ፤ ጌታም አይደለም...»* እዚህ ላይ ሁላችንም የምንረዳው "ሌሎችንም እኔ እላሁ ጌታም አይደለም" ማለት ከፈጣሪ ቃል ውጭ የራሱን መናገሩና ነው የሚገልጸው። ታድያ ይህን እንዴት የፈጣሪ ቃል ነው ብለን ልናምን እንችላለን? ጳውሎስ በዚህ ሳይገደብ በሌላም ቦታ ላይ ጌታ እንዳዘዘው እንደማይናገር የራሱን መስክርነቱ ላይ እንዲህ በማለት አስፍሯል። «እንደዚህ ታምኜ ስመካ የምናገረው በሞኝነት እንጂ ጌታ እንዳዘዘው አልነበረም።» ማንም ይሁን ማን ይህንን አባባል "የአምላክ ቃል" ነው እንደማይል ግልጽ ነው። ምክንያቱም "ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም" ማለቱ

ከራሱ የሆነን ንግግር ነው የሚያመላክተው፤ ስለዚህ "አምላክ ቃል" ነው ለማለት አያስደፍርም። በሌላም ቦታ ላይ እንዲሁ ስለግል ጉዳይ ሆኖ ሳለ በዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስ ግን የአምላክ ቃል ነው ተብሎ መስፈሩ የመጽሐፍ ቅዱስን ምንጭ ጥርጣሬ ውስጥ ውስጥ ይከተላል። የ1980 ዕትም በ2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡9-17 ***«በፍጥነት ወደ እኔ እንድትመጣ ይሁን፤ ዴማስ ይህን ዓለም ወደ ተለይቶኛል፤ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል፤ ቄርቂስ ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ድልማጥያ ሄደዋል። ከኔ ጋር ያለው ሉቃስ ብቻ ነው፤ ማርቆስ ለአገልግሎት ስሚጠቅመኝ ከአንተ ጋር አብሮ ይምጣ። ቲኪቆስን ወደ ኤፌሶን ልኬዋለሁ። <u>ስትመጣ በጤሮአዳ በካርፑስ ዘንድ የተውሁትን ካባ ይዘህልኝ ና</u>፤ መጽሐፍቱንም ይልቁንም የብራና መጻሓፍቱን አምጣልኝ። ዮናስ አንጥረኛው እስክንድር ብዙ ክፉ ነገር አደረገብኝ፤ ጌታ አንደስራው ይከፍለዋል። እራሱን እኛ የምናገረውን በብርቱ ስለ ተቃወመ አንተም ራስህ ከእርሱ ተጠንቀቅ። በተከሰስሁበት ነገር የመጀመሪያ መከላከያዬን ባቀረብሁ ጊዜ ሁሉም ተለዩኝ እንጂ ከእኔ ጋር ሆኖ የረዳኝ ማንም አልነበረም፤...»*** ይህ አንቀጽ የጳውሎስና የባልደረቦቹ የግል ታሪክ እንጂ "የአምላክ ቃል" ነው ማለት አንደፍርም። የግል ታሪክ ደግሞ የአምላክ ቃል ሊባል እንደማይችል ማንም ይስማማበታል። በተጨማሪም የሰላምታ ወይም የደብዳቤን መልእክት ያዘለ እንዲሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። ወደ ቲቶ ሰዎች በላከው መልእክት 3፡15 ***«<u>ከእኔ ጋር ያሉ ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላሃል። በእምነት ለሚወዱና ሰላምታ አቅርብልኝ</u>።»*** ይህ የሰላምታ ደብዳቤ እንጂ "የአምላክ ቃል" እንዴት ሊባል ይችላል? አሁንም መጽሐፍ ቅዱስ ሙሉ በሙሉ "የአምላክ ቃል" ነው ከተባለ የሚነሱ ብዙ ጥያቄዎች አሉ። ከብዙ በጥቂቱ ብንመለከት፡- በ1ኛ ቆሮንቶስ ሰዎች 1፡2 ***«<u>ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ምኝነት ይጠበባልና የእግዚአብሔርም ድካም ይልቅ ይበረታልና</u>።»*** ይህንን የማን ቃል እንበለው? የአምላክ ቃል ነው ማለት እጅግ ይከብዳል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ራሱን ሞኝ ብሎ የሚጠራው ከሰው የባሰ ደካማ ብሎ የእሱን የሚያሳንስ ቃል እንዴት ይናገራል? ስለዚህ ከአምላክ ባሕሪ ጋር የሚቃረን ቃላት እንዴት ተብሎ የአምላክ ቃል ነው ብለን ልንቀበል እንችላለን? "የፈጣሪ ቃል" ላይ መጨመርና መቀነስ ያስፈልገዋል? ለዚህም የትኛውም የክርስትና እምነት ተከታይ ቢሆን የሚሰጠው መልስ "መጨመረም ሆነ መቀነስ አይገባውም። እንዲያውም ኃጢአት ይሆንበታል።" የሚል ነው። ነገር ግን በዘመናችን በሚገኙ መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂዎች በጥንት ትርጉም መጽሐፍት ላይ ያልነበሩ አዳዲስ ቃል ሲጨምሩ

እናያለን ከእነርሱም መካከል፡- በማርቆስ ወንጌል 16፡15 ***«እንዲሁም አላቸው፡- ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ።»*** ይህ አንቀጽ አዲስ የተጨመረ እንጂ በድሮ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰፍሮ አናገኝም። ቀለል ባለ አማርኛ የ1980 ዓ.ም ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ከህዳጉ /ከግርጌ/ ማስታወሻ ላይ የተፃፈውን ይመልከቱ። እንዲሁም ይነበባል፡- "አንዳንድ ቅጂዎችና የጥንት ትርጉሞች ከቁጥር 9-20 ያለውን ክፍል አይጨምሩም" ይላል። የህዳግ ማብራሪያው አንቀጹ በጥንት መጽሐፍ ቅዱስ እንዳልነበረና አዲስ የተጨመረ መሆኑን ይመሰክራልና እንዴት አድርገን አዲሱን ፈጠራ እንቀበል? የሰው ልጅ እንደፈለገ የሚጨምርበት ከሆነ የአምላክ ቃልነቱ ምኑ ላይ ነው? በመጽሐፍ ምሳሌ 9፡12 እና 12 ***«ልጄ አዋቂ ብትሆን ለባልንጀራህም አዋቂ ትሆናለህ፤ ለራስህ ክፉ ብትሆን ግን ክፋትና ትማራለህ። ሐሰትን የሚያዘጋጅ ሰው ነፋሳትን እንደሚያዘጋጅ ሰው ነው የሚበርር ወፍንም እንደሚከተል ይመስላል። የወይኑ ቦታ መንገዱን ተው፤ የሚሰማራባትን መንገደ ዘነጋ፤ ወደ ምድረ በዳ ይሄዳል፤ ለጥም ወደ ተሰራች አገር ይሄዳል፤ የማያፈራ የማይጠቀም ገንዘብንም በእጁ ይሰበስባል።»*** በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 9 ቁጥር 12 እና 13 መካከል የሚገኝ 1954 ዕትም ገጽ 502 ይመልከቱ። በመጽሐፈ ምሳሌ 24፡23 ***«የነገሩትን የሚሰማ ልጅ ከጥፋት የራቀ ነው፤ የነገሩትን የሚቀበልን ሰው እግዚአብሔር ይቀበለዋል። ከንጉሥ አንደበት ምንምን ሐሰት ይናገራል አይባልም፤ ከአንደበቱም የሚወጣ ሐሰት የለም። የንጉሥ ቃል ሾተል ናት፤ ለጥፋት የተሰጠችውን ሰው ሰውነት ታጠሩዋለች እንጂ አንድ አካል ብቻ የምታጠፋ አይደለም። ሰይፈ መዓቱ ብትሳል ግን ከወገኑ ጋር ሰውን ታጠፋለች፤ ከአምሮች ግልገል ወገን የማይበላ እስኪሆን ድረስ እንደ እሳት ነበልባል ታቃጥላለች።»*** በመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 24 ቁ እና 23 መካከል የሚገኝ የ1954 ዕትም ገጽ 512-513 ላይ ይመልከቱ። ከላይ የተመለከትናቸው ሁለት አንቀጾች በሌሎች የአማርኛ ቅጂ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተካተቱም። ማለትም "ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1980 ዕትም"፣" አዲሱ መደበኛ ትርጉም 1993 ዕትም" እና "ቀለል ባለ አማርኛ የተተረጎመ 1997 ዕትም (የታረመ)" ውስጥ አይገኝም። ለምን እንዳይካተት ተደረገ የአምላክ ቃልነቱ ተዘንግቶ ወይስ የአምላክ ቃል አይደለም። እንዴትስ በግሪኩ እና በአማርኛ በ1954 ዕትም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሊኖር ቻለ? ቁላው የተቀጠቀጠ ብልቱም የተቆረጠ ወደ እግዚአብሔር ሁባኤ አይግባ። ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ፤ እስከ አስር ትውልድ ድረስ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ።" ...

የተቀጠቀጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ" የሚለው ቃል ሁለት አይነት መንገድ ማየት ያስፈልጋል፡-

ቀለል ባለ አማርኛ ትርጉም የ1980 ዓ.ም ዕትም ላይ "...." የሚለውን "ብልቱ" ተብሎ ተሸሽሏል፤ ምክንያቱም ቃሉ ፈር የለቀቀ እና ለማንበብም አሳፋሪ ስለሆነ የግድ መቀየር ስለነበረበት መቀየር ወይም መሻሻል አስፈለገው? "... የተቀጠቀጠ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ አይግባ" የሚለውን አባባል ካስተዋልነው "...." የተቆረጠ ብልቱ የተቀጠቀጠ ለምንድን ነው ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ የማይገባው? ምን አጠፋ? መቼም አንድ ሰው በአደጋ ወይም በሌላ አጋጣሚ ሊሰለብ ወይም ሊቆረጥ ይችላል እንጂ ሆነ ብሎ ብልቱን የሚቆርጥ የለም የእጅ ጥፍር አይደለምና፡፡ ስለዚህ የእግዚአብሔር ቃል ከሆነ እንዴት ይቀጣል? እንዲሁም "ዲቃላ ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ የማይገባው? ወንጀል ሰርተው የወለዱት ወላጆቹ ሆነው ሳሉ እንዴት ምንም የማያውቀው ልጅ ይከለከላል? አህያውን ፈርቶ ዳውላውን አልሆነም ነገሩ? ታዲያ ይህ የተሳሳተ ፍርድ እውን የአምላክ ቃል ነውን? ደግሞስ ለምን እስከ ትውልድ ተከለከለ ሌሎችስ ምን ባጠፉ? ***«እርስዋም በልጃገረድነትዋ ወራት በግልጽ አመንዝራ ሆና ሳለ ልታደርግ የነበረውን ሁሉ በመፈጸም አመንዝራነትዋን አበዛች፡፡ <u>ብልቶቻቸው እንደ አህያ ዘራቸውም እንደ አለሌ ፈረስ ሆኖ በፍትወት በሚቃጠሉ ወንዶች ተማረከች</u>፡፡»***

የ1997 ዕትም ትንቢተ ሕዝቅኤል 23፡19-20 *«<u>ብልቶቻቸው እንደ አህያ ዘራቸውንም እንደ አለሌ ፈረስ</u>»* ይህን አባባል አሁን እግዚአብሔር ይናገረዋልን? ጨዋነት የጎደለው አባባል አይደለምን? በዚያን ቀን እንዲህ ይናል፤ እግዚአብሔር በግብጽ ወንዝ ዳርቻ ያለውን ዝምብ በአዎርም አገር ያለውን ንብ በፉጨት ይጠራል፡፡» በትንቢተ.ኢሳያይስ 7፡18 *«<u>እግዚአብሔር በፉጨት ዝምብንና ንብን ይጠራል</u>፡፡»* ይህ አባባል ለአምላክ የተገባው ነውን? እውን ፈጣሪ ዝምብንና ንብን በፉጨት ይጠራል? ታዲያ ይህ ሁኔታ በምን ዓይነት መልኩ የአምላክ ቃል ነው ለማለት የሚያስደፍረው? በትንቢተ.ኢሳይያስ 7፡20 *«<u>በዚያ ቀን እግዚአብሔር ከወንዙ ማዶ በተከራው ምላጭ በአሦር ንጉሥ የራሱንና የእግሩን ጠጉር ይላጨዋል፤ ምላጩም ጢሙን ደግሞ ይበላዋል</u>፡፡»* እውን አምላክ ጢሙን ተላጭቷል ወይም ላጭቷል? የራሱንና የእግሩን ፀጉር የሚላጭ ወይም የሌላውን የሚላጭ አምላክ ፈጣሪ የተናገረው ነው ብለው ይገምታሉን? ሌላ አሁንም

መጽሐፍ ቅዱስ በልበ ሙሉነት “የፈጣሪ ቃል” ነው ለማለት የማንደፍረው ፈጣሪ አግብቷል ወልዷል ማለቱ ነው። ማንኛውም ክርስቲያንም ሆነ ሙስሊም ፈጣሪ ሚስት አለው፤ቢባል አይቀበልም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ አምላክ ማግባት እንዲህ ይናገራል፡- ***«አታፍሪምና አትፈሪ፤ አትዋረጂምና አትደንግጪ፤ የሕፃንነትሽን እፍረት ትረሽዋለሽ የመበላሽትም ስድብ ከእንግዲህ አታስቢም። ፈጣሪሽ ባልሽ ነው፡- ስሙም የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው፤...»*** መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ሚስት አለው ይላል። እንዴት አድርገን ይህን አንቀጽ “የአምላክ ቃል” ወደ ሚለው ድምዳሜ ልንደረስ የምንችለው? እውን ፈጣሪ ሚስት አለውን? እዚህ ላይ ሁለት አማራጮች አሉ። 1ኛው መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ትክክል ነው ካልን መጽሐፍ ቅዱስ አምላክ ሚስት ማግባቱን ስለተናገረ አሜን ብለን መቀበል አለብን። 2ኛው እግዚአብሔር አላገባም የምንል ከሆነ መጽሐፍ ቅዱስ አግብቷል ስለሚለን አንቀጹ “የአምላክ ቃል” አለመሆኑን ይጠቁመናል። በትንቢተ.ሕዝቅኤል 23፥1-4 ***«የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ፡- የሰው ልጅ ሆይ! የአንዲት እናት ልጆች የሆኑ ሁለት ሴቶች ነበሩ። በግብፅም አመነዘሩ በኮረዳነታቸውም አመነዘሩ፤ በዚያ ጡቶቻቸው ምዋሸሹ በዚያም የድንግልናቸውን ጡቶች ዳበሱ። ስማቸው የታላቂቱ ኦሆላ የእህትዋም ኦሆሊባ ነበር። ለእኔም ሆኑ መንዶችና ሴቶች ልጆችንም ወለዱ።...»*** አንዳንድ ክርስቲያኖች ይህ ትንቢተ የተነገረው ለኢየሩሳሌም ነው እንጂ እግዚአብሔር ሚስት አግብቶ ወልዶ አይለም ይላሉ፤ ነገር ግን የ1980 ቀለል ባለ የአማርኛ እትም ንዑስ አንቀጽ “በዝሙት ኃጢአት የተባበሩ እህትማማኞች” ብሎ ሰይሞታል። ታዲያ እንዴት ሆኖ ነው ለእየሩሳሌም የሚሆነው? እየሩሳሌም እህት አላት ማለት ነውን? አገርስ ዝሙት ይሰራል? የኢየሩሳሌም ጡቶች ሚሸሹ ሲባል ምን ዓይነት ትርጉም ይኖረው ይሆን? እነዚህ ዝሙተኛ እህትማማቾች ስማቸው የታላቂቱ ኦሆላ የታናሽቱ ኦሆሊባ ሲሆን መጽሐፉ የሚተርከው ስለዚህ ሴቶች ነው። እንዴት ሆኖ ለኢየሩሳሌም ሲሆን የሚችለው? የሚወክሉት ደግሞ ኦሆላ ሰማርያን ሲሆን ኦሆሊባ ደግሞ ኢየሩሳሌምን ነው ልብ ይበሉ ኦሆሊባ ኢየሩሳሌምን ትወክላለች እንጂ ኢየሩሳሌምን አይደለችም። ምክንያቱም ኦሆሊባ ማለት የኦሆላ ትንሽ እህቷ ነች። ማለትም ሰው መሆኗን እንጂ አገር አለመሆኗን በግልጽ ከላይ ተጠቅሷል። ለምሳሌ እንኳ ብናይ አንድ ሯጭ ሀገሩን ወክሎ ለምሳሌ ኢትዮጵያን ወክሎ ሩጫ ቢወዳደር ተወዳዳሪው ሰው ኢትዮጲያን ወክሎ እንጂ እሱ ራሱ ኢትዮጵያ አይደለም። በዚህ ማንም ይስማማበታል። ልክ

እንደዚሁ ኦሆሊባም ኢየሩሳሌም ወከለች እንጂ ራሷ ኢየሩሳሌም አይደለችም። ከዚህ አንፃር ይህ አንቀጽ እግዚአብሔርን ማግባት በግልጽ ስለሚያሳየን የአምላክ ቃል ነው ማለቱ እጅግ ይሰቀጥጣል። ቀለል ባለ አማርኛ የ1980 ዕትም በትንቢተ.ሕዝቅኤል 16፥3-13 *«ልዑል እግዚአብሔር ስለ እርስዋ የሚለውን እንዲህ ብለህ ንገራት፦ የተወለድሽው በከንዓን ምድር ነበር፤ አባትሽ አሞራዊ ሲሆን እናትሽም ሒታዊ ነበረች፤ በተወለድሽ ጊዜ እትብትሽን የቆረጠ ወይም የጠበሸ ወይም በጨው አሽቶ በጨርቅ የጠቀለለሽ ማንም አልነበረም፤ ስትወጂ ፍቅር ያሳየሽ ማንም ስለሌለ በሜዳ ላይ ተጥለሽ ነበር። እኔም በዚያ ሳልፍ በገዛ ደምሽ ተነክረሽ ስትንፈራፈሪ አገኘሁሽ፤ በደም ተሸፍነሽ ልትሞቺ ነበረ፤ በሕይወት እንዳትኖሪ አደረግሁሽ፤ ምቾት እንደላው ተክል እንድታድጊ አደረግሁ፤ ቁመትና ጠንካራ ሰውነት በመጨመር አደግሽ የተዋብሽ ወጣት ሆንሽ፤ ጡትሽ አጎጠጎጠ፤ ፀጉርሽ ረዘመ፤ ነገር ግን እርቃንሽን ነበርሽ። እንደገና በአጠገብሽ ሳልፍ በፍቅር የምትነደፊበት ጊዜ እንደደረሰ አወቅሁ፤ የተራቆተውንም ውነትሽንም በመጎናፀፊያ ሸፍኜ እንደምወድሽ ቃል ገባሁልሽ፤ ከአንቺም ጋር የጋብቻ ቃል ኪዳን ገብቼ የእኔ የግሌ አደረግሁሽ፤ ይህን የተናገረ ልዑል እግዚአብሔር ነው። ከዚያም በኋላ ሸፍኖሽ የነበረውን ደም በውሃ አጠብሁ፤ የወይራ ዘይትም ቀባሁሽ፤ ጥበብ ቀሚስ አለበስሁሽ፤ ከምርጥ ቆዳ የተሰራ ጫማ አደረግሁሽ፤ ሐር ሻሽ በራስሽ ላይ አሰርሁልሽ፤ ሐር ካባም አለበስሁሽ። በእጅ አንባርና በአንገት ድሪ አስጌጠሁሽ፤ ለአፍንጫሽ ቀለበት፤ ለጆሮሽ ጉትቻ፤ እንዲሁም በራስሽ ላይ የምትደፊው ውብ የሆነ አክሊል ሰጠሁሽ። ከብርና ከወርቅ የተሰሩ ብዙ ጌጣጌጦች ነበርሽ፤ ከልዩ ልዩ የተሰሩና በጥልፍ ጌጥ የተዋቡ ብዙ ልብሶች ነበሩሽ፤ ምርጥ ከሆነ ዱቄት የተጋገረ ዳቦ ማርና የወይራ ዘይት ትመገቢ ነበር፤ አንጸባራቂ ውበት ስለነበረሽ ንግሥት ለመሆን በቃሽ።»* ስለዚህ አምላክ እውን መጽሐፍ እንደሚለው አድርጓል? ያሳደጋት ልጅ በማድነቅ ፀጉርሽም ረዘም፣ ባጠገብሽ ሳልፍ በፍቅር የምትነደፊበት ጊዜ መድረሱን አወቅኩ፣ መጎናፀፊያዬን በላይሽ ዘርግቼ እንደምወድሽ ቃል ገባሁልሽ፤ የግሌ የብቻዬ አደረኩሽ፤ እያለ አምላክ በልጅቱ ፍቅር መለከፉን መጽሐፍ ቅዱስ ይመሰክራል። ይህን እውን "የአምላክ ቃል" እንበለው? በዚህ ምዕራፍ ቁጥር 20 ላይ ታሪኩ ይቀጥላል፦ በትንቢተ.ሕዝቅኤል 16፥20-21 *«የወለድሽልንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወስደሽ ለጣዖታት መስዋዕት በማድረግ አቀረብሽላቸው፤ በእኔ ዘንድ አምነት የጎደለሽ መሆንሽ አልበቃሽ ብሎ ልጆቼን በማረድ ለጣዖት መሥዋት አድርገሽ አቀረብሽ።»*

ለመስዋትነት የቀረቡት እግዚአብሔር የወለዳቸው ልጆች መሆኑን ልብ ይበሉ። ቀለል ባለ አማረኛ 1980 ዕትም በትንቢተ.ሆሴዕ 1፡2 ***«እግዚአብሔር በሆሴዕ አማካኝነት ለእስራኤል ሕዝብ ቃሉን ማስተላለፍ ሲጀምር ሆሴን እንዲህ አለው፡- ሕዝቤ ከእኔ ተለይቶ አጸያፊ የሆነ የዝሙት ሥራ በመስራት ላይ ይገኛል። እንግዲህ አንተም ሂድና ዘማዊት ሴት አግባ፤ እንደ እርስዋ ሴሰኞች የሆኑ ልጆችንም ከእርስዋ ውለድ።»*** ይህ «የፈጣሪ ቃል» ከሆነ ፈጣሪ እንዴት ነብይን ግልሙትናን የምትሰራን ሴት እንዲያገባ ያዛል? መልሱን ይህ «የአምላክ ቃል» ነው ለሚሉ ለመጽሐፉ ባለቤቶች እንተወው። መጽሐፈ ምሳሌ 31፡6 ***«ለጥፋት ለቀረበ ሰው ብርቱ መጠጥ ስጡት ነፍሱ ለመረረውም የወይን ጠጅ ስጡት ይጠጣ ድህነቱንም ይርሳ። ጉስቁልናውንም ከእንግዲህ ወዲህ አያስብ።»*** ይህንን አንቀጽ የሚያነብ ማንኛውም ሰው ድህነት ለጠናበት እና በሕይወቱም ላይ ተስፋ ለቆረጠ መፍትሄው አስካሪ መጠጥ መጠጣት ነው ወደሚለው ድምዳሜ ቢደርስ አይደንቀንም። እውነታ ግን ማንኛውንም ሰው አስካሪን መጠጥ ጠጪ ከሆነ ለመውጣት እጅግ ወደሚከብደው የድህነት አረንቋ ውስጥ መግባቱና በማህበረሰቡም ዘንድ ክብር ያጣ ሆኖ መገለሉ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በየጊዜው እንደሚለወጥ ከራሱ በላይ መቸም ምስክር የሚያሻው አይመስለንም። ምክንያቱም የ1980 መጽሐፍ ቅዱስ ቀለል ባለ አማርኛ ዕትም መቅደም ማንበቡ በቂ ነው። መቅደሙ መጽሐፉ እንዴት እንዴት እንደተዘጋጀ ሲናገር፡- «በ1966 ዓ.ም መጀመሪያ ላይ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር በአንድነት ሰብስቦአቸው ለነበሩ የአብያተ ክርስቲያናት ተወካዮች ስለአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ አዲስ ትርጉም አስፈላነት ባስረዳበት ጊዜ ሁለት አማራጭ ሀሳቦች ቀርበው ነበር። አንደኛው ሀሳብ በ1954 ዓ.ም የታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲታረምና እንዲሻሻል ይደረግ የሚል ሲሆን ሁለተኛው ሀሳብ የተሻሻለው ማንንም ሊያስደስት ስለማይችል አዲስ ትርጉም ቢዘጋጅ ይሻላል የሚል ነበር።» /ቀለል ባለ አማርኛ 1980 ዕትም መቅደም የተወሰደ/ የሚታረመውና የሚሻሻለው የማንን ቃል ነው? እንዴት «የአምላክ ቃል» ከሆነ እንዲታረምና እንዲሻሻል ይባላል? ማረሙና ማሻሻሉ ይቅርና በሒሳብ መልክ ማቅረቡ እንኳን አይሰቀጥጥምን? ይህ በግልፅ የሚያሳየው መጽሐፍ ቅዱስ በሰው ፈቃድ እንደታረመና እንደተሻሻለ ነው። ለዚህም ነው የ1954 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ እትም እና የ1980 የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ዕትም እርስ በርስ የሚጋጩት፤ ማለትም አንድ አይነት አንቀጽ በሁሉቱም መጽሐፍት የተለያዩ ሀሳቦችንና መልዕክቶችን ሲያነንጸባረቁ

ይስተዋላል። ይህም እንደ ሰው ፍላጎት መታረሙንና መሻሻሉን ግልጽ ያደርግልናል። ከሁለቱም መጽሐፍት አንድ ዓይነት አንቀጽ በማውጣት በጥቂቱ እናነጻጽር፡-

| 1954 ዓ.ም ዕትም | 1980 ዓ.ም ዕትም |
|---|---|
| «አሁን ተፈርዶበታል» በዮሐንስ መንጌል 3፡18 | «ገና ድሮ ተፈርዶበታል» በዮሐንስ ወንጌል 3፡18 |

ትክክለኛው የአምላክ ቃል "አሁን ተፈርዶበታል" ወይስ "ገና ድሮ ተፈርዶበታል" የሚለው ነው?

| | |
|---|---|
| «እውነት የነገርኋችሁን ሰው ለትገደሉኝ ትፈልጋላችሁ?» በዮሐንስ ወንጌል 8፡40 | «እውነት ነገርኳችሁ እናንተ ግን ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ?» በዮሐንስ ወንጌል 8፡40 |

"ሰው" የምትለዋን የአምላክ ቃል በ1980 ዕትም ለምን እንድትወገድ ተደረገች? የኢየሱስ (ዐ.ሰ) ሰውነት ለመሸሸግ ይሆን? ነው ወይስ ተረስቶ ነው?

| | |
|---|---|
| «ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበር፤» በሐዋርያት ሥራ 2፡22 | «ከእግዚአብሔር ዘንድ ለእናንተ የተገለጠው መለኮታዊ ስልጣን ያለው ነው፤» በሐዋርያት ሥራ 2፡22 |

አሁንም በድጋሜ በ1980 ዕትም ላይ "ሰው ነበር" የምትለዋ ቃል እንድትሰረዝ መደረጓ ለምን?

| | |
|---|---|
| «ከወንድሞቻቸው መካከል እንደ አንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ፤» በኦሪት.ዘዳግም 18፡18 | «ስለዚህም እንደ አንተ ያለ ነብይ ከሕዝባቸው መካከል አስነሳላቸዋለሁ፤» በኦሪት.ዘዳግም 18፡18 |

"ከወንድሞቻቸው" የምትለዋን የትንቢት ቃል ምን ያህል ግልጽ ያልሆነችንና የተወሳሰበች ቃል ብትሆን ነው ወደ ሕዝቦቻቸው መካከል ወደምትለው መቀየር

ያስፈለገው? “ከወንድሞቻቸው” ማለት የእስራኤል ወንድሞች የሆኑትን አረቦችን ስለሚያመላክት ይህንን ለመደበቅ ሲባል ቀለል ባለ አማርኛ እትም ሽፋን “ሕዝባችን” ወደሚለው መቀየር አስፈለገ።

| 1954 ዕትም | 1980 ዕትም |
| --- | --- |
| ‹‹የሴም ትውልድ ይህ ነው። ሲም የመቶ ዓመት ሰው ነበር አረፋክስንም ከጥፋት ውኃ በኋላ በሁለተኛው ዓመት ወለደ። ሴምም አርፋክሰድን ከወለድ በኋላ አምስት መቶ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ ሞተም አርፋክስደም መቶ ሰላሳ አምስት ዓመት ኖረ ቃይንንም ወለደ፤ አርፋክሰደም ቃይንምን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም ቃይንምም መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ሳላንም ወለደ፤ ቃይምም ሳላን ከወለደ በኋላ ሶስት መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ሳላም መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ዔቦርም ወለደ፤ ሳላም ዔቦርን ከወለደ በኋላ ሶስት መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተሞ ዔቦርም መቶ ሰላሳ አራት ዓመት ኖረ ፋሲቅንም ወለደ፤ ዔቦርም ፋሲቅን ከወለደ በኋላ አራት መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ መንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ሞተም። ፋሲቅም መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ራግውንም ወለደ፤ ራግውንም ከወለደ በኋላ ፋሲቅ | ‹‹የሴም ዝርያዎች የሚከተሉት ናቸው። ከጥፋት ውኃ በኋላ ሁለት ዓመት ቆይቶ ሴም 100 ዓመት በሆነው ጊዜ አርፋክሳድ የተባለ ልጅ ወለደ፤ አርፋክሳድን ከወለደ በኋላ 500 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆች ወለደ። አርፋክሳድ 35 ዓመት ሲሆነው ሼላህን ወለደ። ከዚህ በኋላ 403 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። ሼላህ 30 ዓመት ሲሆነው ዔቦርን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 403 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም መንዶች ልጆችንና ሴቶች ወለደ። ዔርቦ 34 ዓመት ሲሆነው ፈሌግን ወለደ፤ ከዚያ በኋላ 430 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። ፈሌግ 30 ዓመት ሲሆንው ረዑን ወለደ። ከዚህ በኋላ 209 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶቸ ልጆችን ወለደ። ረዑ 32 ዓመት ሲሆነው ሰሩግን ወለደ፤ ከዚያ በኋላ 207 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። ሰሩግ 30 ዓመት ሲሆነው ናኮርን ወለደ፤ |

| | |
|---|---|
| ሁለት መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ሞተም። ራግውም መቶ ሰላሳ ሁለት ዓመት ኖረ ሴሮህንም ወለደ፤ ራግውም ሴሮህን ከወለደ በኋላ ሁለት መቶ ሰባት ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ሴሮህም መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ናኮርንም ወለደ፤ ናኮርንም ከወለደ በኋላ ሴሮህ ሁለት መቶ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ፤ ሞተም። ናኮርም መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ ታራንም ወለደ፤ ታራንም ከወለደ በኋላ ናኮር መቶ ሀያ ዘጠኝ ዓመት ኖረ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለድ፤ ሞተም ታራም መቶ ዓመት ኖረ አብራምንና ናኮርን ሐራንንም ወለድ።›› በኦሪት.ዘፍጥረት 11፡10-26 | ከዚህ በኋላ 200ዓመት ኖረ፤ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችን ወለደ። ናኮር 29 ዓመት ሲሆነው ታራን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 119 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶች ልጆችና ቶች ልጆችን ወለደ። ታራ 70 ዓመት ከሆነው በኋላ አብራሃምን ናኮርንና ሃራንን ወለደ።›› በኦሪት.ዘፍጥረት 11፡10-26 |

| **1954 ዕትም** | **1980 ዕትም** |
|---|---|
| ‹‹የአዳም የትወልድ መጽሐፍ ይህ ነው። እግዚአብሔር አዳምን በፈጠረ ቀን በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው ባረካቸውም። ስማቸውንም በፈጠረበት ቀን አዳም ብሎ ጠራቸው። አዳምም ሁለት መቶ ሰላሳ ዓመት ኖረ ልጅንም በምሳሌው እንደ መል ወለደ ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው ስሙንም ሴት ብሎ ጠራው አዳምም ሴትን ከወለድ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ዓመት ሆነ ወንዶችንም | ‹‹የአዳም ዝርያዎች የስም ዝርዝር ከዚህ የሚከተለውን ነው፤ እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ በራሱ አምሳያ ፈጠራቸው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው፤ በረካቸው፤ ሰው ብሎም ሰየማቸው። አዳም መቶ ሰላሳ ዓመት በሆን ጊዜ በመልክ እርሱን የሚመስል ወንድ ልጅ ወለደ፤ ሴት የሚል ስም |

| | |
|---|---|
| ሴቶችንም ወለደ። አዳምም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ዓመት ሆነ፤ሞተም። ሴትም ሁለት መቶ አምስት ኖረ ወለደ።" አምስት ዓመት ኖረ ሄኖለንም ወለደ፤ ሴትም ሄኖስን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ሰባት ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ሴትም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ አስራ ሁለት ዓመት ሆነ፤ ሞተም። ሄኖስም መቶ ዘጠኝ ዓመት ኖረ ቃይናንም ወለደ፤ ሄኖለም ቃይናንን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ አስራ አምስት ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ሄኖለም የኖረበት ዘመን ሁለት ዘጠኝ መቶ አምስት ዓት ሆነ፤ ሞተም። ቃይናንም መቶ ሰባ ዓመት ኖረ መላልኤልም ወለደ፤ ቃይናንም መላልኤልንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ አርባ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ቃይናንም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ አሥራ ዓመት ሆነ፤ ሞተም። መላልኤልንም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖረ ያሬድንም ወለደ፤ መላኤልንም ያሬድን ከወለደ በኋላ የኖረው ሰባት መቶ ሰላሳ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። መላልኤልም የኖረበተ ዘመን ሁሉ ስምነተ መቶ ዘጠና አምስት ዓመት ሆነ፤ ሞተም። ያሬደም መቶ ስድሳ ሁለት ዓመት ኖረ ሄኖክንም ወለደ፤ ያሬድም ሄኖክነ ከወለደ በኋላ የኖረው ስምንት መቶ ዓመት ሆነ፤ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ያሬድም የኖረበት ዘመን ሁሉ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ሁለት | አወጣለት። ከዚህ በኋላ አዳም 800 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 930 ዓመት ሲሆነውም ሞተ። ሴት 105 ዓመት ሲሆነው" ሄኖስን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ ሴት 807 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 912 ዓመት ሲሆነውም ሞተ። ሄኖክ 90 ዓመት ሲሆነው ቃይናንን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 815 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 905 ሲሆነውም ሞተ። ቃይናንም 70 ዓመት ሲሆነው መላልኤልን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 840 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 910 ሲሆነውም ሞተ። መላኤል 65 ዓመት ሲሆነው ያሬድን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 830 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 895 ሲሆነውም ሞተ። ያሬድ 162 ዓመት ሲሆነው ሔኖክን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ 800 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ወለደ፤ ዕድሜው 962 |

| | |
|---|---|
| ዓመት ሆነ፤ሞተም። ሄኖክም መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ኖረ ማቱሳላንም ወለደ፤ ሄኖክም አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ ማቱሳላንም ከወለደ በኋላ የኖረው ሁለት መቶ ዓመት ሆነ፤ ወንዶችንም ሴቶችንም ወለደ። ሄኖክም የኖረበት ዘመን ሁሉ ሶስት መቶ ስድሳ አምስት ዓመት ሆነ።…" ኦሪት.ዘፍጥረት 5፡1-23 | ሲሆነውም ማቱሳላን ወለደ፤ ከዚህ በኋላ ሔኖክ የእግዚአብሔርን መንገድ በመከተል 300 ዓመት ኖረ፤ ሌሎችንም ወንዶችና ሴቶችን ወለደ፤ ዕድሜው 365 እስኪሆነው ድረስ ኖረ፤…" ኦሪት.ዘፍጥረት 5፡ 1-23 |

| 1954 መጽሐፍ ቅዱስ | 1980 መጽሐፍ ቅዱስ |
|---|---|
| 1. ሴት ሲወለድ አዳም ዕድሜው 230 ዓመት ነበር። | 1. ሴት ሲወለድ አዳም ዕድሜው 130 ዓመት ነበር። |
| 2. ሴት ከተወለደ በኋላ አዳም የኖረው 700 ዓመት ነበር። | 2. ሴት ከተወለደ በኋላ አዳም የኖረው 800 ዓመት ነበር። |
| 3. ሄሮስ ሲወለድ ሴት ዕድሜው 205 ዓመት ነበር። | 3. ሄኖስ ሲወለድ ሴት ዕድሜው 105 ዓመት ነበር። |
| 4. ሄኖስ ከተወለደ በኋላ ሴት የኖረው 707 ዓመት ነበር። | 4. ሄኖስ ከተወለደ በኋላ ሴት የኖረው 807 ዓመት ነበር። |
| 5. ቃይናን ሲወለድ ሄኖክ ዕድሜው 190 ዓመት ነበር። | 5. ቃይናን ሲወለድ ሄኖስ ዕድሜው 90 ዓመት ነበር። |
| 6. ቃይናን ከተወለደ በኋላ ሄኖስ የኖረው 715 ዓመት ነበር። | 6. ቃይናን ከተወለደ በኋላ ሄኖስ የኖረው 815 ዓመት ነበር። |
| 7. መላልኤል ሲወለድ ቃይናን ዕድሜው 170 ዓመት ነበር። | 7. መላልኤል ሲወለድ ቃይናን ዐእድሜው 70 ዓመት ነበር። |
| 8. መላላኤል ከተወለደ በኋላ ቃይናን የኖረው 740 ዓመት ነበር። | 8. መላልኤል ከተወለደ በኋላ ቃይናን የኖረው 840 ዓመት ነበር። |
| 9. ያሬድ ሲወለድ መላልኤል ዕድሜው 165 ዓመት ነበር። | 9. ያሬድ ሲወለድ መላልኤል |

| | |
|---|---|
| 10. ያሬድ ከተወለደ በኋላ መልልኤል የኖረው 730 ዓመት ነበር።<br>11. ማቱሳላ ሲወለድ ሄኖክ ዕድሜው 165 ዓመት ነበር።<br>12. ማቱሳላ ከተወለደ በኋላ ሄኖክ የኖረው 200 ዓመት ነበር። | ዕድሜው 65 ዓመት ነበር።<br>10. ያሬድ ከተወለደ በኋላ መላልኤል የኖረው 830 ዓመት ነበር።<br>11. ማቱሳላ ሲወለድ ሄኖክ ዕድሜው 65 ዓመት ነበር።<br>12. ማቱሳላ ከተወለደ በኋላ ሄኖክ የኖረው 300 ዓመት ነበር። |

እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ በየጊዜው እንደ አስፈላጊነቱና አመቺነቱ እንደሚቀይሩት እንመልከት፡ "ንቁ" በመባል የሚታወቀው ወርሃዊ የይሖዋ ምስክሮች መጽሔት ላይ "ተወዳጅነትን ያገኘ መጽሐፍ ቅዱስ?" በሚል ርዕስ ስር የሚከተለውን አስፍሯል፡- "ምዕመናን ስለ ሶስተኛው ዓለም የዕዳ ጫና፤ ስለ ፍትሐዊ ንግድና ስለ መሳሰሉት ጉዳዮች እንዲያስቡ ለማድረግ ሲባል ከመጽሐፍ ቅዱስ የተውጣጡ ጸሎቶችንና መዝሙራን በሚገኙበት የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን የጸሎት መጽሐፍ ላይ ብዙ ለውጥ ተደርጓል ሲል ሮይተርስ የተባለው የዜና አገልግሎት ዘግቧል። ***ዘ ፓኬት ትሬይስ ፎር ፒስ ኤንድ ጀስቲስ*** የተባለው መጽሐፍ በጌታ ጸሎት ላይ የሚገኘውን "የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን" የሚለው የኢየሱስ ቃል "መሬታችንን መልሰን ስናገኝ ወይም የተሻለ ደመወዝ ማግኘት ስንችል የዕለት እንጀራችንን ሰጠኸኝ ማለት ነው" በሚል ለውጦታል። በተመሳሳይ "በሞት ሸለቆ ጥላ ውስጥ፤ብንሄድ እንኳ" የሚለው የመዝሙር 23 ቃል እንዲወጣ ተደርጎ "ድብልቅልቅ ያለ ጠብና ብጥብጥ ቢነሳ እንኳን አንፈራም" በሚል ቃል ተተክቷል።"[26]

[26] ምንጭ፡- /"ንቁ" ሰኔ 2005 የይሖዋ ምስክሮች ወርሃዊ መጽሔት/

# የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላትና በውስጡ የያዘው እምቅ ሚስጥር።

በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ክርስቲያን ዘንድ “መጽሐፍ ቅዱስ” እንጂ “የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት” እምብዛም አይታወቅም። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ከየት እንደ መጣ ወይም ከማን እንደተወሰደ በግልጽ የሚያውቁት ነገር የለም። በእምነቱ ሰባኪያን ዘንድም “መጽሐፍ ቅዱስን” ከፊሉን ያስተምሩዋቸዋል እንጂ “የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላትን” ስሙ ሲጠቀስ አይስተዋል። አንድ “እምነት” እምነቱ እውነተኛ ለመሆኑ እና መመሪያ መጽሐፉም ትክክለኛ “የአምላክ ቃል” ለመሆኑ ምንጩ መታወቅ አለበት፤ ተከታዩም የዚህን መመሪያ ምንጭ እስካልታወቀ ድረስ በቂ እውቀትን ጨብጦ ሳይሆን ያለ በቂ እውቀት በደመ ነፍስ መከተሉ አይቀሬ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ከሆኑት መጽሐፍት የተወሰነውን በመውሰድ መቼ እንደተፃፉ፣ ማን እንደፃፋቸው እንዴት እንደተፃፉ ለመመልከት እንሞክራለን።

**የኦሪት ደራሲ፡-** ኦሪት ዘፍጥረት፣ ኦሪት ዘጸአት፣ ኦሪት ዘሌዋውያን፣ ኦሪት ዘኁልቁ እና ኦሪት ዘዳግም ሙሴ ፃፋቸው ተብለው የሚነገርላቸው አምስቱ መጻሕፍት እውነት ሙሴ ነው የጻፋቸው? ‹‹“… ከሙሴ በፊት ስለነበሩ አባቶች ታሪክ አስቀደመው ሌሎች ጽፈው ይሆናል። እንዲህም ከሆነ ታሪካቸውን አንድ ላይ ሰብስቦ ሊጽፈው ይላል። ሆኖም ሙሴ ጻፈው አይልም፤ ሙሴ ስለ ራሱ ሞት (ዘዳግም 34.1-12) ከሞት በኋላ ስለሆኑት ድርጊቶች የፃፈ አይደለም። ከሙሴ በኋላ የነበሩት ፀሐፊዎች አልፎ አልፎ ማብራሪያ የሰጡበት ይመስላል።”[27]

ኦሪትን ሙሉ በሙሉ ሙሴ ፃፈ እየተባለ በሐሰት ይሰበካል፤ ነገር ግን በውስጡ የያዘው ከሙሴ በፊት ስለ ነበሩት የአባቶች ታሪክና ሌሎችን ታሪኮች እንጂ “የአምላክ ቃል” አይደለም። በተጨማሪም “ሌሎች ጽፈው ይሆናል” የሚለው ሐረግ የፀሐፊው ማንነት እንደማይታወቅ ያሳያል፤ ሙሴ ነው የፃፈው ለሚለው ከሞተ በኋላ ያለውን ታሪክ እና ሞቶ የት እንደተቀበረ እንዴት ሊጽፈው እንደቻለ ሊቃውንቶችን እንኳን ግራ አጋብቶ “እሱ የጻፈው አይመስልም” ወደሚለው ድምዳሜ አድርሷቸዋል። ታዲያ ማንነታቸው ያልታወቁ የአምላክን ቃል ጻፉ ቢባል

[27] ምንጭ /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

አይደንቅዎትምን? እዚህ ላይ ሩት ስምትባል የዳዊት ቅድመ አያት ታሪክ ነው የሚተርከው ሩት የታሪኩ ባለቤት እናት እንጂ የመጽሐፉን ፀሐፊ አይደለችም፤ ሩት ለመፃፉዋ ማስረጃ የለም። ስለዚህ የሩትን ታሪክ የጻፈው ማን ነው?

**መጽሐፈ ሳሙኤል፦** "የሳሙኤል መጻሕፍት፤ ግን ማን እንደፃፉቸው አልተገለጠም ሆኖም እነሳሙኤል የዘመናቸውን ታሪክ የፃፉ መሆኑ ታውቋል።"[28] ለዚህ ብዙ ማብራሪያ አያስፈልገውም ግልጽ ነውና "ማን እንደጻፉቸው አልተገለጠም" የሚለው ቃል ጸሐፊው እንደማይታወቅ በግልጽ አመላካች ነው። "እነ ሳኤሙል የዘመናቸውን ታሪክ የጻፉ መሆኑ ታውቋል" ከዚህ አባባል የምንረዳው ነገር ቢኖር ጸሐፊዎችም የጻፉት የአምላክን ቃል ሳይሆን የዘመናቸውን ታሪክ መሆኑን ነው።

**መጽሐፈ ነገሥት፦**" መጽሐፈ ነገሥት፤ ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ ንጉሶች የሚተርኩ 1ኛና 2ኛ ነገሥት መጻሕፍት ነው። ከዳዊት ልጅ ከሰለሞን አንስቶ እስከ ይሁዳ መንግሥት ማለቂያ ድረስ የሁለቱን የእስራኤልና የይሁዳን መንግሥታት የነገስታትን ታሪክ ይተርካሉ። የ400 ዓመት ታሪክ ነው። የነገሥታት ታሪክ በሙሉ አስቀድሞ በ1ኛ መጽሐፍ ብቻ ተጽፎ ነበር። 70 ሊቃናት ግን ወደ ግሪክ ቋንቋ በተረጎሙበት ጊዜ መጽሐፉ በሁለት ተከፈለ። መጽሐፉ የተጻፈው ንጉሱ ዮአኪን ከሞተ በኋላ ነውና ምናልባት በስደት ዘመን በባቢሎን አገር ሳይጻፍ አልቀረም። (2ነገ 25፤ 29፡30)። ጸሐፊው ማን እንደሆነ ግን አልታወቀም። ታሪኩን ሲጽፍ ደራሲው ከሌላ መጽሐፍ ደግሞ ቀድቶ እንደጻፈ ታውቋል። (1ገነ.11፡41፤14፡19-29)" ከመጽሐፍ ነገሥት የምንረዳው ከሰሎሞን እስከ ይሁዳ መንግስት ማለቂያ ድረስ የነበረውን የእስራኤልና የይሁዳን ነገሥታት ታሪክ ይተርካል የ400 ዓመት ታሪክ ነው። ሰዎች የራሳቸውን ታሪክ ጻፉ እንጂ "የአምላክን ቃል" አይደለም የጻፉት። ሌላው የነገስት መጽሐፍ በአንድ የተጠቃለለ እንጂ 1ኛ ነገሥት 2ኛ ነገሥት በሚል የተከፋፈለ አልነበረም፤ 70 ሊቃናት ወደ ግሪክ ቋንቋ ሲተረጉሙት በሙብታቸው 1ኛ ነገሥት እና 2ኛ ነገሥት በሚል ከፋፈሉት። የሚያስገርመው ጸሐፊው ማን እንደሆን አለመታመቁ እና ደራሲው

---

[28] ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

ሲጽፍ ከሌላ መጽሐፍ ቀድቶ መጻፉን ነው ታዲያ ይህንን እንዴት የአምላክ ቃል ነው ልንቀበል እንችላለን?

**ዜና መዋዕል፡-** “ብዙ መምህራን መጻሕፍቱን የጻፈው ካህኑ እዝራ ነው ይላሉ፤ ይህም እውነት ይመስላል። ሆኖም የትውልድ ዝርዝሩ ከዕዛራ ዘመን በኋላ ያለውን ዘመን ስለሚያመለክት ምናልባት ሌላ ሰው ጨምሮበት ይሆናል። ዘመኑ ከክርስቶስ በፊት 400 ዓመት ያህል ይሆናል። ጸሐፊውም ሲጽፍ የነገሥታት ታሪክ በተጻፈባቸው በሌሎች ጽሑፎች መጠቀሙ ታውቋል።” 2ኛ ዜ.መ 9፡29፤ 12፡15 20፡34፤ 32፡32) [29]

በዚህ በመጽሐፍ ዜና መዋዕል የምንገነዘበው ጽሐፉን የጻፈው እዝራ ነው የሚሉ ሰዎች ቢኖሩም ታሪኩ ከዕዝራ ዘመን በኋላ አይችልምና ነው። “ሌላ ሰው ጨምሮበት የሆናል” የሚለው ቃልም የጸሐፊውን ማንነት ባለመታወቁ እንደ ዋና ማስረጃ ሊጠቀስ ይችላል። ጸሐፊው ሲጽፍ በነገስታት ታሪክ በተጻፈባቸው በሌሎች ጹሑፎች መጠቀሙ ታውቋል። ስለዚህ የተቀላቀለና ምንጩ የማይታወቅ መሆኑ ግልጽ ነው።

**መጽሐፍ እዝራ፡-** “የእዝራ መጽሐፍ፤ መጽሐፉ የእስራኤል ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ እንደተመለሱ ቤተ መቅደስንም እንደገና እንደሰሩ ይናገራል። መጽሐፍ 537 አንስቶ ዕዝራ ራሱ ወደ እየሩሳሌም እስከመጣበት እስከ 458 ከክ.በ. ያለውን ታሪክ ይተርካል። ቤተ መቅደሱን የጨረሱት የእስራኤል ሕዝብ ቤተ መቅደሱን የጨረሱት በ516 ከክ.በ. ነው።ዕዝራ ራሱ መጽሐፉን ወይም መጽሐፉ የተመሰረተባቸውን ረቂቆች የጻፈ ይመስላል።”[30]

መጽሐፈ ዕዝራ የሚተርከው የእስራኤልን ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ የተመለሱበትን ጊዜና ዘመን ነው” ዕዝራ ጽሐፉን ወይም የተመሰረተባቸውን ረቂቆች የጻፈ ይመስላል።” ማለት ጥርጣሬን የሚያሳይ ነው። “መምሰል” እና “መሆን” የተለያዩ ናቸውና። ስለዚህ እዝራ የጻፈው ይመስላል ከማለት ለምን

[29] ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት/

[30] ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱ መዝገበ ቃላት/

በእርግጠኛነት ዕዝራ ጻፈው አይባልም?ምክንያቱም ዕዝራ ለመጻፉ ማረጋገጫ ስለሌለው ነው።

**መጽሐፍ አስቴር፡-** "አስቴር፡- በፋርስ ቋንቋ "አስቴር" ማለት "ኮከብ" ማለት እንደሆነ ይነገራል። አንዳንዶቹ ግን "አስቴር" ማለት "አሽታሪ" የሚባል ከአንዲት የባቢሎን ጣኦት ስም የተገኘ ነው ይላሉ። መጽሐፈ አስቴር፤ መጽሐፉ በፋርስ መንግስት ጊዜ በምርኮኝነት ይኖሩ በነበሩ እስራኤላውያን ላይ የደረሰውን ስደትና ከሞት አደጋ መዳናቸውን ይተርካል። መጽሐፉ አርጤክስ ከሞተበት ከ465 ነክ.በ. እንደተጻፈ ይገመታል። መጽሐፉን የጻፈው ማን እንደሆነ አይታወቅም።ሆኖም ጸሐፊው የፋርስን ቤተ መንግስት ኑሮና ደንብ ያወቀ አይሁዳዊ ይመስላል። በየዓመቱ በፋሪም ዓመት በዓል አይሁድ ስለሚያነቡት መጽሐፍ የታወቀ ሆነ። መጽሐፍ የተጻፈው በዕብራይስጥ ነው። በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም።" [31] "እንደተጻፈ ይገመታል" "መጽሐፉን የጻፈው ማን እንደሆነ አይታውቅም።" "በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አልተጠቀሰም።" ተብሎ መገለጹ በጣም ግራ የሚያጋባ ምንጭ እንደሆነ ያመላክታል፤ ምክንያቱም የፈጣሪ ቃል በግምት የሚጻፍ አይደለም።

**መጽሐፈ ኢዮብ፡-** "የኢዮብ መጽሐፍ፤ የመጽሐፉ የመጀመሪያውና የመጨረሻው ክፍሎች በስድ ንባብ ተጻፉ፤ ከም.3 እስከ 42፡6፤ ድረስ ያለው ግን በግጥም ተጽፏል። በውስጡ ከሚገኘው የጥበብ ጥልቀትና ከስነ ጽሑፍ ውበቱ የተነሳ የተደነቀ ነው። ***ጸሐፊው ማን እንደ ነበረ አልታወቀም***።" የኢዮብ ዝና ከጥንት ጀምሮ ቢታወቅም እስከ አሁን ድረስ የቆየው "መጽሐፈ ኢዮብ" ለብዙዎች በሰለሞን ዘመን ወይም ከዚያ በኋላ የተጻፈ ይመስላቸዋል። ሌሎችም በአብራሃምና በይስሐቅ ዘመን የተጻፈ ነው ይላሉ። ሙሴ ግን የእስራኤል ሕዝብ የመጀመሪያ መሪያ ነብዩ ስለነበረ ከአምስቱ "ኦሪት መጻሕፍት ጭምር መጽሐፈ ኢዮብን የጻፈው እርሱ እንደሆነ የሚገምቱም አሉ።" "ጸሐፊው ማን እንደነበር አልታወቀም" "በሰለሞን ዘመን ወይም ካዛ በኋላ የተጻፈ" "በአብራሃምና ይስሐቅ ዘመን" "በሙሴ ዘመን ተጻፈ መሆኑን የሚገምቱም አሉ"

[31] ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱ መዝገበ ቃላት/

ተብሎ በየትኛው ነብይና ዘመን መጻፉ ለመታወቁ የፈጣሪ ቃል ነው ብለን እንዴት መቀበል እንችላለን?

**መዝሙረ ዳዊት፡-** “መዝሙረ ዳዊት፤ መዝሙራቱ ሁሉ ዳዊት የጻፋቸው አይደሉም ሆኖም በአርእስቱ ላይ የዳዊት ስም በ82 ተጠቅሷል፤ በተቀሩት የቆሬዋች ልጆች ስም በ11 ተጠቅሷል። የአሳፍ በ12 ተጠቅሷል የኤማንና የኤታን የሙሴም በ3 ተጠቅሷል፤**መዝሙራትን ማን እንደሰበሰበ አልታወቀም፤** ቢሆንም በ1ኛ ዜ.መ 16 ላይ ዳዊት በታቦቱ ፊት የሚዘምሩ መዘምራን እንዳደራጀ ስለምናነብ እረሱ ስራውን ጀምሮ ይሆናል። ከእርሱ በኋላ ግን ሌላ ሰው ነገሩ ገብቷል፤...” [32] ዳዊት መዝሙር ዳዊትን ሁሉንም ካልጻፈ ዳዊት የዳፋቸው ተብሎ ለምን ይታመናል? ሰብሳቢያቸውም ካልታወቀ ደግሞ የዳዊት ለመሆናቸው ምን ማረጋገጫ አለ?

**መጽሐፈ ምሳሌ፡-** “መጽሐፈ ምሳሌ፤... ይሁን እንጂ ምሳሌዎቹ ሁሉ የሰለሞን አይደሉም። “የጠቢባን” የሳሙኤልም አሉ፤... መጽሐፉ መቼ ተጻፈ? ቢባል ምናልባት ሰለሞን በዘመነ መንግስቱ ማለትም በ950 ከክ.በ. ከምርኮው ሲመለሱ መጽሐፉን አጠናቀው ሳይጽፉት አልቀረም።”

**መጽሐፈ መክብብ፡-** “መክብብ፤ መክብብ ማለት ሰባኪ ማለት ወይም አስተማሪ ማለት ነው። በዚህም መጽሐፍ የሚሰብክ የሚያስተምር ሰለሞን ነው። በኢየሩሳሌም የነገሰ የዳዊት ልጅ ተባለ ጥበብም በአያሌው ተጠቅሷል ምሳሌዎችንም መሰብሰቡ ታውቋል፤ የዕብራይስጡ አጻጻፍ የኋላ ዘመን ነው እንጂ የሰለሞን ዘመን አይደለምና ደራሲው ሌላ ነው የሚሉ ቢኖሩም ሌላ ሰው ይጻፋው እንጂ ትምህርቱ ያለ ጥርጥር የሰለሞን ነው።” [33]

**መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፡-** “መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን፤ ማለት ከሁሉ የሚበልጥ የሰለሞን መዝሙር ማለት ነው፤ የሁለት ፍቅረኞች ንግግር ነው። የፍቅረኞች ንግግር ግጥም ነውና አነጋገሩ ከተለመደው አነጋገር የተለየ ነው፤ ትርጉሙ ብዙውን ጊዜ ያስቸግራል። በሙሽራው ዓይን ሙሽራይቱ በገጽዋ ነውር

32 ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገብ ቃላት/

33 ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

ፈጽሞ የሌለባት የውብ መጨረሻ ናት፤ እንደዚሁም ሙሽራይቱ ሙሽራውን ስትመለከት ፈጽሞ ያማረ እኩያ የሌለው ከእልፍ የተመረጠ ሆኖ ታገኘዋለች፤ ይህም ሁሉ በፍቅረኞች አነጋገር በመነገሩ በአንዳንድ ሰዎች ምስጢሩን ባለመስተዋል ይነቅፉታል ሆኖም በእርግጥ ቅዱስ ምሳሌ ነው።"[34] ወሲብ ቀስቃሽ ቃላቶች እንዴት ቅዱስ ምሳሌዎች ተብለው ሊቀርቡ ይችላሉ?

**የኢሳይያስ ትንቢት፡-** "ኢሳይያስ የነገሥታትን ታሪክ መጻሕፍትና ትንቢት ፃፈ፤ ባለፉት 200 ዓታት ውስጥ ግን ብዙ ምርምራ ስለተደረገ በዘመናውያን ሊቃውንት መካከል ልዩ ልዩ ሐሳብ ተገኝቷል። ኢሳይያስ ራሱ ከም. 1-39 ከሚገኙት ትንቢቶች የሚበልጡትን ጽፎ ይናል እንጂ ም. 40-55 በባቢሎን ምርኮ ጊዜ በነበረ ሌላ ነብይ 56-66 ደግሞ ከምርኮ በኋላ በነበረ ሌላ ነብይ ተጽፏል የሚለው አሉ። ሌሎች ደግሞ ም.1-39 እና ም.56-66 በልዩ ልዩ ክፍል ከፋፍለው በብዙ ሰዎች እጅ የተፃፈ ይመስላል ይላሉ።"[35] ማንነታቸው ባልታወቀ ነብይ እንዲያውም ከነሱ ውጪ ባሉ በርካታ ሰዎች የተጻፈው ፅሁፍ እንዴት ትክክለኛ የሆነ የአምላክ ቃል ነው ብለን መቀበል እንችላለን?

**ትንቢተ ኢዩኤል፡-** "የኢዩኤል ትንቢት፤ ኢዩኤል የተናገረውን ትንቢት የያዘ መጽሐፍ። የተፃፈበትን ዘመን **ለማረጋገጥ አልተቻለም**፤ ኢዩኤል ትንቢት የተናገረው ከአሞጽ በፊት ነው የሚሉ ሊቃውንት አሉ፤ ከሚሊክያስ በኋላ ትንቢት የተናረገ የመጨረሻ ነብይ ነበር የሚሉም አሉ፤ ትንቢቱ የተነገረው በኢየሩሳም ይመስላል፤..."[36]

**ትንቢተ አብድዩ፡-** "አብድዩ ትንቢት፤ አብድዩ በኢዶምያስ ላይ ስለሚመጣው ፍርድ ተነበየ። ይህም የይሁዳ የመከር ቀን የናቡከደነፆር ሰራዊት ኢሩሳሌምን ያቃጠለበት ቀን ይመስላል። በዚህ ምክንያት አብድዩ ትንቢቱን የተናገረው ከዚያ ጊዜ በኋላ እንደ ነበር ይገመታል።"[37]

---

[34] ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

[35] ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

[36] ምንጭ፡- /የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

[37] ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

**ትንቢተ ዮናስ፡-** "የዮናስ ትንቢት፤ በሌሎች የትንቢት መጻሕፍት የሚገኘው ዋና ሐሳብ የትንቢት መልእክት የሚገልጽ ሲሆን በዚህ መጽሐፍ ግን የሚበልጠው ክፍል ስለ ራሱ ስለነብዩ የሚተርክ ነው። **መጽሐፉን የጻፈው ዮናስ ራሱ መሆኑ አልተገለጠም**፤ ነገር ግን ሌላ ሰው ከሌላ ሰውሰምቶ የጻፈው ይመስላል።"[38]

**ሰቆቃው ኤርምያስ፡-** "ሰቆቃው ኤርሚያስ፤ ሰቆቃው ማለት ሙሾ ልቅሶ ማለት ነው። ጸሐፊው ኤርሚያስ መሆኑን አለመሆኑ አልተረጋገጠም። ይሁን እንጂ ብዙ ሊቃውንት ኤርሚያስ ነው ይላሉ። **በመጽሐፉ ውስጥ የጸሐፊው ስም አይገኝም**፤ እንዲሁም በዕብራይስጥ በመጽሐፉ አርስት የኤርምያስ ስም አልተጠቀሰም። ሆኖም ጻሐፊው እንደ ኤርምያስ ኢየሩሳሌምን የሚወድ ውድቀትዋን አይቶ ያዘነና በስቃይዋ የተካፈለ ሰው መሆኑ አይጠራጥርም።"[39]

**የማቴዎስ ወንጌል፡-** "የማቴዎስ ወንጌል፤ እንደ ጥንት ቤ.ክ ትውፊት የመጀመሪያውን ወንጌል የጻፈው ማቴዎስ ነው። የማቴዎስ ወንጌል የተጻፈባቸው ዘመናት በብዙ ሊቃውንት የተለያዩ እንደመሆኑ ቢጠቀስም አንዳንዶች ማቴዎች ምንጌሉን የጻፈው ከ50 ዓ.ም በፊት እንደሆነና ሲያመላክቱ ሌሎች ግን ጸሐፊው የማርቆስና ወንጌል ተመልክቶ ኢየሩሳሌም ከወደቀችበት ከ70 ዓ.ም በኋላ እንዳዘጋጀው ይናገራሉ።"[40]

**የማርቆስ ወንጌል፡-** "የማርቆስ ወንጌል፤ ጸሓፊው ማርቆስ የተባለው ዮሐንስ ነው። የቀደሙት የቤ.ክ አባቶች ይህ ወንጌል ለሮማውያን በ60 ዓ.ም ገደማ በሮም ሳይጻፍ እንዳልቀረ ጠቁመዋል።"[41]

**የሉቃስ ወንጌል፡-** "የሉቃስ ወንጌል፤ ሉቃስ ወዳጁ ለሆነው ቴዎፊወሎስ በአክብሮት ሲጽፍ ያላያቸውን ነገሮች ካዩአቸው የዓይን ምስክሮች አረጋግጦ በብዙ ጥንቃቄ ተርኳል። የአጻጻፉም ዘዴ የተማረና በድርሰት ልዩ ሙያ ያለው ሰው መሆኑን ያሳያል። በሉቃስ 1፡1-4፤ ሐ.ሥ 1፡1-3። ሉቃስ የፃፈው ታሪክ

38 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/
39 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/
40 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/
41 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

የአርኬኦሎጂ ምርምር ትክክለኛ መሆኑን ያሳያል። ጳውሎስ በሮም ታስሮ ሳለ "የሐዋርያት ሥራ" በ64 ዓ.ም ገደማ ከጻፈው ወንጌሉን ደግሞ ከዚህ በፊት በ62 ዓ.ም ገደማ የጻፈ ይመስላል።[42]

**የዮሐንስ ወንጌል፡-** "ዮሐንስ ወንጌል፤ ስሙ በዚህ ወንጌል ባይጠቀስም "ኢየሱስ ይወደው የነበረው ደቀ መዝሙር" ሐዋሪያው ዮሐንስ እንደሆነ ይታወቃል። ይህን ወንጌል ሲጽፍ በመጀመሪያ በየትኛው ቀንና ሰዓት ከኢየሱስ ጋር እንደተገናኘ እንደዚሁም በስንት ሰዓት ክስተቶች እንደተፈጸሙ ይመዘግባል፤ 1፡40፤ 4፡6፡52፤ 19፡14። አንዳንዶች ከ85 ዓ.ም በኋላ ሌሎች ደግሞ ኢየሩሳሌም ከወደቀችበት ከ70 ዓ.ም በፊት ወንጌሉ **እንደተጻፈ ይገምታሉ**።"[43]

**የሐዋሪያት ሥራ፡-** "የሐዋሪያት ሥራ፤ "የሐዋሪያት ሥራ" ጳውሎስ ፍርድን ሲጠብቅ ላለ በ64 ዓ.ም ገደማ **እንደተጻፈ ይገመታል**።"[44]

**የያሻር መጽሐፍ፡-** "የያሻር መጽሐፍ፤ በዚህ መጽሐፍ ልዩ ልዩ የእስራኤል ታሪክ መዝሙርና ቅኔ የተጻፈ ይመስላል፤ ይህ መጽሐፍና የጦርነት መጽሐፍ አንድ ይሆን ይሆናል፤ መጽሐፉ በሰለሞን ዘመን የተጻፈ ይመስላል፤ **በኋላ ግን ጠፋ**።"[45] ይህ የያሻር መጽሐፍ በዘመናችን መጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ውስጥ አይገኝም። ከመጽሐፉ ውስጥ እንዲወገድ ተደርጓል።

**መጽሐፈ ኢያሱ፡-** "የኢያሱ መጽሐፍ፤ ይህ መጽሐፍ የእስራኤል ሕዝብ በእግዚአብሔር ሐይልና በኢያሱ መሪነት ከነዓን እንደያዙ ይተረካል። ኢያሱ ራሱ የሙሴን መጽሐፍ አነበበ፤ የሙሴን ሕግ በድንጋይ ጻፈ በሕይወቱ መጨረሻም ከሕዝቡ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን በጹሑፍ አስረዳ። (ኢያሱ 1፡8፤ 8፡32 24፡26)። **ጠቅላላው መጽሐፍ በዚያን ዘመን የተፃፈ ይመስላል**።"[46] መጽሐፍ ኢያሱ በውስጡ የያዘው በራሱ በኢያሱ መሪነት ከነዓንን እንደያዙ ይተርካል እንጂ። እንዲሁም ኢያሱ ከሕዝቡ ጋር ያደረገውን ቃል ኪዳን ይተርካል እንጂ

42 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

43 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

44 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

45 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

46 ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

"የእግዚአብሔር ቃል" አይደልም። "በዚህ ዘመን የተፃፈ ይመስላል" ይህ አባባል ደግሞ የሚያሳየን የተፃፈበት ዘመን በእርግጥኝነት መናገር አዳጋች እንደሆነ ነው።

**መጽሐፈ መሳፍንት፡-** "መጽሐፍ መሳፍንት፡- የመሳፍንትን ታሪክ ይተርካል። መጽሐፉ በሦስት ይከፈላል፡-

1. መሳፍንት የተነሱነት ምክንያት
2. የመሳፍንቱን ታሪክ
3. ስለ ዳን ጭቆናና ስለ ብንያም ኃጢአት

መጽሐፉን ማን እንደጻፈው ምን ጊዜ እንድተፃፈ እርግጡ ባይታወቅም አንኳ የጻፈው ሳሙኤል ወይም በሳሙኤል ዘመን ከነበሩት ከነብያት ወገን እንዱ እንደሆነ ይታመናል። ( ሳሙ 10፡10-12፡25)"[47] መጽሐፈ መሳፍንት የሚተርከው የመሳፍንትን ታሪክ ሲሆን መሳፍንት ስለ ተነሱበት ምክንያት ታሪካቸውንና ስለ ዳን ጭቆናና ስለ ብንያም ኃጢአት ይተርካል። እዚህ ጋ ልብ ይበሉ "መጽሐፉን ማን እንደፃፈው ምን ጊዜ እንደተፃፈ እርግጡ ባይታወቅ" እንዲሁም መቾ እንደተጻፈ

[47] ምንጭ፡-/የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት/

# ምዕራፍ ሀያ

## የክርስቲያን ጥያቄዎችና የሙስሊም መልሶቻቸው

## The Christian qutions and Muslim answers

በሁሉም ክርስቲያኖች አዘውትረው የሚጠየቋቸው ጥያቄዎች አሉ። ይህ ጥያቄ በሁሉም ክርስቲያኖች የተለመደ ጉዳይ ነው። ይህ ጥያቄ ለኔም ስለቀረበልኝ በተጠየኩት መሰረት ማስረጀን ማዕከል ያደረገ መልስ ለመስጠት እሞክራለሁ። ከእነዚህም ጥያቄዎች መካከል እስልምና በሰይፍ ነው የተስፋፋው ሃይማኖቱ በሰይፍ የተመሰረተ ነው በማለት በተከታታይ ይጠይቃሉ። ነገሩ “‹**ዝንጀሮ የራሷን ገጣባ ሳታይ በሌላዋ ትስቃለች**›” ነው። ለእያንዳንዱ ጥያቄ በቅደም ተከተል መልስ እሰጥበታለሁ።

መግለጫ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጥ. ጥያቄ | ክ. ክርስቲያን | መ.መልስ **ሙ** ሙስሊም | ማለት ነው፡፡ |

የመጀመሪያውን ፊደል በመውሰድ በአጭር ቃላት አሳጥሬ ተጠቅሜአለሁ።

**ጥ.ክ** እናንተ ሙስሊሞች እምነታችሁ የተስፋፋው በሰይፍ ነው። ስለዚህ የማስደድና እንቢ ካለም እንዲገዲል ይፈቀዳል ነብያችሁም በሰይፍ ተልከዋል። በአጠቃላይ እምነታችሁ በሰይፍና በጦርነት ነው የተስፋፋው የእኛ የክርስቲያኖች ሃይማኖት ግን በሰላም ነው የተስፋፋው።

**መ.ሙ** በመጀመሪያ ‹**ኢስላም**› የሚለው ቃል ምንን ያመለክታል ብለን ብንጠይቅ እኛ ሙስሊሞች ይህን ጥያቄ ለአንድ ክርስቲያን መቸም አንብበ እንደማይመልስ የታወቀ ነው። ድንገት እስልምናን የምትጠላው ለምንድን ነው ብትለው አሁንም መልሱ አንብበ ሳይሆን ጉረቤቱ ሙስሊም ሰለሆነ ነው ብሎ የሚመልስው እንጂ መልሱ ከዚህ አይዘልም። ለማንኛውም የሰይፍ ሃይማኖት ማን እንደሆነ ሁላችን የምናየውና የምንፈርድው ይሆናል።

‹**ኢስላም**› የሚለው ቃል ሰላም ከሚለው የአረበኛ ቃል የመጣ ሲሆን ትርጉ ራስን ለአንድ ፈጣሪ በማስገዛት የሚገኝ ሰላም ማለት ነው በመሰረቱ ሰላም ወደ አንድነት ይመራል። ለዚህ ደግሞ ሙስሊሞች የሚያሳዩት ሰላምነት በተግባር የሚታይ ነፀብራቅ ነው። ለምሳሌ፡- በክርስቲያኖች ዘንድ ጅሐድ ማለት ሙስሊም ያልሆኑትን መግደል ማለት ብለው ያስባሉ። ይህ ከሆነ በእነርሱ አገላለጽ፡- ቁርአን በሱረቱል አል-አንከቡት ቁጥር 6‹‹**የሚታገል ሰው የሚታገለው ለነብሱ (ለእርሱ) ነው**።›› ጅሐድ ማለት በእናንተ አባባል ነን ሙስሊሞችን መጋደል ከሆነ ለምን ቁርኣኑ የእናንተን ሐሳብ አልገደፈም? የእንግሊዘኛውምም ትርጉም ይኸውና፡- **and who ever strives hard he strives only for his own soul**. እንግዲህ የእንግሊዘኛው ትርጉምም ይህ ነው። ክርስቲያኖች የተለየ አክስፎርድ ከአላችሁ አሳዩን። ለማኛውም ጅሐድ ማለት ራስን ታግሎ ማሸነፍ (**stragle aganst**) ማለት ሲሆን ለምሳሌ፡- አንድ ሰው ዶክተር ለመሆን ጠንክሮ ያጠናል፤ በሌላ አባባል ጅሐድ እያደረገ ነው እንጂ የሰውን ነብስ እየገደለ አይደለም። ስለዚህ አንደ ሰው ነብሱን ከመጥፎ ነገሮች ታግሎ ራሱን ሲያሸንፍና መልካም ነገሮችን ሲሰራ ትልቅ ጅሀድ ነው። ለዚህ ነው ረሱል (ሰ.ዐ.ወ)‹‹**ራስን ታግሎ ማሸነፍ ታላቅ ጅሐድ ነው**›› ያሉት። እንዲሁም አላህ (ሱ.ወ) በሱረቱል አል-አንከቡት ቁጥር.6‹‹**የሚታገል ሰው ለነብሱ (እራሱ) ነው የሚታገለው**›› ብሏል። ታዲያ የሌሎችን ነብስ እየገደለ ነው ማለት ነውን? እንዲሁም የእራሱን ነብስ የሚገድለው እራሱ ነው እያለ ነውን? እውነቱ ይህ ሆኖ ሳለ እናንተ ክርስቲያኖች ሌላ ትርጉም ትሰጡታላችሁ። ለምሳሌ፡- ከእራሴ የሕይወት ተሞክሮ ስነሳ ቀላል ምሳሌ ይሆናል። ማለትም ወደ እስልምና ሲመጣ ማንም ሰይፍና ጦር መዘብኝ አይደለም። ነገር ግን ከሰይፍ የሰላ የእውነት ሰይፍ ስላለና ሐሰቶችን የሚበጥስ ከሰይፍ የባሰ የሐቅ መንገድ ስላለ ብቻ ነው። ያም ማለት የአላህ (ሱ.ወ) የሰላም ቃሉንና የጽድቅ መንገዱን በመናፈቅ ነው። ጥያቄ መጠየቅ የነበረብኝና የነበረብን እኛ ሙስሊሞች ነበር። ጉዳዩ “‹**የተራበ ሳለ የጠገበ ባሰ**›” ሆነና ነገሩ እናንተ በሰዎች ላይ ሰይፍ እየመዘዛችሁ የንጹህንን ደም እያፈሰሳችሁ የሌሎችን ሃይማኖት ትተቻላችሁ። የሰይፍ ሃይማኖት ማን እንደ ሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት፡- በኦሪት.ዘዳግሞ 20፡16-18 የቃል-ኪዳን መሬት ተብሎ ከመጠራው ከተማ ውስጥ በሚኖሩ ነዋሪዎች ላይ የሚደረግ ነው ወራራ አስመልክቶ የሚከናወነውን ድርጊት እንደሚከተለው እናነባለን፡- ***‹‹ነገር ግን አምላክህ እግዚአብሔር ርዕስት አድርጎ ከሚሰጥህ ከነዚህ አህዛብ ከተሞች ምንም ነብስ አታድንም።..........አምላክህ***

*እግዚአብሔር እንዳዘዘህ፤ ኬጢያዊያን፣ አሞራውያንንም፣ ከናዓውያንንም፣ ፌርዛውያንንም፣ ኤዊያውያንንም፣ ኢያቡሳዊያንንም ፈጽመህ ታጠፋቸዋለህ፡፡»*

ከላይ የተጠቀሱት ስድስት የብሔር የሕዝቦች አይነቶች በጥቅሱ ውስጥ በተገለጸው መልኩ ዘራቸው ከምድረ ገጽ እንዲጠፋ በእግዚብሔር ትእዛዝ ተወስኖባቸዋል፡፡ የሚቀርብላቸው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ እርሱም ሰይፍ ነው፤ እነዚህ ሕዝቦች ለመገደልና ለመውደም ፈርደ ገምድላዊ ውሳኔ እንዲበቁ ያረጋው አንዳችም ወንጀል ፈጽመው አይደለም፡፡ ‹**የቃል ኪዳን መሬት**› በሚሉት አካባቢ ተረጋግተው በሰላም በመኖራቸው ምክንያት ብቻ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሌሎች ኦሪታዊ ጥቅሶችና ወንጌልን ጨምሮ አሉ፡፡ በኦሪት.ዘፀአት 23፡23-24 *«"መልአኬ በፊት ይሄዳልና" ደግሞ ወደ አሞራውያንም ወደ ኬጢዊያንም ወደ ፌርዘዊያንም ወደ ከናውያንም ወደ ኤዊያውያንም ወደ ኢያቡሳዊያንም ያገባሃል፤ እኔም አጠፋቸዋለሁ፤ እንደ ስራቸው አትስራ፤ ነገር ግን ፈጽመህ አፍርሳቸው ሐውልታቸውንም ሰባብራቸው፡፡»* በኦረት.ዘኁልቁ 33፡51-56 *‹‹እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፡- ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡- ወደ ከነዓን ምድር ዮርዳኖስ ባሻገራችሁ ጊዜ የአገሩን ሰዎች ሁሉ ከፊታችሁ ታሰድዳላችሁ፤ የተቀረጹ ድንጋዮቻቸውን ሁሉ ታጠፋላችሁ፡፡ በኮረብታ ላይ ያሉት መስገጃዎቻቸውንም ታፈርሳላችሁ፤ ምድሪቱንም ሁሉ ለእናንተ ርስት አድርጌ ሰጥቻችኋለሁ፡፡ ምድሪቱንም ትወርሳላችሁ፤ ትቀመጡበታላችሁም፡፡---የአገሩንም ሰዎች ከፊታችሁ ባታሳድዱም ያስቀራችኋቸው ለዓይናችሁ እንደ ሾህ ለጎናችሁ ንደ ሚወጋ ነገር ይሆኑባችኋል፡፡ በምት በምትቀመጡበት ምድር ያስጨንቋችኋል፤ እኔም በእነርሱ አደርገው ዘንድ ያሰብኩትን በእናንተ አደርግባችኋለሁ፡፡»* እንዲያም ከዚህ ላይ ሰዎችን ካላስወጡና ካልተዋጉ ፈጣሪ እንደሚቀጣቸው ነው የሚነግረን፡፡ በኦሪት.ዘዳግም 6፡1-4 *«እግዚአብሔር ልትወርሳት ምድር ባመጣህ ጊዜ፡- ከፊትህ ብዙ አሕዛብን፤ ከአንተ የበለጡትን የበረቱትንም ሰባቱን አሕዝብ፤ ኬጢያውያን፣ ጌርጌያውንም፣ አሞራዊያውንም፣ ከናዊያውንም፤ ፌርዘዊያንም ኢያብሰዊውንም በመጣህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔርም በእጅህ አሳልፎ በሰጠው በመታሃቸውም ጊዜ ፈጽመህ አጥፋቸው፡፡ ከእርሱም ጋር ቃል-ኪዳን አታድርግ፤ አትማራቸው፤ ከእነርሱም ጋር አትጋባ፤ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጅ አትስጥ፤ ሴት ልጅህን ለወንድ ልጅህ አትውሰድ፡፡»* ከላይ በሳለፍነው ጥቅስ እግዚአብሔር በጥቅሱ የተወሱትን የሰባቱን ብሔር ሕዝቦች ከምድረ ገጽ

እንዲጠፉ አዟል። ከእነርሱ ጋር ምንም አይነት ስምምነት እንዳያደርግ፤ ማምለኪያ ስፍራዎቻቸው እንዲወድሙ፤ ጣዖቶቻቸው እንዲፈራርሱ፤ ምኩራቦቻቸው (የጸሎት ቦታቸውን) እግዚአብሔር ጥብቅና የማያወላውል ትዕዛዝ ሰጥቷል። እንዲህ በማለት፡- እነዚህን ***«ብሔሮች ባታጠፉቸው ግን እኔ በእነርሱ ላድርገው ዘንድ ያሰብኩትን በእናንተ ላይ አደርግባችኋለሁ»*** እያለም ያስጠነቅቃቸዋል። በኦሪት.ዘፀአት 32፡2 እንዲህ የሚል እናነባለን፡- ***«እነሱም የእስራኤል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የእናንተ ሰው ሁሉ ሰይፉን በወገቡ ላይ ይታጠቅ። በሰፈሩም ውስጥ በዚህና በዚያ ከበር እስከ በር ተመላለሱ፤ የእናንተም ሰው ሁሉ ወንድሙን፣ ወዳጁንም፣ ጎረቤቱንም ይግደል አላቸው።»*** የሌዊም ልጆች ሙሴ እንዳለ አድርጉ በሚል ሰበብ 3000 ሰዎች ሙቱ ሙሴ ጥጃን አመልካችኋል በሚል ሰበብ ሦስት ሺህ (3000) ሰዎች እንደ ገደለ ነው ዘፀአት ምዕራፍ የሚነግረን። በኦሪት.ዘኁልቁ 25፡2-8 ***«የሞዓብ ሴት ልጆች ከእሰራላዊያን ጋር በማመንዘራቸውና ለጣዖቶቻቸው ምክንያት እግዚአብሔር አዘዘ።»*** በዚህ መሰረት ሙሴ ሀያ አራት ሺ (24000) ሰዎችን እንዲገደሉ አደረገ።

## ሁሉ መገደል እንዳለበት

በትንቢተ.ሕዝቄኤል 9፡5-6 ***«እንደገናም እግዚአብሔር ሌሎቹን ሰዎች እንዲህ ሲላቸው ሰማሁ፡- በሉ እናንተም እነርሱን ተከትላችሁ በከተማይቱ በመዘዋወር ሁሉንም ግደሉ፤ ለማንም በመራራት ምህረት አታደርጉ። ሽማግሌ ሆነ ወጣት፤ አሮጊትም ሆነ ኮረዳ፤ ሕፃናትን ሳይቀሩ ሁሉንም ግደሉ።»*** ይህን ንግግር የእግዚአብሔር ቃል ነው ብሎ ለማመን ለአዕምሮ ይከብዳል። አስቡት እስኪ ሕፃናት ምን ያውቃሉና የሚገደሉት? **"የቀኝ ጉንጭህ ሲመታህ የግራ ጉንጭህን ስጠው"** የሚለው የክርስቲያኖች አባባል ከዚህ ዘንድ ለአዕምሮ አይጎረብጥምን? ሽማግሌ አሮጊትና ሕፃናት ሳይቀሩ ሁሉንም ግደሉ ይላል። ከዚህ ላይ የሚከብደው ደግሞ የሕፃናት መሞት ነው። ሕፃናት ምንም ሳያውቁ መገደል ነበረባቸው? በመጽሐፈ. በኢያሱ 11፡11 ***«በእርሷም ያሉትን ነፍሳት ሁሉ በሰለት ገደሉ።»*** በ1ኛ መጽሐፈ. ሳሙኤል 27፡9 ***«ዳዊትም ምድሪቱን በመታ ጊዜ ወንድም ሆነ ሴት በሕይወት አለስቀራም።»*** ከዚሁ ምዕራፍ 5፡2-4 ***«የሠራዊት ጌታ እግዚሐብሔር እንዲህ ይላል፡- አሁንም አማሌቅን ምታ ያላቸውን ፈፅመህ አጥፋ፤ አትማራቸውም፤ ወንድንና ሴቱን፣ ብላቴናውንና ሕፃኑን በሬዎች፣***

***ግመሉንና አህያውን ግደል።»*** በኦሪት.ዘኁልቁ 31፡1-18 ላይ የሰፈረውን ታሪክ ስናነብ ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ መሰረት ምደያማዊያን የተባሉ ሕዝቦችን ለመቀበል ከጉልኔዘር ልጅ ፊንሐሰን ጋር አሥራ ሁለት ሺህ (12.000) ለበቀል የተንቀሳቀሱ ሰዎችን መላኩንና በጦርነቱም ድል መንሳቱን እንረዳለን። በበቀል እርምጃውም ወንዶች ሁሉ ተገደሉ። ሴቶችንና ልጆቻቸውን ለባርነት ማርኳቸው፤ ንብረረቶቻቸውንም ሁሉ ዘረፉአቸው፤ የተቀመጡባቸውን ከተሞችና ሰፈሮቻቸው ሁሉ በእሳት አጋዮት።» አሁንም ይደመራል። ይህን ሁሉ ጥፋትና ውድመት ፈፅመው ሲመለሱም ሙሴ ሴቶቹን ሳይገደሉ በማስተረፋቸው በጣም ተቆጣቸው በመቀጠልም ወንድ ሕፃናትና፤ ልጃ ገረድ ያልሆኑ ሴቶች እንዲገደሉ አዘዛቸው፤ ገደሏቸውም። ልጃ ገረድ የሆኑ ሴቶችን ግን ለራሳቸው እንዲያስቀሩ አዘዘ። የሙሴ ሠራዊቶች በወቅቱ ከሕዝቡ የዘረፉት ንብረት የሚከተለው ነበር። ስድስት መቶ ሰባ አምስት ሺህ (675,000) በጎች ሰባ ሁለት ሺህ በሬዎች (72,000) ስልሳ አንድ ሺህ አህዮች (61,000) ልጃ ገረድ የሆኑ ሰላሳ ሁለት ሺህ (32,000) ሴቶች ........ወ.ዘ.ተ. በበቀል ዘመቻ የተሳተፉት ሰራዊቶች የዘረፉትንና የማረኩትን ንብረትና ልጃ ገረዶች ተካፍለው ወሰዷቸው። ሠራዊቱ ከመግደል የተረፉትና ብልግና ሲፈፅሙባቸው ያስቀራቸው ልጃ ገረዶች ቁጥር 32,000 ከሆነ በግፍ የተገደሉ ወንዶችና ልጃ ገረዶች ያልሆኑ ሴቶች፣ አዛውንቶች፣ አረጋውያንና ሕፃናቶች ቁጥራቸው ምን ያህል ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችል መገመት የሚያዳግት አይመስለኝም።

ከሙሴ ሞት በኋላ የተተካው ነብዩ ኢያሱም ቢሆን የኦሪትን ሕግ መሰረት በማድረግ (እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተረካ ሚሊዮኖችን ገድሎ ለሕልፈት ሕይወት አብቁቷል። ይህንን ማወቅ ለሚፈልጉ መጽሐፈ ኢያሱ ወልደ ነወዌን 1፡11 ያለውን ዘገባ እንድታነቡ እጋብዛለሁ። ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 12 ላይ ኢያሱ እራሱ ሰላሳ አንድ (31) ከሐዲያን ንጉሶችን መግደሉና በዘፋናቸው ላይ እስራኤላዊያን እንዲተኩ ማድረጉን ይነግረናል። ይህን ሁሉ መዘርዘሩ ትርፉ ድካምና ቃል በቃል መተርጎም ነው የሚሆነው። ዳዊትም የዚህ ተግባር ተከፋይና ገዳፊ እንደ ነበር፡- በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማይ 27፡8 ጀምሮ እንዲህ የሚል ይነበባል፡- ***«ዳዊትና ሰዎቹም ወጥተው በጌሹራዊያን፣ በጌርዘዊያንና በአማሊቃዊያንም ላይ ዘመቱ፤ እነዚህም እስከ ሱር እስከ ግብጽ ምድር ድረስ ባለው አገር ድሮውንም ተቀምጠው ነበር። ዳዊትም ምድሪቱን መታ፤ ወንድም ሆነ ሴት ማንንም***

***በሕይወት አልተወም። በጎችና ላሞችን አህያዎችንና ግመሎቻቸውንም ልብሰንም ማረከ። ተመልሶም ወደ እንኩስ ገባው።»*** በመጽሐፈ መሳፍንት 2፡10-12 ላይ ሁሉ መገደል እንዳለበት ያዛል። ***«ጉባኤው ወደ ያቤሽ ሄዳችሁ ሴቶችንና ልጆችን ጭምሮ ሁሉንም ግደሉ፤ ወንዶችንና ድንግል ሴቶችንም በሙሉ ግደሉ»*** የሚል መመሪያ በመስጠት ከመካከላቸው ምርጥ የሆኑትን አሥራ ሁለት ሺህ ሰዎችን (12,000) ላኩ በዚም አይነት በያቤሽ ካሉት ሕዝብ መካከል አራት መቶ ድንግል የሆኑ (400) ወጣት ልጃ-ገረዶች አገኙ። ስለዚህም እነርሱን በከነአን ምድር በሴሎ ወደ ሚገኘው ሰፈር ይዘው መጡ ይለናል።

እስኪ ዳዊት ፈፀመ የተባለውን ድርጊት ለአፍታ ቆም ብን እንመልከተው ምድር ላይ ያለውን ነገር ሁሉ ያወድማል ምድሪቱን መታ ሴት ወንድ ሳይል ምንንም ሳይለያይ ያገኘውን ሁሉ ይገድላል። ጌሹራዊያን፣ ጌርዚዊያንና፣ አመሌቃዊያን አንድ በአንደ ንብረታቸውን ሁሉ ዘርፎ ይወስዳል። በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 8፡2-5 ዳዊትም በሞአብ ላይ ፈፅሞታል የተባለው እንደሚከለተው እናንብ.......«***ምዓብን መታ፤ ምዓባዊያንም በምድር ጥሎ በገመድ ሰፈራቸው፤ በሁለት ገመድ ለሞት፤ በአንድም ገመድ ሙሉ ለሕይወት ሰፈራቸው፤ ምዓባዊያንም ለዳዊት ባሮች ሆኑ። ግብርም አመጡለት፤ ዳዊትም ደግሞ በኤፍራጥስ ወንዝ አጠገብ የነበረውን ግዛት መልሶ ለመያዝ በሄደ ጊዜ የዐረብን ልጅ የሱባን ንጉስ አድር አዛርን መታ፤ ዳዊትም ከእርሱ ሺህ ሰባት መቶ (1,700) ፈረሰኞችንና ሀያ ሺህ (20,000) እግረኞችን ያዘ። ዳዊትም የሰረገለኛውን ፈረሰ ሁሉ ቋንጃ ቀረጠ።»*** በመጽሐፈ ሳሙኤል ካልዕ 10፡18 ሌላ የግድያ ታሪክ እንዲህ እናነባለን፡- «***ዳዊትም ከሶሪያዊያን ሰባት መቶ (700) ሰረገለኛዎችንና አርባ ሺህ (40,000) ፈረሰኞች ገደለ፤ የሠራዊቱንም አለቃ ሶባክንም መታ፤ እርሱም በዚያው ሞተ።»*** እንግዲህ እስካሁን የቃኘነው ቅዱስ ከሚለው የአርታዊ ጥቅሶች ነው ቃል በቃል ፊደል በፊደል የተገለበጡ ናቸው። ቅደስ በሚለው አሪት ላይ ገፆች የተጣበቁት ይህን በሞላው የእልቂት ታሪክ ነው። እዚህ የተወሰው አባይን በጭልፋ እንዲሉ ከብዙ በጥቂቱ ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ክርስቲያኖች ብሉይ ኪዳን ተሽሯል ሲሉ ይደመጣሉ። ድንገት ኢየሱስ ከዚህ ተግባር ነፃ ለማውጣት ይሆን? ነውስ ይህችን ምዕራፍ አላዩት ይሆን? የ1980 ዕትም በማቴዎስ ወንጌል 5፡17-20 «***እኔ የሙሴን ሕግና የነብያት ትምህርት ለመሻር አልመጣሁም፤ እኔ ልፈፅመው እንጂ»*** በማለት ለዚህ ተግባር ተቋደሽነቱን ይገልፃል። የሚከተሉት

ምዕራፍ ቁጥሮች ንግግሮን ይበልጥ ያጎሉታል። ከዚሁ ምዕራፍ 10፥34-35 *«እኔ ሰላምን ልሰብክ የመጣሁ ይመስላችኋልን? አይምሰላችሁ ሰይፍ እንጂ ሰላምን ልሰብክ አልመጣሁም። ልጁን በአባቱ ላይ፤ ምራትን በአማትዋ ላይ፤ በጠላትነት ለማስነሳት ነው።»* ይህ የጀመረው እቅድ በሉቃስ ወንጌል 12፥49-51 ላይ ይከናወናል። *«እነሆ እኔ በምድር ላይ ሰላምን ያመጣሁ ይመስላችኋልን? አይምሰላችሁ መለያየትን እንጂ ሰላምን አይደለም።»* ኢየሱስ ሰላምና ፍቅር ካላመጣ በምድር ላይ ምን አመጣ ለሚለው ጥያቄ መልሱ ጠላትነትንና መለያየትን ነው። ውጤቱ ደግሞ በሉቃስ ወንጌል 19፥27 ላይ ተቀምጧል። *«ኢየሱስም አለ፡- እነዚያን ጠላቶችን ግን እዚህ አምጥታችሁ ከፊቴ ግደሏቸው (እረዷቸው)»* አለ። እስካሁን ያየናቸው ጥቅሶች በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ እነዚህን የመሰሉ ጥቅሶች እጅግ በርካታ ሲሆኑ በሰቅጣጭና በዘግናኝ ትረካ የተሞሉ ናቸው። ጭራቃዊ ክንውኖችን በየገፆቻቸው ፊት ለእምነቱ ተከታዮች ያስተላልፋሉ። ሽብር ነዥ ዘገባዎችን ለአንባቢያን ያቋድሳሉ። ሰዎች ያለ ምንም ምክንያት የተለየ ሃይማኖትን ስላራመዱ ወይንም የሆነ መሬት ላይ ሰላማዊ ሆነው ስለ ሰፈሩ ብቻ በግፍ ስለት ይጨፈጨፋሉ። የሽዎች፣ የመቶ ሽዎች፣ የሚሊዮኖች ሕይወት በጠራራ ፀሐይ ይቀጠፋሉ። የደን ምጠራ ያክል እንኳ ሚዛን በልተሰጠው አኳኋን የንጹሐን ደም እንደ ጅረት እንዲፈስ ሲደረግ ቅዱስ በተባለው መጽሐፍ ውስጥ ጥብቅ መልክቱን ሲያዝና ለእምነቱ ተከታዮች የንቃት ደወሉን ሲያሰማ እናገኘዋለን። ይባስ ብሎ ይህን ዘግናን ወንጀል፤ እንዲህ ያለው ሰቅጣጭ ውንብድና የሚፈፀመው እንደ መጽሐፉ አባባል በተከበሩ የአምላክ ነብያቶችና መልእክተኞች ፊት አውራሪነት ነው። በእነ ሙሴ፣ በእነ ኢያሱ፣ በእነ ዳዊት ሌሎች እና ኢየሱስንም ጨምሮ የተግባሩ ተቋዳሽ ሆነው እናገኛቸዋለን። እርግጥ ነው፤ በከንቱ የሰላም ጓዶች ነን እያሉ አጉል ለሚመፃደቁና የሌላው እምነት በጦርነት ለሚፈርጁ ክርስቲያን ወገኖች ምላሽ ይሆን ዘንድ ሚስጢራቸውን በርብረን በማወጣት ራቁቱን በአደባባይ ለማስቀረት ያህል እንጂ እኛ ሙስሊሞች ክቡራን ነብያቶችና የአምላክ መልክተኞች ሰላም በሁላቸውም ይስፈንና ይህን አሳፋሪ ወንጀል ይፈፅማሉ የሚል እምነት ይቅርና ጥርጣሬ እንኳ የለንም። ነብያቶች በእንደዚህ አይነቱ እኩይ ተግባር የራቁና የፀዱ ናቸው ብለን ነው የምናምነው። በኦሪት ቅዱስነት ለሚያምኑ ሰዎች ግን በዚህ መሰሉ እስራኤሰላዊ ትረካ አጠገብ ሲያልፉ ትረካው አሉታዊ ተፅኖዎችን እንደሚያሳርፍባቸው ጥርጥር የለውም። ቅዱስ እየተባለ ሌት ተቀን የሚሞካሽ

መጽሐፍ ቀርቶ ተራ ልብ-ወለድ ድርሰት እንኳ በአንባቢያን ስነ-ልቦና ላይ አንዳች አንድምታ መፍጠሩ አይቀሬ ጉዳይ ነው።አሪት በክርስቲያኖችና በአይሁዳውያኖች ዘንድ ትልቅ ቦታና ቁልፍ ሚና አለው። በዚህ ፈፅሞ ጭካኔና አረመኔነት የተሞላበት በሚተርክ ጥቅስ ተኮትኩቶ ያደገ ሃይማኖተኛ ሰው ምን አመለካከት ሊኖረው እንደሚችል መገመት አያዳግትም። ለዚህም ነው ይህን ጭራቃዊ ድርጊት በጊዜው በተግባር ላይ የሚያሳዩት። በየትኛውም አለማትና ሀገራት ያለውን ድርጊት ወቅትና ዓይን ይፍረደው። ይህን ያህል ካልኩ እስልምና ምን እንደሚመስልና ከላይ ካሳለፍነው እኩይ ተግባር የራቀና የፀዳ ለመሆኑ በትንሹ ቀንጨብ አድርጌ ላከፍላችሁ።

## ‹ኢስላምና› ‹ሰላም› የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች

‹**ኢስላም**› እና ‹**ሰላም**› የሚሉት ሁለት የአረበኛ ቃላቶች መሰረቱ አንድ ከሆነው የቃል ስርወ-ግንድ የሚመዘዙ ናቸው። እነዚህ ሁለት ቃላት ተመዘው የሚወጡት የቃል መሰረት ‹**ሲልም**› የሚለው የአረበኛ ቃል ነው። ‹**ሲልም**› ሰላም ማለትና ሰላምን መጎናፀፍ የሚለውን ትርጉም ይሰጠናል። አላህ (ሱ.ወ) ጥበብ በተዋለው ቃሉ እንዲህ ይለናል፡- በሱረቱል አል-በቀራህ 208‹‹**እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ወደ እስልምና ሙሉ በሙሉ ግቡ የሰይጣንን መንገድ አትከተሉ እርሱ (ሰይጣን) ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነውና**።›› ‹**ሲልም**› የምትለው የአረብኛ ቃል በአንድ ጎንዋ ‹**ሰላም**› የሚለውን ፍች ስትሰጠን በሌላ ጎንዋ ደግሞ ‹**ኢስላም**› የሚለውን ፍች ትሰጠናለች። ቃሏ ሁለት ፍቺዎች አሏት። ‹**ሰላም**› የሚለውን ፍች መሰረት አደርገን ከላይ የተወሳውን የአምላካችን ቃል ሰንተረጉመው የሚከተለውን ትርጉም ይሰጠናል። ሁሉም ምዕመኖች በአንድ ላይ ሆነው ወደ ሰላም እንዲገቡ ጥሪ ማቅረቡን ሲሆን፤ ‹**ኢስላም**› የሚለውን ፍች መሰረት አድርገን አንቀጽ ስንተረጉመው ደግሞ፡- ጥቅልል ብላችሁ ወደ ሁሉም አይነት የኢስላም ክፍሎች ግቡ የሚለውን መልዕክት ይጋብዘናል። ወደ ሁሉም የኢስላም ክፍል .......ወደ እምነቱ ሕግጋቶች ጥቅልል ብላችሁ ግቡ ያኔ እውነተኛውን ሰላም ታገኛላችሁ። ከቤተሰባችሁ፣ ከማህበረሰባችሁ እንድሁም በአጠቃላይ ለሰው ዘሮች በሙሉ ሰላም ትፈጥራላችሁ እያለ አላህ (ሱ.ወ) የአለማቱ ጌታ የሆነው የነጭ ባንዴራንና የሰላም ድህነትን ለሰው ዘር በሙሉ እንዲጎናፀፉ የሰላም ጥሪውን ይጋብዛል።

# ‹ሰላም› የሚለው ቃል በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ቦታና ሙስሊሞች ከሚለዋወጡበት ሰላምታ ጋር ያለው ቦታና ሙስሊሞች ከሚለዋወጡበት ሰላምታ ጋር ያለው ቁርኝት

በየትኛውም ሌላ ሃይማኖት ወይም አስተሳሰብ (ideology) ውስጥ ሊገኝ በማይችል መልኩና የእስልምና ሃይማኖት ሰላም የሚለውን ቃልና የሰላምን ጽንሰ ሀሳብ በተለያየ መልክና ዘዴዎች ሃይማኖቱ ተከታዮች እንዲወዱትና እንዲለመዱት ሲያንፃቸው ይስተዋላል። አላህ (ሱ.ወ) ገደብ የሌላቸው እጅግ በርካታ መልካም ሰሞችና ባህሪያት አሉት። መልካም ከሆኑት በርካታ የአላህ ስሞች መካከል ‹‹<u>**አስ ሰላም**</u>›› የሚለው አንዱ ነው። ‹‹<u>**አስ ሰላም**</u>›› ማለት ሰላምን ሰጭ የሆነና የሰላም ባለቤት ማለት ነው። ስለዚህ አላህ (ሱ.ወ) <u>**አስ ሰላም**</u> በማለት ይጠራል። ለዚህም አንድ ማሳያ እንዲሆነን ለአብነት ያህል የሚከተለውን ምዕራፍ በሱረቱ አል-ሐሽር 23 ያለው እናንብ .‹‹**እርሱ አላህ ነው፤ ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለና ንጉሱ ከጉድለት ሁሉ የጠራው የሰላም ባለቤት ነው።**›› ስለዚህ አላህ የሰላም ባለቤት ስለሆነ ለባሪያዎቹ ሰላምን ይሰጣል። ባሪያዎቹም የሰላም ባሪያ በመባል የሚጠሩ አሉ። ለምሳሌ፡- ‹<u>**አብዱ ሰላም**</u>› የአላህ ባሪያ ማለት ሲሆን በዚህ ስያሜ የሚጠራ ግለሰብ ከእስልምና ኃይማኖት ወጭ በየትኛውም ሃይማኖት ውስጥ የለም። ለምሳሌ፡- በክርስቲያኖች ገብረ እግዚአብሔር፣ ገብረ ማሪያም፣ ገብረ ጊዮርጊስ እንደሚባለው ሁሉ ‹<u>ገብረ ሰላም</u>› በሚል ስያሜ የሚጠራ ክርስቲያን ታይቶም ተሰምቶም አይታወቅም። የፅኑ አማኝ ሙስሊሞች ሁሉ የቀን ሐሳብ የሌሊት ሕልም የሆነው ጀነት ከበርካታ መጠሪያ ስሞች ውስጥ ‹<u>**ዳሩ ሰላም**</u>› የሚለው አንዱ ነው። ትርጉሙም ሰላም የሰፈነበት መኖሪያ ማለት ነው። አላህ (ሱ.ወ) እንዲህ ይላል፡- በሱረቱል አል-ዓናዓም 127‹‹**ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ የሰላም ሀገር (ጀነት) አላቸው። እርሱም (አላህ) ይሰሩት በነበሩት ምክንያት ረዳታቸው ነው**..........።›› በዚያ የሙስሊሞች ብቻ የዝንታለም መኖሪያ በሆነው ዳሩ ሰላም ውስጥ በብዛት የሚደመጠው ቃል ‹ሰላም› የሚለው ቃል ነው። በጀነት (በገነት) ውስጥ የምዕመናትና የምዕመኖች የሰላምታ ቃል ሰላም የሚል ነው። ይህን እውነታ አላህ (ሱ.ወ) በሚከተሉት የቁርአን አንቀጾች አስፈሮት እናገኘዋለን። በሱረቱል አል-አሕዛብ 44 ‹‹**አማኞች (ሙስሊሞች) ከእነርሱ ጋር በሚገናኙበት ቀን የሚያቀርቡት ሰላምታ <u>ሰላም</u> የሚል ይሆናል። የከበረ ምንዳን (ደመወዝን) አዘጋጅቶላቸዋል።**›› በሱረቱል ዩኑስ 10 ‹‹**ከውስጧም**

**ጸሎታቸውም አላህ ሆይ ክብር ላንተ ይሁን ሰላምታቸውም ሰላም ይሆናል።**» በሱረቱል አል-ዋቂዓህ 25-26«**ከውስቷም ፀያፍ ንግግሮችን፤ ኃጢአትንም ፈጽሞ አይሰሙም፤ ሰላም፣ ሰላም የሚሉ ቃላትን እንጂ።**»

‹**ሰላም**› በሚለው ቃል ሰላምታ መለዋወጥ ምዕመኖች በጀነት ውስጥ የሚያንጸባርቁት የተለመደ ባህሪ እንደሆነው ሁሉ ምዕመናን በዚህ አለም (በዱንያ) ሲኖሩም ባሕሪያቸው ልክ እንደ ጀነት ሰላምታ ተመሳሳይ ነው። በተገናኙ ቁጥር «**አሠላም አለይኩም**» ይባባሉ። ትርጉሙም የአላህ ሰላም በእናንተ ይሁን ማለት ነው። በዚህ መልኩ ምዕመኖች ሰላምታ መለዋወጥና ማብዛት (**ኢፍሻኡ ሰላም**) **ሰላምን ማብዛት** ከሚወደዱ ኢስላዊ ግብረ ገቦች ውስጥ እንደ አንዱ ሆኖ ይመደባል። ነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሰላምታን አብዙ ብለው ማዘዛቸውንም እንገነዘባለን።

## ሙስሊም በራሱ ላይና ለሌላው ሙስሊም ሰላምን ይለምናል።

አንድ ሙስሊም ለጌታው ተገዥ መሆኑን በተግባር ለማረጋገጥ የሶላት ስግደት በሚያከናውንበት ወቅት በነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ራሱና በሕዝበ ሙስሊሙ ሰላምን እንዲጎናፀፍ አላህ (ሱ.ወ) ይለምናል። ሙስሊም በሶላት እንዲህ በማለት ተንበርክኮ ስለ ሰላም ጌታውን ይማፀናል። «**ዓሰላሙ ዓለይከ አዩሀ ነብዩ ወረሕሙቱላሂ ወበረካቱም ዓሰላሙ ዓለይና ወዓላ ዒባደሏሂ አሷሊሂን**» ትርጉሙ፡- «**አንቱ የአላህ ነብይ በእርስዎ ላይ የአላህ ሰላም፤ እዝነትና በረከት ይስፈንብዎ። በእኛም ላይ እንዲሁም በመልካም የአላህ ባሪያዎች ላይም የአላህ ሰላም ይስፈን**» በማለት ሁሌ ጌታውን ይለምናል። አንድ ምዕመን ስለ ሰላም ጌታውን በመማፀን ሶላቱን ካከናወነ በኋላ፤ ልክ እንደዚሁ ሶላቱን ስለ ሰላም በመማፀን ያጠናቅቃል። አንገቱን ወደ ቀኝና ወደ ግራ ዞር ዞር በማድረግ በቀኝና በግራ ለከበበው ነገር ሁሉ ሰላምን በመመኘት ከሶላቱ ይወጣል።ወደ ቀኝ በመዞር «**አሰላም አለይኩም**» ወደ ግራ በመዞር «**አሰላም አለይኩም**» **ይላል። ‹ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን›** በማለት ሶላት ውስጥ እያለ ሰላም ውስጥ እንደ ነበር ሁሉ ከሶላቱ ሲወጣም በሰላም ይወጣል።

## ለማጠቃለያ ያህል

የእስልምና ሃይማኖት ሰላምን በእጅጉ ያበረታታል፤ ዘወትር ወደ ሰላም ይጠራል፤ የእስልምና ሃይማኖት ለሰላም ምን ያህል ሰፊና የጎላ ቦታ እንደሚሰጥ ለማወቅ የሚፈልግ ሚዛናዊ የሆነ ሰው የሃይማኖቱን አስተምሮ ሕግጋትና ግብረ ገቦች በሚተገበሩት አማኞች ውስጥ ሰላም ጎልቶና ደምቆ ሲታይ በቀላሉ ማስተዋል ይቻላል። ስለዚህ የሰላም ተቋዳሽ ለመሆን ከፈለጉ ወደ ሃይማኖቱ በሙሉ ልብ በመግባት የበለጠ ድምቀቱን ማየትና ፍሬውንም ማጣጣም ይችላሉ። **‹ማየት ማመን ነውና›** እንደኔ ገብቻችሁ እዩት እያለኩ የሰላም ጥሪዬን አስተላፋለሁ ለእውነተኛ ሰላም ፈላጊዎች በሙሉ።

### ጥ.ክ. የተማረከች ሴት በሙስሊሞች ይፈቀዳል ለምትሉት ጥያቄ

**ሙ.መ.** ከምደግመው ይልቅ በአጭሩ ጠቆም አድርጌ አቀርበዋለሁ፤ ካሳለፍነው ርዕስ ተመልከቱ። በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀደማይ 27፡8 ያጀምሮ ያለው ይነበብ፤ ዳዊት ምን እንደማረከ እንዲሁም በዘኁልቁ 31፡1-12 ሙሴ ምን እንደማረከ ይነበብ ለምሳሌ ዳዊት የማረከው 67500+72000 በፊት 761000 አህያ 32000 ልጃ ረዶች ደምሩን ራሳችሁ ደምሩ ከሞቱት በሕይወት የተረፉትና የተማረኩት ናቸው። ተጨማሪ በመጽሐፈ መሳፍንት 21፡10-17 ላይ 400 ድንገል ሴቶች እንደተማረኩ ይናገራል።

### ጥ.ክ ውሻ የፈጣሪ ፈጥረት ነው እናንተ ሙስሊሞች ለምን ትጠየፉታላችሁ?

ሙ.መ. በኦሪት.ዘዳግም 23፡17-18*‹‹ስለተሳልኸው ስለት ሁሉ የጋለሞታይቱን ዋጋና የውሻውን ዋጋ ወደ አምላክ ቤት አታቅርብ፤ ሁለቱም በአምላክህ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያጸይፉ ናቸው።››* በእናንተ መጽሐፍ ግን አምላክ ነው ተብሎ የተገለጸው ውሻን ይቅርና ሰውን ያክል ፍጡር የሚያጸይፍ ነው ይላል። **‹ዝንጀሮ የሯሷን ገጣባ ሳታይ በሌላዋ ትስቃለች›** አሉ። ሲጀመር የሰው ልጅ እንዴት ከውሻ ጋር ይወዳደራል? የሚገርመው ብዙ ጊዜ ክፉ ሰዎችን በውሻ መስለው ይሳደባሉ። ለምሳሌ ውሻ ነህ፤ የውሻ ልጅ በማለት በብዛት ይሳደባሉ።

የተጨማሪ ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 6፡6«***<u>የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ</u>***» በማለት ለውሻ ክብር እንደሌለው ተናግሯል።

ጥ.ክ. **እናንተ ሙስሊሞች እኛ ክርስቲያኖችን ለምን ወደ እስልምና ትጠራላችሁ እናንተ መጥራት አትችሉም። ምክንያቱም በቁርአን ላይ ለነብያችሁ «አንተ የወደድከውን መምራት አትችልም» ብሏል። እንዲሁም አላህ የፈለገውን ያጠማል፤ የፈለገውን ያቀናል፤ ስላለ እናንተ ማቅናት አትችሉም።**

መ.ሙ.በመጽሐፈ መክበብ 7፡13«***<u>የእግዚአብሔርን ሥራ ተመልከት፡- እግዚአብሔር ጠማማ ያደረገውን ማን ሊያቀነው ይችላል</u>***?» ኢየሱስም በዚህ ላይ የተናገረው ነገር አለ። በዮሐንስ ወንጌል 6፡44«***<u>የላከኝ አብ የሳበው ካልሆነ በቀር ወደ እኔ መምጣት የሚችል ማንም የለም</u>***።» ተጨማሪ ከዚሁ ምዕራፍ 6፡65 እና 3፡18 ተመልከቱ። ጳውሎስ ወደ ሮሜ ሰዎች 9፡16«***<u>እንግዲህ ምህረት ለወደደ ወይንም ለሮጠ አይደለም። ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ</u>***።» ምንም ማብራራት አያስፈልገውም።

ጥ.ክ. **እናንተ ሙስሊሞች ከአንድ በላይ ሚስት ታገባላችሁ እስከ 7 እስከ 9 ሚስት ድረስ ይህ አድራጎት ንግድና ሴቶችን መበደል አይሆንም?**

ሙ.መ. ከአንድ በላይ ሚስት ማግባት በሁሉም ክርስቲያኖች ዘንድ እንደ ጀብድ ነው የሚታያቸው። ምክንያቱም በክርስቲያኖች ዘንድ የሚቀላቸው ነገር ስላለ ነው።እርሱም ዝሙት ነው። የሚገርው ነገር የእስልምና ሃይማኖት እንጂ ከእስልምና ሃይማኖት ውጭ የየትኛውም ሃይማኖት ክርስትናን ጨምሮ የሚስት ገደብን ያስቀመጠ የለም። እስኪ በዚህ ዙሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ወደ ሚለው ነጥብ እናምራ፡-

## ሀ) <u>ሁለት (2) ሚስቶች</u>

በኦሪት.ዘዳግም 21፡25 «***ለአንድ ሰው አንዲት የተወደደች አንዲት የተጠላች <u>ሁለት ሚስት ቢኖሩት</u>***-----።» በመጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማይ 27፡3-4«***ዳዊትም ደግሞ ኢይዝራኤላዊቱን አካናሆምን ወሰደ፤ <u>ሁለትም ሚስቶች ሆኑለት</u>***።» በመጽሐፈ ዜና መዋለ ካልዕ 24፡3«***የደሄም <u>ሁለት</u> <u>ሚስቶች</u> አጋባው፤ ወንዶችና***

*ሴቶች ልጆችንም ወለደ።»* በኦሪት.ዘፍጥረት 4፡22 *«ላሕሜ ሁለት ሚስቶች አገባ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 32፡22*«በዚያች ሌሊት ያዕቆብም ተነሳ ሁለቱን ሚስቶቹን አንዷቱን ሴት አገልጋዮቹንና አሥራ አንድ ልጆቹን ይዞ በያቦቅ መልካ ተሻገረ።»*

## ለ) ሰባት (7) ሚስቶች

በትንቢት.ኢሳይያስ 4፡1 *«በዚያን ቀን ሰባት (7) ሴቶች የገዛ እንጀራችን እንበላለን፤ የገዛ ልብሳችንም እንለብሳለን፤ ስምህ ብቻ በእኛ ላይ ይጠራ፤ መሰደባችንንም አርቅ ብለው አንዱን ወንድ ይይዙታል።»*

## ሐ) አሥራ አራት (14) ሚስቶች

በመጽሐፈ ዜና መዋዕል 13፡21 *«አብያም ፀና አሥራ አራት (14) ሚስቶችን አገባ፤ ሀያ ሁለትም ወንዶች ልጆችና አሥራ ስድስት ልጆችን ወለደ።»*

## መ) አሥራ ስምንት (18) ሚስቶችና ስልሳ (60) ዕቁባቶች

በመጽሐፈ ዜና መዋዕል 11፡21 *«ሮብዓምም ከሚስቶቹና ከቁባቶቹ ሁሉ ይልቅ የአቤሴሎምን ልጅ መዓካን ወደደ፤ አሥራ ስምንት (18) ሚስቶችና ሲድሳ (60) ዕቁባቶች ነበሩት።»*

## ሠ) ሰባት መቶ (700) ሚስቶችና ሦስት መቶ (300) ዕቁባቶች

በመጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ 11፡2-3 *«ከእነዚህ ጋር ሰለሞን በፍቅር ተጣበቀ፤ ለእርሱም ወይዛዝርት የሆኑ ሰባት መቶ (700) ሚስቶችና ሦስት መቶም (300) ዕቁባቶች ነበሩት።»*

## ረ) በቁጥር ያልተገደቡ ብዙ ሚስቶች

በ1ኛ ዜና መዋዕል 14፡3*«ዳዊትም በኢየሩሳሌም ብዙ ሚስቶችን አገባ።»* ተጨማሪ በመጽሐፈ መሳፍንት 8፡29-30*«የኢዩአስ ልጅ ይሩባኤል ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ከዚያም ተቀመጠ፤ ብዙ ሚስቶች ስላገባ ሰባ (70) ልጆች ነበሩት።»*

## ቀ) <u>ለባሏ ሚስት ያጋባች ሴት</u>

በኦሪት.ዘፍጥረት 16፡3-4 *«አብራሃምም በከነዓን ምድር አሥር ዓመት ከተቀመጠ በኋላ የአብራሃምም ሚስት ሣራ ግብፃዊት ባሪያውን አጋርን ወስዳ <u>ለባልዋ</u> ለአብራሃም ሚስት ትሆነው ዘንድ ሰጠችው። እርሱም ወደ አጋር ገባ።»* ከዚሁ ምዕራፍ 30፡10-11 *«ልያም መውለድን እንዳቆመች ባየች ጊዜ፤ ባሪያዋን ዘለፋን ወሰደችለት፤ <u>ሚስት ትሆነው</u> ዘንድ ለያዕቆብ ሰጠችው።»*

## ጥ.ክ. **ከዘመድ ሚስት ማግባት የአጎት ልጅ፤ የአክስት ልጅ፤ ማግባት ዝምድናን መቁረጥ አይሆንምን?**

ሙ.መ. ከዘመድ አዝማድ መጋባት ዝምድናን ማጥበቅ እንጂ መቁረጥ አይደለም። ከዘመድ አዝማድ መጋባትን መጽሐፍ ቅዱስ ከመፍቀድም አልፎ እንዲያውም ያዛል። በመጽሐፈ ጦቢት 4፡12 *«ልጄ እራስን ከዝሙት ጠብቅ፤ <u>ከአባቶችህ ልጆች</u> ወገን አስቀድመህ ሚስት አግባ። <u>ከዘመዶችህ ካልተወለደች ከባዕድ ወገን ግን አታገባ</u>።»* በኦሪት.ዘፍጥረት 28፡1-3 *«ይስሐቅም ያዕቆብን ጠራው ባረከውም እንዲህም ብሎ አዘዘው፡- ከከነዓውያን ሴቶች ልጆች ሚስትን አታግባ። ተነሥና ወደ እናትህ አባት ወደ ባቱኤል ቤት ወደ ሁለቱ ወንዞች መካከል ሂድ፤ ከዚያም <u>ከእናትህ ወንድም (ከአጎትህ)</u> ከላባ ሴቶች ልጆች ሚስትን አግባ።»* ተጨማሪ በኦሪት.ዘፀአት 6፡20 *«እንበረምም <u>የአጎቱን ልጅ</u> ዮካብድን አገባ፤ አሮንና ሙሴን ወለደች።»* የ1993 ዕትም የአባቱን እህት በማለት ይናገራል፤ ያ ማለት አክስቱን ማለት ነው። ይህ ደግሞ የሚከብድ ነው፤ አክስት በኢስላም አትገባም።

## ጥ.ክ. **እናንተ ሙስሊሞች እምነታችን ከድሮ ጀምሮ ያልነበረና ከክርስትና በኋላ የመጣ መሆኑን ለምን ትከዳላችሁ**

ሙ.መ. ማንኛውንም ሰው ወደ እዚህ ምድር ሲመጣ እምነቱ ሙስሊም ነው። ሙስሊም ካልሆነ እምነቱ ጥያቄአችሁን በጥያቄ ልመልስና ምንድን ነው? የሰውል ልጅ ሲወለድ ጅምሮ እምነቱ ሙስሊም ካልሆነ ለምንድን ነው ወንድ ልጅን በ40 ቀኑ ሴት ልጅን በ80 ቀኗ የምትጠመቀው? እንዱሁም እናቶች በአራስነት ጊዜአቸው ከእነ ልጆቻቸው ጋር (ጨደር) እስኪጠመቁ ድረስ በእርግጥ እናንተ

ክርስቲያኖች እውነታውን አትክዱም። ወንድ ልጅ በ40 ቀኑ እስኪጠመቅና ሴት ልጅ በ80 ቀኗ እስክትጠመቅ ድረስ ሙስሊም ናቸው ትላላችሁ። ታዲያ ወደዚች ምድር ሲመጡ ሙስሊም መሆናቸውን ካወቃችሁ አላህ (ሱ.ወ) በተፈጥሮ የለገሳቸውን እምነት በማስቀየር "ያመነ የጠጠመቀ ይድናል" እያላችሁ ለምን ሰዎች ከመንገድ ታሰናክሏችኋላችሁ? ጥያቄ በተፈጥሮ ክርስቲያን ከነበሩ ሙስሊም ካልነበሩ መጠመቃቸው ለምን አስፈለገ? ምክንያቱም መጠመቅ ከተፈጥሮ በኋላ ስለሆነ ማለት ነው። ክርስትና የተፈጥሮ ኃይማኖት ቢሆን ኖሮ ከተወለዱ በኋላ ባልተጠመቁ ነበር። አሁንም ጥያቄ ክርስቲያን ሁኑ ብሎ ኢየሱስ አስተምሯል እራሱስ ክርስቲያ ነበር? እንዲሁም አዳምና ሔዋንስ ክርስቲያን ነበሩ? ክርስቲያኖች መልሳችሁ አዎ ክርስቲያን ነበሩ ካላችሁ ያጠመቃቸውን ቄስ ማን እንደሆነ ንገሩን። ከአዳምና ከሔዋን የሚቀድም ክርስቲያን ካለ መናገር ይቻላል።

## <u>የክርስትና እምነት እንዴት ተጀመረ? ብቸኛው የመዳኛ ሃይማኖት ነውን?</u>

በሐዋሪያት ሥራ 11፡25-26 ከዚሁ ምዕራፍ 6፡11«***ከዚህ በኋላ ባርናበስ ሳወልን ለመፈለግ ወደ ጤርቤስ ሄደ ባገኘውም ጊዜ ወደ አንፆኪያ አመጣው፤ ሁለቱም እዚያ ካለቸው ቤተ-ክርስትያን ጋር በመሆን አንድ ዓመት ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ አስተማር <u>ደቀመዛሙርቱ ለመጀመሪያ ጊዜ በአንፆኪያ ምድር ክርስትያን ተብለው ተጠሩ።</u>***» ታዲያ ለመጀመሪያ ጊዜ ክርስቲያን ተብለው ደቀመዛሙርቱ ከተጠሩ እንዴት የዓለም ሕዝብ በሙሉ ክርስቲያን ነው ይባላል? አስተምሮቱስ የማን ነው? ክርስቶስ ያስተማረውና በጊዜው ላይ የዚህ እምነት ተከታይ ያልነበረው ለምንድ ነው? ይህ ጽድቅ እምነት የመዳኛ መንገድ መሆኑን ስላላወቀ ነው? የመሰረቱት ደቀመዛሙርቶች ለመጀመር ጊዜ በአንፆኪያ ክርስቲያን ከተባሉ ኢየሱስ ያስተማረውና እራሱ ኢየሱስ ምን እምነት ነበረው? እናንተ ናችሁ ክርስትናን የመሰረታችሁት ኢየሱስ ነው የመሰረተው? ኢየሱስ ያስተማረው ያልተከተላችሁት ውሸት ስለሆነ ነው ኢየሱስ ክርስትና አስተምሯል ካላችሁ የመጀመሪያ ክርስቲያን መሆን የነበረባቸው እስራኤላውያ ነበሩ። ምክንያቱም ኢየሱስ የተላከው ለእስራኤል ሕዝቦች ስለሆነ ምንም እንኳ ባይቀበሉትም። ለመጀመሪያ ጊዜ በአንፆኪያ የተመሰረተው ክርስትና ሃይማኖት እንዴት የተፈጥሮ ኃይማኖት ነው ማለት እብደት ወይንስ ቅዠት? ለመጀመሪ ጊዜ ክርስቲያኝ ከተባሉ ታዲያ እንዴት

የዓለም ሕዝብ ክርስቲያን ይባላል? ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 17፡6-9 ላይ ያለውን ስንመለከት፡- «***ለነዚህ ለሰጠኸኝ ሰዎች ስምህን ገልጨላቸዋለሁ፤ እነርሱም ቃልህን ጠብቀዋል። ምክንያቱም የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁ፤ ተቀብለዋል። እኔም ከአንተ እንደመጣሁ በእርግጥ አውቀዋል፤ አንተ እንደላከኸኝም አምነዋል***» ይላል። ቃሉን የጠበቁት ክርስቲያኖች ወይንስ ሙስሊሞች? ቃሉን ጠብቀናል ካላችሁ ታዲያ ለምን እንደ እኛ ሙስሊም አልሆናችሁም? ምክንያቱም ቃልህን ተቀብለዋል ስለሚል ማለት ነው። ቃሉን ከተቀበላችሁ ለምንድነው ከጊዜ በኋላ የመጣውን በአንፆኪያ የተመሰረተውን ክርስትናን የተከተላችሁ? ጥቀሱ ሲቀጥል አንተ እንደላከኸኝ አምነዋል ይላል። ታዲያ በኢየሱስ መላክተኛነት የሚያምን እኛ ሙስሊሞች ወይንስ የዘመናችን ክርስቲያኖች? እኛ ሙስሊሞችን መተቸት ማለት ሐዋሪያቶችንና ኢየሱስን መተቸት ማለት ነው። ምክንያቱም እኛ ሙስሊሞች ቃሉን ጠብቀን የላከውን አምነን እንደ ሐዋርያቶች በኢየሱስ ነብይነት የምናምን ነን። ይህ አድርጎታችን እንደ ክፉ ስራ መታየቱ በጣም ያሳዝናል። ሲቀጥል የእናንተ መካድ አልበቃ ብሎ እኛን የሳት ጓድ ለማረግ ሌት ተቀን ያለሰለሰ ጥረት ታደርጋላችሁ። አንድን ሰው ማሰናከል እንዴት ለእናንተ ቀላል ሆኖ ታያችሁ? ሰውን ወደ ክደት ትጠራችሁ ይህ አድራጎታችሁ ደግሞ ከሰይጣን በምንም ይለያል?

ለመጀመሪያ በኢየሱስ የካዱ እኛ ሙስሎሞች ሳይሆን የአሁኖቹ ክርስቲያኖች ነን ባዮች መሆናችሁ አጠራጣሪ ጉዳይ አይደለም። ኢየሱስ ሁኑ ያላለውንና ያላስተማረውን መከተል ፀረ ኢየሱስ እንጂ ውዱታን አይገልጽም። በዮሐንስ ወንጌል 6፡14 «***ወደዚህ የሚመጣው ነብይ በእርግጥ ይህ ነው አሉ።***» የዓይን ምስክሮችና በጊዜው የነበሩ ሰዎች ነው ይህን ቃል የተናገሩት። ታዲያ እነዚህ ሰዎች ከሀዲ ናቸው ወይንስ አማኝ? ካልተጠመካችሁ ካለመናችሁ መንግስተ ሰማያት ለገነት አትገቡም መልስ ኢየሱስ ዮሐንስ 17፡25 «***ፃድቅ አባት ሆይ! ዓለም ባያውቅህም እኔ አውቅሃለሁ፤ እነዚህም አንተ እንደላከኝ ያውቃሉ***» በማለት በአንክሮት ተናግሯል። ስለዚህ ሐዋሪያቶች በኢየሱስ ነብይነት ሰለሚያምኑ እንደ እኛ ሙስሊሞች መሆናቸውን ነግሮናል። ምክንያቱም በኢየሱስ መላክተኘነት የሚያምኑ ሙስሊሞች ናቸውና። የሚገረመው ኢየሱስ ከሐዋሪያቶችና ከሙስሊሞች ወጭ እንደልተቀበሉት አክሎም ተናግረሯል። «***ዓለም ባያውቅህ እኔ አውቅሃለሁ***» ትክክል ነው፤ ሁሉም ክርስቲያኖች የኢየሱስን ነብይነት አያውቁም

ኢየሱስ ግን ያውቃል። በሌላ ቦታም አላውቅህም ብል እንደነሱ ውሸታም በሆንኩ ነበር ብሏል። አሁን ወደ መልሱና ወደ ዋነው ርዕሴ ላምራ፡-

ሕፃናት ካልተጠመቁ አይድኑምን? እምነታቸውስ ክርስትና ነውን? እንደ አብዛኛው ክርስቲያኖች ሕፃናት ከነኃጢአታቸው ነው ሚወለዱት ስለዚህ ካልተጠመቁ አይድኑም ለዚህም ወንድ ልጅ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ በ80 ቀኗ መጠመቅ አለባቸው ብለው ያምናሉ። አስተምሮቱ የኢየሱስ ነው ወይንስ የክርስቲያኖች? ኢየሱስ በማርቆስ ወንጌል 10፡13-14 ***«ኢየሱስ ሕፃናት እንዲዳስሳላቸው ሰዎች ወደ እሱ አመጡ፤ ደቀመዘሙረቱ ግን ገሰጹአቸው። ኢየሱስ ይህን ሲያይ ተቆጥቶ እንዲህ አላቸው፡- ሕፃናት ወደ እኔ ይምጡ አትከልክሏቸው፤ የአምላክ ቤት መንግስት ሰማያት (ገነት) እንደነዚህ ላሉትና አለ።»*** ጥያቄ ሕፃናት እንዴት እስከ ወንጀላቸው ኢየሱስ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ አለ? ምክንያቱም ይህን ሲናገር ለኃጢአቸው ተሰቅሎ ስላልሞተ ማለትም ነው። ኢየሱስ ሕፃናትን ስላልተጠሙቁና ስላላመኑ መንግስተ ሰማያትን አይወርሱም ያላለው ለምንድን ነው? እንደ እናንተ አባባል ሕፃናት ሲወለዱ ከነኃጢአታቸው ነው የሚወለዱት ስለዚህ መጠመቅ አለባቸው ስለ ምትሉ። ደግሞስ ሕፃናት ምን ያውቃሉ? ምን ኃጢአት ሰርተው ነው? አምላክስ በእነርሱ ላይ ኃጢአት አለባቸው ማለቱ አግባብ ነው? የሰው አዕምሮስ ይቀበለዋል? የክርስትና አስተምሮ ሕፃናት ክርስቲያን ሳይሆኑ ሳይጠመቁ ከነኃጢአታቸውና ከነክደውታቸው ሳይመለሱ መንግስተ ሰማያት አይገቡም ትላላችሁ። ታዲያ ኢየሱስ መንግስተ ሰማያት ይገባሉ ያለው ውሸት ነው ማለት ነው? ኢየሱስ የመሰከረላቸው በእናንተ አባባል ከሀዲ በመነቸው ነው መንግስተ ሰማያት የሚገቡት ሳይጠጠመቁና ሳይበሉ ነው ኢየሱስ የመንግስተ ሰማያት ናቸው ያለው ሰፋ ባለ መልኩ በማቴዎስ ወንጌል 18፡1-10 ***«ደቀመዘሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ነው ብለው ጠየቁት፤ ኢየሱስ ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ፤ እንዲህም አላቸው፤እውነት እውት እላችኋለሁ <u>ካልተመለሳችሁ፤</u>*** (በ1993 ዕትም «<u>ካልተለወጣችሁ</u>» ይላል።) ***እንደ ሕፃናት ካልሆናችሁ ወደ መንግስተ ሰማያት (ገነት) አትገቡም። ስለዚህ በመንግስተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ፤ እንደዚህ ሕፃን ራሱን ዝቅ የሚያደርግ ነው። እንደ እነዚህ ያሉ ሕፃናትን በስሜ የሚቀበል፤ እኔን ይቀበላል። ነገር ግን እኔ ከሚያምኑት ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሰው፤ ከባድ የወፍጮ***

*ደንጋይ በእናቱ ታስሮ ወደ ትልቅ ባህር ተጥሎ ቢሰጥም ይሻለዋል። ይህች ዓለም የመሰናከያ ምክንያት ለሆኑት ወዮለት! መሰከናል ሳይመጣ አይቀየርምና። ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ለሚሰከናል ምክንያት ሰው ወዮለት! እጅህ ወይንም እግርህ ብታሰናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት።ሁለት እጅህ ወይንም ሁለት እግር ኑሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል ይልቅ፤ አንካሳ ወይንም ጎንዳሻ ሆነህ ወደ ሕይወት መግባት ይቻላል። ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላአከቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችሁአለሁና። እንደነዚህ ከታታናሹ አንዱ እንዲጠፋ የሰማያት አባታችሁ ፍቃድ አይደለም*» ይላል። ሙሉ ቃሉን ከመጽሐፉ አንብቡ። ተጨማሪ በያቆብ መልእክት 5፡19-20 «*<u>ከእናንተ ከእውነት ቢስት አንዱንም ቢመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን የኃጢአተኛውንም ብዛት እንደሚሸፍን ይወቅ።</u>*»

ጥያቄ እንደ ሕፃናት ካልተመለሳችሁ፤ ካልተለወታችሁ፤ መንግስተ ሰማያት (ገነት) ከቶ አትገቡም ብሏል። ስለዚህ ኢየሱስ የተናገረው ውሸት ነው? ወይንስ መንግስተ ሰማያት መግባት አትፈልጉም? ክርስቲያኖች የኢየሱስን አስተምሮ የተቃረናችሁት የራሳችሁ መንግስተ ሰማያት ስላላች ነው? ኢየሱስ ሙስሊም ካልሆናችሁ ፈፅሞ ገነት አትገቡም በማለት በአንክሮ አስረግጦ ተናግሯል። ኢየሱስ ወዮላቸው ለሚያስናክሉ ሰዎች ያለው ለክርስቲኖች እንጂ ሙስሊሞችን አይደለም። ለነዚያ ያመነ የተጠመቀ ይድናል ለሚሉ ክርስቲያኖች ነው። አዎ እርግጥ ነው አንድ ሰው ካልተጠመቀ ሙስሊም ነው። የሚየቀረውና የሚሰናከለው በቄሶች ምክንያት ነው። ጥምቀት የመዳኛ መንገድ ነው እያሉ ለሚያሰናክሉ ወዮላቸው! የወፍጮ ድንጋይ በአናቱ ታስሮ ወደ ባህር መስጠም ይሻለው ነበር ያለው። ኢየሱስ ሕፃናት ለመንግስተ ሰማያት የታጩ ናቸው እያለ እናንተ ደግሞ የእሳት ናቸው ስላልጠመቁ ትችላላች። ታዲያ ኢየሱስን ማን ነው የተቃረነው? ክርስቲያኖች ወይንስ ሙስሊሞች? እኛ ሙስሊሞች በሕፃናት ላይ እንደ ኢየሱስ ተመሳሳይ አቋም አለን። መንግስተ ሰማያት ይገባሉ የሚል እምነት አለን። ክርስቲያኖች ደግሞ መንግስተ ሰማያት አይገቡም ኃጢአተኛ ናቸው በማለት ኢየሱስ የመሰከረላቸውን ይቃረናሉ። ይህ አድራጎትታችሁ ከሰይጣንም በምን ይለያል? ሰይጣንስ ወደ ሲያል የሚገባው በዚህ አድራጎቱ እኮ ነው። ተመከሩ ክርስቲያኖች ከነዚህ ከታታነናሾቹ አንዱ ከሚጠፋ የሰማዩ አምላካችን ፍቃድ አይደለም። እናንተም ካልተመለሳችሁ፤ ካልተለወጣችሁ ወደዳችሁም

ጠላችሁም መንግስተ ሰማያት በፍፁም አትገቡም። እኛ አይደለም ያልናችሁ ኢየሱስ ነው።

## <u>ስለጥምቀት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?</u>

ክርስቲያኖች "ጥምቀት" የእምነቱ መሰረት አድርገው ይቆጥሩታል። ለዚህም ሲባል "ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያለመነ ያልተጠመቀ ይደየናል፤ ሲሉ ይደመጣሉ። ስለዚህ ጥመቀት ለክርስትና ሃይማኖት ዋና መሰረቱና የክርስቲያኖች የደኅንነት ቁልፍ እንደሆነ አብያተ ክርስቲያናት ያስተምራሉ። ለማንኛውም በዚህ ዙሪያ የማን አስተምሮ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል ወደ ሚለው ነጥብ እናምራ። በማቴዎስ ወንጌል 3፡11 ‹‹***ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ <u>እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል</u>፤----***›› ዮሐንስ እንዳለው ኢየሱስ ሲመጣ ሰውን የሚያጠምቀው በውሃ አለመሆኑን ጠቁሟል። በማስከተልም እንደ ዮሐንስ ገለፃ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ የሚያጠምቀው ‹**<u>በመንፈስ ቅዱስና በእሳት</u>**› መሆኑን ነው የነገረን። እዚህ ላይ አያሌ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀርም። ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ካጠመቀ በአሁኑ ሰዓት ያሉ ክርስቲያኖች ለምንድን ነው ሰዎችን በውኃ የሚያጠምቁት? የጳውሎስ መልእክትም እንዲህ ይነበባል፡- በ1ኛ ቆረንቶስ 1፡17 ‹‹***<u>ክርስቶስ የላከኝ ወንጌል እንድሰብክ እንጂ እንዳጠምቅ አይደለም</u>።***›› ኢየሱስን በመከተል ነው እንዳይባል ኢየሱስ ራሱ ሰዎችን በውኃ አላጠመቀምና። በዮሐንስ ወንጌል 4፡2-3 ‹‹***---<u>ዳሩ ግን ደቀመዛሙርቱ እንጂ ኢየሱስ ራሱ አላጠመቀም</u>።***›› ከላይ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃል ተብሏል። ታዲያ እሳት ማለት ምን ማለት ነው? በትንቢተ.ኤርሚያስ 23፡2-3 ‹‹***<u>በእውኑ ቃሌ እንደ እሳት ድንጋዩንም እንደሚያደቅ መዶሻ አይደችምን</u>?***›› እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ‹**<u>እሳት</u>**› ማለት ‹**<u>የእግዚአብሔር ቃል</u>**› መሆኑን እንረዳለን። በተጨማሪ እሳት ማለት ኃይል ያለው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ለመጠቆም ነው ቃሌ ድንጋዩን እንደሚያደቅ መዶሻ ነው ያለው። ስለዚህ ኢየሱስ በእሳት ያጠምቃል መባሉ ‹**<u>በእግዚአብሔር ቃል</u>**› በንግግር ማለትና በልብ በማመን መንፃት እንጂ በውሃ መነከር (መጠመቅን) አያመላክትም። ኢየሱስ እንዲህ ይላል፡- በዮሐንስ ወንጌል 15፡3 ‹‹***<u>እናንተ ስለነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ</u>---።***›› ሰዎች ኢየሱስ በነገራቸው ‹**<u>ቃል</u>**› መሰረት ንጹሆች ሆኑ እንጂ በውሃ አልጠጠመቁም። በውሃ ሳይጠመቁ ‹**<u>በቃል</u>**›

ንግግር ብቻ ንጹሆች ሆነዋል። ያ ንጹህ የሚያደርገው ቃል ምነድን ነው ከተባለ በዮሐንስ ወንጌል 17፡3 ***«እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።»*** ልብ በሉ ክርስቲያን ወገኖቻችን ‹**የዘላለም ሕይወት**› የሚገኘው ‹**በጥምቀት**› ሳይሆን ኢየሱስ እንደተናገረው አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ እንዳለ ስንመሰክርና ኢየሱስም የዚያ እውነተኛ አምላክ መልእክተኛ መሆኑን ስንመሰክር በዚህ የምስክር ቃላችን ወደ እውነኛ የዘላለም ሕይወት እንገባለን። እንዲሁም በአሁኑ ዘመን የግድ የዘላለም ሕይወት ለማግኘት ከኢየሱስ በኋላ ለመጡት ነብይ ለፍጥረታት በሙሉ የተላኩት ነብዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛ የአላህ መልእክተኛና ባሪያ መሆናቸውን መመስከርና ኢየሱስ እንዳለው ሁሉ ብቸኛ የሆነውን አምላክ ስናመልክ ብቻና ብቻ ነው።

## ጥ.ክ **እናንተ ሙስሊሞች ጣዖት ታመልካላችሁ ወደዚያም በመዞር ካባን ትገዛላችሁ ካልተገዛችሁት ወደ ጣዖቱ መዞራችሁ ማምለካችሁ ኢያሳሳምን?**

መ.ሙ እንደ ጥያቄ ልመልስላችሁ ነገር ግን ሐቅን ለመረዳት እንደማትፈልጉ ግልጽና ግልጽ ነው። እኛ ሙስሊሞች ጣኦት አምልኮና አቅጣጫ መሰል ነገሮች አናመልክም። ለምሳሌ፡- ወደ ሶላት ሰንቆም ‹**አላሁ አክብር**› ብለን እንጂ ካዕባ አክብር ብለን ለካባ አንሰግድም ካባንም አናመልክም። ወደ ካዕባ የምንዞረው ትዛዝና የቂብላ አቅጣጫ ስለሆነ ብቻ ነው፤ እንዲሁም የሙስሎሞች የአንድነታችን መስመርና መለያ ነው። ይህ በእንዲህ እንዳለ በመጽሐፍ ቅዱስም ወደ ቤተል መቅዲስ ወደ ካባ እንድትዞሩ ታዛችኋል። ነገር ግን በክርስቲያኖች ዘንድ ቦታ ባይኖረውም ማንም ባይተግብረውም። እንዲያውም ክርስቲያኖች በሚተገብሩት ሙስሊሞች ላይ ማፌዝና መቀለድ የተለመደ ተግባራቸው ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ በበርካታ ስፍራ ሰዎች ወደ ካዕባ መዞር እንዳለባቸው ለእምነቱ ተከታዮች ያዛል። ለምሳሌ፡- ያክል በ1ኛ መጽሐፈ ነገሥት 8፡44 ***«ጠላቶቻቸውን ለመዋጋት እንደዘመቱ በምታዝበት ጊዜ፡- በየትኛሁም ስፍራ ሆነህ፤ ወደዚች ወደ መረጥሃት ቤተ መቅደስ ፊቶቻቸውን መልሰው (አዞረው) በሚጸልዩበት ጊዜ በሰማይ ሆነህ ጸለታቸው ልማናቸው በመሰማት ድልን አቀዳጃቸው።»*** በዚህ አይነት ከሆነማ እናንተም አቅጣጫ እያመለካችሁ ነው ማለት ነው።

በኦሪት.ዘፀአት 32፡2-4 ***«አሮንም ሚስቶቻቻችሁ ወንዶችና ሴት ልጆቻችሁ የሚያጌጡበትን የጆሮ ወርቅ ሁሉ ሰብሰባችሁ ኡምጡልኝ አላቸው። ስለዚህ ሁሉም ያላቸውን የወርቅ ጉታቸውን አውልቀው ወደ አሮን አመጡላት እርሱም የወርቅ ጉታቸውን ሁሉ ወሰደ፤ በእሳት አቀለጠው። የቀለጠውንም ወርቅ በቅርጽ መስሪያ ውስጥ አስገብቶ የወርቅ ጥጃ ኢድርጎት ሰራው። ሕዝቡም እስራኤል ሆይ! ከግብፅ ምድር መርቶ ያወጣን አምላካችን ይህ ነው አሉ።»*** እውን የጥጃ ምስል የዓለማት አምላክ ሊሆን ያውም ሕዝቡን መርቶ ያወጣ? በተለይ በክርስቲያኖች የጣዖት አምልኮ ሚሊዮን ደደርሷል። ለምሳሌ፡-የማርያም ስዕል፣ የኢየሱስ ስዕል፣ የጊወርጊስ ስዕል፣ የሚካኤል ስዕል፣ የገብርኤል ስዕል፣ ወ.ዘ.ተ.ስንቱ ተቆጥሮ ይዘለቃል። በክርስቲያኖች ዘንድ ስዕል ማምለክ የእምነቱ አስኳል ተደርጎ የተወሰደ ነው። እስኪ አሁን ደግሞ በዚህ ዙሪያ ኢየሱስ ያለውን እንመልከት፡- በዮሐንስ ወንጌል 4፡19 ***«ሴቲቱ አንተ ነብይ እንደሆንክ ኢያለሁ፤ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አላቸው። ኢየሱስም አንቺ ሰው እመኝኝ በዚህ ተራራ ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አላት።»*** ታዲያ ኢየሱስ ተራራ እያመለከ ነው ማለት ነው? በመቀጠል ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል ብሏል። ያ ጊዜስ አሁን አይደለምን? የትኛው ክርስቲያን ነው ለአብ የሚሰግደው? ክርስቲያኖች ለአምላክ እንደማትሰግዱ ኢየሱስ ነግሮናል። ኢየሱስ በሌላ ቦታ ሕዝቡን አሰናብቶ ወደ ተራራ ወቶ እንደ ሰገደ ይናገራል። ስለዚህ የቂብላ አቅጣጫና ትእዛዝ ሆኖ እንጅ እንደ እናንተ አባባል ተራራ እያመለከ አይደለም። እኛ ሙስሊሞች ካባን አናመልክም። በአጠቃላይ እስልምና ከጣዖት አምልኮ፤ ከፎቶግራፍ ከቅርፃ ቅርፅ የፀዳ ሃይማኖት ነው።

## ጥ.ክ. **እናንተ ሙስሊሞች ለምን የተለየ የዘመን አቆጣጠር ያላችሁም? ጨረቃ ካልወጣች መፆም አትችሉምን?**

መ.ሙ. መጽሐፍ ቅዱስ ትልቁ ብርሃን ፀሐይ በቀን ትንሹ ብርሃን ጨረቃ በሌሊት እንዲሰለጥን እና ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕታት ለዓመታትም ይሁኑ ተብለዋል፡፡ በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡14 ***«እግዚአብሔርም አለ፡፡ ቀንና ሌሊቱን ይለዩ ዘንድ ብርሃናት በሰማይ ጠፈር ይሁኑ፤ ለምልክቶች ለዘመናት ለዕለታት ለዓመታትም ይሁኑ፡፡»*** በኦሪት.ዘፍጥረት 1፡16 ***«እግዚአብሔርም ሁለት ታላላቆች***

***ብርሃናትን አደረገ፤ ትልቁ ብርሃን እንዲሰለጥን፤ ከዋከብትንም አደረገ፡፡»*** በመጽሐፈ መዝሙር 136፡8-9 «***ለፀሐይ ቀንን ያሰገዛቸው፤ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፤»*** ጨረቃ ለምልክቶች ለዘመኖች ለዕለታት ለዓመታትም ከሆነ ለምን ይሆን የምታውቁት በተጨማሪ የጨረቃ መታየት ለጊዜ ማወቂያ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፡፡ በመጽሐፈ መዝሙር 104፡19 «***ጨረቃን ለጊዜዎች አደረገ፤ ፀሐይን መግቢያውያን ያውቃል፡፡»*** በተለይ አይሁዳዊያን የወር መባቻ ጠብቀው በዓላቸውን የሚያውቁበት ነው፡፡ የወር መባቻ የዕብራይስጡ ቃል ‹ቆይሽ› ሲሆን ትርጉሙ፡- ‹አዲስ ጨረቃ› ማለት ነው፡፡ ይህ ቃል 28 ጊዜ ተጠቃሷል፡፡ ዕብራውያን ወራቸውን ሆነ ዓመታቸውን የሚለምሩት በሰጋ ጨረቃ ነው፡፡ King James Verision በኦሪት.ዘፍጥረት 10፡10 «***ደግሞ በደስታችሁ ቀን፤ በበዓላችሁም ዘመን፤ በአዲስ ጨረቃ፤ በሚቃጠል መሥዕታችሁና በደኅንነት መሥዕታችሁ ላይ መለከቶቹን ንፉ፤ እነርሱም በአምላካችሁ ፊት ለመታሰቢያ ይሆንላችኋል እኔ እግዚአብሔር አምላካችሁ ነኝ፡፡»*** King James Verision በመጽሐፈ መዝሙር 81፡1 «***በአዲስ ጨረቃ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን መለከትን ንፉ፤»*** በክርስትና ቀዳማይ የዘመን አቆጣጠር ከ 180-222 A.D ድረስ ለ 42 ዓመት የአሌክሳንድርያ ፓትርያርክ የነበረው ዴሜጥሮስ የቀመረው ነበር፡፡ ይህም የዘመን ቀመር አቡሻኽር ወይም ‹ባሕረ-ሐሳብ› ይባላል፡፡ ‹ባሕር› ማለት ዘመን ማለት ሲሆን ‹ሐሳብ› ማለት ድግሞ ‹ሒሳብ› ቁጥር ኍሉቅ ማለት ነው፡፡ በዚህ የዘመን ቀመር ላይ ስለ ‹አዕዋዳት› ይናገራል፡፡ አዕዋድ ማለት ‹ዖደ› ማለትም ‹ዞረ› ከሚል የግዕዝ ቃል የተገኘ ሲሆን በየጊዜው እየዞረ የሚመጣ ማለት ነው፡፡ ዓውደ- ወርኅ በፀሐይ 30 ቀናት በጨረቃ 354 ቀናት ነው፡፡ በተጨማሪም በመጽሐፈ ሲራክ ጨረቃም ለሁሉም የዘመን መለኪያ ለዓለም ሁሉ ምልክት እና የበዓላት ምልክት እንደሆነች ይናገራል፡፡ በመጽሐፈ ሲራክ 43፡6-7 «***ጨረቃም ለሁሉም የዘመን መለኪያ ናት፤ ለዓለም ሁሉ ምልክት ናት፤ በእርሷም ቀን ይለያል፤ በጨረቃም የበዓላት ምልክት ይታወቃል፡፡»*** ታዲያ ጨረቃን ጠብቆ ፆም መያዝ መፍታትና በዓል ማክበር በዓል ለምን ሂስ ይሰጥበታል? እግር እራስን ያካል እንዴ? የምጣዱ እያለ የእንቅቡ ተንጣጣ ወይም ቅቤ አንጣሪዋ እያለሽ ጎመን ቀቃይዋን ምች መታት ይላል ያገሬ ሰው፡፡ ስለዚህ ቅድሚያ እስልምናን ለመዝለፍ ክርስትናን ጠንቅቃችሁ እወቁ፡፡

ጥ.ክ. **ቁርኣን እርስ በርሱ ይቃረናል፤ ለዚህ ማስረጃ ሶላት የእምነቱ ማዕዘን እንደሆነ ይታወቃል። ሶላትንም ስገዱ እያለ ያዛል። ነገር ግን በሌላ ቦታ ደግሞ ወዮላቸው ለሰጋጀን አሁን በሌላ ቦታ ላይ ወደ ሶላት አትቅረቡ ይላል። ስለዚህ ሁለቱም ንግግሮች ይቃረናሉ።**

መ.ሙ. ‹**ስራ ያጣ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል**› አሉ። በመጀመሪያ ቅዱስ እንዴት እንደሚቃረን አላያችሁም። ከቃሉ እንጀምር መቃረን ማለት እርስ በርሱ የሚጋጭ ከአንዱ አረፍተ ነገር ከሌላኛው ጋር የማይስማማ ማለት ነው። ቁርኣን አልሐምዱሊላህ አይቃረንም፤ እስልምናም ስገባም ከመግባቴም በፊትም አንብቤዋለሁ። ዛሬም በማንበብ ላይ ነኝ፤ አንዲት ቦታ ላይ ተቃርኖ እርስ በእርሱ ተጋጭቶ አይታወቅም። በፍጹም አይጋጭም። ምክንያቱም ቁርኣን የዓለማቱ ጌታ የአላህ ቃል ብቻ ነው። ቁርኣን የሰው እጅ አይገባበትም፤ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ተሸሽሎ ታርሞ የሚባልም ህትመት የለውም። ቁርኣንን ለማንበብ በመጀመሪያ የተስተካከለ መነፅር የቁርኣን አዕምሮ ያስፈልጋል። መቼም ቢሆን አንድ ሰው በሰባራ መስታወት ሙሉ ማንነቱን አይቶ እንደማያምረበት ሁሉ ቁርአንን ለማንበብም የተስተካለ መነፀር ያለው አዕምሮ ያስፈልጋል። ያ ማለት እስልምና ገብቶ በእስልምና መነጽር ማየት ይችላል። አለበለዚያ ግን እንኳን ቁርአን ሊቀራ ይቅርና ቁርኣን በርሱ ላይ እየተቀራ ነው የሚያልፈው። መቃረን ማለት እንደሆነ በአንድ ምዕራፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች እርስ በእርሱ መጣረስ ማለት ነው። ለምሳሌ፡- በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዮሐንስ ወንጌል 5፡31 ‹‹***እኔ ስራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት አይደለም***።›› ከዚሁ ምዕራፍ 8፡14‹‹***እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ምስክሬ እውነት ነው***።›› በኦሪት.ዘፍጥረት 6፡6 ‹‹***እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በመፍጠሩ አዘነ፤ በልቡም ተጸጸተ***፡፡›› በኦሪት.ዘኁልቁ 23፡19 ‹‹***እግዚአብሔር ይጸጸት ዘንድ የሰው ልጅ አይደለምና***፡፡››

## የዮሴፍ አባት ማን ነው?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡16 ‹‹***ያዕቆብ ዮሴፍን ወለደ***፤...››

በሉቃስ ወንጌል 3፡23... ‹‹***ይኸውም ዮሴፍ የዔሊ ልጅ*** ...››

## አሥራ አንድ ወይስ አሥራ ሁለት?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡16‹‹*አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ እንዲሄዱ ወደ አመላከታቸው በገሊላ ወደሚገኘው ተራራ ሄዱ፡፡*››

በ፲ኛ ቆረንቶስ 15፡4-5 ‹‹ ... *በቅዱስ መጽሐፍ እንደተጻፈውም በሦስተኛው ቀን ከሞት ተነሳ የሚል ነው። እንዲሁም ለጴጥሮስ ታዩ፤ ኋላም ለአሥራ ሁለቱ ታዩ፡፡*››

## ምስክርነቱ እውነት ነው ወይስ አይደለም?

በዮሐንስ ወንጌል 5፡31 ‹‹*እኔ ስለራሴ ብመሰክር ምስክርነቴ እውነት አይደለም፡፡*››

በዮሐንስ ወንጌል 8፡14 ‹‹*ምንም እንኳ እኔ ስለ ራሴ ብመሰክር ከየት እንደመጣሁ ወዴት እንደምሄድ ስለማወቅ ምስክርነቴ እውነት ነው፡፡*››

## አሥራ ሁለቱ ወይስ አንዱ ብቻ ዲያብሎስ?

በማቴዎስ ወንጌል 19፡28‹‹*ኢየሱስ እንዲህ አላቸው፡- "በእውነት እላችኋለሁ" የሰው ልጅ በክቡር ዙፋን ላይ የሚቀመጥበት በአዲሱ ዘመን የኔ ተከታዮች ሆናችሁ እናንተም በአሥራ ሁለቱ ዙፋን ላይ ትቀመጣላችሁ። በአሥራ ሁለት የእስራኤል ነገዶች ላይ ተሹማችሁ ትፈርዳላችሁ፡፡*›› በዮሐንስ ወንጌል 6፡70 ‹‹*ኢየሱስም፡- "እናንተ አሥራ ሁለታችሁን መርጬአችሁ የለምን? ታዲያ እኮ ከእናንተ አንዱ ዲያቢሎስ ነው።" አላቸው፡፡*››

## ሰባት መቶ ወይስ ሰባ ሺህ? አርባ ሺህ ፈረሰኛ ወይስ አርባ ሺ እግረኛ?

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 10፡18 ‹‹ ... *ዳዊትና ሠራዊቱ ሰባት መቶ የሶሪያውያን የሰረገላ ነጅዎችንና አርባ ሺህ ፈረሰኞችን ገደሉ፡፡*››

በ፲ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል 19፡18 ‹‹... *ዳዊትና ሠራዊቱ ሰባት ሺህ ሰረገላ ነጅዎችን አርባ ሺህ እግረኛ ወታደሮችን ገደሉ፡፡*››

## ዳዊትና ለመከራ ማን አነሳሳው? እግዚአብሔር ወይስ ሰይጣን?

በ2ኛ መጽሐፈ ሳሙኤል 24፡11 *‹‹እግዚአብሔር እንደገና በእስራኤል ላይ ስለተቆጣ በዳዊት አማካኝነት መከራ እንዲመጣባቸው አደረገ። እግዚአብሔር ዳዊትን "ሄደህ የእስራኤልንና የይሁዳን ሕዝብ ቁጠር" አለው።››*

በ1ኛ መጽሐፈ ሰዜና መዋዕለ 21፡1 *‹‹ሰይጣን በእስራኤል ሕዝብ ላይ መከራ ማምጣት ስለ አቀደ ዳዊትን የሕዝብ ቆራ እንዲያደርግ አነሳሳው።››*

## ሦስት ሰዓት ወይስ ስድስት ሰዓት?

በማርቆስ ወንጌል 15፡25 *‹‹ኢየሱስን ሲሰቅሉት ጊዜው ከጧቱ ሦስት ሰዓት ነበር።››*

በዮሐንስ ወንጌል 19፡14-15 *‹‹የፋሲካ ዝግጅት ቀን ነበር፤ ጊዜውም ወደ ስድስት ሰዓት ገደማ ነበር፤ በዚያን ጊዜ ጲላጦስ አይሁዳውያንን "እነሆ ንጉሳችሁ" አላቸው። እነርሱ ግን "ወዲያ ውሰደው! ወዲያ ውሰደው! ስቀለው!" እያሉ ጮሁ።››*

## መስቀሉን ማን ተሸከመ? ኢየሱስ? ወይንስ የቀሬና ሰው?

በማቴዎስ ወንጌል 27፡32*‹‹ከገዢው ግቢ ሲወጡ ስምዖን የተባለው የቀሬና አገር ሰው አገኙና የኢየሱስን መስቀል እንዲሸከም አደረጉት።››*

በሉቃስ 23፡26*‹‹በወደሰዱትም ጊዜ ስምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መሰቀሉን እንዲሸከም ጫኑበት።››*

በዮሐንስ ወንጌል 19፡17*‹‹ከዚህ በኋላ ኢየሱስ መስቀሉን ተሸክሞ "የራስ ቅል" ወደ ሚባለው ስፍራ ወጣ።››*

## ሐሞት ወይስ ከርቤ?

በማቴዎስ ወንጌል 27፡34 *‹‹በዚያም ከሐሞት ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ለኢየሱስ አቀረቡለት።››*

በማርቆስ ወንጌል 5፡23‹‹*እዚያም በደረሰ ጊዜ ከከርቤ ጋር የተቀላቀለ የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት*።››

## መግደላዊት ማሪያም ብቻ ወይስ ሌሎችም?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡1 ‹‹*ሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ ዕሁድ ጧት በማዳ መግደላዊት ማርያምና ሌላይቱ ማርያም መቃብሩን ለማየጥ ሄዱ*።›

በማርቆስ ወንጌል 16፡1-2 ‹‹*ሰንበት ቀን ካለፈ በኋላ መቅደላዊት ማርያም ያዕቆብን እናት ማርያም ሰሎሜም ሆነው የኢየሱስን አስከሬን ለመቀባት ሽቶ ገዙ። ዕሁድ ጧት ልክ ፀሐይ ስትወጣ ወደ መቃብሩ ሄዱ*።››

በሉቃስ ወንጌል 24፡10 ‹‹*ከመቃብር ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሯቸው። ይህን ለሐዋሪያት የተናገሩት መቅደላዊት ማርያምና የሐናና የያዕቆብ እናት ማሪያም እንዲሁም ሌሎች ሴቶች ነበሩ*።››

በዮሐንስ ወንጌል 20፡1 ‹‹*እሁድ ጧት በማለዳ ገና ጎህ ሳይቀድ መግሰደላዊት ማርያም ወደ ኢየሱስ መቃብር ሄደች*።››

## መልአክ ወይስ ሰዎች?

በማቴዎስ ወንጌል 28፡2-3‹‹*እነሆ በድንገት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ የእግዚአብሔር መልአክ ከሰማይ ወርዶ መቃብሩ የተዘጋበትን ድንጋይ አንከባለለና በላዩ ተቀመጠ። የመልአኩም ፊት እንደ መብረቅ ያበራ ነበር። ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበር*።›› በሉቃስ ወንጌል 24፡3-4‹‹*ወደ መቃብርም በገቡ ጊዜ ግን የጌታ ኢየሱስን አስከሬን አላገኙም፤ ስለዚህም ነገር በመገረም ላይ ሳሉ እነሆ የሚያንፀባርቅ ብሩህ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በድንገት መጥተው በአጠገባቸው ቆሙ*።›› በማርቆስ ወንጌል 16፡5‹‹*ወደ መቃብሩም በገቡ ጊዜ ነጭ ልብስ የለበሱ ጎልማሳ በስተቀኝ በኩል ተቀምጦ በማየታቸው ደነገጡ*።›› በዮሐንስ ወንጌል 20፡12‹‹*የኢየሱስም አስከሬን በነበረበት ሰፍራ ነጭ ልብስ የለበሱ ሁለት መልአክት አንዱ በራስጌ አንዱ በግርጌ ተቀምጠው አየች*።››

## ተናገሩ ወይስ አልተናገሩም?

በማርቆስ ወንጌል 16፡8‹ ***‹ሴቶቹም በፍርሃት እየተንቀጠቀጡ ከመቃብር ወጥተው ሸሹ። እጅግ ፈርተው ስለ ነበር ምንም ነገር ለማንም አልተናገሩም።›*** በሉቃስ ወንጌል 24፡8-9‹‹***ሴቶቹም የኢየሱስን ቃል አስታወሱ፤ ከመቃብር ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለቀሩትም ነገሩዋቸው።››***

## የእግዚአብሔር የበኩር ልጅ ማን ነው? እስራኤል ወይስ ኤፍሬም?

በኦሪት.ዘጽአት 4፡22 ‹‹***በዚያን ጊዜ እኔ እግዚአብሔር ለፈርዖን የምለውን እንዲህ ብለህ ትነግረዋለህ፡- እስራኤል የበኩር ልጄ ነው።››***

በትንቢተ.ኤርምያስ 31፡9 ‹‹... ***እኔ ለእስራኤል አባት ነኝ፤ ኤፍሬምም የበኩር ልጄ ነው።››*** መቃረን ማለት ይህ ነው። ለምሳሌ፡- ይህን ጠቀስኩ እንጂ ከ100 በላይ የሚቃረኑ ትቅሶች አሉ። እነዚህን መዘርዘሩ ቃል በቃል መተርጎም ነው የሚሆነው።ቁርአን ግን ከእንደዚህ አይነት መቃረን የጠራና የፀዳ ነው። ቁርአን በሱረቱል አል-ኒሳእ 82‹‹**ቁርኣንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ ዘንድ (አምላክ) በነበረ ኑሮ በእርሱ ብዙ መለየትን ባኙ ነበር**›› ይለናል። አዎ የማይካድ ሀቅ ነው። ከአላህ ሌላላ አምላክ ቢኖር ልዩነት ይፈጠር ነበር እኔ ያን ልገዛ በማለት ልዩነት ይኖር ነበር። ነገር ግን የአለማቱ ጌታ አንድ አላህ በመሆኑ ሁሉን የሚገዛ እርሱ ብቻ በመሆኑ ቃሉ አይቀያየርም፤ አይጻረርምም። ቁርኣን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ ውሸት የለበትም። በሱረቱል አል-ሰጂዳህ 42‹‹**ከኋላውም ከበስተፊቱም ውሸትም አይመጣበትም፤ ጥበበኛ ምስጉን ከሆነው አምላክ የተወረደ ነው።**›› ቁርአን እንደ መጽሐፍ ቅዱስ የሰው እጅ አይገባበትም፤ አይበረዝበትም፤ አይጨመርበትም፤ አይቀነስበትም። በሱረቱል ሒጂር 9 ‹‹**ዕኛ ቁርኣንን አወረድነው እኛም ለእርሱ ጠባቂዎች ነን።**›› ስለዚህ ቁርኣንን ማንም አይበርዘውም፤ ይቅርና ሙሉ መጽሐፉን መበረዝ አንዲትን ሀርፍ (አሊፍን) መቀየር እንኳ አይችሉም። ቁርኣንን በመጠበቁ በኩል አላህ (ሱ.ወ) እራሱ ለመጠበቅ ሀላፍትና ወስዷል። እንዲሁም ቃል ገብቷል። በሱረቱል አል በቀራህ 28 ‹‹**በባሪያችን ላይ ባወረድነው ኪታብ በመጠራጠር ላይ ብትሆን ከቢጤው አንዲትን ምዕራፍ አምጡ በላቸው**›› በማለት ለሰው ልጆችና ለጋኔኖች ፈተና አቅርቧል። ሆኖም ግን ጅንም ሆነ የሰው ልጅ

አንዲትን ምዕራፍ ይቅርና አንዲት ፊደል ማምጣት እንደማይችሉ እንዲህ ይናገራል። በሱረቱል አል-ኢስራ 88 ‹‹**ጋኔኖችና የሰው ልጆች ቢተባበሩ፤ አንዲትን ምዕራፍ አያመጡም በላቸው።**›› በዚህ ተመሳሳይ መልኩ ከአስር በላይ የሚደርሱ ምዕራፍና ቁጥሮች አሉ። እነርሱን ከመዘርዘር ወደ ቀጣዩ ወደ መልሱ ላምራ፡- በሱረቱል አል-ኒሳእ 42 ‹‹**እናንተ ያመናችሁት ሰዎች ሆይ! ወደ ሶላት የሰከራሁ ሆናችሁ አትቅረቡ፤ የምትሉትን እስከታውቁ ድረስ**›› ነው እንጂ አትስገዱ አላለም። ታዲያ ከምን የቁርኣን አንቀጽ ጋር ነው የሚጻረረው ነው እንደ እናንተ መጽሐፍ ቁዱስ የአስካሪ መጠጥ መፍቀድ ነበረበት ካላችሁ ሌላ ጥያቄ ነው። ሶላት ማለት እኮ አንድ ባሪያ ከጌታው ጋር የሚገናኝበት የአምልኮ መስመር ነው። ስለዚህ አንድ ሙስሊም ከመጥፎ ነገሮች እራሱን አርቆ ሰውነቱን አፅድቶ እንዲሁም ልቡንም እንደዚሁ አፅድቶ ነው ወደ አምላኩ መቅረብ ያለበት። በሱረቱል አል-ማኡን 4-5 ያለውን ስንመለከት ከላይ ካሳለፍነው የቁርኣን አንቀጽ ጋር የሚቃረን ሳይሆን የሚስማማ ነው። ‹‹**ወዮላቸው! ለሰጋጆን፤ ለነዚያ ከስግደታቸው ዘንጊ ለሆኑት ሰጋጆች።**›› ከዚህ ላይ ለነማን ነው ለሚሉት ጥያቄዎች አላህ ሱ.ዐ.ወ) እራሱ መልስ ሰጥቷል። ከስግዳቸው ዘንጊ የሆኑ በማለት መልሱ በቀጣዩ ቁጥር አስፍሮታል። በአለም ላይ እንደ ቁርአን ያለ ትልቅ ታዓምር የለም።!! እንዲሁም እንደርሱ ያለ ትልቅ መጽሐፍ የለም።!!! የሰዎች እጅ አይገባበትም፤ አያርመውም፤ አይጨምሩበትም፤ አይቀንሱበትም፤ ይህንን የማድረግ የሰው ልጅ ስልጣን የለውም።!!! መጽሐፍ ቅዱስ ግን በየጊዜው ታርሞና ተሸሽሎ የቀረበ በማለት የሰው እጁ እንደገባበት እራሱ መልስ ይሰጣል። ለምሳሌ በኦርቶዶክሱ 81ዱ በካቶሊክ 73ቱ በፕሮቴስታንት 66ቱ በማለት ተከፋፍሏል። ታዲያ እነዚህ ሁሉ የአምላክ ቃል ከሆኑ ለምን በሰው እጅ መከፋፈል አስፈለገው? ለምን ተጨመረ? ተቀነሰ? አንዱ 81፣ አንዱ 73፣ አንዱ 66 በማለት ለምን ተቀነሰ ተጨመረ?

## ምዕራፍ ሀያ አንድ

## ክርስቲያኖች የምነቅፍባችሁ ነገር አለ።

በዮሐንስ ራእይ 2፡4-5 ‹‹*ነገር ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ይኸውም የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃል፤ ከመውደቅህ በፊት የት እንደ ነበርክ አስታውስ፤ ንስሓም ግባ*›› እንዳለው እኔም የቀደመውን ሃይማኖት ያዙ ወደ ሲዖል ከመግባታችሁ በፊት ንሰሓ ግቡ። ወደ ሮሜ 12፡3 ‹‹*ደግሞም "እንያንዳንዳችሁ እንግዚአብሔር በሰጣችሁ እምነት በትህትና አስቡ እንጂ ከሚገባችሁ በላይ ስለራሳችሁ በትዕቢት አታስቡ" ብዬ እግዚአብሔር በሰጠኝ ፀጋ እምከራችኋለሁ።*›› በ2ኛ ቆረንቶስ 6፡2-3 ‹‹*እግዚአብሔር፣ "በመረጥሁት ሰዓት ሰማሁህ፤ በኀንነትህም ቀን እረዳሁህ" ስለሚል፤ የተመረጠው ሰዓት አሁን ነው፤ የደኅንነትህም ቀን አሁን ነው።" አገልግሎታችን እንዳይነቀፍ በምንም ነገር ለማንም መሰናከያ አንሁን።*›› ከዚሁ ምዕራፍ የ1954 ዕትም ‹‹*በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ፤ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ! የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ! የመዳን ቀን አሁን ነው።*›› ስለዚህ ወደ አምላክ የምንመለስበት፤ ንሰሓ የምንገባበት ሰዓት አሁን ነው ተመለሱ።

## ክርስቲያኖች ተሳስታችኋል፤ ከመንገድ (ከሃይማኖት) ተመልሳችኋል።

ክርስቲያኖች ያላችሁበትን ሃይማኖት ፈትሹ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ "ክርስቲያን ሁኑ የደኅንነት መንገድ ነው" የሚል አንድም ጥቅስ የለም። የሃይማኖት መሪዎች ነን የሚሉት ከትክክለኛው እስልምና ሃይማኖት መልሰዋችኋል። በትንቢተ.ኤርሚያስ 3፡21 ‹‹*እግዚአብሔር አምላካቸውን በመርሳት መንገዳቸውን (ሃይማኖታቸውን) አጣመዋልና።*›› ከዚሁ ምዕራፍ 5፡4‹‹*የእግዚአብሔርን መንገድ (ሃይማኖት) የአምላካቸውን ሕግ ኣላወቁምና*›› ይላል። አንሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 7፡23-24 ‹‹*ነገር ግን ድምፄን ስሙ፡- እኔም አምላክ እሆናችኋለሁ፤ እናንተም ሕዝቤ ትሆናላችሁ፤ መልካም እንዲሆንላችሁም ባዘዝኳችሁ መንገድ ሁሉ ብዬ አዝኳቸው። እንርሱ ግን አልሰሙም፤ ልብ ብለውም ለማዳመጥም አልፈለጉም፤ ይልቁንም የክፉ ልባቸውን ሐሳብ በልኸኝነት ተከተሉ፤ ወደ ፊት በመሄድ ፋንታም ወደ ኋላቸው ተመለሱ።*›› ከዚሁ ምዕራፍ 7፡28‹‹*ይህ ሕዝብ አምላኩን ያልታዘዘ፤ ምክሩን ያልተቀበለ፤ ወገን ነው።*

*እውነት ጠፍቷል፤ ከአንደበታቸውም ሸሽቷል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 8፡4-6 «*ሰዎች ቢወድቁ እንደገና አይነሱምን ሰው ተሳስቶ ወደ ኋላ ቢሄድ ከስተቱ አይመለስምን ታዲያ ይህ ሕዝብ ለምን ፊቱን አዙሮ ይሄዳል፤ ተንኮልን የሙጥኝ ብለው ይዘዋል፤ ሊመለሱ ፈቃደኛ አይደሉም። እኔ እግዚአብሔር በጥንቃቄ አደመጥኋቸው፤ ትክክለኛ የሆነውን ግን አይናገሩም። ማንም ሰው ከክፋቱ ንስሓ የገባ የለም፤ ምን አድርጊአለሁ ይላል። ለጦትነት እንደተዘጋጀ ፈረስ እንያዳንዱ በራሱ መንገድ ይሄዳል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 9፡3 «*በእውነት ሳይሆን ገነኑ----- ከክፋት ወደ ክፋት ሄዱ፤ እኔንም አላወቁኝም*።» ከዚሁ ምዕራፍ 10፡1-2«*እግዚአብሔር የሚላችሁን ስሙ፤ እንግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- የአሕዛብ መንገድ አትከተሉ*።» በትንቢተ.ሆሴዕ 4፡6 «*ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሳ ጠፍቷል*።»

## ክርስቲያኖች ምክርን ስሙ!!!

ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስ የሚመክራችሁን ከልባችሁ ስሙ። እንዲሁም አንብቡ፤ እውነተኛውን ሃይማኖት ያዙ የሚላችሁ ሰው ለእናንተ ቅን አሳቢ ሰው ነው። መጽሐፈ መዝሙር 16፡7 «*የሚመክረኝን እግዚአብሔር ይባረከው*» ይላል። ስለዚህ የእናንተም መልስ ለሚመክራችሁ ሰው እንዲህ መሆን አለበት። በመጽሐፈ ምሳሌ 12፡1 «*ተግሣጽን የሚወድ እውቀትን ይወዳል፤ ምክርን የሚጠላ ደነዝ ነው*።» ከዚሁ ምዕራፍ 12፡15 «*ተላላ ሰው መንገዱ ትክክል መስሎ ይታየዋል፤ ጠቢብ ግን ምክርን ይሰማል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 13፡13 «*ምክርን የሚያቃልል በራሱ ላይ ጥፋት ያመጣል*።» ከዚሁ ምዕራፍ 13፡14 «*የጠቢብ ትምህርት የሕይወት ምንጭ ናት፤ ሰውን በሞት ወጥመድ እንዳይያዝ ያደርጋቸዋል*።» በሉቃስ 7፡35 «*ነገር ግን የእግዚአብሔር ጥበብ የሚታወቀው በጥበበኞች ዘንድ ነው*።» በትንቢተ.ሆሴዕ 14፡9 «*ጥበበኛ የሆነ እነዚህን ነገሮች ያስታውሳል፤ አስታውሎም እነዚህ ነገሮች ይረዳል፤ የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነውና ፃድቃን ይሄዱበታል፤ አመጻኞች ግን ይሰናከሉበታል*።» በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡6-8 «*በዚህ ነገር ማንም ወንድሙን አይበድል፤ ወይንም አያታልል፤ ከዚህ በፊት እንደ ነገርናችሁና እንደ አስጠነቀቅናችሁ፤ እነዚህን ነገሮች የሚያደርጉትን ጌታ ይቀጣቸዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የጠራን በቅድስና እንድንኖር አይደለም። ስለዚህ ይህን ምክር የሚቃወም፤ የሚቃወመው ቅዱስ መንፈሱን*

*የሚሰጣችሁን እግዚአብሔር ነው እንጂ ሰውን አይደለም።»* ስለዚህ እኔን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው የምትቃወሙት።

## ክርስቲያኖች መሪዎቻችሁ አሳስተዋችኋል።

በመጽሐፈ ምሳሌ 1፡25 *«እናንተ ብስለት የሌላችሁ ማስተዋል የሌለበትን መንገዳችሁን እስከ መቼ ትወዱታላችሁ?* ይላል። ከዚሁ ምዕራፍ 15፡10 *«ከመንገድ (ከሃይማኖት) የሚወጣ ሰው ጥብቅ ቅጣት ይጠብቀዋል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 16፡24 *«ግፈኛ ሰው ወዳ ጁን ያባብላል፤ መልካም ወደላይደለ መንገድ (ሃይማኖት) ይመረዋል።»* ከዚሁ ምዕራፍ 16፡25 *«ለሰው ቀና መስሎ የሚታይ መንገድ አለ፤ በመጨረሻ ግን ወደ ሞት ያመራል።»* በትንቢተ.ኢሳይያስ 3፡12 *«ሕዝቤ ሆይ! መሪዎችህ አሳስተውሃል፤ ከመንገድም መልሰውሃል።»* ከዚህ ላይ መሪዎች ማን ናቸው የሚል ጥያቄ ማቃጨሉ አይቀርም። ለዚህ ምላሽ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ መልስ ይኖረዋል።

ቄሶች ማለት ምን አይነት ሰዎች እንደ ሆኑ በቀጥታ መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንዳላቸው እንመልከት። በመጽሐፈ መቃብያን ካልዕ 7፡2 *«እንደ እግዚአብሔር የምትሰውላቸውና የምትሰግዱላቸው፤ እናንተና ካህናቱ እስከ ዘላለም (ከሲዖል) ከእርሷ መውጫ የላቸውም።»*

## ክርስቲያኖች በእምነትና በተግባር ላይ ሁኑ!!!

የሰውን ልጅ አምላክ የፈጠረበት ዓላማ እሱን እንዲገዙትና እንዲያመልኩት ብቻ ነው። ሰዎች ሁሉ በእምነትና በተግባር ላይ መቆም አለባቸው። ኢየሱስ ምን ያክል ለአምላክ ታዛዥ፣ የእምነትና የተግባር ሰው እንደ ነበር። በዮሐንስ ወንጌል 10፡18*«ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልኩ»* በማለት ይናገራል። ከዚሁ ምዕራፍ 12፡ 49-50*«እኔ የምለውንና የምናገረውን ትእዛዝ የሰጠኝ የላከኝ አብ ነው። የእርሱም ትእዛዝ የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነ አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረው አብ የነገረኝን ትእዛዝ ነው።»* አሁንም ከዚሁ ምዕራፍ 14፡31*«ነገር ግን እኔ አብን እንደምወድ ዓለም ያውቅ ዘንድ አብ ያዘዘኝን ሁሉ እፈፅማለሁ።»* አሁንም በድጋሜ በዚሁ ምዕራፍ 9፡4*«ኢየሱስም እንዲህ አለ፡- ቀን ሆኖ ሳለ የላከኝን ሥራ መስራት አለብኝ፤ ማንም ሰው ሊሰራ የማይችልበት ቀን ይመጣልና።»*

እኛም የምንላችሁ ቀን ሆኖ ሳለ የአላህን ትዕዛዝ ፈፅሙ፤ ኢየሱስ እንደፈፀመው። ትዕዛዝን የሚፈፅሙ ሁሉ ብፁዓን (ፃዲቅ) መሆናቸውንም ጠቁሟል። በሉቃስ ወንጌል 11፡28 «***ብጹዓንስ (ፃድቃን) የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚጠብቁ ናቸው።***» እምነት ማለት መልካም ስራን እንድንሰራ፤ መጥፎን ስራ ደግሞ እንድንርቅና በአጠቃላይ ስራችን ሁሉ በመልካም ስራ የተገነባ መሆን አለበት። አለበለዚያ ግን ማመናችን ትርጉም ያጣብናል። ኢየሱስ በማቴዎስ ወንጌል 7፡19 «***መልካም ፍሬ የማያፈራ ዛፍ ይቆረጣል፤ ወደ እሳትም ይጣላል***» በማለት በአንድ አምላክ እንድናምንና አምነንም መልካም ስራ እንድንሰራ ያስገነዝበናል። በተመሳሳይ በያዕቆብ መልእክት 2፡14 «***ወንድሞቼ ሆይ! ሰው እምነት አለኝ ቢል ነገር ግን እምነቱን በመልካም ሥራ ባይገለጥ ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ያድነዋልን?።***» ከዚሁ ምዕራፍ 2፡19-20 «***አንተ "አንድ እግዚአብሔር አለ ብለህ ታምናለህ፤ "ይህም መልካም ነው፤ ማመንማ አጋንንትም ያምናሉ፤ በፍርሃትም ይቀጠቀጣሉ። አንተ ሞኝ! ከሥራ የተለየ እምነት ፍሬ ቢስ* (የሞተ) መሆኑን ታያለህን?***» ከዚሁ ምዕራፍ 14፡17 «***ከመልካም ሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።***» ከዚሁ ምዕራፍ 2፡26 «***ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ ነው፤ እንዲሁም ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።***» ስለዚህ መልካም ሥራ የሃይማኖት ውጤት ወይም ፍሬ ነው።

## ➢ የደኅንነት ጥሪ ለክርስቲያኖች በሙሉ

በእስልምና ላይ ሂዱ፤ በቀደ

መችው መንገድ (ሃይማኖት) በቀጥተኛዋ ሃይማኖት።በትንቢተ.ኤርሚያስ 16፡16 «*እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡- በመንገድ (ሃይማኖት) ላይ ቁሙ፤ተመልከቱም፤ የቀደመችውን መንገድ (ሃይማኖት) ጠይቁ፤ መልካሚቱ መንገድ (መልካሚቱ ሃይማኖት እስልምና) ወዴት እንደ ሆነች እወቁ፤ በእርሷም ላይ ሂዱ። ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ፤ እነርሱ ግን አንሄድባትም (እስልምናን አንከተልም) አሉ*።» በትንቢተ.ሐጌ 1፡7 «*የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- ልባችሁን በመንገድ (በሃይማኖት) ላይ አድርጉ*።» በትንቢተ.ሆሴዕ 14፡9 «*የእግዚአብሔር መንገድ (ሃይማኖት) ቅን እና ሕይወት ነው፤ ፃድቃን ይሄዱበታል፤ ኃጢአኞች ግን ይወድቁበታል*።»በኦሪት.ዘዳግም 5፡33 «*በሕይወት እንድትኖሩ፤ መልካምም እንዲሆንላችሁ፤ በምትወርሱት ምድር ዕድሜአችሁ እንዲረዝም፤ እግዚአብሔር ባዘዛችሁ መንገድ (ሃይማኖት) ላይ ሂዱ*።» በትንቢተ.ኢሳይያስ 26፡7 «*የፃድቃን መንገድ (ሃይማኖት) ቅን ናት፤ አንተ ቅን የሆንክ የፃድቃንን መንገድ ታቀናለህ*።» ጥሪን ማክበር የጨዋነት ተምሳሌት ነው።

# ምዕራፍ ሀያ ሁለት

## ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ

- **የስራው አይነት**፡- በአላህ ማመን
- **ጾታ**፡- አይለይም፤ ሴትም ሆነ ወንድ፤ ትልቅም ሆን ትንሽ።
- **የትምህርት ደረጃ**፡- አርካኑል አስላምና አርካኑል ኢማን ያሟላ የአካደሚ ደረጃ አይጠይቅም።
- **ተፈላጊ የሰው ብዛት**፡- ለፍጥረታት በሙሉ ቁጥር አይገድበውም።
- **የስራ ቦታ**፡- በአሉበት ሆነው በየትኛውም ሀገር ቅርንጫፉን ማግኘት ይችላሉ። እንዲሁም በአሉበት ሀገር ሆነው የድርጅቱን ሰራተኞች በቀላሉ ማግኘትና ስለ ስራው አይነት መጠየቅና ማወቅም ሆነ መረዳት ይቸላሉ። ድንገት ወደ እኛ ጉራ ካሉም ሙሉ ኢንፎርሜሽን እንዲኖረዎት ሃይማኖታዊ ንጽጽር እንዲሁም ቁርኣንና ሐዲስ እናስተምረዎታለን።
- **የምዝገባ ጊዜ**፡- ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ህይዎትዎ በምድር ላይ እስካለ ድረስ ሞት ሳይቀድመዎት
- **ምዝገባው የሚበቃበት ጊዜ**፡- ሕይዎትዎ ከዚህ ምድር በሞት ሲለይና ወደ ሁለተኛው ዓለም ሲሻገሩ።
- ስለዚህ ሁሉም ፍጥረታት በዚህ ምድር የሚኖሩት እድሜ ውስንና አጭር ስለሆነ ፍጥረታት በሙሉ ጊዜአቸውን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት የድርጅቱ ብቸኛ ኃላፊ የሆነው ጥብቅ መልክቱን ያስተላልፋል።
- ከአመልካቾች የሚጠበቁ መስፈርቶች ሁሉም አመልካቾች ዋናውን ኦርጅናሉን የማይመለስ የመስከር ቃላቸውን መስጠት ይኖርባቸዋል። ኦርጅናሉን ቃል ካልሆነ በስተቀር ኮፒውን ፈፅሞ ድርጅቱ አይቀበልም። ኦርጅናሉ የመመዝገቢያ የምስከር ቃል ላኢላሀ ኢለላህ ሙሐመድ ረሱሉላህ ነው። እንዲሁም ቀሪ ማዕዘናቶቹንና የኢማን ክፍሎቹን ማሟላት ግዴታቸው ነው። ስለዚህ ሁሉም አመልካቾች ይህን መስፈርት ካሟሉ የድርጅቱ ጠንካራ ሰራተኛ መሆን ይችላሉ። ከላይ የተዘዘዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሰራተኞችን በሙሉ ድርጅቱ ተቀብሎ የሚያስተናግድ መሆኑን በደስታ ይገልፃል።

- በተጨማሪም ሁሉም የድርጅቱ ሰራተኞች የተጣለባቸዉ ሀላፊነትና እየተወጡ ፀንተዉ ለተገበሩ የድርጅቱ ሀላፊ ደመወዛቸዉን አዕምሮአቸዉ ያላሰበዉንና ያልገመተዉን እንዲሁም በልባቸዉ ዉል ያላለዉን ምንዳ አዘጋጅቶ ይጠብቃቸዋል። ከተጨማሪ የምስጋናና የምስክር ወረቀት ጋር እንድህ በማለት-----------)
- እንድሁም ከሁሉም የድርጅቱ ሰራተኞች ከተጣለባቸዉ ግዴታ በተጨማሪ ተጨማሪ ሰዓት (over time) ለሚሰሩ ሰራተኞች ከደመወዛቸዉ ተጨማሪ ክፍያ ያገኛሉ።
- በሱረቱል አል ሙዘሚል ቁጥር 20 ‹‹**ለአላህም መልካም ብድርን አበድሩ። ከመልካም *ሥራም* ለነፍሶቻችሁም የምታስቀድሙትን ሁሉ እርሱ የተሻለና በምንዳም *ታላቅ* ኾኖ አላህ ዘንድ *ታገኙታላችሁ*።**›

## <u>የምታመልኩትን ዛሬውኑ ይምረጡ</u>።!!!

ውድ አንባቢያን የመጨረሻ ውሳኔአችሁ የምታመልኩትን መምረጥና ማምለክ ነው። አምላክ ፍጥረታትን በሙሉ የፈጠረው እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩት ብቻ ነው። ይህ ደግሞ በሁሉም የሰው ልጆች ላይ የተጣለ ኃላፊትና ነው። በመጽሐፈ ኢዮብ 34፡4 ‹‹***<u>የሚበጀንን እንምረጥ፤ መልካሙንም አብረን እንወቅ</u>***›› እላለሁ። በመጨረሻም በመጽሐፈ ኢያሱ 24፡15 ‹‹***<u>የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ</u>፤***›› መልካም ምርጫ ተመኝቻለሁ።

# ዋቢ መጽሐፍት


- የ1816 የአራቱ ወንጌሎች ዕትም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረር
- የ1879 ዕትም የመጀመሪያው የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- የ1927 ዕትም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- የ1938 ዕትም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር
- የ1947 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ
- የ1954 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡
- የ1962 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር መጀመሪያ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡
- የ1980 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ መኅበር፡፡
- የ1980 ዕትም መዝሙረ ዳዊትና አዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡
- የ1993 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡
- የ1997 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡
- የ2007 ዕትም የብሉይ ኪዳንና የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ቅዱስ አሳታሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፡፡
- ከአረበኛ አል ኪታቡ ሙቀደስ አሳታሚ ግብጽ ካይሮ፡፡
- King James verision holy bible Thomas nelson since 1798 www. Thomas nelson.com

- New king James verision seattel USA 2000
- New American standard bible Updated editition Seattle. USA 2000
- American Standard Verision Seattel USA 2000
- Revised Stanedard Seattel 2000


## ተጨማሪ መጻሐፍት


- ኢየሱስ ማን ነው 303 ወሳኝ ጥያቄዎች አዘጋጅ አህመዲን ጀበል፡፡
- ኢየሱስ እውን ፈጣሪ ነውን አዘጋጅ አህመድ ዲዳት፡፡
- ክርስቲያን-ሙስሊም ውይይት አዘጋጅ ሐሰን ኤም ባዐጊል፡፡
- ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የታለቆች ታላቅ አዘጋጅ አህመድ ዲዳት፡፡
- ክርስቶስ በኢስላም አዘጋጅ አህመድ ዲዳት፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙሐመድ የተናገረው ቃል አዘጋጅ አህመድ ዲዳት፡፡
- የመጽሐፍ ቅዱስ ሚስጢር በሙስሊም መነጽር አዘጋጅ ቀመር ሁሴን፡፡
- መነጽር አዘጋጅ ዑመር አሩሲ፡፡
- የስላሴ አመጣጥና ታሪካዊ እውነት በኤ.ኤ.ሲ.ኬብ ትርጉም፡-አደም ናስር፡፡
- ጠቃሚ ምክር ለአዲሱ ትውልድ ቀጥተኛውን ሃይማኖት ለማወቅ ያለህን ዕድል ላለማወቅ አትጠቀምበት አዘጋጅ ተሸቴ ሮቤ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር አዘጋጅ አቡ ሰመያ፡፡
- የሐመር ተዋህዶን ቅጥፈት በእስልምና እውነት አዘጋጅ ሐሰን ታጁ፡፡
- ክርስቲያን እና ሙስሊም ውይይት አዘጋጅ፡፡
- ሊቀጳጳሱ እና እስልምና፡- አቡቦክር አለሙ፡፡
- የሴቶች ደረጃ በኢስልምና በክርስትና አዘጋጅ አህመዲን ጀበል፡፡
- ስህተትን መመለስ ኦሪት ወንጌልና ቁርአንን በመጥቀስ አዘጋጅ ቀመር ሁሴን፡፡
- ላለማደናገር ማመሳከር ሷዲቅ ሙሐመድ (አቡ ሃይደር)፡፡
- ነብዩ ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ አዘጋጅ፡፡

- አንድ መልክት አዘጋጅ ናጂ አር ፈረጅ፡፡
- እውነትን እንፈልግ ቀጥተኛውን መንገድ እንያዝ ቁጥር 1 አዘጋጅ ነጃት ግርማ፡፡
- እውነትን እንፈልግ ቀጥተኛውን መንገድ እንያዝ ቁጥር 2 አዘጋጅ ነጃት ግርማ፡፡
- True message of jesus Christ d.r a.b.philip